ባለፉት 40 አመታት የፖለቲካ ስነፅሁፍ ተቀብሮ ከነበረበት፣ ተስፋዬ ገብረአብ ራሱም ባንድ ወቅት ተዘፍቆበት ከነበረው፣ እንጨት እንጨት ከሚል የካድሬ ፖለቲካ መሳሪያነት አውጥቶ አድማሳዊ የሆኑ ሰብአዊ እሴቶችን መፈተሻ በማድረግ ነፍስ ሊዘራበት የጀመረው ሙከራ እየተሳካ ለመሆኑ "የደራሲው ማስታወሻ" በቂ ምስክር ነው።

...ፖለቲካው ሃገርና ህዝብን እያመሰ፣ የነፃነት፣ የሰላምና የብልፅግና ተስፋችንን እየቀበረ፣ የአንድነታችንና የአብሮነታችንን ስር እየቦረቦረ፣ ኢትዮጵያችንን እንደ ገደል ላይ ቀጤማ ከግራ ቀኝ እያላተመ፣ የመኖርና ያለመኖር እጣዋን ጥያቄ ውስጥ ባስገባበት ወቅት፣ ተስፋዬ ገብረአብ የተባ ብእሩን ከፖለቲካው ማራቅ ወንጀል መስሎ የታየው የስነ ፅሁፍ ሰው ነው። ይህንን እምነቱን በቀዳሚውም ሆነ በዚህኛው ማስታወሻዎቹ በግልፅ ያሳየናል።

...በእውነተኛ የህይወት ገጠመኞቹም የሚገናኛቸውን ግለሰቦች እንደበቱ በማድረግ ለእኛ ተራ የሚመስሉ አባባሎቻቸውንና ድርጊቶቻቸውን በመጠቀም ብዙዎቻችን ደፍረን ማየት ከማንፈልገው የሃገራችንና የራሳችን ገበና ጋር ፊት ለፊት እንድንጋፈጥ ያደርገናል - በውብ ብእሩ እያዋዛ።

...የተስፋዬ ገብረአብ ብእር ራሱንም አይምርም። ራሱን ተርቦ በራሱ ላይ ስቆና ቀልዶ እኛንም ፈገግ እንድንል ያደርጋል። የታመቀ ብሶቱንና ሃፍረቱን ገላልጦ በማቅረብ እኛም እንደሱ የህሊና ፅዳት አካሂደን ከጭንቀታችን መገላገል ባንችልም፣ ትንሽ እፎይታ ማግኘት እንደምንችል ይጠቁመናል።

...በጨረፍታ ለሚያያቸው የደራሲው ትረካዎች ተራ ወጎች ይመስላሉ። አስተውሎ ለሚመረምራቸው ግን አእምሮን ሰርስረው የሚገቡ የጠለቀ የፍልስፍና ውይይት የሚካሄድባቸው ናቸው። እያዋዛ ያቀርባቸው እንጂ የዋዛ ጉዳዮች አይደሉም።

..የደራሲው "ማስታወሻዎች" ልብ ወለድ አይደሉም። እውነተኛ ታሪኮች ናቸው። አብዛኞቹ ገፀባህርያት በህይወት ያሉ ናቸው። መፅሃፉን ማንበብ ስንጀምር ግን እንደማንኛውም ቀልብ የሚሰርቅ የልቦለድ ድርሰት ትረካው ይሆን ይነጉዳል። ከመፅሃፉ አንድ ምእራፍ የጀመረ ሰው ሳይጨርሰው ለማስቀመጥ በጣም ይቸገራል። ጠዋት ሥራ መግባት ያለበት ሰው ማታ መፅሃፉን እንዲጀምረው አልመክረውም።

ብርሃኑ ነጋ (ዶክተር)

ISBN 978-1-4507-0943-9
90000>
9 781450 709439

netsanet
Publishing & Distribution Agency
www.npabooks.com

ተስፋዬ ገብረአብ

# የደራሲው ማስታወሻ
## ተስፋዬ ገብረአብ

ነፃነት አሳታሚ
ዋሽንግተን ዲሲ - 2002

Published by Netsanet Publishing Agency.
Email: admin@npabooks.com
http://www.NPAbooks.com

©Tesfaye Gebreab - 2010
®ተስፋዬ ገብረአብ - 2002

የደራሲው መብት በህግ የተጠበቀ ነው።
All rights reserved.

No part of this book may be reproduced in any manner whatsoever without written permission except in the case of brief quotations embodied in critical articles and reviews. For information, address, ttgebreab@gmail.com

ዋሽንግተን ዲሲ፣ አሜሪካ ታተመ።
Printed in Washington DC, USA.

Cover Design: Netsanet publisher.

ምስጋና

"የጋዜጠኛው ማስታወሻ" በሚል ርእስ ቀደም ሲል ለህትመት ያበቃሁትን መፅሃፍ አስመልክታችሁ፣ በኢሜይል የሞራል ድጋፍ ለሰጣችሁኝ ሁሉ የከበረ ምስጋና አቀርባለሁ። በጊዜ ማነስ ምላሽ ላልሰጠሁዋችሁ፣ እንብቤያቸዋለሁና አመሰግናለሁ። ይህን መፅሃፍ ጠንክሬ እሰራ ዘንድ ሃይል ሰጥታችሁኛል። በቀጣይም አስተያየታችሁን በናፍቆት እጠብቃለሁ።



## - ማውጫ -

- መቅድም (ዶክተር ብርሃኑ ነጋ)............5
- እንደ መግቢያ (ደራሲው) ...............12

1. የልጅነት ተራሮች.....................17
2. የቀዌሳ አመፅ.......................... 48
3. ሁለቱ ዝሆኖች....................... 57
4. አብዮታዊ ኦርቶዶክስ............. 76
5. ወርቃማ አመታት......................95
6. ጥቁር አማሮች........................ 123
7. የጀግና ሃገር ድምቢጥ............ 139
8. ጆቤ ልክ ነበር.................... 149
9. የወያኔ ምስጢሮች.................. 164
10. የቁልቢ ሌሊት ውስጥ............. 178
11. እግአዚና ምርጫ 97............. 190
12. ስብሃት ነጋ በጨረፍታ............. 210
13. ተስፋ ሲሞት........................ 227
14. ፃድቃንና ያረና........................ 248
15. ያልተፃፈ መፅሃፍ.................... 256
16. የተቀበረ ህዝብ...................... 279
17. ወንዞች እና ጎርፎች............... 290

18. የከሸፉ ኩዴታዎች.................. 295
19. ከበረሃ ወደ በረሃ.................... 306
20. ዘርና ዘርማንዘር..................... 316
21. ደስተኛው ጄኔራል.................. 325
22. ሮሮ እና ይቅርታ................... 336
23. ቦረና! የስልጣኔ ዋሻ............... 350
24. ደጋግ ሰዎች.......................... 365
25. ሰቆቃወ መህቡባ..................... 396



## መቅድም

ተስፋዬ ገብረአብ የበርካታ መፅሃፍት ደራሲ ነው። ሆኖም ግን ከብዙሃኑ የአማርኛ አንባቢ ጋር በስፋት ያስተዋወቀው "የጋዜጠኛው ማስታወሻ" የተሰኘው የቅርብ ጊዜ ትረካው ነው። በአጭር ጊዜ ውስጥም በአገራችን አሉ ከሚባሉት ዝነኛ ደራስያን ተርታ ተሰልፎአል።

ደራሲው በቀዳሚውም ሆነ በዚህ "የደራሲው ማስታወሻ" በተሰኘው አዲስ መፅሃፉ በአማርኛ የስነፅሁፍ ታሪክ የተለየና የራሱ የሆነ የአፃፃፍ ስልት አስተዋውቆአል። በርካታ የተበታተኑ ፅሁፎችና መረጃዎችን አንድ ወጥ በሆነ የጋራ ጉዳይ ዙሪያ ማስተሳሰር የቻለ ሲሆን፣ ይህም የተስፋዬ ገብረአብ የደራሲነት መለያ ለመሆን በቅቶአል።

ይህ መፅሃፍ ያቀፈው ጉዳይ ፖለቲካ ነው።

የደራሲው ክህሎት ግን በፖለቲካው ጉዳይ ብቻ የተገደበ አይደለም። ስነፅሁፍ ኪነታዊ ውበቱን ሳይለቅ የፖለቲካ ጉዳዮችን የድርሰቱ አካል አድርጎ እንዴት መተረክ እንደሚቻል አሳይቶናል። የፖለቲካ ጉዳይ በአሰልቺ የፕሮፖጋንዳ ወይም ደረቅና ዝርዝር በሆነ ትንተና መልኩ ብቻ መቅረብ እንደሌለበት በጋዜጠኛው ማስታወሻ ተስፋዬ እንዳሳየን ሁሉ፣ በደራሲው ማስታወሻውም ይህንን የአፃፃፍ ስልት በተመሳሳይ ደረጃ ይደግመዋል።

ባለፉት 40 አመታት የፖለቲካ ስነፅሁፍ ተቀብሮ ከነበረበት፣ የዚህ መፅሃፍ ደራሲ ራሱም ባንድ ወቅት ተዘፍቆበት ከነበረው፣ እንጨት እንጨት ከሚል የካድሬ ፖለቲካ መሳሪያነት አውጥቶ አድማሳዊ የሆኑ ሰብአዊ እሴቶችን መፈተሻ በማድረግ ነፍስ ሊዘራበት ተስፋዬ ገብረአብ የጀመረው ሙከራ እየተሳካ ለመሆኑ የደራሲው ማስታወሻ በቂ ምስክር ነው።

"በፖለቲካ ጉዳይ የፖለቲካ ተንታኞች እንጂ

ገጣሚዎች፣ ቅኔ ቋጣሪዎች፣ የልብ ወለድ ደራስያን ምን አገባቸው?" በሚለው የነፃነት ፍራቻ ባመጣው የዘመናችን በሽታ ተስፋዬ አልተለከፈም።

ፖለቲካው ሃገርና ህዝብን እያመሰ፤ የነፃነት፣ የሰላምና የብልፅግና ተስፋችንን እየቀበረ፣ የአንድነታችንና የአብሮነታችንን ስር እየቦረቦረ፣ ኢትዮጵያችንን እንደ ገደል ቀጤማ ከግራ ቀኝ እያላተመ፣ የመኖርና ያለመኖር እጣዋን ጥያቄ ውስጥ ባስገባበት ወቅት ተስፋዬ ገብረአብ የተባ ብእሩን ከፖለቲካው ማራቅ ወንጀል መስሎ የታየው የስነ ፅሁፍ ሰው ነው። ይህንን እምነቱን በቀዳሚውም ሆነ በዚህኛው ማስታወሻዎቹ በግልፅ ያሳየናል።

"የደራሲው ማስታወሻ" ውስጥ ደራሲው ዱባይ ላይ በግርድና ስም የባርነት ህይወት ከምትገፋ መህቢባ ከተባለች አንዲት ሴት ጋር በአጋጣሚ ይገናኝና፣

"ፖለቲካ ምን ያደርግልሃል? ለምን አትተወውም? እንደ 'ሰመመን' እና 'ሳቤላ' ያሉ መፅሃፍትን ብትፅፍ አይሻልም?" ስትል አጥብቃ ትመክረዋለች።

የመህቡባ ምክር በዚህ አያበቃም።

"ስለ ፍቅር መፃፍ አትችልም እንዴ?" በማለት ትፈታተናዋለች። "እኔ ፖለቲካ አልወድም" ብላው ስታበቃም በራሷና በቤተሰቧ ላይ ለደረሰው ግፍና መከራ፤ ለተጣመመ ህይወቷ፤ የሃገሯ የተጣመመ ፖለቲካና ፖለቲከኞች መሆናቸውን አበጥራ ትናገራለች።

ደራሲውም፣ "በሃገራችን ፍቅርን እያነቀዘና እንደ ብል እየበላ ያለው ትል ከበሰበሰው የፖለቲካ ስርአት የሚፈላ ጉድ አይደለም እንዴ? ይህን የጠነባ ዘረኛ ፖለቲካ መታገል ለፍቅር ጥብቅና መቆም አይደለም እንዴ? በተለይ ባሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ስለ ፍቅር ምን ይፃፋል?" የሚል መልሱን በዝምታ እየሰጠ የሚያዳምጣት ይመስላል።

እንዲያ ለማሰቡና የሚለው እውነት ለመሆኑ የመህቡባን ታሪክ አንብበን ስንጨርስ ግልፅ ይሆንልናል። እንደ መህቡባ ዱባይ ውስጥ የመከራና የውርደት ህይወት ከሚገፉት እህቶቻችን ጋር ፍቅር እንዲይዘን ባደረገ ብእሩ ተስፋዬ ገብረአብ ይህን ሃቅ አረጋግጦታል። ይህ ፍቅር ግን የአካል ውበት፣ የስጋና የወሲብ ጥማት የሚዘውረው ፍቅር አይደለም። ሰብአዊና ኢትዮጵያዊ





ፍቅር እንጂ።

የዚህ መፅሃፍ ደራሲ ከማንኛውም ምሁራዊ ትንተና ባልተናነሰ በአገራችን ውስጥ ያለውን የፖለቲካ ሂደትና ይህን ሂደት የሚያሽከረክሩትን ግለሰቦችና የሚመሩበትን ሸውራራ ራእዮቻቸውን በፍፁም ከአእምሮ ሊፋቅ በማይችል መልክ በትናንሽ ታሪኮች ከቦ እያዋዛ በታትኖ ያስቀምጣቸዋል። በእውነተኛ የህይወት ገጠመኞቹም የሚገናኛቸውን ግለሰቦች አንደበቱ በማድረግ ለእኛ ተራ የሚመስሉ አባባሎቻቸውንና ድርጊቶቻቸውን በመጠቀም ብዙዎቻችን ደፍረን ማየት ከማንፈልገው የሃገራችንና የራሳችን ገበና ጋር ፊት ለፊት እንድንጋፈጥ ያደርገናል - በውብ ብእሩ እያዋዛ።

የተስፋዬ ገብረአብ ብእር በሃገራችን ፖለቲከኞችና ተስፋዬ የድርሰቱ አካል ሊያደርጋቸው በመረጣቸው ዜጎች ላይ ብቻ ያነጣጠረ አይደለም። ራሱንም አይምርም። ራሱን ተርቦ በራሱ ላይ ስቆና ቀልዶ እኛንም ፈገግ እንድንል ያደርጋል። የታመቀ ብሶቱንና ሃፍረቱን ገላልጦ በማቅረብ እኛም እንደሱ የህሊና ፅዳት አካሂደን ከጭንቀታችን መገላገል ባንችልም፣ ትንሽ እፎይታ ማግኘት እንደምንችል ይጠቁመናል።

ዘመናት ያለፋቸውን፣ ምላሽ ሳያገኙ ተዳፍነው የቀሩ የፍቅር ስሜቶቹን፣ ረመጣቸው አንባቢን እንዲሞቀው አድርጎ ያቀርባቸዋል። ውዳቂነት እንዲሰማው ስላደረገው ሰነፍ ተማሪነቱና ወዶገብ ባሪያ ሆኖ የወያኔ አገልጋይ ስለነበረበት ዘመን በሚገርም ግልፅነትና ብትህውትነት ይተርክልናል። እንደ ፀሃፊ ትልቁ ጥንካሬውም እዚያ ላይ ነው።

በጨረፍታ ለሚያያቸው የደራሲው ትረካዎች ተራ ወጎች ይመስላሉ። አስተውሎ ለሚመረምራቸው ግን አእምሮን ሰርስረው የሚገቡ የጠለቀ የፍልስፍና ውይይት የሚካሄድባቸው ናቸው። እያዋዛ ያቅርባቸው እንጂ የዋዛ ጉዳዮች አይደሉም። ዘረኛነትና ብሄረተኛነት፣ ጭቆናና ፍትህ፣ በደልና ቂጣ፣ ባርነትና ነፃነት፣ አድልዎና እኩልነት፣ አተላና ውበት፣ ቅጥፈትና እውነት፣ ክህደትና ታማኝነት፣ እሮሮና እምቢተኛነት፣ ውርደትና ክብር፣ ድንቁርናና እውቀት፣ ጥላቻና ፍቅር፣ ሞትና ተስፋ... ወዘተ የፀሃፊውን ትኩረት የሳቡ የትረካዎቹ ድርና ማግ ናቸው። ይህ አፃፃፍ ይመስለኛል የዘመናችን የሃገራችን አስከፊ ፖለቲካ ከምድራችን ከተጠረገ

በኋላም መጪው ትውልድ የተስፋዬ ገብረአብን መፅሃፍ እያነሳ ያነበዋል የሚል እምነት የጫረብኝ።

ደራሲው በሰው ልጅ የረጅም ዘመን ኑባሬና በሁሉም ህብረተሰብ ውስጥ በቋሚነት የዘለቁ ሰብአዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን በዋነኛነት የፖለቲካ ገፅታ ባለው ድርሳኑ ሲያቀርባቸው ጎልቶ የሚታየን የፖለቲካ መልእክታቸው ሳይሆን የስነፅሁፍ ሃያልነትና ውበት ነው። "በደራሲው ማስታወሻ" እነዚህ ከሰው ልጅ ህይወት ጋር የተቆላለፉ ውስብስብ ጉዳዮች በመኝታ ሰአት ለህፃን ልጅ እንደሚነበብ የተረት መፅሃፍ በጣም በሚጥምና በሚማርክ አፃፃፍ ለአንባቢው ይቀርቡለታል።

የደራሲው "ማስታወሻዎች" ልብ ወለድ አይደሉም። እውነተኛ ታሪኮች ናቸው። አብዛኞቹ ገፀባህርያት በህይወት ያሉ ናቸው። መፅሃፉን ማንበብ ስንጀምር ግን እንደማንኛውም ቀልብ የሚሰርቅ የልቦለድ ድርሰት ትረካው ይዞን ይነጉዳል። ከመፅሃፉ አንድ ምእራፍ የጀመረ ሰው ሳይጨርሰው ለማስቀመጥ በጣም ይቸገራል። ጠዋት ስራ መግባት ያለበት ሰው ማታ መፅሃፉን እንዲጀምረው አልመክረውም።

የ"ጋዜጠኛው ማስታወሻ" ላይ የተፈራ ዋልዋና የበረከት ስምኦን አስተሳሰብና ልቦና ቀርቦልን ነበር። "የደራሲው" ላይ ደግሞ "ሌኒን" በሚል ቅፅል ስም ስለሚጠራ አንድ ኢትዮጵያዊ ታሪክ እናነባለን። ሌኒን ዛሬ በህይወት የለም። ከኤርትራ ጋር በተደረገው ጦርነት ለሃገሩ ሲል ህይወቱን ከፍሎአል። ከሞተ በሁዋላ ግን ሳሞራ የኑስ ሞት ፈርዶበታል። እነ በረከት በዚህ ትረካ "ጥቁር ወይም ፎርጅድ አማራ" ሆነው ብቅ ይላሉ።

የነፃነትን ፍላጎትና ባርነትን ያለመቀበል እምቢተኛነትን በቁንድዶ ፈረሶች በኩል በጋዜጠኛው ማስታወሻ ላይ እንዳየናቸው ሁሉ፤ በደራሲው ማስታወሻ ደግሞ ልብ በሚማርከውና በሚሰብረው የቀዌሳና የበርሄ - ጎማ እግሩ ውብ ትረካዎች በድጋሚ እናነባቸዋለን። በርሄ ለነፃነት የታገለ ጤነኛና የዋህ ሰው ነበር። የዘመናችን ገዢዎች በበርሄ ደምና ትግል ላይ ተረማምደው ስልጣን ላይ ከወጡ በሁዋላ አምባገነን ሆነው የበርሄን እምነት ሲያራክሱ እናገኛቸዋለን። በርሄ የአለቆቹን ስህተትና ድክመት መታዘብና መቃወም የቻለ ጀግና ነው። አለቆቹ ማህበረሰቡን ሲበድሉ አይቶ የቅስም መሰበር አደጋ ሲደርስበት፣ አንባቢውም አብሮ ከበርሄ ጋር እያዘነ አብሮት





ይሰቃያል። የአምባገነኖች መሳሪያ ለመሆን የሚሽቀዳደሙ ግብዝ ካድሬዎችንም ከበርሄ ባሻገር እናጤናቸዋለን። በርሄን "ፖለቲካ የማይገባው የዋህ" እያሉ ሊያስተምሩት ሲጋበዙ እናያለን። በግልባጩም ተራው ሰው ብቻ ሳይሆን ተራው ታጋይም እነዚህን ካድሬዎች፣ "ማታ እነመለስ እንደ ባትሪ የሞሉዋቸውን ይኸው አሁን ይተፉታል" እያለ እንዴት እንደሚሳለቅባቸው በበርሄ አንደበት ያሰማናል።

ተስፋዬ ገብረአብ የተዋጣለት የስነፅሁፍ ሰው ነው። የፖለቲካን ጉዳይ ለስነፅሁፍ ውበት እንዲገዛ ማድረግ የቻለ አርቲስትም ነው። ፖለቲካንና ስነፅሁፍን በማይቆጠቁጥ መልኩ ያዋሃደ ይመስላል። በአገራችን ይህንን ለማድረግ የቻሉ በጣም ጥቂት የታደሉ ፀሃፍት ብቻ ናቸው። እነዚህንም ፀሃፍት ተስፋዬ ጠንቅቆ የሚውቃቸው ይመስላል። የበአሉ ግርማ አሰቃቂ ፍፃሜ ከሆዱ አልወጣ ያለው ተስፋዬ፣

"በአሉ ግርማ እንደ ሙሴ መቃብሩ እንደማይታወቅ አስቀድሞ ነግሮን ነበር። ቃሉ ተፈፀመ። ነብይነቱ ቀርቶብን እንደ ደራሲ ቢኖርልን በተሻለን" በማለት ያለቅስለታል። የሃዘኑን ሃቀኛነት አምጦ እየወለዳቸው ባሉት የስነፅሁፍ ውጤቶቹ እያረጋገጠልን ነው።

ከተስፋዬ ገብረአብ የስነፅሁፍ አቅጣጫ ብቻ ሳይሆን፣ በደራሲው ማስታወሻ ውስጥ ከሚያንፀባረቀው የፖለቲካ አመለካከት ጋርም ምንም ፀብ የለኝም። እንዲያውም ብዙውን የምጋራው ነው። በፖለቲካ አመለካከቱ ተስማማንም አልተስማማንም ግን የተስፋዬን የስነ ፅሁፍ ችሎታ ከማድነቅ ልንታቀብ አይቻለንም።

"የደራሲው ማስታወሻ"ን ሳነብ የታወሰኝ በአሁኑ ጊዜ ታሪኩ በብሮድዌይ በቴአትር መልክ የሚታየውን የናይጄሪያዊውን እውቅ የአፍሮ ቢት አቀንቃኝ ፌላ ኩቲን ነው።

ፌላ ድንቅ የሙዚቃ እውቀቱን በመጠቀም በአገሩ በናይጄሪያ የሚያያቸውን አዋራጅ ወታደራዊ የአምባገነን ስርአቶችንና የሚያካሂዱትን አሳፋሪ ሙስና ሳይታክት ሲታገል ያለፈ እውቅ አፍሪካዊ ነው። ለዚህም በህይወቱ ብዙ ከፍሎበታል። እናቱን ገድለውበታል። ሞተ ብለው እስኪተዉት ቀጥቅጠውታል። ለነፃነት ያለው ጥማትና በደልን ለመቀበል የማይችለው ትከሻው ግን ዝም ብሎ ኑሮን እንዲኖር

አላስቻለውም። የሚወደውን ሙዚቃውን ያለነፃነት ሊያየው አልቻለም። ስለዚህም የሙዚቃ ክህሎቱን ከነፃነት ትግሉ ጋር አዳብሎ ተጠቀመበት። በዚህም የአገሩን ልጆች ብቻ ሳይሆን የአለምን የነፃነት ታጋዮችና ሙዚቃ አፍቃሪዎች ድጋፍና አክብሮት አገኘበት። በህይወቱ ብቻ ሳይሆን በሞቱም የሚከበር እውቅ አፍሪካዊ ሆነ።

ቀደም ብዬ የጠቀስኳት ሙህቡባ የተባለችው "የደራሲው ማስታወሻ" ህያው ገፀባህርይ ደራሲውን እንደመከረችው ብዙ ገንዘብ ሊያስገኝለት የሚችል ፍቅርና ወሲብን፣ ማጣትንና ማግኘትን፣ የመሳሰሉ ጉዳዮችን በቅመማ መልኩ ያደራጀ ልብ አንጠልጣይ ልቦለድ የመፃፍ ችሎታ ያለው ደራሲ ነው።

ምርጫውን ግን ይህን አላደረገም።

"የፖለቲካ ጉዳይ ውስጥ እኔ ምናገባኝ? ያፖለቲካ ጉዳይ ለፖለቲከኞች" በማለት የፀሃፊነት እትብቱና ስሩ ከተተከሉበት ምድር ነቅለው ሊያጠወልጉትና ምስጥ እንደ በላው እንጨት ሊያደርቁት የተነሱትን እብሪተኛ ፖለቲከኞች በቸልታ አልተመለከታቸውም። ስነፅሁፍ የፈጠራ ስራ መሆኑን፣ ይህ የፈጠራ ስራ ደግሞ ከምንም ነገር በፊት የደራሲውን ነፃ መሆንና በህብረተሰብ ውስጥ በሚገባ መተከልን የሚጠይቅ ስራ መሆኑን የተረዳ ይመስላል።

ተስፋዬ ገብረአብ "ደራሲ ለራሱ አይፅፍም" የሚል እምነት ተሸክሞ የሚባትል ብእረኛ ለመሆኑ ለአንባቢዎቹ ደህንነት፣ ሰላምና ነፃነት በሚያሳየው ጭንቀት ይገልፀዋል።

"እኔ ያለ አንባቢዬ ትርጉም የሌለኝ የቃላት ጋጋታ ባዶ ጩኸት ነኝ" በሚል መንፈስ የሚፅፍ ለመሆኑ፣ የአንባቢዎቹ፣ የሃገሩ ልጆች ነፃነት ማጣት፣ ውርደት፣ ረሃብና ስደት የሚያንገበግበው መሆኑን ሃሞቱን በምሬት ሞልቶ ከፃፋቸው ታሪኮች መረዳት ይቻላል።

ይህ ጭንቀት እንደ ደራሲ ህይወት ለሰጠው ማህበረሰብ ብቻ አይደለም። እንደ ደራሲም ሊገድሉትና ለስደት ለዳረጉት እብሪተኛ ፖለቲከኞችና አጨብጫቢዎቻቸውም የሚተርፍ ነው።

"በጋዜጠኛው ማስተወሻ" የዘመናችን የክብር አልባነት ሃውልት ሆኖ እንዲቀር በደራሲው የተገተረውን ባጫ ደበሌ "በደራሲው ማስታወሻ" ሌላ ገፅታውን እንድናይ ተደርገናል።

ተስፋዬ ገብረአብ በዚህ ድርጊቱ ለባጫ ደበሌ ያለን





ንቀት እዲደበዝዝ ያደርጋል። ባጫ ዳንስ መውደዱንና ለዳንስ ያለውን ስሜትና ችሎታ ደራሲው ሲተርክልን እኛም አንድ ቀን ይህ ጄኔራል ከነሙሉ ማእረጉና ትጥቁ ሲደንስ ለማየት እንድንጓጓ የሚያደርግ ስሜት ከውስጣችን ሲፈለቅ ይሰማናል። ይህ ማለት ግን የተስፋዬ ገብረአብ ብእር ገራገር ነው ማለት አይደለም። መርዝ ሊረጭባቸው በሚገቡ የነፃነትና የፍቅር ቀበኞች ላይ መርዛማ ቃላቶቹን ለማዝነብ የማያመነታ ብእረኛ ነው።

"የማስታወሻዎቹ" ደራሲ በአገራችን የተንሰራፋው የዘረኛነት በደል ገፈት ቀማሽ ነው። በዚህም ተሰዶአል። በስደትም የስነ ፅሁፍ ችሎታውን በግልፅ ለፀረ-ዘረኛነት ትግል እየተጠቀመበት ነው። በአገራችን ያለውን አዋራጅ ስርአት ለመቀየርና አገራችንን እውነተኛ የነፃነት አገር ለማድረግ በሚደረገው ትግል የአገራችን አርቲስቶችም እንደዚሁ የራሳቸውን አስተዋፅኦ ለማድረግ እንደሚተጉ ተስፋ አደርጋለሁ።

አርቲስቶች በፈጠራ ስራቸው በየትኛውም ህብረተሰብ የለውጥ ፋና ወጊዎች ናቸው። በተለይ የአንድ ማህበረሰብ ግንባር ቀደም የነፃነት ፋና ወጊዎች የስነፅሁፍ ሰዎች፣ ዘፋኞች፣ ሰአሊዎችና የሙዚቃ ደራስያን ናቸው። የኪነት ሰዎች ከማንም ፈጥነው ከማንም ልቀው ለነፃነት ጥብቅና የሚቆሙት ወደው አይደለም። የፈጠራ ሙያቸው የጣለባቸው እርግማን "ያለ ነፃነት ትርጉም አልባ ናችሁ" እያለ እንቅልፍ ስለሚነሳቸው ነው።

ይህ መሰረታዊ እምነት ግን በሃገራችን በተስፋፋው ፍፁም አፋኝ የሆነ የባርነትና የቅጥረኛነት ስርአትና እርሱን ተከትሎ በነገሰው ሃገራዊ የፍርሃት ድባብ የተነሳ ከአብዛኛዎቹ የኪነት ሰዎቻችን ልብ እየተፋቀ ይመስላል።

እነዚህ "ማስታወሻዎች" ይህንን አደገኛ ሂደት ለማስቆም መልካም ጅማሬ እንደሚሆኑና የዚህ አይነቱን መነቃቃት በስነጥበብ ሰዎቻችን መሃል ለመፍጠርም ያግዛሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

ብርሃኑ ነጋ (ዶክተር)

# የደራሲው ማስታወሻ
## (እንደ መግቢያ)

አሳዳጄን አመለጥኳት፣
አመለጠችኝ ያሳደድኳት፣
ኗሪ ሆንኩኝ እንደ ፍየል፣
በነብርና በቅጠል መሃል፣

(ግጥም - ደበበ ሰይፉ)

* * *

የአንድ እናት ልጆች፣
በአስተሳሰብ ተጣልተው፣
በአመለካከት ተለያይተው፣
የሚያስታርቅ ጠፍቶ፣
የእብድ ገላጋይ በዝቶ፣

(ግጥም - በአሉ ግርማ)

ባለፍሁበሻ ዘመን አቆጣጠር 2001 ላይ፣ "የጋዜጠኛው ማስታወሻ" በሚል ርእስ አንድ መፅሃፍ አሳትሜ ነበር።

ይህ ጥራዝ የዚያ ተከታይ ነው።

በርግጥ በተለምዶው አሰራር ይህን መፅሃፍ፣ "የጋዜጠኛው ማስታወሻ - 2ኛ መፅሃፍ" ማለት ይጠበቅብኝ ነበር። ያን ያላደረግሁት አንባብያን ቅፆቹን በቀላሉ መለያየት ይቻላቸው ዘንድ ብቻ ነው። ሌላ ምክንያት የለኝም። በተቀረ ደራሲውና ጋዜጠኛው አንድ ናቸው። እዚህም ቅፅ ላይ ደራሲው





እንደ ጋዜጠኛው ብጭቅጫቂ ወረቀቶቹን ገጣጥሞ ያወጋችሁዋል።

"ወያኔ" ከተባለው የፖለቲካ ድርጅት ጋር በአባልነት የቆየሁባቸውን የባርነት ዘመናት በእነዚህ ሁለት ጥራዞች ተርኬ አገባድጄያለሁ። የኔ ገጠመኞች ቢገባደዱም ከሌሎች የማገኘውን መረጃዎች እያሰባሰብኩ መጠረዜ አይቀርም ይሆናል። እርግጠኛ ባልሆንም በቀጣይ የምፅፈው መፅሃፍ፣ *"የስደተኛው ማስታወሻ"* የተባለ ሊሆን ይችላል። በስደት ያሉ የሃገሬን ልጆች የህይወትና የፖለቲካ ገጠመኞች እየሰበሰብኩ መጠረዙ ሙያዊ ግዴታዬ ይመስለኛል።

እኛ የዚህ ዘመን ሃበሾች እንዴት እየኖርን፣ እንዴት እናስብ እንደነበር ለመጪው ትውልድ ልናቆይለት ይገባል። ይህችን ጣጣዋ ያላለቀ ሃገር የሚረከባት አዲሱ ትውልድ፣ ከኛ የፖለቲካ ድንቁርና ተምሮ የተሻለ ስርአትና ዘመን ይቀይስ ይሆናል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። በመሆኑም የኛ ዘመን ፖለቲከኞች የሚፈፅሙትን በጎም ሆነ ክፉ ተግባራት በተለያዩ መንገዶች መተረኩ እለታዊ ተግባሬ ሆኖ ይቀጥላል።

"የጋዜጠኛው ማስታወሻ" ላይ በጠቀስኳቸው ታሪኮች አከራካሪ ጉዳዮች ብዙም አልተነሱም። ባለስልጣናቱም ስሜታዊ ሆነው "ከደኸናል! አታመልጠንም!" ከማለት አልፈው ጭብጦችን በጭብጥ ለማስተባበል አልቻሉም። በተለይ የደራራ ከፌኔ አሟሟት ሊያስተባብሉት የማይችሉት አይነት ስለሆነባቸው በፀጥታ ማለፉን መርጠዋል። ከተሰነዘሩት አስተያየትና ማስተባበያዎች መካከል በመጠኑ ትኩረት ስቦ የነበረው የሙሴ (መሃሪ ተክሌ) አሟሟት ላይ የቀረበው ትችት ነበር። ግደይ ዘርአፅዮንና አረጋዊ በርሄ VOA ላይ ቀርበው የሙሴን አሟሟት ጉዳይ ሊያስተባብሉ ሞክረዋል። በወቅቱ የVOA ጋዜጠኛ አዲሱ አበበ ወደ ፕሪቶሪያ ስልክ ደውሎልኝ ምላሽ እንድሰጥ ጠይቆኝ እድሉን ሳልጠቀምበት ቀርቻለሁ። በመሰረቱ በሙሴ ገዳይነት ስሙ የተጠቀሰው በርሄ ሃጐስ "ገዳይ ነኝ!" ብሎ የተፃፈውን ያፀድቀዋል ተብሎ አይጠበቅም። እኔም ግራና ቀኝ ያሉ አሳቦችን ነው ያቀረብኩት። ግደይና አረጋዊ የተናገሩትን የህወሃት የፖሊት ቢሮ አባልና የፕሮፓጋንዳ ክፍሉ ሃላፊ የነበረው አለምሰገድ ገብረአምላክ በተመሳሳይ "የሙሴ አሟሟት አከራካሪ ነው" ስለማለቱ ገፅ 38 ላይ አስፍሬያለሁ። ግደይና

አረጋዊ የአለምሰገድን አባባል ነው የደገሙት። ማስተባበል አልቻሉም። "አይመስለኝም" የመሳሰሉ ደካማ ቃላትን በመጠቀም ርግጠኛ ያልሆነ መረጃ የሰጡ በመሆኑ፣ በርሄ ሃጐስ የግድያው ፈፃሚ አለመሆኑን ሊያሳምኑ አልቻሉም። እኔው በመፅሃፌ እንደጠቀስኩትም ይህን መሰል በጨረፍታ የተነካኩ ታሪኮችን ወደፊት ታሪክ ፀሃፊዎች የበለጠ እንደሚቆፍሩት ተስፋ አደርጋለሁ። የሙሴ አሟሟት ብቻ ሳይሆን የዶክተር አታክልቲ (ራስ ወርቅ ቀፀላ) አሟሟትም በተመሳሳይ በህወሃት አመራር ትእዛዝ ስለመፈፀሙ ወሬዎች አሉ። እነዚያ ወሬዎች ተራ አሉባልታዎች አይደሉም። መነሻ አላቸው።

በተቀረ በኔ በኩል የጋዜጠኛነት ግዴታዬን እየተወጣሁ ነው። የአይን ምስክሮች የገለፁልኝን ለመጪው ትውልድ የማስረከብ ሃላፊነት አለብኝ ብዬ አምናለሁ። ወደፊትም የሙያው ስነምግባር በሚፈቅድልኝ ደረጃ እገፋበታለሁ።

ጓደኞቼ ሆይ! ገና ብዙ እፅፋለሁ!!

"ምናገባኝ" ወይም "ጎመን በጤና" ብዬ የምተወው ጉዳይ የለም። የሃገሬ ጉዳይ ይመለከተኛል። 'ጎመን በጤና' የሚለው ዘፈንም የማደንዘዣ መርፌ ነው። እኛ ከክብርና ከኩራታችን ጋር የተፈጠርን ሙሉ ሰዎች ነን። በመሆኑም እንደ ሃበሻ ውሻ ሳይሆን እንደ ሃበሻ ሰው ለመኖርና ለመሞት እንመጥናለን። ስለዚህ 'ጎመን በጤና' የሚለውን ባለ ጎመኖቹ ቀቅለው ይብሉት። እኛ ከዚያ በላይ ላለው አንደኛ ደረጃ ህይወት እንመጥናለን። የምንመኘውን ያን ህይወትም ልንኖረው እንችላለን። ስለዚህ ለመብታችን እንታገላለን።

በኔ በኩል እስትንፋሴ እስካለች ድረስ የማምንበትን በነፃነት ከመግለፅ የሚያቆመኝ ምንም ምድራዊ ሃይል አይኖርም። በቀሪው የህይወት ዘመኔ ጣፋጩንም ሆነ መራራዋን እውነት ለመዘመር ግንባር መስመሩ ላይ አለሁ። እኛ የአፍሪቃ ቀንድ ዜጎች የምንመኘው ዘመን ባለቤት እንሆን ዘንድ መስራቴ ይቀጥላል። ምክንያቱም አንድ ግለሰብ አንድ ነገር ከማድረግ ባሻገር ለውጥ ሊያመጣ እንደሚችል አምናለሁ። እንደ ስነፅሁፍ ሰው ደግሞ ፋና ወጊ የመሆን ግዴታ አለብኝ።

በመጪው ዘመን ወጣቱ ኢትዮጵያዊ ትውልድ ይበልጥ በከረረና በተዋበ ብእር እውነትን ሲዘምራት ይታየኛል። ከዚያም አልፎ ያ ዜማ ከወዲሁ ይሰማኝ ጀምሮአል። በርግጥም አፍሪቃ





ቀንድ ከጦርነት፣ ከሞትና ከስደት አውድማነት የምትላቀቅበት ዘመን ይመጣ ዘንድ እያንዳንዳችን "ከምኞት ባሻገር" አንድ ነገር ማድረግ መቻል አለብን። ይቻለናልም!!

ኢትዮጵያ ትልቅ ሃገር ናት።

በህዝብ ብዛቷም ግዙፍ እንደመሆኗ፤ እኛ ዜጎች በአካባቢው ፖለቲካ ላይ ልናበረክት የምንችለውን አስተዋፅኦ መጠንና ልኩን አውቀን በዚያ ደረጃ ሆነን መገኘት ይጠበቅብናል። በአካባቢያችን ላይ አወንታዊ ተፅእኖ ማሳደር እንችላለን። አቅሙም ብቃቱም አለን። ለተሻለ ህይወት እንመጥናለን።

በጎ ህልሞች ማለም ብቻውን ግን በቂ አይደለም።

እነዚያ በጎ ህልሞች መቼ፣ እንዴትና በማን እንደሚፈፀሙ ካላወቅን ህልም ብቻ ከመሆን ሊያልፉ አይቻላቸውም። ስለዚህ በህልም አለም ያለን ካለን፣ ከቀን ህልም ነቅተን፣ አይንና ህሊናችንን ከፍተን ወደ ተጨባጭ ተግባር እንገባ ዘንድ ይጠበቅብናል...

አንድ የማልረሳው የአረቦች አባባል አለ፣

"አላህን እመን! ግመልህን ማሰር ግን አትርሳ!"

በተቀረ ለቀዳሚው መፅሃፌ ሚዛናዊ የዘገባ ሽፋን ለሰጣችሁ ሚዲያዎች ሁሉ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ። ከአንባቢዎቼም በሺህዎች ሞራል የሚያንፁ የኢሜይል መልእክቶችን ተቀብያለሁ። መገመት ከሚቻል በላይ የብርታት ፀጋ አጎናፅፈውኛል። ለሁሉም በክብር አመሰግናለሁ። እንደ ቀዳሚው መፅሃፍ በዚህ ጥራዝም የኢትዮጵያን የቀን አቆጣጠር የተጠቀምኩ ሲሆን፣ በተለያዩ ምክንያቶች ደግሞ የአንዳንድ ባለታሪኮችን እውነተኛ ስምና ቦታዎችን ለመለወጥ ተገድጃለሁ።

በመጨረሻ...

በቀጣይም በወዳጅነት ያልተገዛ ልባዊ አስተያየታችሁን እንደምጠብቅ እየገለፅኩ፣ መልካም ንባብ!

ተ.ገ.

# - 1 -

# የልጅነት ተራሮች

የልጅነት ዘመን - ጨዋታዎች ሁሉ፣
የሉም ህልም ሆነዋል፣
እንደ ማለዳ ጉም፣
"ብን!" ብለው ጠፍተዋል፣
ሆኖም ምኞት አለ - የሚቃጠል ገና፣
በከባድ ስልጣን ስር - ሳለን በጭቆና፣

(ግጥም - አሌክሳንድር ፑሽኪን)
- አያልነህ ሙላቱ እንደተረጎመው -

በክረምቱ ወራት፣ ቢሾፍቱ ሃይቅ ዳርቻ ወደምትገኝ መንደራችን በድንገት አንዲት ልጅ ብቅ አለች። ትምህርት ቤት በመዘጋቱ ክረምቱን አጎቷ ዘንድ ለማሳለፍ ከአዲሳባ መምጣቷ ነበር።

ጊዜውን በፍፁም ልረሳው አልችልም።

ሃምሌ፣ 1974።

ወደ ስምንተኛ ክፍል ያለፍኩበት ዘመን ነበር። የልጅቱ አጎት ማስተር ገለታ ጅሬኛ ይባላሉ። የኢትዮጵያ አየር ሃይል የጦር ጄቶች ቴክኒሺያን ነበሩ። እንግዳይቱ ልጅ እንደ

ሽንኩርት ድቡልቡል አፍንጫና ወፈር ያሉ ከናፍርት ነበሯት። ቆዳዋ ጠቆር ይላል። በተቃራኒው ጥርሶቿ የሳሙና አረፋ ይመስላሉ። ፈገግታዋን ብልጭ ስታደርገው ገፅታዋ እንደ ጨረቃ ያበራል። ቀጠን ያለች ብትሆንም፣ የስፖርተኛ ሰውነት ነበራት። እንደ ቆዳዋ ጠቆር ያለ ጠጉሯን ወደሁዋላ ለቃው፣ በአረንጓዴ ጨርቅ ቢጤ ሸብ አድርጋ ታስረዋለች።

ከዚህች ልጅ ጋር መተያየትና ማውራት በጣም አስደስቶኝ እንደነበር ትዝ ይለኛል። ወግ የጀመርነው ግን በአጥሩ ላይ በማሻገር ነበር። ልጅቱ በእድሜ እኩያዬ ትሆናለች። በቁመትም አንበላለጥም። በመጣች በሶስተኛው ቀን ነው መሰለኝ አጐቷ ማስተር ገለታ ስራ ከሄዱ በሁዋላ በአጥሩ በኩል ማውራት ጀመርን፣

"ማነው ስምሽ?"

"ሌንሳ አባሜጫ"

እኔም ስሜን ከነአባቴ ነገርኳት። ፈጥነን ተግባባን። ከኔ ይልቅ ነቃ ያለች ነበረች። እንዲህ ስትል ጠየቀችኝ፣

"ቢሾፍቱ የሚባለው ወንዝ ከዚህ እሩቅ ነው?"

"ወንዝ አይደለም ሃይቅ ነው"

"ወንዝ መስሎኝ ነበር። እሩቅ ነው ከዚህ?"

"በጣም ቅርብ ነው"

"ምን ያህል ይሆናል?"

"ሁለት ኳስ ሜዳ"

"ታሳየኛለህ?"

ላደርገው የማልችለውን ጥያቄ ጠየቀችኝ።

በፍፁም የማይሞከር ነበር።

ከሴት ጋር ጎን ለጎን ልራመድ? ጤነኛ ሰው ይህን ሊያደርግ አይችልም። ብቻዬን ከሴት ጋር ወደ ቢሾፍቱ ገደል ብወርድ ሰው ምን ይላል? ወዲያው ነው በሰፈራችን የሚወራው። "ዱርዬው!" ብባልስ? ባልሰራሁት ስራ ብታማስ? "አልዋልኩበትም" ብል ማን ያምናል? ስለዚህ ይህን ብቻዬን ላደርገው የምችለው አልነበረምና ፈጥኜ ዘዴ በማመንጨት እንዲህ አልኳት፣

"በሲሊፐር ገደሉን ልትወርጂ አትችይምና ጫማሽን ለውጪ። እኔ ደግሞ ነብዩ አበበ የሚባል ጓደኛ አለኝ። እሱን ጠርቼው አሁኑኑ እመለሳለሁ። አብረን እናሳይሻለን..."





እንደ አየር ሃይል ጄቶች እየተወነጨፍኩ እነ ነብዩ ቤት ደጃፍ ላይ ተገኘሁ። እኔ ስደርስ ነብዩ የበቆሎ ማሳ እያረመና እየኰተኰተ ነበር። ያጋጠመኝን ከባድ ችግር ባጭሩ አስረዳሁት። ነብዩ ምንም አላመነታም። ዛባውን ወዲያ አሽቀንጥሮ ሊተባበረኝ ዝግጁ ሆነ። ተያይዘን በሶምሶማ ሩጫ የመልስ ጉዞ ጀመርን።

ጥበቡ ሃይሉና ምኒልክ ደሳለኝ መንገድ ላይ አስቆሙን፣

"ምንሆናችሁ ነው?"

"ተልከን ነው"

"ምን ያስሮጣችሁዋል ታዲያ?"

"ቸኩለናል"

ሶምሶማው ቀጠለ።

እኔም ለነብዩ ሁሉን በዝርዝር አጫወትኩት፣

"ልጅቱ ሌንሳ ትባላለች። 'ቢሾፍቱን አሳየኝ' ብላ ራሷ ጠየቀችኝ። የሚገርመውን ልንገርህ? ቢሾፍቱ ወንዝ መስሎአት ነበር። 'ወንዝ አይደለም፣ ሃይቅ ነው' ብዬ ነገርኳት። የሃብታም ልጅ ሳትሆን አትቀርም። ጂንስ ሱሪ አላት። ሲያምርባት ብታይ! ጫማና ሹራቧን ተወው!..."

በነዚያ የልጅነት ጊዜያት በድፍን ሰፈራችን ጂንስ ሱሪ የለበሰ ብቸኛ ልጅ ምኒልክ ደሳለኝ ብቻ ነበር። እናቱ ነጋዴ ናቸዋ! በዚያ ላይ ቤተሰባቸው ብዙ ልጅ የለውም። እህቱና እሱ ብቻ። የሌሎቻችን መቁጠር እንኳ ያስቸግራል። የነነብዩማ አይወራም። መንታ ጭምር፣ ሁለት ጊዜ። የኛስ ቢሆን? ስድስት ደርሰናል። የልጅ ልጆች ሶስት ደርሰው፣ ገና ከፍ ሳንል አጎት ሆነናል። እናቴ በ35 አመት እድሜዋ አያት ሆናለች። ማቆሚያ ያለውም አይመስል። "አምላክ የከፈተውን ጉሮሮ ሳይዘጋው አያድርም" እያሉ መውለድ ነው...

ሶምሶማው ቀጠለ።

ነብዩ ባዶ እግሩን ነበር። እግሩ ጭቃ በጭቃ ሆኖ ጣቶቹ አይታዩም። በማርጀቱ የተወቀጠ ቋንጣ የመሰለ ቡኒ የካኪ ቁምጣ ለብሶአል። በቀበቶ ምትክ በሲባጎ ሸብ አድርጎአታል። የኔም አለባበስ ከነብዩ ጋር ተመሳሳይ ነበር። የአብዛኞቻችን የመንደሩ ልጆች አለባበስ እንዲያ ነበር።

ነብዩ ባዶ እግሩን መሆኑ ግን ደስ አላለኝም፣

"እግርህን ታጥበህ ለምን በረባሶ አታደርግም?" አልኩ።

"ይሁን ያው ነው"

ከማስተር ገለታ ግቢ ደጃፍ ላይ ስንገኝ፣ ሌንሳ ጫማዋን ተጫምታ፣ በረንዳው ላይ ተቀምጣ እየጠበቀችን ነበር።

ከነብዩ ጋር አስተዋወቅሁዋት።

ፈገግ ብላ በአክብሮት ጨበጠችው፣

ከዚያም እሷን መሃል አድርገን ወደ ቢሾፍቱ ሃይቅ አግጣጫ አቀናን።

ሌንሳ በጣም ደስ እንዳላት ታስታውቅ ነበር። እኔ ግራ ተጋብቼያለሁ። እጄን የት እንደማስቀምጠው ቸግሮኛል። መራመዱንም አልቻልኩበትም። ነብዩ እንደኔ ባይሆንም እሱም የጋለ ስሜት ላይ ነበር። የማንለያይ ጓደኛሞች እንደመሆናችን ልብ ለልብ እንተዋወቃለን። እንደዚህ ከሴት ጋር ሆነን ግን በፍፁም አናውቅም። በእኛ እድሜ ከሴቶች ጋር መታየትም ቢሆን በመንደራችን የተለመደ አልነበረም። ነውርም ነው። የአባሚጫ ሴት ልጅ ግን ነፃ ነበረች። አንገቷን ወደኔና ወደ ነብዩ እያመላለሰች እንደልቧ ታወራናለች።

"ስንተኛ ክፍል ተማሪ ነሽ?" ሲል ጠየቃት ነብዩ።

"ወደ ስምንተኛ ክፍል አልፌያለሁ። እናንተስ?"

"እኛም ወደ ስምንተኛ አልፈናል"

"ወደ ገደሉ መውረድ አትፈሪም?" ስል ጠየቅሁዋት።

"ብቻዬን እፈራለሁ"

በዚህ ንግግሯ ስሜቴ ተነካ።

ምክንያቱም አነጋገሯን፣ "ከናንተ ጋር ከሆነ አልፈራም" እንደ ማለት ወሰድኩት። 'ይሄ ደግሞ እኛን እንደ ጓደኞቿ እንዳመነችን፣ ምናልባትም እንደ ወደደችን የሚያሳይ ነው' እያልኩ ነበር ለራሴ።

መንገዱን ጨርሰን ከቢሾፍቱ ሃይቅ አፋፍ ላይ ብቅ! አልን። ሌንሳ ከመደነቋ ብዛት ጩኸቷን ለቀቀችው! በሁለት እጇ አፏን ይዛ፣ አይኖቿ እንደ አሳ አይን ፈጠው፣ ሃውልት መስላ ቆማ ቀረች። በወቅቱ ሌንሳ ለምን እንደ ጮኸች አልገባኝም ነበር። እዚያው ሃይቁ አፋፍ ላይ ተወልጄ ስላደግሁ፣ ሃይቁን ድንገት የሚያይ ሰው እንዲህ ባለ ሁኔታ ሊጮህና ሊደነቅ እንደሚችል ግንዛቤውን ያገኘሁት ዘግይቼ ነበር።

ወደ ገደሉ ማሽቆልቆል ጀመርን።

የጋራቦሩ እረኞች ከብቶቻቸውን ውሃ ሊያጠጡ በብዛት





ወደ ሃይቁ እየወረዱ ነበር። "ጋራ" ማለት በኦሮምኛ "ትንሽ ጉብታ" ማለት ሲሆን፣ "ቦሩ" ደግሞ፣ "የፀሃይ መውጫ" ማለት ነበር። ጋራቦሩ የደብረዘይትና የቢሾፍቱ ሃይቅ ራስጌ ሲሆን፣ ወደር የሌለው ውብ ስፍራ ነው። የጋራቦሩ እረኞች ከብቶቻቸውን ውሃ ሊያጠጡ ቁልቁል ሲወርዱ፣ የሚዘፍኗቸውን ዘፈኖች ዛሬም አህዮቻቸው ላይ ተቀምጠው እያዜሟቸው ነበር፣

ገንዘበ ኪያ - ሻማ ቢቴ፣<br>
ነዱንገዱ ጂናን - ጋዳ ሊጤ፣

(በገንዘቤ ሻማ ገዛች፣<br>
ሳሚኝ ብላት ጓዳ ገባች፣)

ሲያንሸራትታት ግራና ቀኝ እየያዝናት ቁልቁል ወረድን። ከብቶች ይወርዳሉ፣ ከብቶች ይወጣሉ። በጎችና አጋሰሶች ከፊት፣ ከብቶች ከመሃል፣ ውሾችና እረኞች ከሁዋላ። የአሰላለፍ ህጉ ይኸው ነው። ተፈጥሮ ራሷ የደለደለችው። አጋሰስ ከሁዋላ፣ ከብቶች ከፊት ሊሆኑ አይችሉም። ለምን ሊሆን እንደማይችል ደግሞ የሚያውቅ የለም። ይህ የተፈጥሮ የግል ምስጥሯ ነው...

ሌንሳ ለአንድ አፍታ ቆም አለች።

እናም ለእረኞቹ ሰላምታ አቀረበች፣

"Akkam bultanii?"

እረኞቹ በመሽቀዳደም ምላሽ ሰጡ፣

"Negaa bultanii? Ati fayya keetii?"

"Galata Waaqayyoo!"

አያይዛም እንዲህ አለች፣

"Maal gochaa jirtaa? Loontikssaa jirtaa?"

በህብረት ምላሽ ሰጡ፣

"Eeyye!!!"

በመደነቅ ነቢዩን አየሁት።

እሱም ሳይገረም አልቀረም። የአዲሳባ ልጅ ሆና ሳለ በኦሮምኛ መናገሯ እኔን በጣም አስደንቆኝ ነበር። ከዚያ ቀደም ኦሮምኛ ሲናገሩ የምንሰማው የጋራቦሩ ገጠሬዎችን ብቻ ነበር።

ነቢዩ እንዲህ ሲል ጠየቃት፣

"ኦሮምኛ የት ለመድሽ?"

"ብዙ ጊዜ ክረምት አያቴ ዘንድ ጌራ እሄዳለሁ። በዚህ

ክረምት ግን ስላልተቻለ እዚህ መጣሁ። ከአያቴ ጋር በኦሮምኛ ነው የምናወራው። ጌራ ላይ አማርኛ የሚችል የለም።"

አያይዛ ጠየቀች፣

"እናንተስ ኦሮምኛ ትችላላችሁ?"

"እኔ በደንብ እችላለሁ" ሲል መለሰ ነቢዩ።

"እኔ ትንሽ ትንሽ እችላለሁ" አልኩ። አያይዤም፣ "ጌራ የት ነው?" ስል ጠየቅሁዋት።

"ከጅማ ብዙ አይርቅም። የጌራ ወረዳ አገሩ በአብዛኛው የዘመዶቼ ነው። ጌራ ላይ ብዙ አጎቶች አሉኝ። ብታዩት መንግስተ ሰማያት ነው..."

*(ጌራ የሚለውን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማሁት በዚያን እለት ከሌንሳ አንደበት ነበር። በመቀጠል ባለቅኔው ፀጋዬ ገብረመድህን 'እሳት ወይ አበባ' በተሰኙ የግጥም መድበላቸው ላይ 'ጌራ' በሚል ርእስ ግጥም ፅፈው አነበብኩ። ፀጋዬ ቅኔ የተቀኙላት 'ጌራ' ይህቺ ሌንሳ የጠቀሰቻት ወረዳ ትሁን፣ አሊያ 'አንዲት ጌራ የምትባል ሴት' ርግጠኛ አይደለሁም። ሆኖም ጥቁር እንጪኒ የተባለችው የባለቅኔው የትውልድ መንደር ከጌራ ብዙም እንደማትርቅ ተረድቼያለሁ። ባለቅኔውም በልጅነታቸው ነጋዴዎችን ተከትለው ጌራ ይሄዱ ነበር...)*

ገደሉ ላይ ደጋግፈን አወረድናት።

ከዚያ ቀላል ነበር።

እየተንደረደርን ውሃው ደጃፍ ላይ ደረስን። ማእበሉ ተነስቶ ነበር። እየተገማሸረ ከዳርቻው አለትና ከዋርካ ዛፎች ይጋጫል። አልፎ አልፎ አሳዎችን አንገዋሎ ሲተፋቸው እረኞቹ እየተሻሙ ይማርኳቸዋል። ሌንሳ ጉንጮቿ ኮረሪማ መስለው በመደነቅ ውሃውን ስታይ ቆየች፣

"እዚህ ሰው ይዋኝበታል?"

"እዚህ ነው የምንዋኘው" ሲል ነብዩ መለሰ።

"እናንተም እዚህ ትዋኛላችሁ?"

"በየቀኑ ነዋ!"

"አትፈሩም?"

"እዚሁ ነው ያደግነው። ምን ያስፈራል?"

"ጥልቀት አለው?" ስትል ጠየቀች።

"ዘጠና ሜትር ነው ይባላል" ስል መለስኩ።





ብዙም ሳንቆይ የመልስ ጉዞ ጀመርን። እንደ አመጣጣችን ተጠነቀቅንላት። ጭቃ እንዳይነካት ጥረት አደረግን። ገደሉ ላይ ነብዩ ከላይ ሆኖ እጇን ይዞ ሲስባት፣ እኔ ከታች ሆኜ በእጇ ትከሻዬን ተደገፈችው። እሷን ለመርዳት ባደረግነው ጥረት ለስላሳ እጆቿ ሲደገፉኝ ከፍተኛ ደስታ ይሰማኝ እንደነበር አልረሳውም። የነብዩን በርግጥ አላውቅም። ሆኖም እሱም በጣም ይጠነቀቅላት ስለነበር እንደ እኔው መደሰቱን መገመት ችያለሁ።

ቤቷ አድርሰናት ስንሰናበታት ፈቃዱ ከሆነ በነጋታው የመንደራችን ራስጌ ወደ ሆነው ጋራቦሩ ወስደን፣ የረር ተራራን በሩቁ ልናሳያት ቃል ገባንላት።

* * *

በዚያን እለት ተስያት በቆሎ የመኮትኮቱንና የማረሙን ስራ ነብዩን አገዝኩት። ወሬያችን ሁሉ ስለ ሌንሳ ብቻ ነበር። የበቆሎ ማሳውን አርመንና ኮትኩተን ስናበቃ፣ የነቢዩ እናት ቂጣና ጠላ ሰጡን።

ደጃፉ ላይ ተቀመጥን።

ከቂጣው አጨድ እያደረግን፣ ከጠላው ተጐነጨንለት። የነቢዩ እናት እልፍ ብለው ገብስ ያበጥራሉ። ዶሮዎች ብጣሪውን ይለቃቅማሉ። የነነብዩ ውሻ ከበቆሎ ማሳው ጥላ ስር ተኝቶአል። ዝንቦች ወረውት ነበር። ጭራው ላይ የከረመ ቁስል ነበረበት። ጅብ ነክሶት ነው። ከአደጋው በፊት እልኸኛ ውሻ ነበር። ጅቦቹ ሳይደርሱበት፣ 'ለምን በበራችን አለፋችሁ' ብሎ ያለአቅሙ ከጅብ ሲታገል ያድር ነበር። ይኸው! ሂሳቡን ሰጡት። ጭራውን ቀይ ልምጭ አስመሰሉለት። ነብዩ ሲነግረኝ፣ ከአደጋው በሁዋላ እንኳን ከግቢ ሊወጣ፣ አበሻ መሆኑን ረስቶ፣ እንደ ፈረንጅ ውሻ ሳሎን ገብቼ ካላደርኩ እያለ ማስቸገር ጀምሮአል። ተፈቅዶለት ግን አያውቅም። በፍልጥ እየተነረተ ወደ ደጅ ይገፈተራል...

እዚያው ቁጭ ብለን ጠላ ስንጐነጭ ጀምበር ጠለቀች። ወደ ቤቴ ለመሄድ ተነሳሁ። አልቻልኩም። ሁለቴ ስራመድ ተንገዳገድኩ። ባልወድቅም ሚዛኔን መጠበቅ አልቻልኩም። በሶስት ጣሳ ጠላ እንዲህ ሆኜ እንኳ አላውቅም ነበር። የሌንሳ ወሬ ተጨምሮበት ሳያስከረኝ አልቀረም።

የነብዩ እናት እየሳቁ፣
"ብዙ ጠጣህ እንዴ?" አሉኝ።
"ኸረ የተለመደውን ነው"

ያን ቀን እስከ እኩለ ሌሊት ግድም ጥሩ ተኝቼ ነበር። ከዚያ በሁዋላ ግን እንቅልፍ እምቢ አለኝ። እስኪነጋጋ ቁልጭ አልኩ። ሊነጋጋ አካባቢ መልሶ ሸለብ አድርጎኝ ነበር። ዶሮዎች መጮህ ሲጀምሩ እንደገና ነቃሁ። ወንድወሰን የሚባል አንድ ክፍት አፍ! የሆነ አውራ ዶሮ አለን። የሰፈሩ ሰው ሁሉ ያውቀዋል። በደሞዝ ተቀጥሮ የሚጮህ ይመስል ገና ሳይነጋ አቦሬውን ይከፍተዋል። እስኪያስለው ድረስ እየጮኸ፣ ከኛ ግቢ አልፎ እስከነ የሸዋሉል ቤት ድረስ ሰፈሩን ይበጠብጠዋል። ይህን አውራዶሮ አባቴ በጣም ይወደው ነበር። "ፀጠዋት ወደ ስራ ለመሄድ ይቀሰቅሰኛል" ይላል። ስንቶቹ ዶሮዎች እየታረዱ ወጥ ሆነው ሲበሉና ሲጋጡ፣ እሱን የሚነካው የለም። ትጉህ አይነት አውራዶሮ ነው። ለዘር የሚሆን እንቁላል የማስፈልፈል ስራውን ጨርሶ አይዘነጋም። በዚህ ላይ፣ "ውሃ አምጡ፣ ምግብ ስጡኝ" ብሎ አያውቅም። እጅህን ስትታጠብ ጠብቆ ይጠጣል። ቀኑን ሙሉ እረፍት የለውም። እየተሯሯጠ ፈላልጎ ሲበላ ይውላል። ደጅ ቆይቼ በተመለስኩ ቁጥር ምን ጊዜም ሲበላ ነው የማገኘው። ለዚህ ዶሮ፣ "ወንድወሰን" የሚል ስም የሰጠው ታናሽ ወንድሜ ነበር። እና ያን ቀንም ወንዴ እንደተለመደው ገና በማለዳው ቀሰቀሰኝ።

ተነስቼ ወደ ደጅ ወጣሁና ደረጃው ላይ ተቀመጥሁ። ከዚህ ሌላ ላደርገው የምችለው አንዳችም ነገር አልነበረም። ስለ ሌንሳ ማሰቡ ነበር የተመቸኝ። የቢሾፍቱ ሃይቅ ገደል ውስጥ ትከሻዬን የተደገፈችኝ ደጋግሞ ታወሰኝ። ሃይቁን ስታይ የጮኸችው ድምፅዋ መልሶ መላልሶ ይሰማኛል። በሁለት እጇ አፏን መያዟ ምስሉ ይታየኛል። ሁሉም በየረድፉ እየመጣ አእምሮዬን እያቋረጠው ያልፋል። የጋራቦሩ እረኞችን ደግሞ በኦሮምኛ አዋራቻቸው። የአዲሳባ ልጅ ሆና ሳለ በኦሮምኛ ተናገረች። ወይ ጉድ! የሚገርም ነው! የመጠሪያ ስሟ ራሱ ሲገርም። 'ሌንሳ' አሏት። በእኛ እድሜ ያሉ ሴቶች መሰረት፣ ፋና፣ ቅድስት፣ መስከረም፣ አበባ፣ ሸርሸር፣ ዮዲት ምናምን ነበር ስማቸው። 'ሄለን' የሚል ስም ያላቸው ብዙ ጊዜ ከአዲሳባ





የሚመጡት ነበሩ። በወቅቱ 'ሄለን' የሚለው ስም ገና ደብረዘይት አልገባም ነበር። ይህች ልጅ ግን ካዲሳባ መጥታ ሳለ ስሟ 'ሌንሳ' ሆነ። እረኞቹን ደግሞ በኦሮምኛ አዋራቻቸው። ከሁለት ወንዶች ጋር ወደ ቢሾፍቱ ገደል መውረድ ሳትፈራ ቀረች። ወይ ጉድ! ሌንሳ አባሜጫ! ይገርማል!...

ነግቶ ነበር።

ነቢዩ የግቢ በራችንን በቀስታ ከፍቶ ሲገባ አየሁትና ከተቀመጥኩበት ተነሳሁ። እሱም እንቅልፍ አጥቶ አድሮ ኖሮአል። ባዶ እግሩን አልነበረም። መስቀለኛ በረባሶውን ተጫምቶ ነበር...

ከነቢዩ ጋር ደረጃው ላይ ቁጭ ብለን እስኪነጋ ጠበቅንና ሻይ አፍልተን ከቂጣ ጋር ቁርስ በላን። ከዚያም የተከበረች እንግዳችንን ወደ ጋራቦሩ ለመውሰድ ዝግጁ ሆንን!

ከረፋፈደ በሁዋላ ነበር ሌንሳ ብቅ ያለችው። በሞቀ ፈገግታ ተውጣ ጨበጠችን። ፈገግታዋ እንደ ንጋት ጎህ ቀደደ። ጨረቃ መሰለች። እኛም እንደርሷው ፈገግ ማለታችን መቸም አልቀረም። የኛ ፈገግታና የሷ ፈገግታ ግን ሊመሳሰል አይችልም። እኛ ፈገግ ስንል የምናለቅስ ሊመስል ይችላል። ሳቅ የሚያምርበት የተመቸው ነው። ያልተመቸው ሰው ከሚስቅ ስቅስቅ ብሎ ቢያለቅስ ይበልጥ ያዋጣዋል። እንደተቦረቦረ መሬት ወደ ውስጥ የገባ ጉንጭ! የከረዩን ጐራዴ መስሎ የተጋደመ መንጋጪላ! እንደዚያ ነበርን። ለምን ይዋሻል?

"ቁርስ በላችሁ?" ስትል ጠየቀችን።
"በልተናል። አንቺስ?"
"እኔም በልቻለሁ"
"እንሂድ ታዲያ?"
"ቆይ ለሰራተኛዋ ነግሬያት ልምጣ?"

ወደ ኮረብቶቹ ወሰድናት።

ጋራው እንደምንጊዜውም በልጃገረዶችና በእረኞች ዜማ ተሞልቶአል። እየተቀባበሉ ያስተጋቡታል፣

ኢዮሂዮ! ኢዮሂዮ! ኢዮሂዮ!
ያደራረከ፣
ጋራቦሩ እንጬና ስላነገና፣
ወልደብና ኢንሴኔ መሌ ሲላመለና፣

* * *

አበባዬ! አበባዬ! አበባዬ!
*ጋራቦሩን አልተሻገርንም እንጂ እንነግድ ነበረ፣*
*እንደምንለያይ አላወቅንም እንጂ መላ ነበረ፣*

ከጀርባችን ጥቁር ተራራ እንደ ግድግዳ ቆሞአል። ከጋራው ዙሪያ መሬቱን የሸፈነው አዝርእት መልካም ይዟል። ነጫጭ በጎች ከማሳው ዳርቻ ጨሌ ይግጣሉ። መልካው ላይ ከብቶች ፈሰዋል። ማር እና ቅቤ በማሰሮ፣ እንቁላል እና አይብ በዘንቢል የያዙ ባልቴቶች መሬት መሬቱን እያዩ ቀጫጭኖቹን መንገዶች ተከትለው ወደ ገበያ ይጓዛሉ። ቆብ የደፉ አንድ ቄስ በከዘራ መሬቱን እየወጉ አለፉ። ቀጨሞ የጨበጡ ሱተናዎች ገርመም አድርገውን መንገዳቸውን ቀጠሉ። የእፅዋቱ መአዛ የአየሩን ጣእም አጣፍጦታል። መኸር አልፎ`መኸር እስኪተካ የአድአ አየር መአዛ እንዲሁ ነው። "ትንሿ ጋራ" ብለን የምንጠራት ኮረብታ በአህያ ጆሮ ተክል አጊጣለች። ለቡሄና ለእንቁጣጣሽ እሱን ቀጥፈን ችቦ እናበጃለን። ጠንበለል የተባለው አነስተኛ ዛፍ አልፎ አልፎ ጋራው ላይ ይታያል። ምን ጠንበለል ብቻ? ቀበሪቾም አብቦአል። ዳማከሴ፣ ጉሎ፣ እምቧይ፣ እምቧጮ፣ ሙጃ፣ ቋቁቻ፣ የተባሉት ልክስክስ እፅዋት ደግሞ የጎርፍ መውረጃው ዙሪያ አብበው ውሃ ይቀላውጣሉ። ከአዝመራው ዳርዳር ፍቅሩጠና የተባለው እሾክ የበቀለ ሲሆን፤ ሰዎች በአጠገቡ ሲያልፍ እየዘለለ ይጣበቃል። ከልጅነታችን ጋር ፅኑ የአይን ፍቅር ቁርኝት ያለው ሰማያዊው የረር ተራራ ጭንቅላቱን ጉሙ ውስጥ ሸሽጎ በርቀት ይታየናል። እናቱ ላይ የሸውሸዌ ጫካ መኖሩን እናውቃለን። ከግርጌው በአይን የቅርብ ርቀት ላይ ጨለቅለቃ የተባለው የክረምት ሃይቅ ስባሪ ሰማይ መስሎ ተዘርግፎአል። ደብረዘይት ቁልጭ ብላ ትታየናለች...

እነሆ! ከእንግዳችን ጋር ኮረብታው ላይ ቁጭ ብለናል።

"ስለ ጌራ ልንገራችሁ?" ስትል ጠየቀች ሌንሳ።

"ንገሪን?"

እንዲህ ስትል አወጋችን...

"ጌራ ላይ ከአጎቴ ልጆች ጋር ፈረስ እንጋልባለን። ሌላ ደግሞ ወደ ወንዝ እንወርዳለን። ሲያስፈራ ወንዙ መቼም። ጆርጌ ጃገማ የምትባል ጓደኛ አለችኝ። ጌራ ስሄድ ከሷ መለየት የለም። በኦሮምኛ ትዘፍንልኛለች። ጆርጌ ፊደል የሚባል አታውቅም።





በጣም እወዳታለሁ። የጌራን  ጫካ ብታዩት ደሞ? መሬት የሚባል አይታይም። በሳርና በዛፍ ተሸፍኖአል። ጌራ ስሄድ የምንበላው ብዙ ጊዜ ጨጨብሳ ነው። ጭኮ ደሞ እንበላለን። በቅቤ የተሰራ የገብስ ቆሎ! በጣም ይጣፍጣል። ሌላ ደሞ አገሩ በሙሉ ድንች በድንች ነው። ስንበላ ነው የምንውል። የድንቹ አይነት ብዛቱ። ኦሮሜ የሚባል ድንች አለ። እንደ ስኳር ይጣፍጣል። አረንጓዴ ድንች አለ። ወሸቤ ድንች ደግሞ ዱባ ይመስላል። ጎደሬ የሚባልም አለ። ተቀቅሎ ሲበላ ቅቤ ነው። እኔ እሱን ነበር የምወደው። ቅጠሉ ሲጣል ዝምብሎ ራሱ ይበቅላል። ኮቴሃሬ የሚባል ድንች አለ። ተጠብሶ ነው የሚበላው። ሸንኮራ አገዳ በየጓሮው በቅሎአል። እኔ ደሞ ብዙ ሸንኮራ በላሁና ምላሴን ቆረጠኝ። ምላሴ ተሰነጠቀና ደማ። ሲደማብኝ ደነገጥኩ። አጎቴ ግን ሳቀ። አምቡሩጢ ደግሞ እንቁላል ትመስላለች። እሷም ድንች ናት። ውስጧ ቀይ ውሃ አላት። ትጥማለች። ዶቅማ በየቦታው ሞልቶአል። በዴሳ ነው የሚሉት። ፍሬው ልክ እንደ ወይን ነው። ይጣፍጣል። በቃ መብላት ነው በቃ። ብታዩት እንዴት ትወዱት ነበር?"

*(በ1990 ኢህአዴግ 3ኛ ጉባኤውን ጅማ ላይ ሲያካሂድ እኔም ተካፋይ ነበርኩ። የጉባኤው ሂደት እንደ ቻይና የካራቴ ፊልም ጎታታ፣ አሰልቺና አጨራረሱ አስቀድሞ የሚታወቅ ሲሆንብኝ፤ ከአንድ የአካባቢው ሰው ጋር ሹልክ ብዬ ወደ ጌራ ሄድኩ። በርግጥም ታዲያ ሌንሳ እንደጠቀሰችው ጌራ የምድር ገነት ሆኖ ነበር ያገኘሁት። አገሩ ወንዝ ብቻ ነው። እንደ ጌራ በልምላሜ ያበደ ምድር ከዚያ ወዲህ ገጥሞኝ አያውቅም። አውቆበቀል ጌሾ እንደ አረም ምድሩን አልብሶታል። ዛፎቹና ሃረጎቹ ተቆላልፈው አረንጓዴ የተፈጥሮ ድንኳን ተክለዋል። ጌራ ላይ ሁሉም ነገር ርካሽ ነው። አንድ ጉረምሳ በእቅፉ ሊይዘው የማይችለው ጫት በስሙኒ ሲሸጥ አየሁ። አንዳንድ የዋህ የገበሬ ሚስቶች ጉመን ሊሸጡ በአህያ ጭነው ወደ ከተማ ይመጡና የሚገዛቸው ሲያጡ፣ ጉመኑን ለአህያው ያበሉታል። በየመንገዱ እንግዶች የሚያርፉበት መስጊድ አለ። እዚያ አረፍ ስትል ቡና በነፃ ትጠጣለህ። ጫካው ቡና ብቻ ነው። አምላክ የተከለው ነው። ተማሪዎች እሱን ሸምጥጠው እየሸጡ ገንዘብ ያገኛሉ። ጌራ ከሰማይ ብቻ ሳይሆን ከመሬቱ ስርም ውሃ ብቻ*

*ነው። የጌራ ገበሬ ሻሜታ ካልሆነ ሌላ አይጠጣም። ከበሶ ነው የሚሰሩት። ጨውና በርበሬ ይጨምሩበታል። መጠጥ ብቻ ሳይሆን ምግብ ጭምር ነው። ጌራ ላይ አንድ ሌሊት አድሬ ወደ አሰልቺው የቻይና ፊልም ቤት ስመለስ ከመንግስተ ሰማያት የተባረርኩ ያህል ነበር የተሰማኝ።)*

እነሆ! ኮረብታው ላይ ቁጭ ብለናል።

ሌንሳ ስለ ጌራ አጫውታን ስታበቃ እኛም በበኩላችን ከልጅነታችን ጀምሮ የምናውቀውን የመንደራችንን ታሪክ እየተቀባበልን አጫወትናት።

ነቢዩ ጀመረ...

እኔ ቀጠልኩ...

እንደ ሁኔታው እየተነጣጠቅን....

"ተመልከች ሌንሳ! የረር ተራራ ማለት ያ ነው! በጐን በኩል ደግሞ ጨፌ ዶንሳ አለልሽ። የፌታውራሪ ዶንሳ ሃገር...

"ይሄ የምትመለከቺው ሃይቅ አይደለም። የክረምት ኩሬ ነው። ሽምብራ ኩሬ ይባል ነበር ድሮ። አሁን ጨለቅለቃ ነው ስሙ። ግራኝ አህመድና አፄ ልብነድንግል የተዋጉት እዚህ ሜዳ ላይ ነው...

"የውልሽ ሌንሳ! ያ ደግሞ ልብነድንግል ጋራ ይባላል። ከስሩ የምታይው አፄ ልብነድንግል ትምህርት ቤት ነው። እኛ እዚያ ነው የምንማረው...

"ሌንሲ ተመልከች! በዚህ በኩል ከሄድሽ ደግሞ ግዙፉ ዝቋላ ተራራ አለልሽ። ቆሪጥ የተባለው ሰይጣን ተራራው ጫፍ ላይ ካለው ሃይቅ ውስጥ ይኖር ነበር። አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ እግሩን ቆርጠው ቢሽፍቱ ሃይቅ ውስጥ ከተቱት...

"ሌንሳ ወዲህ ተመልከች! አሞራ ገደል ማለት ያውልሽ። የነጋባቸውን ጅቦች የምናሳድዳቸው እዚህ ነው...

ሌንሳ! ...

ሌንሲ! ...

ነብዩ ስለግራኝ አህመድና አፄ ልብነድንግል ጦርነት በዝርዝር መናገር ሲጀምር እኔም እንደ ሌንሳ በጉጉት ነበር ያዳመጥኩት። ከዚያ ቀደም ያልሰማሁዋቸውን ታሪኮች ነበር የሚተርከው...





*...የግራኝ አህመድ ሰራዊት፣ የሶማሌዎች፣ የአደሬዎች፣ የኦሮሞዎች፣ የህንዶች፣ የቱርኮችና የአረቦች ቅልቅል ነበረ' ሲል ነገረን። ምን ይህ ብቻ? 'በአፄ ልብነድንግል ወገን በኩል ደግሞ ትግሬዎችና አማሮች ነበሩ። በቁጥር ትግሬና አማሮቹ ይበዙ ነበር። የግራኝ ወታደሮችን ንቀዋቸውም ነበር። አፄ ልብነድንግል፣ 'እንዳያመልጧችሁ ያዟቸው' ብለው አዝዘው ነበር። ሆኖም ከባድ ውጊያ ተደረገና በአስርሺህዎች ከሞቱ በሁዋላ ግራኝ አህመድ አሸነፈ። ግራኝ አህመድ ኡቅባሚካኤል የሚባለውን የትግሬዎቹን መሪ በውጊያው ላይ ገደለው። ደረቱ ላይ በጦር ሲወጋው የጦሩ ጫፍ በጀርባው በኩል ወጣ። ይህም ጦርነት ከተካሄደ 400 አመታት አለፉት። የኛ ትምህርት ቤት አፄ ልብነድንግል የተባለውም በዚህ ጦርነት ምክንያት ነው...*

በዚህ መንገድ ስለጦርነቱ ብዙ አጫወተን። ከነብዩ ጋር አብረን እየዋልን ከዚህ ቀደም ለምን ይህን ታሪክ እንዳልነገረኝ፣ እያሰብኩ በመመሰጥ ነበር ያዳመጥኩት።

ከሰፈራችን ልጆች አንዱ ስለሆነው ስለ አብዱልፈታ በረዳ መነሳቱም አልቀረም። "አዲሎ" ነበር የምንለው ባጭሩ። አዲሎን የማይወደው ማን አለ? ሁልጊዜ ያስቀናል። 3ኛ ክፍል እያለን ሳይሆን አይቀርም፣ "ከሚበሩ እንስሳት ሶስቱን ጥራ?" የሚል ጥያቄ ቀርቦልን፣ አዲሎ ለማሳቅ ብሎ ደብተሩ ላይ የሚከተሉትን ሞላ፣

"ሚግ፣ ሄሊኮፕተር፣ ካምቤራ"

አዲሎ ቀልደኛ መሆኑን መምህሩ አላወቁም፣

"ተነስ" አሉት።

ተነሳና ቆመ፣

"እነዚህ እንስሳት ናቸው?"

"እንስሳት መስለውኝ ነው"

"ውጣና ጆሮህን ያዝ!"

ሌንሳ በጣም ሳቀች።

እኛ በቀልዱ እስኪበቃን ስቀንበታል። ጨዋታው እንዲሞቅ በሚል ግን በድጋሚ አብረናት ሳቅን።

"እህትህ ያደረገችንን ልንገራት?" ሲል አስፈቀደኝ።

"ምኑን?" አልኩ ኮስተር ብዬ።

"የፋንታውን"

"ንገራት" አልኩ እየሳቅሁ።

ነገሩ እንዲህ ነው።

አራተኛ ክፍል ሳለን፣ አንድ ቀን እኛ ቤት ስንጫወት ታላቅ እህቴ እንዲህ አለችን፣

"ግቢውን ካፀዳችሁ ፋንታ ይሰጣችሁዋል"

ፋንታ ባይሰጠንም ከታዘዝን ማንኛውንም ስራ የምንሰራ ጥሩ ልጆች ነበርን። ፋንታ ሲጨመርበት ግን ሞራላችን ጨመረ። ግቢያችን በጣም ሰፊ ነበር። ግማሽ ኳስ ሜዳ ያክላል። የሸውሸዌ ቅርንጫፍ ገንጥለን ስናበቃ፣ ሳሩንም መሬቱንም ሙልጭ አድርገን አፀዳነው። የማገዶ እንጨቶችን አስተካክለን ከመርናቸው። ቅጠሎችን አቃጠልን። የውሻ መሹለኪያ ቀዳዳዎችን ደፈንን። የበሶብላ፣ የኮረሪማ፣ የቅርንፉድ፣ የጤናአዳም፣ የቀይስር፣ የሚጥሚጣ፣ የዱባ-አታክልቶችን ውሃ አጠጣን። ከዚያም ቧንቧው ስር ተደቅነን ከወገባችን በላይ ከታጠብን በሁዋላ ፋንታ ለመጠጣት ዝግጁ ሆንን። በርግጥም እህቴ በሁለት ብርጭቆዎች ፋንታ ቀድታ አቀበለችን። እኔ ወዲያው ነበር የደነገጥኩት። የፋንታ ቀለም ብርቱካንማ መሆኑ ይታወቃል። ይሄ የተሰጠን መጠጥ ግን ድፍርስ ሆኖ ወደ ነጭ የሚያደላ ነበር። ስቀምሰው ውሃ ውሃ ይላል። ወደ ነብዩ ተመለከትኩ። እሱም ቀምሶት ግራ ገብቶታል። ግራ ገብቶት ዝም አላለም። ቀስ ብሎ፣

"እኔ ውሃ አልጠማኝም" አለኝ።

"ዝምብለህ ጠጣ! ካልጠጣህ እኔን ትቆጣኛለች" አልኩ።

ውሃውን ጠጥተን አመስግነናት ወጣን።

ይህንኑ ለሌንሳ አጫወትናት።

በዚህ ግን አልሳቀችም። በእጆችዋ ጉንጯን ተደግፋ በሃዘኔታ ተመለከተችን። ስታዝንልን ስናያት ግን እኛ በግልባጩ እየተያየን መሳቅ ገባን።

ነብዩም እንዲህ አላት፣

"ማዘን አያስፈልግም። ብርቱካን ከፈለግን ሞልቶአል።"

ስለ ፓራሹት ዘላይ አየርወለዶችም አወራናት፣

"አንዱ የኤሌክትሪክ ሽቦ ላይ ተንጠለጠለ። ሌላው ዛፍ ላይ። አንዱ ደግሞ ቢሾፍቱ ሃይቅ ላይ ሊወድቅ ለጥቂት ተረፈ"

ይህ ወግ ሰቀጠጣትና አማተበች። ይህ ግን ለኛ በየአመቱ የምናየው ቀላል ጨዋታ ነበር።





ነፋሱ በጣም ይጥም ነበር።

እረኞች እንደተለመደው በኦሮምኛ እያንጎራጎሩ መልካውን አድምቀውታል። በዝናብ የረጠበው ዋልካ ሽታ ጋራውን አውዶታል። አንዳንዶቹ እረኞች እኛ ወዳለንበት መጥተው ጋሻውን እያስተኙ በሆዳቸው ጋደም አሉ። እኛም እንደዋዛ አክርማውን እየሰነጠቅን ወጋችን ቀጠለ፣

ነቢዩ እንዲህ ሲል ጠየቃት፣

"ቁልቋል በልተሽ ታውቂያለሽ?"

"አላውቅም"

"ነገ እናበላሻለን። በጣም ይጣፍጣል"

"ዘይቱንና ሮማን ጭምር ልናበላሽ እንችላለን" አከልኩ።

"ገዝታችሁ?" ስትል ጠየቀች፣

ነብዩ እየሳቀ እንዲህ አላት፣

"እኛ ገንዘብ የለንም። ፍራፍሬ ገዝተንም አናውቅም"

በነጋታው ሌንሳን የቀጠርናት ከሰአት በሁዋላ ሲሆን፣ በማለዳው ግን ወደ አርመኖቹ ግቢ በሽቦው አጥር ስር ሾልከን በመግባት የቻልነውን ያህል ፍራፍሬ ዘረፍን፣

ምን የቀረ አለ?

ጊሽጣ፣ መንደሪን፣ ሮማን፣ ዘይቱን፣ እንጆሪ፣ ...

እነዚህ ፍራፍሬዎች በውነቱ ለኛ የሚያጓጉ አልነበሩም። ስንወለድ ጀምሮ እንደልባችን እየቀጠፍን ስንበላቸው ኖረናል። አልፎ ተርፎም በብርቱካን ፍሬ እየተወራወርን እንደባደብ ነበር። ወላጆቻችን በአብዛኛው ለአርመናውያን ተቀጥረው የሚሰሩ ስለነበሩ እዚያው የፍራፍሬው ማሳ ዙሪያ ነበር እድገታችን።

*(ይህች ተወልደን ያደግንባት ሰፈር 'አርመን ሰፈር' ትባላለች። ይህን ስያሜ ያገኘችው መንደሪቱ በአምስት አርመናውያን ቱጃሮች ቢሾፍቱ ሃይቅ ራስጌ ላይ በመቆርቆሯ ነበር። አርመናውያኑ ቅዳሜና እሁድ የፈረስ ሽቅድምድም፣ ሃይቁ ላይ ደግሞ በሞተር ጀልባ ውድድር ስለሚያደርጉ መንደራችን የሞቀችና የደመቀች ነበረች። ከደርግ መምጣት በሁዋላ እነዚህ አርመናውያን ይዞታቸውን ሲያጡ፣ በእግራቸው ራሻውያን ተተኩ። እነዚህ ራሻውያን በብዛት የሁለተኛ ደረጃ ምምህራኖቻችን ነበሩ። አርመናውያን የእርሻ ስራ የሚወዱ፣*

*አካባቢውን የሚንከባከቡ፣ አማርኛ ለምደው ከወላጆቻችን ጋር ጥርት ባለ አማርኛ የሚነጋገሩ ነበሩ። ሩስያውያኑ ትምህርት የሚያስተምሩን በተሰባበረ እንግሊዝኛ ሲሆን፣ በትርፍ ጊዜ ደግሞ የመስኮብኛን ቋንቋ ያስጠኑናል። የልማት ዝንባሌ አልነበራቸውም። አማርኛ ለመልመድም አልሞከሩም። የግቢያቸውን አትክልት እንኳ አይጠብቁትም። ጉሊት ወርደው ድንችና ቲማቲም እየተከራከሩ ሲገዙ በጣም ይገርመን ነበር። ከአርመናውያኑ ልምድ ነጮች ሁሉ ሃብታሞችና ገንዘብ የሚበትኑ ይመስለኝ ነበር። የፈረንጅ ድሃ መኖሩን ያወቅሁት ከእነዚሁ ሩስያውያን መምህራኖቻችን ሲሆን፣ ካስተማሩን የሩስያ ቃላት አሁን አእምሮዬ ውስጥ የቀሩት ሁለት ቃላት ብቻ ናቸው። እነሱም፣ "ስፓሲቫ" እና "ካርቱሽካ" ናቸው። ቀጥታ ሲተረጎሙ፣ "ጤናይስጥልኝ ድንች" ማለቱ ይሆናል። በርግጥ ርእዮተአለማቸውን ይዘው ለመጡት ሩስያውያን ጥሩ ትዝታ ባይኖረኝም፣ ስነፅሁፋቸው ግን ጥሩ አድርጎ ቀርፆኛል። ራሺያ ሲባልም አራት አመታት የቀለዱብን እነዚያ ጣረሞት የመሰሉ መምህራን ሳይሆኑ፣ እነ ዶስተየቭስኪና ሾሎክሆቭን ነው የማስታውሰ...*

*...ዛሬ አርመን ሰፈር ወደተባለችው ወደዚህች ቀበሌ ብትሄዱ ግን አርመናውያኑ የገነቡትን የፍራፍሬ እርሻና ልምላሜ አታገኙትም። ከዘመን ደርግ አንስቶ የፍራፍሬው ማሳ መውደም ጀምሮ፣ አሁን ለይቶለት ምልክቱ እንኳ የለም። ውሃ መሳቢያ ሞተሮቹ ከነቧንቧዎቹ ተሰርቀው ጠፍተዋል። 'ከነገ አቦካዶ - የዛሬ ማገዶ' የሚል አባባል ተፈልስፎ፣ በአባባሉ መሰረት የፍራፍሬ ዛፎች በመጥረቢያ እየታጨዱ ለማገዶነት ውለዋል። "ውሻ! ምናገባት በእርሻ!" የተባለው ምርጥ አባባል የተፈለሰፈውም ደብረዘይት ላይ ነው። አባባሉ ለምን እንደተፈጠረ የሚያውቅ ግን የለም። ግጥሙ እንዲገጥም ተብሎ ሳይሆን አይቀርም። አርመን ሰፈር ከምድረገነት ወደ ምድረአረምነት የተለወጠችበትን አሳዛኝ ውድቀት፣ 'የቢሾፍቱ ቆሪጦች' በተባለው መፅሃፌ ላይ በሰፊው ገልጬዋለሁ። ቆሪጥ እና ቆሪጦች ስል የሰየምኳቸው ለገዛ ምድራቸው፣ ለተፈጥሮ ሃብታቸው፣ ለውሃቸው ደንታ የሌላቸውን የአካባቢያችን ሹማምንት ነበር። አካባቢያችን አፈሩ እየተበላ፣ ውሃው እየተመረዘ፣ ደኖች እየተመነጠሩ፣ መንደራችን እየከሳና እየጠወለገ ሲሄድ፣ ሹማምንቱ በግልባጩ ሲወፍሩና ሲደልቡ ለማየትና ለመታዘብ በቅተናል...)*





ሌንሳን ለመጋበዝ የቻልነውን ያህል ፍራፍሬ ዘረፍን...

ምናልባት ብትደሰት በሚል፣ ከየአይነቱ መራረጥንላት። ወደ ቢሾፍቱ ሃይቅ ወረድ በማለትም በመቃ መንጠቆ አስር ያህል የበሰሉ ቁልቋሎችን ገነጠልንና ሁሉንም አጣጥበን በፕላስቲክ ከረጢት ከተናቸው ስናበቃ ወደኛ ቤት ገባን። ግቢያችን በራፉ ላይ ለሱቅ ተብላ ተሰርታ፣ በእንጥልጥል የቀረች አንዲት ክፍል ቤት ነበረች። እዚያች ክፍል ውስጥ ቁጭ ብለን ሌንሳን እንጠብቃት ጀመር።

ሰማዩ ጠቋቁሮ ነበር።

እንዲህ ሰማዩ ሲጠቋቁርና ሊዘንብ ሲከባብድ ኦሮሞች "ሲሜሶ" ይሉታል። 'ሲሜሶ' ማለት 'ሊዘንብ ምንም አልቀረው' ማለት ነው። "ሲሜሶ!" ከተባለ ወሬ የለም። ሩጫ ብቻ ነው። የተሰጣ ልብስ ወደቤት! ከብቶች ወደ በረት! እህል ወደ ጎተራ! ግርግሩ ተአምር የወረደ ይመስላል። ሩጫ ነው። ህፃናትም 'ሲሜሶ! ሲሜሶ!' እያሉ ከሚወርደው ዶፍ ለማምለጥ ወደየጎጆአቸው ይበራሉ። ክረምት ላይ የአድአ ሰማይ ድፍን ጥቁር ይሆናል። ክረምቱን ሙሉ ከመጥቆሩና ከመክበዱ ባሻገር ሰማዩ በእጅ የሚነካ ያህል እንደ ጃንጥላ ቅርብ ይሆናል። አድአ ላይ የዝናብ አዋጅ ሲታወጅ ጥቁሩ ሰማይ፣ ዝናብ ሳይሆን ተቆራርሶ ሊደረመስ የተዘጋጀ የሰማይ ቁጣ ነበር የሚመስል።

ከምሳ በሁዋላ ሌንሳ ወደኛ ግቢ ስትመጣ ጥቁሩ ሰማይ መደርመስ ጀምሮ ነበር። ከአስር ሰከንድ ላልበለጠ ጊዜ ዝናብ ውስጥ ስለቆየች ጎርፍ የተፋት አይጥ መሰለች። 'ዝናቡ ዘነበ' ከማለት 'ዝናቡ ተደባደበ' ቢባል ይቀላል። እንደ ኮረት የሚፈናከት ዝናብ ይረግጠው ገብቶአል። ይህን መሰል ዝናብ ሲወርድ ጎርፉ አያሌ ጎጆዎችን ከስር እየነቀለ፣ አዝሎአቸው ወደ ቢሾፍቱ ገደል ይወረውራል።

ፍራፍሬዎቹን ሳህን ላይ ዘረገፍንላት። የእነዚያ ትኩስ ፍራፍሬዎች ሽታ ባንድአፍታ ክፍሉን ሞላው። ሌንሳ እንደገና በአድናቆት ጮኸች። እሷን ማስደነቅ መቻላችን ደግሞ እኛን በደስታ አሰከረን። ሌንሳ ተደሰተች። በጣም ተደሰተች።

በህይወቷ ሙሉ እንደዚህ አይነት ልዩ ልዩ ፍራፍሬዎች

በአንድ ሳህን ላይ ቀርበው አይታ እንደማታውቅ ነገረችን። እናም እነዚያን ፍራፍሬዎች ለሶስት ቅርጥፍጥፍ አድርገን በላናቸው። አብዛኛውን የጨረገደችው ግን ሌንሳ ነበረች። በልታ ስታበቃ ታዲያ በጣም እየሳቀች፣

"ሆዴን አመመኝ" አለች።

ዝናቡ እስኪያበራም እዚያው ስናወጋ አመሸን።

* * *

ፍራፍሬ የመዝረፉን ጀብዱ በድጋሚ እንፈፅም ዘንድ ሌንሳ አጥብቃ ጠየቀችን። ፍራፍሬ የመስረቁን ድርጊት ከኛ ጋር አብራ ለመፈፀምም ፈለገች። ይህንን ግን ነብዩ አጥብቆ ተቃወመ። የተቃወመበትን ምክንያትም ያብራራ ያዘ፣

- ድንገት ዘበኛው ቢመጡብንስ?
- ከኛ እኩል መሮጥ ስለማትችይ ብትያዢስ?
- የሽቦው አጥር ጉንጭሽን ቢቧጭረውስ?
- ደም በደም ብትሆኚስ?
- አባትሽና አጎትሽ ለወላጆቻችን ቢነግሩብንስ?

ነብዩ እንዲህ እያለ ሊያስፈራራት ቢሞክርም፣ ሌንሳ "ወይ ፍንክች! እኔ የጌራ ድንች" አለች። በርግጥ "እኔ የጌራ ድንች!" አላለችም። አባባሉ እንዲገጥምልኝ ብዬ የጨመርኩት ነው። ሌንሳ 'ወይ ፍንክች' ስትል ግን ጥበቃው ላላ ወደሚልበት የፍራፍሬ እርሻ ሄደን እንድንዘርፍ አስታራቂ አሳብ አቀረብኩ። ነብዩም፣ የአርመናውያኑን ትተን የኢጣሊያውያን ንብረት ወደነበረው ወደ "ቼቾ ግቢ" እርሻ ሄደን በመዝረፉ ላይ ተስማማ። ሌንሳ በደስታ ሳቅ በሳቅ ሆነች። እንዲያውም እየዘለለች በየተራ አቀፈችን። በርግጥ "አቀፈችን" ማለቴ ጨዋታ ለሟሟቅ ነው እንጂ እውነት እንነጋገር ከተባለ አላቀፈችንም። አዬ ማቀፍ! አዬ መተቃቀፍ! ማቀፍ የት ተገኝቶ? ማንስ አስቦት? እንኳን ማቀፍ በስህተት ስንነካካ እንኳ ከሳቴ ብርሃን እንዳጨሰ ሰው ያለንበት ነው የሚጠፋን። የነብዩን በግምት ነው ልናገር የምችለው። እኔ ግን ሌንሳ ተሳስታ እንኳ እጄን ነካ ስታደርገኝ ፀሃይዋ ጭልም! ትልብኝ ነበር።

የሆነው ሆኖ በነጋታው ተስያት ጨለቅላቃ ከተባለው





የከረምት ሃይቅ ዳርቻ ከሚገኘው የፍራፍሬ እርሻ ዝርፊያ ለመፈፀም ሄድን። እዚያ ስንደርስ የገጠመን ሁኔታ ግን ሌላ ነበር። የሄድንበትን ትተን ያልሄድንበትን ጉዳይ ፈፅመን ተመለስን።

እንዲህ ነበር የገጠመንና የሆነው...

ፀሃይ እልም ብላ ጠፋችና ደመና ሆነ። በግምት ከመቶ ሺህ በላይ "የማታ ተማሪዎች" ብለን የምንጠራቸው ነጫጭ የባህር እርግቦች ሃይቁ ላይ ተነጥፈው ውሃውን ሸፍነውታል። ነጩ ደመና ከሰማይ ተገንጥሎ እንደ ግዙፍ አንሶላ ባህሩን የሸፈነው እንጂ ወፎች አይመስሉም።

በርከት ያሉ የትምህርት ቤት ጓደኞቻችንን እዚያው አገኘናቸው። ዳንኤል ፀጋ አንዱ ነበር። ሃይሌ ይገዙ፣ ሚካኤል ታምሩ፣ እስክንድር ሃይሉና ሳሙኤል ተሾመ እዚያው ነበሩ። አብይ! የአባቱ ስም ማን ነበር? አፌ ላይ አለ። ያኛው ጓደኛችን ደሞ ማን ነበር እውነተኛ ስሙ? እንጃ!? "ሽርርም" ነው የምንለው። ሃይሌ ይገዙ የሚባለው ጓደኛችን እርቃኑን ነበር። ጀምስ ቦንድ 007 የተባለውን ፓንት ብቻ ለብሶ፣ ረጅም ሽመል ይዞ የከረዩ ተዋጊ መስሎአል። ከጀምስ ቦንድ ፓንቱ ላይ ያለችውን ክብ የቀርቀሮ ጌጥ ገንጥሎ እንደ ሰአት እጁ ላይ አስሮአታል።

እኛ እዚያ ስንደርስ ጓደኞቻችን ታንኳ ላይ ሊሳፈሩ እየተዘጋጁ ነበር። ከሃይቁ ዳርቻ አምስት ያህል የአሳ አጥማጅ ጀልባዎች ተገልብጠዋል። የቡድኑ መሪ ዳንኤል መሆኑ ግልፅ ነበር። እንደተለመደው አምባገነናዊ ትእዛዝ እየሰጠ ያስተባብራል። ሁሉም ቡጢ የሚያክል ድንጋይና ፋሪሳ በእጃቸው ይዘዋል። ለምን ይህን እንደደሚያደርጉ አውቅ ነበር። ከነጫጮቹ የባህር እርግቦች ጋር አባሮሽ ለመጫወት ነው። ይህ ከተለመዱ የልጅነት ጨዋታዎቻችን አንዱ ነበር።

*(ከኛ የቀደሙት የደብረዘይት ልጆች ይህን ጨዋታ ተጫውተው ማለፋቸው ምን ያጠያይቃል? ሚኒስትር ግርማ ብሩ አንዱ ነው። አርቲስት ሙሉጌታ ባልቻ እና ብርሃኑ ነጋም የኛው የደብረዘይት ልጆች ነበሩ። ከእነዚሁ "የማታ ተማሪዎች" ጋር አባሮሽ ተጫውተው አልፈዋል። እነሱ ልጅነትን ሲያልፉ እኛ ተተካን። እኛ ስናልፍ ደግሞ ሌሎች ተተክተዋል።*

*'ለመሆኑ የዛሬዎቹ የደብረዘይት ልጆች ልክ እንደኛ ስለ ዘር የማይነጋገሩ፤ በፍቅር የሚዋደዱ ይሆኑ?' ብዬ ማሰላሰሌ መቼም አልቀረም። ከደቡብ አቅጣጫ የሚመጡት እነኛ ነጫጭ እርግቦችስ ዛሬም ይኖሩ ይሆን? ይህን ጥያቄ ለራስ መጠየቅና ምላሹን አለማወቅ ሲቃ እንዲተናነቅ ያደርጋል...)*

የሆነው ሆኖ ጓደኞቻችን ሌንሳን ተዋወቋት...

ሁሉም በአክብሮት እጅ እየነሱ ጨበጧት። ሃይሌ ይገዙ ግን ሳይጨብጣት ቀረ። ጀምስ ቦንድን ብቻ በመልበሱ እንዳያሳፍራት አስቦ ነው መሰለኝ ገለል አለ።

በመቀጠል ዳንኤል እንዲህ አለ፣

"ከኛ ጋር ለምን አትሄዱም? በቂ ጀልባ አለ"

ተስማማንና ለሶስታችን አንድ ጀልባ ያዝን።

ቀላል ነበር።

ውሃውን እየቀዘፍን ወደ እርግቦቹ ገሰገስን። የእርግቦቹ ትእቢት ልክ እንደ ደብረዘይት ልጆች ነበር። እየጮህን የቆሪሳ ድንጋዩን እንደ ካሊበር ብንተኩስባቸውም ካሉበት ንቅንቅ እንኳ አላሉም። ዳንኤልና ሚካኤል ገና ድሮ ከኛ ቀድመው ወደ ሃይቁ መሃል ዘልቀዋል።

ቀና ብዬ አየሁ።

የሰማዩ መጠቋቆር ብሶበታል። ነጎድጓድና መብረቅ ተደበላልቆ ይሰማል። እየተጠጋናቸው በመሄዳችን እርግቦቹ በድንገት ተነሱ። አንቶኖቭ የተባለው የሩስያ ግዙፍ አውሮፕላን መሬት ለቆ እንደሚነሳው፣ ቁርጥራጮቹ እርግቦች እንደ አንድ አካል ውሃውን ለቀው ወደ ሰማይ አሻቀቡ። ውሃውን ከለቀቁ በሁዋላ አቅጣጫቸውን በመቀየር እኛ ወዳለንበት አግጣጫ ታጠፉ። ሙሉ በሙሉ በአናታችን ላይ አንዣበው ሰማዩን ሸፈኑት። ከፍተኛ የማክላላት ድምፅ እያሰሙ በቅርብ ርቀት ሲያንዣብቡ የሚጥሉት ኩስ እንደ ከባድ በረዶ ቀጠቀጠን። እርግቦቹ እንደገና በግማሽ ጨረቃ ቅርፅ ተሽከርክረው ርቀው ውሃው ላይ ሰፈሩ።

ሌንሳ ይህ ሁሉ ሲሆን በደስታ ሰክራ ትጮህ የነበረ ሲሆን፤ ልብሷና ፀጉሯ፣ ፊቷ ሳይቀር በወፎቹ ኩስ ተጨማልቆ ነበር። የነዳንኤልና የነሃይሌ ይገዙ ጀልባዎች እንደገና እርግቦቹን እየተከተሉ ጉዞ ሲቀጥሉ እኛ ታንኳችንን ለማዞር ተገደድን።





ሌንሳ ደስ ያላት ቢሆንም፣ እሷን ይዘን ርቀን መሄድ አልደፈርንም። በፍጥነት ወደ ዳርቻው እየቀዘፍን ሳለ ነብዩ፣ "ሲሜሶ! ሲሜሶ!" ሲል ጮኸ።

እውነቱን ነበር።

ሊዘንብ ምንም አልቀረው። ድፍን ጥቁር ጉም ወደ ታች ወርዶ በቅርብ ርቀት ላይ ያጉረመርማል። ወደ ዳርቻው እየቀዘፍን፣ "ሲሜሶ! ሲሜሶ!" እያልን አስተጋባነው።

"ሲሜሶ! ሲሜሶ!..."

በርግጥም ሊዘንብ ነው!

ጀልባችን የመሬቱን ዳርቻ ስትነካ እንደ ረጃጅም ሽመል ወይም እንደ ጦር የተወረወረ ዝናብ ይዠልጠን ይዞ ነበር። መጠለያ አልነበረንም። ሌንሳን እየጎተትን ወደ ቹቾ ግቢ አጥር ሮጥን። የአጥሩን ሽቦ ሾልከን የመቃ ጫካ መሃል ወደቅን። ጫካው ውስጥ ጠሮ እና እምቧጮ ከመቃው ጋር ተገማምዶ ጠብታ ውሃ እንኳ የሚያሳልፍ አልነበረም። እና በመቃ ግድግዳና በመቃ ጣራ ስር ተጠጋግተን ተቀመጥን። እናም ወደ ባህሩ ርቀው የገቡ ጓደኞቻችን የሄዱበትን አቅጣጫ እንመለከት ቀጠልን። ምልክታቸው እንኳ አይታይም ነበር...

ይህ ሁሉ አልፎአል።

የሩቅ ትዝታ ብቻ ነው። ስንቶች ይሆኑ ግን ድንቅ የልጅነት ትዝታቸውን መተረክ እየፈለጉ ታቅፈውት ቁጭ ያሉ?

*(ከልጅነት ጓደኞቼ ጋር ተለያይተን ቀርተናል። ዳንኤል ፀጋ ጀርመን ሃገር ይገኛል። ታናሽ እህቱ ሸዋድንበር አሜሪካ ናት አሉ። ሃይሌ ይገዙ ደብረዘይት ሲሆን፤ የኢትዮጵያ አየር ሃይል ባልደረባ ሆኖአል። ታናሽ እህቱ ቅድስት ሆስተስ ሆናለች። ሚካኤል ታምሩ ሃኪም ሆኖ አዲሳባ አለ። አባቱ ኮሎኔል ታምሩ እንደ ብረት የጠነከረ ዲሲፕሊን ያላቸው የኢትዮጵያ አየር ሃይል የበረራ አዛዥ ነበሩ። የማይከ ታናሽ እህት መስከረም ትባላለች። መሃንዲስ ሆናለችን ሰማሁ። ሳሙኤል ተሾመ አውሮፓ ላይ የቢዝነስ ሰው መሆኑን በጨረፍታ ሰምቻለሁ። ታናሽ እህቱ ጥርሷ ሸራፋ ሆኖ በጣም ቆንጆ እንደነበረች ትዝ ይለኛል። አብይና እስክንድር የት እንደሚገኙ ወሬኛው Google እንኳ አያውቅም። እስክንድር ግን ኢንጂነየር*

*ሲሆን፤ አንድ ጊዜ ወደ ጋና ሲጓዝ ሆስተሷ ጓደኛችን አይሮፕላን ላይ አግኝታው እንደነበር ከአስር አመት በፊት አጫውታኛለች። ሽርርም ግን እዚያው ደብረዘይት ከአርመናውያን የቆዳ ፋብሪካ ውስጥ ተቀጥሮ ይሰራል። እነዚህ ሁሉ ጓደኞቼ እንዴት ናፍቀውኛል? ሰው ነንና ሁላችንም ጊዜያችን አልቆ መሞታችን መቼም አይቀር። ከዚያ በፊት አንድ ጊዜ ደብረዘይት ከሃይቆቻችን ዳርቻ ብንገናኝ እንዴት መልካም ነበር...)*

* * *

እነሆ! ሌንሳ ምርጥ ጓደኛችን ሆነች!

መፈራራቱና መተፋፈሩም ቀነሰ። አልፎ አልፎ እጅ ለእጅ መያያዝም ጀምረናል። ወዲያው ግን ፊታችን ድልህ እየመሰለ ቶሎ እንላቀቃለን። ነብዩን አንድ ጊዜ ትከሻውን ስትደገፈው የሚያወራው የነበረው ሁሉ ጠፋበት። እጁን ካነሳችለት በሁዋላ እንኳ ሊናገር አልቻለም። እንደ ሽኮኮ የሚፀልይ መስሎ ባለበት ድርቅ ብሎ ቀረ።

ቀስ በቀስ ግን መቀራረባችን ጨምሮአል። በኔ በኩል እጇን ስነካት የሚያስደነግጠኝ ነገር እንደ በፊቱ አልነበረም። ነብዩ በርግጥ ከመጀመሪያውም እንደኔ ርብትብት አልነበረም። ይህም አቀራረቡ ሳያስቀናኝ አልቀረም። ሌንሳ ግን ሁለታችንንም እኩል ትቀርበን ነበር፣

"ጥሩ ጓደኞች አገኘሁ። እናንተን ባላገኝ ደብረዘይት ይሰለቸኝ ነበር" ትለናለች ደጋግማ። በተጨማሪ፣ "አባቴ ሲመጣ አስተዋውቃችሁዋለሁ" ብላናለች።

በዚህ የሌንሳ አነጋገር ሳንገረም አልቀረንም። ከነብዩ ጋር ተነጋግረንበት ነበር። ምክንያቱም አባቷም ሆነ አጐቷ ከሷ ጋር ካዩን የሚደበድቡን እየመሰለን እንሰጋ ነበር። ከአባቷ ጋር ምን ብላ ልታስተዋውቀን እንደምትችል ለመረዳት ተቸግረን ነበር። በዚያው ሰሞንም የኢሬቻ (Hirrecha) በአል የሚከበርበትን ቦታ ልናሳያት ወደ ሆራ ሃይቅ ይዘናት ሄድን።

*(ነፍስ ካወቅሁበት ጊዜ ጀምሮ ኢሬቻ በአል ላይ ምንጊዜም እገኛለሁ። አልፎ አልፎም የነብዩ አባት ወደ ሃይቁ ይዘውን ይሄዳሉ። አንድ ቀን ኢሬቻን ለማክበር ወደ ሆራ ስንሄድ እንዲህ ሲሉ አጫወቱን፣*

*"የኢሬቻ በአል ቅዱስ በአል ነው። የእግዚአብሄር ስጦታ*





*ተመልሶ ለእግዚአብሄር የሚሰጥበት በአል ነው። የዋቀዮ ስጦታ የሚባሉት ውሃና ልምላሜ ናቸው። በዛሬዋ እለት፣ 'ጥቁሩን ክረምት በሰላም ያሳለፍከን አምላክ፣ ከመብረቅ፣ ከበረዶ፣ ከጎርፍ፣ ከውርጭ፣ ከከባድ ነፋስ የከለልከን ፈጣሪ እናመሰግንሃለን። አሁን ያለውን መኸር፣ ያፈራውን አዝመራ በሰላም አብላን' ብለን እግዚአብሄርን እናመሰግነዋለን።"*

*በቅንነት እንዲህ ስል ተናገርኩ፣*

*"እናቴ ግን፣ 'ኦሮሞዎች ውሃውን ያመልካሉ' ብላ ነው የነገረችኝ"*

*ጋሽ አበበ ፈገግ አሉና ጭንቅላቴን አሻሹኝ፣*

*"አላዋቂዎች እናትህን አሳስተዋታል። ከዚያም አልፎ፣ 'ለሰይጣን ያመልካሉ' እንደሚሉን እናውቃለን። ውሃ ዋቀዮ የሰጠን ፀጋ ነው። ውሃ ባይኖር እኛም ባልኖርን። ሰይጣን ከውሃ ይሸሻል እንጂ ውሃ ውስጥ አይቀመጥም። የሰይጣን ማደሪያ የሰው ልብና የሰው አእምሮ ነው። ክርስቶስ ለመጀመሪያ ጊዜ ራሱን የገለጠውም ውሃ ዳር ነው። በውሃ አይደል እንዴ የምንጠመቀው? ውሃ የሰይጣን ማደሪያ ከሆነ ለምን እንጠጣዋለን?"*

*ማምሻው ላይ ጋሽ አበበ ወደ ቤታችን መጡና ከእናቴ ጋር ወግ ጀመሩ። ስለ ኢሬቻ ብዙ ከተነጋገሩ በሁዋላም ተመልሰው ሄዱ። የጋሽ አበበ እግር ወጣ ከማለቱ እናቴ ከጉማሬ ቆዳ የተሰራውን አለንጋ አንስታ ወረደችብኝ። ስትገርፈኝም እንዲህ እያለችኝ ነበር፣*

*"የቤትህን ምስጢር ደጅ እያወጣህ ትዘረግፋለህ? ጅላጅል የሆንክ ፍጡር። ለሰው የሚነገርና የማይነገረው መቼ ይሆን የሚገባህ? በችግር ጊዜ ከሚደርሱልኝ፣ ተከባብረን ከኖርነው ጎረቤቶቼ ልታጣላኝ? ጅል! ጅል የሆንክ ፍጥረት..."*

*እስኪበቃት ቀጥቅጣኝ ሲደክማት ተወችኝ።*

*ያን ቀን ራት ሳልበላ አደርኩ። በነጋታው ቁርስ ሲቀርብ እናቴ ጎትታ በቁርስ ጠረጴዛው ዙሪያ ጎለተችኝ። እየበላን ሳለም በግልባጩ የኢሬቻ ቄስ ሆና አረፈችው። እንዲህ እያለች ታስተምረን ጀመር፣*

*"ኢሬቻ ቅዱስ በአል ነው። አምላክ የሚመሰገንበት በአል ነው። ኢሬቻ ማለትም ስጦታ ማለት ነው። ውሃውን ያመልካሉ የሚባለው ሃሰት ነው። ይህን ማወቅ አለባችሁ..."*

*በጣም ተገርሜ እንዲህ ስል ጠየቅሁዋት፣*

*"ታዲያ ትናንት ለምን ገረፍሽኝ?"*

*"ለምን እንደተገረፍክ እስካሁን አላወቅህም?"*

*በተለመደው ሃይለኛ ገፅታዋ አተኮረችብኝ፣*

*"የተገረፍከው ጅል ስለሆንክ ነው። 'እናቴ እንዲህ አለች፣ አባቴ እንዲህ አለ' እያልክ ደጅ ሄደህ ማውራት ጅልነት ነው። ገብቶሃል? አሁን አርፈህ ቁርስህን ብላ"*

*እናቴ ጠንካራ ሴት ነበረች።*

*እንደ ሽቦ በከረረ ስነስርአት እየቀጣች ልታሳድግን ጥረት ታደርግ ነበር። ምክሮቿ መልካም ነበሩ። ደጋግማ 'ሃበኒ ሀበይ ይገብረካ' እያለች ትናገር ነበር። ቀጥታ ትርጉሙ፣ 'መለመን ጠጣ ያደርጋል' ማለት ነበር። በርግጥ ከእናቴ ምክሮች ያገኘሁት ጥቅም ያመዘነ ቢሆንም፣ በርቧሬ ማጠን፣ በጉማሬ አለንጋ መግረፍ ከመሳሰሉ መረን የለቀቁ ቅጣቶቿ ጥቅም አግንቼያለሁ ማለት ግን አይቻልም። እናቴ፣ 'ከመለመን መሞት ይሻላል' ከሚለው ተደጋጋሚ ምክሯ ቀጥሎ፣ 'የቤተሰብ ምስጢሮች' የምትላቸው ነገሮች ነበሯት። 'የቤትህን ምስጢር ደጅ አወጣህ' በሚል ሰበብ በተደጋጋሚ የተቀጣሁ ሲሆን፣ ይህም ከጅልነት ይቆጠርብኝ ስለነበር ለረጅም ጊዜ ጉዳዩን አሰላስዬዋለሁ። እናቴ የምትፈልገው አይነት ባህርይ መያዝ ግን ሳልችል ቀረሁ። ለነብዩ ሁሉንም እነግረው ነበር። እሱም ቤተሰቡን የተመለከተ ዝርዝር ነገር ያጫውተኛል።*

*አንድ ሰው የግሉንም ሆነ የቤተሰቡን "ምስጢሮች" ለመደበቅ በሚያደርገው ሙከራ "ማስመሰል" ለተባለ በሽታ ሊጋለጥ እንደሚችል ከራሴው ልምድ ተምሬያለሁ። ነብዩም ስለ ራሱ ሲናገር ምህረት አልነበረውም። በጎረምሳነታችን ዘመናት ደጋግሞ፣ 'ምስጢር የሚባል ነገር የለም። እኔ ያደረግሁትን ሌላ ሰውም አድርጎታል' ይል እንደነበር ትዝ ይለኛል።)*

ሌንሳ የኢሬቻ በአል ሲከበር አይታ እንደማታውቅ ነገረችን። ወሰድንና ከሆራ ሃይቅ ዳርቻ ያለውን ዋርካ አሳየናት። ስለ በአሉ አከባበርም አጫወትናት። የበአሉ እለት አዋቂዎች ውሃው ዳር፣ ዋርካው አጠገብ ቆመው የምስጋና ፀሎት ያሰማሉ። የወይራ ቅጠል፣ ሰርዶ፣ ቀጤማ፣ አደይ አበባ ይያዝና ውሃው ላይ እየተነከረ ሰው ላይ ይረጫል። በመጨረሻም አራቱም ቅጠሎች ለዋቀዮ በስጦታ መልክ ውሃው ዳር ይቀመጡለታል።





የመልስ ጉዞ ስናደርግ እግረመንገዳችንን ዱለቻ የተባለውን ተራራ በሩቅ አሳየናት። ግንቦት ወር ላይ ሃርፋሳ የሚባለው በአል ተራራው አናት ላይ ይከበራል። ገበሬዎች፣ "ጨለማውን ክረምት በሰላም አሳልፈን" ብለው ፀሎት ያደርጋሉ። የሳራ ባል አብርሃም ተራራ ላይ ወጥቶ ለአምላኩ በግ አርዶ መስዋእት እንዳቀረበው፣ እዚህም በግ ታርዶ ምህለላ ይደረጋል። ሽማግሎቹ፣ "ከድርቅ ሰውረን፣ እርጥብ አድርገን" ብለው ፀሎት ያደርሳሉ።

* * *

አንድ ቀን ሌንሳን ይዘን እነነብዩ ቤት አመሸን። ከግቢው ደጃፍ ሳሩ ላይ ቁጭ አልን። ከፊት ለፊታችን የቢሾፍቱ ሃይቅ ወለል ብሎ ይታየናል። ከሃይቁ አናት አየር ሃይል ጋራ እንደ አውቶቡስ ተጋድሞአል። ከሃይቁ አቅጣጫ የሚነፍሰው ነፋስ እንደተለመደው አየሩን አቀዝቅዞታል። ሰማዩ ብሩህ ነበር። ከዋክብት ሆጨጭ ብለው ሰማዩን ሞልተውታል።

ሌንሳ ስለ ከዋክብቱ ታጫውተን ጀመር፣

"ጌራ የሄድኩ ጊዜ ማታ ማታ እንደዚህ ደጁ ላይ ቁጭ ስንል አያቴ ስለ ከዋክብት ይነግረኝ ነበር" ብላ ወግ ጀመረች። እናም ቀጠለች፣ "የጌራ ሰዎች ቀን የሚቆጥሩት በከዋክብት ነው። እያንዳንዱ ኮከብ ስም አላት።"

ወሬውን የሚቀጥል በመጥፋቱ ነው መሰለኝ፣

"አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ" አለች፣

በእሺታ ለጥያቄው ተዘጋጀን፣

"ፀሃይ በየት ወጥታ በየት ትጠልቃለች?"

"ይህማ ቀላል ነው"

"ይህንን የማያውቅ የለም" ነብዩ አከለ።

"ጨረቃስ በየት ወጥታ በየት ትጠልቃለች?"

አሁን ግን ለምላሽ የተጣደፈ አልነበረም። ዝም ዝም ሆነ። ጥቂት አሰብኩና እንዲህ አልኩ፣

"ጨረቃ መውጫና መግቢያ የላትም"

"ለምን አይኖራትም?"

"እሷ ዝም ብላ ነው የምትወጣው"

"ዝም ብሎ መውጣት ምንድነው?"

በዚህ ጊዜ ነብዩ ጣልቃ ገባ፣

"እኔ ስለ ጨረቃ መግቢያና መውጫ አስቤ አላውቅም። እስኪ አንቺ ንገሪን? በየት ወጥታ በየት ትገባለች?"

ከት ብላ እየሳቀች፣

"እኔም አላውቅም" አለች። አያይዛም፣ "አያቴ ግን ያውቃል። ሲናገር ሰምቼዋለሁ። ግን አልገባኝም። ጨረቃ ግን መውጫና መግቢያ አቅጣጫ አላት"

የጨረቃና የከዋክብት ወሬያችን እዚሁ ላይ ያበቃ ይመስለኛል። ከዚያ ወዲያም ስለ ጨረቃ መግቢያና መውጫ ያነበብኩ አይመስለኝም። አንብቤም ከነበረ ትኩረት ሳላደርግበት ዘልዬው ሊሆን ይችላል። ከ26 አመታት በሁዋላ ግን ሌንሳን የሚያስታውሰኝ አንድ አጋጣሚ ተፈጠረ።

*(በወርሃ መስከረም 2001 የኢድ አልፈጥር በአል በተከበረበት ምሽት ከፕሮፌሰር አስመሮም ለገሰ ጋር የራት ግብዣ ነበረብኝ። በትሪ ላይ የቀረበውን እንጀራ በልተን እንዳበቃን ከአዛውንቱ ምሁር ጋር ረጅም ቆይታ አደረግን። የከዋክብትና የጨረቃን ጉዳይ አንስተውም ብዙ አወጉን። ፕሮፌሰሩ ያጫወቱንን በዚሁ መፅሃፍ ውስጥ ተርኬዋለሁ።)*

* * *

እነሆ! ሌንሳ ምርጥ ጓደኛችን ሆነች።

በዚያው ሰሞንም ታዲያ ነብዩ እኔን የሚያስከፋ ድርጊት ፈፀመ። ከሌንሳ ጋር የጀመርነው አዲስ ጓደኝነት ሁለተኛ ሳምንቱን እንዳገባደደ፣ አንድ ቀን ማለዳ ነብዩ የትምህርት ቤት ካርዶቹን በሙሉ ይዞ መጣና ለሌንሳ አሳያት። ሌንሳ እንደገና በጣም ተደነቀች። የነብዩን ካርዶች እያገላበጠች በመመልከት ደጋግማ፣

"ይሄን ለአባቴ አሳየዋለሁ!" ማለት ሆነ።

ለነገሩ እውነቷን ነበር፣

ነብዩ ምንጊዜም ከክፍል አንደኛ ስለሚወጣ፣ ከ95 በታች ውጤት አልነበረውም። 98 ወይም 99 እንደ የረር ተራራ ሽውሽዌ ተጠቅጥቀው ይታዩ ነበር፣

በዚያን ቀን በጣም ተጐዳሁ።

ምክንያቱም ወሬያችን ሁሉ ስለ ነብዩ የትምህርት





ውጤት ብቻ ሆነ። ጨርሶ እንዳልተፈጠረ ሰው እዚያው ተረሳሁ። የከፋቱ ከፋት ደግሞ የነብዩን ካርድ የምናየው እኛው ግቢ ውስጥ ደጃፉ ላይ ቁጭ ብለን ነበር። የፈራሁትም አልቀረ። ሌንሳ ወደኔ ዞረች፣

"ያንተስ ካርድ?"

እንደ አለት በከበደ ስሜት መልስ ሰጠሁ፣

"እኔ ሰነፍ ነኝ ሌንሳ!"

ሌንሳ ሳቀች! በጣም ሳቀች!

ነብዩ የትምህርት ካርዱን በማምጣቱ እንዲህ ሊሆን እንደሚችል አለማስተዋሉን ተረድቼ ነበር። ይህንኑ ከቀጣይ አነጋገሩ ተረዳሁ። ሊያስተባብል ፈልጎ ለሌንሳ እንዲህ አላት፣

"ሰነፍ አይደለም። እንደኔ ባይሆንም ጥሩ ውጤት ነው ያሚያመጣው። ድርሰት ደግሞ ይፅፋል። አሁን ትቶት ነው እንጂ ስእል ይስልም ነበር"

"እኔም ጎበዝ ተማሪ አይደለሁም" አለች ሌንሳ።

በውነቱ ከክፍል ክፍል ማለፌ ባይቀርም፣ የትምህርት ካርዶቼ እንደ ውዳሴ ማርያም በቀይ ያጌጡ፣ በቀይ የተሸለሙ ባለ አበባ ወላንሳ ይመስሉ ነበር። በተለይ የሂሳብ ትምህርት 50 እንኳ አግንቼ አላውቅም። ድርሰት መፃፉም ቢሆን በዚያን ጊዜ ገና መጀመሩ ነበር። ስእል መሳል የተባለው ዋጋ አልነበረውም። አፄ ቴዎድሮስን ከነሹራባቸው መሳል ብቻ ነበር የምችለው። እሱም ቢሆን ሹሩባው እንጂ መልካቸው እሳቸውን አይመስልም። 'መንዶሴ የተባሉትን ጥሩንባ ነፊ ይመስላል' እያሉ ከሚቀልዱብኝ አንዱ ራሱ ነብዩ ነበር።

በዚያን ቀን እንደ ማጭድ ጐብጬ ነበር መኝታዬ ውስጥ የገባሁት። በነጋታው ስንገናኝ ሌንሳ ከኔ ይልቅ ወደ ነብዩ ፍላጐት ታሳድር ይሆናል የሚል ስጋት ይዞኝ አይን አይኗን ስመለከታት አረፈድኩ። ሌንሳ ግን ምንም ለውጥ አላሳየችም።

ነብዩ በፈፀመው ድርጊት በመፀፀቱ በነጋታው ያንን ለማካካስ ለሶስታችንም የሚበጁ የጋራ ወሬዎችን ለማምጣት ይጥር ጀመር። በርግጥም ተሳካለት።

ግጥሞችን በቃሌ የመያዝ ችሎታ ነበረኝ። እናም ታዲያ፣ "አለማወቅ" የተሰኘችውን ግጥም እንዳነበንብ ነብዩ አሳብ አቀረበ። ሌንሳም ለመስማት ጓጓች። ሞራሌ ተሻሻለና ጉሮሮዬን ሞረድኩት። ግጥሙንም እንደ ቅዳሴ ዜማ አዘነብኩት፣

ከእለታት አንድ ቀን - በአንዲት ከተማ፣
የገጠር አህያ - መሃል መንገድ ቆማ፣
መኪና መጣና - ድምፁን ሳትሰማ፣
ጨፍልቆ አሳረፋት - ውሃ ሳትል ደግማ፣
ባለቤቱም ነበር - አንድ የዋህ ባላገር፣
በጣም አዝኖ ሳለ - እጅግ አርጎ ከምር፣
መኪናውን ሰማው - ሲል ጓጉተው-እንድር፣
በዚህ ተበሳጨ - መስሎት የሚፎክር!

ከተቀመጥኩበት ተነስቼ፣ ፑሽኪን እንደሚያደርገው እጄን እየዘረጋሁና እያጠፍኩ፣ የአህያውና የባለመኪናውን ትረካ ፈጨሁት። ሌንሳ ተመስጣና ፈዝዛ ትመለከተኝ ስለነበር መወዛወዙ እንደባሰብኝ ትዝ ይለኛል። በተለይ የመጨረሻዎቹ ስንኞች አህያው የተገደለበት ባላገር፣ ወንጀለኛውን መኪና አርባ ጅራፍ ገርፎ እንዳሰናበተው የሚገልፅ ክፍል ነበር። ድምፄን ከፍና ዝቅ በማድረግ፣ ሳቅና ስላቅ ጨማምሬ ያለምንም መደነቃቀፍ አጠናቀቅሁት፣

የሰው ሃዘን ይግባው - ህመምን ይቅመሰው፣
ትንሽ እንዲያለቅስ - ሁዋላ እግሩን ልጥበሰው፣
ብሎ ባለው ሃይሉ - ወዲያው ተያያዘው፣
አርባ ጅራፍ ገርፎ - ይበቃሃል አለው፣

በዚያን ቀን በጣም ተደስቼ ዋልኩ።

በነጋታው ግን ነብዩ ተጨማሪ ትረካ እንዳቀርብ ሞክሮ ሳይሳካለት ቀረ። ጭራሽ በግልባጩ አበላሸው፣

"የቆሪጥን ታሪክ ለምን አትነግራትም?" አለ።

"ማነው ቆሪጥ?" ስትል ጠየቀች።

"ቢሾፍቱ ሃይቅ ውስጥ የሚኖር ሰይጣን"

"ሰይጣን?" ፊቷን አጨፋገገች።

"ምን መሰለሽ ሌንሲ! እሱ ሲተርከው በጣም አሪፍ ነው። እኔ ስንት ጊዜ ሰምቼዋለሁ መሰለሽ? በጣም ነው የሚያስቀው። ንገረን?" አለ ወደኔ እያየ።

አጋጣሚውን ለመጠቀም ሳቆበቁብ ሌንሳ ተቃወመች፣

"በስመአብ!" ብላ ካማተበች በሁዋላ "...ስለ ሰይጣን መስማት አልፈልግም" ብላ ሽምቅቅ አለች። አያይዛም እንዲህ ስትል ከጥያቄ ጋር ገሰፀችኝ፣

"ስለ ሰይጣን መናገር ምን ያደርግልሃል?"

መከራኝ ስታበቃም፣





"አሁን ወደ ቤቴ መሄድ እፈልጋለሁ" ብላን እርፍ!

በዚያን ጊዜ በራስ ላይ ስለ መቀለድም ሆነ፣ በራስ ላይ ስለ መሳቅ ምንም ግንዛቤ አልነበረኝም። በመሆኑም እንዲያ ስትለኝ አጥንቴ የተከታተፈ ያህል ቁጭ ማለት እንኳ አቃተኝ።

በርግጥ በወቅቱ ቆሪጥን እንደ ገፀባህርይ ፈጠራ ጨማምሬበት አንዳንድ ትረካዎችን መስራት ችዬ ነበር። የነብዩ አሳብ ይህ ችሎታዬ ሌንሳ ፊት እንዲታይ ነበር። በመካከላችን የነበረውን የጓደኛነት ሚዛን ወደነበረበት ለመመለስ ነበር ሙከራው። አልሆነለትም። ባልተጠበቀ መንገድ እንደገና የኔ ሚዛን ጐደለና አረፈው።

ሌንሳ ከሄደች በሁዋላ ከነብዩ ጋር ወደ ቢሾፍቱ ሃይቅ አፋፍ ሄደን ቁጭ አልን። የባጥ የቆጡን ስንጨዋወት እንደቆየንም፣

"ቅር አለህ እንዴ?" ሲል ጠየቀኝ።

"ለምን?"

"ሌንሳ በተናገረችው?"

"ምንም ቅር አላለኝም"

"ቢሆንም ተበሳጭተሃል?"

"ሳላስበው ነው። የሚያበሳጭ አይደለም"

"እውነት?"

"ጊዮርጊስን!"

በነጋታው እንደተለመደው ረፋዱ ላይ እኛ ቤት ደጃፍ ላይ ቆመን ሌንሳ ብቅ እስክትል ስንጠብቃት ቆየን። ሆኖም ብቅ ሳትል ምሳ ሰአት በመቃረቡ በአጥሩ በኩል ሰራተኛዋን ጠራሁዋት፣

"ሌንሳ የለችም እንዴ?"

"ሌንሳ ትላንት ሄደች። ከናንተ እንደተለየች አባቷ መጥተው ወሰዷት። ልታገኛችሁ ፈልጋ በጣም ተጨንቃ ነበር። ግን ቤት አልነበራችሁም። አባቷ አጣድፈው ይዘዋት ሄዱ..."

አንዳችም ቃል ሳንተነፍስ ወደ ቢሾፍቱ ሃይቅ ዳርቻ ሄደን ተቀመጥን። አየሩ እንደተለመደው ነፋሻ ነበር። ገደሉ ሁሉ ሳር ለብሶአል። ብዙ ደቂቃዎች እዚያው ገደሉ አፋፍ ላይ ቁጭ ያልን ይመስለኛል። በመካከሉ ግን አልቻልኩም። በተፈነቀለ ስሜት ህቅ! ብዬ ማልቀስ ጀመርኩ፣

ነብዩ በጣም ግራ ተጋብቶ ሊያፅናናኝ ሞከረ፣

“ምን ሆነሃል? ኸረ በጎርጊስ? ሰው ቢያይህ ምን ይላል?”
ሲወጣልኝ እንባዬን ጠራርጌ ዝም አልኩ።
ወደ ቤታችን ስንመለስም እንዲህ ሲል ጠየቀኝ፣
“ምን ሆነህ ነው ግን?”
“ዝም ብዬ ነው”
“ዝም ብለህማ አይደለም። ወደሃታል እንዴ?”
ቆጣ ማለቴ ትዝ ይለኛል፣
“እንዴት እንደዛ ትላለህ? የሁለታችንም ጓደኛ ነች”
“ታዲያ ለምን አለቀስክ?”
ዘግየት ብዬ እንዲህ አልኩ፣
“እውነቱን ልንገርህ?”
“ንገረኝ?”

“የቀዌሳን ታሪክ ልተርክላት አስቤ ነበር። ሌሊቱን ሙሉ ስለማመደው ነበር ያደርኩት” ስል ምርር ብዬ ያለቀስኩበትን እውነተኛ ምክንያት አጫወትኩት።

በሚቀጥለው አመት ሌንሳ ወደ ሰፈራችን ትመጣ ይሆናል ብለን በተስፋ ጠበቅናት። ከመጣች አነብላታለሁ በሚል የቀዌሳን ታሪክ በፅሁፍ ጭምር አዘጋጀሁት።

ሆኖም ሌንሳ ሳትመጣ ቀረች።

የቀዌሳን ታሪክ ለሌንሳ ባለመተረኬም ቅሬታው ለረጅም ጊዜ ልቤ ውስጥ ቆየ። መቆየት ብቻ ሳይሆን ቅሬታው ህመም ሆኖ አሰቃይቶኛል። የቀዌሳን ታሪክ በመተረክ የሌንሳን ቀልብ ለመሳብ ከፍተኛ ፍላጎት አድሮብኝ ነበር።

ምን ማድረግ ይቻላል?

አልተሳካም።

እንዲህ ያሉ ያልተቋጩ ፍላጎቶች ቅሬታ ፈጥረው፣ መጥፎ ትዝታ ሆነው ዝንተአለም ልብ ውስጥ ይኖራሉ። የቅሬታው ምስልም ምሽት ላይ በሚነድ እሳት ዳርቻ ከወገን ርቆ የመቀመጥና የመናፈቅ አይነት ሲሆን፣ ሆድ ይባባል...

እነሆ! ጊዜው ይነጉዳል።

ልጅነት የሩቅ ትዝታ ሆኖአል። ከዚያ ወዲህ ሌንሳን በአይነ ስጋ አይቼያት አላውቅም። 28 አመታትም አልፈዋል። የዚህ ምእራፍ ባለታሪክ የሆንነው ሶስታችንም በየፊናችን





ወደማይቀረው እናዘግመው ይዘናል። የ41 አመት ሰው መሆናችን ነው እንግዲህ። ህይወት እንዲሁ ናት...

ነብዩ አበበ በኑሮው ተሳክቶለታል። ጥሩ ቤተሰብ መመስረቱን ሰምቻለሁ። አሜሪካ ላይ አንቱ ከተባሉ የህክምና ዶክተሮች አንዱ ለመሆንም በቅቶአል። ሙሉ በሙሉ ደስተኛ ሰው ሆኖአል ብዬ ግን በፍፁም አላምንም። ቀደም ባሉት ጊዜያት ደጋግሞ እንዲህ ሲል እሰማው ነበር፣

“ብቻህን መደሰት አይቻልም። ሌላው የተሻለ ህይወት እንዲኖር ማገዝ ካልቻልክ ለራስህ ማግኘትህ ብቻውን የደስታ ምንጭ ሊሆን አይችልም”

ስለ ሌንሳም ቢሆን ቁራጭ ወሬ አለኝ። ሚንአሶታ በተባለው የአሜሪካ ክፍለ ሃገር ነዋሪ ከሆነች 12 አመታት ደፍናለች። ባለ ትዳርና የሁለት ልጆች እናት ለመሆንም በቅታለች። ይህ መፅሃፍ ታትሞ ሲወጣ ሌንሳ አግኝታ ታነበው ይሆናል ብዬ ተስፋ አድርጌያለሁ።

ማን ያውቃል?

የአንድ ክረምት የልጅነት ገጠመኜን ደግማ ደጋግማ አጣጥማ ስትጨርስ፤ ሳልነግራት የቀረሁትን የቀዌሳን ታሪክ አንብባ እንዳበቃች፤ ኮምፒዩተሯን ከፋፍታ ለኔ ደብዳቤ ለመፃፍ ትጣደፍ ይሆናል...

- 2 -

# የቀዌሳ አመፅ

አውሬማ ይጮሃል - ጥቅጥቅ ካለው ጫካ፣
በአዳኞች ሲከበብ - መኖሪያው ሲነካ፣
መብረቃዊ ድምፁም - የደወል አስተኔ፣
እንደ ሙዚቃ ስልት - ይሰማኛል ለኔ፣
ከተራራው ማዶ - ድምፅ እያስተጋባ - ከሚመጣበቱ፣
ዘፈን ስትዘፍን - እንደምትሰማ - ከርቂት ሴቲቱ፣
እያንዳንዱ ድምፅም - እንደ አነዛዘሩ፣
በባዶው ሰማይ ላይ - ይመጣል በአየሩ፣

(ግጥም - አሌክሳንድር ፑሽኪን)
- አያልነህ ሙላቱ እንደተረጎመው -

የቀዌሳ ታሪክ ተረት የሚመስል ቁራጭ እውነት ነው። ድንገት እግር ጥሏችሁ ወደ ዝቋላ ብቅ ካላችሁ፣ መንገድ ላይ የምታገኙትን ማንኛውንም ገበሬ

'ቀዌሳ ማነው?' ብላችሁ ጠይቁት።

ገበሬው ምንም ሳያመነታ ቀዌሳ ለክብሩና ለህልውናው ሲል የፈፀመውን ወደር አልባ ተጋድሎ እንደወረደ ያወጋችሁዋል።

የቀዌሳን አጭር የህይወት ዘመን ታሪክ የሰማሁት በ1973 የክረምቱ ወራት ላይ ለሁለት ሳምንት እረፍት ከነብዩ ጋር ወደ ዝቋላ ገጠር ሄደን ሳለ ነበር።

ለነገሩ ምን እረፍት ይባላል?

ማሳው ላይ አረም ማረም፣ ወደ ዱር ወርዶ እንጨት





መስበር፣ የግጦሽ መስኩ ላይ ከብቶቹን ማሰማራት ይህን ሁሉ እንሰራለን። በአናቱ የነብዩ አባት ቂጭ ማለት የት ያውቁና? የሚሰሩት ካጡ ደኑን እየመነጠሩና እያቃጠሉ ለመጪው ክረምት የሚሆን የእርሻ መሬት ያዘጋጃሉ።

ብዙውን ጊዜ ማምሻው ላይ ከብቶቹን ከሃማጋው ወደ በረት አሸገን ስናበቃ፣ ደጁ ላይ የቁርበት ምንጣፍ አንጥፈን ጋደም እንላለን።

ማለዳው ምንጊዜም ተናፋቂ ነው።

የአተር እሸት ከማሳው ላይ እየመዘረጥን፣ ጠርጥረን እየበላን ከብቶች እያገድን የክረምቱን ፀሃይ እንመገባለን። የገብሱን እሸት እየሸመጠጥን መአዛውን ወደ ሳንባችን መሳቡ የሚሰጠን እርካታ ሌላ ነው። ዋንዛውን እየገነጠልን እናጣጥመዋለን። ጨጓራችን ረሃብ ከተሰማው ወደ አንዱ ገበሬ ጎጆ ብቅ ማለቱ ይበቃል። ወፍራም እርጎ እስክንጠግብ ለመገልበጥ ድምቡሎ አያስፈልግም። እርጎ እንዴት ከገንዘብ ይቆጠራል? ነውር ነው። ከነውርም ነውር፤ የነውሮች ሁሉ ነውር። ለነገሩ ማሩንና አይቡንስ ቢሆን ማን ሲነካው? ዞር ብሎ የሚያየው የለም።

የሚደንቅ ነገር ልንገራችሁ?

ከእንቁላል ይልቅ አንድ የክብሪት እንጨት ይወደዳል።

* * *

አንድ ቀን ታዲያ ሳሩ ላይ ጋደም ብለን ሳለ አንድ ጥቁር አውሬ በላያችን ላይ ፈትለክ ብሎ ወደ ጫካው ገባ። በጣም ደንግጠን ነበር። አውሬውም አላየንም ኖሮአል። እሱም ራሱ ደንግጦ ሳያስበው ላያችን ላይ ሳይወጣብን አልቀረም፣

"ሽላ–ምጥማጥ ነው" አልኩ።

"አይደለም!" ሲል ተቃወመ ነብዩ፣ "...በደንብ አይቼዋለሁ። ድመት ነው። የጫካ ድመት ሊሆን ይችላል።"

በዚህ ጥቂት ተከራከርን።

እኔ ከዚያ ቀደም የጫካ ድመት የሚባል መኖሩን አላውቅም ነበርና አስደንግጦን ያለፈው አውሬ ድመት መሆኑን መቀበል አልቻልኩም ነበር።

*(ድመት እየለመነ ሆዱን ይሙላ እንጂ ከመቼ ወዲህ ነው ጫካ የሚገባ? አይጥ ካባረረና ወንበር ካሞቀ መች አነሰው? መልክ እንጂ ምን ልብ አለው ድመት? 'የነብር ዘር አለብኝ' ብሎ ዘር መቁጠር ምን ያደርጋል? ሆኖ መገኘት እንጂ!' እያልኩ ሳላስብ አልቀረሁም። ዳሩ ግን ተሳስቼ ኖሮአል። ማምሻውን ጥቁሩ አውሬ ድመት መሆኑን አረጋገጥኩ..)*

በእርግጥም ማምሻው ላይ ስራችንን ካበቃን በሁዋላ እንደተለመደው የቁርበት ምንጣፎችን ደጁ ላይ ዘረጋንና ጋደም አልን። ለአይን መያዝ ቢጀምርም ከብቶች ገና ተጠቃለው አልገቡም። ጫጫታው አየሩን ሞልቶታል። አእዋፍ፣ ውሾች፣ ህፃናት፣ ጥጆች፣ ሁሉም በየፊናው የሚያወጣው ድምፅ ጆሮገብ ህብረ ድምፅ ፈጥሮ መንፈስን ይማርካል።

የነብዩ አባት ልብስ የሚሰፉበትን ማሽን በመተው፣ እሳቸውም እንደተለመደው ከወገባቸው በላይ በቀዝቃዛ ውሃ ተጣጥበው፣ የተጠቀለለ ቁርበት ይዘው በመምጣት አጠገባችን ጋደም አሉ።

ምሽት ላይ እንዲህ ደጁ ላይ ጋደም ማለቱን የለመድነው ከእሳቸው ነው። ድቅድቅ ያለው ጨለማ ላይ የፈሰሱትን ከዋክብት እያዩ በፀጥታ አእምሮን ማሳረፍ ከፍተኛ ደስታ እንደሚያጎናፅፍ እኔም ይኸው ተረድቼያለሁ።

"የጫካ ድመት" የተባለው ነገር አእምሮዬ ውስጥ የቀረ ጉዳይ ነበርና ይህንኑ አነሳሁ፣

"ጋሽ አበበ! እዚህ የጫካ ድመቶች አሉ እንዴ?"

"የቀዌሳ ልጆች ናቸዋ!" አሉ ሞቅ ካለ ሳቅ ጋር።

እናም እኛ ማብራሪያ እስክንጠይቅም አልጠበቁ። የቀዌሳን የህይወት ታሪክ በአጭሩ አወጉን።

"ዝቋላ ላይ የቀዌሳን የአመፅ ታሪክ የማያውቅ የለም" ሲሉ ነበር የጀመሩት። እናም ቀጠሉ፣

"...ቀዌ የኔ ድመት ነበር። መቼ ነበር ጊዜው? እናንተ አልተወለዳችሁም። ምን እናንተ ብቻ? ታላላቆቻችሁም አልተወለዱም። ወደዚህ ወደ ዝቋላ መጥቼ እርሻ እና ይህን የልብስ ስፌት ስራ እንደ ጀመርኩ አይጥ አስቸገረኝ። ዱባ





ያክላሉ የዝቋላ አይጦች። እየመጡ ለስፌት የቀረበውን ጨርቅ ቦጫጭቀው ኪሳራ በኪሳራ አደረጉኝ።

ይህቺን ይወዳል አበበ!

ድመት መፈለግ ጀመርኩ። እዚህ ግልገል ድመት ፈልጌ ሳጣ፣ ከደብረዘይት አንድ ጥቁር ድመት አገኘሁና ይዤው መጣሁ። እንደ ኑግ ጥቁር ነበር። ልክ እንደዚህ እንደ ጨለማ! አይኖቹ ብቻ እንደ ከዋክብት ያበራሉ። የሚንበለበል እሳት የሚመስሉ አይኖች ነበሩት።

ይሄማ ለአይጥ መድሃኒት ነው።

ጨለማ ውስጥ ቁጭ ብሎ አይኑን ገርበብ ካደረገ ፈልገህ አታገኘውም። ሃይለኛ ድመት ነበር። ቀዌሳ አልኩት ስሙን። ቀዌሳ ማለት እንግዲህ ረጅም፣ ጥቁር፣ ሃይለኛ የእባብ ዘር ነው። በመልኩና በተግባሩ ጠራሁት። ቀዌሳ! ኮስታራነቱን ተዉት! የአያቱ ልጅ!

የሸንጡና የጭራው ርዝመት ሲታይ ሸለምጥማጥ እንጂ ድመት አይመስልም። ድምፁ ብቻ በቂ ነበር አይጥ ለማባረር። አይጥ የሚባል ካካባቢያችን ድራሹ ጠፋ። ቀዌ አንድ ባንድ እያሳደደ አንቆ ጨረሳቸው..."

ጋሽ አበበ ረጅም ሳቅ ስቀው ትረካቸውን ቀጠሉ፣

"...ዝምተኛ ነበር ቀዌ! እንደ ወታደር እግሮቹን አገጣጥሞ ቁጭ ይላል። አይተኛም ብዙ ጊዜ። ቀን ቀን የቀረሮው ዛፍ ጫፍ ላይ ይወጣል። ከየዛፉ ወፎች ድራሻቸው ጠፋ። ጎጆአቸው እየገባ ከነጫጩቶቻቸው እያነቀ ፈጃቸው። እንዴት ያለ ሃይለኛ ድመት!

ዳሩ አብሮኝ ሊቀጥል አልቻለም። ጠላት ተነሳበት። ለካስ እዚህ ዝቋላ ጥቁር ድመት የክፉ እድል ምልክት ኖሮአል። እኔ ይሄን መች አውቄ? ልብስ ሊያሰፉ የሚመጡ ደምበኞቼ ቀዌሳን ሲያዩ ወደሁዋላ ሩጫ!

'ምነው? ምነካችሁ?' ስል፣

'ጥቁር ድመት በጠዋት መንገዳችንን ካቋረጠ ክፉ ነገር ይገጥመናል። ስለዚህ ቤትህ አንመጣም'

አላስተወዋልኩም እንጂ ለካስ ጥቁር ድመት ዝቋላ አይገባም። አይ አለማወቄ!? ይህን ባውቅ ሌላ ድመት እፈልግ አልነበር? ላግባባ ሞከርኩ፣

'እረባካችሁ ምን ሆናችሁዋል? ጠቆረ ነጣ ያው የድመት

ልጅ ድመት ነው’ ብል ማን ሊሰማ?

ምን ማድረግ ይቻላል? እምነት ነው። አንድ ጊዜ እንዲህ ያለ እምነት አእምሮው ውስጥ የከተተን ሰው መመለስ የዋዛ አይሆንም። ከአያት ከቅድመ አያት የሚወረስ ነው። ምን ይደረግ? እዚህ ቃጂማ ጊዮርጊስ ከሚኖር ሰው ነጭ ድመት አገኘሁና ይዤው መጣሁ። ቀዌሳን ደሞ ከረጢት ውስጥ አስገብቼ ሳበቃ በጨለማ ዝንጀሮ ገደል ወስጄ ጣልኩት።

ቤት ስደርስ ቀዌ ደጃፉ ላይ ቁጭ ብሏል።

ይችን ይወዳል አበበ?

አልተግባባንም ማለት ነው? እንደዚህማ አይሆንም። ለአንድ ድመት ተብሎ ስራ ሊበላሽ አይችልም። ልምጭ ቆረጥኩና ደህና አድርጌ ጀርባው ላይ አሳረፍኩበት።

በጣም ጮኸና ተፈናጠረ። ጥፋት አጥፍቶ የቀጣሁት መስሎታል። አልተግባባንም። የሰው አፍ አያውቅ በምን ልንገረው? በልምጬ ደህና አድርጌ ደገምኩት።

ሁኔታው በፍፁም አይረሳኝም።

ቀዌ ግራ ገብቶት አፍጦ ያየኛል። ‘በእውነት እንዲህ የሚመታኝ አበበ ነው?’ የሚል ይመስል ነበር። ይወደኝ ነበር። ማታ እዚህች አብረን ነበር የምንተኛ። ምን ይደረግ ታዲያ?

ይለይለት አልኩና ለሶስተኛ ጊዜ ስሰነዝር ፈትለክ ብሎ ከግቢው ወጣ። እንዲያም ሆኖ ግን አላመነም። ብዙም ሳይቆይ ተመልሶ መጣ። ‘እንደተባረረ ማወቅ አለበት’ አልኩና ልምጬን አንስቼ ስንደረደርበት ፊቱን አዙሮ ሸሸ።

በነጋታው ጠዋት በር ስከፍት፣ ደጃፉ ላይ ተኝቶአል።

‘ቀዌ እድለቢሱ! እንዳልተፈለግህ አሁንም ገና አልገባህም? ጥቁር ሆነህ ባትፈጠር ይሻልህ ነበር። እንግዲህ አትቀየመኝ ቀዌ!’ አልኩና በተኛበት አንድ ጊዜ አሳረፍኩበት።

እንደዚያ ያለ ድንጋጤ በሰውም በእንስሳት ላይም አይቼ አላውቅም። እንደ ጥይት ተተኩሶ ተነሳ። የአውሬ ቁጣውን ጮኸ ሲያበቃ፣ በጥላቻና በክፉ ፊት ዝቶብኝ ግቢውን ለቆ ወጣ።

ከዚያ በሁዋላ ቀዌሳ እንደማይመለስ ርግጠኛ ሆንኩ። በርግጥም ቀዌ ወደኔ ቤት አልተመለሰም። እዚያው ሰፈር ውስጥ ዛፍ ላይ ማደር ጀምሮ ነበር አሉ። እረኞች ደግሞ አውቀውት ‘ቀዌሳ! ቀዌሳ!’ እያሉ በድንጋይ ሲያዋክቡት፣ መንደሪቷን ለቆ





ወደ ዝንጀሮ ገደል ወደ ጫካው ወረደ።

ከዚያ በሁዋላ ለወራት ያህል ያየው አልነበረም። ሁዋላ ግን ተመልሶ ብቅ አለ። እኔ አላየሁትም። ወሬውን ነው የሰማሁት።

‘ቀዌሳ ሰፈር ገብቶ ዶሮ ይዞ ሄደ!’ የሚል ወሬ መጣ።

‘ተሳስታችሁዋል። ድመት ዶሮ መሸከም አይችልም። ሸለምጥማጥ ይሆናል’ አልኩ።

‘ቀዌሳ ነው’ ብለው አረጋገጡልኝ።

አላመንኩም ነበር።

በዚያው ሰሞን ግን እንደገና ወደ መንደር ገብቶ ጫጩት ይዞ ሲፈተለክ ብዙ ሰዎች አዩት። ይህን ጊዜ ግን አመንኩ።

ምን ማመን ብቻ?

ቀዌሳ እያደፈጠ የመንደሩን ዶሮዎች ይፈጅ ገባ። ዶሮ እየሰረቀ ወደ ዝንጀሮ ገደል እንደሚወርድ ቢገመትም ገደሉና ጫካው ሰፊ በመሆኑ ቀዌሳን ፈልጎ ማግኘት የሚቻል አልነበረም። እረኞች አድፍጠው ሊገድሉት ብዙ ሞክረው አልሆነላቸውም። ሲሽሎከሎክና ሲበር ልክ እንደ እባብ በአይን አይታይም አሉ።

አንድ ጊዜ ግን ቀዌሳ ለጥቂት ሊያዝ ነበር።

ዳሩ በግልባጩ አሳዛኝ ሁኔታ ተፈጠረ። እረኞች እዚሁ ከመንደራችን እልፍ ብሎ አንድ ዛፍ ስር የዶሮ ላባ ተዘርቶ ያገኛሉ። ይጠራጠሩና ዛፉን ሲፈትሹ ቀዌ ጀግናው ከዛፉ ጫፍ ባላ ማሃል ተኝቶ ያዩታል።

ወዲያው ወሬውን ቢያዳርሱ ሰፈሩ ግልብጥ ብሎ ያቺን ዛፍ ከበበ። እኔም ራሴ እየሰፋሁ የነበረውን ልብስ ትቼ በርሬ ወጣሁ።

ቀዌ የቀረሮ ዛፍ ጫፍ ላይ ባላ መሃል ተሸሽጎ ቁልቁል ያየናል። እረኞቹ እንዴት እንዳዩት የሚደንቅ ነው። ዛፉ ጥቁር በመሆኑ ቀዌን መለየት የሚቻል አልነበረም።

ለካስ ጫጩት ሞጭልፎ እዚህ ዛፍ ላይ ነበር የሚወጣ። በድንጋይ፣ በፉሪሳ፣ በወንጭፍ ከዛፍ ሊያወርዱት ሞከሩ። አልሆነም። ባላው ማህል ተለጥፎ ድንጋይ ሊደርስበት አልቻለም። ህዝቡ መቼም ግልብጥ ብሎ ወጥቶአል። ሴቶች፣ ህፃናት፣ ሽማግሌዎች፣ የቀረ ሰው አለ ማለት አይቻልም።

በድንጋይ አልሆን ሲል አንድ እረኛ ሽመል ይዞ ወደ ዛፉ ወጣ። ቀዌሳ አጠገብ ደርሶ በዱላ አንድ ጊዜ ሲሞክረው፣ ቀዌ ማመን የማይቻል ጀብድ ፈፀመ።

ከላይ ቁልቁል ወደ ተሰበሰበው ህዝብ ተወረወረ።

ይህ ይሆናል ብሎ ማን ሊጠብቅ?

ጩኸት እና ሽሽት ሆነ። አንዱ ባንዱ ላይ እየዘለለ። ድመት መሆኑንም ረስተውት ኖሮአል። ሰይጣን ወይ ነብር የዘለለባቸው ይመስል ሽሽት! አንዱ በሌላው ላይ እየዘለለ። ኡኡታው! አቧራው! ድብልቅልቁ ወጣ። ትርምሱ ጋብ ሲል አንድ ሽማግሌና አንድ ህፃን ተሰብረው ተገኙ። ርስበራስ ተረጋግጦ የደረሰውን መለስተኛ አደጋ ተውት።"

ጋሽ አበበ ፋታ ወሰዱና ትረካቸውን ቀጠሉ፣

"...ቀዌሳ ሳይያዝ አመለጠ!

"...ይሄ ሁኔታ አምልኮቱን ጨመረው። በዚያ ሰሞን ሌላ ወሬ አልነበረም። የገበሬ ማህበሩ ሊቀመንበር ጠመንጃ የታጠቁ ሶስት አብዮት ጠባቂዎችን ወደ ዝንጀሮ ገደል ላከ። አንድ ወር ሙሉ በየገደሉ ፈለጉት። ቀዌሳ! ቀዌ! እያሉ እየተጣሩ... ሊታልሉት..."

ጋሽ አበበ እንደገና ረጅም ሳቅ ሳቁ፣

"...ቀዌሳ ግን አልተገኘም።

"...ከዚያ ወዲያም ዶሮና ጫጩት መመንተፉን ተወ። ድምፁ ጠፋ። አየሁት የሚል እረኛም አልተደመጠም።

ሁዋላ ግን እንደገና ወሬው መጣ።

ሌሊት በየጎጆው እየዞረ ሴት ድመቶችን ያንጫጫል ተባለ። ይህም እውነት ነበር። ወሬው ተወርቶ ብዙም ሳይቆይ አንድ ጎጆ ውስጥ ጥቋቁር ድመቶች ተወለዱ።

ደንግጠው ግልገሎቹን ዝንጀሮ ገደል ወስደው ጣሉዋቸው። እረኞችም እነዚያን ግልገሎች በድንጋይ ቀጥቅጠው ገደሏቸው።

መች በዚህ አበቃ!

እዚህም እዚያም ጥቋቁር ድመቶች ይወለዱ ጀመር። አንዳንዶቹ ያረገዙ ድመቶቻቸውን ወስደው ይጥሉ፣ ይገድሉ ገቡ። በዚያን አመት በሚወለዱት ጥቋቁር ድመቶች ምክንያት፣ 'እህሉ ላይ ቸነፈር ይወርዳል፣ እልቂት ይመጣል' እያሉ የሚተነብዩም ተሰሙ። 'የወቀዮ ቁጣ ነው። በየጎጆአችን ጥቁር





ድመት መታየቱም የክፉ ዘመን መምጣት ምልክት ነው' ሲሉ የተናገሩም ነበሩ። ብዙ ተባለ መቼም። አንዳንዶቹ ጥቁር ግልገሎችን ገደል ወስደው ሲጥሉ፣ እናት ድመቶች እያሸተቱ ገደል ወርደው ልጆቻቸውን ሲያጠቡ አይተናል የሚል የእረኞች ወሬም መጣ። የዝቋላ ሰው ይህን እየተቀባበለ አወራ። አንዳንድ ጠንቋዮች ደግሞ 'ቀዌሳ ድመት አይደለም፣ ባለውቃቢ ነው' ሲሉ ተናገሩ።

እንዲህ ከረምን።

ከዛፍ ላይ ዘሎ ካመለጠ ወዲህ ቀዌሳን በአካል ያየው ግን አልነበረም። እድሜውም ስለገፋ ሞቶ ይሆናል ብዬ ገምቼ ነበር። ሆኖም ቀዌ በህይወት ነበረ።

አንድ ምሽት እዚህች ቁርበት ላይ ጋደም እንዳልኩ ቀዌሳ መጥቶ እዚያች ደጃፏ ላይ ቁጭ አለ። እንደ ወታደር የፊት እግሮቹን ግጥምጥም አድርጎ! ከዚያ እኔን ያየኛል።

አህ! ቀዌሳ አርጅቶ ነበር።

ያ እሳት የላሰ ጆግና በመጨረሻ በእርጅና ተረታ። ተርቦ መምጣቱ ነበር። በአጥንቱ ነበር የሚራመድ። ገበሎ እንኳ መያዝ አቃተው ማለት ነው? እንዴት ልቤ እንደተነካ አታውቁም።

'ቀዌሳ! ግባ! እባክህ ግባ! ቤትህ ነው' አልኩት።

አይኖቹን ጨፈን ከፈት እያደረገ ጥቂት ቆየ።

ፈጥኜ ጓዳ ገባሁና ወተት በወጪት አድርጌ ሳስጠጋለት ወደ ሁዋላ ሸሸ። ራቅ ስልለት ግን ተመልሶ መጣና በእርጋታ ከወተቱ ጠጣ። አልጨረሰውም። ጥቂት ጠጥቶ አፉን በምላሱ ያፀዳዳ ያዘ፣

'ቀዌ! እባክህ ግባ! በድዬሃለሁ ይቅር በለኝ' አልኩት።

ድመት ሆኖ ሊሰማኝ አልቻለም። ምን ማድረግ ይቻላል? ከፊቱ መቆም የማልችል ሆኖ ተሰማኝ። ይህ ተራ ድመት ለሶስት አመታት ዝቋላን አንቀጥቅጦ ገዝቶአታል። ይህ እውነት ነው። አንድ ተራ ድመት የልቡን ሰርቶ መኖር ቻለ።

ይኸው አሁን ግን አርጅቶ እፊቴ ቆሞአል።

ቀዌ የሰጠሁትን ወተት ጠጥቶ እንኳ ሳያበቃ ፊቱን አዙሮ ጨለማ ውስጥ ገባ። በነጋታው ይመጣል ብዬ ጠብቄ ነበር። ሳይመጣ ቀረ። 'ሲርበው መምጣቱ አይቀር' ብዬ ጠበቅሁት። ሶስት ቀናት፣ አራት ቀናት አልመጣም። ለካስ ሞቶ

ኖሮአል። ዝንጀሮ ገደል ወድቆ እረኞች አገኙት።

ይህ ወሬ ሲሰማ ድፍን ዝቋላ ግልብጥ ብሎ ወደ ዝንጀሮ ገደል ወረደ። ቀዌሳን ሊያይ! አንድ አርጅቶ የሞተ ድመት ሊያይ…"

ጋሽ አበበ ከት ብለው ሳቁና ትረካቸውን አጠቃለሉ፤

"…እኔም ሄድኩ። እንደ ሁሉም ሰው ተጋፍቼ ተጠግቼ አየሁት። ቀዌ ድንጋይ ላይ ወድቆአል። በእርጅና ምክንያት ገደሉን ሊቆጣጠረው አቅቶት ከላይ ሳይፈጠፈጥ አልቀረም። ሴቶች የሚወዱት ጀግና የሞተ ይመስል በዚያን ሰሞን ወሬያቸው ሁሉ ስለ ቀዌሳ ሆነ። ቀዌ! ቀዌሶ! ቀዌሳ! ሲባል ተሰነበተ። እንደ ባላባት ተለቀሰለት፤ እንደ አርበኛ ተዘፈነለት።

ከዚያ ወዲህ እንግዲህ ዝቋላ ላይ ጥቁር ድመት መፍራት ቀረ። አሁን በየቤቱ ብትሄዱ ጥቁር ድመት ታያላችሁ። ጫካ ውስጥም ጥቋቁር ድመቶች አሉ። ሁሉም የቀዌሳ ልጆች ናቸው!

ለቀዌሳ ሃይል የሰጠው አምላክ ነው ብለው የሚያምኑም አሉ። እንዲህ ያለ የእምነት ነገር መቼም አንዳንዴ አስቸጋሪ ነው። 'ቀዌሳ ነኝ' የሚል አንድ ጠንቋይም ተነስቶ ነበር። ዘጠኝ ጥቋቁር ድመቶች ቤቱ ውስጥ እያርመሰመሰ ይጠነቁል ነበር። እንዲህ ነው እንግዲህ ታሪኩ። ርግጥ ነው፤ አሁን የቀዌሳ ልጆች ዝቋላ ላይ እንደ ድመት ሳይሆን እንደ ሰው ተከብረው እየኖሩ ነው…"

ጋሽ አበበ ይህን ሲያወጉን አብሮአቸው ጋደም ያለውን ጥቁር ድመት እያሻሹት ነበር…



\- 3 -

# ሁለቱ ዝሆኖች

አይን ያለው ይይ!
ልብ ያለው ያስተውል፤ ጆሮ ያለው ይስማ፤
ይህ ፍፁም ባድማ፤
ይህ ፍፁም ድቅድቅ ጨለማ፤
እሚበራ እንዳይመስላችሁ…
በናንተ የይስሙላ ቁራጭ ሻማ፤
መጋረጃው ያልተነሳ ተውኔት…
ያልተፈታ እንቆቅልሽ፤ አለውና ጨለማ፤
ነፋስ እሳተ ጎመራን ሲታቀፍ፤ ይችላልና ጠፍ ባድማ፤

(ግጥም - ደበበ ሰይፉ)

* * *

ናላ በጭጋግ ሲሸፈን - ልቦና በስጋት ሲባባ፤
መርሳት በራስ ቤት ሲሰራ - ፍርሃት ግንቡን ሲገነባ፤
ጭንቀት ጓዙን ሲያሳፍር - መጠርጠር ጫፉ ሲተባ፤
ላወቀ መንቃት ያኔ ነው - የህይወት ክረምት ሲገባ፤

(ግጥም - ጌትነት እንየው)

መለስ ዜናዊ እና ስዬ አብርሃ የተባሉት ሁለት ዝሆኖች በእድሜ እኩያሞች ናቸው። እንደ ጃንሆይ 'ስንወለድ ጀምሮ ስልጣን ይገባናል! ለመምራት እንጂ ለመመራት አልተፈጠርንም' ብለው የሚያምኑ የባላባት ልጆች!

ሁለቱም በትምህርታቸው ሰነፎች አልነበሩም። ሁለቱም ጠብ አፍቃሪ አምባጓረኞች ሲሆኑ፤ 'እብሪት' የተባለው ባለጭራ ኮከብ የጋራ እጣቸው ነው! ሁለቱም የህክምናን የሞያ ዘርፍ

መርጠው ማጥናት ጀምረው እንደነበር የቅድመ ትግል ድርሳናቸው ያወጋናል። ዳሩ ምን ያደርጋል? የሰው አካል በቢላ እየቀደዱ የህብረተሰብ ፈውስ ይሆናሉ ተብሎ ሲጠበቅ፣ በጠመንጃ ሃገር ወደ መቅደድ ገቡ። ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሲጠበቁ ደደቢት በረሃ ተገኙ። 'ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስን ይተካሉ' ተብለው ሲጠበቁ፣ በግልባጩ አስረውና አሰቃይተው ገደሏቸው።

በባህርይ ሁለቱም እብሪተኞች ይሁኑ እንጂ፣ የተለያየ አቅምና ተሰጥኦ ባለቤት ናቸው። የአነጋገር ዘይቤአቸው ሲመዘን መለስ ጭራው ጮሌ ነው። ስዬ እንደ ትንሹ ቡሽ ገገማ ነገር ነው። መለስ ዲፕሎማሲ ያውቃል፣ መተጣጠፍ ይችልበታል። 'አድዋ' እያልከው 'መቀሌ' ታገኘዋለህ። መያዣ መቆንጠጫ የሌለው ልምጭ ነው። የተቃወመህን አሳብ ተገልብጠ እንደራሱ ባንዴራ ሲያውለበልበው ግራ ትጋባለህ።

ስዬ በተቃራኒው ዘነዘና የዋጠ ይመስላል። ከመሬት ተነስቶ ቁጣው አይጣል! ሰዎችን ሁሉ ገና ድሮ ንቆ ጨርሿል። ከስዬ ጋር አብረህ ለመስራት ከወሰንክ ከዳሚ ለመሆን ጫንቃህን አመቻች።

*መለስ ቀጤማ ናት።*

ልክ እንደ አሪቲ ጉዝጓዝ ይሆንልሃል። ጊዜ ጠብቆ ግን መልሶ ጎዝጉዞ ይረግጥሃል። ዝሆን የረገጠው ሳር ያደርግሃል። መለስ ፖለቲካዊ ሰውነቱ ሲልቅ፣ ስዬ ወታደራዊ አቋሙ ያመዝናል። ውጊያ ላይ መለስ ዜናዊ ጀግና አይደለም። ርግጥ ነው፣ ጦር ሜዳ ላይ ጀግና መሆን ቀላል አይደለም። በነገራችን ላይ ሲቪላዊ ጀግንነትና የጦር ሜዳ ውሎ ለየቅል ናቸው። ጀግና አለመሆንም ወንጀል አይደለም። ማንም ሰው ቢሆንለት ጀግና ተዋጊ ቢሆን ይመርጣል። ስዬ አብርሃ በጦር ሜዳ ውሎው ብዙ አይታማም። "ልበ ድንጋይ" የሚሉት አይነት ነው ይላሉ። "ህወሃት አለቀለት፣ ተደመሰሰ" በተባሉ ውጊያዎች ላይ ስዬ ልብ የሚጠይቅ ፅኑ ርምጃ እየወሰደ ድርጅቱን ከሞት ያተረፈባቸው ጊዜያቶች ስለመኖራቸው የሚነገሩ ወጎች አሉ። ጦርነትን በጀግንነት ለድል ማብቃትና ሲቪል ህዝብን በዴሞክራሲያዊ መንገድ መምራት ግን ለየቅል ናቸው። ብዙውን ጊዜ ችግር የሚከተለውም የጦር ሜዳ ጀግኖች ሃገር ለመምራት በሚሞክሩበት ጊዜ ነው። ስዬ በመድፍ ተኩስ አይደነግጥም።





"ተሳስቼ ነበር" የምትለዋን ቃል ግን ከመድፍ በላይ ይፈራታል። ስዬ "ይቅርታ" የምትለውን ቃል ካንደበቱ ሊያወጣ አይቻለውም። ዶክተር ሃይሉ አርአያ እንደሚሉት ሲቪላዊ ጀግንነት የባህላችን አንዱ አካል ሊሆን አልቻለም። ስህተቱን ከማመንና የፈፀመውን ወንጀል ይፋ ከማድረግ አንፃር ስንመዝነው ስዬ ፈሪ ብቻ ሳይሆን ቦቅቧቃ ጭምር ነው።

አዲስ አበባ በተያዘች ማግስት ከስዬ ጋር ሃገረሰላም ዋሻ ውስጥ ተገናኝተን እንደነበር በቀዳሚው መፅሃፌ ተርኬ ነበር። ስዬ በረጅም ርቀት የመገናኛ ሬድዮ ከአዲስ አበባ ከፃድቃን ተከታታይ ሪፖርት እየተቀበለ መመሪያ ይሰጥ ነበር። ከጋዜጠኞቹ ጓደኞቼ ጋር እዚያች ቁጭ ባልኩባት ደቂቃ ስዬ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አመፅን በተመለከተ መረጃ ደረሰው። ስዬ መደረግ ያለበትን መመሪያ ሰጥቶ ሲያበቃ እዚያ ለነበርነው ጋዜጠኞች፣ (መዝሙር ፈንቴ፣ ሙሉጌታ ገሰሰ እና እኔ) እንዲህ አለን፣

"ለምነን ኢትዮጵያዊ አንሆንም። ካልፈለጉ ማይጨው ላይ በታንክ ዘግተን ቁጭ እንላለን!"

*(ስዬ ማይጨው እንጂ አሸንጌ አላለም። በዚያን ወቅት የትግራይ ክልል ድንበር ብለው የሚያስቡት እስከ ማይጨው ያለውን መሬት ብቻ ነበር።)*

በወቅቱ የስዬ ፍርሃት ወለል ብሎ ታይቶኝ ነበር። የጦር ሜዳውን ውጊያ በድል ያጠናቀቀው ጀግናው ስዬ ከሰላማዊው ትግል ፊት ሲርበተበት አየሁት። ከደርግ ግዙፍ ብረት ለበስ ጦር ፊት ግንባር ለግንባር የተዋጋው ስዬ መሳሪያ ካልታጠቁ ተማሪዎች ፊት ሲንቀጠቀጥና ወደ ማይጨው ስለማፈግፈግ ሲያወራ በጆሮዬ ሰማሁት።

ከዚህ አንፃር መለስ ጭልፊት ነው።

ጤፍ በሚቆላው ምላሱ የነደደውን ያበርደዋል። ያም ሆኖ መለስ ሲቪላዊ ጀግና አይደለም። የጦር ጀግንነቱም አልተሳካለት። የጥሎ ማለፍና የጠልፎ መጣል ችሎታዎቹን ማሳደግ ግን ችሎአል።

ስዬና መለስ የሚያደርጉት ግላዊ የስልጣን ሽኩቻ "ቶም ኤንድ ጄሪ" የተባለውን የህፃናት ፊልም ያስታውሰኛል። መለስ ብልጥ አይጥ ነው። ስዬ ጅል ድመት። አይጧ እያንገላታች ትጫወትበታለች። ድመቱ አይጧን ከያዛት እንደሚቀረጣጥፋት

ግልፅ ነው። ክፉቱ ግን መቼም ቢሆን ሊይዛት አይችልም።

ቶገራው ይቆይልኝና ወደ ቁምነገሩ ልመለስ...

አንድ ግልፅ ነገር አለ።

በ"ኢትዮጵያዊነት" አጀንዳ ላይ መለስና ስዬ የአንድ ድምቡሎ ሁለት ገፅታ ናቸው። ሁለቱም የኢትዮጵያዊነትን ሃገራዊ ስሜት ከደማቸው ውስጥ አስወግደው ራሳቸውን ወደ "ንፁህ ትግራዋይነት" ለውጠዋል። 'ስዬ ታስሮ ከተፈታ በሁዋላ ራሱን ኢትዮጵያዊ ማድረግ ችሎአል' ብለው የሚከራከሩ አሉ።

እኔ ይህን ለመቀበል እቸገራለሁ።

መቀበል የተቸገርኩት የማውቀው ነገር ስላለ ነው። አትዮጵያ የተባለችውን እድለቢስ ሃገር ከመምራት አንፃር መለስና ስዬ አንድ መሰረታዊ የሆነ ልዩነት አላቸው።

"የህወሃት ቡድን በኢትዮጵያ ስልጣን ላይ ነግሶ እንዴት ለረጅም ጊዜ ሊቆይ ይችላል?" ለሚለው ጥያቄ የሚሰጡት ምላሽ ላይ በእጅጉ ይለያያሉ።

ይህ ልዩነታቸው በህዋሃት ካድሬዎችና በከፊል ደግሞ በእህት ድርጅቶች ካድሬዎች በግልፅ ይታወቃል። በተቃዋሚዎችና በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ ግን ስለዚህ ልዩነታቸው በግልፅ የሚታወቅ አይመስለኝም። በዚህ ዘመን የፖለቲካ የሃይል አሰላለፍ ውስጥ መለስና ስዬ ወደ ቁንጮው ወጥተው ይህን መከራው የተራዘመ ህዝብ አክሮባት እየሰሩበት ነው ብዬ ስለማምን፣ በዚህ ትረካ የኔን የግል እይታ በጨረፍታ አቀርበዋለሁ።

* * *

የስዬ አብርሃና የመለስ ዜናዊ ሽኩቻ መቼና የት እንደተጀመረ በትክክል አላውቅም። የሁለቱ ዝሆኖች መጠላለፍና ሽኩቻ፣ "ደቂ አድዋ" እና "ደቂ ተምቤን" አይነት መልክ ይዞ ይፋ የሆነው ግን ስዬ የመከላከያ ሚኒስትር በነበረበት በ1985 መጀመሪያ ግድም ነበር።

በህወሃት ትግል የመጀመሪያዎቹ ዘመናት፣ "ህንፍሽፍሽ" በሚል መጠሪያ የሚታወቅ የመከፋፈል ችግር ተከስቶ የነበር መሆኑ ግን፣ ችግሩ ስር ሰዶ የቆየ ስለመሆኑ ጠቋሚ ይመስላል። በ"ህንፍሽፍሽ" ዙሪያ በተለያዩ ጊዜያት ከጥቂት በላይ ተፅፎአል። እዚህ አልደግመውም። ባጭሩ ግን ህንፍሽፍሽ ራሳቸውን፣





"አሽአ" ብለው በሚጠሩና "ደቂ አሉላ" በተባሉት መካከል የተፈጠረ የስልጣን ሽሚያ ነበር። "አሽአ" ማለት አድዋ፣ ሽሬ፣ አክሱም፣ ማለት ሲሆን፣ "ደቂ አሉላ" ደግሞ የተምቤን ተወላጆች ናቸው። የ"ደቂ አሉላ" ቡድን፣ "ስልጣን ሙሉ በሙሉ በ'አሽአ' ተያዘ" የሚል ቅሬታ ነበረው። ይህ የወቅቱ የስልጣን ረሃብና ሽኩቻ ህይወት እስከመጥፋት ያደረሰ ቢሆንም፣ በዚያን ጊዜ ሊያፍኑት አሊያም ሊያቀዛቅዙት ችለው ነበር። ሆኖም ደርግ ከወደቀ በሁዋላ ተዳፍኖ የቆየው የሁለቱ ጎራዎች ቅሬታ ማንሰራራቱ አልቀረም።

መለስ ዜናዊ የሃገሪቱን ስልጣን እንደተረከበ የቤተመንግስቱን የውስጥ እና ዙሪያ ጥበቃ በአድዋ ተወላጆች ሞላው። ይህ መነሻ ተዳፍኖ የቆየውን ቅሬታ ቀሰቀሰውና በ1985 አጋማሽ ላይ በስዬ አብርሃ ዙሪያ የተሰባሰቡ ደቂ አሉላዎች፣ 'መፈንቅለ መንግስት ሊሞክሩ አስበዋል' በሚል ለሁለተኛ ጊዜ ተመቱ። በተጣደፈ ሁኔታም ስዬ አብርሃ ከመከላከያ ሚኒስትርነት ተነስቶ በቅጣት ወደ ትግራይ ተላከ።

ስዬ በርግጥ፣ "ደቂ አሉላ" በሚል ህቡእ መጠሪያ የተምቤን ተወላጆች እንዲሰባሰቡ አድርጎ ነበርን? ይህ ጥያቄ በ1985 በተደረገው የመከላከያ ግምገማ ላይ ተነስቶ ነበር። ጉዳዩ ይበልጥ ከመጮሁ በፊትም እንዲታፈን ተደረገ። ግምገማው የላይኛውን አመራር ሳይነካ፣ ስም ሳይጠቅስ በታችኛው አባል ደረጃ ብቻ እንዲታይ ተወሰነ። 'የላይኛው አመራር ከችግሩ ነፃ መሆኑ በራሱ መድረክ ታይቶ ተረጋግጦአል' በሚል 'ሾላ በድፍኑ' ተብሎ ታለፈ። ታችኛው ካድሬም 'ስልጣን ፈላጊነት' የተሰኘ የመገምገሚያ ነጥብ ተሰጠውና በዚያ ታጥሮ ራሱን እንዲገመግም ታዘዘ። አጀንዳውም ለሁለተኛ ጊዜ ታፈነ።

ስዬ አብርሃ ከመንግስታዊ ስልጣኑ የመነሳቱና ወደ ትግራይ የመላኩ ዜና ግን ምስጢሩን በከፊል ነፋስ እንዲገባበት አደረገው።

በወቅቱ ይህን ጉዳይ አስመልክቶ ለሚስጢሩ የቀረበ መረጃ በሚዲያ ፍንጭ የሰጡን ብቸኛው ሰው ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ነበሩ። ስዬ አብርሃ ከኤርትራ ጋር በተያያዘ አጀንዳ ከመለስ ጋር በፈጠረው ልዩነት ስልጣኑን ተነጥቆ ወደ መቀሌ በቅጣት መዛወሩን ገለፁልን። በወያኔ ጓዳ ዙሪያ ለነበርነው የፕሮፌሰሩ መረጃ አዲስ ባይሆንም ጉዳዩን አንስቶ

ለመወያየት ግን በር ከፍቶልን ነበር።

እኔ በነጋታው ስዬ ዘንድ ወደ መቀሌ ደውዬ አገኘሁትና ፕሮፌሰር መስፍን የፃፉትን በአጭሩ አነበብኩለት።

አንብቤ ሳበቃ፣

“ምን ያውቃልና ነው የሚለፈልፈው?” አለ በስሜት።

እኔም ስራዬን መስራት ያመቸኝ ዘንድ ይችኑ የስዬን ቁጣ ማራገቤ አልቀረም። ዋና ፍላጎቴ ስዬ ቃለመጠይቅ እንዲሰጠኝ ብቻ ነበር። እናም ፈጠን ብዬ፣

“የዛሬው የፒያሳ ወሬ ስላንተ ሆኖአል” አልኩት። አያያዝኩና እንዲህ አከልኩ፣ “ቃለመጠይቅ ብትሰጠኝ ይሻላል። ባይሆን ጉዳዩን በእግረመንገድ እናነሳዋለን”

በዚህ ተስማምተን ስዬ ወደ አዲሳባ እንደመጣ ለእፎይታ መፅሄት ሰፊ ቃለመጠይቅ ሰጠኝና የሽፋን ዘገባ አድርጌ አተምኩት። በውይይታችን ወቅት “የማይታተም” በሚል ‘በህወሃት አመራር ውስጥ የመከፋፈል አደጋ ተከስቶ ነበር’ የሚል ወሬ መኖሩን ጠቆም አድርጌ ነበር።

ስዬ ባጭሩ፣ “ውሸት ነው” ስል አስተባበለ።

በወቅቱ ስዬን የማላምንበት ምክንያት አልነበረም። እና ወሬው ውሸት የመሆን እድል ሊኖረው እንደሚችል ግምት ወስጄ ወደ ቀጣይ ስራዬ አመራሁ። ወሬው ውሸት አለመሆኑ ግን ብዙም ሳይቆይ ይፋ ሆነ። የሁለቱ ዝሆኖች ሽኩቻ በአይን መታየት ጀመረ።

* * *

ሁዋላ “እነ ተወልደ” ተብለው የታወቁት የአመራር አባላት በወቅቱ የስዬን ከመከላከያ መነሳት የደገፉበት የራሳቸው በቂ ምክንያት ነበራቸው። ይህም የስዬ ደጋፊዎች “አሸአ” ብለው የሚጠሩትን ቡድን የመቃወም ዝንባሌ ማሳየታቸው ነበር። ስዬ በቀጥታ ህልዉናቸዉ ላይ መጥቶባቸዉ ነበር። በመሆኑም ስዬ ባለጠመንጃዎችን ከሚያዝበት አደገኛ ወንበር ተነስቶ ትግራይ ላይ እየተጠበቀ እንዲቆይ መለስ ያቀረበውን ሃሳብ ባንድ ድምፅ አፀደቁለት። እንደታቀደውም ስዬ በነአርከበ ኡቅባይና ስብሃት ነጋ ተከቦ፣ እንደ ቆሰለ አውሬ ሲጠበቅ ቆየ። የስዬ አብርሃ ወንድሞችና ዘመድ አዝማድ ያለሃፍረት ሃብት ወደ ማጋበሱ ሲገቡም እነ መለስ ያለ እንቅፋት ለቀዋቸው ቆዩ። ስዬ





በባህርይው ተናካሽ ተፈጥሮ አለው። አመለኛን ወይፈን ጨው እያላስክ አንገቱ ላይ ገመድ እንደምታስርበት ሁሉ፣ ስዬ በዚህ ዘዴ ወደ ሙስናው ሃይቅ ገብቶ እንዲዋኝ መንገዱን ሁሉ ከፊት ሲጠርጉለትና ሲያመቻቹለት ቆይተው ነበር። ስዬ ውሎና አክራሞቱ ትግራይ በመሆኑም “መለስን ሊተናኮል አይችልም” ተብሎ ታስቦ ነበር።

ተገላቢጦሽ ሆነ!

ስዬ አብርሃ መቀሌ ከገባበት እለት ጀምሮ እንደ ትግሉ ጊዜ አንገቱ ላይ ክሹክ መጠቅለሉን ሆን ብሎ ቀጠለበት። ከኤርትራ ጋር በድንበርና በጉምሩክ ነክ ጉዳይ መተናኮል አበዛ። ይህም መለስን የሚረብሸው ሆኖ ተገኘ። ወደ ኤርትራ የሚያልፉ ኤርትራውያን መንገደኞችን እያስፈተሸ ግማሽ ኪሎ በርበሬ መውረስ በመጀመሩ መለስ ወደ ስዬ ደውሎ፣

“የፖለቲካ ዝምድናውን ወደ በርበሬና ሽሮ ደረጃ እያወረዳችሁት ነው” ብሎ ስለማለቱ የአንድ ሰሞን የሰፈራችን ወሬ ለመሆን በቃ።

የስዬና የመለስ አለመጣጣምም በተለያየ ቅርፅና ይዘት እዚህም እዚያም ይሰማ ቀጠለ። ስዬ መለስን ከኤርትራ ጋር ሚዛናዊ ያልሆነ ግንኙነት በመፈፀም ሲያማው፣ መለስ ስዬን በሙስና ያጠቋቁረው ገባ። መዘላለፋቸው በረታ። መለስ በአንድ አጋጣሚ፣ “ክሹክ አንገት ላይ መጠቅለል የጦር መሃንዲስ መሆን አይደለም” ብሎ ስዬ ላይ ሲያሾሟጥጥ፤ ስዬ በበኩሉ የመለስን ባለ ሰባት ሺህ ብር ሱፍ ልብሶች እያነሳሳ በጠረባ ያደባየው ገባ። የሁለቱ ዝሆኖች መዘላለፍ አያሌ መልኮች ነበሩት። ስዬ ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የገዢነት ትውልድ እንዳለው ራሱን አሳምኖ ሲያበቃ፤ መለስ ዜናዊን “የባንዳ ልጅ” ይለዋል። መለስ በበኩሉ፣ “ቀድሞ የታገለ ሳይሆን፣ ቀድሞ አላማችንን የጨበጠ” የምትል ባንዴራ በማውለብለብ የአብዛኛውን የህወሃት አባል ቀልብ ተቆጣጠረ።

ይህ በእንዲህ እንዳለም የኢትዮ-ኤርትራ የድንበር ግጭት ፈነዳ። ይህ ክስተት ለስዬ አብርሃ “ትንሳኤ” እንደሆነለት ብዙዎች ይስማማሉ። ስዬ የሴት ልጁ ሰርግ እንደደረሰበት አባወራ ለታላቅ የጦርነት ድግስ ዝግጅቱን የጀመረው የዜናውን ይፋ መሆን ተከትሎ ነበር። መለስ ብዙ ጊዜ፣

“ጦርነቱ የተካሄደው ከፍላጎቴ ውጭ ነው” ሲል

የሚገልፀው በቀጥታ ስዬን ይመለከታል።

እንደ ሃገር መሪነቱ መለስ በዚህ የጦርነት ዋዜማ ፈታኝና ያልጠበቀው አጣብቂኝ ውስጥ ለመግባት ተገዶአል። ስዬ ለጦርነቱ ባጭር ታጥቆ መነሳቱ፣ የጦርነቱ መካሄድ የሃይል ሚዛኑን አስጠብቆ ለመጓዝ ብቸኛው አማራጭ መስሎ ስለታየው ነበር።

ሁለቱ ዝሆኖች በኤርትራ ላይ ያላቸው አመለካከት ግልፅ ነበር። ስዬ ሻእቢያን እና የኤርትራን ህዝብ በአንድ ላይ ጨፍልቆ "የህወሃት ጠላት" ሲል ፈርጆአቸዋል። ስዬ የኤርትራን ህዝብ በጠላትነት የሚመለከተው ከዚያው ከተለመደው፣ "ይንቁናል" ከሚለው ዘፈን ተነስቶ ነበር።

መለስ በአንፃሩ ሻእቢያን እና የኤርትራን ህዝብ ለያይቶ የማየት ዝንባሌ ነበረው። የኤርትራ ነፃነት በታወጀበት እለት አስመራ ተገኝቶ ያደረገው ንግግር ይህንኑ ይጠቁማል፣ እንዲህ ነበር ያለው፣

"…ለረጅም ዘመናት ከቅኝ አገዛዝ ነፃ ለመውጣት ያደረጋችሁት ትግል ተሳክቶ ለዚህ በመብቃታችሁ እንኳን ደስ ያላችሁ። አንድ ልገልፅላችሁ የምፈልገው ነገር አለ። በናንተ ጀርባ ላይ ያለው ቁስልና ጠባሳ በኛም ጀርባ ላይ አለ። ይሁን እንጂ ቁስሉን በማከክ ያለፈውን ማስታወስ የለባችሁም። ለምን ቢባል የሚያስከትለው ችግር አለና ነው። ቁስሉን መርሳት ደግሞ የለባችሁም። ለምን ቢባል ልንማርበት ስለሚያስፈልግ ነው…"

መለስ ፍላጎቱ ግልፅ ያልሆነ፣ ስሜቱ የተደበቀ፣ የተምታታበት አመለካከት ይዞ ግራ ሲጋባ ስዬ ደግሞ "ይንቁናል" በሚለው ጥቁር ብርድልብስ ተጠቅልሎ የኤርትራ ህዝብ ላይ ቂም ቋጥሮ፣ የበቀል ዜማ እያዜመ ነበር።

የሁለቱ ሃገሮች ግጭት እንደተከሰተም ስዬ የውስጥ ህመሙን ለመፈወስ ይህን አጋጣሚ ሊጠቀምበት ወገቡን ባጭር ታጠቆ ተነሳ። መለስ ሻእቢያ እንዲወገድለት አጥብቆ ቢፈልግም፣ የኤርትራን ህዝብ እንደ ህዝብ ዘሩን የመደምሰስ ቂም በቀል ዝንባሌ አሳይቶ አያውቅም። ስዬ ህዝቡንም ሻእቢያንም የመጨፈላለቅ አይነት በቀል አርግዞ ነበር፡፤

ይህ የሁለቱ ዝሆኖች የአመለካከት ልዩነትና የስልጣን ሽኩቻ የሉአላዊነት መደፈርን ሽፋን አድርጎ በጦፈ ሁኔታ ተጋጋለ። ፖሊት ቢሮውን አልፎ እስከ ካድሬው ድረስ ተቀጣጠለ። እነ ስዬ በወቅቱ ኢትዮጵያ የአሰብን ወደብ እስከ መያዝ ልትደርስ እንደምትችል ለህዝቡ ተስፋ በመመገብ ሰፊ ድጋፍ ለመሸመት መቻላቸው ግልፅ ነበር።

ገብሩ አስራት በስዬ ሴራ ከተጠለፉት የመጀመሪያዎቹ ነበር። የትግራይ ካድሬዎችን ሰብስቦ፣

"ኤርትራውያን 'አንድ ድመት ለሃምሳ አይጥ'፣ 'አንድ ፍሊት ለሃምሳ ዝንብ' ይሉአችሁዋል" ሲል ሚዲያ ላይ ቀርቦ ቀሰቀሰ። የትግራይን ህዝብ በአይጥና በዝንብ መመሰሉ ግን የስዬና የገብሩ ንፁህ ፈጠራ ነበር። የትግራይ ህዝብ 'አይጥ እና ዝንብ' በሚሉት ስድቦች ተቆጥቶ ከኤርትራውያን ወንድሞቹ ጋር በደም እንዲታጠብ ፍላጎት ነበራቸው። 'ዝንብ' እና 'አይጥ' ወይም 'ድመት' እና 'ፍሊት' የሚሉ ቃላት ከኤርትራ ወገን ስለመነገራቸው ግን ማስረጃ አልነበረም። ማነው ይህን ያለው? መቼ? ለማን? ለነዚህ ተራ ጥያቄዎች ገብሩ አስራት መልስ አልነበረውም። የዚህ ዘረኛ ቅስቀሳ ግብ "የኤርትራን ንቀት መቀነስ" የሚል ነበር። በአንፃሩ "አማራን መናቅ" የሚለው የረጅም ጊዜ እቅዳቸው የተሳሳተ መነሻና የተሳሳተ መፍትሄ እንደመሆኑ አካባቢያችንን ወደ ከባድ ቀውስ ሊከት ይችላል የሚል ስጋት የሚፈጥር ነበር። በመሰረቱ፣ "አማራን መናቅ" የሚል ፍላጎት ጦርነትን ብቻ ነው ሊፈጥር የሚችል። "የኤርትራን ንቀት መቀነስ" የሚለው የወያኔ ሰዎች ውስጣዊ ህመምም ከቅዠት ያለፈ መሰረት አልነበረውም። ዞሮ ዞሮ ከኤርትራ ጋር የተደረገው ጦርነት ከሉአላዊነት መደፈር ባሻገር የግለሰቦችን የአእምሮ ችግር የሚያንፀባርቅ ነበር። ወደ መለስና ስዬ ጉዳይ ስንመጣ ደግሞ የሁለቱ ዝሆኖች ሽኩቻ፣ ግልፅ የጥሎ ማለፍ ትንቅንቅ ነበር።

በግልፅ ባልተነገረው የመለስና የስዬ ሽኩቻ የብዙዎች ህይወት ተቀጥፎአል። ሁለቱ ዝሆኖች የበላይነትን ለመጨበጥ ያካሄዱት ትንቅንቅ፣ "ሉአላዊነትን ማስከበር" የሚል ሽፋን ስለነበረው ጉዳዩን በግልፅ መቃወም የሚቻልበት እድል አልነበረም። የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት በሚካሄድበት ወቅት በቅርብ ርቀት የነበርነውና በተለይም ወሬ መልቀም ስራችን ለነበረው ጋዜጠኞች በተለያዩ አጋጣሚዎች የምንሰማቸው ምስጢሮች፣ ሂደቱን በመስመሮች መሃል መመርመር እንችል ዘንድ ብዙ አግዞናል።

በጦርነቱ ወቅት ስዬ አብርሃ አስፈላጊ ሰው ሆኖ ለመገኘት በቅቶአል። በርግጥም በስልጣን ላይ ከነበሩት የህወሃት አመራር አባላት ጋር ሲነፃፀር በወታደራዊ ሙያ ስዬ የተሻለ ብቃት ነበረው። በመሆኑም ከግጭቱ ጋር በተያያዘ ለተከሰቱ አዳዲስ ወታደራዊ ስራዎች ስዬ ወደ ላይኛዉ አመራር እለታዊ ስራ መሳቡ የግድ ሆነ። በመሆኑም መለስ ስዬን ማቆም ከማይችልበት አዲስ መድረክ ጋር ለመላተም ተገደደ። ስዬ አብርሃ የጦርነቱን መካሄድ ከመፃኢ እድሉ ጋር አቆራኝቶት "አዬሎሌ- የብርመስቀሌ" የተባለችውን ዜማ እያዜመ ወደ ቁማሩ ስተት ብሎ ገባ።

ወያኔ ወደ ጦርነቱ የገባዉ የተከፋፈሉ መሪዎችን ይዞ በመሆኑ ምክንያት በጦርነቱ አላስፈላጊ የሰው ሃይል ኪሳራ ለመቀበል ተገዶአል። ከመነሻው ስዬ ቢመለስ ደካማ ጎን ገብቶ ወቅታዊ ቅስቀሳ ማድረግ በመቻሉ ከፍተኛ ድጋፍ አገኘ። የስዬ መከራከሪያ የማያሻማ ነበር፣

"ሻእቢያ ድንበራችንን አልፎ ገብቶአል። ወረራ ፈፅሞብናል። ስለዚህ ሉአላዊነታችንን ማስከበር አለብን። ሻእቢያን ከድንበራችን ማስወጣት ብቻ ሳይሆን ደምስሰን ከምድረገፅ ልናጠፋው ይገባል። ሻእቢያን ነካክተን ልንተወው አንችልም። ከጀመርነው ልንጨርሰው ይገባል። አለበለዚያ ለዘልአለሙ ሰላም አናገኝም። ይህን ማድረግ ደገሞ እንችላለን!" የሚል ግልፅ መነሻና መድረሻ ያለው አቋም ይዞ ቀረበ።

መለስ በበኩሉ "የውጊያ አማራጮችን ብቻ ከማየት በድርድር የድንበር ውዝግቡን ማስወገድ ይቻላል" የሚል እምነቱን ለማራመድ ሞክሮ ሳይሳካለት ቀርቶአል። በግልፅ ከመለስ ጎን የቆመው ዶክተር ካሱ ይላላ ብቻ ነበር። ርግጥ ነው፣ ስብሃት ነጋና በረከት ስምኦንን የመሳሰሉ ጥቂት የአመራር አባላት ከመለስ ጀርባ ነበሩ። በውይይቱ ወቅት ግን ሚዛን አይተው ድምፃችውን ወደ ስዬ ጎራ ጨምረውታል።

"ጦርነቱ ቀርቶብን የሰላም ስምምነቱን እንቀበል" የሚለው የመለስ አሳብ ውድቅ ተደረገና በቀጥታ ወደ ጦርነቱ ተገባ።

ስዬ የሂሳብ ስሌቱን ያሳላው፣

"መለስ ጦርነት መካሄዱን በመቃወም እስከመጨረሻው ሊገፋበት ስለሚችል፣ ተቀባይነቱና የስልጣን ዘመኑ እዚሁ ላይ





ያበቃል" የሚል ነበር።

መለስ ግን 180 ዲግሪ በመጠማዘዝ የስዬ አሳብ አራማጅ ሆኖ ተገኘ። ስዬ የሚያራምደውን አሳብ ልክ እንደራሱ ኦርጅናል አሳብ ያስተጋባው ገባ። በቅርብ የነበርን በወቅቱ ቡና ላይ እንደተጨዋወትነው በመለስ ዜናዊ መገለባበጥ ምክንያት ስዬ አብርሃ እቅዶቹ ሁሉ ፈራርሰውበታል።

መለስ የራሱ ያልሆነውንና አጥብቆ የሚቃወመውን አሳብ እየዘለለ ገባበት። ዛሬ "ጦርነቱን ተቃውሜ ነበር" ቢልም በጦርነቱ ወቅት ግን ሙሉ ሃይሉን ወደ ዘመቻው አውሎ ነበር። ያላመነበትን እንዴት በዚያ ደረጃ ሊያስፈፅም እንደቻለ ሲጠየቅም ስለዴሞክራሲያዊ ማእከላዊነት ሊሰብከን ይሞክራል። ብዙውን ጊዜ አንድ የሃገር መሪ በወሳኝ ጉዳዮች ላይ የተከራከረባቸው ወይም ያቀረባቸው አሳቦች ሙሉ በሙሉ ወድቅ ከሆኑበት ስልጣኑን መልቀቅ ይመርጣል።

"በድምፅ ብልጫ የተሸነፈ የድርጅቱን ውሳኔ የማስፈፀም ግዴታ አለበት። የድርጅቱ ባህልም እንዲያ ነው' የሚለው ሙግት የኢህአዴግ ውስጣዊ አሰራር መገለጫ ሊሆንም አይችልም። የመለስን ተገለባባጭነትና ውስጣቸው የሚላወሰውን ሽኩቻ ብቻ ነው ሊጠቁም የሚችል።

ከላይና ከሩቅ ለሚያየው "የማታምንበትን አሳብ በድምፅ ተሸንፈህ ማስፈፀም የዴሞክራሲ አንዱ ገፅታ ነዉ" ለሚል መሰረታዊ ክርክር በር መከፈቱ አይቀርም።

ኢህአዴግ እንደ ድርጅትም ሆነ መለስ እንደ ግለሰብ ግን በታሪካቸው ለአሸናፊ ድምፅም ሆነ አሳብ ተገዢ ሆነው አያውቁም። ያልነበረና የሌለ ባህል በአንድ አዳር ሊከሰት አይችልም። የምርጫ 97 ልምድም ስላለን መለስ "ኢህአዴግ ለተባለዉ ፓርቲው ታዛዥና ተገዥ ነዉ" ብለን ለመቀለድ አይዳዳንም። "መለስ ባልተመቸው ጊዜ ራሱን ቀብሮ አደፈጠ" ልንል እንችላለን። በመሆኑም በጦርነቱ ወቅት ከስዬ ጋር የደፈጣ ድብብቆሽ ተጫወቱ እንጂ በአሳብ ብልጫ ተሸናነፉ ሊባል አይቻልም። በመሰረቱ ለህዝብ ድምፅ የማይገዛ ሸፍታ ግለሰብ፣ እንደ አሻንጉሊት ሲጫወትበት ለኖረ ፓርቲው ደንብና አሰራር ተገዢ ሊሆን ይችላል ተብሎ ሊታመን አይችልም።

ከኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ጋር በተያያዘ በኢህአዴግ አመራር ወስጥ የተከሰተው ግጭትና ሽኩቻ ለስልጣን ጥሎ

ማለፍ የተደረገ ግላዊ ጦርነት ነበር እያልኩ ነው። ስዬ አብርሃ መለስን ለመገልበጥ የድንበር ግጭቱን ወደ ከፍተኛ ጦርነት እንዲያድግ አድርጎታል። መለስ ደግሞ የሃይል ሚዛኑ ሲከዳው ስዬን ለመቋቋም የስዬን የጦርነት አዋጅ እንደራሱ አድርጎ ግንባር ቀደም ተሳታፊ ሆነ። ውጤቱም አሳዛኝና በይፋ ያልተነገረ ለመሆን በቃ።

ጦርነቱን የሚመራው ማእከል እዝ ሲቋቋም ስዬ አብርሃ የዚያ ማእከል ባልደረባ ይሆን ዘንድ መጠራቱ ግድ ነበር። አከራካሪ አልነበረም። መለስ የሃገራዊው ማዘዣ መሪ ሲሆን፣ ፖሊት ቢሮ አባላቱና ኤታማዦር ሹሙ በአባልነት ተካተዋል። በዚህ ወቅት "አሽአ" በሚለው ስውር ጃንጥላ ስር መለስን ደግፈው የነበሩት "እነ ተወልደ" በጦርነቱ ወቅት "ንፁህ ትግራዋይ" የሚል ስውር ባንዴራ ካስቀደመው የስዬ አቋም ሁዋላ መከተል ጀመሩ። እነ ተወልደ በዚህ ባንዴራ ስር የተሰለፉት በስሜት ነው የሚል እምነት የለም። በዚህ አጋጣሚ "ሻእቢያን ማንበርከክና ኤርትራን በእጅ አዙር ማስተዳደር" የሚለው የስዬ ቅስቀሳ ግን ለተቀበረ ስሜታቸው ፍቱን ማነቃቂያ ሆኖ ነበር። ስዬ በቂ ድጋፍ የሚያስገኝለትን አጀንዳ በትክክል መምዘዙ ይታመናል። ህልሙን ከግቡ ሊያደርሰው ስለመቻሉ ግን በቂ ግምገማና ጥናት አድርጎአል ማለት የሚቻል አልነበረም።

የመለስና የስዬ ሽኩቻ በጠፈ ሁኔታ ውስጥ ውስጡን ቢቀጥልም አንዱ ሌላውን ጥሎ ለማለፍ የሚያደርጉት ትግል ግን አማራውን ወይም ኦሮሞውን ወደ ስልጣን እስካላመጣ ድረስ ብቻ ነበር። ትግላቸውና ሽኩቻቸው እስከ ህይወት መጠፋፋት ሊዘልቅ የማይችልበት መነሻውም ይኸው ነው። የሁለቱ ዝሆኖች ሽኩቻ በከፋ መልኩ የተገለፀው በኢትዮ - ኤርትራ ጦርነት ላይ ሲሆን፣ ሁለቱ ዝሆኖች የአካል ጉዳት ባይደርስባቸውም ሳሩ አፈር ድሜ በልቶአል። በቀጣይ ምእራፋት በዝርዝር የምንቃኘው የፆረና ግንባር እልቂት ከሁለቱ ዝሆኖች ጋር ቁርኝት እንዳለው የሚያምኑ ጥቂት አይደሉም። ከጦርነቱ ማብቃት በሁዋላ በተደረገ ግምገማ ላይም ጉዳዩ ተነስቶ ውይይት እንደተደረገበት አስታውሳለሁ።

መለስ ስዬን አሸንፎ ለመውጣት ጦርነቱን የራሱ ጦርነት





አድርጎ፣ ጦርነቱን በድል ለመወጣት መስራት ከጀመረ በሁዋላ ትግሬ የሆኑ የሰራዊቱ አመራር አባላት ለሁለት ተከፈሉ።

የመለስ ደጋፊዎች ከሚባሉት ቀዳሚዎቹ ወዲ አሸብር፣ ሳሞራ የኑስና ዮሃንስ የተባሉት ጄኔራሎች ነበሩ። ሳሞራ በጦርነቱ ወቅት ከጨዋታ ውጭ ነበር። ተክለ አሸብር (ወዲ አሸብር) የፆረና ግንባር ላይ 20ኛ ሜካናይዝድ ክፍለ ጦርን ይዞ ነበር። ይህም ከወያኔ ክፍለ ጦሮች በብቃቱና በትጥቁ የተሻለ ነበር። በመሆኑም ወዲ አሸብር ጠንካራ የተባለውን ክፍለ ጦር ይዞ ነበርና ተሰሚነት ነበረው።

እዚህ አካባቢ አንድ አሰቃቂ ታሪክ ተፈፅሞአል።

ወዲ አሸብር ፆረና ግንባር ላይ ባደረገው ማጥቃት በስሩ ያለው አንድ ክፍለ ጦር ከ50 በላይ ብረት ለበስ ጋር ሙሉ በሙሉ ተደመሰሰበት። በዚህ ጊዜ ጄኔራል ፃድቃን ወዲ አሸብርን ጊዜያዊ ወታደራዊ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ አድርጎ በተፋጠነ ሁኔታ ሞት ሊያስፈርድበት ሞከረ። መለስ ዜናዊ የፃድቃንን ሙከራ አከሸፈና ወዲ አሸብርን ወደ ለንደን ለእረፍት ላከው።

*(ወዲ አሸብር አዲ ሃገራይ የተባለ ቦታ ለፍርድ በቀረበ ጊዜ ዳኞች ሆነው የተሰየሙት ጄኔራሎች፣ ሃይሌ ጥላሁን፣ ታደሰ ወረደ፣ አባዱላ ገመዳ እና አበባው ታደሰ ነበሩ። ብርሃነ ነጋሽ እና ሰአረ መኮንን ምስክሮች ሆነው በመቅረብ ወዲ አሸብር ላይ ሞት ይፈረድ ዘንድ ጥረት አድርገው ነበር። በ1993 መቀሌ ላይ በተደረገው ግምገማ ግን ጄኔራል ሰአረ፣ 'በውሸት እንድመሰክር ፃድቃን ግፊት አድርጎብኝ ነበር' ሲል ግለሂስ አውርዶአል።)*

የምስጢሩ ማፈትለክ እዚህ ላይ ነበር የሚጀምረው። የፆረና ውጊያ መሪ የነበረው ወዲ አሸብር የመለስ ደጋፊ ነበር። የጦርነቱን የዘመቻ እቅድ አውጥተው የሰጡት ደግሞ ስዬ አብርሃ እና ፃድቃን ናቸው። ወዲ አሸብር በእቅዱ መሰረት ወደ ፆረና ውጊያ ገባና ሰራዊቱ ሙሉ በሙሉ አለቀ። እዚህ ላይ ማነው ተጠያቂው?

የፆረናን አሰቃቂ እልቂት በተመለከተ በኢህአዴግ ከፍተኛ አመራር ደረጃ በተደረገ ግምገማ፣

"አንዱን ወንጀለኛ በማድረግ በሰው ደምና በሃገር ሃብት

የተጫወቱ ግለሰቦች አሉ" የሚል አስተያየት ተሰጥቶአል።

ይሄ ምን ማለት ነው?

ስዬ አብርሃ መለስ ዜናዊን ተጠያቂ ለማድረግ ሲል የፆረናን ግንባር ሆን ብሎ እንዲደመሰስ አደረገ? ከሆነስ ለምን ስዬ አብርሃ ይህን በማድረጉ ለፍርድ አልቀረበም?

ምንድነው ያልተነካካው ምስጢር?

'የውጊያ እቅዱን አስቀድሞ ለሻእቢያ ያቀበለ ሰው በመካከላችን አለ' እያሉ ይሆን? ከሆነ ያ ሰው ማነው?

ካልሆነስ በፆረና ውጊያ ያ ሁሉ የሰው ህይወትና ንብረት ለምን እንደወደመ በግልፅ ሳይቀመጥ ቀረ? ወዲ አሸብር ከተጠያቂነት እንዲያመልጥ ከተደረገ በሁዋላ እንዴት ነው በዚያው ፍጥነት ለእረፍት ወደ ለንደን የተላከው? መለስ ወዲ አሸብርን በዚያ ደረጃ የሚያባብለው ምን ለመደበቅ? ምን ለመሸፈን ይሆን?

የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ይህን በመሰለ ውጥንቅጡ በወጣ የግለሰቦች ሽኩታ ተሸፋፍኖ ተጠናቀቀ። በፕሮፓጋንዳው ክፍል ያለን ጋዜጠኞች በመሪዎቻችን የሚገለፅልንና በተግባር የምናየው እንደተደበላለቀ ጦርነቱ ተፈፀመና የአልጀርስ ስምምነት ተደረገ!

የጅምላ ሞት ለጊዜው ተገታ።

የመለስና የስዬ ሹኩቻ ግን መልኩን ቀይሮ ቀጠለ። የህወሃት ክፍፍል ተከሰተና እንደገና መለስ አሸንፎ ስዬ ወደ እስር ቤት ተላከ። በአገር ውስጥና በውጭ ሃገራትም "ደቂ አሉላ" የሚሉ ድምፆች በረከቱ። "ደቂ አሉላ" የሚል ጋዜጣ አገር ውስጥ ተከፈተና ብዙም ሳይዘልቅ ተዘጋ። "ደቂ አሉላ" የተባለ ድረገፅ በዳያስፖራ "ስዬ ይፈታ" ሲል ወተወተ። ትግራዋይ ከሚለው ዝቅ ሲል በዘር ሃረጋችን ለስዬና ለመለስ እንቀርባለን የሚሉት ጎራ ለይተው በድረገፅ መተጋተጉን ተያያዙት። እንደ ጆርጅ ኦርዌል የእንስሳ አብዮተኞች፣ የዋልታና የአይጋ ፎረም ድረገፆች "ስዬ መጥፎ! መለስ ጥሩ!" የሚል ባንዴራ ሲያውለበልቡ፤ የደቂ አሉላና የኢትዮ ሚዲያ ድረገፆች በበኩላቸው፣ "መለስ መጥፎ! ስዬ ጥሩ!" የተሰኘ ሙዚቃ አቀናበሩ። የሁለቱ ዝሆኖች ደጋፊዎች ሽኩቻም እስከ ምርጫ 97 በተጠናከረ ሁኔታ ለመቀጠል በቅቶአል።





ህወሃት ሲከፋፈል አመራር አባላቱ የትግራይ አባላቶቻቸውን ለማሳመን ወደ መቀሌ ተጉዘው ነበር። በዚያ ስብሰባ መለስና ስዬ ቦክስ ሊገጥሙ ጥቂት እስኪቀራቸው ተፋጠጡ። ዳሩ ገላገሏቸው። ስለዚህ፣ "ወዲ ሸርሙጣ!!" ተባባሉና ተለያዩ።

ከክፍፍሉ በሁዋላ ዘግይቶ እንደሰማነው መለስ ከመቀሌ ሲመለስ በጦር ጄት አየር ላይ እንዲመታ እቅድ ተይዞ ነበር። መለስን አየር ላይ እንዲመታ የተዘጋጀው ፓይለት ይልማ መርዳሳ የተባለ የSU27 አብራሪ እንደነበር በወቅቱ ተነግሮአል። ለኦሮሞው ፓይለት ሊገለፅለት የተዘጋጀው፣

"መለስን የያዘው አይሮፕላን ወሻእቢያ ስለተጠለፈ ይመታ!" የሚል ነበር ተባለ። "ዳቦ" በሚል ቅፅል ስም የሚታወቅ ትግሬ ፓይለት ደግሞ ወዲያውኑ አየር ላይ ይልማን እንዲመታ አዘጋጅተውት ነበር። ለዚህ የተዘጋጀው ምክንያት ደግሞ፣ "እነግ በይልማ መርዳሳ በኩል መለስን ገደለ። ስለዚህ ይልማ ይመታ" የሚል ነበር። ይህን ሁሉ "የግድያ ሴራ" ሃይሌ ጥላሁንና ክንፈ ገብረመድህን አከሸፉት ተብሎ የነመለስ ሰዎች ርስበራስ ሲሞገጋሱ ሰነበቱ። በየግብዣው ላይም 'ለማንም እንዳትነግሩ፣ ጥብቅ ምስጢር ነው' ከሚል ማስጠንቀቂያ ጋር ለኛ "ለታሪክ መዝጋቢዎች" ተተረከልን። በዚያኑ ሰሞን "ዳቦ" ኮብልሎ ካናዳ ሲገባ፣ ይልማ መርዳሳ ከመለስ የገንዘብ ሽልማትና ሹመት ተቀብሎአል።

*(ይህች ወሬ በወቅቱ አልጣመችኝም። የህንድ ፊልም ትመስላለች። የአየር ሃይል አዛዡን ጆቤን ከስልጣኑ በፍጥነት ለማስወገድ ምክንያት ለመፍጠር በጀማሪ ደራሲ የተፃፈች አጭር ልቦለድ ትመስላለች። በርግጥ ይህ እውነት ከነበረ ሃይሌ ወይም ጆቤ ተጨማሪ መረጃ ሊነግሩን ይችላሉ። መለስ ፖለቲከኛ ከሚሆን፣ የልብ አንጠልጣይ ልቦለድ ድርሰት ፀሃፊ ቢሆን ይበልጥ ያዋጣው ነበር።)*

አንድ እውነት ግን አውቄያለሁ።

መለስ ከመቀሌ ሲመለስ ቦሌ እየተጠበቀ አሮጌው አይሮፕላን ማረፊያ ነበር ያረፈው። እነ ስዬ በኮማንዶ ሊያሳፍኑት እንደሚችሉ ተጠርጥሮ ነበር። መለስ አሮጌው

አይሮፕላን ጣቢያ ሲያርፍ ጆቤ በቁም እስር ላይ ነበር። መለስን የተቀበሉትም አባዱላ፣ ባጫ ደበሌና ሃይሌ ጥላሁን ብቻ ነበሩ…

*(ህወሃት ለሁለት ሲሰነጠቅ ጆቤ 'ቢሮህን ለሃይሌ አስረክብ' ተባለ። የጆቤ ታናሽ ወንድም ጄት አብራሪ ነበር። ከአየር ሃይል ተባረረ። ሲባረር ነጎደ - ወደ አሜሪካ! የጆቤ እህት የፋና ሬዲዮ ሃላፊ ነበረች። 'መንገዱን ጨርቅ ያርግልሽ!' የሚል ደብዳቤ ደረሳት። የጆቤ እህት የአለምሰገድ ሚስት ናት። የአለምሰገድ ሚስት ቀደም ሲል የሳሞራ ሚስት ነበረች። የጆቤ ሚስት ደግሞ የሳሞራ ሚስትም ነበረች። የቀድሞዋ የአለምሰገድ ሚስትና የአሁኗ ሚስቱ ዘመድ ናቸው። የተቆላለፈ ከመሆኑ የተነሳ ለመረዳት እንኳ ያስቸግራል። ዝምድናው ፖለቲካው ላይ ተፅእኖ የማሳደር ችሎታ አለው። ጠለቅ ብሎ ለሚመረምረው ልዩነታቸው ከፖለቲካ አቋም ባሻገርም ነው። እነዚህ የቀድሞ አለቆቼ ሚስት የመለዋወጡን ባህል ከየት እንዳመጡት ለማወቅ ሞክሬ ሊሳካልኝ አልቻለም። ቀደም ሲል የምናውቀው ባለስልጣናት ስልጣን ሲቀያየሩ ብቻ ነበር።*

*ይህ የምነግራችሁ ሚስጥር እንዳይመስላችሁ። እኔ በተገኘሁበት ስብሰባ ላይ ስለዚህ ጉዳይ ለአለምሰገድ ጥያቄ ቀርቦለት ነበር።*

*አለቃችን እንዲህ ተጠየቀ፣*

*'አለምሰገድ! ሚስትህን መፍታት መብትህ ነው። ከፈታሃት በሁዋላ ግን የሚስትህን የቅርብ ዘመድ ማግባትህን ከስነምግባር አንፃር እንዴት ታየዋለህ?'*

*አለምሰገድ አጭር መልስ ሰጠ፣*

*'ስለ ወደድኳት አገባሁዋት'*

*ከፍተኛ ሳቅ አዳራሹን ነቀነቀው።*

*በስብሰባው ላይ ከ200 በላይ የህወሃት ካድሬዎች ተካፋይ ሆነው ነበር። በአለምሰገድ ምላሽ ከልባቸው ከሳቁት አንዱ እኔ ነበርኩ።)*

* * *

ድረገፆችን ሳነብ ብዙዎች ስዬ አብርሃን እንደተቃዋሚ ለመቀበል በቅድሚያ የህወሃት አመራር አባል ሳለ የፈፀማቸውን





ወንጀሎች ይናዘዝላቸው ዘንድ ሲጠይቁ ተገርሜያለሁ። ያስገረመኝ ጠያቂዎቹ ስዬ ከህወሃት አስተሳሰብ ወጥቶ ወደ ህዝባዊው የትግል ጎራ ተቀላቅሎአል ብለው በማመናቸው ነው። ይህን ምእራፍ የምቋጨውም መለስና ስዬ ኢትዮጵያን ከመምራት አንፃር ያላቸውን አመለካከት ግልፅ በማድረግ ነው።

በርግጥም ስዬና መለስ ኢትዮጵያን ከመምራት አንፃር አንድነትም ልዩነትም አላቸው።

የአመለካከት አንድነታቸው "አቅም እስከፈቀደ ድረስ ኢትዮጵያ በትግራይ አስተዳደር ስር መቆየት አለባት። አለበለዚያ ህወሃት የከፈለው መስዋእትነት ከንቱ ይቀራል" የሚለው ነው።

"የኢትዮጵያ ማእከላዊ ስልጣን ከእጃችን እንዳይወጣ ምን አይነት የአስተዳደር ብልሃትና ስልት መከተል አለብን?" በሚለው ጥያቄ ላይ ግን ከመነሻውም ልዩነት ነበራቸው።

ላለፉት 18 አመታት መለስና አብዛኞቹ አመራር አባላት ባመኑበት መንገድ ተጉዘዋል።

"ከቁጥጥራችን ውጭ ሊሄድ የማይችል ፌደራሊዝምና የምርጫ ሂደት ከተከልን ለረጅም ጊዜ ትግራይን ስልጣን ላይ ማቆየት ይቻላል" ይላሉ እነመለስ።

ስዬ ከመነሻውም ይህን ይቃወማል፣

"በዚህ ዘዴ ለረጅም ጊዜ መዝለቅ አንችልም" ባይ ነው። በአንፃሩ፣ "አማራው እስከዛሬ እንደተጠቀመበት 'ኢትዮጵያዊነት' የሚለውን በሽፋን ተጠቅመን ውስጥ ውስጡን ግን የትግራይ ተወላጆችን በሃብትና በእውቀት በማጠናከር፣ በኢትዮጵያዊነት ስር የትግራይን ብሄርተኛነት አጠናክሮ የትግራይ ተወላጆችን አቅምና ሃብት የሃገሪቱ መሰረት በማድረግ ለረጅም ጊዜ ልንዘልቅ እንችላለን" ሲል ይሟገታል። መለስ በገሃድ ፌዴራሊዝምን ማወጁንም "ለጥቃት የሚያጋልጥ ስልት" ይለዋል።

ይህ መሰረታዊ ልዩነታቸው በአብዛኛው የህወሃት ካድሬ የሚታወቅ ሲሆን፣ ለረጅም ጊዜ በዝግ ስብሰባ ውይይት ሲደረግበት ቆይቶአል። ይህ ልዩነታቸው ለስልጣን ከሚያደርጉት ሽኩቻ ባሻገር የሚንፀባረቅ ነው። ስዬ አብርሃን ለእስር ያበቃው ግን ይህ ልዩነታቸው ሳይሆን የስልጣን ሽኩቻቸው ነበር።

መለስ ስዬን በሙስና ሰበብ አሰረው። እናም ስዬ ያበጠ

እብሪቱ ተነፈሰ። መለስ የነደደ ቁጣው በረደ። ከዚያም እንደገና ወደ አላማዎቻቸው ተመለሱ።

ስዬና መለስ አሁን በስልጣን አይሻኮቱም።

የጋራ ጠላት አላቸው።

ይህን የጋራ ጠላታቸውን በጋራ መመከት ከቻሉ ብቻ ነው ከሁለት አንዳቸው ስልጣን ላይ መቆየት የሚችሉት። ይህን ሁለቱም መገንዘብ ይችላሉ። በወጣትነታቸው ጓደኛሞች ነበሩ። በሁለቱ ሽኩቻ ሳሩ መጐዳቱንም ይረዳሉ። አሁን ግን መድረኩ ተቀይሮአል። ሙሉ ጊዜያቸውንና ህይወታቸውን ሰውተው ያመጡትን ስልጣን በቀላሉ ማስረከብ እንደሌለባቸው ሁለቱም ያውቃሉ። "አፄ ዮሃንስ የሰሩትን ስህተት አንደግምም" ባዮች ናቸው። "ስልጣን አንድ ጊዜ ከእጃችን ከሾለከ ዳግም ለማግኘት መቶ አመታት ላይበቃንም ይችላል" ሲሉ ይሰጋሉ።

ይህን መሰል አመለካከቶቻቸውን በአደባባይ እንደማይገልፁትም ግልፅ ነው። ስዬ እና መለስ አማሮችና ኦሮሞዎች እንደበረቱባቸው አስተውለዋል። የኢትዮጵያዊነት መንፈስ እያሸነፈ መሄዱንም በገሃድ ተመልክተዋል። በዚህ ወቅትም መተባበር ብቻ እንደሚያዋጣቸው ያውቃሉ። ስዬ የታሰረው በስምምነት ነው ብዬ አላምንም። የተፈታው ግን በስምምነት ሊሆን እንደሚችል እጠረጥራለሁ። መድረኩ ይተባበሩ ዘንድ አስገድዶአቸው ሊሆን ይችላል።

ይህ መረጃ አይደለም። ትንተና ነው።

የህወሃት ሰዎች በአንድ መሰረታዊ ነጥብ ይስማማሉ። የትግራይ ተወላጆች መስዋእትነት የከፈሉበትን ስልጣን እንደዋዛ ለቀዳሚ ተቀናቃኞቻቸው፣ ማለትም ለአማራ ወይም ለኦሮሞ አሳልፈው መስጠት ከቶውንም አይሹም። ስለዚህ ሁለቱ ዝሆኖች በሰከነ ሁኔታ ድርድር ለማድረግ በቅተው ሊሆን ይችላል።

ድርድር አድርገው ከሆነ ነጥቦቹ ግልፅ ናቸው።

ስዬ አብርሃ የትግራይን የበላይነት ሊያስጠብቅለት የሚችለውን የራሱን ዘዴና መንገድ ይሞክራል። በዚህ ሙከራ ሁለት አማራጮችን ይዞ ይጓዛል።

የመጀመሪያውን ገልጬዋለሁ።

ሁለተኛው፣ ማለትም (Plan B) የህወሃት አመራር አባላትና ካድሬዎች ለፈፀሙት ወንጀል በማይጠየቁበት መልኩ





በኢትዮጵያዊነት ስር ያለ አደጋ መቆየት ይችሉ ዘንድ መጠባበቂያ ማረፊያ ይዘው ይቆያሉ።

መለስ በበኩሉ የአገዛዝ ስልጣኑን ለማቆየት ጥረቱን ይቀጥላል። አዳልጦት ስልጣኑ ቢያመልጠው ከስር የሚረከበው ስዬ ይሆናል። በዚህም አለ በዚያም የህወሃትን መሰረታዊ አቋሞችና ህልውና የሚያስቀጥለው ሃይል በስልጣን ላይ መቆየቱ እንደተረጋገጠ ይቆያል። እንዳልኩት ይህ የኔ ትንተና ነው። በቀጣይ መንገዱ ወዴት ይዞን እንደሚጓዝ እናየዋለን።

ከዚህ ባሻገር ህዝብ ምንጊዜም የዋህ ነው።

ይህ የፖለቲካ ጥልፍልፍም ለመገምት ከሚያስቸግር በላይ ድብቅ አጀንዳዎች ያሉት እንደሆነ አስባለሁ። በፖለቲካ መንገድ ላይ ህይወት ሊቀጠፍ ይችላል። አላማህን ለማስፈፀም ግን የአንድ ሰው ህይወት ቀርቶ የብዙሃን ህይወትም ቢሆን አሳሳቢ አይደለም።

ኒኮሎ ማኪያቬሊ ገና ድሮ መመሪያውን ፅፎታል። ማንኛውንም ህገወጥ ድርጊት ፈፅመህ አላማህን ተግባራዊ አድርግ...

## - 4 -

# አብዮታዊ ኦርቶዶክስ

የቀደመኝ ትውልድ - ባሳብ የሰከረ፣
በተራማጅ ባህል - አናቱ የዞረ፣
በኢቮልዩሽን ህግ - ጠበል እየጠጣ፣
ፈጣሪን ለመግጠም - ወደ ትግል ወጣ፣

(ግጥም - ሰብሃት ገብረእግዚአብሄር)

* * *

ለምን ሞተ ቢሉ…
ንገሩ ለሁሉ፣ ሳትደብቁ ከቶ…
ከዘመን ተኳርፎ፣
ከዘመን ተጣልቶ፣

(ግጥም - ደበበ ሰይፉ)

ዘግይቼ በመድረሴ ከመጨረሻው ረድፍ ላይ ለመቀመጥ ተገደድኩ። እስከ ጉሮሮው ጢም ብሎአል አዳራሹ። የመጨረሻው ረድፍ ላይ ግን ማንም አልነበረም። ከበርሄ በቀር። የበረሃ ስሙ ሲታከልበት፣ "በርሄ - ጎማ እግሩ" ተብሎ ይታወቃል።

አጠገቡ ሄጄ ተቀመጥኩ። ጊዜው 1989 ነበር።

በመጨባበጥ ብቻ ሰላምታ ተለዋወጥን።

ሶስት የኢህአዴግ የአመራር አባላት መድረኩ ላይ





ተቀምጠዋል። መካከሉ ላይ አብርሃ ሳንቲም ማይክራፎኑን ይዞ ፖለቲካውን እንደ ሞርታር ያምበለብለዋል! ከአብርሃ ሳንቲም ግራናቀኝ የመላእክት ክንፍ መስለው የተቀመጡትን በመልክ እንጂ በስም አላውቃቸውም። የብአዴንና የኦህዴድ ወኪሎች ሳይሆኑ አይቀሩም።

አስር ቀናት እንደሚፈጅ ፕሮግራም የተያዘለት ውይይት አጀንዳው አንድ ብቻ ነበር።

"አብዮታዊ ዴሞክራሲ - ከተጨባጭ ሁኔታዎች አንፃር"

ወደ በርሄ ዞወር አልኩ!

በቅርብ ባይሆንም እንተዋወቃለን። በሙያው መካኒክ ነው። ለነገሩ ስለ በርሄ ማን የማያውቅ አለ? በተለይ ዝነኛ የሆነው በአፈንጋጭነቱ ነበር። የህወሃት ስም 'ተሃህት' በነበረበት በነዚያ ዘመናት ነበር ትግሉን የተቀላቀለው። ተማሪ አልነበረም እንደ ሌሎቹ። ዲያቆንና ገበሬ ነበር ይላሉ። ሁለቱንም ስራዎች ለትግሉ ሲል ሰዋቸው። እና የአርነት ታጋይ ሆነ።

ስለ በርሄ አያሌ አስቂኝ ወጎች ይሰሙ ነበር። በርግጥ የሚነገሩት ሁሉ እውነተኛ ስለመሆናቸው ማረጋገጥ የሚሻ ያለ አይመስልም። እንደ ዋዛ ተነግረው፣ እንደዋዛ ያልፋሉ። እንደ አለቃ ገብረሃና ቀልዶች፣ እንደ ቆምጬአንባው ወጎች…

"ጐማ እግሩ" የተባለውን ቅፅል ስም ያገኘው ለስልጠና ኤርትራ በነበረባቸው በእነዚያ የመደጋገፍ ዘመናት እንደነበር ይነገራል። "መትረየስ ተሸክሞ የናቅፋን ተራሮች እንደ ወፍ በርሮባቸዋል" ይላሉ አብረውት በቀይ ኮከብ ዘመቻ የተካፈሉ። እናም የሻእቢያ ታጋዮች ነበሩ፣ "በርሄ! ጐማ እግሩ!" ሲሉ በአድናቆት የጠሩት። ሲገሰግስ እንደ መኪና ነበር አሉ። አይደክመውም። እነዚያ ዘመናት አሁን ሩቅ ናቸው - እንደ አክሱም ሃውልት። እንደ ወርሃ ሃምሌ ጨላልመዋል…

እነሆ! ወደ ስብሰባው አዳራሽ ዘግይቼ በመድረሴ ከበርሄ አጠገብ እቀመጥ ዘንድ አጋጣሚው ፈቀደ። በዚያን እለት የአክሱም ልጅ ከሆነው ታጋይ አጠገብ በመቀመጤ አንድ ሰው ለማወቅ በቃሁ።

ያ ሰው ይህ ትረካ ነው…

አብርሃ ሳንቲም ከፊቱ የተዘረጋውን አንድ ጥራዝ እየገለጠ፣ "አብዮታዊ ዴሞክራሲ" የተባለው መርህ ኢትዮጵያ ለተባለችው ሃገር ብቸኛ ፈውስ መሆኑን ያብራራል። አብርሃ

የሚያብራራው ፅሁፍ ከትግርኛ ወደ አማርኛ እንደተተረጐመ ቅጂውን አጊንቼ አንብቤው ነበር። አረፍተ ነገሮቹ ከመርዘማቸውም በላይ፣ ለመረዳት በሚያስቸግር ደረጃ ሃሳቦቹ የተደጋገሙና የተቆላለፉ ነበሩ። የፅሁፉን ይዘት ለመረዳት በጣም ነበር የተቸገርኩት። ፀሃፊው ደግሞ መለስ ዜናዊ ራሱ ነበር። ቢሆንም አንብቤ ጨረስኩት። ጥራዙን አጥፌ ካስቀመጥኩ በሁዋላ አእምሮዬ ውስጥ ምን እንደቀረ ለማወቅ የአንጎሌን ጓዳ በረበርኩት። አንዳችም ግልፅ መርህ ወይም ፅንሰ ሃሳብ አሊያም ፍልስፍና፣ ካልሆነም ሌላ ስም ሊሰጠው የሚችል ነገር ማግኘት አልቻልኩም።

ግን ለምን?

ሁለት አማራጭ ምክንያቶች አንጎሌ ውስጥ ነበሩ።

የመጀመሪያው "ፀሃፊው ማለት የፈለገውን በቀላል መንገድ ማስረዳት አልቻለም"

ሁለተኛው፣ "ፀሃፊው እያጭበረበረ ነው"

ከሁለቱ አማራጮች አንዱን መያዝ ነበረብኝ።

አለቆቼ "አብዮታዊ ዴሞክራሲ" የተባለውን መርህ፣ ከተጨባጭ ሁኔታው ጋር አዛምደው ለሃገራችን በሽታ ፈውስ መሆኑን ሊያሳምኑኝ ካልቻሉ፣ የነሱ ችግር ነው ብዬ ባጭሩ ለጉዳዩ መቋጫ አበጀሁለት።

የሆነው ሆኖ ወደ ውይይቱ አዳራሽ የገባሁት ይህንኑ የመሰላቸት ባርኔጣ ደፍቼ ነበር። የውይይቱ መሪ አብርሃ ሳንቲም መሆኑን ሳውቅ ደግሞ ይበልጥ ተስፋ ቆረጥሁ።

አብርሃ ሳንቲም ቦዘኔ ድመት ናት።

ከአእምሮዋ እፍልቃ፣ አሊያም ግራና ቀኝ አገናዝባ ማስረዳትም ሆነ መረዳት አትችልም። ወደ አለቆች ስትሄድ ለመቀበልና ለማመን ተዘጋጅታ ትሄዳለች። ወደኛ ስትመጣ ለመስጠትና ለማሳመን ቆርጣ ትመጣለች። የተሰጣትን የቤት ስራ እንዳለች በማስፈፀም ችሎታዋ ብዙዎች ሲያደንቋት ሰምቻለሁ። በመሆኑም መጪዎቹ የማዳመጥ ቀናት በእጅጉ አሰልቺ እንደሚሆኑብኝ ከወዲሁ አምኜ ነበር።

*(አብርሃ ሳንቲም ፆታው ወንድ ቢሆንም ፊቱ እንደ አምስት ሳንቲም ትንሽ ስለሆነ ሁሉም 'አንቺ' እያለ በሴት ፆታ ይጠራታል። እሷም በዚህ ተቃውሞ የላትም።)*





በርሄ ሲጋራውን እየማገ ቆየና እንደዋዛ ጥያቄ ቢጤ ጣል አደረገ። በትግርኛ ቋንቋ ነበር የጠየቀኝ፣

"እንዲያው ወንድሜ፣ ይሄ ነገር ይገባሃል?"

"ምኑ?" ስል በአማርኛ መለስኩ።

እሱም በአማርኛ ቀጠለ፣

"ይሄ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚሉት?"

አነጋገሩ ስላስገረመኝ፣ በቅጡ አጤንኩትና፣

"ብዙም አልገባኝም" ስል መለስኩ።

በርሄ ፈገግ ሲል አየሁት። ቆየና አከለበት፣

"ከኔ ጋር የሚሰሩት መካኒኮች ግን ገብቶናል ነው የሚሉት። ረዳት መካኒኮቹ ሳይቀር ገብቶናል ይላሉ።"

መልስ ሳልሰጠው ጥቂት ዘገየሁና፣

"ገብቶአቸው ሊሆን ይችላል" አልኩ።

አያያዝኩናም ጠየቅሁት፣

"የቀረበውን ፅሁፍ አንብበኸዋል?"

"ስራ ቦታ አምጥተውት ጀመርኩትና ተውኩት..."

"ለምን ተውከው?"

"ስጀምረው ካልገባኝ እንዴት እጨርሰዋለሁ?"

ቆየት ብሎም እንዲህ ሲል አከለ፣

"አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚባለው ነገር ወደ ድርጅታችን ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ እየጠየቅሁ ነበር። የሚሰጡኝን መልስ ጆሮዬን ተክዬ፣ ቀልቤን ሰብስቤ አዳመጥሁ። ምንም ነገር ሊገባኝ ሳይችል ቀረ።

'ይሄ ነገር አልገባኝም!' ስላቸው፣

'አንተ ሊገባህ አይችልም። የተራማጅ አስተሳሰብን ተቀብለህ ከወቅቱ ጋር አዋህደህ ለመራመድ አትችልም' አሉኝ። ሊሆን ይችላል ብዬ ተውኩት..."

ሲጋራውን እየማገ ቀጠለ፣

"እኔ ዲያቆን ነበርኩ። አልተማርኩም። አክሱም ሃውልቱ ስር ነው የተወለድኩት። አንተ ጋዜጠኛ ነህ። እንዲያው ልጠይቅህና መካኒኮቹ ከነረዳቶቻቸው፣ 'አብዮታዊ ዴሞክራሲ ገብቶናል' እያሉ አንተ እንዴት 'አልገባኝም' ትላለህ?"

"አንተ ምኑ ነው ያልገባህ?" ስል መልሼ ጠየቅሁት።

"ቃሉ ራሱ አልገባኝም" አለ ርግጥ! አድርጎ። ድምፁ

በራስ የመተማመን ውስጣዊ ሃይል ነበረው። ቀጠለበት፣

“...አብዮታዊ ዴሞክራሲ ጠመንጃ ይሁን፣ ታቦት ይሁን፣ ምን ይሁን፣ ገና አልገባኝም። ‘ስላልገባኝና ሊገባኝም ስለማይችል ውይይቱ ላይ ባልሳተፍ ይሻላል’ ብዬ አመልክቼ አልተቀበሉኝም። ሌሎቹ መካኒኮች ሁሉ ‘ገብቶናል’ ይላሉ - ከነረዳቶቻቸው። አስረዱኝ ስላቸው የተፃፈውን መልሰው በቃላቸው ይደግሙታል። ቃላት እንኳ አያሳስቱም።”

ስለ በርሄ ሲነገሩ የነበሩ ወጐች ታወሱኝና ፈገግ አልኩ። እኒያ የሰማሁዋቸውን የሚያስታውሰው የአነጋገር ዘይቤውን ከራሱ አንደበት በመስማቴ ተዝናናሁ። ከግዙፍነቱ እና እንደ ወይራ የተጠመዘዘ ከሚመስሉት ክንዶቹ፣ በጠባሳዎች ከተሸላለመ ገፅታው ጋር ተዳምሮ፣ ለሚመለከተው የምድርን መከራ ሁሉ ለመሸከም የተፈጠረ ደራጎን አስመስሎታል።

አነጋገሩን ወደድኩት።

በራስ የመተማመን ኩራቱ ልብ ይሞላል። ፌሽካና ጡሩንባ፣ አሽቃባጭና ከተፎ በተጠራቀመበት የካድሬ ስብሰባ መሃል በርሄን ማግኘት በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ የብርሃን ጭላንጭል እንደማየት የሚቆጠር ነበር።

አካባቢው እንዳይረበሽ እየተጠነቀቅሁ ምላሽ ሰጠሁት፣

“እኔ አልገባኝም ያልኩህ የቀረበው ፅሁፍ፣ ‘አብዮታዊ ዴሞክራሲ እንደ ኢትዮጵያ ላለች ብዙ ብሄረሰቦችን ላቀፈች ሃገር ፈዋሽ መፍትሄ ነው’ ሲል ሊያብራራ የሞከረበትን መንገድ ነው። የሆነው ሆኖ ፅሁፉ ግልፅነት ይጐድለዋል...”

“አብዮታዊ ዴሞክራሲ” የተባለው ፅንሰ ሃሳብና ኢህአዴግ ሃገሪቱን የሚያስተዳድርበት “ፖሊሲ” ወይም “መርህ” ፍየልና ቅዝምዝም መሆናቸውን መለስ ዜናዊ ያውቃል። አሳምሮ ያውቃል። “የብሄረሰቦች መብትና እኩልነት” የሚባለው መሪ ቃል አፍአዊ እንደሆነም ማንም ይገነዘባል። በዚያ አዳራሽ ተሰብስበን የምናደርገው ውይይትም ፋይዳ ቢስ ስለመሆኑ ሁላችንም እናውቃለን። ከኛ መሃል ይህን የሚናገር ግን የለም።

በዚያች እለት በመላ ሃገሪቱ የኢህአዴግ ካድሬዎች ስብሰባ ተቀምጠው በዚህ ፅሁፍ ላይ እየተወያዩ ነበር። ምናልባት ግን የልቡን እየተናገረ ያለው ዲያቆኑ፣ “በርሄ ጐማ እግሩ” ብቻ ሳይሆን አይቀርም። እሱም ‘ጤነኛ አይደለም’ ተብሎ እንዲገለል ተደርጐ ነበር...





ከፊታችን የተቀመጡትን የስብሰባው እድምተኞች እየረበሽን እንዳይሆን ስለሰጋሁ ከበርሄ ጋር በተናጠል የጀመርኩት ውይይት ምቾት ሳይሰጠኝ ቀረ። እና ትኩረቴን ወደ ዋናው መድረክ አደረግሁ።

በርሄ ግን ሊለቀኝ አልቻለም፣

“ጋራዡ ውስጥ ስምንት ተበላሽተው የቆሙ መኪኖች አሉ። ‘እዚህ ቁጭ ብዬ የማይገባኝን ነገር ከማዳምጥ መኪኖቹን ብጠግን ይሻላል’ ብዬ በቃልም በፅሁፍም አመልክቼ አልተቀበሉኝም...”

ራሴን ላይ ታች ነቅንቄ ዝም አልኩ።

በርሄም ከኔ ጋር የጀመረውን ወግ አቋርጦ የመድረክ መሪውን ትንታኔ ሲያዳምጥ ቆየና መልሶ ወደኔ ዞረ፣

“ወደ ትግል ስትመጣ እኔ ነኝ ተቀብዬ ያሰለጠንኳት!” አለኝ በአገጩ ወደ መድረክ መሪው ወደ አብርሃ ሳንቲም እየጠቆመኝ፣ “...ደቃቃ ስለነበረች ‘ሳንቲም’ ብዬ ጠራሁዋት። ተመልከታት አሁን! የተሞላችውን ትተፋዋለች! ማታ ማታ ወዲ ዜናዊና ስብሃት ነጋ እንደ መኪና ባትሪ ሲሞሏት ያድራሉ። እዚህ መጥታ ደግሞ ትተፋዋለች! የተሞላችው እስኪያልቅ!”

ሳቄን አፈንኩት።

ሌላ አማራጭ አልነበረኝም።

በሶስተኛው የስብሰባ እለት ከበርሄ ጋር የጀመርነው ጓደኛነት ከፍ አለ። ይበልጥ ተግባባን። ተማመንን። በርሄ እንኳ ከመጀመሪያውም እንደልቡ ነው። ‘እኔ ነፃ መሆን ጀመርኩ’ ብል ይቀላል። እንደልቤ ያለስጋት አወጋው ጀመር። አሰልቺውን የውይይት ጊዜ ለመግደል በራሳችን ወጐች መጠመዱ የሚያዋጣን ነበር። የበርሄ አፈንጋጭነትና ግልፅነት ከሰማሁት በላይ ሆኖ ነበር ያገኘሁት። በአሉታዊ መልኩ የሚወሩበት ሃሜቶች መሰረት የሌላቸው ሊሆኑ እንደሚችሉ ለመረዳት ጊዜ አልፈጀብኝም።

እውቀትን ለመቀበል የሚችል አእምሮ እንደሌለው ነበር በዋናነት የሚነገርበት። ‘ወቅታዊ ሁኔታዎችን መገንዘብ የማይችል’ ሲሉም ይመርቁለታል። ‘ከመደቡ የተነቀለ ገበሬ!’ የሚል ኮፍያም ያጠልቁለታል። በርግጥ በርሄ በንግግሩ መሃል ሃይማኖታዊ ጥቅሶችን በግእዝ ቋንቋ ስለሚደባልቅ አሰልቺ ጠባያት አሉት። ያም ሆነ ይህ፣ ሁዋላ ቀርም ሆነ ገጠሬ፣ በርሄ

የራሱ የሆነ ሙሉ ሰው መሆኑን ለመረዳት ቻልኩ። በርሄ ከፋብሪካ የወጣ ዕቃ አልነበረም። ከኰካኰላዎች ተርታ ሊመደብም አይችልም።

በአራተኛው የስብሰባ እለት እንዲህ ሲል አወጋኝ፣

"ህወሃት ማለት ለኔ ህይወቴ ናት። ከቤተክህነት ጋር የነበረኝን ቁርኝት ግን ልተወው አልቻልኩም። በእግዚአብሄር አምናለሁ። የትግል ጓደኞቼ፣ 'ተቀላቅሎብሃል! ተምታቶብሃል!' ይሉኛል። በየግምገማው ብዙ ተደብድቤያለሁ። እውነታቸውን ሊሆን ይችላል። አየህ እኔ ወደ ትግሉ ስገባ ህወሃትን እንደ ፅዮን ታቦት ነበር የማምናት። 'ህወሃት ዘእንበለ ባእደ ኢነአምር!' እያልኩ እዘምር ነበር። ግእዝ ካላወቅህ ትርጉሙ ምን መሰለህ? 'ህወሃት ካንቺ በቀር ሌላ አናውቅም' ለማለት ነው። የእግዚአብሄርን ነበር በቀጥታ ለድርጅታችን የሰጠነው። ህዝቡም 'ወወፃእከ ለአድኅኖ ህዝብከ' እያለ ነበር መርቆ የላከን። እንደዚያ ነበር..."

ጥቂት በፀጥታ ከቆየ በሁዋላ፣

"የልቤን ልንገርህ?" አለ ገፅታው ሁሉ ንቁ ሆኖ "... 'ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ' ይልቅ 'አክሱም ፅዮን' ሲሉኝ ይበልጥ ደሜ ይሞቃል። እኛኰ የፃድቁ ዮሃንስ ልጆች ነን። በራስ መንገሻ አባት በስዩም ወይም በማርያም ፅዮን ነበር መሃላችን! ወዲ ዜናዊ ይህን አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከየት እንዳመጣው አይታወቅም። 'ወእምድምፀ ነጐድጓድከ ይደንግፁ ወወያናይ ወወዴሞክራሲ' እየተባለ ይኸው ስንት ዘመኑ? ደማችን ውስጥ ሊገባ ግን አልቻለም። በአይናችን የምናየው፣ በደመነፍስ የምንረዳው አንዳች ነገር የለም። ለመንፈስ አልሆነን ወይ ለስጋ..."

አያያዘና በአገጩ የመድረኩን መሪ እያመለከተኝ፣

"እያት ከአፏ እንዴት እንደምትተፋ!? ማታ ማታ አቦይ ስብሃትና ወዲ ዜናዊ በየተራ ይሞሏታል - እንደ መኪና ባትሪ!"

በነጋታው እቤቴ ምሳ ጋበዝኩት!

እየተመገብን ሳለ የሳንቲምን ስም ይቦጫጭቀው ቀጠለ፣

"አትወደኝም! መድረክ ካገኘሁ ምን እንደምናገር ታውቃለች። ስለዚህ እድል ትነፍገኛለች!"

አያያዘና ቀጠለ፣





"አብርሃ የኔን እውቀት ትንቃለች። እውቀት እንዴት ይናቃል? 'ጊዜያችንን በተረት ታባክናለህ' ብላ መድረክ ላይ በንዴት ተናገረች። 'መዝሙረ-ዳዊት' እንዴት ተረት ሊሆን ይችላል? 'ወይጉየዩ ፀላእቱ እምቅድመ ገፁ' የሚለውን ከምንጩ ጠቅሼ ስነግራት፣ ምን አለቺኝ መሰለህ? 'ውሃ ላይ የበቀለ ዛፍ ነህ! ስርህ ካፈር ጋር ካልተገናኘ ህይወት አይኖርህም' ብላ መድረክ ላይ ተናገረች..."

"እየበላህ!" አልኩት።

ጥቂት ጐራርሶ ግን ቀጠለ፣

"እስቲ ራስህ ታዘብ? ስብሰባ ከጀመርን ስንት ቀን ሆነ? አምስት ቀናት! ስለሃይማኖታችን አንዲት ደቂቃ እንኳ መች ተናገረች? ምንታርግ? ያልተሞላችውን ከየት አምጥታ ትትፋ?"

ተመግበን አብቅተን ነበር።

በርሄ የተናገራቸውን የግእዝ አረፍተነገሮች እንዳልረሳቸው ቁራጭ ወረቀት ላይ ላሰፍራቸው ሞከርኩ። ሁሉንም ማስታወስ ግን አልቻልኩም። በርሄ የጫጫርኩትን እንደዋዛ ተመለከተና እንዲህ ሲል ጠየቀኝ፣

"ግእዝ መማር ትፈልጋለህ እንዴ?"

"ጥሩ ነበር። ከዜሮ መጀመር ግን ይከብዳል" አልኩ።

በርሄ ግን በሞራል ገፋፋኝ፣

"አንተ ፍላጐት ካለህ በቀላሉ አስተምርሃለሁ"

የበርሄ የአማርኛ ቋንቋ ችሎታ የሚደነቅ ነበር። ሲያወጋኝ ግን ከትግርኛ ጋር እየቀላቀለ ያስኬደዋል። አልፎ አልፎ ደግሞ አሳቡን ሙሉ በሙሉ በአማርኛ መግለፅ ሲሳነው ትግርኛ ብቻ ይጠቀማል። ማለት የሚፈልገውን ግን በቀጥታ የመግለፅ ብቃት ነበረው።

ግእዝ ሊያስተምረኝ በሞራል ሲነሳሳ እንደማይሆን ላስረዳው ሞከርኩ። ቋንቋውን ለማስተማር የማስተማሪያ ዘዴ እንደሚያስፈልግ በመግለፅ ተቃወምኩት። በርሄ በጥሞና አዳምጦኝ ሲያበቃ፣

"በቀላል አባባሎች ጀምረን ከዚያ ወደ ከባዱ ልንገባ እንችላለን" አለ።

"እንዴት ማለት?"

"ምሳሌ ልስጥህ" ካለ በሁዋላ፣ "...እስኪ 'እንደ ምድረ በዳ አህያ ሆንኩ!' የሚለውን ወደ ግእዝ ለመተርጐም ሞክር?"

ሲል ፈተነኝ።

ይህን ስናወጋ የኔ ጨዋታ ቀልድ የቀላቀለ ነበር። በርሄ ግን እንኳን ሊቀልድ፣ ቀልድ ያዘለ ያነጋገር ዘይቤ ስለመኖሩ እንኳ ግንዛቤ ያለው አይመስልም። የሚናገረው ከልቡ ነበር። ግእዝን በቀላሉ ሊያስተምረኝ በማሰብ የመረጠው አረፍተነገር ቢያስገርመኝም እኔም በቁምነገር ምላሽ ሰጠሁት፣

"ይህን አረፍተነገር ወደ ግእዝ ለመተርጐም አልችልም። ስለ ግእዝ ቃላት አላውቅም። በዚህ መንገድም ማስተማር አይቻልም" አልኩ።

በቀላሉ ተስፋ አልቆረጠም።

አረፍተነገሬን ራሱ ተረጐመልኝ፣

"ወኰንኩ ከመ አድግ መረብ ዘገዳም"

ረጅም ሳቅም ሳቅሁ።

በትርጉሙ ውስጥ 'መረብ' የምትለው ቃል ማንን ወክላ ልትገባ እንደቻለች ግን እስከዛሬም ግልፅ አልሆነልኝም። ግእዝ ቃላቶቹን ሁሉ እንደ ከረሜላ በዘንቢል አጭቆ፣ ሰረገላ ላይ ጭኖ ወደ ሞት ሃገር ሲጓዝ በርሄን ረስቶት የሄደ መስሎ ተሰማኝ።

እንደገና በሌላ ዘዴ ሊያስተምረኝ እንዲህ አለ፣

"ወደ ግእዝ መተርጎም ሊከብድህ ይችላል። ከግእዝ ወደ አማርኛ ግን ቀላል ነው" ካለ በሁዋላ፣ "...ለምሳሌ 'ወኩሉ ከመ ልብስ ይበሊ' የሚለውን እስኪ ሞክር?" አለኝ።

ማሰብም አላስፈለገኝ፣

"ይሄ ቀላል ነው" አልኩት።

"እስኪ ተርጉመው?"

"ሁሉም እንደ ልብስ ያረጃል"

በርሄ በጣም ተደሰተ።

"አየህ!? ግእዝ ለመድክ። አበቃ! አንድ ስህተት እንኳ የለብህም። ከንግዲህ ስንገናኝ በግእዝ ማውራት እንችላለን"

በበርሄ ሁኔታና አነጋገር በጣም ተዝናናሁ።

ቡና ለመጠጣት አንድ ካፍቴሪያ ውስጥ ገብተን ተቀመጥን። የተስያቱ የስብሰባ ሰአት ዘጠኝ ሰአት ላይ የሚጀምር በመሆኑ ረጅም የጊዜ ክፍተት ነበረን።

በርሄ ቡናውን አጣጣመና ሲጋራ ለኰሰ። ማግ ማግ አድርጐ ሲያበቃም፣ እንዲህ አለኝ፣





"ከህወሃት አመራር አባላት መካከል በጣም የማከብረው አቦይ ስብሃትን ነው። እሱ ሃይማኖታችንን ያውቃል..."

"መለስስ?" ስል ጠየቅሁት።

"አልወደውም"

"ምነው?"

"ምላሱ ነፋስ የበዛበት ባንዴራ ነው። ሲናገር ብቻ ነው የምትሰማው። ጆሮ ያለው እንኳ አይመስለኝም"

"አብራችሁ ሰርታችሁ ታውቃላችሁ?"

"አናውቅም"

እንደገና በተቀሰቀሰ የስሜት አነጋገር ያብራራ ጀመር፣

"መትረየስ በለው ሲናገር! እሳት የሆነውን ሰብስቦ ውሃ ያደርገዋል። በረዶ የሆነውን ደግሞ ነበልባል ያደርገዋል። ሰራዊቱን እንደፈለገ! ወአልቦ ህልቁ ለቃሎ እንዲሉ..."

ያጋመሰውን ሲጋራ መተርኰሻው ላይ ደፈጠጠው።

"ጉና ላይ ስናምፅ ትግሉ ውስጥ ነበርክ?" ሲል ጠየቀኝ።

"አልነበርኩም! ወሬውን ግን ሰምቻለሁ..."

"ካመፁትም ካሳመፁትም ውስጥ ነበርኩበት። 'ትግራይን ነፃ ካወጣን በሁዋላ ለአማራው አገር ምናገባንና ነው የምንሞተው?' ብለን ጉና ላይ አመፅ በአመፅ ሆነ! 'አንዋጋም' ብለን ተመለስን። የኔ ፍላጐት ምን እንደነበር ልንገርህ?

'እኛ ወደማናውቀው የአማራ አገር ሄደን ከምንሞት፣ 'ፅዮናዊት ትግራይ' ብለን ከእስራኤል ጋር ስምምነት ማድረግና ገዳማትን ማስፋፋት ነበር ምኞቴ። ከዚያም ትምህርት ቤት፣ ሆስፒታል፣ መንገድ...እኔ ምኞቴ እንደዚያ ነበር። የሌላውን አላውቅም። መለስ ሲበር መጣ ወደ ግንባር! አቤት ሲናገር! ያምበለብለዋል! ሰራዊቱ በፀፀት እንባ በእንባ ተራጨ። አመፁ ወዲያው ከሽፎ ቁጭ! እና ውጊያው ቀጠለ..."

"የአመፁ ጊዜ መለስ ነበር እንዴ የመጣው?"

"ታዲያ ማነው?"

"አልመሰለኝም ነበር" አልኩ።

"መለስ ነው የመጣው..."

ፋታ ወሰደና አከለበት፣

"መለስ የወሬ ሰው ነው። ይኸው ወሬ በወሬ አደረገው አገሩን በሙሉ። ዛሬ የሚናገረውን ነገ ይገለብጠዋል። ችግር ሲመጣበት ማምለጫ አያጣም። ሃቁን አይነግርህም። ስብሃት ነጋ

ቢመርም ቢጣፍጥም ልቡ ውስጥ ያለውን ሁሉ ይናገራል። አቦይ ስብሃት ወንበሩን ለመለስ ከሰጠው በሁዋላ ስራ ቀረና አገሩ ሁሉ ወሬ በወሬ። ተመልከት! ጋራዥ ውስጥ ስምንት መኪና ተበላሽቶ ቆሞአል። ስራ ሁሉ ቆመና ውይይት። ስንት ቀን እዚህ ተጐለትን ያለ ስራ? አብዮታዊ ዴሞክራሲ!! ውይይቱ የገባው አንድም ታጋይ የለም። ሁሉም እያስመሰለ ነው። አንዱ የተናገረውን ሌላው ይደግማል። በቃ!"

በዝምታ ተከዝኩ።

ስለ በርሄ አመለካከት እያሰላሰልኩ ሳለም እንዲህ አለኝ፣

"አንተ ጥሩ ሰው ነህ!"

"አመሰግናለሁ" አልኩት።

ቀጠለበት፣

"እኔን አክብረህ ቤትህ ምሳ ጋበዝከኝ። ባልማርም እድሜዬን አክብረህ በጥሞና አዳመጥከኝ። ልቦና አለህ"

ትንፋሼን ውጩ ዝም አልኩ።

በርሄ ከሚለው አንፃር ከሆነ በርግጥም ጥሩ ሰው አለመሆኔን ልቤ ያውቀው ነበር። በርሄን ምሳ ጋብዤ ለምን በርጋታ ላዳምጠው እንደቻልኩ በርግጥ ማብራራት አልችልም። በርሄ ላይ ከሚያላግጡት አንዱ አይደለሁም ብዬ ግን ከቶውንም አልመፃደቅም። በርሄ ለምን ጥሩ ሰው እንደሆንኩ ሲያብራራልኝ ግን ከማዳመጥ የተሻለ አማራጭ አልነበረኝም። እና ቀጠለ፣

"ታጋዮችን ሁሉ ጠላሁ። አንተ ግን ጥሩ ሰው መሆንህን በመጀመሪያው ቀን ነው ያወቅሁት። የህወሃት ታጋዮች ተንኰለኞች ሆነዋል። ተጠግተው ይነድፉሃል። 'እምዘ አርዌ ምድር ታሕተ ከናፍሪሆሙ' ይላል መዝሙረ-ዳዊት። 'ከምላሳቸው ስር መርዝ የቀበሩ እባቦች' ማለት ነው። እውቀት ሳይኖራቸው እውቀት እንዳለው ሰው ይሆናሉ። እነሱ ብቻ የሚያውቁ ይመስላቸዋል። እንደ ድንጋይ የእድሜ ዘመን እየቆጠሩ ይመካሉ። የአክሱም ሰው ሲተርት፣ 'እድሜ እውቀት ቢሆን ኖሮ የአክሱም ሃውልቶች ትግርኛ መናገር ይጀምሩ ነበር' ይላል። መመካት በእድሜ ከሆነ መቼም፣ የኔን ያህል የታገለ የለም። እኔ ነበርኩ መመካት የነበረብኝ። እኔ ግን አልመካም። ገበሬና ዲያቆን ነው የነበርኩት። በትግሉ ጊዜ ደግሞ መኪና መጠገን ተማርኩ። አሁን መካኒክ ነኝ። ሌላ ምንም ልሆን አልችልም። ሌሎች የተናገሩትን በረጅሙ መድገም ጠቢብነት





ይመስላቸዋል። አይደለም፣ ጠቢብ ብዙ አይናገርም። ከኔ ጋር የሚሰሩትን መካኒኮች ታውቃቸዋለህ አይደለም? በስራ ከሆነ እኔን የሚወዳደር ማንም የለም። ስራቸውን ትተው ግን በኔ ላይ ሲያላግጡ ይውላሉ። የተሰጠን ስራ የተበላሹትን መኪኖች መጠገን ነው። ወሬ ምን ያስፈልጋል? መዝሙረ-ዳዊትን ወይም ተአምረ ማርያምን የጠቀስኩ እንደሁ፣ አንካሴ የመሰለ ጥርሳቸውን እያሳዩ ይስቃሉ። ምን የሚያስቅ ነገር አለው? እነሱ አንድም የሚጠቅሱት መፅሃፍ የላቸውም። አብዮታዊ ዴሞክራሲንም ቢሆን አያውቁትም። አብዮታዊ ዴሞክራሲ ጀበና ይሁን ስኒ ገና አልታወቀም። ንቃት አላቸው እንዲባሉ ብቻ ከፊት ይቀመጣሉ። እንደ መኪና ባትሪ ሲሞሉ ይውሉና ያቺ እስከታልቅባቸው የተሞሉትን ይተፋሉ። ንጉስ ዳዊት ብልህ መሪና ጀግና ነበረ። ጐልያድን በወንጭፍ ገድሏል። ሃጢአት ሲሰራ ደግሞ ሰውነቱ ላይ አመድ ነስንሶ ንስሃ ገብቶአል። ወዲ ዜናዊ ከዳዊት ጋር የሚስተካከል አይደለም። ታዲያ ዳዊትን መጥቀስ ምን ያስቃል? ታጋዮችን ጠላሁ። ከማንም ጋር አልቀርብም..."

በርሄ እየጋለና ስሜታዊ እየሆነ ሄደ።

የከረመ ብሶቱን ሁሉ እየዘረገፈልኝ እንደሆነ ስለተረዳሁ እንዳሻው ይናገር ዘንድ ተውኩት፣

"'ሰንበት ቤተክስያን ይሄዳል' ብለው ደግሞ ያሙኛል። ቤተክስያን ብሳለም...እንዴት ነው ነገሩ? ክርስትያን አይደለሁ እንዴ? እስላም መስጊድ ይሄዳል። ክርስትያን ደግሞ ወደሚያምነው ታቦት ሄዶ ይሳለማል። ሰንበት ቤተክርስትያን ካልሄድኩ የት ልሂድ ታዲያ? ቤተክስያን ስስም ብዙ ምእመናን ተዋውቄያለሁ። አማሮች ናቸው ብዙዎቹ። ምእመናኑ አይወዱንም። ወያኔ መሆኔን ሲያውቁ ቅሬታቸውን ሳይደብቁ በአንደበታቸው ነገሩኝ።

'ልትሰልለን እንዳይሆን እንጂ እናንተ ከመቼ ወዲህ ነው ቤተክሲያን የምትስሙት?' ብለው ጠየቁኝ።

ጉድ እኮ ነው!

'ኸረ በስመአብ በሉ! እንዲያው ለመሆኑ የኛን የሚያህል ቤተክስያን ሳሚ ማን አለ? እንዴት እንዲህ ያለ ንግግር ትናገራላችሁ? የሙሴ ፅላትስ እኛ ዘንድ አይደል እንዴ በአደራ የተቀመጠው? ትግራይ እንዴት በዚህ ይታማል?' ብዬ ስል

ምናሉኝ መልሰው፣

'የቀድሞዎቹማ የሚያሙ፣ የሚፀልዩ፣ አማኞች ነበሩ። ያሁኖቹ እንዲያው መላ አጣችሁ እንጂ' አሉኝ።

በዚህ ንግግር ተጀመረና ከመላመድ ብዛት አመኑኝ። ለምንድነው ህዝቡ የጠላን? ደማችንን አፈሰስን እንጂ ምን በደልን? ወዲ ዜናዊ፣ 'አብዮታዊ ዴሞክራሲ' ከሚለን ለምን ስለዚህ ጉዳይ አያዋየንም? አብዮታዊ ዴሞክራሲ ምንድነው? ጠንቋይ ነው? መልአክ ነው? ምንድነው? ህዝቡ እንዳይጠላን ማድረግ እንዴት ሳይቻል ቀረ? እኔ መኪና ሲበላሽ መስራት ነው ስራዬ። የተበላሹ መኪኖችን ጥሩ አድርጌ ሰርቻለሁ። መኪናውን ባግባቡ ካልሰራሁ፣ አደጋ ይደርስና ሰው ይሞታል። እነ ወዲ ዜናዊ ደግሞ ህዝቡ እንዳይጠላን ለምን አላደረጉም? ወደ ሰው ሃገር መጥተን ለምንድነው ሰው የምናሰቀይመው? ካልሆነልን ደግሞ ፅዮናዊት ትግራይን ማቋቋም ይሻላል። 'የለም ኢትዮጵያዊ ሆነን አብረን ነው መኖር ያለብን' ከተባለ ደግሞ፣ አብሮ መኖር እንዳለበት ሰው እንኖራለን እንጂ ሰው ማስቀየም ምን ይጠቅማል? አጤ ምኒልክ ባስተዳደሩን ጊዜ ትግሬን አላስቀየሙም። ራስ መንገሻ ሲያምፁ ስንት ጊዜ ምህረትና እርቅ አድርገዋል። ሁሉን በሽምግልና በመግባባት ነበር የሚይዙት። አሉላ ሲከዳቸው፣ መንገሻ ከአንድም ሁለቴ ሲወጋቸው 'ተዉ አይሆንም' ብለው ሽማግሌ ላኩ እንጂ ህዝቡን አልበደሉም። እነ ወዲ ዜናዊ ምን ነካቸው? ወዲ ዜናዊስ እሺ ይሁን ልጅ ነው። አቦይ ስብሃት ይህን እያየ እንዴት ዝም ይላል?..."

"ምእመናኑ ለምንድነው የጠሉን?" ስል ጠየቅሁት።

"በማንኛውም ስራችን አይደሰቱም" ሲል ፈጥኖ በግለት ቀጠለ፣ "...ህዝቡን ከፋፈላችሁት። አላወቃችሁበትም' ብለው አሉኝ። እንዲህ ኖሮአል ነገሩ? ሌላ ሌላውን ተወውና ባንዲራው ላይ በለጠፍነው ነገር ቅሬታ አላቸው። እኔ በፊት ይህን ልብ አላልኩም ነበር። ከምእመናኑ ጋር ስናወጋ መምሬ ሃይሉ የሚባሉ ቄስ ገለል አድርገው ወስደው ምን ይሉኛል?

'እንዳንተ አይነት ፈሪሃ እግዚአብሄር ያለው ሰው ወያኔ ውስጥ ይኖራል ብሎ እንኳ ማን ያስባል? እንዲያው ልንገርህና ሰው ሁሉ ጠልቷችሁዋል' ይሉኛል።

ይሄ ነገር ስለሚደጋገም፣

'እስኪ አንድ ጥፋት የሚሉትን ይንገሩኝና እኔ ሄጄ





ለአቦይ ስብሃት ለራሳቸው አደርሳለሁ' አልኳቸው።

'ምን ሩቅ አስኬደህ? መሪያችሁ ገና አዲሳባ እንደገባ አይደለም እንዴ ባንዴራውን የተሳደበው?' አሉኝ።

እኔ በዚህ አልተረታሁም።

'አባቴ!' አልኳቸው። 'መቼም ያ የቆየ ነገር ነው። ያፍ ወለምታም ነበር። ወዲ ዜናዊ እንዲያው በቴሌቪዥን ሲታይ ጠጉሩ ሙልጭ ብሎ ትልቅ ሰው ይመስላል እንጂ፣ ገና አንድ ፍሬ ልጅ ነው። እኔ ሳውቀው ጠጉሩ ግንባሩ ድረስ የተዳፋ፣ ህንድ የሚመስል ትንሽ ልጅ ነበር። ተማሪዎች ናቸው። ቢሳሳቱ ይታረማሉ' አልኩ።

መምሬ ሃይሉ መዳመጥ ሲችሉ ሞቸም ተአምር ነው። የረቀቁ ካህናት ባሉበት ደብር የተማሩ ቄስ ናቸው። ቅኔ ቆጥረዋል። ቤት ሞልተዋል። መፅሃፈ ስንክሳርን ሳይቀር ያነበቡ፣ የበቁ፣ ምራቃቸውን የዋጡ ጨዋ ሰው ናቸው። ንግግሬን ሁሉ በጥሞና ካብላሉ በሁዋላ፣

'አባባልህ ሁሉ መልካም ነው። ያፍ ወለምታም ከሆነ ይሁን! ከመናገር ብዛት ስህተት ያጋጥማል። በዚያው ቢበቃ ኖሮ መልካም በነበረ። አሁን ደግሞ ባንዴራው መሃል ላይ አምባሻ አስቀመጣችሁበት የሚባለውስ?' ብለው አይጠይቁኝም?

'ይሄ ሊደረግ አይችልም!' አልኳቸው።

'ተደርጐአል!' አሉኝ።

'ርስዎ ራስዎ ባይንዎ አይተውታል?' ስል ጠየቅሁ።

'እኔ እንኳ አላየሁትም። ያዩ የደብሩ ምእመናን ግን ነግረውኛል። በመጀመሪያ ባንዴራው ጨርቅ ተባለ። አሁን ደግሞ ሳህን አደረጉት። እንግዲህ ሁሉም ጉሳ እየተነሳ የየራሱን ዳቦ፣ 'ባንዴራው ላይ ይቀመጥልኝ' ካለ እንዴት ሊሆን ነው? ድፎ ዳቦ አለ፣ አነባበሮ አለ፣ ቆሎ አለ፣ ገንፎ አለ፣ ጨጨብሳ አለ፣ ባንዴራው ይህን ሁሉ እንዴት ይሸከማል?'

እንዲህ ሲሉኝ የምመልሰው ጠፋኝ።

ከመምሬ እንደ ተለየሁ በቀጥታ ወደ ቀበሌ ሄድኩ። ፈቃድ እንኳ አልጠየቅሁም። ባንዴራውን አውርጄ አየሁት።

ደርቄ ቀረሁ!

አምባሻው መሃሉ ላይ ቁጭ ብሏል።

ወንድሜ ልንገርህ? ያን እንዳየሁ ምንም አልተናገርኩ። ባንዴራውን ወደ ነበረበት መልሼ በቀጥታ ቤቴ ግብቼ ተጠቅልዬ

ተኛሁ። በብሽቀት እህል የሚባል ወደ አፌ አልገባም። ጨጓራዬ ሲቃጠልና ሲገላበጥ ይታወቀኛል። እንዴት ይንጋልኝ? 'እህ!' እንዳልኩ ነጋ መቼም። በመከራ ነጋ! በጠዋት ወጣሁ። ጋራዥ አልሄድኩም። በአስቸኳይ ሰርቪስ እንድትደረግ ቀጠሮ የተያዘላት የሰለሞን ጢሞ መኪና ነበረች። 'የራሱ ጉዳይ' ብዬ በቀጥታ ወደ ኢህአዴግ ፅህፈት ቤት ሄጄ አብርሃ ሳንቲም እስከትገባ ጠበቅሁዋት። ቢሮ ስትገባ ጠብቄ አብሬያት ገባሁ፣

'ምንድነው የምትሰሩት?' አልኳት በቁጣ።

'ምን ሆነሃል?'

'ባንዴራው ላይ አምባሻ ተልጥፎአል። እንዴት ነው እንደዚህ ሊደረግ የቻለው?'

'ስለምንድነው የምታወራው? ባንዴራው ላይ ያለው አምባሻ አይደለም። ኰከብ ነው' አለችኝ።

'እኔ በ65 አመት እድሜዬ ኮኮብና አምባሻ ለይቼ አላውቅም?' ብዬ ስቆጣት እሷም በቁጣ መለሰችልኝ፣

'ችግር ከገጠመህ የቅርብ አለቃህን ሄደህ አናግር። ከንግዲህ እኔ ዘንድ እየመጣህ ስራ አስታስፈታኝ' አለችኝ።

አብርሃ ልጅ ስለሆነች አልያዝኩባትም።

ትቼያት ወደ አቦይ ስብሃት ገባሁ። ትልቅ ሰው ናቸው መቼም። የሰው ልክ ያውቃሉ። ከመቀመጫቸው ተነስተው ተቀበሉኝ። ከዚያም እሳቸው ቁጭ ሳይሉ በቁማቸው ሆነው፣

'በርሄ አረፍ በል። ጤንነትህ እንዴት አለ?' አሉኝ።

እንዲያ ሲሉኝ ንዴቴ ሁሉ ባንዴ በረደ።

ወንበር ያዝኩና ጊዜም ሳላጠፋ የሆነውን ሁሉ ዘርዝሬ ነገርኳቸው። ባንዴራውን ራሴ ከቀበሌ 23 ፅህፈትቤት አውርጄ መሃሉ ላይ የተጋገረውን አምባሻ በአይኔ ማየቴን በዝርዝር አጫወትኳቸው።

ስብሃት ነጋ አዳምጠው ሲያበቁ፣

'ህዝቡ ተወያይቶበት የፀደቀ ባንዴራ ነው። መውለብለብ ከጀመረም ሁለት አመት አለፈው። አንተ እስከ ዛሬ የት ነበርክ?' ሲሉ ጠየቁኝ።

'እኔማ ስራ ይበዛብኛል' አልኩ፣ '...ታጋዩ ሁሉ መኪና ሲያጋጭ ነው የሚውለው። መቼ ጊዜ አገኝቼ ነው ባንዴራውን የማየው? ጋራዥ ውስጥም ባንዴራ የሚባል የለም። ሆኖም ትናንት መምሬ ሃይሉ እንዳጫወቱኝ ከሆነ አገር ሁሉ





በአምባሻው ባንዴራ ተቀይሞአል' አልኩ።

'ማናቸው መምሬ ሃይሉ?' ሲሉ ጠየቁኝ።

'ቄስ ናቸው። ጊዮርጊስ ያስቀድሳሉ'

አቦይ ስብሃት እየሳቁ፣

'አሁንም ቤተክስያን ትሄዳለህ እንዴ?' ሲሉ ጠየቁኝ።

'እንዴት ያለ ጥያቄ ነው? ክርስትያን አይደለሁ እንዴ? እስላም መስጊድ ይሄዳል፣ ክርስትያን ደሞ ቤተክስያን ይሄዳል። እንደማያውቁ ሆነው እንዴት እንደዚህ ያለ ጥያቄ ይጠይቁኛል?' አልኩ።

ስብሃት ነጋ አስበው አስበው ምን አሉኝ?

'እዚህ ካልተስማማህ ወደ አክሱም ብናዘዋውርህስ?'

'ይሻለኛል!' አልኩ። '...ክፉ እየሰማሁ ከምቃጠል ወደ አክሱም መመለስ ይሻለኛል'

ይህን የተባባልነው እንግዲህ ከኤርትራ ጦርነት በፊት ነበር። እስካሁን እዚህ ነኝ። ጦርነቱ ሲጀመር የኔን ጉዳይ ያስታወሰውም የለ። በየስብሰባው በየግምገማው ግን የባንዴራውን ጉዳይ አነሳለሁ። ማን ሊሰማ? ወጣቶቹ ይስቃሉ። ያላግጣሉ፣ በተናገርኩ ቁጥርም እንዲህ ይሉኛል፣

'አንጐልህ ደንዝዞአል! ፖለቲካ አይገባህም! የዋህ ነህ!'

'እንዴት ነው አንጐሌ የደነዘዘው? የመደንዘዝን ትርጉም ታውቁታላችሁን?' ብዬ ጠየቅሁ። ከመዝሙረ ዳዊትም ጠቀስኩ።

'ዘተከላሁ ለእዝን ኢይሰምእኑ? ወዘፈራሁ አኢይን ኢይሬኢኑ? አብዳንኬ ማእዜ ይጠቡ?'

ይህን ስጠቅስ ታጋዩ ሁሉ ሳቅ በሳቅ።

ምን የሚያስቅ ነገር አለው?

'ደንዝዘሃል' አሉኝ።

አይኔ ያያል፣ ጆሮዬ ይሰማል፣ አእምሮዬ ያስባል የሚለውን ለማስረዳት ከዳዊት መዝሙር መጥቀስ ምን የሚያስቅ ቀልድ አለው? ወይም ምን የሚያስገለፍጥ ነውር ተናገርኩ? አንዳንድ ልጆች ደግሞ፣

'ኢድዩ ነህ' አሉኝ።

እንዴት ነው ነገሩ?

እኔ ገበሬና ዲያቆን ነበርኩ። እንዴት ነው ኢድዩ የምሆነው? ትግሬይ ሳሉ ቤተክስያን የሚስሙ፣ ጥሩ ልጆች የነበሩ ታጋይ ከሆኑ በሁዋላ ሆን ብለው እኔ ፊት እየሱስ

ክርስቶስ ላይ ያላግጣሉ፣

'ቡርዣው ጭቁኖችን ለማታለል የፈጠረው ነው' አሉኝ። ምን ማለት ነው ይሄ?

ይህን ስድነት ከየት አመጡት? እየሱስ ክርስቶስ ከድንግሊቱ ማርያም የተወለደ የአምላካችን ልጅ፣ መድሃኒታችን መሆኑን ለማስረዳት ስጀምር እየሳቁ በቆምኩበት ጥለውኝ ይሄዳሉ። የጊዮርጊስን ጠበል በብልቃጥ ይዤ አይተውኝ እንደ አህያ መሬት ላይ እየተንደባለሉ ሳቁ። 'ጠበል ሲያይ የሚንፈራፈረው ዲያቢሎስ ነው' ብዬ ስላቸው ብሶባቸው እንባቸው እየተዝረበረበ ይስቃሉ። እነዚህ ሰዎች ምን ሆነዋል? የጤና ነው? ይህን ሁሉ ብልግና ከየት አመጡት? ለምን ያላግጡብኛል? በመሆኑም ይኸው 'ወኩሉ አሚረ ትኩዝየ አንሶሱ። እስመ ፀግበት ፅእለተ ነፍስየ' እያልኩ አለሁ። ይሄ ምን ማለት ነው? ነፍሴ ስድብን ጠግባለችና ትካዜዬ በዝቶአል...

'...ሳህል ሳለ ጭንቅላቱ ላይ በጥይት ተመቷል' የሚል ነገር ደሞ አመጡ። ይሄን ያስወሩት እንግዲህ 'አብዱል' ማለት ፈልገው ነው። ይሄ ውሸት ነው። ሻእቢያ ዘንድ ሳህል ሳለሁ ሁለት ጊዜ በጥይት ተመትቻለሁ። እሱም ጉልበቴ ላይና ጉንጩ ላይ ነው። ጭንቅላቱ የተነካ ሰው እንዴት ሞተር አውርዶ መልሶ ይገጥማል? አእምሮው በጥይት የተመታና ያበደ ሰው እንዴት መዝሙረ ዳዊትን በቃሉ ያውቃል? የጐረቤት መዘባበቻ ሆንን። ወተሳለቁ ላእሌነ ፀላእትነ።

'መዝሙረ ዳዊትን ብቻ ነው የሚያውቀው' እያሉ ደግሞ አላገጡብኝ። ይሄም ውሸት ነው። የዘብዴዎስ ልጅ የፃፈውን የዮሃንስን ወንጌልም ያለንባብ አውቀዋለሁ። በፅርእ ቋንቋ ለኤፌሶን ሰዎች የፃፈላቸውን..."

ወደ ስብሰባው አዳራሽ በመመለስ ላይ ሳለንም እንዲህ ሲል ተስፋ ባጣ ስሜት ወጉን ቋጨ፣

"በርግጥ ወጣቶቹ እንደሚሉት ተቀላቅሎብኝ ሊሆን ይችላል። ዞሮ ዞሮ ግን ሰው በአምላክ የሚተካ አይደለም። ወጣትነት የሚፈጥረው ነገር አለ። ወጣት ሳለሁ አማሮች ጠላታችን ይመስሉኝ ነበር። ይኸው! አገራቸው መጥተን አየናቸው። ሃይማኖተኞችና ሰው አክባሪ ደግ ሰዎች ናቸው። ግፍ እየሰራንባቸውም ችለውን ተቀምጠዋል።

'ግፍ ግፍን ይፈለፍላል እንጂ ግፍ ስንዴ አይወልድም። ጥላቻ ተተክሎ ሮማን አያፈራም። መዘዝ አለው። ጐረቤቶቻችንን ማስቀየም ተመልሶ ጉዳቱ ለኛው ነው' ብዬ ብናገርም የሚሰማኝ አላገኘሁም። 'ከግፍም ግፍ ልባቸው ወደ ገንዘብ ሄዶአል' የሚባልም አለ። እንዲያ ከሆነ መቼም ጉድ ነው። ለየትኛው አለም ይሆን? ወከመ ሃመልማለ ሃምል ፍጡነ ይወድቁ። 'እንደ ለምለም ቅጠል ይወድቃሉ' ተብሎ ተፅፎአል - ዳዊት ላይ።

'ፖለቲካ አይገባህም' ይሉኛል።

ፖለቲካ ምን ማለት ይሆን?

ፖለቲካ ማለት ጐረቤቶችህን ማስቀየም ነው እንዴ? ራስህ ላይ እንዲደረግ የማትፈልገውን ሌላው ላይ ማድረግ ፖለቲካ ከሆነማ ንስሃ መግባት አለብኝ..."

* * *

ከዚያ ስብሰባ በሁዋላ በርሄን አላየሁትም።

እንደሰማሁት ግን በ1994 ማብቂያ ግድም በጡረታ አግልለው ወደ አክሱም መልሰውታል። ስለ በርሄ ልፅፍ ከወሰንኩ በሁዋላ አክሱም በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ ጥረት አድርጌ ነበር። እንደተመኘሁት ዝርዝር ነገር ላገኝ አልቻልኩም። ከቀድሞ ወዳጆቼ አንዱ ግን ጥቂት መረጃዎችን ልኮልኝ ነበር...

በጥቅሉ ላውጋችሁ...

አክሱም ላይ አቶ በርሄን የማያውቅ ማንም የለም። "ጐማ እግሩ" የሚል ቅፅል ስማቸው ተረስቶአል። አዛውንቱ በጡረታ ላይ የሚገኙ የህወሃት ነባር ታጋይ መሆናቸውን ግን የከተማዋ ነዋሪ ሁሉ ያውቃል። ሰንበት ዞሮ ሲመጣ ማርያም ፅዮን ደጀ ሰላም ላይ በፍፁም አይጠፉም። ከእግዚአብሄር ሰላምታ በቀር ሌላ ቃላት ሲናገሩ ሰማሁዋቸው የሚል ከቶውንም አይገኝም። ጠጉራቸው የተባዘተ ጥጥ መስሎአል። ሲራመዱ ግራ እግራቸውን ይጐትቱታል። ቢሆንም እድሜ ጥንካሬያቸውን ገና አልነካውም። ማንኛውም አይነት የፖለቲካ ስብሰባ ላይ ሲሳተፉም ያያቸው የለም።

በሃዘን ወቅት ግን ርዳታ ለመስጠት አቶ በርሄን ማንም አይቀድማቸው። ድንኳን በመትከል፣ ወንበሮች በመሸከምና

ንፍሮ በመቀቀል ህዝቡን ያገለግላሉ። ድንኳን በሚፈርስበት ጊዜም ከባድ በተባሉት ተግባራት ሁሉ ይሳተፋሉ። የተበላባቸውን ሳህኖች ያጥባሉ። አግዳሚ ወንበሮችን በእድሩ መጋዘን ያከማቻሉ። ቆሻሻዎችንም ጠርገው ይደፋሉ።

ከዚህ ባሻገር አዛውንቱ በርሄ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ሲናገሩ ተሰምተው አያውቁም። ይልቁን እንደ አክሱም ሃውልቶች በጥልቅ ዝምታቸው ይታወቃሉ። ተፀመምኩ ወኢከሰትኩ አፉየ...



- 5 -

# ወርቃማ አመታት

የተፈጥሮ ልጅ ነኝ - የዚህ ግዴለሹ፣
ወርቃማ ዘመኔን - ማወቅ ለምትሹ፣
ከመሃል ግን ነጥቆኝ - የሞት አራሙቻ፣
ወስዶ ከጨመረኝ - የሲኦል ዳርቻ፣
እኔነቴ ጠፍቶ - ሲማስ መቃብሬ፣
ሞትኩ የምል ያኔ ነው - ሲነጠፍ ብእሬ፣

(ግጥም–አሌክሳንድር ፑሽኪን)
- አያልነህ ሙላቱ እንደተረጎመው -

* * *

አንገቱን ሸቅብ አርዝሞ - የዘመን ቁመት ተራራ፣
በሰው ባዶነት መዝገብ ላይ - "ከንቱ ነህ!" ብሎ ሲያጓራ፣
የሰው የተስፋ ካብ ፈርሶ - የውስጥ ሃውልቱ ሲሰበር፣
"መኖር!" የሚሉት ቋንቋ - ለካስ ከፊል ገፅታው ይህ ነበር!?

(ግጥም - ደረጄ በላይነህ)

እነሆ! የልጅነት ጓደኞቼ አብዛኞቹ ማትሪክን አልፈው ዩኒቨርሲቲ ገቡ። እኔ ወደቅሁ። በወቅቱ "ወደቅህ!" የሚለው ቃል እብድ አድርጎኝ ነበር። አእምሮዬን ልስት ምንም አልቀረኝ። ቀኑን ሙሉ አንጎሌ ውስጥ የሚያቃጭለው ቃል "ውዳቂ!" የሚለው ነበር። "ወደቀ" የሚለው ቃል የእርባታ ግሶች እንደ አንበጣ እየተፈናጠሩ አእምሮዬን አቆሰሉት። ወደቀ፣

ውዳቂ፣ ውድቅዳቂ፣ ውድቅዳቂዎች፣ የወዳደቁ እቃዎች...

ከእናቴ ሞት በሁዋላ ቤተሰባችን ብዙም አልተመቸውም ነበር። እኔም የትዳር ጎጆ ከመሰረተች ታላቅ እህቴ ዘንድ ተጠግቼ ነበር የተማርኩት። ያን ቀን ሰርተፊኬቴን አንጠልጥዬ እቤት እንደገባሁ እህቴ በቁጣ እየጨሰች ጠበቀችኝ። የጓደኞቼን ማለፍና የኔን መውደቅ ሰምታ ኖሮአል። ማን እንደነገራት አምላክ ይወቅ። ራሴው እንደሚሆን አድርጌ ላጫውታት ነበር አሳቤ።

የተቆጣ አንበሳ ሆና ጠበቀችኝ።

እኔ ስገባ ወጥ ቤት ውስጥ የተበላበትን ትሪ እያጠበች ነበር። ትሪውን አንስታ አወዛወዘችብኝ። ትሪው ላይ የአንበሳ ስእል አለ። የኢትዮጵያን ባንዴራ ያነገበ የጃንሆይ አንበሳ!

እህቴን ላረጋጋት በማሰብ፣

"ነጥቤን ተመልከችው..." ብዬ ላሳያት ጠጋ ስልና ትሪውን ከግድግዳው ጋር ስታላትመው አንድ ሆነ።

በድንጋጤ በቆምኩበት ጨው ሆንኩ።

ትሪው የፈጠረው የጩኸት ድምፅ ቀሌዬን ገፈፈው። እንደ ቃጂማ ጊዮርጊስ ደወል ነበር ያስተጋባው። ትሪው ሳይሆን ትሪው ላይ ያለው የንጉሱ አንበሳ የጮኸ ነበር የሚመስል። ትሪውን እናቴ ላይ ከማሳረፏ በፊት ግን ጎረቤታችን ዮሃንስ ጆቴ ከመካከላችን ተገኝቶ ነበር። እህቴ ትሪውን፣ እኔ ሰርተፊኬቴን ይዘን ተፋጠን ቆመናል። ተያይዘው በተሰሩ የመንግስት የቁጠባ ቤቶች ውስጥ እንኖር ስለነበር፣ ዮሃንስ በትሪው ድምፅና በእህቴ ቁጣ ተስቦ ነበር የመጣው። እሱም ተደናግጠ፣

"ምን ሆናችሁዋል?" ሲል ጠየቀ።

"ወደቀ!" ስትል በብሽቀት ድምፅ ነገረችው።

አያይዛም ቀጠለች፣

"...ሌሊቱን ሙሉ ቁጭ ብሎ ሲያጠና ከርሞ ይኸው ወድቆ መጣ። ጓደኞቹ ሁሉ አልፈዋል። እሱ ወደቀ። አጠናለሁ እያለ ልቦለድ መፅሃፍ ሲያነብ ነው የከረመው። ስንት ጊዜ አይቼዋለሁ!?" ከዚያም ወደኔ ዞራ ቀጠለች፣ "...አሁኑኑ ሻንጣህን ይዘህ ወደምትሄድበት ሂድ! እኔ ሃላፊነቴን ጨርሻለሁ። ሌሊቱን ሙሉ ኤሌክትሪክ ስታበራ አድረህ፣ ኪሳራ ብቻ!"

ዮሃንስ የማትሪክ ካርዴን ተቀብሎ መመልከት ጀመረ። ውጤቴን እያየም እንዲህ አለ፣





"እንዴ! ጥሩ ውጤት ነውኮ ያመጣኸው! ወድቀሃል እንዴ? መች ወደቅህ? 4B አግኝተህ የለም እንዴ? አሃ! ሂሳብና እንግሊዝኛ C እና D? ስንት ማለት ነው ይሄ? እሱ ነው የጎዳህ! ቢሆንም በዚህ ነጥብ የሆነ ኮርስ አታጣም። ካልሆነ ደግሞ በድጋሚ ተፈትነህ ሁለቱን ካሻሻልክ..."

እህቴ ግን ልታስጨርሰው ሳትችል ቀረች፣

"በፍፁም! ሻንጣውን ይዞ ይውጣልኝ። ሶስት አመት አስተምሬዋለሁ። በቃኝ! አንድም ቀን እዚህ ቤት አያድርም! ታናናሾቹ አሉ። እነሱን አስተምራለሁ። ይሄ ዋጋ ቢስ ነው..."

ዮሃንስ ወደ ደጅ ይዞአት ወጥቶ ያነጋግራት ጀመር። ሲቆጣትና ሲመክራት እየሰማሁ ነበር፣

'ምንም ቢሆን ወንድምሽ ነው...ደሞም እኮ በዚህ ነጥብ ዩኒቨርሲቲ መግባት ይቻል ነበር...ጊዜው ተበላሽቶ ነውንጂ በኛ ጊዜ ከዚህ በታች ባለ ነጥብ... የሱ ጥፋት አይደለም... መቼም ያቅሙን ሞክሮአል...ባይሆንስ ደግሞ እንደዚህ ልታስደነግጪው አይገባም...ታዛዥ እና ትሁት ልጅ ነው...አንቺስ ብትሆኚ ማትሪክ መቼ አለፍሽ?...ስራ ሊያገኝም ይችላል...መቼም ችግር ካለ..."

እሷም ቀዝቅዛ እንዲህ ስትለው ሰማሁ፣

'እሱስ ልክ ነህ! ተናድጄ ነው እንጂ ልጁስ አስቸጋሪ አይደለም። በሌላም ነገር ተበሳጭቼ ነበር። አንተንም አስቸገርንህ መቼም..."

የእህቴ ቁጣ ከዚሁ እንደማያልፍ አውቅ ነበር።

አፏ ይናገራል እንጂ ልቧ ገር ነው። ዮሃንስም የረጅም ጊዜ ጎረቤታችን እንደመሆኑ ጠባይዋን ያውቃል። ተቆጥቶአትና አረጋግቶአት ተሰናብቶን ሄደ።

አልጋዬ ላይ ጋደም ብዬ ጣራጣራውን ስመለከት ሳለ እህቴ ወደ ነበርኩበት ክፍል ገብታ አንድ ብር እየሰጠችኝ እንዲህ አለች፣

"ዛሬ ማክሰኞ ነው! ፊልም ለምን አትገባም?"

አመስግኜያት ተነስቼ ወጣሁ።

ደብረዘይት ላይ በሳምንት አራት ቀናት ማታ ማታ ፊልም ይታይ ነበር። በርግጥ ፊልም ቤቱ የአየር ሃይል ካምፕ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፣ ለአየር ሃይል መለዮ ለባሽ ልጆች ብቻ የተፈቀደ ነበር። ቢሆንም ሲኒማ መግባት ሲያምረን

የጓደኞቻችንን መታወቂያ እየተበደርን ፊልም እናያለን። በዚያን እለት ታዲያ ሲኒማ ቤት ማምሸቴ ጭንቀቴን በመጠኑ ቀነሰልኝ። የዮሃንስ የተስፋ ቃላትም ልቤ ውስጥ ማበብ ችለዋል።

*( ከዚያ ወዲህ ታዲያ ተስፋ ያጡ ወጣቶች ሲገጥሙኝ ብዙውን ጊዜ ዮሃንስ ጆቴን በማስታወስ ለወጣቶች ተጨባጭ ተስፋና ምክር ለመስጠት ጥረት ማድረግን ለምጃለሁ። "እፍታ" የተባሉትን አምስት ተከታታይ ቅፅ መፃህፍትን ለማተም የተጋሁበት ዋና መነሻም ተሰጥኦ ያላቸው ወጣቶችን ለማገዝ ነበር። በቀላሉ ሊሰባበሩ የደረሱ ወጣቶችን በጥቂት ተስፋ ሰጪ ቃላት ከመሞት ማዳን እንደሚቻል ከራሴው ልምድ ተምሬያለሁ። 'የጋዜጠኛው ማስታወሻ' ሲታተም ዮሃንስ ከጀርመን ሃገር የኢሜይል መልእክት የላከልኝ ሲሆን፣ በጋለ ስሜት አድናቆቱን ገልፆልኛል። እህቴም መፅሃፉ ሲታተም ባህሬይን ከተባለው ሃገር ነበረች። መፅሃፉን በፖስታ ቤት ልኬላት፣ አንብባ እንደ ጨረሰች በጣም ተደስታ ለላኩላት አንድ መፅሃፍ 500 ዶላር ከፍላኛለች። የእህቴ እነዚህ ሁለቱ ተቃራኒ የስሜት ጫፎች፣ የሰዎችን ስሜታዊ ባህርያት በጥልቀት እንዳጤን እገዛ አድርጎልኛል።)*

ዞረም ቀረ ዩኒቨርሲቲ መግባት አልተቻለም።

አወዳደቁ በዚያም አላበቃ። ከህልሜና ከምኞቴ በከፍተኛ ፍጥነት ቁልቁል ተንሸራትቼ የመጨረሻው ወለል ላይ ተዘረርኩ። ባጭሩ የሆነው እንዲህ ነበር። ዩኒቨርሲቲ መግባት አለመቻሌን ሳውቅ ለዲፕሎማ ማጥናት እችል እንደሁ ሞከርኩ። በወቅቱ የአንደኛ ዙር ብሄራዊ ውትድርና ተመላሾች በዝቅተኛ ነጥብ (1.8) ወደ ዩኒቨርሲቲ እንዲገቡ በመፈቀዱ በሮች ሁሉ ተጣበው ነበርና ሳይቻል ቀረ። እንደ ጥንቸል እዚህም እዚያም እየዘለልኩ ብዙ ጣርኩ። አልሆነም። በቀሪዎቹ ቦታዎች በአብዛኛው አሰራሩ በዘመድ አዝማድ የሚፈፀም ነበር።

በመምህርነት ለመሰልጠን TTI ለመግባት ሞክሬ ነበር። ይህን ስልጠና ለማግኘት በምኞት ተቃጥዬ እንደነበር ትዝ ይለኛል። እሱም አልተሳካም። የሰው ልጅ ፍላጎቱን ባላገኘ ቁጥር ዝቅ እያለ መውረዱ አይቀሬ ነው። በመሆኑም እዚያው ደብረዘይት "እንድርያስ" ለተባለ የህዝብ ትምህርት ቤት የ4ኛ ክፍል የአማርኛ መምህር ለመሆን ተፈተንኩ። እሱንም ወደቅሁ። በርግጥ ከተመዘገብነው ውስጥ ሶስት ወጣቶች





ለማጣሪያ አልፈን ነበር። የሚፈለገው ግን አንድ መምህር ብቻ ነበርና በጠቅላላ እውቀት ችሎታ አወዳደሩን። ለኔ የደረሰኝ ጥያቄ እንዲህ የሚል ነበር፣

"ከA እስከ Z ያሉ ፊደሎችን የያዘ አረፍተ ነገር ጥራ?"

እንዲህ ያለ አረፍተነገር ሊኖር እንደማይችል በርግጠኛነት ተናገርኩ። በርግጥም ርግጠኛ ነበርኩ።

"ወድቀሃል!" ተባልኩ።

ከዚያም መልሱን ነገሩኝ።

"The quick brown fox jumps over the lazy dog"

ለማጣሪያ ከቀረብነው ሶስት ተፈታኞች እኔና አንድ ጓደኛዬ ወደቅን። እድለኛው ሶስተኛው ተፈታኝ እኛን አሸንፎ የመምህርነት ስራውን በማግኘቱ ፊቱ በደስታ ጨረቃ መስሎ አየሁት። እኔም በቅናት ብረት ምጣድ ሳልመስል አልቀረሁም። ከኔ ጋር የመውደቅን ክፉ እጣ የተቀበለው ወጣት ሚልኪያስ አልበርት የተባለ በእሩብ ጎኑ የእንግሊዝ አይሁድ ዘር ያለበት ጓደኛዬ ነበር። ክልስ በመሆኑ "ቀዮ!" ነበር የምንለው። እና ያን ቀን እኔና ቀዮ በሃዘን ተውጠን ወደ ቤታችን አዘገምን። ርስበርሳችንም የማፅናኛ ቃላት ተለዋውጠናል። ለነገሩ በኔ በኩል መውደቅን ተላምጄው ነበርና ብዙም አልተጎዳሁ። ሚልኪያስ እንደ ጭስ እየጨሰ ልጁ እንዲያልፍ የተደረገው በዘመድ በር ሊሆን እንደሚችል በቁጭት ነገረኝ። እኔም ሊሆን እንደሚችል ተስማማሁ።

ዞሮ ዞሮ እኛ ወድቀን ነበር።

መውደቅ ሁሉ መጥፎ፣ ማለፍ ሁሉ ጥሩ አለመሆናቸውን ለመገንዘብ ግን ጥቂት አመታት ብቻ ነበር ያስፈለጉኝ። ሚልኪያስም መውደቅ ጠቃሚ የሚሆንበት ጊዜ መኖሩን እንደተረዳ ሁዋላ ላይ አጫውቶኛል። የህይወትን የጉዞ መንገድ ከቶ ማን ያውቃታል?

*(ይህቺን በምጫጭርባት ደቂቃ ሚልኪያስ "ሚሊዮኔር" ከሚባሉት ባለሃብቶች አንዱ ለመሆን የበቃ ሲሆን፣ "አድማስ አስመጪና ላኪ" የተባለ ኩባንያ ከፍቶ ተቀማጭነቱን አዲሳባ ላይ አድርጎአል። ስለ ሚልኪያስ ይህን ዝርዝር የነገረኝም google ነበር። በአንድ ወቅት በተስፋ መቁረጥ ጎዳና ላይ አብሮኝ*

*የተጓዘው የልጅነት ጓደኛዬ፣ ከዜሮ ተነስቶ ወደ ሚሊዮናት ይተኮስ ዘንድ አይሁዳዊነቱ ሳያግዘው አልቀረም። 'በአለም ላይ ካሉ ሶስት ሚሊዮኔሮች አንዱ ይሁዲ ነው' የሚል አባባል አለ። በዚያን እለት ከሚልኪያስ ከተለያየን በሁዋላ በቀጥታ ወደ ቤቴ አዘገምኩ። ከመውደቄ ይልቅ እንዲያ ያለ አረፍተ ነገር ስለ መኖሩ ጉዳይ ብዙ እያሰላሰልኩ ነበር። የ4ኛ ክፍል የአማርኛ መምህር መሆን ካልቻልኩ ምንድነው መሆን የምችለው? ከዚያ ዝቅ ያለ ምን አይነት ስራ ላገኝ እችላለሁ? በርግጥ ከመምህርነት ስራ ዝቅ ያሉ፣ ሆኖም ከፍተኛ ስልጣን ላይ የሚያስቀምጡና ከፍተኛ ደሞዝ የሚያስገኙ በርካታ ስራዎች መኖራቸውን ደርግ ከወደቀ በሁዋላ ተረድቼያለሁ። እነዚያን ስራዎች ለማግኘት ሰርተፊኬት አያስፈልግህም። በርግጥ ቀጣሪዎችህ ሀሊናህን እንድትሸጥላቸው ይጠይቁሃል...)*

* * *

በዚያው ሰሞን በዘመድ በር አንድ ስራ አገኘሁ።

በርግጥ ስራ አገኘሁ ከማለት 'ወደ ስነፅሁፍ ኮሌጅ ገባሁ' ማለቱ ይቀል ነበር። ከህብረተሰብና ከህይወት ብብት ውስጥ ሊገኝ ወደሚችለው ወደ ስነፅሁፍ ኮሌጅ የመግባቱን ልምድ ያገኘሁት በቀጥታ ከጎርኪይ መፃህፍት ሲሆን፤ በውድቀትና በተስፋ ማጣት መካከል ባሉት በእነዚያ ጊዜያትም ብርታት አገኝ ዘንድ በእጅጉ አግዞኛል። በርግጥም ጎርኪይ እንደገለፀው የሰው ልጅ ለተፈጥሮ ሳይንስ ምርምር እንደ ጥንቸል ራሱን ሳጥን ውስጥ ሊያገኘው ይችላል። በመሆኑም በአጭር ጊዜ ውስጥ ራሴን በራሴ የለውጥ ሂደቴን፣ የእድገት ደረጃዬን መከታተል ችዬ ነበር...

ነገሩ እንዲህ ነበር የሆነው...

አንድ ምሽት ላይ ሰለሞን የተባለ ጎረቤታችን "ታላቅ ዜና" ይዞልኝ መጣ። ከሰላምታ በፊትም ቸኩሎ እንዲህ አለኝ፣

"ስራ አግንቼልሃለሁ"

"እውነት?"

"አየር ሃይል ሆቴልን ታውቀዋለህ?"

"አውቀዋለሁ"





"የሆቴሉን ባለቤትስ?"

"አላውቃቸውም"

"አቶ እውነቱ ሞላ ይባላሉ። ልታውቃቸው ይገባ ነበር። የተከበሩ ትልቅ ሰው ናቸው። የትውልድ መንደራቸው ጎጃም ላይ በገንዘባቸው ቤተክርስትያን ያቆሙ የታወቁ አማኝ ናቸው። ብዙ ባለስልጣናትንም ያውቃሉ። አንተንም ሊረዱህ ይችላሉና ይህን እድል ተጠቀምበት።"

"ያልከው ገብቶኛል። ስራው ግን ምንድነው?"

"ሁለት መንታ ልጆች አሏቸው። 3ኛ ክፍል ይማራሉ። እነሱን በየቀኑ ማታ ማታ ታስጠናለህ። በወር 25 ብር ይከፈልሃል። ይስማማሃል?"

እነሆ! በዚህ መንገድ ደሞዝተኛ ለመሆን በቃሁ።

የሚያሳዝነው ነገር ግን ስራዬን ቀጥ ብዬ መስራቱን ትቼ አንድ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በእድሜ እኩያዬ ከሆነችው ከመንትዮቹ ታላቅ እህት ጋር ፍቅር ይዞኝ አረፈው። እንደ እሳት የሚፋጅ ነበልባላዊ ፍቅር ውስጥ በመውደቄ በዚያን ወቅት ደሞዝ ባይከፍሉኝ እንኳ መንትዮቹን በነፃ ለማስጠናት ፈቃደኛ ነበርኩ።

ልጅቱ ባጋጣሚ ማንበብ ትወድ ነበር።

ትኩረት መሳብ ከቻልኩ በሚል በየቀኑ አንድ አጭር ልቦለድ በመፃፍ ልጅቱን ለመማረክ ስቃይና ፍዳ መቀበል ጀመርኩ። ከዚህ ሌላ ልጅቱን ለመማረክ የምችልበት አንዳችም ማግኔት አልነበረኝም። ያም ቢሆን ማግኔት ሆኖ ልጅቱን ለመሳብ ስለማገልገሉ እርግጠኛ መሆን የሚቻል አልነበረም። በመሰረቱ እንደ ቦዮቹ ወይም ኬክ ጋጋሪዎቹ እኔም የዚያ ግቢ ተቀጣሪ ሰራተኛ ነኝ። ስራዬ ህፃናቱን ማስጠናት ቢሆንም እንኳ ልጅቱ ከጉልበት ሰራተኞቹ በተለየ ልታየኝ አትችልም ነበር። በየእለቱ ማታ ማታ መንትዮቹን ወደ ማስጠናበት ክፍል ብቅ ማለቷ አልቀረምና ግን ተስፋ አሳደርኩ።

ብዙውን ጊዜ እንደልማዴ አዳማጭ ነበርኩ።

እሷ ስታወራ በጥሞና አዳምጣታለሁ። በብዛት ስለ እንግሊዝኛ ሙዚቃዎች ትነግረኛለች። እኔ ምኑንም አላውቀው። በርግጥ እህቴ ቴፕ ነበራት። ነገር ግን ቀን ቀን የእህቴ መኝታ ክፍል ስለሚቆለፍ ቴፑም አብሮ ይቆለፍበታል። ስለዚህ ሙዚቃ

አዳምጬ አላውቅም። ቲቪም አልነበረንም። እህቴ ቲቪ እገዛለሁ ብላ እቁብ ገብታ ነበር። ልክ እቁቡ ሲደርሳት አሳቧን ለወጠችና ሶፋ ገዛች። በመሆኑም ልጅቱ ስለ ምእራባውያን ሙዚቃ ስታወራልኝ አንዲት ቃል አስተያየት እንኳ መስጠት አልችልም ነበር። የምትጠራቸው የሙዚቀኞች ስም ለኔ ባእድ ነበሩ። ቢቸግረኝ እንደ ምንም እያልኩ መፅሃፍ የማንበብ ልምዷን እንድታዳብር ገፋፋሁዋት። ስላነበበቻቸው መፃህፍት ታወራልኝ ዘንድ አደፋፈርኳት። ቀስበቀስም ለመደችው። እንዲያውም በግልባጩ ወደደችው። ከትምህርት ቤት እንደተመለሰች ልብሶቿን ትቀያይርና ወደኔ መብረር ሆነ፣

"የሚነበብ አልያዝክም?"

"ይዤያለሁ"

በነጋታውም እንዲሁ፣

"ዛሬስ ምን ይዘሃል?"

"ዛሬ አሪፍ ፅፌያለሁ። በሳቅ ትሞቻለሽ። ያዢ ይቺን"

ሌላ ቀን ደግሞ ሁለት ገፆች ወረቀት እያቀበልኳት፣

"እስኪ ይቺን አንብቢ! የቆንጆ ሴት ታሪክ"

የምስላቸው ሴት ገፀባህርያት መልክና ጠባይ ሆን ብዬ እሷን እንዲመስሉ ስለማደርግ፣ ይህን ሳትረዳ አልቀረችም። በአጭር ጊዜ ውስጥ ከምፅፋቸው ፅሁፎች ጋር በፍቅር መውደቅ እንደጀመረች ተረድቼያለሁ። እሷኑ በቃላት ፎቶግራፍ ስለማነሳት፣ በየቀኑ ፎቶዋን የማየት ጉጉቷ እየጨመረ ነበር። ስለዚሁ ጉዳይ በግልፅ ነግሬያት አላውቅም። እሷም አልጠየቀችኝ። "ሃና" የሚል ስም የሰጠሁዋት ገፀባህርይ የምፅፋቸው ትረካዎች ውስጥ ሁሉ ስላለች በልቧ ሃና የራሷ ምስል መሆኗን ተረድታው ሊሆን ይችላል። ትንፋሿን ውጣ በጉጉት ስታነብ አስተውላታለሁ።

ቀስ በቀስ ከትረካዎቹ መሃል እየመረጠች ለታላላቅ ወንድሞቿና ለእህቶቿ ማስነበብ ጀመረች። ወደ ጓደኞቿም ማሻገር ጀመረች። ይህም በመሆኑ ባጭር ጊዜ ውስጥ የቤተሰባቸው አካል አደረጉኝ። እንደ ወንድማቸውም ተቀበሉኝ። እኔም ሙሉ በሙሉ ራሴን እዚያ ቤተሰብ ውስጥ ጨመርኩት።

አንድ ቀን አቶ እውነቱ "ኦሮማይ" የተባለውን በወቅቱ ተከልክሎ የነበረ መፅሃፍ ይዘው መጡ። መፅሃፉን ለማንበብ





መጓጓቴን አዩናም እንዲህ ሲሉ ጠየቁኝ፣

"ምን ያህል ጊዜ ይበቃሃል?"

"አንድ ሙሉ ቀንና ሙሉ ሌሊት"

"ከግቢ ሳትወጣ እዚሁ ሆነህ ጨርሰው" ብለው ሰጡኝ።

አይኔ እስኪያብጥ ድረስ መፅሃፉ ላይ አፈጠጥኩ። ሳልመገብና ሳልጠጣ፣ ከተቀመጥኩበት ሳልንቀሳቀስ አንብቤ ጨረስኩት። ስጨርስ በስቃይ ተቦርቡሬ ነበር። ፊያሜታ፣ ጋዜጠኛው ፀጋዬ ሃይለማርያም፣ ፓራዲዞ፣ ስእላይ፣ ኢሳይያስ አፈወርቂ፣ ቢሮክራሲ፣ ኦሮማይ፣ ናቅፋ፣ ሰለሞን በትረጊዮርጊስ፣ ኮሎኔል ታሪኩ የመሳሰሉ ስሞችና ቃላት አእምሮዬ ላይ ተመርገው ቀርተው ነበር። በርግጥም በአሉ ግርማ ይህን ከፃፈ በሁዋላ በህይወት ሊኖር እንደማይችል ርግጠኛ ሆንኩ። "በአሉ ግርማ በህይወት የለም" እያልኩ ነበር ለራሴ። "በአሉ ለዘላለሙ አይኖርም። ዳግም አይፅፍልንም።" ይህን ማሰቡ ብቻውን ወደ እብደት ሊወስደኝ ምንም አልቀረው። በአሉ ግርማ እውነት ፃፈ። እና ሞተ...

ንጋት ላይ "ኦሮማይ" የተባለውን መፅሃፍ ለአቶ እውነቱ ስመልስላቸው የተሰፋ እንጥፍጣፊ አልነበረኝም። "በአሉ ግርማ ሞቶአል" የሚለውን ማሰቡ እንደ ቅዠት መልሶ መላልሶ ያባንነኛል። የበአሉ ግርማ ገፀባህርያት ለኔ ምንጊዜም ህያው ነበሩ። አበራና ሉሊት፤ ሃዲስና አይናለም፤ ደርቤ እና ሂሩት፤ ሲራክና ፅጌ፤ እና አሁን ደግሞ ፀጋዬና ፊያሜታ። የበአሉ ብእር እዚሁ ላይ አበቃ!

ኦሮማይ!

በአሉ ሌሎች መቶ መፃህፍት ሊፅፍ እየቻለ ጉዞው ተገታ። ለምን? እኮ ለምን? መደብደብና ጨለማ ቤት ውስጥ ማሰር ብቻ ለምን አልበቃቸውም? በርግጥ እንደሚወራው በአሉ ግርማ ሞቶ ይሆን? ምንም ይፃፍ ምን በአሉ ግርማ በህይወት እንዲኖርና እንዲፅፍ ብቻ እየተመኘሁ ነበር።

*(ኒኮላይ ጎጎል ይፅፈው የነበረውን ድርሰት አቃጥሎ ራሱን በገደለ ጊዜ፣ ኢቫን ቱርጌኔቭ ለጓደኞቹ በፃፈው ደብዳቤ ላይ እንዲህ ሲል ጠቅሶ ነበር፣*

*"ይህንን መራራ ሃዘን ለመገንዘብ የግድ ሩሲያዊ መሆን*

*ያስፈልጋል። ጎጎል ለኛ ራሳችንን ነበር።"*

*እኔም እንዲያ ያለ ስሜት ነበር የተሰማኝ። በአሉ ግርማ እኔኑ እራሴኑ ነበር። የሱ መንፈስ እኔ መንፈስ ውስጥ ነበር። ከ"ኦሮማይ" ይልቅ "ሃዲስ" የተባለውን ትረካ ይበልጥ እንደምወደው አውቃለሁ። በአሉ ግርማ ለኦሮማይ ከሚገባው በላይ ብዙ ዋጋ ከፈለ። ርግጥ ነው፣ በወቅቱ ልባችን ዘንድ የሚደርስ ሚስጥር ሹክ ብሎን ነበር። ትንቢት ነግሮን ነበር። አዲስ ነገር ለመግደል የተፈጠርን "ጉዶች!" ነበርንና በአሉ ግርማ እያየነው ተበላ። ሳናለቅስ ተቀበረ። መቃብሩም አልታወቀ - እንደ ሙሴ! የራሱ ጎጆም አልነበረውም - እንደ አብርሃም! ነቢይ ነበር በአሉ። መቃብሩ እንደማይታወቅ አስቀድሞ ነግሮን ነበር። ቃሉ ተፈፀመ። ነቢይነቱ ቀርቶብን እንደ ደራሲ ቢኖርልን በተሻለን።)*

በዚያን ሰሞን አቶ እውነቱ የበኩር ሴት ልጃቸውን ለማየት አሜሪካ ደርሰው መጥተው ነበር። ከአሜሪካ በተመለሱ ሰሞን አንድ ምሽት መንትዮቹን አስጠንቼ ስወጣ እሳቸውም ከግቢው ሲወጡ አገኙኝና እስከ ቤቴ ሸኙኝ። በመንገድ ላይም እንዲህ ሲሉ አጫወቱኝ፣

"አሜሪካኖቹ የትና የት ገስግሰዋል። ሰላም አላቸው። ጠንካራ ሰራተኞች ናቸው። እዚያ የሃብታም ልጅና የድሃ ልጅ የሚባል ልዩነት የለም። ሁሉም ጠንክሮ ይሰራል። እኔ በእግዚአብሄር እርዳታ እዚህ ጥሩ ሰርቼያለሁ። ልጆቼ ግን ልባቸው ወደ አሜሪካ ነው። ክብር በሃገር ነበር። ይሄ ሃገር ሃብታም ሃገር ነው። ሰላም ብቻ ነው የሚያስፈልገው። ሃገራችን ሰላም አግኝታ ባለ ፀጋ እንዳትሆን የሚፈልጉ ጠላቶች አሉን። ጦርነት ብቻ ሆነን ቀረን። የእግዚአብሄር ቁጣ ነው..."

*የመጀመሪያዬን ማስታወሻ መያዝ የጀመርኩት ያን ቀን* ሲሆን፣ የ16 ሉክ ደብተር ላይ ስለ አሜሪካ እና ስለ ስደት፣ *ጦርነቱ ተስፋ ቢስ ሊያደርገን እንደበቃ፣ ያሰፈርኩትን በነጋታው* ወስጄ ለአቶ እውነቱ አሳየሁዋቸው።

*መነፅራቸውን ሰክተው* በጥንቃቄ አንብበውት ሲያበቁ እንዲህ ሲሉ *መከሩኝ፣*

"የነገርኩህን ልቅም አድርገህ ይዘሽዋል። ቢሆንም ግን አያያዙ ላይ ተጠንቀቅ። በቀጥታ 'እገሌ ነገረኝ' ብለህ መፃፍ ደግ





አይደለም። የሰው ስም አትጥቀስ። ስም እየለወጥክ ብትይዘው የሚሻል ነው። የኔን ስም እንዳለ ፅፈኸዋል። እንደሱ አይደረግም። 'ወረቀትና ሞኝ የያዘውን አይለቅም' ይባላል። ይሄ የፃፍከው በርግጥ ክፋት የለውም። እኔ የነገርኩህ መቼም ሁሉም ሰው የሚያውቀውን ነው። ከዚህ ባሻገር ግን የፖለቲካ ወሬዎችም አሉ መቸም። ባለፈው ያነበብከውን፣ 'ኦሮማይ' የተባለውን መፅሃፍ የፃፈው ሰው ዛሬ የት እንዳለ አይታወቅም። ፖለቲካ ውስጥ መግባት ከባድ ዋጋ ያስከፍላል..."

"በአሉ ግርማ ተገድሏል ይባላል!" ስል በፍጥነት አስተያየት ሰጠሁ። አቶ እውነቱ በታከተ ስሜት ትከሻዬን ያዙኝና እንዲህ አሉ፣

"ስለ መገደሉም ቢሆን የተረጋገጠ ነገር የለም። የዋህ አትሁን። እንደሱ ተብሎ አይወራም። ከእኛ ጋር ቤተሰብ ነህ። ከኛ ጋር እንደምትጨዋወተው ደጅ ሄደህ እንደሱ ካወራህ ልክ አይመጣም። ማን ምን እንደሆነ በምን ይታወቃል?"

ከዚያም እንዲህ አሉኝ፣

"ልጆቹ እንዴት ናቸው ለመሆኑ?"

"ደህና ናቸው። ምንም አይሉም"

"አንተስ እንዴት ነህ? የሚቸግርህ ነገር አለ?"

"ምንም የለም። ደህና ነኝ"

"መልካም! በል ሂድ እንግዲህ..."

* * *

የመንትዮቹን እህት ስነግጥም ማዳመጥ ላስለምዳት ጥረት ጀምሬ ነበር። በመጀመሪያው ቀን ሙከራዬ ለፀፀት በቃሁ።

አባቷ አበበ ቢቂላን በጣም ያደንቁትና ይወዱት ነበር። እሷም ተመሳሳይ ስሜት ሊኖራት ይችል ይሆናል ብዬ ገመትሁ። እናም ፀጋዬ ገብረመድህን ለአትሌቱ የቋጠሩለትን ስንኞች በቃሌ አጠናሁና ማታ ላይ ዘፈንኩላት፣

የምድር አለሙ ገሞራ - አገሩን በክብር ያስጠራ፣
ሳተናው እግረ ጆቢራ - ሎጋ ቢቂላ ዋቅጅራ፣
ባገር ፍቅር ልቡን ሞልቶ - ላቡን ነጥቦ የዋተተ፣
የአለምን ጀግና በአድናቆት - በቅን ቅናት ያሸፈተ፣
አልሞተም እንበል እባካችሁ! - አበበ እንጂ መቼ ሞተ?

ብዙም ሳይጥማት ቀረ።

ይልቁን የእንግሊዝኛ ዘፋኞችን ግጥሞች የገለበጠችበትን ደብተር አውጥታ ታነብልኝ ጀመር። ካነበበችልኝ ሶስት የዘፈን ግጥሞች አንዱም ያልገባኝ ሲሆን፣ ይሉኝታ ይዞኝ ራሴን ላይ ታች መነቅነቅ ብቻ ሆኜ ቀረሁ። የዚያን እለቱ ጦስ በዚያም አላበቃ። ግጥሙን ማንበብ ካበቃች በሁዋላ የዘፋኞቹን ታሪክ ታወጋኝ ቀጠለች፣

"እገሌ ከእንትና ጋር ሆኖ የዘፈነውን ብትሰማው? ሩፋኤልን! ማርያምን! ትወደዋለህ! ደሞ እንትና እንትናን አግብቶአት ሲያበቃ፣ በሶስተኛው ወር ጓደኛዋን እንደገና ወደደና ያቺን ፈትቶ እከሊትን አገባትና ሰርጋቸው ላይ እንትን የተባለውን ዘፈን እንደዲዘፍን ታዋቂው ጓደኛው እንትና ጠየቀውና፣ ሁለት እህትማማቾች ደግሞ ፈርምልን ሲሉት፣ ስልካቸውን ከወሰደ በሁዋላ ሁለቱንም ለየብቻ እያገኘ፣ ከዚያ እህትማማቾቹ በዚህ ምክንያት ሲጣሉ..." እያለች አድክማ አድክማ ለቀቀችኝ።

ከዚያ ወዲያ በድጋሚ የግጥም ማጠራቀሚያ ደብተሯን እንዳታነሳብኝ በመስጋት የግጥም ወሬ እሷ ፊት ማንሳት ተውኩ። የዘፋኝ ወሬ ድንገት ከተነሳም ቶሎ ብዬ ወሬ እለውጣለሁ።

አባቷ የጉጃም ባህላዊ ዘፈኖችን በጣም ስለሚወዱ ብዙ ጊዜ ዋሽንትና መሰንቆ ነክ ሙዚቃዎች በቤቱ ውስጥ ይከፈቱ ነበር። እነዚያ ድምፆች ይዘውኝ ወደ ሌላ አለም ጭልጥ ይላሉ። መንትዮቹን እያስጠናሁ ከሩቅ የሚመጣው የዋሽንት ዜማ መንፈሴን እየሰረቀው በተቀመጥሁበት ፈዝዤ፣ አይኖቼን በመስኮት ወደ ውጭ እሩቅ እሰዳቸዋለሁ።

አንዳንድ ጥቃቅን ምኞቶችም ነበሩኝ፣

በተለይ ግን "የራሴ ሙዚቃ ማጫወቻ ሬድዮ ቴፕ ቢኖረኝ" የሚል ምኞቴ ይበልጥ ከፍ ያለ ነበር። ሬድዮ ቴፕ ቢኖረኝ ዋሽንትና መሰንቆ መሰል ሙዚቃዎችን ሰብስቤ፣ ፀጥ ያለ ኮረብታ ላይ ተቀምጬ፣ መፃፍ! ያለማቋረጥ መፃፍ! በቃ ዝምብሎ መፃፍ! ስለገበሬዎች፣ ስለእናቶች፣ ስለወታደሮች፣ መፃፍ!

መፃፍ እንዴት ደስ ይላል?

ለመሆኑ የመፃፍን ያህል የሚያረካ ነገር ይኖር ይሆን?





ወፍራም መፅሃፍ!

ቶልስቶይ እንደሚፅፈው፣ እንደ በአሉ ግርማ! እንደ ፀጋዬ ገብረመድህን ቅኔዎችን መቋጠር፣ ድምቢጥ ወፍ የመሰሉ ውብ ቃላት፣ እንደ ቀጫጭን ጅረቶች፣ ጋዛውን እያስተኙ እንደሚጓዙ...

እንዲያ እያልኩ አልም ነበር።

ይህ ምኞቴ ከጥቂት አመታት በሁዋላ በፈለግሁት አይነትና ደረጃ በእጥፍ እንደሚሟላልኝ ባውቅ ኖሮ፣ ያን ያህል በተቃጠለ ስሜት ህልም ውስጥ ባልገባሁ ነበር።

ዳሩ የህይወት ጣፋጭነቷ ይኸው አይደል?

መጪውን ካወቅነውማ ምኑን ኖርነው? ሃዘንና ደስታ ድንገት ይመጣሉ፣ ድንገት ደግሞ ይሄዳሉ። ሃብትም እንዲሁ። ይመጣል፣ ይሄዳል። ወጣትነትም ያልፋል። ማርጀትም ፀጋ ነው። የማርጀትን ፀጋ የሚያገኝስ የታደለ አይደል? ስንቶች እርጅናን ሳይቀምሱ ረግፈዋል?

ህይወት እንዲሁ ናት።

አንዳንድ ጊዜ ትዝታና ፀፀት አብረው ይመጣሉ።

"ያኔ ይህን አድርጌ ቢሆን ኖሮ" የሚል ነገር እንደ ነፋስ ሽው እያለ አእምሮን አቋርጦ ያልፋል። ህይወት ግን መች እንዲያ ሆና? ወደፊት ብቻ ናት። የሚጣፍጠውም እንዲያ ነው። ህይወት! ረጅም የምትመስል አጭር። እና ህይወት ሃዘንና ደስታን በአንድ አገልግል ቋጥራ ከሚቀረን ጊዜ ጋር አብራን ትጓዘዋለች...

* * *

ለአንድ አመት ያህል መንትዮቹን አስጠናሁ።

በዚህ የአንድ አመት ጊዜ ቆይታ በመቶዎች የሚቆጠሩ ምርጥ የስነፅሁፍ ስራዎችን በጥንቃቄ ያነበብኩ ሲሆን፤ ከ50 በላይ አጫጭር ትረካዎችንና ሁለት ረጃጅም ልቦለድ ድርሰቶችን ለመፃፍ ችዬ ነበር። ከእነዚህ ድርሰቶች የተመረጡትን ከጓደኞቼ ባሻገር አንጋፋዎቹ ደራስያን ጭምር እንዲያነቡልኝ ሞክሬያለሁ። በዚሁ የአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ሃዲስ አለማየሁ፣ ብርሃኑ ዘርይሁን እና ከበደ አኒሳ የተባሉትን አንጋፋ ጋዜጠኞችና የጥበብ ሰዎች ለመተዋወቅ በቅቼያለሁ።

የደብረዘይት ነዋሪ ከነበሩት የጥበብ አድናቂዎችና የጥበብ ሰዎች መካከልም ፍቅሩ ደበበን ብዙ ጊዜ አገኘው ነበር። ወደ አርቲስት ለማ ጉያ ስቲድዮ ብቅ እያልኩ ስእሎቻቸውን ማየቴም አልቀረ።

*(የአርቲስት ለማ ጉያ ልጆች ጓደኞቼ ነበሩ። በተለይ ደረጄ ለማ አፄ ልብነድንግል ከተባለው የድሆች ትምህርት ቤት አብሮኝ ተምሮአል። ከእህቱ ከነፃነት ጋርም መጠነኛ አግባብ ነበረን። ነፃነት ለማ የአባቷን የጥበብ ተሰጥኦ ሙሉ በሙሉ መውረስ የቻለች ድንቅ ተፈጥሮ ያላት ውብ ልጅ ነበረች። በተለይ "የተቆጣ ፈረስ" ስእሏ ሊያሳብደኝ ደርሶ ነበር። ሁዋላ ልገዛው ፈልጌ እንደተሸጠ ነገሩኝ። የዚያ ቁጡ ፈረስ ምስል እስካሁን አእምሮዬ ላይ አለ። የነፃነት ፈረስ አንዳች ነገር አይቶ በጣም መቆጣቱ ይታያል እንጂ፣ ምን አይቶ እንዲያ አውሬአዊ ገፅታ እንደያዘ ማወቅ የሚቻል አልነበረም። ያ ፈረስ ሰው እየጋለበው ባይሆን ኖሮ ከቁንድዶ ፈረሶች አንዱን መስሎ ይሰማኝ ነበር። ነፃነት ለማ ይህንን መፅሃፍ አግኝታ እንደምታነበው እገምታለሁ። ያንን ቁጡ ፈረስ በድጋሚ ሰርታው "የቁንድዶ ፈረስ" የሚል ስም ሰጥታ ለህዝብ እይታ በድረገፆች ላይ ብታቀርበው እንዴት ይዋጣለት ነበር? ነፃነት ሆይ! አንቺ የቢሾፍቱ ቀጤማ! የት ነሽ?)*

ሃዲስ አለማየሁ በተደጋጋሚ አስመራ መንገድ ከሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው ተቀብለው ምክርና ልምዳቸውን አካፍለውኛል። ከብርሃኑ ዘርይሁን ጋር ያስተዋወቁኝም ሃዲስ አለማየሁ ሲሆኑ፣ ደራሲ ሃዲስ ከመፃፍ ባሻገር እንዴት ማንበብ እንዳለብኝ ቀደም ሲል የማላውቀውን ምክር ሰጥተውኛል፣

"መፅሃፍ ስታነብ ከታሪኩ ባሻገር፣ አረፍተ ነገሮቹን፣ ቃላቶቹንና ፊደሎቹን ሳይቀር በጥንቃቄ አንብባቸው። ብዙ ማንበብ ብቻውን ዋጋ የለውም። የተመረጡ መፃህፍትን በጥልቀት ማንበብ የተሻለ ነው። አንድን መፅሃፍ ሃያል የሚያደርገው ታሪኩ፣ መዋቅሩና የአፃፃፍ ጥበቡ ብቻ አይደለም። ቃላት ስትመርጥ በከፍተኛ ጥንቃቄ መሆን አለበት። 'ዘወትር' ነው ማለት ያለብህ ወይስ 'ሰርክ' ወይስ 'ሁልጊዜ?' 'መንገድ' ነው ማለት ያለብህ ወይስ 'ጥርጊያ?' 'ጎዳና' በሚለውና 'መንገድ' በሚለው መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?





የምታገጣጥማቸው ቃላት ላይ መጠበብ አለብህ..."

ሃዲስ አለማየሁ ሲያሰናብቱኝ ምንጊዜም እንዲህ ይላሉ፣

"ከደብረዘይት ነው የመጣኸው? ለአውቶብስ መሳፈሪያ ይኖርህ ይሆን ታዲያ? ያዝ እስኪ ይቺን?"

የብርሃኑ ዘርይሁን መስተንግዶ ላቅ ያለ ነበር።

ወስዶ ከባለቤቱና ከልጁ ከሚሼል ብርሃኑ ጋር ጭምር አስተዋወቀኝ። ፒያሳ አጂፕ ፊትለፊት ካለው አፓርታማ ውስጥ ይኖሩ ነበር። ወደ ቢሮው ስደውልለት እዚያው አጂፕ ባር ውስጥ ይቀጥረኛል። የመጀመሪያው ቀን ወንበር እንደያዝን እንዲህ ሲል ነበር የጋበዘኝ፣

"ወተት ይሻልሃል ወይስ ቢራ?"

"ቢራ ይሻለኛል"

*(ከብርሃኑ ዘርይሁን እና ከሃዲስ ሃለማየሁ ጋር የነበረኝን ቆይታ፣ "የተሰፉ ቃላት" በሚል ርእስ በመፅሄትና ሁዋላም የ"እፍታ" ቅፆች መፅሃፍ ላይ አትሜዋለሁ። ከእነዚህ ሁለት አንጋፋ ደራስያን ጋር ያደረግሁት ተከታታይ ግንኙነት በትክክል እንዴት ፀሃፊ ልሆን እንደምችል፣ በተለይም አንድን ክስተት እንዴት ባለ ቀላል መንገድ ልገልፀው እንደሚገባ መሰረታዊ የሆነ እውቀት እንድጨብጥ አድርገውኛል። ሁለቱ አንጋፋ ደራስያን በረጅም ዘመን ሂደት ያካበቱትን ልምድ በቀላሉ ያስረከቡኝ ሲሆን፣ እነዚህን ጊዜያትም "ወርቃማ ዘመናት" እያልኩ አስታውሳቸዋለሁ።)*

* * *

እነሆ! ከመንትዮቹ ታላቅ እህት ጋር የጀመረኝ የፍቅር እሳት፣ የልቤ ምድጃ ውስጥ ተዳፍኖ ቁጭ ብሏል። ከስሞ አመድ አልሆነም። ከመላ ቤተሰቡ ጋር ቤተሰባዊ ዝምድና በመፍጠሬ ልገፋበትም ተቸግሬያለሁ። ሊያውስ ከተሳካ አይደል?

በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለሁ አንድ ቀን አንድ አሳዛኝ ሁኔታ ተከሰተ። በርግጥ አሳዛኝ ሊባል አይችልም። አስቂኝ ብዬ ልጠራውም እቸገራለሁ።

እንዲህ ነበር የሆነው፣

መንትዮቹን ለማስጠናት ወደ መኖሪያ ቤታቸው እየተጓዝኩ ነበር። ሲዘንብ ውሎ ገና በማባራቱ አየሩ ቀዝቀዝ

ያለ በጣም ውብ ምሽት ነበር። ወደ ሆራ ሃይቅ በሚወስደው መንገድ ላይ ሳዘግም ከወዲያኛው አስፋልት ዳር ስሜ ተጠራ።

ዘወር ብል እሷ ነበረች።

ከላይ በሸራ የተሸፈነች ወታደራዊ ጂፕ ላይ ተቀምጣለች። ነጭ በነጭ ለብሶ ፓስተር ቢን ሂንን የመሰለ መልከ ቀና ወጣት መሪው ላይ ቁጭ ብሏል። እሷ ደግሞ ከጎኑ ጉብ ብላለች። በዚያችው ቅፅበት፣ ታገል ሰይፉ እንደሚለው ልቤ ውስጥ የተዳፈነው የፍቅር እሳት የአመዱን ሽፋን ገላልጦ፣ የእሳቱን አይን አበራው።

በእጇ ምልክት ጠራችኝ።

አስፋልቱን ተሻግሬ ወደ ጂፗ ሄድኩ።

ሁለቱንም ጨበጥኳቸው፣

"ወደ ቤት ነህ?" ስትል ጠየቀችኝ።

"አዎን"

"አብረን እንሄዳለን ግባ"

ከሁዋላ ተሳፈርኩ።

ጂፗ መንገድ ቀጠለች። ሁለቱ እያወሩ፣ እኔ በዝምታ እንደተጀቦንኩ መኪናዋ ከግቢው ደጃፍ ደርሳ ቆመች። በተፈጥሮዬ ረጋ ያልኩ ነኝ። ምን እንደ ነካኝ ባላውቅም ከጂፓ ላይ እንደ ቄንጠኛ የፊልም አክተር ተፈናጥሬ ለመውረድ ሙከራ አደረግሁ።

የተከሰተው ሁኔታ አሳዛኝ ነው ወይስ አስቂኝ የሚለውን ለመፍረድ አስቸጋሪ ሳይሆን አይቀርም። አዳለጠኝና እጅና እግሬን እንደ ፓራሹት ዘርግቼ፣ ያቆረ ጭቃና ውሃ ላይ፣ በደረቴ ቸንቧህ! አልኩት። ብዙም አልተጎዳሁ። ከጭቃው ላይ ስነሳ ግን ከፀጉሬ እስከ ጫማዬ ጭቃ በጭቃ ሆኜ ነበር።

እሷ ሆዷን ይዛ ፍርፍር! ብላ ስትስቅ አየሁዋት።

እሱ አልሳቀም።

ደንግጦ ሊያፅናናኝ እየሞከረ ነበር።

"ተረፍክ?" አለኝ።

"ደህና ነኝ" ብዬው ወደ ውስጥ ገባሁ።

ልብስ ተሰጥቶኝ ቀያየርኩ።

በዚያን ቀን መንትዮቹን ሳላስጠና ቀረሁ። ደብተራቸውን እንዲያነቡ አዝዤ ከኬክ መጋገሪያው ደጃፍ፣ ስኳር ከሞላ ጆንያ ላይ ተቀምጬ ተከዝኩ። ከግቢው ባሻገር





እድሜ የጠገበ የሸውሸዌ ዛፍ አለ። ወደ ጎጆአቸው ለመግባት የሚሻሙ ቁራዎች ድምፅ አካባቢውን ቀውጢ አድርጎታል። እነዚህኑ ፍጥረቶች እያስተዋልኩ ሳለ ልብሷን ቀያይራ መጣች፣

"ተጎዳህ እንዴ?'

"ደህና ነኝ"

"ቀስ ብለህ ብትወርድ ኖሮ አትወድቅም ነበር"

"ልክ ነሽ"

"ስለሳቅሁ ቅር አለህ እንዴ?"

"ሊያስቅ ይችላል" ስላት እንደገና መሳቅ ጀመረች።

እየሳቀች፣

"ይቅርታ" አለች፣ "...ሰው ሲወድቅ ካየሁ አያስችለኝም። እስቃለሁ። እናቴ እንኳን ብትሆን ያስቀኛል"

እየሳቀች የበረንዳው ደፍ ላይ ተቀመጠች።

የቤት ልብስ ለብሳለች። ጠጉሯን እንደምንም ሰብስባ ወደ ሁዋላ ቋጥራው ነበር። ብታነጥስ ይበታተናል። ጠይም ናት። በጣም እንደምታምር ርግጠኛ ከሆንኩ ይኸው 13 የፀሃይ ወራቶች አለፉ።

በድንገት እንዲህ ስል ጠየቅሁዋት፣

"አብሮሽ የነበረው ማነው?"

"አታውቀውም እንዴ? ጓደኛችን ነው..."

በመሰረቱ ይህን ጥያቄ በማንሳቴ ወዲያውኑ መልሼ በራሴው ላይ ተበሳጨሁ። ምን የሚያስጠይቅ ነገር ነበረው? እሷም በአጠያየቄ ድንገተኛነት ሳትገረም አልቀረችም።

"ምን ሆነሃል?" ስትል አጥብቃ ጠየቀችኝ።

"ምን ሆንኩ?"

"የተበሳጨህ ትመስላለህ"

"ስለ ወደቅሁ ይሆናል"

"ሌላ ያበሳጨህ ነገር አለ እንዴ?"

"ቀናሁ" ልላት አልችልም። ባለፉት 13 የፀሃይ ወራት ሙሉ በየቀኑ እያገኘሁዋት ይህን የመሰለ ነገር አላነሳሁም። መናደዴ ደግሞ የሚደበቅ አይደለም። ስለዚህ ሰበብ ለመፍጠር ተገደድኩ፣

"በሌላ ነገር ተበሳጭቼ ነበር..." አልኩ።

"ምንድነው?" አለች በጉጉት።

"ትናንት አዲሳባ ሄጄ ነበር። ያጫወትኩሽ የጋዜጠኛነት

ስራ የማግኘቱ ነገር የሚሳካ አልሆነም…"

"ምናሉህ?"

"ምንም አላሉኝ። ደብዳቤዬንና ያቀረብኳቸውን ፅሁፎች ያዩት አይመስለኝም። በዘመድ በር ነው የሚሰሩት ይባላል…"

ዘግየት ብላ እንዲህ ስትል አፅናናችኝ፣

"ይሳካልሃል ብዬ ጠብቄ ነበር። ግን ተስፋ አትቁረጥ…"

ነጭ በነጭ የለበሰውን ሰው ወሬ ለማስተባበል እንጂ ይሆን ልነግራት አሳብ አልነበረኝም። ከነገርኳት በሁዋላ ግን ጉዳዩ ሲያሳስባት አድሮ እንደነበር ሁዋላ ተረዳሁ። ጉዳዩን ለአባቷ እስከመንገር ደረሰች…

* * *

በዚያው ሰሞን አእምሮዬ ተቃወሰና ለእብደት በቃሁ። እብደቱ ከ48 ሰአት በላይ አልዘለቀም። በርግጥ ሁዋላ እንደተረዳሁት እብደቴ ከጊዜያዊ የአእምሮ መቃወስ (መዛባት) ያለፈ አልነበረም። ታናሽ ወንድሜ አንድ ችግር እንደ ገጠመው ሲያጫውተኝ ችግሩን ለመፍታት ሙከራ አደረግሁና ሳይሳካልኝ ቀረ። ችግሩን በፈለግሁት መንገድ ልፈታው ባለመቻሌ ቁጣና እልህ እንደ እሳት አነደደኝ።

ከዚያ በሁዋላ ግን የሆንኩትን ላውቅ ሳልችል ቀረሁ።

አእምሮዬን የሳትኩት እዚያው አቶ እውነቱ ግቢ ውስጥ ነበር። አቶ እውነቱ አንዳንድ እርዳታ አድርገውልኝ እንደተሻለኝ ሁዋላ ተነግሮኛል። በዚያች የእብደት ጊዜያት ውስጥ ግን አንድ ታሪካዊ ጀብድ ፈፅሚያለሁ። ይህም ተድላ ሙዚቃ ቤት ደጃፍ ላይ በቦም ማርሌይ ሙዚቃ መደነሴ ነበር። ይህን መፈፀሜን ግን በፍፁም አላውቅም ነበር። ከተሻለኝ በሁዋላ እኔ ስደንስ የተመለከቱ ሁሉ ታሪኩን አጫውተውኛል። አሰቃቂ የሆነውን ይህን የህይወቴን ክፍል አሁን በጣም እወደዋለሁ። ሞትና እብደት አንድ አይነት ሊሆኑ እንደሚችሉም ግንዛቤ አግንቼበታለሁ።

ተድላ ሙዚቃ ቤት ደብረዘይት ከሚገኘው ንግድ ባንክ አጠገብ ይገኛል። እኔ እዚያ ደጃፍ ላይ ህዝብ በተሰበሰበበት በቦብ ማርሌይ ሙዚቃ ደንሻለሁ። ያንን ግን አላውቅም። እጄን ይዛ ትጓዝ የነበረችው ታላቅ እህቴ በኔ መደነስ የምትገባበት





ጠፍቶአት፣ በሃፍረት መሸማቀቋን ጭምር ሰምቻለሁ። ሁዋላ እንደሰማሁት የኔን ዳንስ እየተመለከቱ የደብረዘይት ሰዎች ይስቁ ነበር። የሚያውቁኝ ደግሞ አፍረውና ደንግጠው ሸሽተዋል። ተደብቀው ያለቀሱም እንደነበሩ ሰምቻለሁ። አቶ እውነቱ በበኩላቸው፣ አእምሮዬ የተቃወሰው 'ኦሮማይ'ን በማንበቤ ምክንያት መስሎአቸው ስጋት አድሮባቸው ነበር። በ48ኛው ሰአት አእምሮዬ ወደ ትክክለኛ ቦታው ሲመለስ በቅድሚያ ያነጋገሩኝ አቶ እውነቱ ነበሩ፣

"ምን ነበር የሆንከው?"

አጫወትኳቸው!

የቤተሰብ ጉዳይ ነበር። ታናሽ ወንድሜ ከእንጀራ እናታችን ጋር ተጋጭቶ አንዳንድ ችግሮች ደርሰውበት ነበር። አእምሮዬ ሊሸከመው ያልቻለውን ዝርዝር አጫወትኳቸው።

አቶ እውነቱ እንዲህ አሉኝ፣

"ይህ ነበር ችግሩ? እኔ እያለሁ አንተ እንዲህ ትሆናለህ? እኔ አባትህ አይደለሁም? መጥተህ ለኔ አትነግረኝም? ባለፈው 'ችግር አለ ወይ?' ብዬ ስልህ 'ችግር የለም' አላልከኝም? እንዴት እንዲህ ሊሆን ቻለ? እኔ እያለሁ? ሞልቶ ለተረፈ ሃብት?"

በቁጣ እሳት ለብሰው የሚይዙት የሚጨብጡትን አጡ። እንዲህ ሲሉ ቁጣቸውን አወረዱብኝ፣

"ካልተናገርክ ችግርህን በምን እናውቃለን? 'ጋዜጠኛነት ለመቀጠር አመልክቻለሁ' ስላልከን ከዛሬ ነገ 'የሚመኘውን ስራ ያገኛል' ብለን እየጠበቅን ነበር። እንዲህ ውስጥ ውስጡን በእሳት እንደምትነድ እኛ በምን እናውቃለን? በጣም ነው ያጠፋኸው። እኛ ልጃችን ነው እያልን አንተ ግን ባዳ ነበርክ። 'መንፈሱ ጠንካራ ነው' እያልንህ አንተ እንዲህ በቀላሉ የምትሰበር ኖረሃል! እኛን ነው የበደልከን። በጣም በደልከን። ቤታችን ምን ጎደለው? እንኳን ላንተ ለማንም የምንበትነው አይደለም እንዴ?"

ቁጣቸውን ለማብረድ ጥቂት ቃላት ጣል አደረግሁ፣

"አይቀየሙኝ። የማይሆን ሆኖብኝ ነው"

"ምንድነው የማይሆነው?"

"'ስጡኝ' ብዬ መጠየቅ አልችልም"

"እና ማበድ ይሻላል?"

"ማበድ አይሻልም። መሞት ግን ይሻል ይሆናል።"

በትኩረት ሲያጤኑኝ ቆዩና፣

"መሞት ይሻላል?" ሲሉ ጠየቁኝ።

ምንም መልስ ሳልሰጥ ዝም አልኩ። ጥቂት እንደማሰብ አሉ። ተክዘው በዝምታ ሲመለከቱኝ ቆዩናም ያልጠበቅሁትን ንግግር ተናገሩ፣

"እንዳልከው ከመለመን መሞት ይሻላል። ግን እኛ ላንተ ባዳ ነን እንዴ? እንዴት ነው እኛን የምታየን? ባዳ ከሆንን 'ችግርህን ንገረኝ' አልልህም። መሞትን ልትመርጥ ትችላለህ። እንደ ቤተሰብህ የምታየን ከሆነ ግን በችግርህ ልንደርስ ይገባል። ሰው የመሆናችን ትርጉሙ ደስታንም ሆነ ሃዘንን መካፈል ነው። አይደለም እንዴ? ልጆቼ ይወዱሃል። ጎበዝ ፀሃፊ ነው እያሉ ይነግሩኛል። ሁሉም እንደ ወንድማቸው ያዩሃል። እኛ ላንተ ምንድነን?"

ስሜታቸው በጣም ተነክቶ አየሁና ፀፀት እንደ እሳት በላኝ። ስለዚህ እንዲህ አልኩ፣

"ተሳስቼያለሁ፤ ይቅርታ አድርጉልኝ!"

ዘግየት አሉና፣

"ከልብህ ነው?" ሲሉ ጠየቁኝ።

"ከልቤ ነው፣ ጋሽ እውነቱ!"

"ከልብህ ከሆነ ዛሬውኑ ወንድምህን አምጣውና ከኛ ጋር ይኖራል። እንደ ልጆቼ አስተምሬ ለቁም ነገር አበቃዋለሁ!"

መልስ አልሰጠሁዋቸውም።

በዝምታ አሰብኩበት። ይህ እድል ለወንድሜ ጥሩ ሊሆን ይችላል ብዬ አመንኩ። እናም የእሺታ ቃሌን ሰጠሁ።

"ዛሬውኑ ደብተሮቹን ይዞ ይምጣ"

"ነገ ጠዋት ይገፍው እመጣለሁ" አልኩ።

በነጋታው ታናሽ ወንድሜ አቶ እውነቱ ቤት ጠቅልሎ ገባ። በአጭር ጊዜ ውስጥም ህይወቱ ተለወጠ። ገፅታው ፈካ። አለባበሱ የተለየ ሆነ። ይህ ግን ብዙም አልዘለቀ። አንድ ቀን ፈልጐ ካገኘኝ በሁዋላ እንዲህ አለኝ፣

"አልተመቸኝም"

"ምነው?" አልኩ በጣም ደንግጬ።

"በጣም ይንከባከቡኛል። እንክብካቤያቸው ያሳቅቃል። ልብሱና ምግቡ አይቼው የማላውቀው አይነት ነው። ወደ ትምህርት ቤት ስሄድ ለጋሪ የመሄጃና የመምጫ ገንዘብ





ይሰጡኛል። ያሳቅቃል..."

"ምኑ ነው የሚያሳቅቀው?"

"እንክብካቤያቸው ይጨንቃል"

ምንም ልናገር አልቻልኩም።

ለምን እንዳልተመቸው ስለገባኝ ዝም አልኩ። አቶ እውነቱና ልጆቻቸው ወንድሜን ለማስደሰት ባደረጉት ጥረት በግልባጩ ጭንቀት እንደለቀቀበት ግልፅ ነበር። ይህ ስሜት ርስበርሱ የሚቃረን ቢመስልም ገብቶኝ ነበር። ዳሩ ምን ልለው እችላለሁ? የማደርገው ቸገረኝ። እሱም ፋታ አልሰጠኝም። እንዲህ ሲል የመጨረሻ ውሳኔውን ነገረኝ፣

"እንዳትደነግጥ! ወታደርነት ተቀጥሬያለሁ። ነገ እየሄድኩ ነው። ምናልባት ወደፊት የማንገናኝ ከሆነ ደህና ሁን!"

ይህን ብሎ ከአጠገቤ እንደ ነፋስ ተፈትልኮ ጠፋ። ይህን የምናወራው ባቡር ጣቢያው አጠገብ በሃዲዱ ላይ በእግር እያዘገምን ነበር። ድንገት ከአጠገቤ ተፈትልኮ ሲሄድ ብቻዬን ቀረሁ። ጥቂት ደቂቃዎች ካለሁበት ደንዝዤ የቆምኩ ይመስለኛል። ከደነዘዝኩበት ስነቃ ወደሁዋላ ዞርኩና የባቡር ሃዲዱን ብረቶች እየቆጠርኩ ማዝገም ጀመርኩ። ከተዋጥኩበት ድንዛዜ የነቃሁት፣ የባቡር ጥሩንባ ሰምቼ ነበር። ኦተራይ 101 ባቡር በግምት በሁለት መቶ ሜትር ርቀት ላይ ነበረች። እንደዋዛ ሸርተት ብዬ ሃዲዱን ለቀቅሁላት። ካለፈች በሁዋላ መልሼ ሃዲዱን ያዝኩ። እስኪመሽም እዚያው ሃዲዱ ላይ ቁጭ አልኩ።

ከፊት ለፊቴ ዮሴፍ የተባለው የአርመናዊ ቱጃር ግቢ ተዘርግቶ ይታየኛል። በአትክልቱ እርሻ ውስጥ ወፎች ይንጫጫሉ። አእምሮዬ ውስጥ አንድ ነገር ይላወስ ነበር። እኔ እህቴ ቤት ውስጥ የያዝኩትን ቦታ ብለቅ እህቴ ሁለቱንም ታናናሾቼን ጠቅልላ መያዝ በቻለች። ግን ወዴት መሄድ እችል ነበር? ወዴት?

ወንድሜ ከኮበለለ ከአንድ ሳምንት በሁዋላ አንድ ምሽት ላይ አቶ እውነቱ አስጠሩኝ። ለብቻው ከተሰራ ውብ ሳሎን ቁጭ ብለው መፅሃፍ ቅዱስ እያነበቡ ነበር። አቋረጡትና መነፅራቸውን አወለቁ። ጨበጡኝናም "ቁጭ በል" አሉኝ።

ቁጭ አልኩ።

"ስለወንድምህ ወሬ አለህ?"

"ምንም ወሬ የለኝም""
"ወረቀት አልፃፈም?"
"እስካሁን አልፃፈም"
"የጋዜጠኛነቱስ ከምን ደረሰ?"
"አልሆነልኝም"
"ምነው?"
"ምክንያቱን አላውቅም"
ጥቂት እንደማሰብ አሉና እንዲህ አሉ፣
"ደጋግመህ መሞከር ይገባል። ተስፋ መቁረጥ የለብህም። መቼም ያሰብከው ካልተሳካ ለጊዜው የሚሆን ስራ ልፈልግልህ ይሆን?"
"ከተገኘ ጥሩ ነበር" አልኩ።

በሳምንቱ የታንክ መገጣጠሚያ ፋብሪካ ግንባታ ውስጥ የዚል ክሬይን ረዳት ኦፕሬተር ሆኜ ተቀጠርኩ። ሶስት ወራት ብቻ ሰራሁና ጠላሁት። ከመጥላት በላይም አንገፈገፈኝ። ደሞዙ ጥሩ ነበር። እቃ የሚያነሱና የሚጭኑ መኪኖች ባለሙያ የመሆን ስሜት ግን በውስጤ አልነበረም። በጣም አሰለቸኝ። መንትዮቹን ማስጠናትና ለእህታቸው አጫጭር ትረካዎችን ማንበብ መቶ በመቶ የተሻለ ስራ ነበር። ያለብኝ የኑሮ ችግር እንኳ ስራውን እወደው ዘንድ ግፊት ማድረግ ሳይችል ቀረ። የክሬይኑ ኦፕሬተር በሌለበት ጊዜ ማሽኑን ራሴ መያዝ ጀምሬ ነበር። በአብዛኛው ቱቦ ነበር የምናወርደው። ግዙፍ ቱቦዎች እየተጫኑ ይመጣሉ። እነሱን እያወረድን ስንከምር እንውላለን። በመጀመሪያዎቹ የስራ ቀናት ኩንታሎች የሚመዝኑ ቱቦዎችን የማንሳቱና መሬት ላይ የማሳረፉ ስራ እንደ መዝናኛ አስደስቶኝ ነበር። ሳምንት ሳይሞላ ግን ቱቦዎቹን ማየት አንገሸገሸኝ። እና አንድ ሰኞ ማለዳ የስራ መልቀቂያ ማመልከቻ አስገባሁ። የትራንስፖርት ክፍል ሃላፊው ደብዳቤዬን ካነበበ በሁዋላ በመደነቅ እንዲህ አለ፣
"የሰጠንህ ቦታ በቀላሉ የማይገኝ ቦታ ነበር። አቶ እውነቱ ስለጠየቁኝ እንጂ ክፍት ቦታ አልነበረንም። አታምነኝም! አቶ እውነቱን ስለማከብራቸው 'አይሆንም' ማለት ከብዶኝ፣ ሰው አባርሬ ነበር አንተን የቀጠርኩህ። ምንድነው ይሄ ማመልከቻ? አቶ እውነቱ ይህን ያውቃሉ? ለሶስት ወር ነበር እንዴ ስራውን





የፈለግኸው?"
"ይቅርታ! ሌላ ስራ ስላገኘሁ ነው" አልኩት።
"ነው? አሃ! ጥሩ ነዋ። መልካም እድል እንግዲህ"

*(በታንክ መገጣጠሚያ ፋብሪካው የሰራሁባቸውን ጥቂት ወራት፣ 'ያልተመለሰው ባቡር' የተባለው ልቦለድ መፅሃፌ ላይ በጨረፍታ ዳስሼዋለሁ። የወዝአደርነትን ህይወት የቀመስኩበት በመሆኑም ከወርቃማ ልምዶቼ አንዱ ለመሆን በቅቶአል። በርግጥ በቀዳሚው መፅሃፌ ላይ እንደገለፅኩት ሲያትል ዋሺንግተን ላይም ላባደር ሆኜ ሰርቻለሁ። ይህ የደብረዘይቱ የጉልበት ስራ ያጎናፀፈኝ ልምድ ግን የላቀ ነው።)*

በሳምንቱ ደብረዘይትን ለቅቄ ወደ ምስራቅ ተጓዝኩ።
ከመሄዴ በፊት አንድ ምሽት ወደ አቶ እውነቱ ግቢ ብቅ ብዬ ነበር። ደግነቱ እሳቸው ቤት ውስጥ አልነበሩም። መንትዮቹና እህታቸውን ብቻ አገኘሁዋቸው። ምንም የምናወራው አልነበረንም።
ብቻ ተሰናበትኳቸው።
ዝርዝር ነገር አልነገርኳቸውም። ራቅ ያለ ቦታ ስራ ማግኘቴን ተናገርኩ። እውነቱን ከነገርኳቸው ሊያስቀሩኝ መሞከራቸው አይቀርም ብዬ ሰግቼ ነበር። ከጉዞ እንደማልቀር ባውቀውም ግርግሩን ግን አልፈለኩትም ነበር። ተሰናብቼያቸው ስወጣ "ልሸኝህ" አለችና ጃኬቷን ደረበች።
በጨለማው ውስጥ እያወጋን መንገድ እንደጀመርን ምን አይነት ስራ እንዳገኘሁና የምሄድበትን ከተማ አጥብቃ ስትጠይቀኝ ነገርኳት።
ጮኸች ማለት ይቻላል፣
"ወታደር ቤት? አብደሃል?"
ፈገግ ብዬ ዝም አልኩ።
"ለአባቴ ልንገረውና እሱ የተሻለ ስራ ይፈልግልህ! ወደ ጦርነቱ በፍፁም መሄድ የለብህም።"
"ያለቀ ጉዳይ ነው" አልኳት።
አያያዝኩናም አከልኩ፣
"በርግጥ የወሰንኩት ውሳኔ ህይወቴን ለአደጋ የሚያጋልጥ መሆኑን አላጣሁትም። ሞት ሊገጥመኝ ይችላል።

ዳሩ ግን ወስኛለሁ። ከዚህ መሄድ አለብኝ...”

ምን ይሄ ብቻ?

ስለክብር አመለካከቴን በጨረፍታ አጫወትኳት። ቃል በቃል ባይሆንም፣ ‘ክብርና ተስፋ የሌለው ሰው ምንም ነገር የለውም’ ያልኳት ይመስለኛል። በመጨረሻ እንዲህ ስል አሳረግሁ፣

“በይ ደህና ሁኚ! ብርድ ነው ወደ ቤት ተመለሽ...”

“እስከ መንገዱ ልሸኝህ” አለች።

ወደ ሆራ ሃይቅ እስከሚወስደው አስፋልት ድረስ ሸኘችኝና ተመለሰች። ተቃቅፈን ተሰነባበትን። በዚያች ደቂቃ ውስጤ ተዳፍኖ ይረብሸኝ የነበረው ጊዜውን ያላመዛዘነ የፍቅር እሳት በቦታው አልነበረም። ንፁህ በሆነ የእህትነት ስሜት ተተክቶ ነበር። እንዴት እንዲህ ሊሆን እንደቻለ ’ብርግጥ አላውቅም። ሆኖም ይህ ስሜት ሰላም ሰጥቶኝ ነበር።

በፈጣን ርምጃ ወደ እህቴ ቤት ገሰገስኩ።

እለቱ አርብ ነበር።

ጊዜው ክረምት። 1979።

ከተማዋ ሞቃለች።

የቢራ ጠርሙስ ኳኳታ ከየአቅጣጫው ይሰማል። የአየር ሃይል መኮንኖችና የአይሮፕላን ቴክኒሻኖች ከተማዋ ላይ ፈሰዋል። የአየር ወለድ መለዮ ለባሾች ቢሾፍቱን አጥለቅልቀዋታል። ከዩኒቬርሲቲ ለክረምቱ እረፍት የተመለሱ ተማሪዎች በጎዳናዎቹ ላይ በርጋታ ሲናፈሱ ይታያሉ። ከሆራ እና ከቢሾፍቱ ሃይቆች ግራና ቀኝ በኩል የሚነፍሰው ነፋስ ደብረዘይትን አቀዝቅዞአታል።

ይኸው ነበር...

በነጋታው የምወዳትን የትውልድ መንደሬን ለቅቄ በባቡር ወደ ምስራቅ እጓዛለሁ። ምናልባትም መመለስ ላይኖር ይችላል። ማን ያውቃል? እንደተለመደው በጣም የምወዳትን የቀኝ ጌታ ዮፍታሄ ንጉሴን ዜማ እያዜምኩ ወደ ማረፊያዬ ገሰገስኩ፣

አይዞህ የኛ ጌታ - ነገርህን አትርሳ፣
አለስልሰህ ዝራ - የስንዴውን ማሳ፣
የተዘራችው ዘር - ፈርሳና በስብሳ፣
ታፈራለች ፍሬ - ሙታ ስትነሳ፣





* * *

ደርግ በወደቀ በሁለተኛው ወር ግድም፣ በእለተ ቅዳሜ ወደ ደብረዘይት አቀናሁ። በመንግስት ስልጣን አቻዬ የነበረው አማረ አረጋዊ አብሮኝ ነበር። የትውልድ መንደሬን ላስጎበኘውና ያንን የተከበረ ቤተሰብ ላስተዋውቀው ፕሮግራም ይዤ ነበር። እህቴ ቤት ጥቂት ካረፍን በሁዋላ ወደ አየር ሃይል ሆቴል አቀናን።

ከሆቴሉ ግቢ ስንገባ አንዲት ልጅ የሪሴፕሽኑ በረንዳ ላይ ተቀምጣ የእጇን የጥፍር ቀለም እያስለቀቀች ነበር። ከመኪና ወርጄ ወደሷ ሳመራ ቀና አለች። እንዳትደነግጥ ሰግቼ ነበር። በርግጥም እንዳሰብኩት ሆነ። እጇ ላይ የነበረውን ወርውራ፣ ስሜን በጩኸት ጠርታ፣ ከተቀመጠችበት ተስፈንጥራ ተነሳች...

* * *

ጥሩ የእረፍት ጊዜ አሳለፍን።

እስከ እኩለ ሌሊት ስንጫወት አመሸን። ስለ ጦርነቱ በጠየቀችኝ ጊዜም ስሜታዊ ሆኜ መረር ባለ መንፈስ ምላሽ ሰጠሁዋት። በርግጥ በአጠቃላይ ስሜቴ መራራ ሁኔታ ላይ አልነበረም። ኢህአዴግ ከፍተኛ ስልጣን የሰጠኝ ሰው እንደመሆኔ ደስተኛ ነበርኩ። የነበርኩበት ህይወትና ያሳለፍኩት ገጠመኝ ተጨማምሮ እንዲህ መናገሬን ግን አስታውሳለሁ፣

“ምኑ ይነገራል ብለሽ ነው?

ጦርነት ማለት የሬሳ ክምር ማለት ነው። የቆሰለውና የሞተው ተደራረቦ ተኝቶ ማደር ማለት ነው። አንዳንድ ህሊና ቢስ ዘራፊዎች የቆሰለውን ሰው በማገዝ ፈንታ ከሞተው ወታደር ኪስ ገንዘብ ሲበረብሩ ማየት ማለት ነው።

ስለጦርነቱ ምን ልንገርሽ?

አንዱ ሃበሻ ሌላውን ሃበሻ ሲገድል አየሁ። ጦርነት ምን የሚወራ ይኖረዋል ብለሽ ነው? የተጠበሰ የሰው ስጋ ሽታ በአፍንጫሽ ሙሉ ይገባል። ይሄ ምን ተብሎ ለሰው ይነገራል? የስጋው ሽታ አእምሮን ይረብሻል። የሚያብዱም አሉ። የሚያሳብደው ምኑ መሰለሽ? ተርበሽ እያለ የሞት ሽታ በጥብስ

ተመስሎ ይሸትሻል። የተራበ ሆድ ይህን ሽታ መለየት ሲያቅተው አስተሳሰብ ይናጋል። ይሄ ምኑ ይወራል? ባይወራ አይሻልም?

"በሺህዎች ቁስለኞች ከሬሳ መሃል ወድቀው አየሁ። 'ጨርሱኝ! ወገኖቼ' እያሉ ሲማፀኑ ሰማሁ።

አንዱ በተለይ፣

'በገብርኤል ይዤሃለሁ ጨርሰኝ!' ብሎ ተማፀነኝ። 'አልችልም' አልኩት።

'ካልቻልክ ጠመንጃ አቀብለኝ' አለኝ።

ከሬሳ ጋር ከወደቁት ጠመንጃዎች አንዱን አቀበልኩት። ጠመንጃውን ከያዘ በሁዋላ ምን እንዳለኝ ልንገርሽ?

'አመሰግናለሁ' አለኝ።

ከዚያ ራሱን ገደለ። ይሄ ምኑ ለሰው ይወራል?

"በሞት አፋፍ ላይ የነበሩ ወታደሮች፣ 'ልጆቼን ሜዳ ላይ በትኜ እንዲህ ቀረሁት!' ሲሉ ሰማሁ።

ሌላው ደግሞ፣

'አዬ እናቴ! የልጅሽን አወዳደቅ ባየሽው!' ይል ነበር። 'ሽፍቶች እንዲህ ጉድ ያድርጉን?' የሚሉም ነበሩ።

'አይ እድለ ቢሷ ኢትዮጵያ! እኔስ አረፍኩት! ይብላኝ ላንቺ!' እንዲህ ያለ ንግግርም ይሰማል።

አንድ መስመራዊ መኮንን ደግሞ፣

'እናት ኢትዮጵያ አሉሽ? እንዲህም አድርጎ እናትነት የለ! መካን ኢትዮጵያ' ቢሉሽ ይሻል ነበር' ሲል ሰማሁት። "ምንም ቢታክቱ - ከቶ አይቀርም ሞቱ!" እያሉ በከንቱ የሚሞቱትን ማየት አታካች ነበር።

"ተስፋ ሲሞት አየሁ...

"ተስፋ ሲሞት ሰው ወዲያውኑ ይወይባል። ከቁጭት ጋር የሚሞቱ ይበረክታሉ። ይኸው ነው ጦርነት ማለት...

"ስለኔ ግን ምን ልናገር እችላለሁ?

ከሞት ተርፌ ወያኔ ሆኛለሁ። ቀደም ሲል የነበረኝ ሰብእና ሙሉ በሙሉ ተገፎ ጠፍቶአል። አሁን ለሞት አልደነግጥም። እንባዬ ደርቆአል። ልቤ እንደ አለት ጠጥሯል። ቀድሞ የነበረኝ ሰብአዊነትና ሰብአዊ ርህራሄ ከደሜ ውስጥ ጠፍቶ ይሆን? እያልኩም እሰጋለሁ።

ምን ልበልሽ?





ተለውጫለሁ።

'ለውጡ ጥሩ ነው ወይስ መጥፎ' ብለሽ ብትጠይቂኝ ግን ምላሽ የለኝም። አላውቅም። ደግ ገበሬ ብቻ ብሆን ይሻለኝ ነበር። ስለ አዝርእት፣ ስለ ቡቃያው፣ ስለ ዋልካው ብቻ ማሰብ ይሻል ነበር። ቀብር መሄድ፣ ሰርግ ላይ መገኘት፣ ቤተክርስትያን መሳለም መልካም ነገሮች ነበሩ። አሁን ከውስጤ ሳይጠፉ አልቀሩም። ልመልሳቸው እፈልጋለሁ። ሌላ ምን ይባላል ብለሽ ነው?"

ይህን ሳጫውታት ከንፈሮቿ ኩበት መስለው አንዲትም ቃላት እንኳ መተንፈስ አቅቷት እንደ ዱዳ ተለጉማ፣ አይኖቿ ረጣጥበው በፀጥታ ትመለከተኝ ነበር።

ወደ መፀዳጃ ቤት ሄደች። ፊቷን ተጣጥባም ተመለሰች። ለደቂቃዎች ያህል በዝምታ ከቆየን በሁዋላም በድንገተኛ የመደነቅ ስሜት ተውጣ እንዲህ ስትል ጠየቀችኝ፣

"ወያኔ ሆንክ ማለት ነው በቃ?"

ምላሽ ለመስጠት በጣም እንደተቸገርኩ ትዝ ይለኛል። ዝም ብዬ አቀርቅሬ እያሰብኩ ነበር።

በርግጥም ወያኔ ሆኜ ነበር።

እንደ ወያኔዎቹ በትክክል ወያኔነት ይሰማኝ እንደነበር ግን በርግጠኛነት መናገር አልችልም። በዚያች አጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ለውጦች ተከስተዋል።

እና እንዲህ ስል ምላሽ ሰጠሁ፥

"አዎን፤ ወያኔ ሆኛለሁ"

በዝምታ ስታጤነኝ ቆየችና እንዲህ አለች፣

"እኔ ግን ወያኔ የሆንክ አይመስለኝም"

"ለምን?"

"እንጃ! ድሮ የማውቅህ ሰው ነህ። ወያኔ ሆነሃል ብዬ ማሰብ አልቻልኩም።"

ምላሽ ልሰጥ ሳልችል ቀረሁ። በመሆኑም ርእሰ ጉዳዩን ከዚያ በላይ አልቀጠልንበትም።

ቅዳሜ ምሽት በጥሩ ሁኔታ አለፈ።

በአቶ እውነቱ ሞላ መኖሪያ ቤት ለኔና ለአማረ አረጋዊ መልካም ግብዣ ተደረገልን። ቤተሰቡ ሁሉ አማረን በተግባቢነቱ ፈጥነው ቀረቡት። ከወያኔ ነባር መሪዎች አንዱ መሆኑን

ስነግራቸው ግን ሊያምኑኝ አልቻሉም። አማረ ቀልድ በጣም ስለሚችልበት ወዲያው ተግባብተው ነበርና በአእምሮአቸው ሲስሉ ከቆዩት የወያኔነት ምስል ጋር ፍፁም ተጋጭቶባቸው ነበር። "ወያኔዎች የገቡ ጊዜ" እያሉ ሲያወሩት እየሳቀ ያዳምጣቸው ነበር። እስከ እኩለ ሌሊት አልተኛንም ነበር። በመጨረሻ እዚያው መኝታዎች ተዘጋጅተውልን አሸለብን።

በነጋታው ሰንበት ነበር እለቱ።

ማታ ላይ በተነጋገርነው መሰረት በጠዋት ቀሰቀሰችኝ። አማረ አረጋዊን በተኛበት ትተነው ከቤት ወጣን። እቅፍ አበባ ይዘንም ወደ ሩፋኤል ቤተክርስትያን ገሰገስን።

ብርድ ነበር።

ምእመናን ነጫጭ ለብሰው ወደ ኮረብታው ያቀናሉ። ኮረብታው ደፍ ላይ ስንደርስ ከመኪና ወርደን ቀሪውን ዳገት በእግር ወጣነው። እንባዋ እንደ ጅረት እየወረደም አቶ እውነቱ ሞላ ያረፉበትን መካነ መቃብር አሳየችኝ። ስለ አባቷ አሟሟትና ከአባቷ ሞት ወዲህ ቤተሰባቸው ላይ ስለወረደው ከባድ ሃዘን እያጫወተችኝ ለግማሽ ሰአት ያህል በመካነ መቃብሮቹ መሃልና በአፀዱ ውስጥ ተቀመጥን። ከሩፋኤል ቤተክርስትያን አናት ደብረዘይት ቁልቁል ወለል ብላ ትታያለች። አፀዱ እንደ ገነት ፍፁማዊ በሆነ ፀጥታ የተሞላ ነበር...



- 6 -

# ጥቁር አማሮች

ተማምለን ነበር - በጋራ ልናርስ፣
ቃልኪዳን ነበረን - በጋራ ልናፍስ፣
ማተብ የሌለው ሰው - ሆዱን የሚወድ፣
ዘሬን ሸጦ በልቶ - አደረገኝ ጉድ፣

(ቅኔ - አንዳርጋቸው ፅጌ )
'ኢህዴን የተባለውን የታምራት ላይኔ ድርጅት ተከትሎ ገደል የገባ የወሎ አርሶ አደር የተቀኘው' በሚል ደወል ጋዜጣ፣ ግንቦት 1985 እንዳተመው -

* * *

አለመሳቅ እኮ ይቻላል - አለማልቀስ ነው ጭንቁ፣
የመንፈስን እንጉርጉሮ - በመንፈስ እምባ ማመቁ፣
ውስጥ ውስጡን እየደሙ - በቀቢፀ ተስፋ መድቀቁ፣
ለተስለመለመች እውነት - የደም ደብዳቤ ማርቀቁ፣
በቅሬታ ሰደድ እሳት - ህዋሳትን መጨፍለቁ፣
አለመሳቅ እኮ ይቻላል - አለማልቀስ ነው ጭንቁ፣

(ግጥም - ደበበ ሰይፉ)

ህዳር ወር፣ 2001 ማብቂያ ግድም አንዳርጋቸው ፅጌን አስመራ ላይ አግንቼው ነበር። ምን ማግኘት ብቻ? ሁለታችንም በየፊናችን ስንባዝን ውለን ማምሻው ላይ መገናኘቱን እንደ ልምድ ያዝነው። መጀመሪያ ያገኘሁት ቀን ሰማያዊ ሸሚዝ ለብሶ ነበር። ይህችን ሸሚዝ በየድረገፆቹ ላይ ከሚወጡት ፎቶዎች ላይ አውቃት ነበርና እየሳቅሁ እንዲህ አልኩት፣

"ወያኔ ሰማያዊ ሸሚዝ የለበሱትን ሁሉ መግደል ከጀመረ አንድ ቀን እጁ ላይ ትገባለህ። አታመልጠውም"

"መቀያየሪያ ሸሚዝ አጥቼ እንዳይመስልህ። ያገሬን ሰው

ደግነት ስለምታስታውሰኝ ነው።"

አንዳርጋቸውን በቅርብ ለማወቅ እድል በማግኘቴ በውነቱ በጣም ደስ ብሎኛል። ወደፊት ስለዚሁ የፖለቲካ ሰው ጥቂት ሳላወጋችሁ አልቀርም። እንደሚጠበቀው ግን ወጎቻችን ፖለቲካ ብቻ አልነበሩም። ልክ እንደኔው የስነፅሁፍና የስነግጥም ወሬዎችን አንስቶ ማውራት የማይሰለቸው ሆኖ አገኘሁት። ከአጭር ጊዜ ቆይታችን እንደታዘብኩት አንዳርጋቸው ቅኔዎችን ቢቋጥርና ትረካዎችን ቢጫጭር የበለጠ ሊረካ የሚችል አይነት ሰው ሆኖ ተሰማኝ።

ከኢትዮጵያ ከኮበለልኩ ጀምሮ ከስነፅሁፍ ጋር የተያያዙ ወሬዎችን ሊያወጋኝ የሚችል ሰው እጥረት ነበረብኝና፣ ስራውን የሚጨርስበትን ሰአት እየጠበቅሁ አሳድደው ገባሁ። በርግጥ እንደተመኘሁት ረጃጅም ስነጥበብ ነክ ወጎችን ኰጨዋወት የሚቻል አልነበረም። አንዳርጋቸው ወደ ወቅታዊ ሁኔታው ዞሮ ይገባል።

አንድ ምሽት፣ "ብአዴን" ተብለው ስለሚጠሩት የኢህዴን አመራር አባላት ስናወጋ አንዳንድ ገጠመኞቹን አንስቶ አጫወተኝ፣

"ኢህዴን ከኢህአፓ የወጣ 'ህብረብሄራዊ ነኝ' የሚል ድርጅት ስለነበር አባላቱ ከተለያዩ ብሄረሰቦች የተውጣጡ እንደነበሩ ያው የምታውቀው ነው" ሲል ጀመረና እንዲህ ሲል ቀጠለ፣

"...ከኦሮሞ፣ ከጉራጌ፣ ከአማራ፣ ከከምባታ፣ ከሁሉም ነበሩበት። ተፈራ ዋልዋ ጊሚራ ነው። ካልተሳሳትኩ አሁን የብሄረሰቡ ስም ቤንች ማጂ ተብሎአል መሰለኝ። እንደ በረከት ያለ ኤርትራዊም የድርጅቱ አመራር ላይ አለ። እና በወቅቱ የሃገሪቷን ፖለቲካ በዘር ማደራጀቱን ወያኔ እየገፋበት ነበር። ሁሉንም ብሄረሰቦች የሚወክሉ ተለጣፊ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለማቋቋም የኢህዴን አባላት የዘር ምንጭ እየተጣራ ወደሚፈለጉበት ቦታ ተወሰዱ። እነሱም ከነበረከት አሽከርነት ተላቀው የራሳቸው ድርጅት ጌቶች የሚሆኑ መስሎአቸው ጮቤ ረግጠው ነበር። ከኢህዴን ውስጥ ያልተገኙት ዘሮችም ከሻእቢያ የምርኮኛ ካምፖች ተለቀሙ። በመጨረሻ ኢህዴን ውስጥ ከታች አማራ የሆኑ አባላት ብቻ ቀሩ። አመራሩ ላይ የቀሩት ግን አማራ ባይሆኑም የአመራሩን ቦታ ሊለቁ የማይፈልጉ ነበሩ።





አማራውም ያለተወካይ የቀረበት ሁኔታ ስለነበር፣ የፕሮፌሰር አስራት መአህድ እንቅስቃሴም በመጀመሩ አንድ ወቅታዊ ጥያቄ ተነሳ፣

"ኢህዴን በአማራ አባላት ተሞልቶ ሳለ ህብረብሄራዊ ድርጅት ሆኖ መቀጠል የለበትም። እንደ ወቅቱ ሰልፉን ማሳመር አለበት' የሚል ነገር መጣ።

በኢህአዴግ የድርጅት ኮሚቴ ደረጃ ውይይት ከተደረገበት በሁዋላም፣ 'ኢህዴንን ወደ አማራ ድርጅትነት ለመለወጥ ጥናት ይደረግ' ተባለ። ጥናቱ 'አማራነት ምንድነው?' ለሚለው ጥያቄ ምላሽ እንዲሰጥ መመሪያ ተሰጠ። ከዚህ በሁዋላ ቀጣዩ ጥያቄ፣ 'ጥናቱን ማን ይስራው?' የሚል ነበር..."

አንዳርጋቸው ትረካውን አቋርጦ መሳቅ ጀመረ።

"ምንድነው የሚያስቅህ?" አልኩ።

"ጥናቱን ማን እንዲያካሂድ እንደተወሰነ ታውቃለህ?"

"ማን ሆነ?"

"በረከት ስምኦን"

አንዳርጋቸው ቀጠለ፣

"የኢህአዴግ የድርጅት ኮሚቴ በተሰበሰበበት...እኔም እዚያው ቁጭ ባልኩበት...ሌሎች ጥቂት አማሮችም እንደ ጉቶ በተጎለቱበት ስብሰባ... 'አማራነት ምንድነው?' የሚለውን ጥናት ኤርትራዊው በረከት ስምኦን እንዲያጠናው ታዘዘ። በረከት ስምኦን በአማራ ጉዳይ ላይ ጥናት ያደረገ ምሁር ቢሆን ችግር አልነበረውም። የአማራ ጉዳይ በአማራ ብቻ መጠናት አለበት እያልኩ አይደለም። በረከትን ግን ታውቀዋለህ። ላንተ አልነግርህም። እንግዲህ 'ጥናቱን የማጥናቱ ስራ ለምን ለበረከት ተሰጠ?' ሲባል ኮሚቴው የሚሰጠው መልስ፣ 'በወቅቱ በረከት የፕሮፓጋንዳና የፖለቲካ ሃላፊ ስለነበር ነው' የሚል ይመስለኛል። የሆነው ሆኖ ይህን ጥናት እንዲሰራ ሃላፊነቱን የሰጡት እነ ተወልደ፣ እነ ተፈራ ዋልዋ፣ እነ አለምሰገድ ራሳቸውም አማሮች አልነበሩም። አማራው በሌለበት ስለ አማራው ማንነትና፣ ስለ አማራ ምንነት እየተጠና ነበር። አዛዦቹም ሆኑ አጥኚዎቹ ከአማራው አማራነት ጋር ምንም የስነልቦና ግንኙነት የሌላቸው ካድሬዎች ነበሩ..."

ይህን ስናወጋ መሃል አስመራ ከተማ ላይ አዲስ ከተመረቀው የአሌክሳንደር ፑሽኪን ሃውልት ዙሪያ ከእምነበረዱ

መቀመጫ ላይ ተቀምጠን ነበር።

ፑሽኪን በቀኝ እጁ የላባ ብእር፣ በግራ እጁ ግጥም የፃፈበትን ደብተር ይዞ እጁን ዘርግቶአል። የፑሽኪን ሃውልት ዙሪያ የሳር መስኩ ውበት ልክ እንደ ግጥሞቹ ቀልብን የሚቆጣጠር ነበር። የሃውልቱ ምረቃ ላይ ተገኝቼ ነበር። በርካታ ሩሲያውያንም ነበሩ። በዚያን እለት የፑሽኪን ግጥሞች ሲነበቡ አያልነህ ሙላቱ እና ዶክተር ካሳ ገብረህይወት ታወሱኝ። በዚያ የምረቃ በአል ላይ መገኘት ነበረባቸው። በአያልነህ ሙላቱ የተተረጎመችውን የፑሽኪን "ሃውልት" የተሰኘች ግጥም ሳዜማት ኖሬያለሁ፣

ወደዚህም ቦታ ሰዎች ይመጣሉ፣
የሃውልቱን መንገድ እየተከተሉ፣
እንደ መሰንቆ ምት ወይ እንደ በገና፣
ይኖራል ወደፊት ብዙ ዘመን ገና፣
ሃውልት አቁሜያለሁ ለመታሰቢያዬ፣
ለሚመጣው ትውልድ ለወደሁዋላዬ፣

እና ምሽቱን ሃውልቱ አጠገብ ተቀምጠን አንዳርጋቸው "ስለ አማራ ምንነት ጥናት" ጉዳይ እያወጋኝ ነበር። እንዲህ አለ፣

"...የአማራው ማንነት በበረከት ስምኦን እንዲጠና ታዘዘ!" አያይዞም ቀጠለ፣ "...በረከት ስምኦን ጥናቱን አጥንቶ ጨርሶ ይዞ መጣ። የሚደንቅ ጥናት ነበር። ፅሁፉ ገና ሲጀምር አማራውን ያወግዛል። አማራው ሌሎች ብሄርብሄረሰቦችን እንዴት እንደጨቆነ ይተነትናል። የአማራው ነፍጠኛ ሌሎች ላይ አደረሰ የሚለውን በደልም ያብራራል። አማራው ሌሎች ህዝቦች ላይ ፈፀመ የሚባለውን ግፍ አንድ ባንድ ለቅሞ ፅፎአል። በረከት ይሄን ሁሉ አንብቦ ሲያበቃ፣ 'አማራነት ምንድነው?' ለሚለው ጥያቄ በቂ ምላሽ እንደሰጠ ተማምኖ ወረቀቱን አጣጠፈ..."

አንዳርጋቸው ሲያወጋኝ እያዳመጥኩ ነው።

አይኔ ግን የፑሽኪን ሃውልት ላይ ተተክሏል።

"ሃውልት" የተሰኘችው ግጥም ለእውነት ለቆሙ የሰው ልጆች ሁሉ የቆመች ነበረች፣

ልብ እንደሚነካ - የሙዚቃ ቃና፣
በማነሳሳቱ - በሰዎች ህሊና፣
ሁሉም ይወዱኛል - ያፈቅሩኛል ገና፣





"...አማራነት ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ አማራነትን በማውገዝ የሚጀምር ፅሁፍ! ምን ማለት ነው? በአማራ ላይ ከፍተኛ ጥላቻ አለን የሚሉት እንኳ ይህን ፅሁፍ ሊቀበሉት አልቻሉም። እኔ ተናገርኩ። ባጭሩ ፅሁፉ ተቀባይነት እንደሌለው ገለፅኩ። ተወልደም ይህንኑ ደገፈ። ምንተእፍረት ይዞት ይሁን ከልቡ አላውቅም። ፅሁፉን ግን ሙሉ በሙሉ ተቃውሞታል። እናም ጥናቱ እንደገና እንዲሰራ ታዘዘ።

"...ከምን ያህል ጊዜ በሁዋላ እንደሆነ ትዝ አይለኝም። ምናልባት ስድስት ሳምንታት ሳያልፍ አይቀርም። በድጋሚ ይሰራ የተባለው ጥናት በመዘግየቱ በተለመደው የኢህአዴግ የድርጅት ኮሚቴ ስብሰባ ላይ፣

'ለመሆኑ የአማራው ጥናት ጉዳይ ምን ደረሰ?' ብዬ ጠየቅሁ። ይህን ስጠይቅ ሁሉም ነበሩ። በረከት፣ ተፈራ፣ ተወልደ፣ አለምሰገድ። በረከት ስምኦን ቃል በቃል ምን ብሎ ምላሽ እንደሰጠ ልንገርህ?

'እኔ ያቅሜን ሞክሬያለሁ! እናንተ አማሮች ደግሞ እስኪ ሞክሩት?' እንዲህ ብሎ ምላሽ ሰጠ!"

ጀርባችንን ለሃውልቱ ሰጥተን ወደ ነፃነት መንገድ አቅጣጫ አዘገምን። ፑሽኪን ሆይ! ደህና እደር...

በዚያ በአሰቃቂው በክፉ ዘመን፣
የነፃነት ትግል እንዲያገኝ ብይን፣
ለተበደሉና አቅም ላነሳቸው፣
ጠበቃቸው ሆኜ ስለቆምኩላቸው፣
የማያስታውሰኝ የማይጠራኝ የለም፣
ነገም ከነግ ወዲያም ዛሬም ለዘልአለም፣

አንዳርጋቸውም አጠቃለለ፣

"...ከዚያ ወዲያ ብዙም አልቆየሁ። ድርጅቱን ጥዬ ወጣሁ። ዛሬ 'አማራን ያለኔ የሚወክለው የለም' የሚለው የብአዴን የመመስረቻ ፅሁፍ አማራነትን እንዴት እንደገለፀው ግን እስካሁን አላወቅም!"

* * *

በነጋታው 'ሲኒማ ሮማ' ተብሎ ከሚጠራ ካፌ ብቻዬን ተቀምጬ አንዳርጋቸው ያጫወተኝን እያመነዠክሁ ብዙ ቆየሁ። የበረከትን ንግግር ነክሼ ያዝኳት፣

"እኔ ያቅሜን ሞክሬያለሁ! እናንተ አማሮች ደግሞ እስኪ ሞክሩት?"

የአንዳርጋቸው ወግ ወደሁዋላ ይዞኝ ነጎደ።

በርግጥ አንዳርጋቸው ፅጌ ወያኔ ካምፕ ውስጥ የቆየው በጣም ለአጭር ጊዜ በመሆኑ ብአዴን ከተመሰረተ በሁዋላ የተከሰቱ ታሪኮችን አያውቅም። እርግጥ ነው፣ በወቅቱ ከፍተኛ ስልጣን ላይ የነበርኩ እንደመሆኔ በኢህዴን በሁዋላም በኢህአዴግ ላይ የመጀመሪያውን ተቃውሞ ያሰማው አንዳርጋቸው እንደነበር አውቃለሁ።

*(በወቅቱ የድርጅት ጉዳይ ሃላፊ ከነበረው ከተወልደ ጋር ቀጠሮ ይዞ እንደተወያየበትና "ስታጠፉ የሚያርማችሁ ጠንካራ ድርጅት ከሌለ፣ የኢህዴን ደካማነት ለህወሃት ጊዜያዊ ጠቀሜታ ቢኖረውም ውሎ አድሮ ድርጅታችሁም የትግራይ ህዝብንም ለከፍተኛ አደጋ ያጋልጠዋል" ብሎ መናገሩን ሰምቻለሁ። ስራ በለቀቀበት የመጨረሻ ስብሰባ ላይም ይህንኑ ደግሞ የገለፀ ሲሆን፣ ማስታወቂያ ሚኒስቴር የቀረፀውን ፊልምም ተመልክቼው ነበር። በዚያ የተቀረፀ ፊልም ላይ፣ "ከመቼ ጀምሮ ነው አንተ ለትግራይ ተቆርቋሪ የሆንከው?" ብለው ሲሟገቱት ይደመጣሉ። 'ትግሬ ያልሆነ ስለ ትግራይ አይመለከተውም' የሚል እምነት ያላቸው ሲሆን፣ በአማራና በኦሮሞ ጉዳይ ግን ይመለከተናል ብለው ስለሚያምኑ በክልሎቹ የውስጥ ጉዳይ ጭምር ገብተው ውሳኔ ይሰጣሉ። )*

ከከቦለለ በሁዋላም ግን ብአዴንን መምራት የቀጠሉት ጥቁር አማሮች፣ (አማራ ያልሆኑ ብአዴኖች) ቀላል የማይባል ፈተና ገጥሞአቸዋል። አማራ ከሆኑ አባላት የገጠሟቸውን እንቅፋቶችም እስከ መግደል በሚደርስ የማስወገድ እርምጃ እየፈቱ እስካለንበት ዘመን ዘልቀዋል።

ኢህዴን በይፋ ራሱን ወደ አማራ ድርጅትነት ከለወጠ በሁዋላ በርካታ ተቃውሞዎች ገጥመውታል። የከረረ ተቃውሞ በመሰንዘሩ በመላ አባላቱ ዝናን ያተረፈው ግን "ሌኒን" በሚል





ቅፅል ስም የሚታወቅ የመከላከያ አባል ነበር። እውነተኛ ስሙን አላውቀውም። በመከላከያ ሰራዊት ውስጥ ሁሉም የሚያውቀው በዚሁ ቅፅል ስሙ ነው። ሌኒን እና በረከትን ከማስለቀሱና ከማንቀጥቀጡ በፊትም ግን መለስተኛ ተቃውሞዎች ነበሩ…

በ1987 3ኛው የብአዴን ድርጅታዊ ጉባኤ ባህርዳር ከተማ ላይ ነበር የተካሄደው። አይረሳኝም። ጊዜው ለአማሮች መጥፎ ጊዜ ነበር። ለአማሮች ሊቆረቆር የሚችል አንድም አማራ ስልጣን ላይ አልነበረም። አማራ ነን የሚሉት በአማራ ስም ትኬት የቆረጡ ጥቁር አማሮች ነበሩ።

*("ጥቁር አማራ" የሚለውን ቃል ማን እንዳመጣው አላውቅም። በዝቅተኛ ስልጣን ላይ የነበሩ የብአዴን አባላት ቢራ ላይ እንደ ቀልድ ይጠቀሙበት እንደነበር ግን ትዝ ይለኛል። "Black Market" ከሚለው ቃል ወስደው ሳያዳቅሉት አልቀሩም። አልፎ አልፎም "ፎርጅድ አማራ"፣ 'ኦሪጂናል አማራ" እያሉ ይገልፃሉ። ለአብነት ኩማ ደመቅሳ (ታዬ ተክለማርያም) አማራ ሆኖ ሳለ የኦህዴድ ሊቀመንበር በመሆኑ "ጥቁር ኦሮሞ" ይሉት ነበር።)*

በወቅቱ (1984 ጀምሮ) በኦሮምያና በሶማሊያ የሚኖሩ አማሮች ከሚኖሩባቸው አካባቢ ህዝቦች አያሌ ጥቃት ይሰነዘርባቸው ነበር። "የህወሃት ካድሬዎች ሆን ብለው ግጭቶች እንዲከሰቱ ያደርጋሉ" የሚል ሃሜትና ክስም በስፋት ነበር። በባህርዳሩ ጉባኤ ላይ የብአዴን ካድሬዎች ይህን ጥያቄ አንስተው ነበር። ታምራት ላይኔ ነበር የጉባኤው መሪ። እንዲህ የሚል ጥያቄ ቀረበለት፣

"በርካታ አማሮች ከክልላችን ውጭ ይኖራሉ። ከሚኖሩበት ክልል ህዝብ ጋርም ግጭት ውስጥ እየገቡ ነው። ለምንድነው ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥታችሁ የማትከላከሉላቸው? ህወሃት ትግሬዎችን በየክልሉ አደራጅቶ ህልውናቸውን፣ መብታቸውንና ጥቅማቸውን ያስጠብቅላቸዋል። እናንተስ አማራውን ለምንድነው የማታደራጁት?"

ታምራት የመለሰውን ብዙዎች በሃዘን ያስታውሱታል። እንደሚከተለው ምላሽ ሰጠ፣

"ከክልላችን ውጭ ያለ አማራ በሙሉ ነፍጠኛ ነው።

በነፍጠኛነት ሌሎችን ሊገዛ ሄዶ ነው እዚያ የቀረው። እኛን አይመለከተንም"

በዚያን ጊዜ፣ 'ታምራትም ጥቁር አማራ ሳይሆን አይቀርም' ተብሎ ተወርቶበት በሚዲያ ቀርቦ ጎንደሬ መሆኑን እስከመናገር ደርሶ ነበር። ብአዴን በደል የሚደርስባቸውን አማሮች ለመታደግ ፈቃደኛነት ባለማሳየቱ ከባዱን የህሊና ስቃይ የተሸከሙት የወያኔ አገልጋይ የሆኑ አማሮች ነበሩ።

ሶስት ምርጫዎችም እጃቸው ላይ ነበሩ።

የመጀመሪያው ፕሮፌሰር አስራት እንደገለፁት 'ሆዳም አማራ' መሆናቸውን አምነው ለሆዳቸው ሲሉ ከስርአቱ ጋር መቀጠል። ሁለተኛው ምርጫ፣ ድርጅቱ ውስጥ ሆነው ለውጥ ለማምጣት በህቡእ መታገል። ሶስተኛው ምርጫ ድርጅቱን ለቀው መውጣት ነበር።

በርግጥም የብአዴን አመራር በጥቁር አማሮች ቁጥጥር ስር መሆኑ ከተረጋገጠ በሁዋላ አባላቱ ከሶስቱ አማራጮች አንዱን በመምረጥ ላይ ነበሩ። ድርጅቱ ውስጥ አድፍጠው ለውጥ ይጠብቁ የነበሩ አባላት በአብዛኛው ሁዋላ ላይ ለቅንጅት ድጋፍ በማድረጋቸው እየተመነጠሩ ተባረዋል። ሆዳሞቹ ለጥቁሮቹ እየሰገዱ የግል ህይወታቸውን ማደላደሉ ላይ ብቻ አተኩረዋል። በርግጥ ይህን በማድረጋቸው አንዳንድ ጥቅሞች አግኝተዋል። ቤት የሰሩ፣ መኪና የገዙ አሉ። በአናቱ ጥሩ ይመገባሉ፣ ጥሩ ጥሩ ይለብሳሉ። የተቸገሩ ዘመዶቻቸውንም ከችግር ማላቀቅ ችለዋል። ሌኒንን የመሰሉ ትንታጎች ደግሞ በረከት ስምኦንን በአደባባይ ደም እንባ አስለቅሰው የማይቀርላቸውን ሞት በፈገግታ ጠጥተዋታል። ስለ ጄኔራል ሃይሌ ጥላሁን ከማንሳቴ በፊት ስለ ሌኒን አነሳስና አወዳደቅ በጣም ባጭሩ ላጫውታችሁ።

የብአዴን 3ኛ ድርጅታዊ ጉባኤ ባህርዳር ላይ ከተካሄደ በሁዋላ በየፖለቲካ ድርጅቶቹ ስር ታቅፈው የነበሩ የሰራዊቱ አባላት የህወሃት ሰራዊት ማእከል ሆኖ በአንድ አካል እንዲዋሃዱ ተደረገ። ሰራዊቱ ሲዋሃድ የህወሃት ሰራዊት ኮር እንዲሆን በመደረጉ አማራ ታጋዮች ቅሬታ ያዙ። የኦህዴድ ታጋዮች በዝምታ ይመለከቱ ነበር። ዝምታቸውም ይበልጥ ጎዳቸው፣

"የኦህዴድ ሰራዊት የበታችነት እየተሰማው ግዳጁን በትክክል አይወጣም" ተብለው ተገመገሙና በቅድሚያ እንደ





ጨው ተበተኑ። ከኦህዴድ ይልቅ በውህደቱ ተጠቃሚ የነበሩት የህወሃት የሰራዊት አባላት ቅሬታ ነበራቸው።

"ደርግን ለመጣል በዋነኛነት የታገልነው እኛ ሆነን ሳለ፣ እንዴት የሃላፊነት ቦታዎች ለአማራና ለኦሮሞ ይሰጣል" ሲሉ ቅሬታቸውን ገለፁ።

ብአዴኖች ከኦህዴድ የተሻለ ጉልበት ነበራቸው፣

"ለህወሃት ቁምጣ መልበስ ያስተማረው ኢህአፓ ነው። ሊመፃደቁብን አይገባም። እኛም ታግለናል። ስለዚህ የህወሃት ሰራዊት ኮር ሆኖ እኛ ማሟያ እንድንሆን መወሰኑ ፍትሃዊ አይደለም" ሲሉ ጅራፋቸውን አጮሁ።

ይህን መሰል ማጉረምረም በመበርከቱ በየብሄር ድርጅቱ ውይይትና ግምገማ እንዲደረግ ተወሰነ። የህወሃት ካድሬዎች ወደ መቀሌ፣ አማራ የሆኑ የመከላከያ አባላት ወደ ባህርዳር ተጠሩ። ኦህዴዶች ደብረዘይት አየር ሃይል ግቢ መሰብሰባቸው ትዝ ይለኛል። ስብሰባውን የመሩት አባዱላና ኩማ ነበሩ። በስብሰባው መዝጊያ ላይ መለስ ተገኝቶ፣

"ግኡዝ አትሁኑ! ግኡዝ አካላችሁ ብቻ ከኛ ጋር መሆኑ ይሰማናል። የግኡዝ አካል እጥረት የለብንም። ታንክና አይሮፕላን አለን። ተወልዶ፣ በልቶ፣ የሚሞት አሳማ ብቻ ነው። ታሪክ ስሩ! የሰው ልጅ ታሪክ ሰርቶ ማለፍ አለበት" ሲል አሽሟጥጦ ተመለሰ።

አማሮቹን የሰበሰቡት በረከትና አዲሱ ነበሩ። በታዛቢነት ደግሞ ጄኔራሎች ሁሉም እንዲገኙ ተደረገ። ሳሞራ፣ አባዱላ፣ ባጫ ተካፍለዋል። ከጄኔራሎች በስብሰባው የተካፈለ ብቸኛ አማራ ሃይሌ ጥላሁን ነበር። ካሳ ደሜና አበባው የተባሉት ጄኔራሎች አማራን ወክለው በስብሰባው ላይ ቢገኙም አማራ አልነበሩም።

ገለፃው እንደተለመደው ከተካሄደ በሁዋላ የውይይት መድረክ ተከፈተ። በዚህ ጊዜ ነበር ሌኒን ቆፍጠን ብሎ ከመቀመጫው የተነሳው። ከውይይቱ ርእስ አፈንግጦ እንዲህ ሲል በረከትን አፋጠጠው፣

"በረከት! አንድ ያልገባኝ ነገር አለ!" ሲል ነበር የጀመረው፣ "....ሁላችንም እንደምናውቀው ከብአዴን አመራር አባላት መካከል ጄኔራል ሃይሌ ጥላሁን ብቻ ነው አማራ። ሌሎቻችሁ አማራ አይደላችሁም። በረከት ስምኦን! አንተ ራስህ

ኤርትራዊ ነህ! አዲሱ ለገሰ ኦሮሞ! ተፈራ ዋልዋ ደቡብ ነው! ታደሰ ጥንቅሹ ትግራይ! አመራሩ አማራ ሳይሆን እንዴት ነው በአማራ ጉዳይ ላይ እዚህ የምንነጋገረው? አባዱላና ሳሞራስ እዚህ ስብሰባ ላይ ምን ያደርጋሉ? ይሄ የአማሮች ስብሰባ ነው ከተባለ አማራ ያልሆኑ ከዚህ ስብሰባ ይውጡ! ወይ ደግሞ እንደ ቀድሞአችን ህብረብሄራዊ ሆነን ከቀጠልን ልትመሩን ትችላላችሁ። ኢህዴን 'ብአዴን' ተብሎ የአማራ ድርጅት ሆኖአል ከተባለ፣ ይህ ስብሰባና አጀንዳውም የአማሮች ከሆነ ግን ስብሰባው በአማሮች መመራት ያለበት ይመስለኛል! ለዚህ ጥያቄ መልስ እፈልጋለሁ... "

አዳራሹ በጭብጨባ ጦፈ!!

እንደተለመደው ጫጫታ!! ብአዴኖች መሪ ካገኙ አይቻሉም። ለአመፅ በጣም ቅርብ ናቸው። እንደ እንግሊዞች አባባል ሻይ ብርጭቆ ውስጥ ማእበል ያስነሳሉ። ምክንያቱ ባልታወቀ ምክንያት ደግሞ ፈጥነው ሲበርዱና ሲከፋፈሉ ይስተዋላል።

ሌኒን የለኮሰው አመፅ ወዲያውኑ ታፈነ።

በረከት መድረክ ከያዘ ተሰብሳቢውን ርስበራስ አለያይቶ ሾልኮ የመውጣት ችሎታው የተጨበጨበለት ነው። የንግግር ስልቱም "ሲሞቅ በሹካ" አይነት ነው። እና ያን ቀን 'ሌኒን" የተባለው ታጋይ ላቀረበው አደገኛ ጥያቄ "የስምኦን ልጅ በረከት" ስሜት የሚነካ ምላሽ ሰጠ። አዳራሹን በሞሉት ታጋዮቹ ፊት እንባ ተናነቀው። ለ20 ደቂቃ ያህልም ተናገረ።

"ምነው ይህችን ቀን ባላየሁዋት ኖሮ!" ሲል እንደ ወጋየሁ ንጋቱ ተወነ። እያለቃቀሰ እንዲህ አለ፣

"ምነው ይህችን ቀን ባላየሁዋት ኖሮ? ያኔ በረሃ ላይ ስንታገል ምነው የስልጣን ጉዳይ ሳይነሳ ቀረ? ምነው ኤርትራዊነቴን ያኔ ሳታነሱ ቀራችሁ? የወጣነው ተራራ፣ የወረድነው ቁልቁለት ተረሳ? 'ያልተንበረከክነው' እያልን እየዘመርን ጓዶቻችንን አፈር በምናለብስበት በእነዚያ ዘመናት ምነው የኔ ኤርትራዊነት ሳይነሳ ቀረ?"

እንዲህ ሲል ማስፈራሪያ ቢጤ ደሞ አከለባት፣

'ከእረኛነት እያነሳን አማራ ያደረግናችሁ እኛ አይደለንም እንዴ? አማራነታችሁን የት ታውቁት ነበር?"

መልሶም ንግግሩን በመግቢያው አረፍተ ነገር ቋጨ፣





"ምነው ይህችን ቀን ባላየሁዋት ኖሮ?"

በረከት እንባውን ቸፍ አድርጎ፣ ብሶቱን ሲያንተከትከው አንዳንድ ሆደ ቡቡዎች በመሃረም አይኖቻቸውን ሲያባብሱ ታይተዋል። ውይይቱ ቀርቶ አዳራሹ የሃዘን ቤት ሆኖ ቁጭ አለ። አገጩን መዳፉ ላይ ያስደገፈው ይበዛ ነበር...

አይ አበሻ!?

እኛ አበሾች መቼም የዋህ ነን።

ሰው ሲያለቅስ አያስችለንም። ቁጣችን ከምኔው በርዶ፣ ፕሮፌሽናል አስለቃሽ የምንሆንበትን ፍጥነት ለራሳችንም አናውቀው። አንዳንዱማ አንዴ ለቅሶ ከጀመረ ሟች አያቱን ወይም አማቹን እያስታወሰ ለቅሶውን በዚያው ይቀጥልበታል።

እና ያን ቀን በረከት አስተዛዝኖም አስፈራርቶም አጀንዳውን አስቀየረ። የበረከት ኤርትራዊነት አጀንዳው በዚህ ከተዘጋ በሁዋላ ወዲ ስምኦን የመድፉን መሪ፣ "ብቸኛ አማራ!" ወደተባለው ወደ ጄኔራል ሃይሌ አዞረበት።

"የብአዴን አባላት ጠባቦች አይደሉም። ከሁዋላ ሆኖ ያሳሳታቸው መኖር አለበት። ሃይሌ ጥላሁን 'አማራ እኔ ብቻ ነኝ እያለ ቀስቅሶአል" ተባለ።

ስብሰባው ከእንባ ወደ ቁጣ ዞረ።

ጄኔራል ሃይሌ ጥርስ ውስጥ ገባ። የጄኔራል ሃይሌ ይቆይልንና የሌኒን ፍፃሜ ምን እንደሆነ ልግለፅላችሁ።

ባጭሩ ሌኒን የባድመ ውጊያ ላይ ተገደለ።

ታሪኩ እንዲህ ነበር...

ሌኒን 300 የወታደር ሃይል ያላት ጦር መሪ ነበር። ሌኒን የሚመራት የሻለቃ ጦር ኢላላ የተባለ ቦታ ላይ የማጥቃት ግዳጅ ተሰጣት። ሌኒን ሶስት ጊዜ ያህል የታዘዘውን ለመፈፀም ሞክሮ ነበር። የተሰጠው ግዳጅ ግን የማይቻል አይነት ነበርና ሳይሆንለት ቀረ። የሰው ሃይሉ ተመናምኖበት ሳለም ለአራተኛ ጊዜ እንዲያጠቃ አዘዙት...

በዚሁ ቀውጢ ደቂቃ ይኸው ሁኔታ ደምበ ገዳሙ ከተባለ የማዘዣ ቦታ ላይ ለነበረው ለጄኔራል ሳሞራ ሪፖርት ይደረግለታል። ሌኒን ይመራው ለነበረው የሻለቃ ጦር የተሰጠው ግዳጅ አለመሳካቱ ለጄኔራል ሳሞራ ሪፖርት ሲደረግለት አራት ከፍተኛ መኮንኖች ከሳሞራ ጋር አብረውት ነበሩ። ከእነዚህ

አንዱ ኮሎኔል አበበ ገረሱ ይባላል።

ሳሞራ፣ "ሌኒንን ግደሉት!" ብሎ ትእዛዝ ሲሰጥ አብረውት የነበሩት አራቱም መኮንኖች ሰምተውታል።

ሳሞራ ሌኒን እንዲገደል ትእዛዙን የሰጠው ከወታደራዊ የቅጣት ደንብ ውጭ ሲሆን፤ በመከላከያ ሚኒስቴር የቅጣት ደንብና ህግ ውስጥ ወታደሮች በዚህ መንገድ እንዲረሸኑ የሚፈቅድ አንቀፅ አልነበረም።

ሌኒን እንዲገደል ትእዛዝ የተላለፈው ለወዲ እምበይተይ (ጄኔራል ሃይለስላሴ ግርማይ) እና ለጄኔራል አበባው ታደሰ ነበር። ትእዛዙ ሲተላለፍ በወቅቱ የመድፈኛ አስተባባሪ የነበረው ኮሎኔል ገመቹ አያና እዚያው ነበር። ትእዛዙን መስማቱንም አረጋግጦልኛል።

ጄኔራል አበባው ወደ ሌኒን የበላይ አለቃ (አርባእተ አይኑ ይባላል) ደውሎ ሌኒን እንዲገደል ትእዛዝ ይሰጣል። በዚያች ደቂቃ ደግሞ አርባእተ አይኑ ሌኒንን በወታደራዊው የሬዲዮ መገናኛ መስመር ላይ ሊያገኘው እየሞከረ ነበር። ሌኒን በበኩሉ ለአራተኛ ጊዜ ጉብታዋን ለመቆጣጠር በቀለጠ ውጊያ መሃል ነበር።

በመጨረሻ የሌኒንን ሬድዮ ሌላ ወታደር ተቀብሎ ለአርባእተ አይኑ መልስ ሰጠ። ሬድዮኑን የተቀበለው ወታደር ሌኒን በውጊያው ላይ መሞቱን በኮድ ለአርባእተ አይኑ ገለፀለት። አርባእተ አይኑ ይህንኑ የሌኒንን መሞት ለአበባው ሪፖርት አደረገ። አበባው ለሳሞራ በተመሳሳይ መንገድ፣ "ሌኒን ቀደም ብሎ በውጊያው ላይ ሞቶአል" ሲል ገለፀለት።

በርግጥም ከሳሞራ፣ ከበረከት እና ከአበባው ጋር መግባባት ያልነበረው ሌኒን ከሚመራቸው ወታደሮች ጋር በውጊያው ላይ ሞቶ ነበር። አንድን ሰው ሁለት ጊዜ መግደል አይቻልምና የሳሞራ ትእዛዝ ሳይፈፀም ቀረ...

በሰላም ወቅት ጥርስ የሚነከስባቸው ወታደሮች፣ በውጊያ ወቅት ወደ አስቸጋሪ ውጊያ እንዲገቡ በማድረግ የማስወገዱ ዘዴ በሃገራችን በጣም የተለመደ ነው። በደርግም ሆነ በጃንሆይ ዘመን ሲሰራበት ቆይቶአል። ሌኒን ግን ሃገሬ ለሚላት ሃገር ከሞተላት በሁዋላ ሞት የተፈረደበት ብቸኛው ኢትዮጵያዊ ጀግና ወታደር ሳይሆን አይቀርም። ሌኒን ላይ ተላልፎ የነበረው





የሞት ፍርድ በቀጥታ ከበረከት ጋር የተያያዘ ነው ለማለት የሚያበቃ ማስረጃ የለኝም። ሌኒን በደፋር ተናጋሪነቱና የዘር መድልዎን በመቃወም ጠባዩ ግን ጥቁር አማሮችና የህወሃት ወታደራዊ አዛዦች ጥቁር መዝገብ ላይ አስፍረውት መቆየታቸው ግልፅ ነበር።

*(የሌኒን አስከሬን በኤርትራ ወታደሮች ቁጥጥር ስር ከዋለ በሁዋላ መኮንን መሆኑን ሲያውቁ ኪሱን ፈትሸውት ነበር። ሌኒን ለእጮኛው የፃፈላትን ያልተላከ ደብዳቤ ያገኙ ሲሆን፤ ያንን ደብዳቤም በኤርትራ ሬድዮ አንብበውታል።*

*የሌኒን እጮኛ እዚያው ግንባር ደምበ ገዳሙ ከተባለ ቦታ ላይ የሰራዊት ሃኪም ነበረች። በጣም ቆንጆ ልጅ መሆኗን ሰምቻለሁ። ህይወት ትባላለች። ሌኒን ለህይወት የፃፈላትን ደብዳቤ የኤርትራ ሬድዮ ማንበብ ሲጀምር ህይወት ቁስለኞችን እየረዳች ነበር። ሬዲዮ ይከታተሉ የነበሩ ቁስለኞች ጠርተው የሌኒንን ደብዳቤ እንድትሰማ ሲያደርጓት፣ ጩኸቷን ለቃ፣ ራሷን ስታ ወደቀች ብለው ነግረውኛል።*

*ወጣት ደራሲያን ሆይ!*

*የሌኒን እጮኛ ዛሬም በህይወት አለች። ሃገር ውስጥ መግባት ቢፈቀድልኝ ኖሮ ያቺን የጀግና ጓደኛ ፈልጌ አገኛት ነበር። የኔን ብእር ይዛችሁ፣ ፈልጋችሁ ታገኟት ዘንድ አደራ እላችሁዋለሁ። አግኟት። እናም ይህን የዘመናችንን ትራጀዲ ጥሩ አድርጋችሁ ተርኩልን። በኔ በኩል አልቻልኩም እንጂ የሌኒንን ሙሉ ስምና የህይወት ታሪክ በጨረፍታም ቢሆን እዚህ ማስፈር ነበረብኝ። መረጃዎች አልተሟሉልኝም በሚል ይህን ታሪክ አፍኜ መያዙ ግን ሃጢአት መስሎ ስለተሰማኝ የማውቀውን ያህል ፅፌላችሁዋለሁ።)*

ብአዴን ውስጥ የተሻለ ግንዛቤ ያላቸው ሊባሉ የሚችሉ ሶስት አማራ ጄኔራሎች ብቻ ነው የነበሩት። ተፈራ ማሞ፣ አሳምነው ፅጌና ሃይሌ ጥላሁን። ሁለቱ ጄኔራሎች ከግንቦት7 ጋር በተያያዘው የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ተይዘው ወደ ወያኔ ማጎሪያ ተልከዋል። አበባው ታደሰ አገው ነው ቢባልም ግማሽ ጎኑ ግን ከትግራይ ነው። ሆኖም እንደ አማራ ወኪል ሲታሰብ ቆይቶአል።

ይህን ምእራፍ በምፅፍበት ወቅት በተረጋገጠ አማራነት ሊጠቀስ የሚችል ጄኔራል ቢኖር ዘውዱ እሸቴ ብቻ ነው። እሱም ቅፅል ስሙ፣ "ጄኔራል እሺ!" ሆኖአል። "ለተጠየቀው ጥያቄ ሁሉ እሺ! ይላል፣ ግን አይፈፅመውም" እያሉ ያሙታል። ይህን መኮንን ደርግ ሳይወድቅ ጀምሮ አውቀዋለሁ። በጣም ጥሩ ሰው ነው። "ሰው መግደል ሃጢያት ነው" ብሎ የሚያምን ንፁህ የእግዚአብሄር ሰው ነው። በዚህ ላይ ደግሞ ማንኛውንም አለቃ በጣም ያከብራል። "አለቃ ሊሳሳት ይችላል" ብሎ አያስብም። ሰላምተኛና ሳቂታ ነው። እንደ ሴት ጥርስ ችምችም ያሉ፣ አገዳ ማኘክ የማይችሉ መስታወት የመሰሉ ንፁህ ጥርሶች አሉት። ጥርሶቹን ብዙ ጊዜ ለሳቅ አገልግሎት ይጠቀምባቸዋል። እንደተኮረኮረ ሰው ሲስቅ የሚውል ጄኔራል እንዴት አደርጎ ወታደሮችን ሊመራ ይችላል? ዘውዱ ከደግነቱ ብዛት ሜቆጣት አይሆንለትም። እና ጄኔራል ዘውዱ እንኳን መፈንቅለ መንግስት ሊሞክር፣ ባዶ ዙፋን ቢያገኝ ቁጭ አይልበትም። ምንቸግሮት? እግዜር ሲፈጥረው ዘውድ ጭኖለታል - ዘውዱ!

በተቀረ ከጄኔራል መአረግ በታች የሚገኙ አስቸጋሪ አማራ መኮንኖችና በድርጅት ስራ ላይ ያሉ ካድሬዎች ሁሉ እየታፈኑ አድራሻቸው ወደማይገኝበት አለም በተለያየ ዘዴ ተልከዋል። ፀጋ ሞልቶ የተረፈውን የሁመራ፣ የወልቃይት፣ የዳንሻና የራያ የእርሻ መሬቶች ለህወሃት ያስረከቡት እነዚሁ ጥቁር አማሮች ናቸው። የአማራ ክልል መሬት ህጋዊ ባልሆነ መንገድ እየተቆረጠ በመወሰዱ ጥያቄ ያነሱ ታፍነው ጠፍተዋል። እነ አሻግሬ በለው፣ ስማቸው ጉበዜ፣ መንግስቱ ተበጀ ዛሬ የት ናቸው? ይህን የሚመልስ ጀግና የወያኔ አመራር ከቶ ማነው?

ከላይ የጠቀስኳቸው ሰዎች፣

"አማራውን እያፈናቀላችሁ ለም መሬታችንን ለትግራይ መስጠታችሁ አግባብ አይደለም" ብለው በመናገራቸው በረከት ስምኦን አፍኖ አጠፋቸው።

በአማራው ክልል መሬት ጉዳይ በረከት እንዴት ብቸኛ አዛዥ ናዛዥ ሊሆን ቻለ? በረከት ስምኦንና መለስ ዜናዊ ቁጭ ብለው በአማራው መሬት ጉዳይ ለመፈራረም ችለዋል። ከተፈራረሙ በሁዋላ ደግሞ በረከት አማራ ካድሬዎችን እየሰበሰበ የውሳኔውን ትክክል መሆን ይሰብካል። 'ኢትዮጵያ' እና 'ኢትዮጵያዊነት' የሚለው ቃል አይነሳብን ይላሉ። 'እንግዲያው





አማራ አይደላችሁምና የአማራውን ክልል ለአማሮቹ ልቀቁ' ሲባሉ፣ 'ትምክህተኞች ነፍጠኞች' እያሉ ይሳደባሉ። 'ህወሃት ትግራይ ውስጥ ፋብሪካዎች እየገነባ ነው። እናንተ ግን በአማራው ክልል ዳሽን ቢራ ፋብሪካ ብቻ ነው የገነባችሁት' ብሎ የሚጠይቀውን፣ 'ደመኛ ጠላት! ዘረኛ!' ይሉታል። 'ምቀኛ' የሚልም ይመርቁለታል። ይህን መጠየቅ እንዴት ምቀኝነት ሊሆን እንደሚችል የማብራራት ችሎታ ግን የላቸውም።

ወደ ጄኔራል ሃይሌ ጥላሁን ልመልሳችሁ።

በርግጥ ሃይሌ ከመነሻው ህዝባዊ አመለካከት የነበረው አርበኛ አልነበረም። እንደ አብዛኞቹ የወያኔ አመራር አባላት እጁ በደም የታጠበ ነው። በቀዳሚው መፅሃፌ ጠቁሜው እንዳለፍኩት የአምቦው አዛውንት፣ የድምፃዊት አበበች አባት፣ አቦ ደራራ ከፊኔ እንዲገደሉ ውሳኔ ካስተላለፉት ጄኔራሎች አንዱ ሃይሌ ጥላሁን ነው። ይህ ጥቁር ታሪኩ እንዳለ ሆኖ ሃይሌ በተለይ በሸዋ አማራነቱ ብቻ ከስርአቱ ተፅእኖ እየደረሰበት ፊት ለፊት ሲናጭ ኖሮአል። በመጨረሻም በጡረታ አግልለውት ድምፁ ጠፍቶአል። ስሙ ደብዝዞአል።

ሌኒን ባህርዳር ላይ ካስነሳው ማእበል በሁዋላ ሃይሌ ከነበረበት ስልጣን ተነስቶ ወደ ደብረዘይት አየር ሃይል ተላከ። በወቅቱ የአየር ሃይል አዛዥ ለነበረው ለጄኔራል ጆቤ፣ "ጠብቀው! ተጠንቀቀው!" የሚል ምክር አብሮ ሳይላክለት እንዳልቀረ እንጠረጥራለን።

ሃይሌ ጥላሁን የህወሃትን መከፋፈል ሊጠቀምበት ሞክሮ ነበር። ሳይሳካለት ቀረ። በርግጥ ሃይሌ ከልቡ ለመለስ ታማኝ ሊሆን አይችልም ነበር። አየር ሃይልን ከተረከበ በሁዋላ የጆቤን ደጋፊዎች እንደ ጫት ቃማቸው። ደብረዘይት ላይ አብዮት ተነሳ። አማራና ኦሮሞዎችን፣

"ብሶታችሁን ተናገሩ!" አላቸው ስብሰባ ጠርቶ።

የአየር ሃይል አባላት ቁጭታቸውን ተናግረው ሳያበቁ ጄኔራል ሃይሌ እንዲህ የሚል የትግርኛ መልእክት ደረሰው።

"እስካሁን ያልከውን ብለሃል። አሁን በቃህ!"

ይህ አባባል ሲተነተን፣

"ህወሃትን መቃወም ታክቲክ እንጂ ስትራቴጂ አይደለም። እና ጊዜ ተገኘ ብለህ አትጃጃል" ማለት ነበር።

መለስ ራሱን ካረጋጋ በሁዋላ ሃይሌን ከአየር ሃይል

አነሳው። ሳይቀደም ቀደመው። በዚህ ዘመን አማራ ለሆነ ሰው የአየር ሃይል አዛዥነት ስልጣን ከቶውንም ሊሰጥ አይችልም።

ሃይሌ ጥላሁን በጡረታ እስከተገለለበት እለት ድረስም ድምፁን ከፍ አድርጎ የህወሃት እኩዮቹን ዝርፊያ ተቃውሞአል። ተቃውሞው በርግጥ ለሃገር ከመቆርቆር ነው ወይስ የዝርፊያ ድርሻውን በማጣቱ በርግጠኛነት ማወቅ ይቸግራል። ስርአቱን የማስወገድ ሃሳብ ልቡ ውስጥ ቢኖር ኖሮ ከነበረው የማእረግና የስልጣን ደረጃ አንፃር የማድረግ ብቃቱን ባላጣ ነበር። "ሰው ማለት ሰው የሚሆን ነው፣ ሰው የጠፋ እለት" ይባል የለ?

ወያኔዎችም ይህንኑ ይላሉ።

'አማራው በታሪክ የሚኖር የወረቀት ነብር ነው' የሚለውን ብዙ ጊዜ በአደባባይ ይናገሩታል። በርግጥም በረከት ስምኦን ክልሉን እንደፈለገ እየተጫወተበት፣ ሁለት አሰርት አመታት መድፈናችን ነው። በጥቂር አማሮች የስልጣን ቀንበር ስር የጭቆና፣ የዘረኝነትና የውርደት ጎርፍ በአማራ ምድር እንደ አባይ ወንዝ ሲፈስ በአይናችን የምናይ የአይን ምስክሮች ነን።

ይህን አባባሌን በመምዘዝ፣ "ህዝብና ህዝብን ለማጋጨት" የሚል እሪታ የሚያሰሙ መጣጥፎች መነበባቸው አይቀርም። እኔ እስከማውቀው ግን ጥቁር አማሮች ህዝብ አይደሉም። በጣት የሚቆጠሩ ማጅራት መቺ አደገኛ ቦዘኔዎች ብቻ ናቸው።

በጥንት ዘመን የቡርቃ ወንዝ ውርደትን መሸከም ባለመቻሉ አካሉን ሰብስቦ ከመሬት ስር የመደበቁን ታሪክ ሰምተን ነበር። በዚህ በኛ ዘመን አባይ እና ቡርቃ ውስጥ ውስጡን እየተገናኙ ወግ ሳይጀምሩ አልቀሩም። ወሬው እውነት ከሆነ ከሁለት አንዱ አይቀሬ ይሆናል። አባይ እንደ ቡርቃ አንገቱን ይደፋል። አሊያ ደግሞ አባይና ቡርቃ በአንድነት ተያይዘው በነፃነት መዘመር ይጀምራሉ…



# - ፇ -

# የጀግና አገር ድምቢጥ

አንዲት ፍጡር ካዳንሁ - ባዘን የምትደማ፣
ኖሬአለሁ እላለሁ - ምንም ሳላቅማማ፣
ውጋት የሰቀዛት - አንዲት ነፍስ አግንቼ፣
ከስቃይ ባወጣት - እጆቼን ዘርግቼ፣
ወይም አንዲት ድምቢጥ - ከመሬት አንስቼ፣
ጎጆዋ ባስቀምጥ - እስትንፋስ ዘርቼ፣
ምንም አላፍርበት - ኖሬያለሁ ለማለት፣

(ግጥም - ኤሚሊ ዲክንሰን)
- መንግስቱ ወልደማርያም እንደተረጎመው -

በ1988 የጥምቀት በአል ምሽት በአጋጣሚ የተዋወቅሁዋት አንዲት ልጅ ልቤ ውስጥ ለዘልአለሙ ተሰንቅራ ቀርታለች። በመሆኑም የዚያችን ውብ ጮርቃ ታሪክ በዚህ መድበል ለማካተት ተገድጄያለሁ። አንዳንድ ጊዜ ትዝታ የሚመስል ፀፀት ከአእምሮ ሳይጠፋ ለረጅም ጊዜ ይቆያል። ርግጥ ነው፣ 'የፈሰሰ ወተት አይታፈስም' የሚሉት አይነት ነው። ህሊናዬ ውስጥ የቀረው ቁራጭ ፀፀት ግን በከባድ ጎርፍ እንኳ አይጠረግም።

ይህ ትረካ ይፋ በመሆኑ ያች ልጅ የምታገኘው ጥቅም የለም። ይህን ትረካ አግኝታ ታነበዋለች ብሎ ማሰብም የዋህነት

ነው። ሊያውስ በህይወት ካለች አይደል? ለእኔ ግን መናዘዙ ይሻለኛል። ለሰው ሲነግሩት ቀለል ማለቱ አይቀር መቸም። ህሊናን ለፍርድ ማቅረብ እንደ ቋጥኝ የከበደን ሸክም አውርዶ የመገላገልን ያህል እረፍት ይሰጣል። ቀላል የሚመስሉ አያሌ ክስተቶች በየእለቱ ያጋጥሙናል። በቀላሉ ካለፍናቸው ቀላል ሆነው ይቀራሉ። የሚጣላ ህሊና ካለን ግን ፈተና ውስጥ መውደቃችን አይቀሬ ይሆናል። የገጠመኝ እንዲያ ያለ ነበር...

* * *

ታቦት ሸኝቶ በመመለስ ላይ ያለው ህዝበ - ክርስትያን ጎዳናውን ሞልቶ ይተማል። መኪናዬን በተገቢው ፍጥነት ማሽከርከር ተቸገርኩ። ጡሩንባውን እያጮህኩ መራገም ብቻ ሆነ። እንዲሁ እንደበገንኩ ስጓዝ ሳለ ነበር ያች ልጅ የለከፈችኝ።

"እባክህ ሸ'ኝን?"

የአስፋልቱን ጠርዝ ይዞ ከሚነጉደው የሰው ጎርፍ መካከል አንዷት ልጅ ፈገግታዋን ብልጭ አደረገችልኝ። ሁለት ነበሩ። ከኮረዳዋ ጋር ያለችው ሴት እያነከሰች ነበር የምትጓዝ። ሁለቱም የተበጣጠቀ ነጠላ ቢጤ ተከናንበዋል። በተሰነጣጠቀ ሲሊፐር ኮሮኮንቹን እያደቀቁ ከኔ መኪና እኩል ይራመዱታል። እንደዋዛ አየት አድርጌያቸው መልስም ሳልሰጥ በብስጭት ጡሩንባውን አጮህኩት።

ምንም ተስፋ አልነበረውም።

ህዝበ ክርስቲያኑ አስፋልቱን ከዳር እዳር ሞልቶታል።

"ደክሞን ነው'ኮ። ምናለበት ብትሸ'ኝን?"

አሁን ግን መልስ ሰጠሁ፣

"መንገዱ ተዘግቶ አታዩትም? በእግር ይሻላችሁዋል"

ልጅቱ ወደ ጓደኛዋ እያመለከተች ተለማመጠችኝ።

"እሷን እግሯን ስላመማት ነውኮ"

ድህነት እንዴት አድርጎ እንደተጫወተባቸው ማስተዋል ይቻላል። ችምችም ያሉ ጥርሶቿ ከአይኖቿ ጋር ህብረ-ውበት ፈጥረዋል። በአደፈ ነጠላዋ ስር ምላሱን ያወጣውን ሰማያዊ ሹራብ ደጋግማ ታስተካክለዋለች። ጠይም ናት። ካሮት የመሰለ ውብ አፍንጫ። ከነጠላዋ ሾልኮ የወጣው ጠጉሯ እስኪበቃው አቧራ መጥምጦአል። ማድቤት ውስጥ ስትንደፋደፍ የዋለች ትመስላለች። አብራት ያለችው የምታነክስ ሴት በእድሜዋ ገፋ





ከማለቷ በቀር አለባበሳቸውና ጉስቁልናቸው ይመሳሰላል።

"በገብርኤል! ሸኝን እባክህ?" ለሶስተኛ ጊዜ ጠየቀች።

በትክክል መናገር አልችልም። ከልጅቱ ቡትቶ ስር የተሸሸገውን ውበት ገልቤ በማየት ይሁን፤ አለያ የገብርኤል ስም ስለተጠራ እርግጠኛ አይደለሁም። የወንድነት የስሜት ነፋስ መቼም አቅጣጫው አይታወቅም። እንዳልኩት የትኛው እንደገፋፋኝ ርግጠኛ አልነበርኩም። የሆነው ሆኖ፣

"የት ነው ሰፈራችሁ?" ስል ጠየቅሁ።

"ገርጂ"

"መንገዴ ወደዚያ አይደለማ" አልኩ እያመነታሁ።

"22 ካደረስከን ይበቃናል"

ጥቂት አመንታሁና መኪናዬን ዳር አስይዤ አቆምኩ። የምታነክሰው ልጅ ከሁዋላ ተሳፈረች። ካሮት አፍንጫ ከፊት ገባች። እኔ ራሴ የነጣሁ ነጭ ነጫጭባ የድሃ ልጅ ነኝ። የእነዚህ ግን የተለየ ነው። ድህነት ከነቁሳቁሱ ድንኳኑን ተክሎባቸዋል። አናታቸው ላይ ባንዴራውን እያውለበለበ፣ ሊኖራቸው የሚችለውን ውበት ሁሉ ሸፋፍኖታል። በምናብ እንኳ ውበታቸውን መፈለግ ይከብዳል...

ጡሩንባ እየነፋሁ መንገድ ስጀምር ከሁላ የተቀመጠችው ሴት መራረቀችኝ። ዝምተኛ መሆኗ ይታወቃል። እድሜዋ ከ30 በላይ ሊሆን ቢችልም ያረጀች ነበር የምትመስል። እንደዋዛ ከካሮት አፍንጫ ጋር ወግ ጀመርኩ። 'እድሜዋ ከ16 አይበልጥም' ብዬ ገመትኩ።

"ማነው ስምሽ?"

"ብስኩት" አለች።

ሳቅሁ።

"ምናሳቀህ?"

"እየቀለድ'ሽ ነው?"

"እውነቴን ነው፣ ስሜ ነው"

"እንዲህ አይነት ስም ሰምቼ አላውቅም" አልኩ።

"እኔም ሰምቼ አላውቅም። ያንተስ ስም ማነው?"

ነገርኳት።

በተራዋ እየሳቀች እንዲህ አለች፣

"እኛ ጎረቤት በጣም ብዙ 'ተስፋዬ' አሉ። አስር ይሆናሉ። ኸረ እንዲያውም ሃያ ይሆናሉ..."

ስቄ ዝም አልኩ።

*( ለነገሩ እውነቷን ነው። አገሩ በሙሉ 'ተስፋዬ' ነው ስሙ። ህዝቡ በልጆቹ ለመጠር ያለውን ምኞት ለመግለፅ ሳይሆን አይቀርም ይህን ስም በገፍ የተጠቀመበት። አሁን እንኳ ህዝቡ ተስፋ ቆረጠ መሰለኝ ይህ ስም ከአገልግሎት ውጭ ከሆነ 40 አመት አለፈው። በርግጥ ከሃያ አመታት በፊት የደርግ አባል የነበረው ሻለቃ ካሳዬ አራጋው፣ "ተስፋዬ" የተባለ መፅሃፍ አሳትሞ ነበር። በህይወቴ ሙሉ ገና ሳላነበው የጠላሁት መፅሃፍ ቢኖር ይኸው "ተስፋዬ" የተባለውን መፅሃፍ ነበር። መፅሃፉ በየቀበሌው ከመኮሮኒና ከሳሙና ጋር በግድ ይሸጥ ነበር። ካሳዬ አራጋው ለመፅሃፉ ይህን ስም የመረጠው በመንግስት ስልጣን ላይ በርከት ያሉ ተስፋዬዎች ስለነበሩ ነው ይባላል። ተስፋዬ ገብረኪዳን፣ ተስፋዬ ዲንቃ፣ ተስፋዬ ወልደስላሴ። "እጥፍቶ መጥፋት" ላይ ሙሉጌታ ሉሌ "የተስፋዬዎች መንግስት" ሲል ቀልዷል።)*

ወደ ርእሰ ጉዳዬ ልመልሳችሁ...

ህዝበ ክርስትያኑ መንገዱን ሞልቶ ይጓዛል። ዥንጉርጉር ሽመል ይዞ እየዘለለ የሚጨፍረውን ህዝብ እየተጋፋሁ እንደምንም ወደ አስመራ መንገድ ገባሁ።

"ተማሪ ነሽ?" ስል ጠየቅሁዋት።

"ዘጠነኛ ክፍል እማራለሁ"

"እድሜሽ ስንት ሆነ?"

"15"

ቤታቸው ላደርሳቸው ወሰንኩ። ወደ ገርጂ ማምራት ስንጀምር ግን ወሬ አልቆብን ነበር። መቼም "ዝም ከማለት" አንዳንድ ጨዋታ ጀመርኩ።

"ትምህርት እንዴት ነሽ?'

"ብዙም አይደለሁ። በቃ ያው እንደ ሁሉም..."

"ምነው አልጎበዝሽም?'

ስቃ ዝም አለች፣

"የአባትሽ ስም ማነው?"

"አማረ"

"አባትሽ ምን ይሰራሉ?"

"በህይወት የለም። መድፈኛ ሻምበል ነበር። በጦርነቱ ደሴ ላይ ሞተ ብለው መርዶ አረዱን"





ድምፅዋ ሲቀየር አስተዋልኩና ፊጥኜ ርእስ ለወጥኩ።

"ትምህርትሽን አታጠኚም እንዴ?"

"አጠናለሁ!" አያያዘችና፣ "...ግን ይደክመኛል"

"ምነው?"

"ቤት ውስጥ ስራ እሰራለሁ! ማታ ላጠና ስሞክር ወገቤ ይሰበራል። ከዚያ በቃ እተኛለሁ።"

በእጇ እያመለከተች፣

"ደርሰናል! እዚህ ጋር አቁምልን?" አለች።

መኪናዋን ዳር አስይዤ አቆምኩ።

ከሁዋላ የተቀመጠችው ልጅ ቀድማ ወረደች። ብስኩት በሩ እንዴት እንደሚከፈት ጠፍቷት ነበርና አገዝኳት። ከመውረዱ በፊትም እንዲህ አለች፣

"እናመሰግናለን።"

"ምንም አይደል። ቻው ብስኩት"

"ደህና ሁን"

የመኪናውን በር ዘግታ ከባልንጀራዋ ጋር በኮረኮንቹ መንገድ ላይ መጓዝ ጀመሩ። መኪናውን ለማዞር አላፊ መኪኖች አልፈው እስኪያልቁ እየጠበቅሁ ነበር።

ብስኩት ቆመች።

ዘወር ብላ አየችኝ። ከባልንጀራዋ ጋር የሆነ ነገር ተነጋገሩ። ጓደኛዋ መንገዱን ቀጠለች። ብስኩት ያመነታች መሰለች። ለመሄድ ያሰበች መሰለችና ሃሳቧን ለውጣ በቀጥታ ወደኔ መጣች። እና ጎንበስ ብላ ተጠጋችኝ፣

"ይቅርታ አድርግልኝና አንድ ነገር ልጠይቅህ?"

በእሺታ ራሴን ላይ ታች ወዘወዝኩ፣

"እንዲሁ ሳይህ ቀለል ስላልከኝ ነው የደፈርኩህ።"

"ምንም አይደል። ምን ሆንሻል?"

"ምንም አልሆንኩም" እንደገና አመነታች፣ "...እዚህ ስላደረስከን አመሰግናለሁ። ግን ስለ እናቴ ልነግርህ ብዬ ነው..."

"ንገሪኝ ደህና..."

"እናቴ ታማ ዘጠኝ ወር ዘውዲቱ ሆስፒታል ቆይታ አሁን ተሽሎአት ከሆስፒታል ወጣች። ግን በጣም ስለተጎዳች እንጀራ አትበላም። ሃኪሞቹ መረቅ ነገር ተመገቢ ብለዋታል። ሶስት ልጆች አሉ ቤት ውስጥ። ምግብ የሚባል የለም። መረቅ ካላገኘች እናቴ እንደገና እንዳትታመምብኝ ፈራሁ።

ብትሞትብኝ ምናደርጋቸዋለሁ ልጆቹን?"

እንባዋ ዝርግፍግፉ ወጥቶ የመኪናው በር ላይ ተደገፈች። ስሜቷን ለመቆጣጠር ጥረት አድርጋ ነበር። አልሆነላትም። አይኖቿ እሳት እያመነጩ እንባዋን ለቀቀችው። ይህ ሁሉ የተፈፀመው አንድ ደቂቃ እንኳ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ነበር። ከሁዋላ መኪና ውስጥ እንድትገባ አደረግሁና ላፅናናት ሞከርኩ። ስሜታዊ ሆኜም ልረዳት እንደምችል ቃል ገባሁላት። በርግጥም የመጀመሪያውን የነፍስ አድን እርዳታ ወዲያው ነበር የጀመርኩት። እዚያው አካባቢ ካሉ መደብሮች ጥቂት ገዛዛን። ለመረቅ የሚሆን አጥንት በአስር ብር አገኘን። ቀይ ስር እና ድንች ጨመርንበት። ዳቦና ከሰልም ገዛች። ስኳር፣ ቡና፣ እጣን ታከለበት። አምስት ብር ለእጇ አስያዝኳት። ይሄ ሁሉ ሆኖ ያወጣሁት ጠቅላላ 25 ብር ቢሆን ነበር።

ብስኩት በጣም ተደሰተች።

እና እንዲህ አለችኝ፣

"እናቴን ለምን አይተሃት አትሄድም?"

"እቸኩላለሁ ብስኩት"

"በቁምህ አይተሃት ትሄዳለህ። ያደረግሽውንም ልንገራትና ትመርቅህ። ይሄውና ቤታችን"

ገባሁ።

በአንድ ጠባብ ክፍል ውስጥ አንዲት አጥንቷ ያገጠጠ ሴት አልጋው ላይ ተጋድማለች። ከንፈሮቿ ኩበት መስለዋል። ቡትቶ ጨርቆች ተደራርበውላት ቁና ቁና ትተነፍሳለች። የግንባሯ ላይ ደም ስሮች አግጠዋል። አፈሩ በጎርፍ ተበልቶ የወጣ የዛፍ ስሮች ይመስላሉ።

ግድግዳው ላይ ሶስት ኮከቦች የደረደረ መኮንን ከአንድ የመድፍ ባትሪ ጋር የተነሳው ፎቶግራፍ ተሰቅሎአል። በግራና በቀኝ የማርያምና የገብርኤል ምስሎች ተለጥፈዋል። ሟቹ ሻምበል የኢትዮጵያን ባንዴራ ይዞ የተነሳው ፎቶግራፍ በሌላ በኩል በመስታወት ውስጥ ያረጀ ኮመዲኖ ላይ ተቀምጦአል። የህንድ አማልክት ይሁኑ የፊልም አክተሮች የማይታወቅ ፖስተርም ከአልጋው ማዶ ተሰቅሎአል።

ጤንነቷን ከጠያየቅሁ በሁዋላ ሌላ ላወራው የምችለው በማጣቴ፣ የመድፈኛውን ሻምበል ፎቶግራፍ እያጤንኩ እንዲህ ጠየቅሁ፣





"አሟሟቱን ሰምታችሁዋል?"

"ሞተ ብለው ነው ያረዱን። ሌላ የነገሩን ነገር የለም። ምን ያደርጋል ብለህ ነው? ሞት እንደሁ ያው ሞት ነው" አለች በደከመ ድምፅ።

"ዘመዶቹስ አሉ?"

"አናውቃቸውም። እሱም በረሃ በረሃውን ነበር። መንግስት ወድቆ እነዚህኞቹ ከመጡ ወዲህም ያው ጡረታ የለ ምን የለ፣ 'የደርግ ወታደር' አሉና ወረወሩን። ጉሊት እየቸረቸርኩ የልጆቹን ትንፋሽ አቆይቼ ነበር። አሁን ታመምኩ። ጨጓራ ነው በሽታዬ። ወያኔዎቹ ከመምጣታቸው በፊት ለመኮንኖች የሚሰጥ ቤት ውስጥ ነበርን። ከዚያ አውጥተው ሲጥሉን ቁጭትም ድንጋጤም ተጨማመረና ጨጓራዬን እንደ እሳት ለበለበኝ። በዚያ ጀመረኝና ይኸው ለዚህ በቃሁ።"

ተሰናብቼ ወጣሁ።

ብስኩት እስከ መንገዱ ሸኘችኝ። ስንለያይም የጠፋ የቅርብ ዘመዷን ያገኘች ያህል በስስት አይን እያየችኝ፣

"እየመጣህ ትጠይቀናለህ?" አለች።

"ሲመቸኝ ብቅ እያልኩ አያችሁዋለሁ" አልኩ።

"እንዳትጠፋ አደራ። ወንድም ትሆነናለህ"

"አልጠፋም ብስኩት"

"በገብርኤል?"

"እመኚኝ ብስኩት"

ስጨብጣት እጄን አጥብቃ ይዛ እንዲህ አለችኝ፣

"መረቅ ከተመገብሽ ሰውነትሽ ይጠገናል ብሏታል ሃኪሙ። እንዳትሞትብኝ ብዬ ነው። ሳላውቅህ ዝም ብዬ አስቸገርኩህ። እድሜዬ ትንሽ ስለሆነ ነው እንጂ፣ አንድ ቀን እንደ ሰው ሁሉ ሰው ሆኜ ቤተሰቤን ማገዜ አይቀርም። ውለታህን አልረሳውም። እናቴ እስኪሻላት ብቻ እርዳን"

"በአቅሜ እሞክራለሁ፣ ብስኩት"

በዚሁ ተለያየን።

* * *

ከዚያ በሁዋላ ግን አልሄድኩም።

ለብስኩት ቃል የገባሁላት ለማስመሰል አልነበረም።

በወር በዛ ቢባል ሃምሳ ብር ይበቃቸው ነበር። ለጥቂት ጊዜያት ያን ማድረግ ደግሞ ባልቸገረኝ። ዛሬ ነገ እያልኩ የመጀመሪያውን ሁለት ሳምንታት ሳልሄድ ቀረሁ። በሶስተኛው ሳምንት ልሄድ ወስኜ ሳለሁ፣ ሌላ ጉዳይ ገጠመኝ። በነጋታው እሄዳለሁ ብዬ ነበር ረሳሁት። እንዲህ እያለ ቆየና በዚያው ቀረ። ልክ እንደዚህ ነበር የሆነው።

በአመቱ ግድም ብስኩትን አገኘሁዋት። አየሁዋት ቢባል ይቀላል መሰለኝ። ራስ የሚመታ መጥፎ አጋጣሚ ነበር።

በወቅቱ ቦሌ ነበር የመኖሪያ አፓርታማዬ።

ብዙውን ጊዜ ፍራፍሬዎችን የምገዛው ወሎ ሰፈር መገንጠያው ላይ ከነበሩት ግሮሰሪዎች ሲሆን፣ እዚያ መአዘን ላይ ወጣት ሴትኛ አዳሪዎች ተኮልኩለው ለአላፊ አግዳሚው የተካፈፈተ ገላቸውን ይጋብዛሉ። ፍራፍሬ ልገዛ ሳቆም፣ እልፍ ብለው ከቆሙት ሁለት ኮረዶች አንዷ ብስኩት አማረ መሆኗን በትክክል ለየሁዋት። የጉንጮቿ ስርጉዳት፣ አሳሳቋ! ካሮት አፍንጫ! ራሷ ብስኩት ነበረች። አጭር ቀሚስ ለብሳለች። ለሚያልፉት ባለመኪኖች ታፏጫለች...

ለጥቂት ደቂቃዎች መኪና ውስጥ ቁጭ ብዬ በፀጥታ ተመለከትኳት። ደስተኛ ትመስላለች። ትስቃለች። ተስፋ የቆረጠ ሰው ወይም ያበደ ሰው የሚስቀው አይነት ሳቅ ይመስላል። ሲጋራ ቢጤም ተዋውሰው ሲያጨሱ አየሁ።

ከዚያም መንገዴን ቀጠልኩ።

ወደ ቤት አልገባሁም።

ካራማራ ጭፈራ ቤት ገባሁ። ፎቁ ላይ ወጣሁና ቁጭ አልኩ። ከታች የኛ ሰዎች በይሁኔ በላይ ዜማ እስክስታውን እየሸከሸኩት ነበር። በትግሉ ወቅት ያመለጣቸውን ጭፈራ ለማካካስ ይመስላል። ያለ እረፍት ይወዛወዙታል። ይሁኔ በላይ እንዲህ እያለ ነበር...

አንቺም ሂጂ ሂጂ - ወደ ነጫጮቹ፣
ለኛም እግዜር አለን - ለጥቋቁሮቹ፣

በደሌ ቢራ አዘዝኩና ማስታወሻ አወጣሁ።

ስለ መድፈኛው ሴት ልጅም መፃፍ ጀመርኩ።

"ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ?" ብዬ መጀመሪያ ትዝ ይለኛል። አያይዤም ጥቂት አከልኩበት፣ "...ይህች ልጅ





እያለቀሰች እናቷን እንድረዳላት ስትጠይቀኝ ለምን ችላ አልኩ? ምን ሆኛለሁ? ይህን አውሬነት ከየት ወረስኩት? ወይስ ተፈጥሮዬ እንዲያ ይሆን?"

መጫጫሩን ተውኩና ቅኔ ልቋጥር ሞከርኩ፣

አንዲት አበባ የፀደይ፣
ጠይም ሰቆቃ መሳይ፤
ተጥላ አየሁ ቦሌ ላይ፣
አንቺ የፀደይ አበባ?
የኛ መስከረም ሲጠባ፣
የአንድ አገር ሰው ሆነን ሳለ...
ያንቺ ጀምበር ወዴት ገባ?

በዚህ መንገድ መዘባረቁን ግን ሳልቀጥል ቀረሁ። ህሊናዬ በህሊና ጥያቄ ህሊናዬን በቡጢ አፈረጠው፣

"አሁንስ ቢሆን ይህችን ርቃኗን መንገድ ዳር የቆመች ለጋ ልጅ መርዳትና ማዳን አትችልም?"

ብእሬ ባለበት ዶሎዶመና ቆመ።

ወደ ማመን ሳይሆን ወደ መከላከል ገባሁ።

"መርዳት በፊት ነበር። አሁን ጊዜው አልፎአል። እንደ ብስኩት ያሉ ሺዎች ቆነጃጅት መንገዱን ሞልተውታል..."

ከግራና ከቀኝ በሁለት ከተወጠሩ ጫፎች የሚመጡ ጭቅጭቆች አእምሮዬን ሊያፈነዱት ደረሱ።

ህሊናዬ ቃል በቃል እንዲህ እያለኝ ነበር፣

"ሰበብ አትፍጠር! ከፈለግህ ልትረዳት ትችላለህ።"

"የኔ ስራ አይደለም..." ስል ራሴው ላይ ጮህኩ።

ህሊናዬ ግልፅ መልስ ሰጠኝ፣

"ስራህ አለመሆኑ ግልፅ ነው። ዋናው ነገር ራስህን አታታልል። ሌላው ደግሞ አትፈላሰፍ..."

ወረቀቱን አጠፍኩና ኪሴ ከትቼ ከፎቁ ወረድኩ። በጭፈራና በአልኮል ከተጠመቁትና በላቦት ከተጥለቀለቁት የትግል ጓዶቼ ጋር ተቀላቀልኩ። እንደነርሱ ክራቫቴን አላላሁና ወደ ዳንሱ መድረክ ገባሁ።

"ደንስ ጀግና!" አልኩት ስጋዬን።

እንደ ፀጋዬ ስንኞች....

ጭንቅላቴ ላይ የጃዝ ፋንፋር አንኳኳሁበት።

የሲቃ ሳቅ አስካካሁበት።

ዝግ ብሎ እንዳያስብ፣ እንዳይነግረኝ አንዳች እውነት።

**እናም ለዚያች ሌሊት…**
**ሁሉንም እርግፍ አድርጌ ረሳሁት።**
**ገብረክርስቶስ ደስታ!!**
**ምን ብለህ ነበር?**

እንካ! ባለክራር…
ተቀበለኝ ግጥም - ዝፈን ስለ ፍቅር፣
እንካ! ስለኑሮ - አሰማ ዜማህን…
በክራሩ ጅማት - የሚነደፈውን፣
ሙዚቃን አንስተህ - ማለው በሙዚቃ፣
የፈዘዘው ይንቃ፣
ተክዝ ግጥም ይዘህ፣
'ወዳጅ ማለት' ብለህ - በሞት በህይወት ኑሮ፣
ነፍስና ስጋ ነው - የሚጨነቅ አብሮ!



# - 8 -

# ጆቤ ልክ ነበር

አያይም ባይኖቹ - ጆሮውም አይሰማ፣
ደንዝዟል ህሊናው - በውዳሴ ዜማ፣
የባዶነቱን ልክ - ነውሩን ሳያውቀው፣
አጓጉል ይወድቃል፣
ዘመን ደግሶለት - ዝና ያሰከረው፣

(ግጥም - አረጋሽ ሰይፉ)

ጄኔራል አበበ ተክለሃይማኖት (ጆቤ) በ1993 ከኢትዮጵያ አየር ሃይል አዛዥነቱ ከመባረሩ በፊት፤ እንደ ጓደኞቹ ከመንግስት በስጦታ ባገኘው 500 ካሬሜትር ቦታ ላይ አንዲት አነስተኛ ቪላ ሰርቶ ነበር።

ጆቤ ያቺን "ቪላ-ጆቤ" በ2.5 ሚሊዮን ብር ሸጦ አዲስ አበባ ዩኒቬርስቲ የህግ ፋካልቲ ትምህርት ጀመረ። መማር መልካም ነው። ጆቤ በሃገራችን የዩንቬርሲቲ ተማሪዎች ታሪክ ይህን ያህል ገንዘብ ባንክ አስቀምጦ ተማሪ የሆነ የመጀመሪያው ሰው ሳይሆን አይቀርም።

ጄኔራል ጆቤ ትምህርቱን ካበቃ በሁዋላ እዚያው እተማረበት ቦታ በመምህርነት ተቀጥሮ ስራ ጀምሮ እንደነበር ሰምቼ ነበር። ይህን እየጫርኩ ሳለ ግን 'መምህርነቱን በመተው

አሜሪካ ላይ መሽጎአል' ብለው ነገሩኝ።

በሚሊኒየሙ ማግስት ጀቤ፣ "ደሃይ" ከተባለ መፅሄት ጋር ባደረገው ቃለምልልስ የኢህአዴግን አመራር በሁለት ቃላት ጥሩ አድርጎ ሊገልፀው ሞክሮአል። እንዲህ ነበር ያለው፣

"አለማወቅና እብሪት (Ignorance and arrogance) ዋነኛ ችግራችን ነበር"

ጀቤ ሳይሸፋፍን ሃቁን በማስቀመጡ ልናመሰግነው ይገባል። የወያኔን ስርአት በጥቅሉ ለመግለፅ ከጀቤ አባባል በላይ ተጨማሪ የመግለጫ ቃል አያሻውም። ቢሆንም የወያኔ ድንቁርናና እብሪት በተግባር ምን እንደሚመስል ጀቤ አልነገረንም። ሊነግረንም አይችልም።

ለነገሩ ስንቱን ዘርዝሮ ይችላል?

የወያኔን አለማወቅና እብሪት የሚገልፅ አስረጅ ሁሉ ይፃፍ ከተባለ ሶስት ትልልቅ ጥራዝ አይበቃውም። ቢሆንም ለማሳያ ይሆኑ ዘንድ የማስታወሻ ደብተሬ ላይ ካገኘሁዋቸው መካከል አንዳንዶቹን ቀነጫጭቤ ላውጋችሁ። በትረካዎቹ የመሳቅም ሆነ የመናደድ መብታችሁ የተጠበቀ ነው..

* * *

በ1988 አሜሪካኖች አንድ የኰማንዶ ብርጌድ ለማሰልጠን ደብረዘይት መጥተው ነበር። ለስልጠናውም ከየጦር ክፍሉ ብቁ ሊሆኑ የሚችሉ ወታደሮች ተመለመሉ። በአጋጣሚ ይሁን በአድልዎ ባይታወቅም ሰልጣኞቹ በሙሉ የህወሃት አባላት ሆነው ተገኙ። ለአስተርጓሚነት ደግሞ አባይነህ ደምሴ የተባሉ ኰሎኔል ተመደቡ። እኚህ ኮሎኔል የመድፍ ተኩስ መምሪያ ልዩ ባለሙያ ናቸው። በደርግ ዘመን ኤርትራ ላይ የመድፈኛ ቡድን አስተባባሪ ሆነው፣ ሻእቢያን እንቅልፍ ነስተው፣ መግቢያ መውጫ አሳጥተውት የነበሩ በጣም አደገኛ መድፈኛ የጦር መኮንን ነበሩ።

ደርግ ከወደቀ በሁዋላ ወያኔ የሙያ ብቃታቸውን ቢገነዘብም፣ የፖለቲካ አመለካካታቸውን በመጠራጠር በአማካሪነት ደረጃ ብቻ ራቅ አድርጎ ይጠቀምባቸው ጀመር። አሜሪካኖች ሲመጡም በአስተርጓሚነት ተመደቡ።

የታቀደው ስልጠና በፕሮግራሙ መሰረት እየቀጠለ





ነበር። ከስልጠናው መርሃ ግብር መካከል በቅርብ ርቀት አየር ላይ ከቆመ ሄሊኰፕተር በሚለቀቅ ገመድ እየተሳቡ ወደ ሄሊኰፕተሯ የመግባት ልምምድ አንዱ ነበር።

ኰሎኔል አባይነህ ሁኔታውን በቅርብ ይከታተሉ ስለነበር እንዲህ ሲሉ ሙያዊ ምክር ቢጤ ያቀርባሉ፣

"ከልምምዱ በፊት ወታደሮች ምግብ በደንብ መመገብና በስፖርትም ሰውነታቸውን ማዳበር አለበት። ሰውነታቸው ለስልጠናው ዝግጁ ካልሆነ ልምምዱን ሊቋቋሙት አይችሉም። በቅድሚያ ይመገቡ! መመገብ አለባቸው!"

የስልጠናው መሪ ገብረኪዳን የተባለ ነባር የህወሃት አባል ነበር። በትግሉ ወቅት የአግአዚ ክፍለጦር ኮሚሳር ነበር። ይህ የወያኔ ታጋይ የኮሎኔል አባይነህን ሙያዊ ምክር ካዳመጠ በሁዋላ የሰጠው ምላሽ ጀቤ የጠቀሰውን እብሪትና አለማወቅ በትክክል የሚያሳይ ነው። ቃል በቃል እንዲህ ሲል ሰደባቸው፣

"ሆዳም ኰሎኔል! እኛ እናንተን ያሸነፍነው በምግብ ሳይሆን በአላማ ፅናት ነው!"

የኮሎኔሉ ልብ ስራዋን ባለማቆሟ እድለኛ ቢሆኑ ነው።

የተባለው ከተባለ በሁዋላ ስልጠናው ተጀመረ።

ሄሊኰፕተር መጣችና አየር ላይ ቆመች። ገመድ ከሰማይ ተለቀቀ። የመጀመሪያው ሰልጣኝ ወታደር በገመዱ እየተሳበ ወደ ሄሊኰፕተሯ ለመውጣት ሞከረ። ሁለት ጊዜ ተሳበ። ዳሩ አልቀጠለም። ትንፋሽ ከየት ይምጣ? ጡንቻ አልዳበረም። እንደ ጅማት ከርረው እንደ ሲባጐ የቀጠኑት የሰልጣኞቹ እጆች መንቀጥቀጥ ሆነ። ተራቸውን የሚጠብቁት ሰልጣኞች ሜዳው ላይ ተኰልኩለው፣

"አጆኻ! አንበሳ! አጆኻ! አንበሳ!" እያሉ በጭብጨባ ሞራል ይሰጣሉ። ሲተረጎም፣ "አይዞህ አንበሳዬ" ማለት ነው። ገብረኪዳንም እንደ ክቡር ዘበኛ የኦርኬስትራ ባንድ መሪ እጁን እያወዛወዘ ጭብጨባው እንዲሞቅ ያበረታታል። ጭብጨባውና ዘፈኑ እየጋለ ሄደ። በጭብጨባው ተገፋፍተው ከተቀመጡበት እየተነሱ መደነስ የጀመሩም ነበሩ...

ሰልጣኞቹ ግን ወደ ሄሊኰፕተሯ ሊደርሱ አልቻሉም። መላ ሰውነታቸው እየተርገፈገፈ ፌሊት እንደተነፋባቸው ቢንቢዎች ገመዱን እየለቀቁ መሬት ይወድቁ ጀመር። ጭብጨባውና የአላማ ፅናቱ በፍፁም ሊያግዛቸው ባለመቻሉ

ገብረኪዳን፣ "ሆዳም" ኰሎኔሉን አስጠራቸው። አባይነህ ደምሴ ታጋዩ ፊት ቀረቡ። ገብሬ ጀግናውም እንዲህ ሲል ጠየቀ፣

"ምን ያህል ጊዜ መመገብ አለባቸው?"

* * *

ግንቦት20 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የምርጦች ምርጥ ትምህርት ቤት ነበር። ዳሩ ምን ያደርጋል!? ተማሪዎቹ ሳይጠቀሙበት ቀረ። የመጀመሪያው ዙር ተማሪዎች የመለስን ሚስት ጨምሮ አብዛኞቹ የመማር ፍላጐት አልነበራቸውም። በመሆኑም 'ተምረዋል' እንዲባል ያህል ብቻ ክፍል ውስጥ እንዲቀመጡ ይደረግ ነበር።

"ኳርተር" በሚል ቅፅል ስም የሚታወቅ አንድ የወያኔ ጀኔራል ነበር። እውነተኛ ስሙ አብርሃ ወልደማርያም ነው። 9ኛ ክፍል እየተማረ ነበር። እጁን አውጥቶ ዘሚካኤል የሚባለውን የባዮሎጂ መምህር እንዲህ ሲል ጠይቆታል፣

"ስለ ትላትል እያስተማርከን ነው። እነዚህ ትላትሎች ከኔ ስራ ጋር ምን ግንኙነት አላቸው? ስለነዚህ ትላትሎች ማወቅ ምን ይጠቅመኛል?"

እውነቱን ነበር!

ኳርተር እድሜውን ሙሉ ጦርነት ላይ ነው ያሳለፈው። ጦርነት ደግሞ መግደልና መሞት፣ መቁሰልና ማቁሰል ማለት ነው። ጦርነቱ አሁን አልፎአል። ኳርተርም ባለ ብዙ ገንዘብና ባለ ብዙ ስልጣን ለመሆን በቅቷል። ገንዘብ ጥሩ ነገር መሆኑንም አውቋል። ውድ የተባለውን ዊስኪ ጭምር ቀምሶታል። እንቁላል የሚመስል አደገኛ መኪና ይዟል። የከተማ ሴቶችም የፈረንጅ እንቁላል ይመስላሉ። እና ታዲያ አራት መአዘን ክፍል ውስጥ አስቀምጠው ስለ ትላትል ሲነግሩት ቢናደድ ምን ይፈረድበታል? ጀቤ ልክ ነበር...

* * *

ጀኔራል ሳሞራ የኑስ ለማስትሬት ዲግሪ በተልእኰ እየተማረ ሳለ እንዴት እንደሆነ ባይታወቅም አጋማሹ ላይ፣





ከአብዛኞቹ ተማሪዎች የበለጠ ጥሩ ውጤት አመጣ። መምህሯም ከእንግሊዝ ሃገር መጥታ ማብራሪያ ስትሰጣቸው ቆይታ፣ ከተማሪዎቹ አንዳንዶቹ ጥያቄ ያነሳሉ። መምህሯ የሳሞራን ስም አስታወሰች። ምክንያቱም አንዳንድ ተማሪዎች "አልገባንም" ብለው የጠየቁትን ጥያቄ ጄኔራል ሳሞራ ጥሩ አድርጎ መመለሱ ታወሳት። ስለዚህ ላልገባቸው ተማሪዎች እንዲያብራራ እድል ሰጠችው። ሳሞራ ሳያመነታ እንዲህ ሲል መለሰ፣

"አላውቀውም"

"በላክሽው ወረቀት ላይ ግን ጥሩ ሰርተሽዋል"

ብሶት የወለደው ጀግናው ሳሞራ ምንተእዳው?

እየሳቀ እንዲህ አላት፣

"እሱን ጓደኞቼ ናቸው ሰርተው የላኩልሽ"

መምህሯ ጆሮዋን እየተጠራጠረች እንዲህ አለች አሉ፣

"በ25 አመታት የመምህርነት የስራ ዘመኔ ሁሉ እንዲህ ያለ ግልፅ ተማሪ ገጥሞኝ አያውቅም"

የጄኔራል ሳሞራ ግልፅነት ከመምህሯ ቦርሳ ውስጥ በአደራ ይቀመጥልን። የሳሞራ ንግግር፣ "ማን ይነካኛል?" የተባለ ስድነት እንጂ የሚጨበጨብለት ግልፅነት ሊሆን አይችልም። ምናልባትም ፈተናህን በሌሎች ማሰራትና በማእረግ ማለፍ እየተለመደ በመምጣቱ ሊሆን ይችላል ሳሞራ ተማሪዎች ሁሉ ፊት ያንን የተናገረው። ለሳሞራ ወረቀቱን የሰራለት ንዋይ ገብረአብ ሲሆን፣ Open University የተማሩትና የሚማሩት የወያኔ አባላት ጀምረው እስኪጨርሱ ለእያንዳንዳቸው እስከ 15 ሺህ ዶላር ተከፍሎላቸዋል። እንዲያ ተከፍሎም ግን አብዛኞቹ አልተጠቀሙበትም። የማስትሬት ዲግሪያቸውን የያዙት በህገወጥ መንገድ በእገዛ ነው።

ህገወጥነቱ በችሎታ ያገኙት አለመሆኑ ብቻ አይደለም። በኢትዮጵያ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላገኘ ሰው ሁለተኛ ዲግሪ ቢያቀርብ ተቀባይነት አይኖረውም የሚል ለዘመናት ሲሰራበት የቆየ የትምህርት ሚኒስቴር ህግ አለ። ከዚህ ህግ አንፃር በረከትና ተፈራ ዋልዋ ብቻ ሳይሆኑ መለስ ዜናዊ ጭምር የማስትሬት ዲግሪ ለመያዝ ህጉ አይፈቅድላቸውም። በረከት ጎንደር ሳለ ትምህርቱን 10ኛ ክፍል ላይ ነበር ያቋረጠው። ተፈራ አዲሳባ ላይ ተግባረእድ ሲማር ከ9ኛ ክፍል በላይ አልዘለቀም። የ12ኛ ክፍል ሰርተፊኬት ሳይዙ የሃርቫርድና የኦክስፎርድ ዲግሪ

ለማግኘት የበቁ የወያኔ አባላት ከጥቂት በላይ ናቸው። ካሳ ሽሪፎ ከእነዚህ አንዱ ነው።

* * *

የማስትሬት ዲግሪ ይዘዋል ተብለው የመምሪያ ሃላፊነት ቦታዎችን የወረሩት አብዛኞቹ የወያኔ ባለስልጣናት የግንቦት 20 ፍሬዎች ናቸው። ግንቦት 20 ትምህርት ቤት ከመነሻው አስቂኝ ህጎች ነበሩት። ተማሪዎቹ 75% ማርክ የሚያዝላቸው በትምህርታቸው ሳይሆን፣ በመስሪያ ቤታቸው የስራ አፈፃፀማቸው ነበር። 25% ደግሞ ከወረቀት ፈተና ይያዝላቸዋል። በመሆኑም አንድ የግንቦት 20 ተማሪ ትምህርቱን 0 ከ 25 ቢያገኝ እንኳ፣ በስራ አፈፃፀሙ ከ50 በላይ ማግኘቱ ስለማይቀር መውደቅ አይኖርም።

ይህ እንደ ቀልድ ሊታለፍ በቻለ ነበር።

ግንቦት 20 ትምህርት ቤት ገብተው ያልተማሩ ወይም ትምህርቱን ያቋረጡም ነበሩ። እነዚህ 12ኛ ክፍል ሳይደርሱ በድብቅ ለማትሪክ ፈተና እንዲቀመጡ ተደርገዋል። ለፈተናው የተቀመጡት ምስጢር እንዲጠበቅ ተብሎ በቀድሞው ሙሉጌታ ቡሊ የጦር ማሰልጠኛ ካምፕ ውስጥ ነበር።

እዚያ ካምፕ ለፈተና እንዲቀመጡ ከተደረጉት የጦር ሰራዊትና የሲቪል ባለስልጣናት መካከል ከመለስ ሚስት ባሻገር፣ ሰአረ መኮንን፣ ባጫ ደበሌ፣ ወዲ መድህን፣ አብርሃ መጅሙእ፣ አበባው ታደሰ፣ የተባሉት ጄኔራሎች ጥቂቶቹ ናቸው። ባለስልጣናቱ እንደ ችሎታቸው ሳይሆን፣ እንደ ስልጣን ደረጃቸው ውጤት እንዲያገኙ ተደርገዋል። ፈተና አቀማመጣቸው በፕላኔታችን ላይ ተፈፅሞ የማያውቅ ተአምራዊ የሚባል ነበር። በተዘጋጀላቸው ወንበር ላይ ተቀመጡ። የፈተና ወረቀቱና መልስ ማቅለሚያው ተሰጣቸው። መልሱም በሌላ ወረቀት ታደላቸው። ያንን ገለበጡት። ከዚያም መኪኖቻቸውን እያስነሱ ወደ አዲስ አበባ ተፈተለኩ።

ይህ መልስ የመስጠቱ ሂደት ልዩ መመሪያ ተዘጋጅቶለት ነበር። ለጄኔራል መኮንኖች ከ7 የትምህርት አይነት የ4ቱ ሙሉ መልስ ተሰጣቸው። ለኮሎኔሎች 3A፣ ለበታች ሹሞች 2A፣ ለተራ ወታደሮች 1A መልስ ተሰጣቸው።





ቀሪውን እንደየችሎታቸው እንዲሞሉ ተነገራቸው። ለአብነት 2A ብቻ የተፈቀደለት የመምረጥ መብት ነበረው። 'የሚከብዱኝ ፊዚክስ እና ባዮሎጂ ናቸው' ካለ እነሱ ይሰጡታል። መልሱን በትክክል መገልበጥ ተቸግረው ከተፈቀደላቸው ውጤት በታች ያመጡም ነበሩ። ከተፈቀደላቸው ውጤት በላይ ያመጡም አሉ። ግርማ በዶ አንዱ ነው። የመከላከያ ባልደረባ ሲሆን፣ አብርሃ መጅሙእ ከተባለው ጄኔራል ጀርባ በመቀመጡ፣ ከጀርባ እየነካካ ሲያስቸግረው እሱ እንዲኮርጅ የተሰጠውን የመልስ ወረቀት አሳልፎ ሰጥቶታል። በመሆኑም ከተፈቀደለት A በላይ አግኝቷል። በዚህ መንገድ እንደ ስልጣንና መእረግ ደረጃቸው ደረጃውን የጠበቀ ውጤት እንዲያመጡ ተደረገ። በመሆኑም መልሱን በትክክል መገልበጥ የቻሉ ጄኔራሎቹ 3.8 ሲያመጡ፣ ኮሎኔሎቹ 3.6 አገኙ። እንደዚያ እያለ እንደ ደረጃቸው መጠን የማትሪክ ውጤት ድልደላ ተደረገላቸው። ይህ በወቅቱ አባል ለነበርነው ምስጢር አልነበረም። መዝሙር ፈንቴ የተባለው ባለስልጣን እዚህ ቅሌት ውስጥ መግባት ባለመፈለጉ ምኒልክ ትምህርት ቤት የማታ ተምሮ፣ በግሉ ተፈትኖ፣ ዝቅተኛ ነጥብ ቢሆንም የሚገባውን አግኝቶአል። የማትሪኩ ጣጣ በዚህ ከተዘጋ በሁዋላ የዩኒቨርሲቲው ጉዳይ መጣ።

ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅም እንዲሁ እስከ ሁለተኛው ዙር ድረስ ተመሳሳይ የቡድን አሰራር ይከተል የነበረ ሲሆን፣ መልስ እየተሰጣቸው ፈተናውን እንዲያልፉ ተደርገዋል። የማስትሬት ዲግሪያቸውንም በዚህ መንገድ በእጃቸው በማስገባት የመንግስትን ስልጣን የመያዝ መብታቸውን ለማረጋገጥ ቻሉ። በሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ከሶስተኛው ዙር በሁዋላ አማራና ኦሮሞዎች ወደ ኮሌጁ በብዛት በመግባታቸው ኮሌጁም ሆነ የግንቦት20 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወደ መደበኛው ህጋዊ አሰራር ተመልሰዋል።

ይህ ሁኔታ የአንድ ሰሞን ክስተትና ችግር ብቻ ቢሆን ምንም አልነበረም። እነ መለስ የተማሩ ሰዎች እጥረት ስላለባቸው አብረዋቸው የታገሉ ገበሬዎችን ለስልጣን ለማብቃት ሲሉ አይናቸውን ጨፍነው ይህን አደረጉ በማለት ይቅርታ ሊደረግላቸው በተቻለ ነበር። መነሻውና መድረሻው ይህ ብቻ ቢሆን ችግሩን ልንገነዘብላቸው በተገባ። አባላቱ መቸም ታግለዋል፣ ቆስለዋል፣ ደምተዋል። በመከራው ጊዜ ችግሩን

የተሸከሙ ናቸውና በሰላም ጊዜ ሜዳ ላይ ሊወረወሩ አይገባም። ወይም 'ወደ እርሻ ስራህ ተመለስ' ሊባሉ አይችሉም። በህይወት እያሉ ሙዝየም ውስጥ ሊቀመጡም አይችሉም። 'ተማሩ' ሲባሉ ደግሞ፣ 'ስለ ትላትል ምን ያደርግልኛል' እያሉ አስቸገሩ። በወቅቱ ስልጣን ላይ የነበረው ስዬ አብርሃ ይህን መፈፀሙ 'ልክ ነበር ወይስ አይደለም' የሚለው ጥያቄ ቢነሳ አከራካሪ ይሆናል። በዚህም ተባለ በዚያ በዘዴም ቢሆን ዲግሪ ቢታደላቸው መቼስ ምን ይደረግ … ምናምን እየተባለ አጀንዳውን መዝለል ባልከፋ።

አደገኛው ነገር ግን ወያኔ ይህን አሰራሩን እንደገና በሰፊውና በተጠናከረ መንገድ እየገፋበት መሄዱ ነው። በትግሉ ጊዜ ባንክ ሲዘርፉ፣ 'ለትግሉ መሳካት ሲባል' የሚል ምክንያት ሊሰጠው ይችላል። የመንግስት ስልጣን ከያዙ በሁዋላ ባንክ ዘረፋውን ከቀጠሉስ? ምን ስም ይሰጠዋል? የትምህርቱም ጉዳይ እንዲሁ ነበር የሆነው።

አድማስ ኮሌጅ የሚማሩ የወያኔ አባላት (በአብዛኞቹ የመከላከያ መኮንኖች) እንዳይወድቁና ተንጠልጥለውም ቢሆን እያለፉ እንዲመረቁ እገዛ ይደረግላቸዋል። ቢያንስ "C" ይሰጣቸዋል። መከላከያ ለአንድ አባሉ 20ሺህ ብር እየከፈለ የአድማስ ኮሌጅን ገቢ ሲያጠናክር፣ ተማሪዎቹ ደግሞ የድኅማ ማርክ እየተሰጣቸው ዲግሪ ይይዛሉ።

መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ "መስማት የተሳናቸው" የሚል ቅፅል ስም ያገኘ አንድ ክፍል አለ። እነ ሃለቃ ፀጋይና ሌሎች ባለስልጣናት የሚማሩበት ነበር። ሃለቃ ፀጋይ "መስማት የተሳናቸው" ክፍል ውስጥ በድብቅ ተምሮ ጨርሶ በማእረግ መመረቁን በሚዲያ ሰምተናል። አንድ ሰው በማንኛውም እድሜ ተምሮ እውቀቱን ማሻሻል ከቻለ ሊበረታታ ይገባል። ራስህን ማታለል ግን ከእብደት የማይተናነስ በሽታ ነው። የወያኔ ሰዎች በትምህርት ዙሪያ የሚፈፅሟቸውን ወንጀሎች ስለለመዱቸው በቀላሉ ሊመለከቷቸው በቅተዋል። ሳትማር የስርቆት ዲግሪ መያዙን ከጉምሩክ ኮንቴይነር ያለቀረጥ የማስገባት ያህል ቀላል አድርገው አዩት። ህወሃት ቤት ይሰጥሃል፣ መኪና ይሰጥሃል፣ መሬት ይሰጥሃል፣ የፈተና መልስም ይሰጥሃል!

በደርግ ዘመን ዜጎቻችን ወደ ህንድና ራሺያ ተጉዘው ሳይማሩ ዲግሪ እየገዙ ይመጡ እንደነበር እናውቃለን። የመንግስቱ ሃይለማርያም ወንድም "ዶክተር" ጥላሁን አንዱ





ነው። ታምራት ፈረደም የሃሰት ዶክተሬት ዲግሪ መያዙ ይታወቃል። በገዛ ሃገራችን፣ የገዛ ዜጋችንን ፎርጅድ ዲግሪ እንዲይዝ በመንግስት ደረጃ ማበረታታት ግን ትውልድን የሚገድል ዘር መዝራት ማለት ይሆናል። አስተሳሰቡ ብቻውን እንደ ተስቦ ተሰራጭቶ ባጭር ጊዜ እንደ ልማድ ሊስፋፋ የሚችል በሽታ ነው። ምናልባትም ፖለቲካዊ አላማ ያለው ጄኖሳይድ ተብሎ ሊጠራ የሚችል ወንጀል ነው። የዚህ ወንጀል አመንጪና አስፈፃሚ ከነበሩት አንዱ ጀቤ ነው። ንስሃ እንኳ ሳይገባ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውስጥ በመምህርነት እንዲሰራ ፈቅደውለታል…

* * *

**የ**ግንቦት7 ሬድዮ 2001 ላይ የጄኔራሎችን የሃብትና የስልጣን ድልድል መረጃ ይፋ ሲያደርግ ብዙዎች መደንገጣቸውን ታዝቤያለሁ። ርግጥ ነው ያስደነግጣል። መደንገጥም መልካም ነው። እውነታው ግን ከዚያም የከፋ ነበር። ከህወሃት ባሻገር ያሉ ዜጎች ያገኟትን ስልጣን ይዘው እየቀጠሉ ያሉት ከውርደት ጋር ጭምር ነው። "ለህወሃት ካድሬዎች ያዳላል" በሚባለው የስልጣንና የማእረግ ድልድልም ቢሆን ደስተኛ ያልሆኑ በርካታ የህወሃት አባላት አሉ። በኰሎኔል ደረጃ ያሉ የህወሃት መኮንኖች "ተበድለናል" የሚል ከፍተኛ ቅሬታ ያቀርባሉ።

"በርሄ ሻእቢያ" የተባለ አንድ የህወሃት ኰሎኔል የስልጣን ድልድል ከተደረገ በሁዋላ በአንድ ግምገማ ላይ (1990) አባዱላና ባጫ በተገኙበት የመኮንኖች ስብሰባ እንዲህ ሲል ቅሬታውን አቅርቦ ነበር፣

"እኛ (ህወሃት ማለቱ ነው) ተዋርደናል። የኛ ምርኮኛ የነበሩ፣ ዳቦ ቆጣሪ የነበሩ፣ የጄኔራልነትን ማእረግ ሲያገኙ እኔ ኮሎኔል ነኝ!"

*( የኢትዮ - ኤርትራ ጦርነት በመካሄድ ላይ ሳለ ኮሎኔል በርሄ የሰራዊት ነርስ ውስጥ አዲስ ተማሪ ከነበረች ሴት ጋር ፍቅር ጀመረ። የልጆቹ እናት ይህን በመስማቷ በAk47 በአራት ጥይት ገድላው ራሷንም አጠፋች። ሁለቱንም እዚያው አዲስ አበባ እያለቀስን ቀበርናቸው። ሚስቲቱ በጣም ጥሩ ሰው*

*ነበረች። ትዳሯንና ልጆቿን ትወድ ነበር። በርሄም ቢሆን መጥፎ ሰው አልነበረም። በርግጥ ባልኋል። እንደ አብዛኛው ከፍተኛ መኮንን ባልኋል። ሚስቱም ግን ነባር ታጋይ ነበረች። ጠመንጃ ነበራት። ተናደደችና ገደለችው። ከህብረተሰብ አስተሳሰብና ከሚስቶች ባህላዊ ትእግስት ጋር አትተዋወቅም ነበር...)*

* * *

**ከ**ወያኔ የእብሪትና የአለማወቅ ታሪኮች መካከል የኰሎኔል ሲሳይ አመዴ አሟሟት ተጠቃሽ ሊሆን የሚችል ነው። ከህወሃት የአመራር አባላት የአንዱ ወንድም (ቢተው በላይ) የነበረው ሲሳይ በትግሉ ወቅት የጉና ክፍለ ሰራዊት አዛዥ ነበር። ከደርግ ውድቀት በሁዋላ ሲሳይ የኢትዮጵያ አየር ሃይል መስሪያ ቤት ውስጥ የሄሊኰፕተር ኦፕሬሽን አዛዥ ሆኖ ተመደበ። ይህ ስልጣን ሲሰጠው ግን ኰሎኔል ሲሳይ ሄሊኰፕተር ላይ ተሳፍሮ ያውቃል እንጂ ስለ ሄሊኰፕተር አንዳችም እውቀት አልነበረውም። በመሆኑም የሲሳይ ስህተት እንደ ጋዜጣ በ"ማረሚያ" ሊጠገን ባለመቻሉ ህይወቱን ከፈለ። ታሪኩ እንዲህ ነበር...

ኰሎኔል ሲሳይ አመዴ የውጊያ ሄሊኰፕተር አዛዥ መሆኑ ካልቀረ ተብሎ ሄሊኰፕተር የማብረር ትምህርት መከታተል ይጀምራል።

አሰልጣኞች የደርግ ተሸናፊ መኰንኖች ነበሩ። ሰልጣኞች ደግሞ አሸናፊዎች። መምህራን ከልብ ሊያስተምሩ አልቻሉም። ተማሪዎች ደግሞ በመምህሩ ላይ የበላይነት ካላሳየሁ ይላሉ። አስተማሪ ደፍሮ ተማሪውን አይናገረውም። በመሆኑም በመማር ማስተማሩ ሂደት የትምህርት ጥራት ወደ ታች አሽቆልቁሎ መሬት ወርዶ በቂጡ ዘጭ! አለ። ከሲሳይ መምህራን አንዱ ሻምበል እሸቱ ገመቹ ይባላል። ሲሳይ የዚህ ሰው አለቃ ሆኖአል። የትምህርት ክፍለ ጊዜው ሲያልቅ ሲሳይ እያሽቆጠቆጠ መምህራኖቹን ያዛል። ተማሪ የአስተማሪው አለቃ ሆኖ መዋሃድ የሚቻል አልነበረም። አየር ሃይል እንደ ህክምና ሙያ ጥብቅ ዲሲፕሊን የሚጠይቅ መስሪያ ቤት ነው። በጥንቃቄ ጉድለት ህይወት ሊጠፋ ይችላል። በመሆኑም በትምህርትና በስልጠና ሂደት ድክመት ላሳየ ተማሪ አስተያየትና የድጎማ ውጤት





የሚታሰብ አይደለም። በዚያን ወቅት ግን መምህራን ሲሳይን "አልቻልክም! ወድቀሃል! ቻው" ሊሉት አይችሉም ነበር። ሻምበል እሸቱ ገመቹ ይህን ቢያደርግ "አነግ ነህ!" እንዳይባል ይሰጋል። ስለዚህ መምህራን ሁሉ ሲሳይን እሹሩሩ እያሉ የሄሊኰፕተር ተዋጊ ለማድረግ መከራቸውን እያዩ ነበር።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የኤርትራ ጦርነት ተከሰተ። ከእለታት አንድ ማለዳ ወደ ቡሬ ግምባር ሄሊኰፕተር እንዲላክ ትእዛዝ መጣ። ኰሎኔል ሲሳይ ባስቸኳይ ሻምበል እሸቱን ያስጠራል። ሻምበል እሸቱ ገመቹ ግን በአካባቢው ሳይገኝ ቀረ። ምናልባት ሻይ ለመጠጣት ወደ ክበብ ጐራ ብሎ ሊሆን ይችላል። ወዲያ ወዲህ በማለት እሸቱን ማፈላለግ በተቻለ። ሲሳይ ግን ያን አላደረገም። እራሱ ወደ ሄሊኰፕተሯ ገብቶ ቀሰቀሳት። በህጉ መሰረት ሲሳይ የበረራ ትምህርቱን ያልጨረሰ እንደመሆኑ ሄሊኰፕተር ብቻውን ይዞ መሄድ የሚፈቀድለት አልነበረም። እሱ ግን የሄሊኰፕተር ውጊያ ኦፕሬሽን አዛዥ ስለሆነ ያን እንዳያደርግ የሚከለክለው አልነበረም። ልክ እንደ ሚኒ ባስ ሄሊኰፕተሯን አስነስቶ ወደ ቡሬ ግምባር ጭልጥ አለ። ሄሊኰፕተር እየነዱ መሄድና፣ እየነዱ መዋጋት ግን ለየቅል ነበሩ። ገና ቡሬ ከመድረሱ የሻእቢያ ፀረ አይሮፕላን ሚሳይሎች "እንኳን ደህና መጣህ!" ሲሉ የሞቀ አቀባበል አደረጉለት። ሲሳይና ጓደኞቹ ከነሄሊኰፕተራቸው አየር ላይ ጋዩ። ወርደውም አሰብ ላይ ተከሰከሱ። የኤርትራ ወታደሮች ሄሊኰፕተሯን ሲፈትሹ ሰዎቹ በመቃጠላቸው ማንነታቸውን ለመለየት የሚቻላቸው አልነበረም። የጦር አይሮፕላን አብራሪዎች ግን ከብረት የተሰራች መታወቂያ አላቸው። ያንን የብረት መታወቂያ ሲፈልጉ "ሻምበል እሸቱ ገመቹ" የሚለውን ያገኛሉ። ምክንያቱም እሸቱ ለበረራ ዝግጁ ስለነበር የብረት መታወቂያውን እዚያው ትቶአት ኖሮአል። በነጋታው የኤርትራ ሬድዮ ሻምበል እሸቱ ገመቹ የተባለ ፓይለት ከነሄሊኰፕተሩ ተመቶ መውደቁን ዜና ሲያውጅ ሻምበል እሸቱ በሞቀ አልጋ ውስጥ ነበር። በዚያን ጊዜ የመስሪያ ቤቱ አዛዥ ጆቤ ነበር..

* * *

**በ**1997 ህዳር ወር ላይ ጄኔራል ሳሞራ የእዝና

የመከላከያ የፖለቲካ ሃላፊዎችን አስቸኳይ ስብሰባ ጠራ። የተሰብሳቢው ቁጥር ወደ 20 ይጠጋ ነበር። የ1997 ምርጫን ታሳቢ አድርጎ ነበር ሳሞራ ስብሰባውን የጠራው።

ሰብስቦ በሰራዊቱ ውስጥ ምን አይነት የፖለቲካ ስራ መስራት እንዳለባቸው መመሪያ ሰጠ። ነጥቦቹ የታወቁ ነበሩ።

*'ሰራዊቱን ለህገመንግስቱ ታማኝ ማድረግ! ስልጣን ላይ ያለውን መንግስት ትእዛዝ ማክበር! የብሄር ብሄረሰቦችን መብት ማክበር!'*

ጄኔራል ሳሞራ የኑስ፣

"በእነዚህ መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ በመመርኰዝ ሰራዊቱ ውስጥ የፖለቲካ ግንባታ ማካሄድ አለብን" ሲል ማብራሪያውን አጠቃለለ።

በዚህ ውይይት ከተሳተፉት አንዱ የነበረው ኮሎኔል አለበል አማረ አንድ ጥያቄ አነሳ፣

"ከእነዚህ ነጥቦች በተጨማሪ ሰራዊቱን ስለ ሃገር ፍቅር ብናስተምረው፣ የሰራዊቱን ሰብእና የምንገነባበት መሰረትም ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ቢሆን አይሻልም ወይ?"

ሳሞራ ጥያቄውን ለውይይት አቀረበው፣

አከለ አሳየ እና ሃሰን ኢብራሂም የተባሉ ሁለት ጄኔራሎች በየተራ "ጠቃሚ አሳብ ይመስለናል" ሲሉ ተጨማሪ አስተያየት ሰጡ። በተቃራኒው ደግሞ ጄኔራል አብርሃ አረፈ፣ ጄኔራል መሃሪ ዘውዴ፣ ጄኔራል ኤፍሬም ባንጌ እና ሌሎችም በየተራ እየተነሱ የኮሎኔል አለበልን አሳብ አምርረው ተቃወሙ፣

"እኛ የታገልነው ለኢትዮጵያ አንድነት አይደለም። ለየብሄራችን ነፃነት ነው የታገልነው። ይህን ያረጀ ያፈጀ የነፍጠኞች የማታለያ ፕሮፓጋንዳ አንቀበልም። ነፍጠኞች ተስፋ ቢስ ፍላጐታቸውን ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በሚል ስውር መርዝ ሊጭኑብን ይፈልጋሉ!"

ተቃውሞ ጐረፈ። ቁጣ ጭምር ነበር። ሳሞራ የኑስ የወረደውን የውግዘት ዶፍ በፈገግታ ሲያስተናግድ ከቆየ በሁዋላ እንዲህ ሲል አሳረገው፣

"ምንም ተጨማሪ መስጠት አያስፈልገኝም። ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያዊነት፣ የሃገር ፍቅር የሚሉት ቃላት የነፍጠኞችን ህልም የተሸከሙ ማደንዘዣዎች ናቸው። ይህን አሳብ እዚህ ያራመዱት መኰንኖች ችግርም ነፍጠኛነት ነው"





* * *

ጄኔራል ተስፋዬ ሃብተማርያም የሚባሉ ሰው ታውቃላችሁ? "የጦር ሜዳ ውሎ" የተባለ መፅሃፍ ያሳተሙ፤ በሶማሊያ ጦርነት የጀግና ሜዳሊያ ተሸላሚ፤ ኢትዮጵያዊ ቆፍጣና የጦር ሰው ናቸው።

የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት እንደፈነዳ ወያኔ፣ "ሆዳም" እና "ፈሪ" እያለ ያላግጥባቸው የነበሩ የጦር መኮንኖችን በባትሪ ወደ መፈለግ ገብቶ ነበር። ጄኔራል ተስፋዬ የመጀመሪያው ተፈላጊ ሰው ሆኑና ለግዳጅ ወደ ትግራይ ተላኩ። ትግራይ ውስጥ ቤየራ ከተባለ ቦታ ከኮሎኔል በላይ ወታደራዊ ማእረግ ያላቸው 40 ያህል የወያኔ መኮንኖችን እንዲያሰለጥኑ ግዳጅ ተሰጣቸው። ጄኔራሉ ደርግ እንደወደቀ ለሶስት አመታት በወያኔ ታስረው የነበረ ቢሆንም፣ "መቼም ሃገር አደጋ ላይ ወድቃለች" ብለው በማመናቸው የወያኔን ጥሪ ተቀበሉ። ጄኔራሉ ከዚያ በፊት ስለ ወያኔ የጦር መሪዎች በቂ እውቀት የነበራቸው አይመስለኝም። የትም አገር ይሁን የት ግን አንድ ኮሎኔል ቢያንስ መሰረታዊ የሆነ የወታደራዊ ሳይንስ እውቀት ሊኖረው ይችላል ተብሎ ይገመታል። ጀግንነትና የወታደራዊ ሳይንስ እውቀት ለየቅሉ ናቸው። የወያኔ ከፍተኛ መኮንኖች አብዛኞቹ ጀግንነቱን ባያጡትም መሰረታዊ የሆነ የውትድርናና የአዛዥነት እውቀቱ ግን አልነበራቸውም። ጄኔራል ተስፋዬ በመጀመሪያው ቀን የትምህርት ክፍለ ጊዜ አንዲት ቀላል ጥያቄ በመጠየቅ ገመገሟቸው፣

"ማጥቃት ማለት ምን ማለት ነው?"

ወዲ እምበይተይ የሚባል ኮሎኔል እጁን አውጥቶ ማብራሪያ መስጠት ጀመረ፣

"ማጥቃት ማለት በሻእቢያ የተወረረብንን ሉአላዊ መሬታችንን ለማስመለስ የምናደርገው ፍትሃዊ ጦርነት..."

ጄኔራል ተስፋዬ አቋረጡት፣

"በቃህ! ቁጭ በል!"

ከዚያም ሲንጎራደዱ ቆዩና፣

"አይ ኢትዮጵያ!" ሲሉ አማረሩ።

እናም እንዲህ ሲሉ የመጀመሪያውን ትምህርት ሰጡ፣

"'ማጥቃት ማለት ጠላትን ደምስሶ መሬትን መንጠቅ

ማለት ነው። አበቃ!"

አያያዙናም እንዲህ ሲሉ አከሉ፣

"የመለስን ፕሮፓጋንዳ ርሱት። እናንተ ወታደሮች ናችሁ። 'ሉአላዊነት፣ ፍትሃዊ ጦርነት፣ በሻእቢያ የተወረረ መሬት...ይሄ ሁሉ እናንተን አይመለከትም። ወታደራዊ ሳይንስ ሙያ ነው። መጀመሪያ ሙያውን ማወቅ አለባችሁ። ሉአላዊነትህ ቢደፈርም ባይደፈርም፣ ብትወረርም ባትወረርም አጥቃ ከተባልክ ታጠቃለህ!"

* * *

አጤ ቴዎድሮስ ተዋበች የተባለች ባለቤታቸውን በሞት የተነጠቁ ጊዜ ችሎት አቁመው ተከታዮቻቸውን እንዲህ ሲሉ ጠይቀው ነበር፣

"ወይ ፍረዱልኝ! ወይ ፍረዱብኝ! ባልና ሚስት አንድ አምሳል ናቸው። ሚስቴን የሰደበ እኔን ሰደበ ማለት ነው። ነውም አይደል?"

"ልክ ነው" የሚል ድምፅ አስተጋባ።

"ምን ጥርጥር አለው?" የሚል ታከለ።

ችሎቱ ላይ በጥፋተኛነት ተይዘው ወደ ቀረቡት ተከሳሾች እያመለከቱም እንዲህ ሲሉ ቀጠሉ፣

"እነዚህ ሰዎች ተዋበችን ከባድ ስድብ ሰድበዋል። ፍርድ ስጡኝ? ወይ ፍረዱልኝ!? ወይ ፍረዱብኝ!?"

"ሞት!" የሚሉ ፍርዶች አስተጋቡ።

ስለዚህ የተዋበችን አስከሬን የሰደቡ ወታደሮች ላይ ሞት ተበየነ። በአሰቃቂ ሁኔታም ወደ ገደል ተወርውረው እንዲሞቱ ተደረገ። የአጤ ቴዎድሮስ ውድቀት የጀመረው በዚያን እለት መሆኑ ይነገራል። እነዚያ ወታደሮች በተገደሉበት በዚያን ሌሊት 100 ወታደሮች ኮብልለው አደሩ። አጤ ቴዎድሮስ ቋራ ላይ 50 ሰው ይዘው የትጥቅ ትግል ከጀመሩበት እለት አንስቶ ይህን ያህል ቁጥር ያለው ወታደር ሲከዳቸውም የመጀመሪያ ጊዜው ነበር። በርግጥ ይህን የቴዎድሮስ ስህተት ልንመዝነው የሚገባው፣ አጤ ቴዎድሮስ የነበሩበትን ዘመን ግምት ውስጥ በማስገባት ነው። ከ100 አመታት በሁዋላ መለስ ዜናዊ ይህንኑ የቴዎድሮስን የሆግ አልባነት ድርጊት እየደገመ ይገኛል።





በ1998 የመከላከያ የአምስት አመት እቅድ ውይይት የተካሄደው በፕላዝማ የቪዲዮ መረብ አማካይነት ነበር። ከስብሰባው ተካፋዮች አንዱ የነበረ አበበ ገረሱ የተባለ ኮሎኔል እንዳጫወተኝ መለስ ዜናዊ ከቤተመንግስት ሆኖ ውይይቱ ላይ ተሳትፎ ነበር። ከፍተኛ መኮንኖች ኮንፈረንሱን መቀሌ፣ ባህርዳር፣ ሃረርና አዲሳባ ሆነው ይከታተሉት ነበር። ከአንዱ አቅጣጫ እንዲህ የሚል ጥያቄ ለመለስ ዜናዊ ቀረበለት፣

"የመከላከያ አመራር ዝርክርክ ነው። ገንዘብ አባካኝም ነው። ስለዚህ ጉዳይ ርስዎ ምን ይላሉ?"

መለስ ግልፅና አጭር ምላሽ ሰጠ፣

"የመከላከያ አመራር አካባቢ ገንዘብ የማባከንና እንደተባለው የመዝረክረክ ችግር ሊኖር ይችላል። ቢሆንም አመራሩ የህገመንግስቱ የቁርጥ ቀን ልጅ መሆኑን ሁለት ጊዜ አስመስክሮአል። የመጀመሪያው በህወሃት መከፋፈል ወቅት ሲሆን፣ ሁለተኛው በምርጫ 97 ግርግር ጊዜ ነው። የመከላከያ አመራር በሁለቱ ወሳኝ ጊዜዎች ያሳየው ብቃቱ ከደካማ ጎኑ ይልቅ ሚዛን ይደፋል። የመከላከያ አመራር ምንም ቢቀጥን ጠጅ ነው..."

የመከላከያ ሰራዊት የብቃት መለኪያ የመለስን ስልጣን ከመጠበቅ አንፃር ብቻ የሚለካ መሆኑን መለስ ግልፅ አደረገ።

ልቡና አንጎሉ በእብሪት የተሞላ ሰው የማዳመጥ ችሎታውን እያጣ የሚሄድ ሲሆን፣ ዝንባሌውም መናገር ብቻ ይሆናል። የራሱ ድምፅ መልሶ ጆሮው ላይ እስኪጮህበት ድረስ ስለ ራሱ ውዳሴ ከንቱ ያበዛል። እዚህ ደረጃ ላይ የደረሰ ሰው ወደ ሁዋላ ተመልሶ የራሱን ሚዛን ለመረዳት በእጅጉ ይቸገራል። እብሪት ወደ ድንቁርና ገደል ይዞህ የማሽቆልቆል ጠባይም አለው።

አንቶን ቼኮቭ የተባለው የሩስያ ደራሲ በዘመኑ የነበሩ ሃኪም ጓደኞቹን እንዲህ ሲል ተችቶአቸው ነበር።

"...ከ40 አመት እድሜያቸው በሁዋላ ከጤና መፅሄት በቀር ሌላ ማንበብ አይሹም። በመጨረሻም 'የበሽታዎች ምንጭ ሁሉ ብርድ ነው' ብለው ይደመድማሉ"

# -9-

# የወያኔ ምስጢሮች

ሰይጣን ሰለጠነ፣
ቀንዶቹን ነቃቅሎ፣ ጭራውንም ቆርጦ...
ዘመናዊ ሆነ፣
ፊደል ቆጠረና፣ ዳዊትም ደገመ፣
ውዳሴ ማርያምን፣ አንቀፀ ብርሃንን፣ አጠና ፈፀመ፣
ግና ተቸገረ፣ እንዲያው በየእለቱ፣
ጨርሶ አላወቀም፣ ለማን እንደሆነ ያምና ፀሎቱ፣
ቢጨንቀው ጊዜና፣ ቆይቶ ሰንብቶ,
ክርስትያን የሆነ አንድ ሰው አግኝቶ፣
ተወዳጅውና ብሶቱን ነገረው፣ ሁሉንም ዘርዝሮ፣
በጣፈጠ ቋንቋ፣ በውነት አሳምሮ፣
"አትቸገር!" አለው፣ ክርስትያን ወዳጁ አፅናናው መልሶ፣
ሰይጣኑ ካሰበው አለመጠን ብሶ፣
"ይህስ ቀላል ነገር፣ ችግርም የለው፣
እንደኛው ክርስትያን፣ ሆንክ ማለት ነው"

(ግጥም - ዮሃንስ አድማሱ)

"የወያኔ ምስጢሮች" በሚለው በዚህ ርእስ አንድ ሙሉ መፅሃፍ መፃፍ በቻልኩ ነበር። አጀንዳዎቹ ግን ተደጋጋሚ ይሆናሉ። "የወያኔ አመራር አባላት ገንዘብ እየዘረፉ በውጭ ሃገር ባንኮች ያከማቻሉ፤ አለያም ሰው ይገድላሉ" የሚል ዜና ምስጢር አይደለም። ምንጊዜም የትረካ ትኩረቴ ሰው መግደላቸው ሳይሆን፣ ሰው የሚገድሉበት መንገድ ላይ ነው። ገንዘብ መዝረፋቸው ሳይሆን ገንዘብ ለመዝረፍ የሚጠቀሙበት ስልት ነው። በዚህች አጭር አንቀፅም ይህን መሰል አንዳንድ ነጥቦችን አወጋለሁ...

* * *

ሚያዝያ አጋማሽ፣ 2002 የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ





ኮሚቴ አባላት አዲሳባ ላይ ስብሰባ ማድረጋቸው ወሬው ሾልኮ ወጥቶ ነበር። ስብሰባው አስቸኳይ የነበረ ሲሆን፣ በአጀንዳ የተያዘ አልነበረም። መለስ ለፖሊት ቢሮ አባላቱ ቀልድ የሚመስል አንድ ግዙፍ ጥያቄ አቀረበ፣

"የ2002 ምርጫ እየተቃረበ መጥቷል። ስለዚህ ይህ የኢህአዴግ አመራር አካል መቀጠል አለበት ወይስ የለበትም?"

አያያዘና አከለበት፣

"...የት ድረስ ነው የምንቀጥለው? የት ድረስስ መሄድ እንችላለን? ግልፅ በሆነ መንገድ እንወያይበት። ተወያይተንም የአብዛኛውን ውሳኔ እናሳልፋለን"

በቅድሚያ ጥያቄ አዘል አሳብ የተሰነዘረው ከህወሃት ወገን ነበር። እየተቀባበሉ እንዲህ አሉ፣

"በመሰረቱ ስልጣን እንልቀቅ ብንል የሚረከበን አለ ወይ? ሊረከበን የሚችለው የተዘጋጀ ሃይል ማነው? በዙሪያችን በጠላት ተከበናል። በዚህ ሁኔታ ላይ ሆነን በቀላሉ የስልጣን ሽግግር ማድረግ ይቻላል ወይ? የተጀመሩት የልማት ስራዎችስ አይቋረጡም ወይ?"

በመቀጠል ተፈራ ዋልዋ አስተያየት ሰጠ።

ተፈራ ረዘም ያለ ዲስኩር ቢጤ ያሰማ ሲሆን፣ ጭማቂው እንዲህ ነበር፣

"ረጅም ጊዜ በስልጣን ላይ ቆይተናል። እድሜያችንም ገፍቶአል። እያረጀን ነው። ሃገሪቱን በመምራት ረገድም ተሳክቶልናል ማለት አይቻልም። እኔ በበኩሌ በቅቶኛል። እናንተ ባትለቁም እኔ ስልጣን ላይ የመቆየት ፍላጎት የለኝም..."

በረከት ስምኦን በመቀጠል፣

"መልቀቅ አለብን" ሲል ተፈራን ደግፎ ተናገረ "...ሌላውም ይሞክረው። አምባገነን እየተባልን እንወገዛለን። ሰርተንም አልተመሰገንንም። እኛ የቆምንበትን እሳት ሌላውም ይሞክረው። ምናልባትም እኛ አፍነን ይዘነው ይሆናል እንጂ ከስር ጠንካራ አመራር ሊወጣም ይችላል። እንግዲህ ስትራቴጂውን ነድፈናል። በተነደፈው ስትራቴጂ ደግሞ የልማት ስራውን በተቻለ አቅም ሞክረናል። ጉልበት ያለው ደግሞ ስልጣኑን ይረከብና ይቀጥለው። ህወሃቶች ስልጣን ላይ ለመቆየት ብትወስኑ እንኳ እኛ ብአዴኖች ስልጣን መልቀቁን እንመርጣለን..."

በዚህ ውይይት የህወሃት ፖሊት ቢሮ አባላት ለሁለት ተከፍለው ነበር። "እንልቀቅ"፣ "የለም አንለቅም" በሚል ክርክር ቢጤ አሰምተዋል። የአህዴድና የደቡብ ፖሊት ቢሮ አባላት በቁጥር እኩል ውክልና የተሰጣቸው ቢሆኑም አንዳችም ቃል አልተነፈሱም።

በመጨረሻ መለስ፣ "ስልጣናችንን እንልቀቅ" የሚለውን ወገን ደግፎ አስተያየት ሰጠና አጀንዳውን በድምፅ ብልጫ ዘጉት። "የተዘጋጀ የሚረከበን ሃይል ስለሌለ ስልጣን መልቀቅ የለብንም" ያሉ ሶስት ሲቀሩ፣ ቀሪው፣ "ስልጣናችንን እንልቀቅ" የሚለውን ደገፈ።

በክርክሩ ወቅት፣ "ስልጣን መልቀቅ የለብንም" ያሉት የህወሃት ወገኖች በመከራከሪያነት ካቀረቡት ነጥብ ዋናው፣ "ሻእቢያ ስልጣን ላይ እያለ ስልጣን ከለቀቅን ሃገሪቱን በእጅ አዙር ይቆጣጠራታል" የሚል ነበር። ለዚህም የመከራከሪያ ነጥብ አንድ ማሰሪያ ተበጀለት።

ይህም፣ "እኛ ስልጣን ከመልቀቃችን በፊት በማንኛውም መንገድ ሻእቢያ ከስልጣኑ መወገድ አለበት" የሚል ሆነ። ሻእቢያን እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል ግን አልተገለፀም። 'በጦርነት ወይስ በመፈንቅለ መንግስት?' ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ሳያስቀምጡ ስብሰባው ተቋጨ።

በዚሁ የፖሊት ቢሮ ስብሰባ ከስልጣን ለሚለቁ ባለስልጣናት ሊሰጥ ስለሚገባ ጥቅማ ጥቅም ጉዳይም ተነስቶ ነበር። ዝርዝር ተሰርቶለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲፀድቅና ለፓርላማው እንዲቀርብ ወስነው ተለያዩ።

ይህን የወያኔ የፖሊት ቢሮ ስብሰባ መረጃ ያገኘሁት ስብሰባው በተካሄደ በአስረኛው ቀን ግድም ነበር። መረጃውን ከአስተማማኝ ሰው በማግኘቴ ወሬውን እንደሰማሁ በትኩሱ፣

"እነዚህ ሰዎች ተቸግረዋል ማለት ነው" ብዬ ነበር። መረጃውን ተኝቼበት ካደርኩ በሁዋላ ግን የመለስና የበረከትን ቁማር ለመተንተን ጥረት አደረግሁ።

ገና ከመነሻው የፖሊት ቢሮው ስብሰባ ምስጢር እንዲህ ቃል በቃል እንዴት እኔ ዘንድ ሊደርስ ቻለ?

እኔ በቀላሉ ነበር ያገኘሁት።

ከቀድሞ የወያኔ ጓደኞቼ አንዱ ነበር ዝርዝሩን የላከልኝ። ጓደኛዬ ነባር ታጋይ ቢሆንም ከከፍተኛ አመራር





አባላት አንዱ አልነበረም። የፖሊት ቢሮውን የስብሰባ ምስጢር እንዴት ሊያገኝ እንደቻለ እንዲያብራራልኝ በነጋታው መልእክት ፃፍኩለት።

የፖሊት ቢሮ አባላቱ ስብሰባ በተካሄደ በ2ኛው ቀን በተደረገ አንድ የኮክቴል ግብዣ ላይ ተፈራ ዋልዋ በመጠጥ ተገፋፍቶ ይህን ምስጢር እንደተናገረ ጓደኛዬ አጫወተኝ።

*(ጓደኛዬ ይህን እንዳጫወተኝ እዚህ በይፋ መፃፌ የሚያስከትልበት አደጋ አለመኖሩን አረጋግጬ ነው ይህን የማወጋችሁ።)*

የሆነው ሆኖ ጓደኛዬ ዋሽቶአል ብዬ አላስብም። ጓደኛዬ እኔን የማሳሳት አላማ ሊኖረው አይችልም። እኔ የጋዜጠኛነቱን ስራ ትቼ በሙሉ ጊዜ የደራሲነት ስራ ላይ በመሆኔ መረጃውን ወዲያው እንደማልጠቀምበት ግልፅ ነበር። ስለሆነም ጓደኛዬ በትክክል መረጃውን ግብዣው ላይ እንደሰማው ግምት ወስጃለሁ። ተፈራ ዋልዋም የስብሰባውን ይዘት ሳይቀንስና ሳይጨምር እንዳለ ተንፍሶታል ብዬም አምኛለሁ። ተፈራ ይህንን ምስጢር ያወጣው ግን በመጠጥ ተገፋፍቶ ነው ብዬ አላምንም። ይህን ወሬ በዚያ የኮክቴል ግብዣ ላይ እንዲያወራ መለስ ዜናዊ ራሱ አዞታል። የስብሰባው አላማም ሆነ ይዘት ወሬው እንዲወራ ብቻ ነበር። አሰራራቸውን በቅርብ የማውቅ እንደመሆኔም ግምቴ ወደ እውነቱ ሊቃረብ እንደሚችል አስባለሁ።

ወያኔ እንዲወሩለት የሚፈልጋቸውን ወሬዎች በምስጢር መልክ እየሾለኩ እንዲወጡ የማድረግ ልማድ እንዳለው አውቃለሁ። ለዚህ አይነት ድብቅ አላማ ያላቸው ዜናዎች ከተጋለጡት ሚዲያዎች Indian Ocean news letter የተባለው በራሪ ጋዜጣ ዋነኛው ነው። የወያኔ የፀጥታ ክፍል ተቀማጭነቱ አዲስ አበባ ላይ ሆኖ ለፈረንሳይ የስለላ ድርጅት የሚሰራውን ጆሮ ጠቢ ማንነት አያውቁም ለማለት አይቻልም። ለገሰ አስፋው በKGB ይታማ እንደነበረው ሁሉ፣ ለተለያዩ የስለላ ኤጀንሲዎች መረጃ የማቀበል አገልግሎት የሚሰጡ የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት መኖራቸው ግልፅ ነው። መለስ ዜናዊ ራሱ ለCIA ቢሰራ ሊደንቀን አይገባም። ስልጣን በከዳው ጊዜ ከነቤተሰቡ መጠለያ ለማግኘትና በወንጀል ያለመጠየቅ ዋስትናውን ለማስጠበቅ ያን ሊያደርግ ይችላል። ምእራባውያኑ የሃገር ፍቅር

ስሜት የሌላቸውን መሪዎች አፍሪቃ ላይ ለማንገስ የሚባዝኑት ጥቅማቸውን ያለ እንቅፋት ለማስጠበቅ መሆኑ በግልፅ የሚታወቅ ነው።

ከዚህ ባሻገር ወያኔ ከቁጥጥሩ ውጭ ለውጭ መንግስታት የሚሰሩ ሃበሻ ሰላዮችን በሁለት መንገድ ያስተናግዳቸዋል። የመጀመሪያው ይገለብጧቸውና እንዲወራላቸው የሚፈልጉትን መረጃ ይመግቧቸዋል። (መገልበጥ ማለት ተመልሶ ለነሱ እንዲሰራ ማስገደድ ማለት ነው።) ሁለተኛው አማራጭ ያስወግዱቸዋል። (ማስወገድ ማለት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መግደል ማለት ነው) ከዚህ ሌላ በራሳቸው ፍላጎት ለሁለቱም ወገን የሚሰሩም አሉ። አብዛኞቹ ከፍተኛ ምሁራን ናቸው። የሲአይኤ ሰላይ መሆናቸው እየታወቀ ሹመት የተሰጣቸው ኢትዮጵያውያን አሉ። እኔ ቢያንስ አንድ ሰው አውቃለሁ። እኔ ከማውቀው በላይ የሚያውቁ መኖራቸውንም አውቃለሁ። አንዳንድ ሰዎችን አደጋ ላይ ላለመጣል ስል እዚህ በዝርዝር ላሰፍረው የማልችለው መረጃ ሊኖር እንደሚችል መገንዘብ የሚቻል ይመስለኛል። በደፈናው ለመግለፅ ያህል ግን በተለይ የተለያዩ የተራድኦ ድርጅት ያቋቋሙ ግለሰቦች በአብዛኛው ለአንዱ ወይም ለሁለቱም ወገን ያገለግላሉ። ጠንካራ ገቢም ያገኙበታል። ከህወሃት የማእከላዊ ኮሚቴ አባላት መካከል አንዱ (ሙሉጌታ አለምሰገድ) መለስ እያወቀ ለሲአይኤ ይሰራል። ይህ መረጃ በከፍተኛ ምስጢር የተያዘ አይደለም። እንደ ብልጠትና ጥበብ በመቁጠር በተለያዩ አጋጣሚዎች ለቅርብ ሰዎቻቸው ይናገሩታል። በዚህ ስራ ከፍተኛ ገቢ ቢያገኙበትም አላማቸውና ግባቸው ግን ገንዘብ ማግኘት አይደለም። በጥቅሉ ሙሉጌታ አለምሰገድ ለሲአይኤ የሚልከው መረጃ የመለስ-ስብሃትን የስልጣን እድሜ የሚደግፍ ቢሆንም፤ ኢትዮጵያን እንደ ሃገር ሊጎዳት እንደሚችል አያጠራጥርም። ጉዳቱ ዛሬ ላይታይ ይችላል። እኛ በህይወት እያለን ግን ይህ መከረኛ ህዝብ የገፈቱ ቀማሽ ይሆናል። በቀጥታ ለማስቀመጥ የወያኔ ሰዎች የሃገሪቱን ብሄራዊ ምስጢርና ደህንነት ለህወሃት በሚጠቅም መንገድ እየሸጡት ይገኛሉ። የብሄረሰቦች የርስበርስ ግጭት፣ መሬት፣ የአፈርና የውሃ ሃብቶች፣ የሶማሊያ ጣልቃ ገብነት፣ የኢጋዴን የከርሰምድር ሃብት፣ የአኝዋክና የጋምቤላ ትርምስ በሚዲያ ከምንሰማው ባሻገር የተወሳሰቡ የጥቅም ይዘት ያላቸው ናቸው።





እንግሊዛውያን ፋሺስት የተባለውን የኢጣሊያ የፖለቲካ ድርጅት ከኢትዮጵያ ይዞታው በማስወገዱ ዘመቻ እርዳታ በሰጡበት ወቅት ኢትዮጵያን ወደ አምስት ሃገራት ለመከፋፈል ያደረጉት ሙከራ አልተሳካላቸውም። በወቅቱ ስልጣን ላይ ያልነበሩት መሳፍንት ይህን ለማስፈፀም ዝግጁ ሳይሆኑ ቀርተዋል። በዚህ ዘመን ግን የኢትዮጵያ ጠላቶች የዚህችን ሃገር ህልውና በሚፈልጉት መንገድ አዳክሞ ለመግዛት የተመቸ ለም መሬት አግኝተዋል።

ኢትዮጵያ የሃገር ፍቅር በሌላቸው ኢትዮጵያውያን ቁጥጥር ስር ናት የሚለውን አባባል ካመንኩበት ቆይቻለሁ። ህዝቡ ይህን ያውቃል። መርቶ ነፃነቱን የሚያስጨብጠው እስካላገኘ ድረስ ግን አንዳችም ምርጫ የለውም። በፖሊስ ጡጫና በህገመንግስት ዘፈን ተቀፍድዶ ህይወቱን ይገፋል። እንግሊዞች ቻይና ላይ ኮኬይንና ሄሮይን መሸጥ እንዲችሉ ስልጣን ላይ የነበረውን መንግስት ለማስገደድ የቻሉበት አንድ ዘመን ነበር። በተመሳሳይ መለስ ዜናዊ ብብቱን ከፍቶ መሬቱንም ሆነ የከርሰ ምድር ሃብቱን፤ ከዚህም ባሻገር የፀጥታ ምስጢሩን ለምእራባውያኑ እየቸበቸበው ይገኛል። ምእራባውያኑ ሙጋቤን ያደርጉት እንደነበረው አቅሙ እስኪደክም ወተቱን ያልቡታል። የሚያሳዝነው ነገር መለስ ዜናዊ 'የሚታለበው ወተት የኔ አይደለም' ብሎ ማመኑ ነው።

* * *

አሰፋ ማሩ 'የእንግሊዝ ሰላይ' እንደነበር ስዩም መስፍን እንደነገረኝ በቀዳሚው መፅሃፌ ገልጬ ነበር። ስዩም ያን ምስጢር የነገረኝ እኔ ለህወሃት ታማኝ ስለነበርኩ አይደለም። ጋዜጠኛ ነኝ። በአናቱ ከትግራይ ጎሳ አይደለሁምና አምኖ ምስጢር ሊነግረኝ አይችልም። ወሬው እንዲወራ ተወስኖ ስለነበር ሊሆን ይችላል በቀላሉ የነገረኝ። አሰፋ ማሩ የእንግሊዝ ሰላይ ተብሎ ሲረሸን ከሁለት በላይ የምእራባውያን ሃበሻ ሰላዮች በፍርሃት ተንቀጥቅጠው በፈቃዳቸው ራሳቸውን እንደ ገለበጡ ሰምቻለሁ። ይህ ደግሞ ከሚጠበቁ ውጤቶች አንዱ ነበር።

ወያኔ ስልጣን ሊለቅ የማሰቡ ወሬ እንዲወራለት በመፈለጉ በኮክቴል ግብዣው ላይ ወሬው እንዲሾልክ አድርጎአል። አስቂኙ ቀልድ ግን አብዛኞቹ የአመራሩ

አሻንጉሊቶች የዚህ ድራማ አካል አለመሆናቸው ነበር። የህወሃት አመራር አባላት፣

"ስልጣን እንልቀቅ"

"የለም! አንለቅም" ክርክር ድራማ መሆኑን ሊያውቁ የሚችሉበት እድል አልነበረም።

*(የተሻለ፣ የተማረ፣ ያነበበ የሚባለው ዶክተር ካሱ ይላላ እንኳ ምሁራዊ ነፃነቱን ሊያስጠብቅ አልቻለም። ህወሃት በሰላይነት ካስቀመጠለት ፀሃፊው ጋር ፍቅር ይዞት ቢሮው ብቻ ሳይሆን የአንሶላ ውስጥ ምስጢሩ ሳይቀር በቁጥጥር ስር ውሎአል። አዲሱ ለገሰ እንደተምታታበት የተጎለተ አሞሌ ጨው ነው። እድሜው በብስጭት እየሟሟ አልቆ አንዲት የንስሃ ሃሙስ ብቻ ቀርታዋለች። በረከት የድራማውና የፉገራው አካል ሊሆን እንደሚችል ግልፅ ነው። "የፍየል ጃኬት የለበሰ ቀበሮ" መሆኑን የጎንደር እረኞች ገና ድሮ ነቅተውበታል። ፍየሎቹም በረከት ፍየል እንዳልሆነ ገና ድሮ አውቀዋል። ቢሆንም ያላወቁ መስለው ቅዳሜ ዞሮ እስኪመጣ፣ አብረውት ቅጠል ይቀነጣጥባሉ። ተራቸው ሲደርስ ቀበሮው ከቅጠሉ ጋር ደርቦ እንደሚቅማቸው ያውቃሉ። በቀበሮ እስኪቃሙ ቅጠል እየቃሙ ይቆያሉ። በዚህ መሃል የበረከትን ጃኬት ለመግፈፍ የሚደፍር አልታየም ማለት አይቻልም። እየተቀደሙ አልቀዋል። የሌኒን እጣ እንዳይደርስባቸው ሰግተው ያደፈጡም ከጥቂት በላይ ናቸው...)*

ወደ ነጥባችን እንመለስ...

መለስ የዚያ ስብሰባ ዝርዝር ድራማዊ ይዘት እንዲወራ ፈልጎ ነበር። ተወራለት። ወሬውም የሚፈልገውን ውጤት አስገኝቶለታል። መለስና ጓደኞቹ ከወሬው ምን ፈልገው እንደነበር ግልፅ ነው። እነ መለስ የዚያን ስብሰባ ድራማ የሰሩት በትክክል ስልጣን ለመልቀቅ ፍላጎት እንደነበራቸው እንዲታመንላቸው ብቻ ነበር። ሁዋላ፣ "ፓርቲያችን ከለከለን" ብለው ለማመካኘት እንዲመቻቸው ቀደም ብለው ይህችን "የሾለከች" ምስጢር በተኑ። እርግጥ ነው እኛ ደቂቃን ለጊዜው ብንሸወድ እንኳ ዞሮ ዞሮ እናውቃቸዋለን። በገንዘብ እየደጎሙ እዚህ ያደረሷቸውን ምእራባውያን ግን አታለውበት ሊሆን ይችላል....





* * *

ኦነግ ከምርጫ 84 ራሱን ባገለለ ማግስት ተፈራ ዋልዋ ከ150 በላይ የምንሆን የአዲሳባ ክልል ካድሬዎች፣ ጋዜጠኞችና የመምሪያ ሃላፊዎችን ሰብስቦ እንዲህ ሲል መመሪያ ሰጠን፣

"የኦነግ ሰራዊት ብዛት ከ50 ሺህ በላይ መሆኑን ከተማ ውስጥ በሰፊው አውሩ። ላገኛችሁት ማንኛውም ሰው በእግረ መንገድ ወሬ እያደረጋችሁ ስለ ኦነግ ሰራዊት ሃያልነት ንገሩ!"

በወቅቱ ተፈራ ዋልዋ ይህን ወሬ እንድናወራ ለምን እነደፈለገ አልገባኝም ነበር። ምስጢሩን የተረዳሁት ከሶስት ሳምንታት በሁዋላ ነበር። እንደተፈለገውም ወሬው በከተማዋ ውስጥ በአጭር ጊዜ ውስጥ በሚፈለገው ደረጃ ሊሰራጭ በቅቶ እንደነበር አስታውሳለሁ። ስብሰባው ላይ ካልነበሩና የኢህአዴግ አባል ካልሆኑ ሰዎች ጭምር ወሬው ተመልሶና ተጨማምሮበት ለኔ ደርሶኝ ነበር።

"ሰማህ ወሬውን" አለኝ አንዱ በሶስተኛው ቀን አካባቢ።

"የምን ወሬ?"

"የኦነግ ሰራዊት ካምፑን ለቆ ሊወጣ ነው ይባላል። 75 ሺህ የታጠቀ ሰራዊት አላቸው ነው የሚባለው። ለኢህአዴግ ከባድ ይሆንበታል። ቢያንስ መላ ኦሮሚያን ሊቆጣጠሩ ይችላሉ እየተባለ ነው።"

ሌላው ደግሞ፣

"ምንድነው ባክህ የሚሰማው?"

"ምን ሰማህ?"

"ወጣት ኦሮሞዎች በብዛት ኦነግን ለመቀላቀል ወደ ጫካው እየጎረፉ ነው ይባላል። ገላሳ ድልቦ ራሱ ነው አሉ የሚመራቸው። ይህች ሃገር ከጦርነት መላቀቅ አልቻለችም። ሃገሪቱ በእሳት መቀጣጠሏ ነው። አወይ መከራ! እንደ ሩዋንዳ እንዳንሆን ብቻ!"

እኔ ስብሰባው ላይ እንደነበርኩ ያላወቀ የወያኔ አባል ለኔው መልሶ እንዲህ አለኝ፣

"የኦነግ ሰራዊት ከኢህአዴግ ጋር የሚመጣጠን ቁጥር አለው ይባላል። ከባድ ውጊያ የሚቀርልን አይደለም።"

ወሬው ሲቦካና ሲጋገር ከሰነበተ በሁዋላ ሚስጥሩን ደረስኩበት። እርግጥም እንደተወራው የኦነግ ሰራዊት ካምፑን ለቆ ወጣ። ምንም ሊያደርግ የሚችል ግን አልነበረም። የኦነግ

ሰራዊት ሰፍረውባቸው የነበሩ ካምፖች በሙሉ ቀደም ብለው በሶስት ዙር የቀለበት ከበባ ስር ነበሩ። ከካምፕ ወጥተው ለመግደያ ምቹ ከሆነ ሜዳ ላይ ሲገቡ፣ በድምፅ ማጉያ ጠመንጃቸውን እንዲያወርዱ ተጠየቁ።

የተፈፀመው በጀግንነት ወይም በፈሪነት መለኪያ የሚመዘን አልነበረም። ባጭሩ የአነግ ሰራዊት ሊዋጋ የሚችልበት ሁኔታ ውስጥ አልነበረም። ሰራዊቱን የሚመራ የተደራጀ ሃይልም አልነበረም። እየተካሄደ ስለነበረው የፖለቲካ ሸኩቻም ሰራዊቱ በቂ ግንዛቤ አልነበረውም። ሰራዊቱ በዚህ ሁኔታ ላይ ሆኖ ከባድ መሳሪያ በተጠመደበት ሜዳ ላይ ተገኘ። የህወሃት ወታደሮችም ቢሆኑ በዚህ ሁኔታ ላይ ቢገኙ ተዋግተው ውጤት ሊያመጡ አይችሉም ነበር። በመሆኑም የአነግ ሰራዊት በጀብደኛነት ህይወቱን ማጣት፣ አሊያም ጠመንጃውን አውርዶ መማረክ ቀሪ አማራጮቹ ነበሩ። የአነግ ሰራዊት በዚህ መንገድ ጠመንጃውን አውርዶ ከተማረከ በሁዋላ ግን ብሶት የወለደው "ጀግናው" መለስ ዜናዊ በቴሌቪዥን መስኮት ቀርቦ እንዲህ ሲል ተመፃደቀ። አሊያም ባዲሳበቤ ቋንቋ መለስ እንዲህ ስትል ጉራዋን ቸረቸረች፣

"ሰሞኑን ከተማ ውስጥ ሲወራ እንደ ነበረው የአነግ ሰራዊትን መቆጣጠር ለኛ አስቸጋሪ አልነበረም። ውጊያ አካሄድን ማለትም አይቻልም። የአነግን ሰራዊት በቁጥጥር ስር ለማዋል የፖሊስ ስራ ብቻ ነበር የሰራነው።"

ሚዲያዎችም አይናቸውን በጨው አጥበው፣ ጆሮአቸውን በጥጥ ደፍነው እንዲህ እያሉ የህዝቡን ጆሮ አደነቆሩ።

"ገናናነቱ ሲነገርለት የነበረው የአነግ ሰራዊት ግማሽ ቀን ባልሞላ ውጊያ ፍርክስክሱ ወጣ! ኢህአዴግ የማይደፈር ህዝባዊ ሃይል መሆኑ ተረጋገጠ! የአነግ ሰራዊት እንደ አቧራ በነነ!"

ከፀሃፊዎቹ አንዱም እኔ ነበርኩ...

* * *

በአንድ ስብሰባ ላይ መለስ ዜናዊ፣

"ከቡና ይልቅ ሰላም አስከባሪ ሃይል በማሰማራት የምናገኘው ገንዘብ የላቀ ነው" ሲል ተናግሮ ነበር።

መለስ አልዋሸም።

ገንዘቡ ወደ ሃገሪቱ ካዝና አይገባም እንጂ ከሰላም





አስከባሪነት ቢዝነስ ወፍራም ገንዘብ እየተዛቀ ይገኛል።

መለስ አንድ ጊዜ መቀሌ ላይ፣

"ኦሮምያ የቡና እግሮች አሏት። እኛ ደግሞ የገበሬ እግሮች አለን" ብሎ ሲናገር በህብረት ተስቆለታል።

አያያዘናም አባባሉን አብራራ፣

"...ትግራይ የተማረ የሰው ሃይል የላትም። የማእድን ሃብት የላትም። የእርሻ መሬት የላትም። በዚህ ወቅት ያለን ሃብት ገበሬ ብቻ ነው። ስለዚህ የሌሉንን እስክናፈራ ባለን ሃይል መጠቀም ይገባናል።"

የመለስ አባባል ግልፅ ነበር።

ገበሬ በአንድ አዳር ምሁር ወይም ባለሃብት ሊሆን አይችልም። በወቅቱ ትግራይ ውስጥ ፋብሪካ ስላልነበረ ገበሬው በአጭር ጊዜ ወደ ላባደርነት ሊቀየር የሚችልበት እድል አልነበረም። ወታደር መሆን ግን ይቻለዋል። ይቻለዋል ብቻ ሳይሆን የትግራይ ገበሬ አነጣጥሮ የመተኮስን ሙያ እየተማረው ቆይቶአል። እነ መለስ፣ 'የውትድርናው ዘመናዊ ሙያ ባይኖረን እንኳ፣ ለመሞት ባለን ቁርጠኛነት የተሻለ ብቃት አለን' ብለው ያምናሉ። ገበሬዎች ከውትድርናው ባሻገር በጉልበታቸው ግድብ እና የመሳሰሉትን የጉልበት ስራዎች ሊሰሩ እንደሚችሉ መለስ አብራርቶ ሲያበቃ፤ ወታደር በበኩሉ ገቢ በሚያስገኝ ስራ ላይ ሊሰማራ እንደሚችልም ጠቀሰ።

የቡና እግሮች! የወታደር እግሮች!

ከወያኔ በፊት ስልጣን ላይ የነበሩት መሪዎች ከነሙሉ ችግሮቻቸው በሃገሪቱ ላይ ያላቸው አስተሳሰብ ግልፅ ነበር። እንዲህ ያምኑ ነበር፣

"ቡናው የኢትዮጵያ ነው። እኛ ደግሞ ኢትዮጵያውያን ነን። ስለዚህ ቡናው የኛ ነው"

የወያኔ ሰዎች በዚህ ቀመር ማሰብ ስላልቻሉ፣ ማሰብ በቻሉበት መንገድ እየነጎዱ ይገኛሉ። መንገዱ ወዴት እንደሚያደርስ ማሰብ ያስቸግራል።

ከቡናው ይልቅ የሰላም አስከባሪ ሃይል ማሰማራት ለወያኔ ታላቁ የገቢ ምንጭ ሆኖ ቆይቶአል። ቀጥሎአልም። ይህን እስከምፅፍበት እለት ድረስ ወያኔ ወደ ሩዋንዳ ሁለት ዙር፤ ወደ ብሩንዲ ሶስት ዙር፤ ወደ ላይቤሪያ አራት ዙር፤ ወደ ዳርፉር አንድ ዙር የሰላም አስከባሪ ሰራዊት አሰማርቶአል።

በአንድ ዙር አንድ ብርጌድ ሰራዊት ይዘምታል። አንድ ብርጌድ ሰራዊት ማለት 1700 የሰው ሃይል አለው። UN ለአንድ ወታደር በወር 500 ዶላር ይከፍላል። ከዚህ የሙሉ ክፍያ ገንዘብ ውስጥ ለወታደሩ የሚሰጠው 20% ብቻ ሲሆን፣ ቀሪው የት እንደሚገባ የሚያውቁት አባ ዲያቢሎስና አባ መለስ ብቻ ናቸው። አንድ ዙር ሰራዊት በውጭ ሃገር እስከ 11 ወራት ይቆያል። እያንዳንዱ ወታደር ለያዛት ጥይት UN ለአንድ ጥይት በቀን አንድ ዶላር ይከፍላል። ነጭ ቀለም እየተቀቡ የሚላኩት ታንኮች፣ ከባድ መሳሪያዎች፣ የነፍስ ወከፍ ጠመንጃዎች፣ ቦቴዎች እና ሌሎች መኪኖች ወደ ሃገር አይመለሱም። 'እንደ ወጣች ቀረች' ይሆናሉ። UN ኪራይ ሲከፍልባቸው ይቆይና በዚያው ይሸጣሉ። የዳቦ መጋገሪያ ማሽኖች፣ ሄሊኮፕተሮች፣ መኪኖች ለሲቪሎች ይከራያሉ። በሰላም አስከባሪው ስም የሚወጣው ነዳጅ በጎን ሳይሆን በግልፅ ይቸበቸባል። ከዚህ በተጨማሪ በአንድ ዙር ከሰላሳ ያላነሱ ወታደራዊ ታዛቢዎች ይላካሉ። UN ለአንድ ታዛቢ በቀን 130 ዶላር ይከፍላል። ይህን ክፍያ ታዛቢው ሙሉ በሙሉ አያገኘውም። ታዛቢው ለህወሃት መኮንኖች 50% ኮሚሽን ይከፍላል። ታዛቢው ገና ካዲሳባ ሳይነቃነቅ ከህወሃት ወሮበሎች ጋር የኮሚሽን ስምምነት ይፈፅማል።

በአጠቃላይ ከሰላም አስከባሪ የሚገኘው ገቢ ወደ ገንዘብ ሚኒስቴር ወይም ወደ መከላከያ ካዝና የገባበትን ሰነድ ማቅረብ አይችሉም። በመጀመሪያዎቹ ዘመቻዎች ወቅት ጥቂት ገቢ የሆነ ገንዘብ ነበረ። ለሰራዊት መዝናኛ በሚል ርእስ ወጪ ሆኖ የደረሰበት ሳይታወቅ ቀርቶአል። "የወታደር እግር፣ ከቡና እግር ይልቃል!" የተባለው መፈክር መከላከያ የቡና እርሻውን ቁልቁል ለማየት ይችል ዘንድ አደፋፈረው። እና መለስ ዜናዊ በአደባባይ ቡና ላይ ለማላገጥ በቃ።

የቡና እግር! የወታደር እግር!

የሰላም አስከባሪ ሃይል ማሰማራት የቡና እርሻ ከማስፋፋት በላይ የመለስን ትኩረት ሊስብ በመቻሉ ሩዋንዳ፣ ብሩንዲ፣ ዳርፉር፣ ላይቤሪያ ሲተራመሱ 'ቡናው ጎመራ፣ ቡናው አፈራ' ብለው ጮቤ ይረግጣሉ። "የገቢ ምንጫችን - ውጊያ! ውጊያ!" የሚል ዘፈን ማለዳ ማለዳ ይደመጣል...

* * *





"ወያኔ ሃውዜንን ሆን ብሎ አስደብድቦአል" ብለው የሚያምኑና የሚከራከሩ ጥቂት አይደሉም። ሲያብራሩም የሃውዜንም ሆነ የደቡብ ትግራይ ህዝብ በወቅቱ የወያኔን ትግል የማይደግፍ፤ ባንፃሩ የደርግ ደጋፊ ነበር ብለው ይገልፃሉ። ስለዚህም የደቡብ ትግራይ ህዝብ ከደርግ ጋር እንዲቆራረጥና ሙሉ ድጋፉን ለህወሃት ይሰጥ ዘንድ የሃውዜን ድብደባ ተቀነባበረ ይላሉ። አስረጅ ብለው የሚያቀርቡት፤ ጄቶቹ ሲደበድቡ ቪዲዮ መቀረፁ አንዱ ነው። የህወሃት ሰራዊት ከዚህ ቀደም አድርጎት በማያውቀው መልኩ ሃውዜን በተደበደበችበት እለት በጠራራ ፀሃይ የሃውዜንን ገበያ አቋርጦ አልፎአል። ይሄ ለአይሮፕላን ጥቃት ሊያጋልጥ እንደሚችል እያወቁ እንዴት ፈፀሙት? ሲሉም ይሞግታሉ። ሃውዜን ከተደበደበ በሁዋላም በአንድ ቀን 13 000 ወጣቶች ከደቡብ ትግራይ ወደ ትግሉ መግባታቸውንም በመጥቀስ ጥርጣሬያቸውን ያሰፉታል።

አበበ በለው የተባለው ተቀማጭነቱን ዋሽንግተን ዲሲ ላይ ያደረገው የሬድዮ ጋዜጠኛ ስለዚሁ ጉዳይ በጠየቀኝ ጊዜ "ሊሆን አይችልም" ስል አስተባብዬአለሁ። በማስተባበሉ ጠንከሬ ልገፋበት ጉልበት የለኝም። የታሪክ ፀሃፊዎች ይመረምሩት ዘንድ በእንጥልጥል የሚተው አጀንዳ በመሆኑ በዚህ ትረካ በጨረፍታ ነክቼው ማለፉን መርጬያለሁ።

በደርግ ዘመን በአንድ ወቅት ሻእቢያ የአስመራን ኤርፖርት ለመምታት የተኮሰው መድፍ ገጀረት ላይ ወድቆ ሰዎችን ገድሎ ነበር። ይህ ሊሆን የቻለው መድፉ በእርጥበት ምክንያት የታለመለት ቦታ ላይ ሊደርስ ባለመቻሉ ነበር። ይህ ከተከሰተ በሁዋላ ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን የአስመራ ነዋሪ በሻእቢያ ላይ እንዲቆጣ ለማድረግ መደበር ላይ (አስመራ መሃል) መድፍ እንዲወድቅ አድርጎአል። ዊኒስተን ቸርቺል እንግሊዛውያን በናዚ ጀርመን ላይ በቁጣ እንዲነሳሱ የራሱን የጦር አይሮፕላኖችን የናዚ አርማ ቀብቶ የለንደንን ህዝብ እንዲደበድቡ ማድረጉንም አንብቤያለሁ። ወያኔዎች ይህን ታሪክ ለመድገም ሞክረው ይሆን?

በዚህ ጉዳይ ላይ ማናችንም ብንሆን በቂ ማስረጃ የለንም። ግምታዊ ትንታኔ ነው። ይህ በርግጥ ተፈፅሞ ከሆነ በወቅቱ የወያኔ ወታደራዊ ሃላፊ የነበረው ስዬ አብርሃ እንደመሆኑ መረጃው ያለው ስዬ እጅ ላይ ነው። ስዬ ይህን

መረጃ ይነግረናል ብዬ ግን አልጠብቅም። ፈፅሞት ከሆነ በ2700 ገበሬዎች ህይወት ተጠያቂ ይሆናልና ከቶውንም ይህን ሊያምንልን አይችልም። በኔ በኩል ማስተባበሉን ጠንከሬ ባልገፋበትም መረጃውን ለማመንና ለመቀበል ደግሞ ተጨማሪ ማስረጃ እፈልጋለሁ። በመሆኑም ጉዳዩን በእንጥልጥል መተውን እመርጣለሁ። ምናልባት ግን ስዬ አብርሃ ፅፌዋለሁ ባለው ያልታተመ መፅሃፉ ላይ ጉዛዜውን አስፍሮ ሊሆን ይችላል።

* * *

በርግጥ ሁልጊዜ አይደለም እንጂ አልፎ አልፎ የፖሊት ቢሮው ጥብቅ ሚስጥሮች ሾልከው መውጣታቸው አልቀረም። በተለይም አሁን አሁን የብአዴን አመራር አባላት ተስፋ የቆረጡበት ሁኔታ ላይ በመድረሳቸው በብስጭትም ሆነ በሞቅታ አንዳንድ ወሬዎችን ያሾልኩ ይዘዋል።

ግንቦት7 ሞክሮት ነበር ከሚባለው የመፈንቅለ መንግስቱ ሙከራ ጋር በተያያዘ የፖሊት ቢሮው ቆይታም የእንጦጦን ጋራ ዞሮ፣ በYahoo መሃረብ ተቋጥሮ እጄ ላይ ገብቶአል።

የብአዴን ሊቀመንበር አዲሱ ለገሰ ከምንጊዜውም በላይ አንደበቱን ከፍቶ ማማረር መጀመሩ ተሰምቶለታል። በመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ተጠርጥረው የተያዙት ከፍተኛና ጄኔራል መኮንኖች ወደ ከርቸሌ በተላኩ ማግስት መለስ ዜናዊ የፖሊት ቢሮ አባላቱን ለአስቸኳይ ስብሰባ ጠርቶ ነበር፣

አጀንዳቸውም አንድ ነበር።

መለስ ዜናዊ በግንቦት7 ስለ ተጠረጠሩት የመፈንቅለ መንግስቱ ሞካሪዎች ማብራሪያ ሰጣቸው...

የመጀመሪያው ፍንጭ መቼ እንደተገኘ፣ ከደህንነቱ መስሪያ ቤት አንድ የክትትል ቡድን ተቋቁሞ ሲያጠና እንደከረመ ገለፀ። "ጥናቱ በስሎአል" ብለው ባመኑበት ጊዜ ደግሞ እርምጃ መውሰዳቸውን በመግለፅ ማብራሪያውን አበቃ።

እናም አስተያየት ጠየቀ።

ከፖሊት ቢሮ አባላቱ አዲሱ ለገሰ፣

"ይህ ጉዳይ ብአዴንን ይመለከታል። በቀጥታ ደግሞ እኔን ይመለከተኛል። በተገለፀልን አድማ ውስጥ ተሳተፉ የተባሉት በሙሉ አማራና የብአዴን ታጋዮች ናቸው። ይህ መረጃ ሲገኝ እኔ ለምን ሳላውቅ ቀረሁ? ይህ ሁሉ ሲፈፀም





የብአዴን ትብብር ለምን ሳይጠየቅ ቀረ? እኔ ስለምመራው ድርጅት በዚህ ስብሰባ ላይ መስማት ይገባኝ ነበር ወይ?" ብሎ አለቃቀሰ።

መለስ ዜናዊ የክትትሉን ሚስጥራዊነት በመግለፅ አጭር ምላሽ ሰጠው። ከዚያ በሁዋላ ጥያቄ ያቀረበ አልነበረም። በረከትና ተፈራ ዋልዋ በስብሰባው ላይ የተካፈሉ ሲሆን፣ አስተያየት ሳይሰጡ ስብሰባው ተዘግቶአል።

ከኢህአዴግ የፖሊት ቢሮ ስብሰባ በሁዋላ የብአዴን የፖሊት ቢሮ ክፊል አባላት ጉዳዩን በተናጠል ሊያዩት መሞከራቸውንም ሰምቻለሁ። ተፈራ ዋልዋ አዲሱ ለገሰን በመቃወም እንዲህ ሲል ተናግሮአል፣

"ብአዴንን እጁን ጠምዝዘን ለህወሃት ያስረከብነው እኛው ራሳችን ነን። አንተም እኔም ይህን አድርገናል። ምን አዲስ ነገር ተፈጠረና ነው ተበሳጭተህ እንደዚያ የተናገርከው?"

በረከት ስምኦን በርግጥ ስለታሰሩት ነባር የብአዴን ወታደራዊ ታጋዮች ያውቅ ነበር ብለው ይጠረጥሩት ይሆናል። ይህ ጉዳይ ሚስጥር ሆኖ የቆየው ለቀሪዎቹ የብአዴን አመራር አባላት ብቻ እንደሚሆን ግልፅ ነው።

እርግጥ ነው፤ አዲሱና ዋልዋ ማምለጫ የላቸውም። እስከ ፍፃሜው በህወሃት መንጋጋ ስር ይቆያሉ። የስልጣን ፍቅር ጋማቸውን ይዞ ጎትቶ ካስገባቸው የጭቃ ኩሬ በቀላሉ መውጣት የዋዛ አይሆንም። ብዙ ገድለዋል። መግደል ቀላል አይደለም። ሟች ጉልበት አለው። የፈፀሙትና ያስፈፀሙት ጥብቅ የምስጢር ጎተራ ውስጥ ተቆልፎባቸዋል። ከፍፃሜው በፊት አንድ ርምጃ መውሰድ ይችሉ ይሆናል ብዬ ተስፋ አላደርግም። ፀፀታቸውን እያስታመሙ ይዘልቁት ይሆናል። አሟሟታቸውን የማሳመር እንጥፍጣፊ እድል ግን አያጡም። እንደ ታምራት ላይኔ ማልቀስ ሳይሆን መናዘዝ ይጠበቅባቸዋል! ያን ማድረግ ከቻሉ ቢያንስ በታሪክና በልጆቻቸው ፊት ሞገስና ምስጋና አያጡም።

ሌላማ ምን ቀሪ ነገር ሊኖር?

ቀሪው ግልፅ ነው።

እነርሱም እንደማንኛውም ሰው ማንኛውም አጥንት፣ ማንኛውም አስከሬን ይሆናሉ...

## - 10 -

# የቁልቢ ሌሊት ውስጥ

ልብን ጋን አድርጎ - ችግር ሲጠነሰስ፣
ጭንቀትና ጥበት - ብቅልና ጌሾው፣
ይገባሉ በፊት - ከሁሉ አስቀድመው፣
ከዚያ የሚቀጥለው፣
መተከዝ የሚሉት - የጠላ ቂጣ ነው፣
ከዚያም ይዘጋጃል - እንዲስማማ አብሮ፣
መባከን የሚሉት - የአሳብ እንኩሮ፣
ሁሉም ይገባና - ሲምታታ ሲፈላ፣
ያኔ ይጠመቃል - የመከራ ጠላ፣
ስካሩም እብደት ነው - የሚያናውጥ ናላ፣

(ግጥም - ፍቅረ ድንግል በየነ)

የኦርቶዶክስ ተዋህዶ አማኝ እንደመሆኔ ይኸው የቁልቢውን ገብርኤል ታቦት ለማንገስ ምስራቅ ኢትዮጵያ ተገኝቼያለሁ። በርግጥ ጉዞዬ ለስራ ጭምር ነበር። ለእፎይታ መፅሄት "የጉዞ ማስታወሻ" ለተባለው አምድ አንድ ቀልብ የሚስብ ትረካ ለማግኘት መባዘን የማይቀር ነው። ጊዜውም 1989 ታህሳስ ወር ነበር። በዚህ መልኩ የመፅሄቴን ጉሮሮ ለመሙላትና የመንፈስ ፀጋ ለመቋደስ ቁልቢ ስመጣ ይህ ሶስተኛዬ መሆኑ ነው…

* * *





ፀሃይቱ ቸኩላ ቀዝቅዛለች…

ከተከልኩት ድንኳን ደጃፍ ላይ የሸራ ወንበር ዘርግቼ ተቀምጫያለሁ። በደጀ ሰላሙ ዙሪያ ህዝበ ክርስትያኑ እንደ ጫካ ተጠቅጥቆአል። ምእመናኑ ለቁልቢው ገብርኤል የየስለቱን እያስገባ ነበር። አንዲት ሴት በጥርሷ የሞተ አይጥ አንጠልጥላ ቤተክርስትያኑን በእንብርክኳ በመዞር ላይ ነበረች። በቀኝና በግራ እጆቹ የሚንፈራገጡ እባቦችን የያዘ ሰው እንደ ሃውልት ቆሞ አንዳች ነገር ያነበንባል። ይህን መሰል እምነታዊ ትርኢት ለመጀመሪያ ጊዜ የሚመለከት፣ ወደ ሌላ የማያውቀው አለም የገባ ያህል ቀልቡ በተደበላለቀ ስሜት ሊሰረቅ ይችላል። ማለቂያ አልባ የስለት ቁሳቁስ ወደ ደጀ ሰላሙ ይጎርፋል። የሚዘረገፈው ገንዘብ ልክ የለውም። ጃንጥላው፣ ምንጣፉ፣ ሰንጋው፣ ሸህሩ፣ ጠቦቱ፣ ሽቶው፣ ሻማው፣ እየተጫነ ይዘረገፋል። ከድሬዳዋ እስከ ቁልቢ በእግራቸው ለመንዝ የተሳሉና ስለታቸውን የፈፀሙ ከቤተመቅደሱ ደጃፍ ላይ ተዝለፍልፈው ወድቀዋል። በቤተክርስትያኑ ዙሪያ ምግብና መጠጡ ይቸበቸባል።

ከኔ ድንኳን አጠገብ አንዲት ሴት ቤዥ የሸራ ድንኳን ተክላለች። የድንኳኗ ደጃፍ ላይ ወዲያ ወዲህ እየተንጎራደደች ይህንኑ ልብ የሚነካ እምነታዊ ትርኢት እየተመለከተች ነበር። ፍም የመሰለች ቀይ ስትሆን፣ እድሜዋ ከሰላሳ በላይ ሊገመት ይችላል። በጣም ቆንጆ ናት። እግር ግን ነፍጓአታል። እግሮቿ እንደ ወፍ እግር ቀጫጭኖች ሲሆኑ፣ ስትራመድ ተገልብጣ በእጇ የምትሄድ ነው የምትመስል።

ደጋግማ ተመለከተችኝ።

እንኳን ዘንቦልኝ፣ ቀድሞውንም የደብረዘይት ልጅ ነኝ። በቢሾፍቱ ልጆች ባህል ሴት ልጅ ከአንድ ጊዜ በላይ ካየችህ ፈልጋሃለች ማለት ነው። አንተ ባትፈልጋት እንኳ ልታነጋግራት ይገባል። ስለዚህ በባህላችን መሰረት ወግ ጀመርኳት፣

"ብቻሽን ነው እንዴ የመጣሽው?"

"አይደለም። ጓደኛዬ አብራኝ አለች"

"መተዋወቅ መልካም! ማን ልበል ስምሽን?"

"ሃረግ ተበጀ እባላለሁ። አንተስ?"

እኔም ስሜን ከነአባቴ ተናገርኩ።

በዚያው ቅፅበት እጄን ወደ ድንኳኔ በመስደድ አንድ ተጣጣፊ የሸራ ወንበር አወጣሁና እየዘረጋሁት እንዲህ አልኩ፣

"አረፍ በያ ታዲያ?"

"አመሰግናለሁ። እንዲሁ ይሻለኛል"

ከድንኳኑ ደጃፍ ላይ ወዲያ ወዲህ ማለቱን ቀጠለች። እግሮቿ ስትራመድባቸው የሚሰበሩ ስለሚመስሉ ያሳቅቃሉ። ለበረዶ አየር የተሰራ ነጭ ጃኬትና ጉልበቷ ላይ የሚደርስ ሰማያዊ ቱታ ለብሳለች። ቡኒ ላንድሮቨር ጫማ ተጫምታለች። የግራ እጇ ሶስቱ ጣቶች ላይ ቡጢ የሚመስሉ የወርቅ ቀለበቶች ሰክታለች። ሰላማዊና የተረጋጋ ፊት አላት። አይኑ ውሃዋ ደግነትን የተላበሰ ነበር። አንዲት ቃላት ከአንደበቷ ከመውጣቱ በፊት ፈገግታዋ ይቀድማል። ያቀረብኩላትን የወንበር ግብዣ ባለመቀበሏ ከኔ ጋር የማውጋት ፍላጎት አይኖራትም ይሆናል ብዬ ገምቼ ነበር። መሳሳቴን ግን ወዲያውኑ አረጋገጠችልኝ። መንጎራደዱን ትታ ያቀረብኩላት ወንበር ላይ አረፍ አለች።

"አንተስ ብቻህን ነው የመጣኸው?"

'ጓደኞቼ አሉ" አልኩ። አያያዝኩናም፣ "በየአመቱ ትመጫለሽ?" ስል ጠየቅሁ።

"በየአመቱስ አልመጣም። ስለት ላስገባ ነው የመጣሁት"

"ስለትሽ ደረሰልሽ?"

"ለቅዱስ ገብርኤል ምን ይሳነዋል? ስለቴን ሰምቶ ፈፅሞልኛል። አምና እዚህ መጥቼ መርፌ ወግቼ እያለቀስኩ ነበር የተሳልኩት። በአምስተኛው ወር ስለቴ ተፈፀመልኝ"

ይህን ስትገልፅልኝ ገፅታዋ በሃይልና በራስ መተማመን መንፈስ ተሞልቶ ነበር።

"መርፌ መውጋት" የሚለውን ቃል ቀደም ሲል ሰምቼዋለሁ። እምነትን የሚፈታተን እምነት ነበር። ይህን ቃል ከዚህች ደግ ገፅታ ካላት ቆንጆ ሴት መስማቴ ደግሞ ይበልጥ ትኩረቴን ሳበው። ከባድ በደል የደረሰባቸው ሰዎች መርፌ ወግተው ከተሳሉ ቅዱስ ገብርኤል በደላቸውን በትክክል እንደሚሰማ በወሬ ደረጃ ብቻ ነበር የማውቀው። መርፌ የመውጋቱ ሂደት በጣም ቀላል ቢሆንም የራሱ አደጋም ነበረው። ምእመናን የቤተመቅደሱ ግድግዳ ላይ መርፌ ይሰኩና እያለቀሱ በደላቸውን በመንገር በደል የፈፀመው ሰው ላይ ክስ ያቀርባሉ። መርፌ የተወጋበት ሰው በርግጥ በደሉን ፈፅሞት ከሆነ ህይወቱን ከማጣት በላይ ዘርማንዘሩ ጭምር እንደ ቅጠል ሊረግፍ እንደሚችል ሰምቻለሁ። መርፌ ወግቶ የተሳለ ሰው ግን





አጋጥሞኝ አያውቅም ነበር። እርግጥ ነው፣ ለሆነው ላልሆነው መርፌ መውጋት የራሱ አደጋም አለው። መርፌ እስከ መውጋት የሚደርስ ሰው በትክክልም በደል የደረሰበት ሊሆን ይገባል። ካልሆነ ተገልብጦ መርፌ ወጊው ለሃጢአትና ለአደጋ ሊጋለጥ ይችላል። ይህች ሴት "መርፌ ወግቼ ተሳልኩ" ስትለኝ ታዲያ ለወሬ አቆበቆብኩ። እናም እንዲህ ስል ጠየቅሁ፣

"እንዴት ያለ በደል ቢደርስብሽ ነው መርፌ እስከመውጋት የደረስሽው?"

"በጣም ከባድ ነበር" አለች ቅጭም ብላ።

ወሬውን መቀጠል ስላልፈለገች ነው መሰለኝ ርእሰ ወሬውን ወደኔ አዞረችው፣

"አንተስ ተስለህ ነበር?"

"ገና እያሰብኩ ነው። እስከሚቀጥለው አመት ልቤን የምትማርክ መልኳ ጨረቃ፣ ቅጥነቷ እንደ መቃ፣ ለባሿ ጠበቃ፣ ዘሯ መጢቃ፣ የሆነች ሚስት ካገኘሁ እዚህ መጥቼ አንድ ጣቃ ለመስጠት እያሰብኩበት ነው"

ሃረግ ሳቀች። ከት ብላ ሳቀች።

"ምን አሳቀሽ?"

"አነጋገርህ ያስቃል"

በመገረም ስታጤነኝ ቆየችናም፣

"ሚስት ለማግኘት ስለት እንኳ ልክ አይመስለኝም። ባይሆን ካገባህ በሁዋላ ልጅ ቢከለክልህ 'ልጅ ስጠኝ' ብለህ ልትሳል ትችላለህ። ለሴት ደግሞ ምን ስለት ያስፈልገዋል? ቆንጆዎች ሞልተው ተርፈዋል። ይልቁን ደህና ባል ነው የጠፋው።"

"በርግጥ እንዳልሽው ቆንጆ ሴት ሞልቶ መትረፉን አውቃለሁ። የእኔ መለኪያ ግን ቁንጅና ሳይሆን ብስለትና መግባባት ነው። በርግጥ ቁንጅናን ማጣጣሌ አይደለም። በቁንጅናዋ ብቻ ሴትን መምረጥ ግን አደጋው ይበዛል። ቁንጅና እንደ አበባ ረጋፊ ነው። ባህርይ ግን እንደ ከዋክብት ዘላለማዊ ነው። የአሁኖቹ ወጣት ሴቶች ደግሞ እንደምታውቂው ያለቀ ሳሙና ናቸው። እንደ በረሮ አይያዙም። ሰርጋቸው ላይ የባላቸውን ሚዜ ያበስሉታል..."

ከት ብላ ስቃ ስታበቃ እንዲህ አለች፣

"ወንዶች አይብሱም እንዴ? ሴቷን አንድ ጊዜ

እስኪያገኟት የቃል ኪዳናቸው ብዛቱ? እንክብካቤያቸው ተአምር! በነጋታው ጠባያቸው ቅይርይር! ትናንት የተናገሩትን ሁሉ ይረሱታል። ሴት ምናላት ብለህ ነው? የዋህ ናት። እስክትወልድ ብቻ ነው። አንድ ከወለደች በሁዋላ ልቧ ወደ ልጇና ወደ ባሏ ነው። ገንዘቧን ለትዳሯ ነው። ወንዱ ግን በነጋታው ሌላ ማየት ይጀምራል። ያለቀ ሳሙናስ ወንዱ ነው..."

ይህን ስትናገር ድምፅዋ ወደ ማምረር አዘነበለ። ከወንዶች ጋር ያላት ልምድ በጎ አለመሆኑን ማስተዋል ይቻል ነበር። እጇ ላይ ጠባሳ እንዳለባት ያስተዋልኩት በዚህ ጊዜ ነበር። ጠጉሯን ወደ ሁዋላ ለማሰር እጇን ብድግ ስታደርገው ግራ እጇ ላይ በእሳት የተለበለበ አይነት ቆዳዋ መጨማደዱን አስተዋልኩ።

ከሃረግ ተበጀ ጋር እንዲህ የተጀመረው ትውውቅ እየሞቀ ሄደ። ወደ ድንኳኔ ገብተን ወይን እንጠጣ ዘንድ ያቀረብኩትን ግብዣ ተቀበለችና ወደ ውስጥ ገባን። በብርጭቆ የቀዳነውን ወይን እያጣጣምን ሳለ ለኑሮ ምን እንደምትሰራ ጠየቅሁዋት። አንድ የግል ኮንስትራክሽን ድርጅት ውስጥ የንብረት ክፍል ሃላፊ ሆና እንደምትሰራ፤ ከንግድ ስራ ኮሌጅም በዲፕሎማ መመረቋን አጫወተችኝ። የኔን ስራ ስትጠይቀኝ ግን እውነቱን አልነገርኳትም። ጋዜጠኛ መሆኔን መናገር አስፈላጊ አልነበረም። ብዙውን ጊዜ "የመንግስት ሰራተኛ ነኝ" በማለት በጥቅሉ ማለፉን እመርጥ ነበር።

"ሚስት ለማግኘት የምር ልትሳል ነው?"

"ስቀልድ ነው" አልኩ።

"ሚስት መፈለጉንም እየቀለድክ ነዋ!"

"እሱ እውነቴን ነው። ሚስት ከመፈለግ የቦዘንኩበት አንድም ቀን የለም። እስካሁን ግን አልተሳካልኝም"

"ወረተኛ መሆን አለብህ"

"እንዴት?"

"ከአንድ ሴት መቆየት ከማይችሉት አንዱ እንዳትሆን?"

"አይመስለኝም" ካልኩ በሁዋላ "ለምን አትሞክሪኝም?" አልኳት በቁም ነገር ፍጥጥ ብዬ።

ሳቀች። በመገረምም እንዲህ አለችኝ፣

"ለጋብቻ እንዲህ ነው የምትጠይቀው?"

"ማመልከቻ መፃፍ አለብኝ እንዴ?"

"ማለቴ አነጋገርህ ቀልድ ነው የሚመስለው።"





"የምሬን ነው" አልኳት። በርግጥም የምሬን ነበር።

ሶስተኛውን የወይን ብርጭቆ እንደተያያዝነው፣ 'እኔ ደግሞ ራት ልጋብዝህ' አለችና ወደ ድንኳና ሄደች። በሁለት ሳህን የዶሮ ፍርፍር ይዛ ተመለሰች።

በጣም የሚጥም ነበር።

ራት እየተመገብን ስናወጋ ሳለ ታዲያ፣

"ምን ገጥሞሽ ነው መርፌ ወግተሽ የተሳልሽው?" ስል መልሼ ጠየቅሁዋት። ለማወቅ ጉጉት አድሮብኝ ነበር።

"ስለት ይነገራል እንዴ?" አለች እየሳቀች።

"ለሚቀርቡት ሰው ይነገራል" አልኩ።

"አንተን ታዲያ የት አውቅሃለሁ?"

"ከዚህ በላይ ምን መተዋወቅ አለ? አብረን በላን፤ አበብረን ጠጣን፤ አልቋጨነውም እንጂ ስለ ጋብቻም እያሰብንበት ነው። እንደማየው ደግሞ በጣም ተግባብተናል። የተዋደድንም ነው የሚመስለው..."

"ፈጣጣ!" አለችኝና ምግቧ ላይ አቀረቀረች።

"ንገሪኝ ስለትሽን?"

"አልነግርህም። ምን ያደርግልሃል?"

"ምንም አያደርግልኝም። ለጨዋታ ያህል ነው። እስካሁን ለሌላ ሰው አልነገርሽም?"

"ለምቀርባት ጓደኛዬ ነግሬያታለሁ"

"ስለዚህ ህጉ ፈርሶአል ማለት ነው።"

"አንተን ግን አላውቅህም። ዛሬ አውቄህ እንዴት ዛሬውኑ ሚስጥሬን እነግርሃለሁ?"

"ሰውን የት አውቀዋለሁ አይባልም። በአንድ ቀን ትውውቅ ስንት ቁምነገር ይሰራል? ከቀረብሽኝ በግማሽ ልብ አትቅረቢኝ። ሁሉን ነገርሽን እንድትሰጭኝ እፈልጋለሁ። ካልፈለግሽ ግን አልጫንሽም..."

እንደገና ሳቀች፣

"ቸኮልክ እኮ ታዲያ? ከተዋወቅን ገና ሁለት ሰአት እንኳ መች ሞላ? ሁሉም ነገር ላይ እንደዚህ ችኩል ነህ እንዴ?"

"የቸኮልኩ መስሎ ከተሰማሽ ይቅርታ። ደስ ስላልሺኝ ነው እንጂ ካገኘሁዋት ሴት ጋር ሁሉ እንደዚህ የምሆን ይመስልሻል? ችኩልም አይደለሁም። በግልባጩ ፈዛዛ ነኝ።"

"እንጃ! አስፈራኸኝ። ቶሎ የምትቀርብ፤ ቶሎ ደግሞ

የምትርቅ ትመስላለህ። እኔ እንደሱ አልወድም። ቶሎ አልቀርብም። የቀረብኩትን ሰው መራቅ ደግሞ ያስፈራኛል።"

"አንድ ጥያቄ ልጠይቅሽ? እውነቱን ትነግሪኛለሽ?"

"እነግርሃለሁ፤ ጠይቀኝ?"

"ደስ ብዬሻለሁ?"

"ወይ መከራ?" አለችና ሳቀች።

"ምን መከራ አለው? መልሺልኝ?"

እያቅማማች መለሰች፣

"ገና አሁን አይደል እንዴ የተዋወቅነው? ለነገሩ ያው ደስ ባትለኝ ዝም ብዬ ድንኳንህ ውስጥ አልገባም ነበር። ግን አላውቅህም። አታውቀኝም። መተዋወቅ ጥሩ ነው። ወደፊት የሚሆነውን ደግሞ ማን ያውቃል? ያንተ ችኮላ ግን..."

ለጥቂት ሰከንዶች በዝምታ ቆየን፣

"ቅር አለህ እንዴ?" አለች አይን አይኔን እያየች።

"ለምኑ?"

"የተሳልኩትን ስላልነገርኩህ?"

"ቅር አይለኝም። ወደፊት ትነግሪኛለሽ። አሪፍ አይቸኩልም" ካልኩ በሁዋላ ተገለበጥኩና መቸኮል እንደማይገባ ልመክራት ጀመርኩ፣

"ምን መሰለሽ ሃረግ? መቸኮል አይገባም። ለሁሉም ጊዜ አለው። ቴጃሮች እንደሚሉት፣ 'የነቶሎቶሎ ቤት - ግድግዳው ቡለኬት' እንዳይሆን ረጋ ማለት ጠቃሚ ነው..."

እየሳቀች አቋረጠችኝ፣

"ራስህ ነህ ችኩል። ራስህን ምከር"

ወይን በድጋሚ ቀዳሁላትና ጋቢውን እንደ ትራስ አመቻችቼ ጋደም እንድትል አደረግሁዋት። በርግጥም ተመቻት። የመዝናናት ሁኔታም ታየባት፣

"እንክብካቤዬ እንዴት ነው?" ስል ጠየቅሁዋት።

"እርግብ ነገር ነህ" ብላ በረጅሙ ሳቀች።

"አዲሳባ የት ሰፈር ነሽ?"

"አፍንጮ በር"

"የቀለጠው መንደር?"

"አንተስ?" አለች።

"የረርና ከረዩ"

ወደ ተውነው ርእሰ ጉዳይ ራሷ ተመልሳ ገባች፣





"ከፈለግህ ልነግርህ እችላለሁ"

"ምኑን?"

"የተሳልኩትን"

"አትንገሪኝ። ለጨዋታ ብዬ እንጂ ምን ያደርግልኛል ብለሽ ነው?"

"ልነግርህ ፈልጌያለሁ"

"ቅድም ስለምንሽ ለምን እንቢ አለሽ?"

"አሁን ልነግርህ ፈለግሁ፤ አትድረቅ"

"በይ ንገሪኝ?"

አጫወተችኝ።

ከሁለት አመታት በፊት ከምትሰራበት ከሜክሲኮ አካባቢ ወጥታ ታክሲ እየጠበቀች ነበር። ነሃሴ ነበር። ካፊያ ቢጤ ያካፋል። አንድ ሰው መኪና አቆመላትና 'ልሸኝሽ' ይላታል። ፈቃደኛ ሆና ተሳፈረች። እያወሩ እስከ ቤቷ ሸኛት። አስመጪና ላኪ ነጋዴ መሆኑንም ነገራት። ቤቷ ካደረሳት በሁዋላ ስልኳን ተቀብሏት እንደሚደውልላት ገልያላት ተሰነባበቱ። በነጋታው ቃሉን ጠብቆ ወደ ቢሮዋ ደውሎ ፈቃዷ ከሆነ ራት ሊጋብዛት እንደሚፈልግ ይጠይቃታል። 'ጨዋ ሰው ነው' ብላ ስላመነች የራት ግብዣውን ተቀበለች። ግዮን ሆቴል ባህላዊው አዳራሽ ወስዶ ጥሩ ራት ጋበዛት። በነጋታው እለቱ አርብ ስለ ነበር ወደ ምሽት ክለብ ይሄዱ ዘንድ ይጠይቃታል። ተስማማች። ሲጨፍሩ አመሹና አብረው አደሩ። ከዚያ በሁዋላ በፍቅር ከነፉ። በወሩ ሊያገባት እንደሚፈልግ ነገራት። በጣም ተደስታ ሙሉ ልቧን ሰጠችው። ቤተሰቧን ወስዳ አስተዋወቀችው። በጣም ተዋደው ነበር። እሷ በተለይ ከነፈችለት። የምትፈልገውን ሁሉ ያደርግላት ነበር። ከዚያም አልፎ የልቧን ሁሉ ስለሚረዳላት 'ያለሱ ወንድ የለም' ብላ ደመደመች። ማከዳ የምትባል ጓደኛ ነበረቻት። ከእሷም ጋር አስተዋውቃው ነበር። ወደ ምሽት ክበብ ሲወጡም ብዙውን ጊዜ ከነጓደኛዋ ይዟት ይወጣል። እና ሁሉም ነገር ጥሩ ነበር...

"በመጨረሻ የሆነውን ልንገርህ" አለች ሃረግ መጢቃ የመሰለ ፊቷ ይበልጥ እየፋመ። እና ቀጠለች፣

"አንድ የዘመዴ ሰርግ ላይ እሳት ላይ ከተጣደ ቡፌ ምግብ ስናነሳ የለበስኩት ከጥጥ የተሰራ እጅጌ እሳቱን ይስብና ግራ እጄን ተቃጠልኩ። በዚያም ያለፈልኝ እድለኛ ሆኜ ነው።

በኔ መቃጠል ምክንያት ግብዣው ተተራምሶ ወደ ሆስፒታል ተወሰድኩ። ጓደኛዬ ሆስፒታል ከገባሁ ጀምሮ አንድ ቀን ሳይለየኝ፣ አጠገቤ ቁጭ ብሎ አስታመመኝ። እና ድኜ ወጣሁ…"

የጃኬቷን እጅጌ ሰብስባ አሳየችኝ።

ጠባሳው እስከ ክንዷ የዘለቀ ነበር። ሙሉው ሲታይ ይሰቀጥጣል። እንደ ትኩስ ቁስል አይን የሚወጋ ነበር። ቋዳዋን ከማበላሸት አልፎ ግን ወደ አጥንቶቿ ያለፈ አልነበረም። ጃኬቷን መልሳ ጠባሳውን ከሸፈነችው በሁዋላ ትረካዋን ቀጠለች፣

"አላረዝምብህም። ባጭሩ ልንገርህ። ድኜ ከወጣሁ በሁዋላ ጓደኛዬ ይርቀኝ ጀመር። ፀባዬ ተቀየረ። የጋብቻውን ጉዳይ ሳነሳለትም ወሬውን በዚህም በዚያም ብሎ ይዘጋዋል። እኔ ጅል አይደለሁም። ገባኝ። ከኔ ጋር መቀጠል አይፈልግም። ላስገድደው አልችልም። ካልፈለገ መብቱ ነው። ግን በግልፅ መነጋገር ስለነበረብን ደወልኩና ቀጠርኩት። አልዋሸኝም። እውነቱን ነገረኝ፣

'ብንጋባ ትዳራችን ጥሩ አይሆንም።' አለ።

'ለምን?'

'በመካከሉ አንድ ነገር ቢፈጠር፣ እጄ እንዲህ ስለሆነ ነው እያልሽ ሁሉን ከዚያ ጋር ልታያይዢው ስለምትችይ፣ እኔም እየተሳቀቅሁ እንዳይሰማት እያልኩ አርተፊሻል የሆነ ፀባይ ከማሳይሽ ቢቀርብን ይሻላል። እንደዚህ በማሰቤ ይቅርታ። ልዋሽሽ አልፈልግም' አለኝ።

ወስኖ ስለነገረኝ ልከራከረው አልችልም።

በዚያው ተሰነባበትን።

ሁለት ወር ካለፈ በሁዋላ ይመስለኛል ከጓደኛዬ ከማክዳ ጋር ወደ ክለብ እንደሚወጡ ወሬ ሰማሁ። ማክዳን ስጠይቃት፣

'በአጋጣሚ ተገናኝተን ነው አብረን ያመሸነው' አለች።

አምኜ ተቀብያት ነበር። ሆኖም ከእኔም እየራቀች ሄደች። ከዚያ መከታተልና ማጠያየቅ ስጀምር በአንድ ሳምንት ውስጥ ሁለት ጊዜ እንደገና ክለብ ውስጥ መታየታቸውን ሰማሁና እንደገና ደወልኩላት፣

'አጋጣሚ ነው ብለሺኝ ነበር። በተደጋጋሚ እንደምትገናኙ ነው የሚሰማው። ምንድነው ጉዳዩ? በግልፅ ንገሪኝ' አልኳት። እሷም፣

'ካንቺ ጋር ተለያይታችሁዋል። ባገኘውስ ባንቺ ላይ ምን





ለውጥ ያመጣል?' ብላ ጠየቀችኝ።

'ጓደኝነታችንስ? ሞራሌስ?' ብዬ ስላት፣

'ደስ ካላለሽ እንዳይደውልልኝ እነግረዋለሁ' አለች።

አላደረገችውም።

መከታተሌን ስቀጥል ይበልጥ እንደሚገናኙ፣ ላንጋኖ ጭምር እንደሄዱ ሰማሁ።

ማክዳ የልጅነት ጓደኛዬ ናት። ተለያይተን አናውቅም። አብረን ነው ያደግነው። በርግጥ በጣም ቆንጆ ናት። ወንዶችን የማፍዘዝ ሃይል እንዳላት አውቃለሁ። እሷ ፊት ካልሰጠችው ግን እሱ ሊደፍር አይችልም ነበር። በጣም ስለበሸቅሁ ይህን ለማጣራት ወደ እሱ ደወልኩ፣

'ከማክዳ ጋር ምን እያካሄዳችሁ ነው?' ብዬ ስጠይቀው፣

'የምትናገሪውን አስበሽ ተናገሪ' አለና ስልኩን ዘጋብኝ።

ከዚህ በሁዋላ 'እንደፈለጋቸው ይሁኑ' ብዬ ልረሳቸው ሞክሬ ነበር።

በመካከሉ ግን ከራሱ ከጓደኛው አንድ ምስጢር ሰማሁ። ጓደኛዬ እኔን ለምን እንደተወኝ እውነተኛውን ምክንያት አወቅሁ። ለካስ ከማክዳ ጋር በፍቅር ማበድ የጀመሩት ከአደጋው በፊት ጀምሮ ነበር። እኔ እንዳላውቅ እየተጠነቀቁ ሲወጡ ቆይተዋል። ልክ አደጋው ሲከሰት ሰበብ አገኙ። የሰጠኝን ተልካሻ ምክንያት አቅርቦ ከማክዳ ጋር ቀጠለ።

ይህን ሳወቅ አበድኩ።

እንቅልፍ መተኛት አቃተኝ። ሁለቱም ባለጌዎችና ከሃዲዎች ነበሩ። ስለዚህ ፍርዱን ቅዱስ ገብርኤል እንዲሰጠኝ ወሰንኩ። እናቴም አባቴም አያቶቼም ቅዱስ ገብርኤልን እየተሳለሙ ያደጉ ናቸው። የቁልቢው ቅዱስ ገብርኤል በደሌን እንደሚሰማኝ ደግሞ ርግጠኛ ነበርኩ…"

በርበሬ መስሎ የተለበለበ ፊቷን ሞዠቀችና ቀጠለች፣

"…አምና ቁልቢ መጣሁና ተሳልኩ። መርፌ ወግቼ እያለቀስኩ ሁሉንም ለቅዱስ ገብርኤል ተናገርኩ። በኔ ላይ ያን በማድረጋቸው ፍርዱን እንዲሰጠኝ እያለቀስኩ…ሶስት መርፌ ወግቼ ለመንኩት…"

ፊቷን ሞዠቀችው።

ከወይኑ ቀመስ አደረገችለትናም እንዲህ አለች፣

"የቁልቢው ቅዱስ ገብርኤል እንባዬንና ልመናዬን

እንደሚሰማ እርግጠኛ ነበርኩ። መርፌ ወግቼ በተሳልኩ በአምስተኛው ወር ሞተ!"

ደንግጬ አባባሏን ደገምኩት፣

"ሞተ!?"

"አዎን ሞተ! ዝርዝሩን አላውቅም። ሎምብሬሌ የሚባል የምሽት ክለብ ደጃፍ ላይ በጩቤ ተወግቶ ወድቆ ተገኘ። የወጉት ሰዎችም አልተያዙም። አራት ቀናት ሆስፒታል ቆይቶ ሞተ።" አያይዛ እንዲህ አለች፣ "...የቅዱስ ገብርኤል ጦር ሲወጋ እንጂ ሲወረወር አይታይም!"

ይህን ብላ ቅጭም አለች።

በኔ በኩል አንዲት ቃል እንኳ መተንፈስ አልቻልኩም። በዝምታ አይን አይኗን እመለከታት ጀመር። የታመቀ አየር ከሳንባዋ ካስወጣች በሁዋላም እንዲህ ስትል አከለችበት፣

"በመሞቱ ደስ አላለኝም። መርፌ ባልወጋበት አይሞትም ነበር። በወቅቱ ግን ተጎድቼና ተናድጄ ስለነበር ያንን አድርጌአለሁ። እኔ ሳልሆን ስራው ነው የገደለው።"

ከዚያ በሁዋላም ሌላ ርእስ ጉዳይ ልንነጋገር አልቻልንም። ወደ ደጅ እንድንወጣ አሳብ አቀረብኩና ወጣን።

ለአይን ያዝ አድርጎአል።

እዚያው ደጃፉ ላይ ከታጣፊ የሸራ ወንበሮች ላይ ቁጭ አልን። ቅዳሴው ከፍ ብሎ እየተሰማ ነበር። ምእመናን ነጫጭ ለብሰው ቤተመቅደሱን ከበውታል። በፀጥታ አካባቢውን እያስተዋልነው ቆየን።

ብዙም ሳንቆይ አንዲት ጋቢ የተከናነበች ሴት መጥታ ተቀላቀለችን። የሃረግ ጓደኛ መሆኗ ነው። በጋቢዋ መሃል ልቅም ያለ ቁንጅናዋ ፉዋ! ብሎ ወጥቶአል። ማርያም ከሰማይ የወረደች ያህል ውብ ነበረች።

"ተዋወቂው" አለቻት።

"ማክዳ" አለች።

ከመደንገጤ ብዛት ስሜን መናገር አልቻልኩም። ደረቅ ፈገግታ ብቻ አሳየሁዋት። ማክዳ ወደ ድንኳኑ እንደገባች የፈጠጡ አይኖቼን ወደ ሃረግ መለስኩ። ለምን አይኖቼ እንደፈጠጡ ተረድቷት እንዲህ ስትል ተነፈሰች፣

"እሷም እንድትጎዳ አልፈልግም። ቅዱስ ገብርኤል ይቅር እንዲላት እየለመንን ነው"





ይህን ብላኝ ማክዳን ተከትላ ወደ ድንኳኑ ገባች።

ለረጅም ጊዜ እዚያው ጨለማው ውስጥ ቁጭ ብዬ እንደነበር ትዝ ይለኛል። የመርፌውን ታሪክ ደግሜ ደጋግሜ እያውጠነጠንኩት ነበር። ሃረግ እኔም ላይ መርፌ እንዳትወጋ የሰጋሁ ያህል ሰውነቴ ደጋግሞ ተሸማቀቀ። በእርግጥ ከዚያ ባሻገር የማልፈልገው ሌላ አዲስ አደጋ በውስጤ እየተላወሰ ነበር። ገፍቶ መጣብኝ። ተከላከልኩት። ተፈታተነኝ። በዚያን ሌሊት በህልሜም በውኔም ውስጤ የቀረችውን ጭላንጭል እምነት ከሞት ለማትረፍ ስታገል አደርኩ...

- 11 -

# አግአዚና ምርጫ 97

ስለመራራው ኑሮአችን፣
ለተሰፋ ቢሱ ህይወታችን፣
ምስጋና ይግባው ለፓርቲያችን፣
ለቀረናው ዝምታችን፣
ምስጋና ለፓርቲያችን፣
ለታወቀው ፅሞናችን፣
ምስጋና ለፓርቲያችን፣
ለከባዱ መከራና ስቃያችን፣
ምስጋና ለፓርቲያችን፣
እውነትን አምቆ ለያዘብን፣
ከባዱንም ቀንበር ለጣለብን፣
ምስጋና ለፓርቲያችን፣
ለሚደርስብን የተኩስ እሩምታ፣
ለሚከተለውም የጦርነት ጋጋታ፣
ለፓርቲያችን ምስጋናና ሰላምታ፣

(ግጥም - አንዲት ሩስያዊት ገጣሚ)
- ማሞ ውድነህ እንደተረጎመው -

ከአእምሮ የሚጠፋ አልነበረም...

ወጣቷ የአዲሳባ ልጅ ሺብሬ ደለለኝ ጡቷ ላይ በጥይት ተመታ ስትገደል እኔ ፕሪቶሪያ ነበርኩ። ግንቦት 29 ቀን፣ 1997 ነበር እለቱ። የመጀመሪያዋ የወያኔ ጥይት የሺብሬን ህይወት እንደቀጠፈ ድረገፆች እየተቀባበሉ የሚፅፉትን ሳነብ አደርኩ።





እዚያው ወንበሬ ላይ ተቀምጬ ሂደቱን ስከታተልና ከጓደኞቼ ጋር መስመር ላይ ሆኜ ሳወጋ ሌቱ ወገግ አለ። ያስጨነቀኝ ጉዳይ "ቀጥሎ ምን ሊፈፀም ይችላል?" የሚለው ነበር።

የቀድሞ አለቆቼ ወደ ግድያው ጨዋታ ሰተት ብለው መግባታቸውን ተረድቼ ነበር። ጠባያቸውን አውቀዋለሁ። መለስና ስብሃት አሰርቱ ቃላትን ያውቋቸዋል። ከዘጠኙ መስኮቶች አንደኛው ክፍት ከሆነ ዋጋ የለውም። ሌባው ስርቆት ለመፈፀም አንድ መስኮት ብቻ ይበቃዋል። ስለ ወንጀልና ቅጣት ካሰብን አንድ ሰው መግደልና መቶ ሰው መግደል ልዩነት የለውም። ስለዚህ የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም እንዲሉ ግድያው ሊቀጥል እንደሚችል ርግጠኛ ሆኜ ነበር።

የሺብሬ አሟሟት አቅጣጫ ጠቋሚ ነበር...

የአዲሳባ ፖሊስ የዩኒቬርሲቲ ተማሪዎችን አስሮ ሊገርፋቸው ወደ ሰንዳፋ እየተጓዘ ሳለ ኰተቤ ላይ ህዝቡ ከየቤቱ ግልብጥ ብሎ በመውጣት መንገዱን ዘጋና፣

"ልጆቻችንን ወዴት ነው የምትወስዱት?" ሲል ጠየቀ።

ህዝቡና ፖሊስ ተፋጠጠ...

ታጣቂዎቹ በታዘዙት መሰረት የእሩምታ ተኩስ ከፈቱ። ሺብሬ ጉሮሮዋ ላይና የግራ ጡቷ ላይ ተመትታ ወደቀች። ሺብሬ ከተቃውሞ ሰልፈኞቹ አንዷ አልነበረችም። ጓደኛዋን ለመሸኘት ነበር ከቤት የወጣችው። እንደወጣች በሁለት ጥይት ተመትታ ወደቀች። ፖሊስ የሺብሬን ሬሳ ወስዶ አሰረው። ወላጆች ሬሳ ሲጠይቁም የሬሳ መልቀቂያ መቶ ብር እንዲከፍሉ ተነገራቸው። ክፍያውን ፈፅመው የሺብሬን ሬሳ ወሰዱ። ከዚህ በሁዋላ የወያኔ ማጅራት መቺነትም በሰፊው ቀጠለ...

ሰኔ 1 ቀን፣ 1997 42 ሰዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ተገደሉ። በዚያም አላበቃ። በጐጃም በረንዳ፣ በመሳለሚያ፣ በአብነት፣ በአዲስ ከተማና በመርካቶ ግድያው በሰፊው ቀጠለ። የወጣቶችና የህፃናት ሬሳም በየጐዳናው ተሰጣ። የአዲሳባ እናቶችም እንዲህ ሲሉ ጠየቁ፣

"ዴሞክራሲ ነውና የፈለጋችሁትን ምረጡ አላችሁን። እኛም የፈለግነውን መረጥን። ግድያው ታዲያ ለምን መጣ?"

ለዚህ ጥያቄ ወያኔ ምላሽ አልሰጠም። ጥያቄውን ላለመመለስ ሲል በተከታታይ በርካታ ወንጀሎች ፈፅሞአል። ይህን እየፃፍኩ ሳለም ጥያቄው የቀጠለ ሲሆን፣ የብርቱካን

ሚደቅሳ ዳግም እስርም ጥያቄውን አፍኖ ሊያስቀረው አልቻለም። እርግጥ ነው የወያኔ መሪዎች ከዚህ ጥያቄ ለማምለጥ ማንኛውንም አይነት አፈና ይፈፅማሉ። ለጊዜው ጥያቄውን በማፈን አጀንዳውን ሊያቀዘቅዙት ይችሉ ይሆናል። ወደፊት ወንበሩ ሲከዳቸው ደግሞ ከሃገር በመኮብለል ማምለጥ ይችሉ ይሆናል። ከማይቀረው የታሪክ ተጠያቂነትና ከህሊና ወንጀለኛነት ማምለጥ ግን ከቶውንም የሚቻል አይሆንም። ይህ ትረካም ለመጪው ትውልድ የሚቀይ ሰነድ ነው...

* * *

እነሆ! ከአንድ የቀድሞ የወያኔ ኮሎኔል ጋር ተቀምጫለሁ። እኔ ስለዚሁ ኮሎኔል ቀደም ስል የማውቀው ከጥቂት በላይ ነበር። እሱ ግን ስለኔ ብዙ እውቀት አልነበረውም። ምናልባት ከኔ ጋር ተገናኝቶ ቆይታ ለማድረግ ፈቃደኛነት ያሳየው፣ "የጋዜጠኛው ማስታወሻ"ን ስላነበበ ሊሆን ይችላል።

አለበል አማረ የተባለው ይህ ኮሎኔል፣ "ትግሬን በድፍኑ ይጠላል" ተብሎ ይታማ ነበር። እንደተወራበት ግን አልነበረም። ሶስት ቀናት ሙሉ አብረን በወዳጅነት ሰነበትን። እሱም በሙሉ ፈቃደኛነት ለጠየቅሁት ሁሉ ምላሽ ሰጠ። በቅድሚያ ግን፣

"ለመሆኑ ስለኔ ምን ታውቃለህ?" ሲል ጠይቆኝ ነበር።

በአጭሩ እንዲህ አልኩት፣

"ከመነሻው የነፍሰ ገዳዩ የአግአዚ ኮማንዶ ክፍለ ጦር አመራር አባል እንደነበርክ የማያውቅ የለም። በምርጫ 97 የአግአዚ ሰራዊት ንፁሃን ዜጎችን በሳንጃ እያረደ፣ በአረር ሲያነድ አንተ ስልጣን ላይ ነበርክ። 'ትግሬን ትጠላለህ' ተብሎ ደግሞ ይነገርልሃል። ትግሬን የሚጠላ ሰው እንዴት የአግአዚ ሰራዊት መሪ ሊሆን እንደሚችል ግን ሳጥናኤል ብቻ ነው የሚያውቀው። ከምርጫ 97 በሁዋላ ደግሞ ታስረህ እንደነበር ድረገፆች ላይ ተፅፎ አንብቤ፣ ጉዳዩ ሲከነክነኝ ቆይቶአል። ሁዋላ ግን መፈታትህ ተሰማ። በመቀጠል ደግሞ ከነ ጄኔራል አሳምነው ፅጌ እና ጄኔራል ተፈራ ማሞ ጋር የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ለማድረግ ስታስቡ እንደተደረሰባችሁ በወያኔ ሚዲያ ሰማን። ወያኔ 'በተገኘበት ይገደል!' የሚል መመሪያ አንተ ላይ





ማስተላለፉን ከቀድሞ ጓደኞቹ ሰምቼም ነበር። ርግጥ ነው፣ ብዙ በእእምሮዬ ውስጥ የሚጉላሉ ጥያቄዎች አሉ። ኩዴታው እንዴትና ለምን ከሸፈ? እነ መለስ እነ ተወልደ በተከፋፈሉበት ዘመንም አንተ ቤተመንግስት ነበርክ። መቸም ብዙ የምታውቀው ይኖር ይሆናል። በኢትዮ - ኤርትራ ጦርነትም ተካፍለሃል። በኔ በኩል ስላንተ የማውቀው ይህን ነው። በርግጥ ከምር ድንጋይ ተወልደህ ያደግህ የበጌምድር አማራ መሆንህን፣ ከ1982 የደብረታቦር ውጊያ በፊት ኢህዴንን መቀላቀልህንም አውቃለሁ።" አልኩት።

"ስለኔ ብዙ እንደምታውቅ ተረድቼያለሁ። በመከላከያ ቆይታዬ በ23ኛ እና በ24ና ክፍለ ጦሮች በአመራር ደረጃ የተወሰነ ጊዜ ከመስራቴ በቀር ሙሉ ታሪኬ ከአግአዚ ክፍለ ጦር ጋር የተያያዘ ነበር። ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ከጭራቅ ጋር የሚያመሳስሉት የማፍያ ቡድን ከኔ የህይወት ታሪክ ጋር የተቆራኘ ታሪክ ስላለው ከልብ አዝናለሁ...የሆነው ሆኖ አንተ የማታውቀው እኔ የማውቀው ምን ሊኖር ይችላል?" አለ በጥርጣሬ።

"በምርጫ 97 እኔ ሃገር ውስጥ አልነበርኩም። አንተ ግን በወቅቱ የአግአዚ አመራር አባል ነበርክ። በወቅቱ ምን እንደተካሄደ ልትነግረኝ ትችላለህ" አልኩ።

በዚሁ ተስማምተን ይነግረኝ ጀመር...

* * *

ኮሎኔሉ እንዳጫወተኝ...

ኢህአዴግ አዲስአበባን ከተቆጣጠረ በሁዋላ ቤተመንግስቱን እንዲጠብቅ የተመረጠውና ተጨማሪ ስልጠና የተሰጠው አግአዚ ክፍለ ጦር ነበር። ከአግአዚ ሌላ አንዷት 'የእጀባ ሻለቃ' የምትባል 180 የሰው ሃይል ያላት የጥበቃ ቡድን ነበረች። ይህች ሻለቃ በአብዛኛው የባለስልጣናትን የእጀባ ስራ የምታከናውን ናት። አብዛኞቹ የአድዋ ተወላጅ ወታደሮች ነበሩ። ሻለቃዋ በሶስት ጋንታ ትከፈላለች። 'አንደኛ ጋንታ' የምትባለው 30 ወታደሮችን ያቀፈች ናት። እነዚህ ሁሉም የአድዋ ተወላጆች ነበሩ። ቅልቅል የለባቸውም። መቶ አለቃ ሙከራ የተባለ ሰው ይመራታል። ቀጥተኛ ስራቸው የመለስን

መኖሪያ ቤትና ቢሮውን መጠበቅ ብቻ ነው። መለስ ወደ ውጭ ሃገር ሲጓዝም እየተቀያየሩ ያጅቡታል። 2ኛ እና 3ኛ ጋንታ የተባሉት ደግሞ የቤተመንግስቱን ዙሪያና ከመለስ ቢሮ ወደ ቤቱ የሚወስደውን መንገድ ጭምር ይጠብቃሉ። በእነዚህ መካከል አልፎ አልፎ የሽሬና የአክሱም ተወላጆች ከመቀላቀላቸው በቀር በሙሉ የአድዋ ሰዎች ብቻ ነበሩ። አማራ ወይም ኦሮሞ እዚያ ውስጥ ማግኘት ግን ፈፅሞ አይታሰብም። የአግአዚ አዛዥ ሆነው ሁለቱም በተከታታይ የተሾሙት የአድዋ ተወላጆች ናቸው። ጄኔራል ፍሰሃ ኪዳኑ፣ ሁዋላም ጄኔራል ሙሉጌታ በርሄ አግአዚን መርተውታል። ከነዚህ በመቀጠል ኮሎኔል አለበል አማረ በአመራር ደረጃ ተቀምጦአል።

በአግአዚ ክፍለ ጦር ስር ያሉት ሁለት ኰማንዶ ሻለቃዎች (ጉና እና ወጋገን) እስከ 1986 ድረስ እየተቀያየሩ የቤተ መንግስቱን ዙሪያ ሲጠብቁ ቆይተዋል። በ1986 ማብቂያ ግድም አግአዚ ተጨማሪ ሃይል ገባለት። ከተለያዩ የሰራዊት ክፍሎች ብቁ ወታደሮች እየተመለመሉ ወደ አግአዚ እንዲገቡ ተደረገ። የክፍለጦሩ የሰው ሃይልም ወደ አራት ሻለቃ ወይም ወደ 2000 የሰው ሃይል ከፍ አለ። ይህም አንድ የኰማንዶ ብርጌድ ሆነ ማለት ነው። የብርጌዱ ማዘዣ ጣቢያም ከአጤ ሚኒልክ ቤተመንግስት ውስጥ ነበር። በ1990 ብርጌዱ እንደገና ወደ 6 ሻለቆች አደገ። የኢትዮ-ኤርትራ የድንበር ግጭት ሲከሰትም አግአዚ ወደ ክፍለጦር ደረጃ እንዲያድግ ተደረገ። በ9 ሻለቃና በ3 ብርጌዶች ተዋቅሮ 'አግአዚ ኰማንዶ ክፍለጦር' የሚል ስያሜ አገኘ። "አግአዚ" የሚል ስያሜ ያገኘው በህወሃት ትግል መጀመሪያ ወቅት በጦርነት ህይወቱ ያለፈች፣ "አግአዚ" የተባለ ጓደኛቸውን ለማስታወስ ነበር። አግአዚ ክፍለጦር በዚህ ሁኔታ ተወልዶ አደገ። ይህ በእንዲህ እንዳለ ምርጫ 97 ጊዜውን ጠብቆ መጣ። ምርጫ 97 እና አግአዚም እንደ አጥፊና ጠፊ ስማቸው ለዘልአለሙ ለመቆራኘት በቃ።

ኮሎኔሉ እንዲህ አለኝ፣

"...የአግአዚ ኮማንዶ ክፍለጦር አዛዥ የነበርነው ሁሉ በመጪው ትውልድ ዘንድ ስማችን በክፉ መነሳቱ አይቀርም። ምንም ይሁን ምን ግን የተፈፀመውን እውነት ሁሉ መግለፅና የህሊና እረፍት ማግኘት እንደሚገባ አምናለሁ..."

አያይዞ እንዲህ ሲል አወጋኝ፣





"...ምርጫ 97 ከመቃረቡ በፊት ከአንዳንድ የኢህአዴግ የማእከላዊ ኰሚቴ አባላት ጋር ስለምርጫው እያነሳን እንጨዋወት ነበር። ያው መቼም አማራ እንደመሆኔ፣ ወደ ሰራዊቱ ከመግባቴ በፊት በአማራው ክልል አካባቢ በካድሬና በህዝብ አስተዳደር ስራ እሰራ ስለነበር ከሁሉም ካድሬዎች ጋር እንተዋወቃለን። ከስራ ሰአት ውጪም እንገናኛለን! በመተማመንና በግልፅነት፣ በወዳጅነት መንፈስም እንጨዋወት ነበር። ሁሉም የሚነግሩኝ አንድ ግልፅ ነገር ነበር፣

'የዘንድሮው ምርጫ ፍፁም ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን ተወስኖአል። የምርጫውን ዴሞክራሲያዊነት የሚያደናቅፍ የኢህአዴግ አባል ያለ ምህረት እንዲቀጣ የላይኛው አመራር ትእዛዝ ልኳል። ተቃዋሚዎች ነፃ ሆነው በነፃነት መንቀሳቀስ እንዲችሉ መመሪያ ወርዷል። ይህ መመሪያም እስከታችኛው የቀበሌ መዋቅር ድረስ መስመሩን ተከትሎ ወርዶአል' እያሉ አጫውተውኛል።

በእውነቱ ይህ ከተለያዩ አቅጣጫዎች፣ ከአመራሩም ከካድሬዎቹም የሚደመጥ ስለነበር በጣም ደስተኛ ሆንኩኝ። ኢህአዴግ ይህን መሰል ውሳኔ መወሰኑ፣ ውሳኔውንም ተግባራዊ ለማድረግ መትጋቱ በእጅጉ አኩርቶኝ ነበር። የኢህአዴግ አባል በመሆኔ ኩራት የተሰማኝ ጊዜ ነበር።

እነ ተወልደና ስዬ ከመጀመሪያውም እብሪተኛና ዘረኞች እንደሆኑ ማንኛውም አማርኛ ተናጋሪ ታጋይ ያውቅ ነበር። በአንፃሩ ይህ የነፃ ምርጫ አዋጅ ከታወጀ በሁዋላ ለመለስ ዜናዊ የነበረን አድናቆት በእጥፍ አደገ። ኢትዮጵያ ከአምባገነንነት አመራር የምትላቀቅበት ዘመን ላይ መገኘቴ ልዩ ኩራት አሳድሮብኝ ነበር። እኔ አባል የሆንኩበት ፓርቲ ይህን ፀጋ ለማምጣት መዘጋጀቱ የህሊና ርካታ አሳድሮብኝ ነበር። እንዲህ ነበር በወቅቱ የተሰማኝ..."

ከጥቂት ዝምታ በሁዋላ ኰሎኔሉ ትረካውን ቀጠለ፣

"...ምርጫው ሳምንታት ሲቀሩት የወያኔ ከፍተኛ አመራር አባላት መንፈስ ሁሉ በድንገት ተለወጠ። በአንድ ጉዳይ ላይ መግባባት የጀመሩ ይመስለኛል። ምክንያቱም የዴሞክራሲያዊ ምርጫ ሰበካቸውን በመተው የጦር ሃይሉን ማዘጋጀት ላይ ትኩረት ሰጡ። 'የምርጫ ኰማንድ ፖስት' የሚል ግራ የሚያጋባ የወታደራዊ ጊዜያዊ ማዘዣ ጣቢያ አዲሳባ ላይ

ማቋቋም እንደሚያስፈልግ የሚገልፅ እቅድ አዘጋጁ።

ጄኔራል ሳሞራ የኑስ የሚመለከተንን ስድስት መኰንኖች ሰብስቦ ገለፃ አደረገልን። ከስድስታችን አምስቱ የህወሃት መኮንኖች ነበሩ። እነርሱም ገዛኢ. አበራ፣ ዮሃንስ ገብረመስቀል፣ ገብረእግዚአብሄር መብራህቱ፣ ሙሉጌታ በርሄ፣ ገብረመድህን ፈቃዱ ሲሆኑ፣ ስድስተኛው እኔ ነበርኩ። እንደ ማጣፈጫ የተጨመርኩ አማራ ኰሎኔል። እነ ሳሞራ ስለኔ ምን እንደሚያስቡ በእውነቱ አላውቅም። ምናልባት 'አይደፍረንም' ብለው ገምተው ሊሆን ይችላል። እብሪትና ንቀታቸው ያው የታወቀ ነው። እኔን መሃላቸው ቁጭ ያደረጉኝ አንድ አማራ ጣልቃ በማስገባት ከሃሜት ለመዳን ሊሆን ይችላል። የሆነው ሆኖ ሳሞራ ሰበሰበንና፣

'ምርጫው ችግር ቢገጥመው እኛ መዘጋጀት አለብን። በተለይም የአግአዚ ክፍለጦር ይህ ግዳጅ ተሰጥታችሁዋል። ከፌደራል ፖሊስ ጋር የጋራ እቅድ አውጥተናል። እናንተም ከእነሱ ጋር በመሆን የጋራ ኰሚቴና ኰማንድ ፖስት (ማዘዢያ ጣቢያ) መስርቱ' አለን።

እንደገለፅኩልህ በዚህ ወቅት እኔ በታማኝነት ለኢ.ህአዴግ ህልውና እየሰራሁ ነበር። 'ኢ.ህአዴግ ለሃገራችን ብልፅግና ሊያመጣ ይችላል' ብዬ አምኜ ነበር የምሰራው። ሳሞራ የኑስ ከምርጫው ጋር አያይዞ አዲሳባ ላይ የወታደራዊ ማዘዣ ጣቢያ ስለማቋቋም ያነሳው ጉዳይ ግን ግራ ስላጋባኝ እንደዋዛ አንድ ቀላል ጥያቄ አነሳሁ፣

'ኢ.ህአዴግ ምርጫው ሰላማዊ በሆነ ሁኔታ በድል እንደሚጠናቀቅ እየገለፀ ነው። ለአባላቱ ሁሉ የስነ ምግባር መመሪያ በጥብቅ ሰጥቷል። የእኛ ዝግጅት ከዚህ ጋር አይቃረንም ወይ? ላልታጠቀ ህዝብስ ምን ኰማንድ ፖስት ያስፈልጋል?' ስል ጠየቅሁ...

ሳሞራ እንደ ማፌዝ ባለ ድምፅ፣

'ምን ይታወቃል? ነፍጠኛው ጦር ቢመዝብንስ? መቼም ወደ ጫካ ተመልሰን እንገባለን እንጂ ዳግም በትምክህተኛው አንገዛም! ደግሞስ ወታደር መሆንህን ረሳኸው እንዴ? ወታደር እንደ ወታደር ማሰብ አለበት...'

እኔ መቼም ከላይ ያለውን ጥያቄ ያቀረብኩት በቅንነት ነበር። ጥያቄው የተቃውሞ አላማ አልነበረውም። 'ነፃ ምርጫ





ይኖራል ተባለ። ምርጫው ነፃ ከሆነ ምን የጦር ሰራዊት ጋጋታ ያስፈልጋል?' ብዬ ጠየቅሁ።

በዚህ ጥያቄዬ ግን በሳሞራ የኑስ የብረት ጥርሶች ተነከስኩ። እኔ ወያኔ ነበርኩ። የወያኔ የጦር መሪ ነበርኩ። ለኢ.ህአዴግ ህልውና ላቤንም ደሜንም ያፈሰስኩ ሰው ነኝ። ኢ.ህአዴግን የሚነካብኝንም በፍፁም አልወድም ነበር። ሳሞራ ሲሰበስበን ግን ያቺን ተናገርኩ። ያቺ እንደተቃውሞ ተቆጠረች። ምርጫው ዴሞክራሲያዊ ምርጫ እንዲሆን ኢ.ህአዴግ ወሰነ ተባለ። 'ታዲያ ጦር ሰራዊት ለምን አስፈለገን?' ብዬ ነው የጠየቅሁ። ይሄ ሳሞራን በጣም አናደደው። 'ነፍጠኛው ቢዘምትብንስ?' ብሎ ከብሽቀት ፈገግታ ጋር መልሶ ጠየቀኝ።

ነፍጠኛው ማነው? የታለ? ነፍጠኛ የሚባል አለ እንዴ? ወይስ አማራ ሁሉ ነፍጠኛ ነው? ሊገባኝ አልቻለም። እኔ አማራ ነኝ። ዘርና ጐሳ ሳልለይ በኢ.ትዮጵያዊነት ስሜት ለሃገሬ እየሰራሁ አይደል እንዴ? ሳሞራ ምንድነው የሚናገረኝ? መለስና ሳሞራ እንዲመሩኝ ተቀብያለሁ። ትግሬ ስለሆኑ ለምን ትግሬ ሆናችሁ አላልኩም። ኢ.ትዮጵያዊ መሆናቸው ብቻ ለኔ በቂ ነበር። መለስ በምርጫ ከተሸነፈ ደግሞ ብርሃኑ ነጋ ወይም መረራ ጉዲና ሊመሩ ይችላሉ። የተመረጠው ፓርቲ ሊመራ ይችላል። ነፃ ምርጫ ከተባለ በሁዋላ 'ጫካ መግባት' የሚለውን ምን አመጣው?

የሆነው ሆኖ በዚያው ሰሞን ወደ ተግባር ተገባና የአዲሳባ ወታደራዊ ማዘዢያ ጣቢያ ተቋቋመ። የኰማንድ ፖስቱ አመራር አባላት፣ መለስ ዜናዊ፣ በረከት ስምኦን፣ አባዱላ ገመዳ፣ ሙሉጌታ አለምሰገድ መሆናቸው ተነገረን። ኦፕሬሽናል አመራር ደግሞ፥ ጌታቸው አሰፋ (ክንፈን የተካው የደህንነት ሹም)፣ ሳሞራ የኑስ፣ ኢ.ሳይያስ ወልደጊዮርጊስ (ደህንነት)፣ ግርማይ ማንጁስ (ፖሊስ)፣ ተስፋዬ መረሳ (ፖሊስ)፣ ታደሰ መሰረት (ፖሊስ)፣ ታደሰ ወረደ (የመከላከያ ጄኔራል)፣ ዮሃንስ ገብረመስቀል (መከላከያ መረጃ)፣ ገብረእግዚአብሄር መብራህቱ (መከላከያ ዘመቻ)፣ ሙሉጌታ በርሄ (የአግአዚ ክፍለጦር አዛዥ) መሆናቸው ተገለፀልን።

የአመራሩ ዋና ማዘዣ ጣቢያ የምድር ጦር ግቢ ከቀድሞው አውሮፕላን ማረፊያ አቬሽን ህንፃ፣ የአሁኑ የመከላከያ የመገናኛ መምሪያ ላይ ሆነ። በየክልሉ፣ በየከተሞችና

ቀበሌዎችም ንኡሳን ማዘጋርያ ጣቢያዎች ተቋቋሙ።

አደረጃጀቱ እንግዲህ ከላይ ያለውን ይመስል ነበር። የአግአዚ ክፍለጦር ግማሽ ሃይል ታዲያ አዋሳ ነበር። የአግአዚ አመራር አባላት ሁሉ አዲሳባ ሲመደቡ እኔ ወደ አዋሳ እንድሄድ ተደረገ። ወደ አዋሳ የተላከሁት ምናልባት በስብሰባው ወቅት ለሳሞራ ባነሳሁት ጥያቄ ሊሆን ይችላል። የሆነው ሆኖ ትእዛዙን ተቀብዬ አዋሳ ሆኜ ሂደቱን መከታተል ቀጠልኩ። ገብረዴላ የተባለ የ44ኛ ክፍለጦር አዛዥ መምሪያውን ሻሸመኔ ላይ አድርጐ የአዋሳና የአርባምንጭን የምርጫ ሂደት ይከታተል ነበርና ከእሱ ጋር ሆኜ እንድሰራ ተነገረኝ። የአዲሳባውን ዘመቻ የኔ የበላይ የነበረው ሙሉጌታ በርሄ የተባለ ጄኔራልና ገብረመድህን የተባለ ኰሎኔል እንዲመሩት ሳሞራ አዘዘ። የፌደራል ፖሊስም ከእነዚህ ከፍተኛ መኰንኖች ጋር በጋራ መስራቱን ቀጥሎ ነበር።

በዚሁ መሰረት ወደ ስራ ገባን!

ያው ሁሉም እንደሚያውቀው ምርጫው ግንቦት 7 ቀን ተካሄደ። ውጤቱም ወያኔዎች ያልጠበቁት ሳይሆን፣ ያልፈለጉት ሆነ። በዚያው በምርጫው እለት ምሽት የተዘጋጀው የጦር ሰራዊት ሃይል ወደ አዲስ አበባ መግባት ጀመረ። የአግአዚ ክፍለጦር ሶስት ሻለቆች ሌሊቱን ከአዋሳ ተጉዘው አዲሳባ ገብተው አደሩ። ደብረ ዘይት አየር ሃይል ግቢ ውስጥ የነበሩ 23 ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች ሌሊቱን ተጉዘው አዲስ አበባ ምድርጦር ግቢ ገብተው አደሩ። ከየእዙ የተውጣጡ 30 ያህል ዙ23 ከባድ መሳሪያዎች ወደ አዲስ አበባ ገቡ። ከ60 በላይ ዶሽቃ የጫኑ ፒክአፕ መኪኖች በፓትሮል መልክ ሊነጋጋ ሲል አዲሳባ ገቡ። የዚያን እለት ሌሊቱ ዘመቻ ሲታሰብ፣ ይህ ሁሉ የጦር መሳሪያ ጋጋታ ድምፁን በነፃ ፍላጐቱ የሰጠውን የአዲስ አበባ ህዝብ ለማፈን ነው ተብሎ እንዴት ሊታሰብ ይችላል?

ይህ እንግዲህ የመከላከያ ሃይል ዝግጅት ብቻ ነበር። የፌደራል ፖሊስ በበኩሉ ከፍ ያለ ዝግጅት ማድረግ ችሎ ነበር። በየክልሉ ዋና ዋና ከተሞች በተለይም በአማራና በኦሮሚያ ከተሞች በተመሳሳይ በፖሊስና በመከላከያ የተጠናከረ አፋኝ ቡድን ከተሞቹን እያጥለቀለቀ ነበር።

ምርጫው በተካሄደ በ2ኛው ቀን፣ ማለትም ግንቦት 9፣ 1997 ለመረጃ ልውውጥ ወደ አዲሳባ መጥቼ ነበር። አዲሳባ





እንደደረስኩ በቀጥታ ወደ ምድር ጦር ግቢ ነበር ያመራሁት። በግቢው ከፍተኛ ትርምስ ጠበቀኝ። የጦር አዛዦች ላንድክሩዘሮች ግቢውን ወረውታል። የሲቪል ባለስልጣናት ከነጠባቂዎቻቸው ይተራመሳሉ። የመገናኛ ሬድዮዎች ስራ ብዙ ሆነዋል። አንዳንድ ጄኔራሎች ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች ላይ ተኰፍሰው ወዲያ ወዲህ ይላሉ። የመገናኛ ሬድዮዎች ጫጫታ የምድርጦር ግቢን ቀውጢ አድርጐታል። አንዲት ሃያል ሃገር ኢትዮጵያን የወረረች ይመስላል እንጂ ህዝቡ የድምፅ ምርጫ ካርዱን ተጠቅሞ ፍላጐቱን ስለገለፀ የተከሰተ ግርግር ነው ብሎ ማሰብ ከቶ እንዴት ይቻላል?

እኔ ወደዚያ ግቢ የመጣሁት የአግአዚ ክፍለ ጦር አዛዥ የሆነውን ጄኔራል ሙሉጌታ በርሄን ለማግኘት ነበር። እዚያ ግቢ ውስጥ የተሟላ ጊዜያዊ ወታደራዊ ቢሮ ተሰጥቶታል። ስደውልለት ቢሮው የሚገኝበትን ቦታ ጠቆመኝና ወደዚያው ሄድኩ። በሞቀ ሁኔታ ሰላምታ ከተለዋወጥን በሁዋላ መረጃዬን እሰጠው ጀመር። እሱም ወቅታዊና ተጨባጭ ሁኔታውን ያብራራልኝ ያዘ።

ከጄኔራል ሙሉጌታ ጋር በግል እንግባባ ነበር። በርግጥ ጥሩ ጠባይ የለውም። ነጭናጫ ነው። የወያኔ ባለስልጣናትን የማንቋሸሽና የማጥላላት ቋሚ ጠባይ አለው። ሃሜተኛ ነው። ፈገግ ካልክለት ግድቡን እንደሰበረ ወንዝ በልቡ ያለውን ሁሉ የመዘርገፍ ጠባይ አለው። እናም ይህን ስለማውቅ ቆሰቆስኩት፣

'ሙሌ! እንዴት ነው ሁኔታው? የባድመን ጦርነት እዚህ አመጣችሁት እንዴ? ዝግጅቱ እኮ ጠላት የወረረን ይመስላል' አልኩት።

ጄኔራል ሙሉጌታ የብሽቀት ሳቅ ሳቀ፣

'እውነቱን ልንገርህ?' አለ አገጩን ከጠረጴዛው ጋር አሳስሞ፣ '...አመራሩ ስለሚያዘን ጉዳይ በቂ መረጃ የለውም። ህዝቡ ኢህአዴግን ጠልቶታል! ይህ እውነት ነው! በቃ! ስልጣን ላይ ያሉት ደግሞ...በፍርሃት ተንቀጥቅጠዋል። ስልጣን እንደማይለቁ ካወቁ ነፃ ምርጫ ለምን ፈቀዱ? በፊት እንዳደረግነው አያደርጉም? ተመልከት ላልታጠቀ ሰራዊት ይህ ሁሉ መሳሪያና ዘመቻ! ምን ሊባል ይችላል? እግዚአብሄር ብቻ ይርዳን! ህዝቡን ፈርተውታል! አድርጉ ያሉንን ደግሞ እኛ እናደርጋለን። ወታደሮች ነን!'

ይህን እየተጨዋወትን ሳለ ኰሎኔል ስብሃት ድንገት ገባ። የመከላከያ ሚኒስቴር የመገናኛ ሬድዮ ግንኙነት ሃላፊ ነበር። እንተዋወቃለን። ከመተዋወቅም በላይ ደህና እንግባባ ነበር። በሞቀ ሁኔታ ሰላምታ ከተለዋወጥን በሁዋላ፣

'አዋሳ ለመሆኑ እንዴት ነው?' ሲል ጠየቀኝ።

'ያው ነው። አመፅ አለ። እንደ ሁሉም ቦታ' ብዬ ሳበቃ፣ 'በእናንተስ በኩል አጠቃላይ ሁኔታው ምን ይመስላል?' ስል ጥያቄዬን አስከተልኩ።

'ምን ዋጋ አለው ብለህ ነው?' ሲል እጁን አወናጨፈ፣ 'አማራና ኦሮሞ ኢ.ህአዴግን ከድቶታል!' አለኝ።

አባባሉ ደስ አላለኝም፣

በርግጥ ኰሎኔል ስብሃት የሳሞራ ጆሮ ጠቢ ስለመሆኑ ሲወራ ቀደም ብዬ ሰምቼ ነበር። እንዲህ ያለ ወሬ ግን በብዛት ስላለ ያን ያህል ትኩረት የሚስብ አይደለም። ስብሃት ከጆሮ ጠቢነት ይልቅ ልክስክስ ጠባዩ ይበልጥ ያናድደኝ ነበር። ወሬኛ ቢጤ ነው። 'ከኔ በላይ ለኢ.ህአዴግ ታማኝ የለም' እያለ በባዶ ሜዳ ይመፃደቃል። ፊቱም ጠባዩም ጠፍጣፋ ጣውላ ነገር ነው። እናም ባልተገራ አንደበቱ መሃይምነቱን ይተረትረው ቀጠለ። እኔ አማራ መሆኔን እያወቀ ቃል በቃል እንዲህ አለኝ፣

'አማሮችና ኦሮሞዎች ኢ.ህአዴግን ከዱት! ትግራይ ብቻ ነው በዚህ ጊዜ አስተማማኝ። ሌላውን ተወው! ህዝቡስ ግዴለም ይክዳን፣ ደህና! የብአዴንና የኦህዴድ አባላትም ነውኮ የከዱን'

በዚህም አላበቃ። ኢያያዘና ቀጠለ፣

'ነፍጠኛ ከተመረጠ እኛ እንደለመድነው ጫካ እንገባለን። አማራ ዳግም ይመራ ዘንድማ አንፈቅድለትም። በማን ደም ማን ሊነግስ? ነፍጠኛ እንደ እባብ አፈር ልሶ ከመቃብሩ ወጥቶ ወደ ስልጣን ሊመጣ? አፄ ዮሃንስ ስልጣኑን ለነፍጠኛ አስረከበ። ያ ስህተት አይደገምም...'

ብዙ ብዙ ዘበዘበ።

በተለይም የአማራን ህዝብ ወንጀልና ሃጢአት እያነሳ በጣም ደጋገመብኝ። ኰሎኔል ስብሃት ይህን ሁሉ አስፀያፊ ንግግር ሲዘረግፈው ጄኔራል ሙሉጌታ አንገቱን አቀርቅሮ በፀጥታ ሲያዳምጥ አስተውዬዋለሁ። ሁለቱም የትግራይ ሰዎች ናቸው። ጄኔራል ሙሉጌታ ግን በስብሃት ንግግር ሃፍረት ተሰምቶት ሲሸማቀቅ እያስተዋልኩት ነበር። አንዳችም ቃል





ሊተነፍስ ግን አልቻለም። አቀርቅሮ ዝምታውን ገፋበት።

በመጨረሻ ግን መሸከም አቃተኝ።

ኮሎኔል ስብሃት የሚያዘንብብኝን አማራን የሚያጥላላ ጭቃ በጫንቃዬ መሸከም ከቶውንም ሳልችል ቀረሁ። ስሜታዊ ሆኜም እንዲህ አልኩት፣

'ስማ ስብሃት! አንተ ስለ አማራ ህዝብ ክህደት፣ ስለ ኦሮሞ ህዝብ ክህደት ምን ታውቃለህ? ምንስ አገባህ? አንተ ወታደር ነህ። ወታደር ፖለቲካ ውስጥ መግባት እንደሌለበት ህገ-መግስቱ ያዛል! ታዲያ አንተ ይህን ሁሉ የምትጮኸው በምን መነሻ ነው? በተለይም ስለ ህዝብ ክህደት የምትናገረው የማታውቀውን ነው። ህዝብ ከሃዲ ሆኖ አያውቅም። ህዝብ ማንን ነው የሚከደው? ግለሰብ ህዝብን ሊክድ ይችላል። ህዝብ ግን ክህደት ፈፀመ ሊባል አይችልም። ይህ አለማወቅህን ያሳያል። አቅምህን ያስገምትሃል!' ብዬ በከፍተኛ ብስጭት ተናገርኩት።

ኮሎኔል ስብሃት የኔን መራራ ንግግር ካዳመጠ በሁዋላ ጥርሱን አገጠጠብኝ። እናም እንዲህ አለ፣

'አሃ! አንተም ከነፍጠኞቹ አንዱ ሳትሆን አትቀርም! ምን ሩቅ አስኬደን ታዲያ!? ዋናው ነፍጠኛ፣ ዋናው ቅንጅት! ዋናው ጠላታችን እዚሁ ጉያችን ውስጥ እያለህ...'

እንዲህ እያለ ባለጌ አፉን ከፈተው።

እኔም ባሰብኝና ከፍተኛ ጭቅጭቅ ተፈጠረ።

በዚህ ጊዜ ጄኔራል ሙሉጌታ እኔን በመደገፍ ጣልቃ ገባ። ሊገላግለንም ሞከረ። ኰሎኔል ስብሃትም ተመናጭቆ ወጥቶ ሄደ። ከሙሉጌታ ጋር ብቻችንን እንደቀረን ሙሉጌታ እንዲህ ሲል ሊገስፀኝ ሞከረ፣

'ስብሃት የሳሞራ ጆሮ ጠቢ መሆኑን እያወቅህ እንዴት እንዲያ ትናገራለህ? ስብሃት በየቢሮው እየዞረ እንዲህ እያናገረ፣ ወሬ እየለቀመ ለሳሞራ ሲያደርስ ነው የሚውለው። ሌላ ስራ የለውም። ይህን የማያውቅ የለም። አንተም ታውቃለህ! እያወቅህ ደግሞ ይህን መናገርህ ልክ አይደለም...'

ሙሉጌታ የሚናገረኝን መቀበል ቀርቶ መስማት እንኳ አልቻልኩም። በመሰረቱ የተፈጥሮ ባህርዬ ይህን የመሰሉ ልክስክስ ጠባዮችን የሚያስተናግድ አልነበረም።

እኔ አማራ ነኝ!

አማራ ሲሰደብ አጐንብሼ መስማት አለብኝ? እንዴት

ሊሆን ይችላል? ይህን መሰል ባህርይ እኔን ለማለማመድ ከቶ እንዴት ደፈሩ? ይህ ፈፅሞ ሊገባኝ ያልቻለ ሁኔታ ነበር። አሁንም ሳስበው ሁኔታውን ልገነዘበው እቸገራለሁ። የሆነው ሆኖ ከሙሉጌታ ጋር ወደ ዋናው ጉዳያችን ገብተን የመረጃ ልውውጥ አካሄድን። በዚያን ቀን የተናገርኩትን ኰሎኔል ስብሃት ለሳሞራ እንዳቀበለው ግልፅ ነበር። ያ ግን ለኔ በወቅቱ አሳሳቢ አልነበረም። ከዚያ በላይ የስብሃት ንግግር የልብ ቁስል ሆኖ እያደማኝ ነበር።

ከዚያ ዝግጅት በሁዋላ የአዲስ አበባ ኦፕሬሽን ጀመረ። በኦፕሬሽን ዝግጅቱ ላይ መመሪያ በሚሰጥበት ጊዜ በስብሰባው እኔ አልተሳተፍኩም። ጄኔራል ሙሉጌታ ግን አጫውቶኛል።

'አመፅ ከተነሳ፣ የአመፅ ግንባር ቀደም ግለሰቦችን ለይቶ መምታት!' የሚል ቁርጥ ውሳኔ ተላልፎ ነበር።

የአመፅ መሪዎች ከተመቱ ተከታዩ ህዝብ ከተመቱት ተምሮ፣ አደብ ገዝቶ እንደሚቀመጥ ትንታኔ ተሰጥቶበታል። ይህን መመሪያ ያስተላለፈው በመለስ የሚመራው ኰሚቴ ሲሆን፣ መመሪያውም እስከታችኛው መዋቅር ድረስ ወርዶ ነበር።

ሙሉጌታ መመሪያውን ለኔም አብራራልኝ።

እኔ በተመደብኩበት በአዋሳ፣ በሻሸመኔና በአርባምንጭ አካባቢዎች አመፅ የሚነሳ ከሆነ በመመሪያው መሰረት ተግባራዊ እንዳደርግ፣ በዚያ ሂደት በሚሞቱ ሰዎች ተጠያቂነት እንደማይኖር ቃል በቃል ነገረኝ።

ጄኔራል ሙሉጌታ፣

'ሰው መግደል ይቻላል' የሚለውን መመሪያ ሲገልፅልኝ ለውሳኔው ንቀት ያለው መሆኑን ከአነጋገሩ ተረድቼያለሁ።

'ውሳኔው ትክክል አይደለም። ሆኖም እኛ ወታደሮች ስለሆንን የመንግስትን ውሳኔ ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ አለብን' አይነት ነበር አነጋገሩ።

ሆኖም በርግጥ ሙሉጌታ ለውሳኔው ንቀት ነበረው ብዬ ልሟገትለት አልችልም። 'እያስመሰለ ሊሆን ይችላል' የሚል የራሴ ጥርጣሬ ነበረኝ። ምክንያቱም ግንባር ቀደም አመፀኞችን ለመቀጣጫ የመግደሉን መመሪያ ልንተገብረው እንደሚገባ ደጋግሞ ነግሮኛል። 'ተጠያቂነት አይኖርም' የሚለውን ቃልም ከሶስት ጊዜ በላይ አፅንኦት ሰጥቶ ደግሞታል።





ከጄኔራል ሙሉጌታ ጋር ቆይታዬ ካበቃ በሁዋላ አማራ የሆኑ የአግአዚ ክፍለጦር የሻለቃና የሻምበል አመራሮችን በስልክ አግኝቼያቸው ነበር። ሁሉም የጠየቁኝ፣

'የአመፅ መሪዎችን ግደሉ! ተጠያቂነት አይኖርም!' ስለሚለው መመሪያ ነበር። የታዘዙትን ሁሉ አጫወቱኝ።

'እንዲህ ተባልን፣ እንዴት ነው? አንተ መመሪያውን ሰምተሃል ወይ? ምን ማድረግ አለብን? አንተስ ይህን መመሪያ እንዴት ነው የምታየው?' ሲሉ በጭንቀት ጠየቁኝ።

እነዚህ ከበታቼ የሚገኙ አማራ መኰንኖች ላቀረቡልኝ ጥያቄ በግልፅ ምላሽ ሰጥቼያቸዋለሁ።

'ውሳኔው ትክክል አይደለም። በውሳኔው መሰረት የታዘዛችሁትን ከፈፀማችሁ፣ የገዛ ወገናችሁን ነው የምትጨርሱት። በተቻለ መጠን ሰዎች ሳይሞቱ አመፆችን ለማስቆም ሞክሩ። ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ ግርግሮችን ለማብረድ መሞከር ይገባል' ስል ገለፅኩላቸው።

ይህንንም ለሚያምኗቸው ወታደሮች ሁሉ እንዲነግሩ ተነጋግረናል። በዚህ መንገድ ተግባባን።

ሁሉም እንደሚያውቀውና እንደተጠበቀው በአዲሳባም ሆነ በመላ ሃገሪቱ ከግንቦት 97 እስከ መጪው 1998 አጋማሽ ድረስ አመፁ ቀጠለ። የበርካታ ንፁሃን ዜጎች ህይወትም ጠፋ። በዚህ ጊዜ ውስጥ በአዲስ አበባ ብቻ 30 ሻለቃዎች ተሳታፊ ሆነዋል። አንድ ሻለቃ ጦር እስከ 600 የሰው ሃይል ይይዛል። ማለትም ከ18 ሺህ በላይ የታጠቁ ወታደሮች በአዲሳባ ተሰማርተው የህዝቡን ቁጣ በማፈን ተግባር ተሰማርተዋል። ከዚህ ሃይል ውስጥ አግአዚ 3000 የሰው ሃይል ብቻ ነው ያሰማራው። ፌደራል ፖሊስም 6000 የሰው ሃይል የነበረው ሲሆን፣ ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር ውስጥ የደህንነትና የአዲሳባ ፖሊሱን ቁጥር የሚጨምር አይደለም።

በዚህ ኦፕሬሽን በህዝቡ ላይ ከፍተኛውን ጉዳት ያደረሱት፣ ከአግአዚ ሌላ 1200 የሰው ሃይል የነበረው የአየር ሃይል ሁለት ሻለቆችና፣ 44ኛ ተብሎ የሚታወቀው ክፍለጦር ውስጥ የነበሩ ሻለቆች ናቸው። እንዲያም ሆኖ የአግአዚ 5 ሻለቆች በአመፁ መጨረሻ ላይ በደካማነት ተገምግመዋል። በአማራ መኰንኖችና ወታደሮች በኩል ውስጥ ለውስጥ ሲተላለፍ የነበረውን ፀረ ግድያ መመሪያ የደህንነት መስሪያ ቤቱ

እንደደረሰበት ሁዋላ ሰምተነዋል። መመሪያው ከማን እንደመነጨ ግን መረጃ ያገኙ አይመስለኝም። ቅንጅት ያደራጀው ሃይል ሰራዊቱ ውስጥ ሊኖር እንደሚችል ግን በቀላሉ ይገምታሉ።

ከምርጫው ማብቃት በሁዋላም በርካታ የአግአዚ ክፍለ ጦር ወታደሮች፣ 'የገዛ ወገኖችንን አንጨፈጭፍም' በሚል ትጥቃቸውን እየተዉ በመኮብለላቸው በ1997 ክረምት ላይ የአግአዚ ክፍለ ጦር መኰንኖች አዋሳ ላይ ግምገማ እንዲያደርጉ ሳሞራ የኑስ ወሰነ።

ግምገማውን ጄኔራል ሙሉጌታና ኰሎኔል ገብረመድህን የተባሉ የህወሃት መኮንኖች እንዲመሩት ታዘዙ። 300 ያህል መኰንኖች ነበርን ተሰብሳቢዎች። የመገምገሚያው ነጥብም፣

'በምርጫ 97 አግአዚ ክፍለ ጦር የመንግስት ጠላት ነበር ወይስ የመንግስት ወገን?' የሚል ሆነ።

ተያይዞም በመንግስት ጠላትነት የሚታዩ የአግአዚ መኰንኖች በአስቸኳይ እንዲወገዱ የሚል ትእዛዝ መጣ። በዚህ መሰረት ግምገማው ቀጠለ። ግምገማው ሙሉ በሙሉ በምርጫውና በአፈፃፀም ሂደቱ ላይ እንደሚሆን በተገለፀው መሰረት ጄኔራል ሙሉጌታ እንዲህ ሲል የመነሻ አሳብ አቀረበ፣

'የአግአዚ አባላት በምርጫ እንድትሳተፉ ያደረግነው ኢ.ህአዴግን እንድትመርጡ ነበር። ነገር ግን ያለን መረጃ እንደሚያመለክተው የአግአዚ ሁሉም አባል ማለት ይቻላል ቅንጅትን ነው የመረጠው። አመፁን ለማቆም መንግስት የሰጠውን መመሪያ ችላ በማለት በግልባጩ ስታጥላሉም ነበር። ከዚህም በላይ ኢ.ህአዴግ ከስልጣን እንዲወርድ ትፈልጋላችሁ! መንግስት አመፅን ለመግታት እንድንፈፅም የሰጠን ግዳጅ በተጠበቀው ደረጃ አልተፈፀመም። ይህ ደግሞ ግዳጅን ባለመቀበል የሚፈጠር የአመለካከትና የዲሲፕሊን ችግር ነው። በሰራዊቱ የሚታየው መክዳትም የዚሁ ችግር ነፀብራቅ ነው። ይህ ችግር በተለይ በአማርኛና በኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ላይ ጐልቶ የሚታይ በመሆኑ ግምገማችንም በዚያው ዙሪያ ያተኩራል'

ጄኔራል ሙሉጌታ ከላይ ያለውን ተናግሮ የግምገማውን ትኩረት አቅጣጫ ግልፅ አደረገ። ከምርጫው በሁዋላ ከሙሉጌታ ጋር የነበረን ግንኙነት ሻክሮ ነበር። እንደገለፅኩት ሙሉጌታ ሲበዛ ሃሜተኛ ነበር። ይሙለጨለጫል። ይገለባበጣል። ራሱን





ከፍ ማድረግ መለያ ጠባዩ ነው። እንዲነካ አይፈልግም። ሌላውን ግን እንደፈለገ ማንገላታት ይወዳል። ከምርጫው በሁዋላ ሰው መግደል እንደተጀመረ ሙሉ በሙሉ ከእኔ ርቆ ነበር። እሱም ሆነ ሌሎቹ እኔን በጠላትነት እንደሚያዩኝም አውቂያለሁ።

ግምገማውን ከሚመራው ከኰሎኔል ገብረመድህንም ሆነ ከሌሎቹ የትግራይ ኰሎኔሎች ጋር አብረን ብዙ ስለሰራን በቅርብ እንተዋወቃለን። ገብረመድህን ጠባብ አእምሮ እንዳለው አውቃለሁ። የኮሎኔልን ያህል ማእረግ ይዞ ከጐጡ ባሻገር ማየት ይሳነዋል። ከትግሬ ባሻገር ያለነው ኢትዮጵያውያን ላይ ጥላቻውን በግልፅ ያንፀባርቃል። በትንሽ ነገር ይቀናል። የበታችነትና የድህነት ተፅዕኖ ያሰቃየዋል። ሚሊዮን ብር በእጁ ይዞም የድህነት ስቃይ አለበት። ገንዘብ ተሸክመህም ከድህነት አስተሳሰብ መላቀቅ እንደማይቻል ከዚህ ሰው ግንዛቤ አግንቼበታለሁ። አንጐሉ ውስጥ እንደ ሙጫ የተጣበቀ የበታችነት ስቃይ አጨማዶ ይዞታል። ከወጥ ቤት ሰራተኞች ጋር ሲነታረክ ይውላል። ሱቅ ሄዶ ከባለሱቁ ጋር ይጋጫል። ቡና ቤት ገብቶ ካስተናጋጆች ጋር በጠርሙስ ይደባደባል። ካልተነጫነጨ በሰላም መዋል አይችልም። ሌሎችን ማበሳጨትና ነገር መፈለግ የኑሮውና የህይወቱ ብሂል ይመስላል። ከኔ ጋርም እንዲሁ ተግባብቶ አያውቅም። አማራ በመሆኔ ብቻ በጥርጣሬ ያየኛል። አማራ በመሆኔ ብቻ ስልጣኑን ልነጥቀው እንደምችል ገና ድሮ ደምድሞ ጨርሶአል። እንደማልንቀው ለማረጋገጥ ልዩ ልዩ የተንኰል ወጥመዶችን ሲያጠምድ ይውላል። እንግዲህ ይህ የአዋሳው ግምገማ ለዚሁ የጫጨ ኮሎኔል ምቹ አጋጣሚ ነበር የሆነለት። እየተቀባበሉ ይፎክሩብን ቀጠሉ፣ ገብረመድህን እንዲህ አለ፣

'እንግዲህ አግአዚን የምናፈርሳት ወይም የምናድናት አሁን ነው። ሁላችንም ቆርጠን መነሳት አለብን!'

አያያዘና ጨመረበት፣

'እዚህ ውስጥም ከዚህ ውጭም የአግአዚ ክፍለጦር ባልደረባ ሆኖ ቅንጅትን የመረጠና ቅንጅትን የደገፈ ጠላት ነው። መታሰርም ሆነ መመታት አለበት። ከጠላቶቻችን ጋር አብረን መስራት አንችልም!'

ሙሉጌታ በርሄም ተቀበለው፣

'ከዚህ በሁዋላ እንደነበርነው ሆነን መቀጠል አንችልም።

እንፈርሳለን! ወይም እንድናለን! ስለዚህ የምታውቁትን ሁሉ ተናገሩ'

ከዚያም እድሉን ለተሰብሳቢው ሰጠ፣

ትግሬዎቹ እጅ እያወጡ ተናገሩ። ኰሎኔል አይናም መስፍን፣ ሻለቃ መብራህቱ፣ ሻለቃ ተስፋይ፣ የስብሰባዎቻችንን አስተሳሰብ እየደገሙ ረጃጅም ንግግር አደረጉልን። አሳባቸው ሲጨመቅ፣ 'አግአዚ አመፁን ለማቆም የተጠበቀበትን ያህል አልሰራም' የሚል ነበር። በሌላ አነጋገር 'በቂ ሲቪል ዜጋ አልገደላችሁም' ማለት ነበር። ከዚህ የተለየ ሊሰጠው የሚችል ትርጉም አልነበረውም። ስራችንን በሚፈለገው መልኩ መስራት ያልቻልነው ደግሞ፣ 'ከውስጥ እንቅፋት ስላለ ነው' ሲሉ አጠቃለሉ። ከትግሬዎቹ ባሻገር ያለው ኢትዮጵያዊ አንዳችም ሳይተነፍስ በፀጥታ እያዳመጠ ነበር።

እኔ ከፊት ነበር የተቀመጥኩት። እጄን አወጣሁ። ሙሉጌታ ወዲያውኑ እድሉን ሰጠኝ። እንዲህ አልኩ፣

'ቅንጅትን የመረጠ ሁሉ ጠላት ነው ተብሏል። እንግዲህ ምርጫው የተካሄደው በምስጢር ነው። ማን ቅንጅትን ይምረጥ ማንስ ኢህአዴግን ይምረጥ እንዴት ሊታወቅ ይችላል? ይህን ማወቅ የሚችል ጠንቋይ እዚህ አለ? ከዚህ ባሻገር በሃገር ደረጃ ነፃ ምርጫ ነው ተብሎ ታውጆ የለም እንዴ? ማንኛውም ዜጋ በግሉ የፈለገውን ድርጅት የመምረጥ መብት አለው አልተባለም? እኛ ራሳችን እንዲህ ብለን አልቀሰቀስንም? ኢህአዴግም እስከምናውቀው ድረስ በዚህ መርህ ነው ሲሰራ የነበረው። አሁን እንዴት ነው፣ 'ኢህአዴግን ያልመረጠ ይገደል! ይቆረጥ!' ማለት የተጀመረው? ሌላው ጉዳይ ግምገማው በአማራና በኦሮሞ ላይ ብቻ ለምን አነጣጠረ?

አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ!

ቤተመንግስት ውስጥ 270 የሚሆኑ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የውስጥ እጀባ አሉ። ሙሉ በሙሉ የአድዋ ትግሬዎች ናቸው። የቤተ መንግስቱ ዙሪያ ጥበቃ 550 የሰው ሃይል ይዟል። በአብዛኛው ትግሬዎች ናቸው። ጥይት ቤት ካምፕ ከ500 ያላነሰ ወታደር አለ። ሚስቶቻቸው አሉ። ሰራተኞቻቸውም አሉ። አብዛኞቹ ትግሬዎች ናቸው። የእነዚህ ሁሉ ድምር ከ2000 በላይ ነው። እነዚህ ሁሉ በምርጫው ተመዝግበው እንዲመርጡ ተደርጐአል። ሆኖም በቤተ መንግስቱ ዙሪያ፣ እነዚህ 2000





ትግሬዎች በምርጫ በተሳተፉበት ቀበሌ፣ ኢህአዴግ 165 ድምፅ ብቻ ነው ያገኘው። እንግዲህ ትግሬውም ሙሉ በሙሉ ኢህአዴግን አልመረጠም ማለት ነው። ይህ ከሆነ ለምንድነው ትግሬውን ታማኝ ሌላውን ጠላት አድርጋችሁ የምታቀርቡት?'

ይህን ካልኩ በሁዋላ የስብሰባው መንፈስ ሙሉ በሙሉ ተለወጠ። ተስፋ ቆርጠው አቀርቅረው በዝምታ ተቃውሞ ላይ የነበሩ መኰንኖች ሁሉ እጅ እያወጡ በጨዋ አነጋገር አሳባቸውንና ምክራቸውን ጭምር ሰነዘሩ። ማንም ከማንም የተሻለ ለዚህች ሃገር ያስባል ሊባል እንደማይችል የጠቆሙ ነበሩ። 'ሃገራችን ሰፊ ናት። ይህችን ሰፊ ሃገር፣ ሰፊ ህዝብ ያቀፈች ምድር ለመምራት ሰፊ ልቦናና ሰፊ አእምሮ ያስፈልጋል' ያሉም ነበሩ። ልብ የሚነኩ አባባሎች ተደመጡ። 'ለመጪው ትውልድ ምን ይሆን ትተንለት የምናልፍ?' ሲሉ በትካዜ ጥያቄ ያነሱም ነበሩ።

በርግጥ የዚህን ውይይት በር የከፈትኩት እኔ ነበርኩ። እኔ ያንን የተናገርኩት መናገር ስለነበረብኝ ብቻ ነው። የተናገርኩት ሁሉ ተመዝግቦ ወደ ሳሞራ እንደሚላክ አውቀዋለሁ። እያንዳንዱን ቃል ሰንጥቀው እንደሚያዩትና በቀላሉ እንደማያልፉትም እረዳ ነበር። አማራጭ ግን አልነበረኝም።

እንጭጭና አጥፊ፣ ሃላፊነት በጐደለው መንፈስ የቆሸሹና አሳፋሪ ቃላትን ለተፋብን ለነዚያ ሰዎች ምንም አይነት አሳማኝ ቃላት እንደማይገኝ ግልፅ ነበር። እኔን በግሌ ቢሰድቡኝ ቢያዋርዱኝ በቻልኩት ነበር። ዝንባሌያቸው የዘረኛነት መንፈስ ነበረው። በጥቅሉ ሃገሪቱን የሚያወድም ነበር። የምንኖርባት ይህችው ሃገር ናት። ሌላ ሃገር የለንም። ከፋም ለማም ከነችግሯም ሆነ ከነፀጋዋ አባቶቻችን አውርሰውናል። ይህ የመማር ያለመማር ጉዳይ አይደለም። አባቶቻችን ገበሬዎች ነበሩ። ሞተውም ተሰውተውም የሃገሪቱን ክብር ባህልና ማንነታችንን ሰጥተውን ሄደዋል። እኛም ያንን የማስተላለፍ ግዴታ አለብን። የኛ ፈተና ግን ሃገሪቱን በማውደም ተግባር ላይ የመሳተፍና ያለመሳተፍ ጥያቄ ሆኖ ነበር። 'ሰው ግደሉ! ተጠያቂም አትሆኑም!' ብሎ በስብሰባ የሚነግር መንግስት ባልደረባ መሆኔን እንዴት ልክድ እችላለሁ? ሰምቼ እንዳልሰማሁ እንዴት በፀጥታ መተኛት ይቻለኛል? እነዚህ ስብሰባውን

የሚመሩት ጄኔራሎች፣ 'አማራና ኦሮሞ የሃገሪቱ ጠላት ነው' እያሉ ይህን ትልቅ ህዝብ እየሰደቡት ነበር። ጆሮአችን ላይ ፊት ለፊት እየነገሩን ነበር። እንዳነጋገራቸው መትረየስ አንስተን ደምና ጭቃ ልናደርጋቸው በተገባ። ያን አላደረግንም። በረጋ አንደበት የአንድነት መንፈስ፣ የሃገር ሃላፊነት እንዲሰማቸው ለማድረግ ነበር የሞከርነው። በዚያ ስብሰባ ተቃውሞ ያሰማነው መኰንኖች በምሳ እረፍት ላይ ስንጨዋወትም ያለንበትን ሁኔታ ተገንዝበነው ነበር።

'በጠላትነት ተፈርጀናል። በጠላትነት እንድንታይ ያደረገን ወንጀላችን ደግሞ አማራ መሆናችን ነው' የሚል ነገር ለመነጋገር በቅተን ነበር።

የሆነው ሆኖ በዚያ ስብሰባ እኔ ያደረግሁትን ንግግር አብዛኛው ተሰብሳቢ ደግፎት ነበር። ከስብሰባው ውጭ አማራና ኦሮሞ መኮንኖች ጠጋ እያሉ፣

'ጥሩ አደረግህ! እግዚአብሄር ይስጥህ! ይህችን ሃገር አምላክ ይጠብቃት!' ይሉኝ ነበር።

እኔን ተከትለውም እነ ሻለቃ አዱኛ አለማየሁ፣ ሻለቃ ምስጋናው ተሰማ፣ ሻለቃ አምሃ ስዩም፣ ሻለቃ ብርሃኑ፣ ሻለቃ ደምስ፣ ሻለቃ ጌታቸው አንድ ባንድ እየተነሱ የኔን አሳብ መነሻ በማድረግና በማጠናከር የግምገማውን መሪዎች ተጋፈጧቸው።

ለአንድ ወር ያህል ስብሰባው የቀጠለ ሲሆን፣ በመጨረሻ የኢትዮጵያዊነት ስሜት እያየለ መጣ። አማራና ኦሮሞዎች እንደ አንድ ሰው ሆነን ተጋፈጥናቸው። በጠበበ የጐጠኛነት ኩሬ ውስጥ ሲምቦጫረቁ የነበሩ አንዳንድ የትግራይ መኰንኖችም ወደ ሰፊው ጐራ መምጣት ሲጀምሩ፣ ስብሰባው ባጭሩ እንዲቋጭ ተደረገ። ሳንስማማ እንደተስማማን ተደርጐ አፈርሳታው አበቃ።

ከስብሰባው በሁዋላ ግን ነጣጥለው መቱን!

ነሃሴ መጨረሻ ላይ እኔን ወደ "የአዛዥነትና የመምሪያ መኰንንነት ኰሌጅ" ለትምህርት ወደ ደብረዘይት ላኩኝ። መስከረም ላይ በስብሰባው ላይ እኔን ደግፈው ሽንጣቸውን ገትረው ከተሟገቱት መካከል ጥቂቶቹ ተይዘው ታሰሩ። እነዚህም ሻለቃ አዱኛ አለማየሁ፣ ሻለቃ ምስጋናው ተሰማ፣ ሻለቃ ብርሃኑ፣ ሻምበል ውብቱ፣ ሃምሳ አለቃ ዘላለም፣ ሃምሳ አለቃ ተስፋዬ ናቸው።





ሁሉም አማርኛ ተናጋሪ ነበሩ።

በሌሊት ከየተኙበት እየታፈኑ ተወሰዱ።

'መለስ ዜናዊ ላይ የግድያ ወንጀል ለመፈፀም አሲራችሁዋል' የሚል ጥያቄ እየቀረበላቸው ማእከላዊ ምርመራ ከባድ ፍዳ እየደረሰባቸው መሆኑን ሰማሁ። አንድ ጄኔራልና አራት ኰሎኔሎችን ያቀፈ ኰሚቴ አቋቁመውም በምናብ የፈጠሩትን የግድያ ሙከራ እቅድ ለማግኘት ሲደክሙ ሰነበቱ። የግድያ ሙከራው የህቡእ አደራጅ ብለው የጠረጠሩት እኔን ሲሆን፣ በደብረዘይት ቆይታዬ ገረንስኤ የተባለ ኰሎኔል፣ (በአሁኑ ሰዓት የመለስ የነፍስ ጥበቃ የቅርብ ሃላፊ) መድበውብኝ ሲመርጁኝ ሰነበቱ። ሆኖም የኰሚቴው ምርመራም ሆነ ስውር ክትትላቸው ውጤት ሳያስገኝላቸው ቀረ።

በመጨረሻ ቤተመንግስቱ አካባቢ የነበሩ አማሮችን በሙሉ ከአካባቢው በማራቅ፣ አንዳንዶችን በማሰር ስራቸውን አጠናቀቁ። የታሰሩት አብዛኞቹ ከቤተሰቦቻቸው ሳይገናኙ ለአንድ አመት ያህል በከባድ ምርመራና ድብደባ ስር ከርመው መረጃ ሲያጡ ለቀቋቸው። እኔንም ችላ ብለው ትተውኛል ብዬ ወደ ማመኑ ነበርኩ። ዳሩ ግን ተሳስቼ ኖሮአል። ለአንድ አመት ከሶስት ወር ያህል ታስሬ ከሰራዊቱ ተባረርኩ..."

በሚቀጥለው ቀን "በፃድቃንና በፆረና" ጉዳይ ልናወጋ ተነጋግረን በቀጠሮ ተለያየን።

# - 12 -

# ስብሃት ነጋ በጨረፍታ

ብልጭ ብሎ ጠፋ፣
ተወርዋሪ ኮከብ - የሃሳብ አንጋፋ፣
እንደዚህ ከሆነ - ጨለማው በርክቶ - ቆንጆዋ ታጥር፣
ዘልአለም ታልቅሰው - ሙታ እስክትቀር፣
በጨለመ ቦታ - የተሰፋ ዛፍ ሁላ፣
ያለምንም መላ፣
ቅጠልዋ ጠውልጐ፣
ግንደ ቆርቁር ሁላ - ውስጧ ተመስጐ፣
ደሞ ፍሬ እንዳትሰጥ - ፍሬ እንዳታበላ፣
ተቆራርጣ ቀረች - ከስር ተመንግላ፣
እንግዲህ ማን ቀረ - ጨለማና ቆንጆ፣
የህሊና ድምፁ - ይግባ ተመልሶ - ከህሊና ጐጆ፣

(ግጥም - ዮሃንስ አድማሱ)

*ከእለታት አንድ ቀን አንድ ሰው ነበረ። ሲያድግ፣ ሲማር፣ ሲያስተምር፣ ቆየና እድሜው ለትግል እንደደረሰ ወደ በረሃ ሸፈተ። ደደቢት ከተባለው በረሃ እንደደረሰም በቅድሚያ አምባሻ የተባለ ዳቦ አስጋገረ። ከዚያም አምባሻው ተቆረሰና የጠመንጃ ስም ወጣላት። የወተት ስሙንም፣ "ጠሴን ጥምቡሳሴን፣ አታውቃትም ነብሴን" ብሎ ጭንቅላቱ ላይ ሶስት ጊዜ አሽከርክሮ ሲያበቃ፣ ወደ ኤርትራ አቅጣጫ ወረወረው።*

*አምባሻው ሲቆረስ 7 ነበሩ ይባላል። በ17ኛው አመት ለቢሾፍቱ ቆሪጥ የይለፍ ነጭ ላም አርደው አዲሳባ ሲደርሱ 77 ሺህ ደርሰው ነበር። የክፉ እድል ቀን ብለው የሚጠሯት ቀንም በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ የመጀመሪያው ዴሞክራሲያዊ*





*ምርጫ የተካሄደባትን እለት ሲሆን፣ ያቺም ቀን ግንቦት 7፣ 1997 ናት። 7 ቁጥር ላይ የመጠንቆል አሳብ የለኝም። ለዛሬው እንግዲህ ቁጭ ከማለት ብዬ ከመሪዎቹ አንዱን መደበሪያ ላደርጋቸው ፈቀድኩ። ስብሃት ነጋ!*

* * *

ከህወሃት መስራቾች አንዱ የሆኑት ስብሃት ነጋ ወደ ሚዲያ ብቅ ብለው በተናገሩ ቁጥር በርካታ ጫጫታ እንደሚከተል መቼም አስተውላችሁ ይሆናል። ለምን እንዲያ ሆነ ሲባል አንዳንድ ሚዲያዎች፣

"አቦይ ስብሃት ስላረጁ እየዘላበዱ ነው" ይላሉ።

በዚህ እንኳ እኔ አልስማማም።

በርግጥ ስብሃት ነጋ እድሜያቸው መግፋቱ እውነት ነው። እንደሚገመተው ግን አሳባቸውን አቀናብረው መግለፅ እስኪቸገሩ ድረስ ጃጅተዋል ብዬ አላምንም። "ዘላበዱ" የሚያሰኝ ንግግር የሚያደርጉበትን ምክንያት መገመት ሳይሻል አይቀርም። በመጠኑም ቢሆን ቀረብ ብዬ ስለማውቃቸው በጨረፍታም ቢሆን አንድ ነገር ማለት የምችል ይመስለኛል...

"በፍቅር ላይ ፍቅር - ፍቅር ተደርቦ" የሚለውን የአስቴር አወቀ ዘፈን ሰምታችሁታል? በእነዚያ በወያኔነት ዘመናት ደግሞ፣ "በአድዋ ላይ እንግሊዝ ተደርቦ" እያልን እንቀልድ ነበር። አቦይ ስብሃት እሩብ የእንግሊዝ ዘር አለባቸው። በጄኔራል ናፒየር መሪነት አፄ ቴዎድሮስን ሊወጉ መቅደላ አምባ ከመጡት ወታደሮች አንዱ መልኩን ሳይሆን ከፋፍሎ የመግዛት ተንኮሉን አቦይ ስብሃት ዘንድ ትቶልን ሄዶአል። የዚህን መረጃ እውነትነት ለማረጋገጥ ተፈራ ገዳሙ የተባለውን የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ጋዜጠኛ ዋቢ እጠቅሳለሁ። እሱም የአቦይ ስብሃት የስጋ ዘመድ እንደመሆኑ፣ የዚያን እንግሊዛዊ ወታደር ደምና ስጋ ይቋደሳል። ወያኔ በነበርኩባቸው በእነዚያ ዘመናት ከተፈራ ጋር አንዳንድ ጊዜ ቢራ ቤት ስንገናኝ እንግሊዛዊውን መኮንን ማነሳሳታችን አልቀረም፣

አንድ ቀን አንድ የጋራ ጓደኛችን እንዲህ ጠየቀው፣

"እንግሊዛዊው እንዴት ከጦሩ ተለይቶ አድዋ ሊቀር ቻለ? እንዴት ያለች የአድዋ ሽኮሪና(ቆንጆ) ትሆን ልቡን ነድፋ

ያስቀረችው?"

ሌላው ተረበ፣

"ፍቅር ይዞት ሳይሆን፣ ወባ ይዞት ነው የቀረው"

ይህ እንግዲህ ቀልድና ቁምነገር ነው። ቀልዱ ይቆይልንና ወደ ቁምነገሩ እንዝለቅ...

አቦይ ስብሃት ከመቀሌ ሬድዮ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ፣ "ኤርትራ የውጭ ወረራ ቢገጥማት ከህዝቡ ጎን ሆነን እንዋጋለታለን" ሲሉ በመናገራቸው አንድ ሰሞን፣

"አዛውንቱ ለየላቸው" የሚል ትችት ተደምጦ ነበር።

ሌላ ጊዜ ደግሞ፣

"EFFORT በኢትዮጵያ ውስጥ ቀዳሚው ቢሊዬነር ኩባንያ ነው" ሲሉ ደረታቸውን ነፍተው ተመኩ።

ስለ ስዬ አብርሃ ተጠየቁና ደግሞ፣

"ስዬ አብርሃ የሰገራ ቤት አይጥ ሆኖአል" ሲሉ ተናገሩ።

አቦይ ስብሃት ስዬን ለምን እንዲያ እንደሰደቡት ቤተኞች እናውቃለን። ህወሃትን እንደ ጣውላ ለሁለት በሰነጠቀው ስብሰባ ወቅት ስዬ ሽማግሌውን፣ "ሰካራም!" ሲል ሞልጮአቸው ነበር። ስዬ ተሳዳቢ ነው። ክንፈን፣ "አሽከር!" ሲል ሰድቦታል። አቦይ ስብሃት እንግዲህ ለዚያች ምላሽ መስጠታቸው ሊሆን ይችላል። መሰዳደቡን ከልጅነታቸው የለመዱት ስለሆነ ብዙም አይጎዱም። "ክብሬ ተነካ" ብሎ ያዙኝ ተውኝ የሚል የለም። በተቀረ አቦይ ስብሃት መጠጥ እንደሚወዱ አይክዱም። ቃለ መጠይቅ የሚሰጡት ግን ጠጥተውና ሰክረው አይደለም። ማታ ላይ ወይም በሰንበት ካልሆነም ጋን ገልባጭ የሚባሉ አይነት አይደሉም። ከቀማመሱ በሁዋላ ግን መስከር ያለ ነው። ሞቅ ሲላቸው ግልፍተኛ ናቸው። በከረንቦላ ኳስ አናትህን ሊበረቅሱህ ይችላሉ። ከተበረቀስክ በሁዋላ ምን ታመጣለህ? ኮሎኔል አበበ ከመበርቀስ እግዜር ነው ያተረፈው። ይሄን በቀጣዩ ምእራፍ አወጋችሁዋላሁ...

ስለ "ብሽሽቅ" ታውቃላችሁ?

አቦይ ስብሃት ቀልድና ብሽሽቅ አጥብቀው ይወዳሉ። የፖለቲካ ጥበባቸው እንዲያ ነው። "የኔ የራሴ - የልቤ ነብሴ!" የሚሉትን የቅርብ ሰው ሳይቀር በብሽሽቁ ጨዋታ አፈር አባቱን ብቻ ሳይሆን፣ አፈር እናቱን ጭምር ያስግጡታል።

የአቦይ ስብሃትን "ብሽሽቅ" መውደድ እንዴት ብገልፀው





ይሻል ይሆን? ለአብነት ንዋይ ደበበ የተባለው የኛ ዘመን ድምፃዊ፣ አለማየሁ እሸቴ የተባለውን ቀደምት ድምፃዊ ማብሸቅ ይወድ ነበር። ንዋይ እያበሸቀው አለማየሁ እየበሸቀ ረጅም ዘመን ተጉዘዋል። አቦይ ስብሃትና የኢትዮጵያ ህዝብ ንዋይና አለማየሁ ማለት ይመስሉኛል። አቦይ ስብሃት እያበሸቁን፣ እኛ እየበሸቅን ይኸው ስንት ዘመናችን? 'ትረካን ትረካ ያነሳዋል' እንዲሉ...

*(....በደርግ ዘመን እውቅ ድምፃውያን ሁሉ ተሰባስበው ደሴ ከተማ ላይ የዘፈን ትርኢት ሊያሳዩ ሄደው ነበር። በቡድኑ ውስጥ ከጥላሁን ገሰሰ ጀምሮ ታዋቂ የተባሉት ድምፃውያን ሁሉ ነበሩበት። ይህን ታሪክ ያጫወቱኝ ኮሜድያን ደረጄና ሃብቴም አብረው ተጉዘዋል። አጣፍጬ ላውጋችሁ...*

*ንዋይና አለማየሁ እንደልማዳቸው እየተበሻሸቁ መጓዝን ለምደውታል። እና ታዲያ፣ የደሴ ከተማ ህዝብ ጀርባውን ለጦሳ ተራራ ሰጥቶ ዘፈን ሊያዳምጥ ዝግጁ ሆነ። አለማየሁ እሸቴ ከቀደምት ድምፃውያን አንዱ እንደመሆኑ ታዲያ ዜማውን ሊያዜም ወደ መድረክ ብቅ አለ። እና እንዲህ እያለ ዘፈነ፣*

*"አዲስ አበባ ቤቴ!*
*ቀንጆ ልጅ፣ ሸጋ ልጅ፣*
*አለች ጎረቤቴ!"*

*እንደ ኤልቪስ ፕሪስሊ፣ ያንን የምንወድለትን ድምፁንና እግሩን እያንቀጠቀጠ፣ እንደ ቆመ ዜማውን አዘነበው።*

*ዳሩ ምን ያደርጋል?*

*ደሴ በዚያ ዜማ ሊማረክ ሳይችል ቀረ።*

*ደሴ የሚወደውን አለማየሁ እሸቴ ሳያውቀው ቀረ። የታለ "የጁ የጁ?"፣ የታለ "የአምባሰል ዳገት?"፣ የታለ "ገራዶ ገራዶ?" የደሴ ታዳሚ ተበሳጨ።*

*"ኢሰፓ! ፓርቲያችን!*

*የድል ውጤታችን!" የተባለው ዘፈን የተዘፈነ ይመስል፣ ደሴ በዝምታ አለማየሁን ሸኘው።*

*እስኪ ራሳችሁ አስቡት? ደሴ ከተማ ላይ፣ "አዲስ አበባ ቤቴ!" ብሎ ማዜም ምን ማለት ነው?*

*"ደሴ ወልዲያ ቤቴ፣*
*የጁ፣ ወሎ ቤቴ*
*አምባሰል ጉረቤቴ!" ብሎ መለወጥ ሲገባው፣ ያንን*

*ባለማስተዋል የደሴን ሰው አስቀየመ። የደሴ ህዝብ አዲሳባ ዋና ከተማው እንጂ ቤቱ ስላልሆነች በደስታ ሊጮህ አልቻለም። ደሞ አዲሳባ ጠይም ትሁን ጥቁር የት ያውቃታል?*

*አሌክስ ቴክሉ ዘፍኖ ጨርሶ ሲወጣ እንደ ቀፋፊ ዝናብ "እኝኝ" ባለ ጭብጨባ ነበር የሸኙት።*

*የቀጣዩ ዘፈን ተረኛ ጨረቃማ ፊት ያለው ንዋይ ደበበ ነበር። ንዋይ ወደ መድረክ እንዲወጣ ተጠርቶ ሲሄድ፣ አለማየሁ ተሰናብቶ ሲወጣ ከመድረክ በስተጀርባ ተገናኙ።*

*ንዋይ እንዲህ አለው፣*

*"ጋሽ አለማየሁ! ያስተኛኸውን ህዝብ እንዴት እንደምቀሰቅሰው በል አሁን ተመልከት!"*

*ንዋይ ደበበ ማይክራፎኑን እንደጨበጠ፣*

*"የጥቅምት አበባ!" ብሎ ቢያምባርቀው ደሴ ከመቀመጫዋ ተነሳች። በመቶዎች፣ ምናልባት ከዚያ በላይ የደሴ ነዋሪ አብሮት ዘፈነ!*

*"...የጥቅምት አበባ! ነሽ አሉ፣*
*አወድሽው አካሌን በሙሉ..."*

*ወጣቶች ተቃቅፈው እንባ በእንባ!*

*እንደ ነጎድጓድ በከባድ ጩኸት! ደሴ ተናወጠች! የደሴ ህዝብ የጥቅምትንም ሆነ የመስቀልን አበቦች ቦሩ ሜዳ ላይና ጦሳ ተራራ ላይ ያውቃቸዋል። ጉረምሶች ልጃገረዶችን በጥቅምት አበባ መመሰል የተለመደ ነበር። እና ንዋይ ልባቸውን ጮቤ አስረገጠው። ደምስራቸውን በደስታ ስሜት ነካው! ወደ ልብ የሚያደርሰውን ዋናውን የደምስር ቱቦ!!)*

አቦይ ስብሃት በርግጥ የኢትዮጵያውያንን ደም ስር መንካት የሚፈልጉት አስደስተው ሳይሆን በተገላቢጦሹ ነበር። የህዝቡን ደም ስር በመንካት ህዝቡ እንዲቆጣ የማድረግ ችሎታ አላቸው። አቦይ ስብሃት ይህን የሚያደርጉት ግን ብዙዎች እንደሚገምቱት ጃጅተው አይደለም።

ምክንያት አላቸው።

የህዝቡን የቁጣና የአመፅ ደረጃ ይለኩበታል። የተቃውሞውን መጠን ያጤኑበታል። አጤ ምኒልክም በተመሳሳይ የህዝቡን የቁጣ ደረጃ የሚለኩበት የራሳቸው ዘዴ ነበራቸው። አጤ ምኒልክ 'ህዝብ በአደባባይ ከተቆጣ ችግር





የለውም። ህዝብ ካልተቆጣና ዝም ካለ ያን ጊዜ አደጋ አለ።' ይሉ ነበር። አቦይ ስብሃት ይህን ልምድ ከአጤ ሚኒልክ ይውረሱት፣ አለያ ከእንግሊዛዊው አያታቸው ለማወቅ ግን ጥቂት ጥናት ሳያስፈልገው አይቀርም።

በርግጥም የአቦይ ስብሃት አብሻቂ ንግግር ጥሩ የፖለቲካ ትኩሳት መለኪያ ቴርሞሜትር ሊባል የሚችል ነው። ውሻህን እስከ ምን ድረስ እንደምትገርፈው ካላወቅህ መጠን ታልፍና ተመልሶ ሊነክስህ ይችላል። ግመል ቂም ከያዘችብህ አትለቅህም። ጊዜ ጠብቃ ማጅራትህን ነክሳ ትገድልሃለች። ቂም በማትይዝበት ደረጃ እንድትጭናት ግን ትፈቅድልሃለች። ትጭናታለህ፣ ታልባታለህ፣ ሌላም ሌላም ታደርጋታለህ። በመጨረሻ እግርና እጁን አስረህ አርደህ ስጋዋን ትበላለህ። ከቆዳዋ ደግሞ ጫማ ትሰፋና ትጫማዋለህ። ሌሎች ግመሎች ጫማህ በእናታቸው ቆዳ እንደተሰራ አያውቁም። እነሱም ተራቸው ደርሶ ጫማ እስኪሆኑ ድረስ በታማኝነት ያገለግላሉ። ጫማ ከመሆኗ በፊት ከበረሃ ወደ በረሃ የኰበለለች የግመል ልጅ የለችም። ግመል ምንጊዜም የእናት ያባቷን ተከትላ ታገለግላለች።

*( በዚህ በኛ ዘመን ወተቱን እያሳለበ ያለ ዜጋ እያሻቀበ በመሄድ ላይ ይገኛል። የወተቱስ ደህና! እዳው ወተት ነው። ቆዳውን ለጫማ አሳልፎ መስጠትም አለ። በኔ በኩል በከፊል መታለቤን አልክድም። ለግለሰቦች የስልጣን ረሃብ ከብት ሆነህ ማገልገል ማለት ወተትህን ማሳለብ ማለት ነው። በአንድ ነገር ግን ርግጠኛ ነኝ። ቆዳዬ ጫማ ከመሆኑ በፊት ማምለጥ ችያለሁ። ማምለጥ ሲባል ከሃገር መኮብለል ማለት አይደለም። በሃገር ውስጥ እየኖረ፣ ወተቱን ቀርቶ ፀጉሩን የማያስነካ አለ። በአንፃሩ አውሮፓና አሜሪካ ተቀምጦ፣ ወተቱን አሳልቦ ጨርሶ፣ 'ስለ ፈጣሪ ብላችሁ - ጫማ አድርጉኝ እባካችሁ' እያለ የሚያስቸግረውን* Google *ይቁጠረው።)*

አቦይ ስብሃት በአመት አንድ ጊዜ ወደ ሚዲያ ብቅ እያሉ ደም ስርን በሚያናውጡ ቃላት የቁጣ ስሜታችንን መለካታቸውን ቀጥለዋል። አቦይ ስብሃት ወደ ሚዲያ ብቅ ከማለታቸው በፊት ከመለስ ዜናዊ ጋር ሊነጋገሩ የሚችሉትን

በምናብ ላስደምጣችሁ፣

“ቃለመጠይቅ እያሉኝ ነው። ትምክህተኛው ትንሽ ቢንጫጫ ምን ይመስልሃል?”

መለስ እየሳቀ፣

“አንጫጫው!”

“ቆየት ብለህ አንተ ታስተኛዋለህ!”

ከፍተኛ ሳቅ!

መለስ ህዝቡን ተስፋ እየመገበ፣ ባዶ ኩራት እያሸከመ ለማስተኛት ጥረት ማድረግ ዋና የስራ ተግባሩ ነው።

*(...ኢኮኖሚያችን 11% አደገ። ከአውሮፓና ከአሜሪካ መንግስታት ጋር ያለን ወዳጅነት እመርታ አሳየ። ያራ የተባለ የኖርዌይ ፋንዲያ ነጋዴ ኩባንያ ሽልማት ሸለመን! ጃፓኖች የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ሰጡን! የ2002 ምርጫ ላይ አመፅ ከተነሳ ጥይት ላለመተኮስ ወስነናል። አመፁን በውሃ ብቻ እንበትነዋለን። መለስ ዜናዊና ሃይሉ ሻውል በመጨባበጣቸው ተደስቶ ባራክ ኦባማ እስክስታ ወረደ። ግንቦት7 የተባለው ቡድን አሸባሪ መሆኑ ስለተረጋገጠ ሞት ፈረድንባቸው። መለስ ‘ብርቱካን ሚደቅሳን ከምፈታ፣ አዜብ መስፍንን መፍታት ይቀለኛል።’ አሉ። ብሄሮችና ብሄረሰቦች በአመራር ችሎታችን ተደነቁ። የአዲስ አበባ ህዝብ ቅንጅትን በመምረጡ ተፀፅቶ ‘ማረኝ ኢህአዴግ!’ አለ። ሞቃዲሾን በመቆጣጠራችን የሶማሊያ ህዝብ በጭብጨባ ተቀበለን። ክልሎች ከትግራይ ክልል የአስተዳደር ችሎታ ትምህርት ቀሰሙ። የተከዜ ግድብ ከአፍሪቃ አንደኛ ሆነ። የኢትዮጵያ ገበሬ ሚሊዬነር ሆነ። ኤርትራ ላይ ማእቀብ እንዲጣል አደረግን። ቀዳሚ እመቤት መልቲ ሚሊዮኔር ሆነች። የጎተራ ድልድይ የብሄር ብሄረሰቦች እኩልነት፣ የአንድነታችን፣ የመፃኢ ልማታችን፣ የህዳሴ አርማችን መሆኑን እንትና የተባለው እንትን ገለፀ...)*

“መለስ ጠቅላይ ሚኒስትር ቢሆንም፣ ይህችን ሃገር ከጀርባ ሆነው የሚመሯት አቦይ ስብሃት ናቸው!” የሚል አነጋገር አንብባችሁ ሊሆን ይችላል።

አባባሉ የተጋነነ ነው።

አባባሉን የምንቀበል ከሆነ መለስና አባዱላ አንድ ሆኑ ማለት ነው። ይሄ ሊሆን አይችልም። ኢትዮጵያን በመምራቱ





ሂደት፣ አቦይ ስብሃት “የማይናቅ ተፅእኖ ያሳድራሉ” ማለት ግን ይቻላል። ይህችን አገር በመምራቱ ሂደት የማይናቅ ተፅእኖ ስለሚያሳድረው ስውር ሰው መነጋገር ግን ተገቢ ይሆናል።

አቦይ ስብሃት ማናቸው?

ታክቲካቸው፣ ስትራቴጂያቸው፣ ምኞትና ህልማቸው ምንድነው? ምንስ ነበር? ወደፊትስ ይህችን አጀንዳዋ የተንዛዛ፣ ጣጣዋ የበዛ ሃገር ወደየትኛው ገደል ይገፈትሯት ይሆን?

እኚህ አዛውንት በጋዜጣና በሬድዮ የተናገሩትን በማንበብ አመለካከታቸውን መመዘን ያስቸግራል። የወያኔ አመራር አባላት የሚናገሩትን ሆነው አያውቁም። እኔም ታዲያ ከሚናገሩት ባሻገር ያሉ ትእዝብቶቼን ነው በጨረፍታ የማወጋችሁ።

የግንቦት 20 በአል እየተከበረ ነበር።

ካልተሳሳትኩ ጊዜው 1989 ይመስለኛል። እኔም በወቅቱ ጋዜጠኛ እንደመሆኔ በቦታው ቀደም ብዬ ተገኝቻለሁ። የግብዣው አዳራሽ ደጅ ላይ ከአንድ የህወሃት ባለስልጣን ጋር ቆሜ እያወጋሁ ነበር። የአቦይ ስብሃት ነጭ ኩብራ መጥታ ቆመች። ጠባቂዎቹ ግራና ቀኝ ተቀላጥፈው ወረዱ። ሽማግሌው ከመኪና ከመውረዳቸው በፊትም ሁለት ህፃናት ልጆቻቸው ቀድመው ወረዱ። እየተሯሯጡም ወደ አዳራሹ ገቡ። ልጆቹን አውቃቸዋለሁ። የለየላቸው ቀበጦች ናቸው...

*(አቦይ ስብሃት ወደ መኰንኖች ክበብ ከረንቦላ ሊጫወቱ ሲመጡ ይዘዋቸው ይመጣሉ። በሽቦ አለንጋ ሚኒስትሮችንና የጦር መሪዎችን እየገረፉ ሊጫወቱ ይሞክራሉ። ከራቫቱን አሳምሮ ቁጭ ያለ አማራ ወይም ኦሮሞ ሚኒስትር በስብሃት ቀበጥ ልጆች ሳያስበው “ሾጥ” ሲደረግ፣ መጀመሪያ ይቆጣል። ቀጥሎ የስብሃት ነጋ ልጆች መሆናቸው ትዝ ሲለው ይስቃል። ስብሃት ልጆቹን አይቆጣቸውም። ልጆቹ ደግሞ የሚቃለዱት ከሚኒስትሮችና ከጄኔራሎች ጋር መሆኑን አያውቁም። እኩያ ዘመዶቻቸው መስለዋቸው ሊሆን ይችላል። ሚኒስትሮቹም የሽቦ ግርፊያውን መቻል ይመርጣሉ፣ “የልጅ ነገር” እያሉ። ግርፊያው እኔንም አጋጥሞኛል። ሳላስበው ነው። ቁጭ ባልኩበት ከሁዋላ በኩል እንደ ሽቦ በጠነከረ የፕላስቲክ ገመድ ነገር ወደ ጆሮዬ ሊከቱ አሰበው፣ ሳቱትና ጐማው በአንገቴ በኩል ብቅ ሲል እባብ የተጠመጠመብኝ መሰለኝ በጣም ደነገጥኩ። ዘወር ስል*

*ልጆቹ ናቸው። አንዱን ቀጨም አደረግሁትና እንዲህ አልኩት፣*

*"እኔ ላይ እንደሱ አታድርግ! ሌላ ሰው ሄደህ ግረፍ! ሌላ ሰው ከገረፍክ እኔ በጣም እስቃለሁ" አልኩና እንዲህ ያለውን ሰቆቃ የመሸከም ጫንቃ ወዳለው የወያኔ ጄኔራል ላክሁት።*

*የስብሃት ጩጩ እኔን ተወና ወደ አባዱላ ሄደ። አባዱላን ገርፎ ሲያበቃ ወደኔ ተመልሶ መጣና፣ "ሳቅህ?" ሲል ጠየቀኝ። የምር ስቄ ነበርና "አዎን! በጣም ሳቅሁ!" አልኩት። እንደገና ሊያስቀኝ ወደ ሌሎች ባለስልጣናት ሄደ።*

*ይህ ልጅ ዛሬ ጎረምሳ ሆኖአል።*

*መጎርመሱን ያየሁት የንጉሳዊ ህይወትና ቅብጠታቸውን የሚያሳየው ፎቶግራፋቸው የኤልያስ ክፍሌ ethiopianreview ላይ የተለጠፈ ጊዜ ነበር። የስብሃት ወንድ ልጅ አስቂኝና ጥሩ ልጅ ነበር። በእነዚያ ዘመናት ብዙ አስቆኛል። በቀሪው የህይወት ዘመኑ የቃጅማው ጊዮርጊስ የሳቅ ፀጋ ያብዛለት...)*

እና ያን ቀን የግንቦት 20 በአል እየተከበረ ነበር...

የአቦይ ስብሃት ልጆች እየተሯሯጡ ወደ አዳራሹ ገቡ። ከፊት ቀድሞ የወረደው ትልቁ ልጅ ሰማያዊ ሹራብ አድርጎ ነበር። የሹራቡ ደረት ላይ በነጭ Free Eritrea የሚል ፅሁፍ አነበብኩ። ሁለቱን ቃላት በመደነቅ ነበር ያስተዋልኳቸው...

አቦይ ስብሃት ከመኪና ወርደው ወደ አዳራሹ ከመዝለቃቸው በፊት ለኔና አብሮኝ ለነበረው የህወሃት ባለስልጣን የሞቀ ሰላምታ አቅርበውልን ጨበጡን። እናም እኔን እንዲህ አሉኝ፣

"ምነው ጠፋህ ታዲያ?"

"ስራ እንዳላስፈታህ ብዬ ነው።"

"ደውልና ብቅ በል፣ እናወራለን"

ቀጥለው እንዲህ አሉ አቦይ ስብሃት፣

"የፃፍከውን ደግሞ አንብቤዋለሁ"

"የትኛውን?"

"የኰሎኔሉን ሚስት!"

እና አቦይ ስብሃት ሳቁ! እኔም ከፍ ባለ ድምፅ ሳቅሁ።

*("እፍታ" ቅፅ 3 ላይ እሳቸውን የተመለከተ አንድ ትረካ አትሜ ነበር። ትረካው በጣም አስቂኝ ሲሆን፣ እሳቸው በግል ያጫወቱኝን ነበር በመጠኑ አሳምሬ ለንባብ ያበቃሁት። ትረካው*





*በትግሉ ጊዜ አቦይ ስብሃት መድሃኒት ለመግዛት አዲሳባ መምጣታቸውን፣ ከደርግ ነጭ ለባሾች ለመሰወር ሲሉ ከአንድ ኮሎኔል ቤት በዘበኛነት ተቀጥረው እንደነበር፣ የኮሎኔሉ ሚስትም በብቸኛነት በመጎዳቷ አቦይ ስብሃት ያቀብሏት ዘንድ ፊልጋ እንዴት እንደተፈታተነቻቸው የሚያወጋ አስቂኝ ትረካ ነበር።)*

አቦይ ስብሃት በ"ኮሎኔሉ ሚስት" ትረካ ቀላልደው ሲያበቁ፣ ወደ አዳራሹ ዘለቁ። እሳቸው ወደ አዳራሹ እንደገቡ አብሮኝ የነበረውን "ብፃይ" እንዲህ ስል ጠየቅሁት፣

"ስብሃት በኤርትራ ላይ አሟለካከታቸው እንዴት ነው?"

ከዚህኛው ታጋይ ጋር ስለምንግባባና ኢህአዴግን የማማት ልምድ ስላዳበርን እንጂ ይህን የመሰለ ወግ ከህወሃት ካድሬዎች ጋር የሚሞከር አልነበረም፣

"ሹራቡን አይተህ ነው?" ሲል መልሶ ጠየቀኝ።

"ሹራቡ አንዱ ነው። ሌላም ግን የታዘብኩት ነገር አለ"

"ምን ታዘብክ?" ሲል ጠየቀኝ።

አንድ አጭር ታሪክ አጫወትኩት።

"ግንቦት ሃያ እለት አዲስ አበባ ሲያዝ አቦይ ስብሃት ደሴ ነበሩ። ዜናውን እንደሰሙ፣ 'አንድ የታሪክ ምእራፍ ተዘጋ' ካሉ በሁዋላ፣ ሾፌራቸውን ወደ አስመራ እንዲነዳ አዘዙት። እስከ ሰኔ አጋማሽም አስመራ ነበሩ..."

"ማን ነገረህ ይህን?" ሲል ጠየቀኝ።

"ራሳቸው"

እየሳቀ እንዲህ አለኝ፣

"ነገር ማቆላለፍ መቼም ትወዳለህ። ሁለቱም ትዝብቶችህ ለኔ ትርጉም አይሰጡኝም። አቦይ ስብሃት ፊቱን አዙሮ ወደ አስመራ ያመራው ከአዲሳባ ይልቅ አስመራ ያሉ ጓደኞቹና ዘመዶቹ ስለሚበረክቱ ሊሆን ይችላል። ስራም ሊኖረው ይችላል። የሹራቡም ቢሆን አጋጣሚ ሊሆን ይችላል። ከዚያ ባሻገር ግን አቦይ ስብሃት ከድርጅቱ አስተሳሰብ የተለየ ስሜት ሊኖረው አይችልም" ሲል ግላዊ አስተያየቱን ነገረኝ።

"ብፃይ" ጓደኛዬ እንደገመተው የስብሃት ነጋ ወንድ ልጅ በግንቦት 20 በአል ላይ Free Eritrea የሚል ሹራብ ለብሶ የመጣው በአጋጣሚ ነው ለማለት ግን ሳልችል ቀረሁ።

አቦይ ስብሃት ለበአሉ ታዳሚያን ማስተላለፍ የፈለገው መልእክት ሊኖር አይችልምን? ይህን ለማለት የሚያበቃ ሙሉ መረጃ ባይኖረኝም የመገመት መብት ግን አለኝ። ነገሮችን የማቆላለፍና የተለየ ትርጉም እንዲሰጡ የማድረግ አሉታዊ ዝንባሌ አለኝ ብዬም አላምንም። ምክንያታዊ መሆን እሻለሁ።

በሰርግ ላይም ሆነ በግብዣዎች ላይ የሚገኙ ህፃናት ብዙውን ጊዜ ትኩረት ይስባሉ። ሲሯሯጡና ወዲያ ወዲህ ሲሉ ሁሉም ያያቸዋል። ሁሉም ይይዛቸዋል። ሁሉም ይስማቸዋል። "የማን ልጆች ናቸው?" የሚል ጥያቄ ማንሳት የተለመደ ነው። የአቦይ ስብሃት ልጆች መሆናቸው በራሱ ትኩረት ይስባል። ልጆቹ በጥባጭ መሆናቸው ደግሞ ትኩረት የመሳብ እድሉን ይጨምረዋል። "ግንቦት 20" በአል "ኢትዮጵያዊ በአል" ነው ብለን ካመንን፣ "ኢትዮጵያዊ" የሆነ በአል ላይ "Free Eritrea" የሚል መፈክር በመስቀል ከቶ ምን ጥቅም ሊገኝ ይችላል? ለምን አስፈለገ? የኤርትራ ነፃነት ጉዳይ በኢትዮጵያውያን ዘንድ እንዴት እንደሚታይ፣ ምንስ ቅሬታ እንዳስከተለ እየታወቀ፤ ይህ በአናቱ ሲጨመር በአሉ ይደበዝዛል ወይስ ይደምቃል? አቦይ ስብሃት ከቤታቸው ከመነሳታቸው በፊት ይህን ማስተዋል አይችሉም ነበር? የኤርትራ የነፃነት በአል ሲከበር ለልጃቸው ያን ሹራብ቎ ቢያለብሱ፣ "ወንድማማችነት" ምናምን የሚባል ምክንያት ሊሰጠው ይችላል። የኢትዮጵያ "የድል ቀን" ላይ ግን እንዴት ሆኖ?

"ሻእቢያ ወይም የኤርትራ ህዝብ 30 አመት ተዋግቶ ነፃነቱን አግኝቶአል። ይህንንም እኛ የማንሰጠው ወይም ልንከለክለው የማንችለው መብቱ ነው!" ብለህ የፖለቲካ ፕሮግራምህ ላይ መፃፍ ትችል ይሆናል። ወደህ ወይም ተገደህ፣ አለያም አማራጭ አጥተህ፣ የኤርትራን ነፃነት መቀበል ይቻል ይሆናል።

ኢህአዴግ የድል በአሉን ሲያከብር አብዛኛው አባልህን የሚያስከፋ መፈክር ይዞህ በድግሱ ቦታ መምጣት ግን ብሽሽቅ ካልሆነ ከቶ ሌላ ምን ሊባል ይችላል? አቦይ ስብሃት የኢትዮጵያ፣ የኤርትራና የእንግሊዝ ደም ያላቸው ሰው ናቸው ብለናል። ስነልቦናቸው ወዴት እንደሚያደላ እሳቸው ነው የሚያውቁት። ኤርትራዊ መሆናቸውን ለመግለፅ ይሆን ልጃቸውን ያን ሹራብ ያለበሱት? 'የታገልኩት ለኢትዮጵያ





ሳይሆን ለኤርትራ ነው!' ለማለት ነው? ሌሎች የኢህአዴግ አባላትን ለማብሸቅ ነው? የትኩሳታቸውን መጠን ለመለካት ነው? የተቃውሞ አቅማቸውን ለመፈተሽ ነው? የአጐብዳጅነት ደረጃቸውን ለመታዘብ ነው? ንቀት ነው? ከቶ ምንድነው?

አንድ ግልፅ ነገር አለ።

ስዩም መስፍን ወይም ተወልደ ወልደማርያም ያንን ሊያደርጉ አይችሉም። ስብሃት ነጋ ታዲያ እንዴት ይህን ሊፈፅሙ ቻሉ? ወይስ የወያኔ ፅንፈኛ ተቃዋሚዎች በአንድ ቃል እንዲሚደመድሙት፣ "ስብሃት ነጋ ሻእቢያ ነው" ብለን እንደምድም? አስገደ ገረላሴ የፃፈውን ሳናመነታ ልንቀበል እንችላለን? ወይስ አንዳንዶች እንደሚገምቱት ስብሃት ነጋ ኤርትራና ትግራይን አዋህዶ፣ "ትግራይ ትግርኚ" የተባለ ሃገር የመመሰረት ህልም ይኖራቸው ይሆን? ምንድን ነው ወይም ምን ነበር የአቦይ ስብሃት ግብና ልብ? አሁንስ ወዴት ነው የሚነዱን?

አቦይ ስብሃት ልጃቸውን Free Eritrea የሚል ነጭ ፅሁፍ ያለበትን ሰማያዊ ሹራብ አልብሰው የግንቦት 20 በአል ላይ ከተገኙበት እለት አንስቶ እንደተለመደው ልማዴ፣ "ስብሃት ነጋ" የሚል ፋይል ከፈትኩ።

ሰነድ አያያዜ ውስብስብ አይደለም።

ባለ 50 ገፅ ደብተር ገዛሁና "ስብሃት ነጋ" የሚል ቃል አሰፈርኩ። ቀጣዩ ተግባሬ እኒህን አንጋፋ ሰው ጠጋ ብሎ ማስተዋልና ማዳመጥ ነበር። ምሽቱ ላይም በዚያች ደብተር ላይ የሰማሁትን አሰፍራለሁ። አስተያየቴንም አክልበታለሁ።

አማረ አረጋዊ እንዳጫወተኝ ህወሃትን የመምራቱ ስልጣን ከስብሃት ወደ መለስ የተዘዋወረው በምርጫ አልነበረም። በአንድ የፖሊት ቢሮው መደበኛ ስብሰባ ላይ አቦይ ስብሃት እንዲህ የሚል አሳብ አቀረቡ፣

"ሁላችንም እንደምንታዘበው መለስ የስብሰባችን Brain እየሆነ ነው። በፈቃዴ ስልጣኔን ልለቅለት እፈልጋለሁ..."

ተሰብሳቢዎቹ ተቃውመው ነበር። ግን ተፈፀመ። ርግጥ ነው፣ ተቃውሞአቸው፣ "አቦይ ስብሃት አንተው ልትመራን ትችላለህ" አይነት እንጂ፣ መለስን ባለመቀበል አልነበረም። የሆነው ሆኖ መለስ ወንበሩን ያዘ። የአቦይ ስብሃት ግራና ቀኝ እጆች እንደ ሚካኤልና ገብርኤል ለመለስ የከለላ ክንፍ ሆነው እስከ ሚሊኒየሙ ማግስት ዘልቀዋል። ይህቺን እየጫጫርኩ ሳለም

የተለወጠ ነገር አልነበረም።

መለስና ስብሃት ኢትዮጵያ በተባለችው ሃገር ላይ የልባቸውን እየሰሩ በመዝለቅ ላይ ናቸው። መለስ ይህችን አባባል ይወዳታል።

"ምርጥ ኑሮ ማለት የልብህን ሰርተህ ማደር ማለት ነው" ይላል አዘውትሮ።

"የልብህን ሰርተህ ማደር" ማለት "ሌሎች የልባቸውን እንዲሰሩ መፍቀድ" ማለት ግን አይደለም። ይህ የመለስ አባባል ሌሎች የልባቸውን እንዲሰሩ ቀርቶ፣ የልባቸውን እንዲናገሩ እንኳ አይፈቅድም። መለስና ስብሃት 'የአንድ ስሙኒ ሁለት ገፅታ ናቸው' ካልን ሃገራችን ለገባችበት ችግር ቀዳሚ ተጠያቂዎቹ እነዚህ ሁለቱ ዜጎች መሆናቸውን ማመን እንችላለን።

ሁለቱ መሪዎች ተደጋግፈው ለመቆም ያስቻላቸው የጋራ ባህርያት አሏቸው። ይህ ምስጢር አይደለም። ፀሃይና አቧራ የጠጣ እውነት ነው። የሁለቱ ግለሰቦች የኢትዮጵያዊነት ስሜት ከልብ ሳይሆን ከምላስ ነው። ኢትዮጵያን በማፍቀር ሳይሆን በግልባጩ ይጠረጠራሉ። በመሆኑም የሚናገሩትና የሚፈፅሙት ተጣጥሞ ማየት ሳንችል ቀርተናል። ብዙውን ጊዜ የቃላት ጨዋታ ይጫወታሉ። ከአስር አመታት በፊት መለስ በሚዲያ ቀረበና እንዲህ አለን፣

"ደርግ ካመጣው ጉዳት ሁሉ በአስተሳሰብ ላይ ያመጣው ቆሻሻና በሽታ የከፋ ነው!"

አቦይ ስብሃትም ይህንኑ አባባል ቀደም ብለው ተናግረውት ነበር። የሁለቱ መሪዎቻችን አባባል ሜዳ ላይ የሚደፋ እጣቢ አይደለም። ደርግ የሰከረ ወይፈን ነበር። በዚህች በጋራ ቤታችን ላይ ያደረሰው ጉዳት መጠን አልነበረውም። ያንን የካደም የለም። ፈሪና የሃገር ፍቅር ስሜቱ የደነበሸ ትውልድ ፈጥሮአል። ለሃገር ምሰሶና ዋስትና ሊሆን ይችል የነበረውን አንድ ወርቃማ ትውልድ በጅምላ ያወደመ ስርአት ነው። በጦርነት ፖሊሲው የኢትዮጵያን አንድነት ማረጋገጥ አልቻለም። ስለዚህ መለስና ስብሃት ደርግን በተመቻቸው ቋንቋ ሁሉ ቢያወግዙ ይገባቸዋል።

ቀጣይ ጥያቄ ግን አለ።

ወያኔስ ለዚህች ሃገር ምንድነው ያስገኘው? ምንድነውስ





ያጣነው? ወያኔና ደርግ ሚዛን ላይ ሲቀመጡ ማነው በአስተሳሰብ ደረጃ ለከፋ ጉዳት የዳረገን? ሰዎችን ሳይሆን ትውልድን የሚገድል ያስተሳሰብ ቆሻሻውን ያራገፈብን በርግጥ ማነው? ያለመተማመኑን በሽታ ይበልጥ ያዛመተው ወያኔ ይሆን ደርግ?

አቦይ ስብሃት እንዲህ ይሉናል፣

"ደርግን ስንገለብጠው አንድ ዩኒቨርሲቲ ብቻ ነበር። አሁን ሃምሳ ዩኒቨርሲቲ ተከፍቶአል"

ይህን ለማሳመንም ዩኒቨርሲቲዎችን ብቻ ሳይሆን የዘረጉትን የኤሌክትሪክ መስመር፣ መንገድና የውሃ ቧንቧ ባማሩ ሰንጠረዦች ያቀርቡልናል። ይህንንም ከደርግ ጋር እንድናወዳድርላቸው ይጠይቁናል። ርግጥ ነው የሚነግሩንን ሁሉ አድርገውት ሊሆን ይችላል።

ግን ጣራችን የታለ?

ይህችን ሃገር እንደ ሃገር አንድ አድርጎ፣ በሃገር ፍቅር ሊያቆማት የሚችለው ምሰሶ የታለ? ጣራው የፈረሰበት ህዝብ፣ ምሰሶው የተገነደሰበት ዜጋ ምን ተስፋ አይቶ ልጆች ወልዶ ሊያሳድግ ይችላል? መንገድና ህንፃ ግንባታው ቀርቶብን የአንድነቱ ሃውልት በቅድሚያ ቢታነፅ ይበጀን ነበር። አንድ ሃገር ጠንካራ የአንድነት መሰረት ከሌለው እንደ ሃገር ሃብቱን ጠብቆ ለማቆየት ምን ዋስትና አለው? የተከዜን ወይም የቆቃን ግድብ በህይወት ይዞ ለመቆየት አንድነት ያስፈልገናል። የተከፋፈለ ቤት ሊቆም አይችልም። የሃገር ፍቅርና አንድነት ከሌለ ያ ሃገር ግንባታዎቹን ጠብቆ ለማቆየት የሚቻለው አይሆንም። የሶማሊያ ሪፓብሊክ በጣም ጠንካራ መንግስት ነበር። ዛሬ ፍርስራሹ እንኳ የለም። እነዚያ እውቅ የነበሩት የሶማሊያ ዩኒቨርሲቲዎች ዛሬ የታሉ? የሶማሊያ የዘመናት የታሪክ ቅርሶችና የታሪክ ሰነዶች የት ገቡ? ሶማሊያ ብዙ ህንፃዎች ነበሯት። ዛሬ የሉም። ፍርስራሻቸው የሜዳ ውሾች በረት ሆኖአል። የሞቃዲሾ መንገዶች ወድመዋል። የሶማሊያ ከፍተኛ ዩኒቨርሲቲዎች፣ የምርምር ተቋማቱን ምን በላቸው? ምን ሩቅ አስኬደን? የኢትዮጵያ አየር ሃይል ትናንት የት ነበር? ዛሬ የት ይገኛል?

አቦይ ስብሃት፣ በ1990 ለእፎይታ መፅሄት ቃለመጠይቅ ሲሰጡኝ እንዲህ አሉኝ፣

"ኢትዮጵያ ከሰሃራ በረሃ በታች ካሉ ሃገሮች

የመጨረሻዋ ደሃ ሃገር ናት። የኢትዮጵያ ህዝብ ለምን በዚህ ደረጃ ላይ ተገኘ? ኢትዮጵያዊ አመራር ስላላገኘ ለዚህ ውድቀት ተዳርጐአል። ይሄ ብሄርተኛ የነበረ ህዝብ አሁን ከሞራል አንፃር ስንለካው ስደትን እንደ ክብር የሚቆጥር ህዝብ ሆኖአል። ታላላቅ ከሚባሉ የኢትዮጵያ ሰዎች ጋር ስለ ኑሮ ወግ ሲነሳ፣ 'መድሃኔአለም ክብሩ ይስፋ! አምስቱም ልጆቼ አሜሪካ ናቸው' የሚል አነጋገር ትሰማለህ። ይሄን የሚለው እንግዲህ ደህና ሰው ኩሩ የምትለው የነበረ ነው። ይህን ሁኔታ የፈጠሩት ያለፉት ስርአቶች ናቸው። የወደቀ የደኸየ ህዝብ ነው የተዉልን..."

አቦይ ስብሃት ይህን ለኔ ከተናገሩ፣ እኔም ይህን ለኢትዮጵያ ህዝብ ካሰራጨሁ 12 አመታት አልፈዋል። ያ የወደቀና የደኸየ ህዝብ ካለፉት ረጅም አመታት በሁዋላ ከአቦይ ስብሃት አመራር ምን አገኘ? ብዙ ንግግር አያስፈልግም። የአንድነት መሰረቱን ከማጣቱ ላይ የውሸት ባህል ተመረቀለት። ደርግ ውሸታም ነበር። የወያኔን ያህል ዋሾ ግን አያውቅም። አቦይ ስብሃት እንደሚሉት የደርግ ችግር የኢትዮጵያዊነት ችግር አልነበረም። የደርግ ችግር አለማወቅና እብሪት ነበር። እብሪቱና አለማወቁም ጐርፍ ሆኖ ይዞት ገደል ገብቶአል።

አቦይ ስብሃት እና መለስ ኢኮኖሚክስ አጥንተዋል። በቅርብ እንደማውቀውም ያነበቡ ብቻ ሳይሆኑ፣ በማንበብ ላይ ያሉም ናቸው። ችግራቸው እውቀት ሳይሆን የኢትዮጵያዊነት የሃገር ፍቅር ስሜት አለመኖር መሆኑን ተከራክሮ ማሳመን ይቻላል። ይህ ተራ የቅስቀሳ ትረካ አይደለም። መሪዎቻችን ለመዋሸት የሚገደዱት የሃገር ፍቅር ስሜት ስሌላቸው ነው። በአናቱ የህዝቡን የተቃጠለ የሃገር ፍቅር ስሜት አጥብቀው ይፈሩታል። ስለዚህ ሊያታልሉት ይሞክራሉ። ስስ ጎኑን እየነካኩ ሊደልሉት ይጥራሉ። መሪዎች ከሚዋሹ ደግሞ አምባገነን ቢሆኑ ይመረጣል። አፄ ቴዎድሮስ አምባገነን ነበሩ። ውሸት ግን አያውቁም። አቦይ ስብሃት የሚያሽከረክሩት ኢህአዴግ አስፀያፊ ባህሪ መረን የለቀቀ ውሸቱ ነው። "ነፃ ምርጫ እናደርጋለን" ብለው ለምን ይዋሻሉ? ህዝቡ ስለዴሞክራሲ ያለውን አስተሳሰብና እምነቱን ለምን ያበላሹበታል?

አቦይ ስብሃትና መለስ ከቶኒ ብሌየር ጋር ራት ሲበሉ፣ "ነፃ ምርጫ እናሳይሃለን!" ብለው በሞቅታ ቃል ገብተውለት ነበር። ቶኒ ብሌየርም፣ "ከፍተኛ የተቃውሞ ምንጭ የሆነውን





አዲስ አበባን ከያዛችሁ ሌላው ስንዴ ነው" ሲል መከራቸው።

"አዲስ አበባን በኮንደሚነየም ቤት ግንባታ እንይዘዋለን" ብለው የቀን ህልም አለሙ። ህልማቸው የማለዳ ጤዛ ሲሆንባቸው "እፍርታም" ሆኑ። የጨዋታውን ህግ አፈረሱና ጠመንጃቸውን አንስተው ህፃናትንና ሴቶችን ሳይቀር በጥይት እንደ ንፍሮ ቀቀሏቸው።

ወያኔ ነፃ ምርጫ ፈቅዶ ከሚያጭበረብር፣

"የለም! ምርጫ አያስፈልግም! እኔ እመራችሁዋለሁ" ቢለን እንመርጣለን። ህዝብ በምርጫ ስርአት ላይ ተስፋ እንዲቆርጥ ማድረግ ግን ከወንጀሎች ሁሉ የከፋ ወንጀል ነው። ስለዚህ አቦይ ስብሃት ደርግን የአስተሳሰብ ቆሻሻና በሽታ በማምጣቱ የመክሰስ የሞራል መሰረት የላቸውም።

መለስ እንዲህ ሲል ሰምቼዋለሁ፣

"በአሜሪካ በሰፊ ህዝባዊ ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ ዴሞክራሲ አለ ለማለት አስቸጋሪ ነው። በርግጥ በአሜሪካ የዴሞክራሲ ጫፎች አሉ ማለት ግን እንችላለን። በኔ አመለካከት ምርጥ ዴሞክራሲ ማለት የህዝብ ተሳትፎ ነው"

መለስ ይህን ለመናገር ከቶ ምን የሞራል ብቃት አለው? ቢራ ላይ ቢያወራው ችግር የለውም። በሚዲያ ቀርቦ ለህዝብ እንዲያ ሲል ግን ይሰቀጥጣል። መለስ ከላይ ያሉትን አረፍተነገሮች ከሚናገር ዝም ቢል ይሻለው ነበር። ዝም ማለት ካልቻለ ደግሞ እውነቱን ቢነግረን እናከብረው ነበር። የልቡን እንዲህ ሲል መግለፅ በተሻለው፣

"ወገኖቼ ሆይ! ይህችን ስልጣን ያገኘሁት በጠመንጃ ነው። ስለዚህ በምርጫ ካርድ ስልጣኑን ይለቃል ብላችሁ አትድከሙ። በጠመንጃ ሃይል መንጠቅ ከቻላችሁ መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ። እስካልቻላችሁ ድረስ ግን ድዳችሁን እየደረመስኩ፣ በድዴም ቢሆን እገዛችሁዋለሁ!"

እውነቱን መግለፅ ያስከብራል።

መሪ እንደ ሳሙና ሙልጭልጭ ከሆነ ያ ዘመን የመከራ ዘመን መሆኑን ማስተዋል ይቻላል። ግለሰብ መንግስትን ቢያታልል አይገርመንም። መንግስት ግለሰቦችን ማታለል ከጀመረ ግን 'ሃገር የለም' ማለት ይሆናል። የስብሃት ነጋ ፍሬ የሆነው የዘመናችን የአገዛዝ ስርአት ያላለቀ የባቡር መንገድ መስሎ ይሰማኛል። ባቡሩ እየተጓዘ ነው። የተቋረጠው ሃዲድ

ላይ ሲደርስ ምን ይሆን የሚገጥመው?

ከእለታት አንድ ቀን ታዲያ "ስብሃት ነጋ" የሚል ርእስ የሰጡሁትን ደብተር ስገልጠው እንዲህ የሚል ተፅፎ አገኘሁ፣

*(የፊታውራሪ ነጋ 4ኛ ልጅ፣ ወልደስላሴ ነጋ በ1934 አድዋ ከተማ ተወለደ። ስብሃት ወደ ትግል ከመውጣቱ በፊት፣ በ1964 ከአዲሳባ ዩኒቬርሲቲ በኢኮኖሚክስ ተመርቆአል። አድዋ ላይ የንግስት ሳባ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዳይሬክተር ሆኖም ሰርቶአል። "የህወሃት የአስተሳሰብ መሃንዲስ" በሚል የተቀፅላ ስም የሚገልፁት በርካታ ብእረኞችም አሉ። በርግጥም ስብሃት ነጋ መለስ ዜናዊን ወደ ስልጣን በማምጣቱ ረገድ መሪ ሚና ነበረው። ሚዲያዎች ስብሃትን አስመልክተው በርካታ ፅሁፎችን አስነብበውናል። እንደ ሚካኤል ስሁል "King Maker" ይሉታል። መለስ ከስልጣኑ እንዳይነካም አቢይ አስተዋፅኦ እያደረገ ዘልቆአል። የህወሃት ተመራጭ መሪ የነበረውን አረጋዊ በርሄን በማስወገዱ ረገድም ከፍተኛ ድርሻ ነበረው። በ1993 የህወሃት ክፍፍል ወቅት መለስ ዜናዊ ስልጣኑን ይዞ እንዲቀጥል ስብሃት ነጋ አደገኛ የተባሉትን ቋጥኞች ሁሉ ፈነቃቅሎአል። ተሳክቶለታልም።*

*ስብሃትና መለስ በታሪክ ፊት እንደ ቀዳሚዎቹ አምባገነኖች መጠየቃቸው አይቀሬ ነው። የሆነው ሆነና እነዚህ ሰዎች እንደ ሻህ ሬዛ ፖህላቪ፣ እንደ ፌርዴናንድ ማርቆስ፣ ሳሙኤል ዶ፣ ዚያድባሬ፣ ቻውቼስኩና ቦካሳ በክፉ መታወስን ለምን መረጡ? ይህን ጥያቄ ደግሜ ደጋግሜ ባነሳውም ምላሽ አላገኘሁለትም...)*



# - 13 -

# ተስፉ ሲሞት

አብዮት አብቦ - ጎምርቶ አሽቶ፣
የሚዘነጥፈው - የሚቆርጠው ጠፍቶ፣
ጅቡ በላው አሉ - ሌት ከማሳው ገብቶ፣

(ግጥም - ሂሉ መሃመድ)

* * *

ጭንቅም በሳቅ ያልፋል – ፍቅርም በወረት፣
ሃዘንም ይረሳል - በጊዜ ብዛት፣
ስቃይም ይቻላል – በተስፋ ፍኖት፣
እንዴት ይሆኑታል!? - ተስፋ ግን ሲሞት?

(ግጥም – በቀለ መንገሻ)

ከልቤ በፈለቀ ስሜት እንዲህ ስል ጠየቅሁት፣

"ስማ እስኪ አበበ! አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ? ከኦነግ ተጣላህና ከጄኔራል ከማል ጋር ለብቻችሁ ተገነጠላችሁ። በመቀጠል ከጄኔራሉም ጋር አልተግባባችሁም። አሁን ብቻህን አድፍጠሃል! ለዚች መከራዋ የበዛ ሃገር የፖለቲካ ችግር መፍትሄው ምንድነው እያልክ ይሆን? ለምን ይሆን የትብብር ቁጣ መቆጣት ያልተቻለው?"

እየሳቀ እንዲህ መለሰ፣

"የሸዋ ሰው ወደ ስልጣን ካልመጣ መረጋጋት አይኖርም። ሸዋ ስልህ የሸዋ ኦሮሞና የሸዋ አማራውን ማለቴ አይደለም። ሸዋ ማለት የሁሉም ዘር ቅልቅል ማለት ነው።

በተቀረ እንደምታየው ወለጋ፣ አድዋ፣ አርሲ፣ መንዜ፣ ጎንደሬ፣ ተምቤን ሆኖአል የዘመናችን ፖለቲካ። ሃገሪቱን ለማፈራረስ የምንሰራ እስክንመስል ድረስ ውጊያችን ርስበርስ ሆኖአል..."

ኮሎኔል አበበ ገረሱ ስለ ሸዋ ያነሳው እየቀለደ እንደሆነ ተስፋ አደረግሁ። አቤ ቀልዱን ካልሆነ፣ "ሸዋ - ለኢትዮጵያ" የተባለ አዲስ ፓርቲ ያቋቁም ይሆናል። ከቀልዳችን ባሻገር ግን ኮሎኔሉ በጥሞና ሊያዳምጡት የሚገባ ሰው ሆኖ አግንቼዋለሁ።

* * *

አዲስ አበባ ጦርሃይሎች ሆስፒታል አጠገብ፣ "መኮንኖች ክበብ" ተብሎ የሚጠራ አንድ ግዙፍ የመዝናኛ ማእከል አለ። ለአራት አመታት ያህል ምሽት ላይ ወደዚያ ክበብ ብቅ እያልኩ በከረንቦላ ጠረጴዛው ዙሪያ ማንዣበቡን እንደ ልማድ ይዤው ነበር። ጥቂት የማይባሉ የኢህአዴግ ወታደራዊና ሲቪል ባለስልጣናት በከረንቦላው ዙሪያ ይሰባሰባሉ።

ስብሃት ነጋ ዋናው ናቸው። ጄኔራል ሳሞራ የኑስም የከረንቦላ ቀበኛ ነው። የስዬ ታናሽ ወንድም አሰፋ አብርሃ፣ የከረንቦላ ኳሶቹን እያንኳኳ፣ "ዶጋ ተምቤን!" እያለ ሲፎክር እስካሁን ድምፁ ጆሮዬ ላይ አለ። 'ታንኪ' በሚል ቅፅል ስም የሚታወቅ የአዴት (ትግራይ) ልጅም ከከረንቦላው ዙሪያ አይጠፋም ነበር። አሰፋ አብርሃ 'ታንኪ'ን እየተረበ የከረንቦላ ኳሶችን ያንኳኳል፣

"ታንኪ! አንተ ወደ ትግል ስትወጣ አዴት አለቀሰች የሚባለው እውነት ነው? የአዴት አንድ ምሁር አንተ ነበርክ፤ አይደለም እንዴ? ስንተኛ ክፍል ደርሰህ ነበር? 6ኛ?"

ከዚያም ኳሷን ወርውሮ "ዶጋ ተምቤን!" ሲል ይጮሃል።

*('ዶጋ' ምን ማለት እንደሆነ አላውቅም። 'ደጋ' ማለት ይሆን? 'ተምቤን' ግን አውራጃ ነው። የስዬ ቤተሰብ ሁሉ የሚመካበት የትውልድ ቦታ። የመመካታቸው መነሻ አፄ ዮሃንስና ራስ አሉላን ጨምሮ በርካታ ስመጥር የትግራይ ሰዎች ከዚህ ከተምቤን አውራጃ የበቀሉ ናቸው ብለው ስለሚያምኑ ነው። 'እኛም ንግስናው ይመለከተናል' አይነት ዜማና ቅላፄ ያለውም ይመስላል።)*





በዚያ በባርነቱ ዘመን "እኛ አንበሶች!" መኮንኖች ክበብ እያመሸን ውስኪና ቢራ በነፃ እንጠጣለን። እኔ ከፍዬ አላውቅም። ልክፍል ሂሳብ ስጠይቅ፣ "ተከፍሏል" ይሉኛል። ማን እንደከፈለልኝ አላውቅም። ማወቅም አያስፈልግም። ገንዘቡ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ የተባለችው ሃገር ራሷ በመዳፋችን ላይ ናት። በመሆኑም ማንም ከፈለ ማን ማመስገን አያስፈልግም። ገንዘቡ የሚያልቅ ስላልሆነ አያሳስብም።

አንጋፎቻችን ከረንቦላ በሚጫወቱበት ጊዜ እኛ ደቂቃን ለአንዱ ደጋፊ መሆኑን ለምደነው ነበር። ጠረጴዛውን ከብበን እናሟሙቃለን። እኔ ብዙውን ጊዜ የአቦይ ስብሃት ደጋፊ ነበርኩ። ደብል ቮድካ በጨረሽኩ ቁጥር፣

'አቦይ ስብሃት! እንዴት ነው ነገሩ? አንኳኩት እንጂ!" ብዬ ሳበቃ ወደ አስተናጋጇ ዘወር በማለት እንዲህ እላለሁ፣

"ደብል ጨምሪ!"

እኔ ከረንቦላ ተጫውቼ አላውቅም።

ደጋፊ ብቻ ነበርኩ። እንግዲህ አንዳንዶች ሊቨርፑል፣ አርሴናል እንደሚሉት መሆኑ ነው። እኛ ወያኔዎችም ዝሆኖች ከረንቦላ ሲጫወቱ፣ "አቦይ ስብሃት"፣ "አሰፋ አብርሃ"፣ "ሳሞራ"፣ "ሃይሌ ጥላሁን!' እያልን እንደ አባኮዳ እንንጫጫለን። በዚያ በደጉ ዘመን፣ በዚያ በባርነቱ ዘመን...

የከረንቦላ ላይ ምሽቶች አያሌ አይረሴ ገጠመኞችን ትተውልኝ አልፈዋል። ከነዚህ አይረሴ ገጠመኞች አንዱ በኮሎኔል አበበ እና በአቦይ ስብሃት መካከል የተፈጠረው ሁኔታ እና መዘዙ ነው።

እንደተለመደው ጥግ ላይ ተቀምጬ የከረንቦላ ተጋጣሚዎችን እየተመለከትሁ ነበር። በተሰላቸ ሁኔታ ላይ ሆኜ ስቶልቺኒያ የተባለውን ቮድካ ተያይዤው ነበር። ጋባዣችን ነባር የህወሃት አባል መሆኑ የሚነገርለት የአዲግራት ልጅ፣ ኮሎኔል ጎልያድ ነበር።

እንደገባ እንዲህ ሲል ነበር የጋበዘን፣

"ለኔ ሺቫዝ ዊስኪ! እናንተ የፈለጋችሁትን ጠጡ"

የሚደንቀው ነገር እንደ አባዱላ አይነቱ ጄኔራል ሳይቀር በኮሎኔሉ መጋበዛቸው ነው።

'ማእረጉ ኮሎኔል የሆነ አንድ የአስተዳደር ሃላፊ የሃገሪቱ ጄኔራሎች ፊት፣ እንዴት እንዲያ ሊናገር ደፈረ?' ብላችሁ

እንደማትጠይቁ ተስፋ አደርጋለሁ።

ጎልያድ ህወሃት ነው።

ጎልያድ ድምፁን ከፍ አድርጎ፣

"ለኔ ሺቫዝ! እናንተም የፈለጋችሁትን!" ብሎ ሲጋብዝ የደብረዘይት ልጅ የሆነው ሚኒስትር ግርማ ብሩም ሰምቶአል። እኔ ጋዜጠኛውም እዚያው ነበርኩ።

የሆነው ሆኖ በዚያን እለት በጎልያድ ግብዣ ቮድካ እየገለበጥሁ የከረንቦላ ጨዋታውን እየተመለከትሁ ነበር። አቦይ ስብሃትና አሰፋ አብርሃ ከረንቦላ እየተጫወቱ ነው። ጎልያድ ተራውን ይጠብቃል። ግርማ ብሩ ተመልካች ነው። ሜጀር ጄኔራል ባጫ ደበሌ ገባ ወጣ ይላል። ጫት ሲቅም መዋሉ ያስታውቅበታል። አይኖቹ እንደ ባውዛ ፈጠው ሊወድቁ በመድረሳቸው ጡት መያዣ ወይም አይን መያዣ እንዲሰጣቸው የሚማፀኑ ይመስላሉ። ባዶ ጉንጩን እያላመጠ ምላሱ እንደ ቆሰለ እባብ ገባ ወጣ ይላል። "አቶ" ይሁን "ጄኔራል" ገና ያልለየለት አባዱላ ገመዳ ከግርማ ብሩ አጠገብ የመንግስት ጎተራ መስሎ ቆሞአል። "እንደ ጀርመን ዘመናዊ መኪኖች የአባዱላን ፊትና ሁዋላ መለየት አይቻልም" የሚሉ አሉ። ይሄ ውሸት ነው። የአባዱላን ስም ለማጥፋት ነው። ቀይ ዋንዛ የመሰሉ አይኖቹን በማየት የአባዱላን ፊት መለየት ይቻላል። የአባዱላ አይኖች ምንጊዜም ለምን ደም እንደሚመስሉ ግን ሃኪም ይወቅ! ከልብና ከአንጎሉ ውስጥ የዛር ድቤ አዶከበሬውን የሚያስጨፍርበት የቢሾፍቱ ባለ ውቃቢ መስሎ ይሰማኛል። ኮሎኔል አበበ ገረሱ አጠገቤ ቆሞ ለአሰፋ አብርሃ የሞቀ ድጋፍ እየሰጠ ነበር። የስብሃት ነጋ ልጆች የፕላስቲክ አለንጋ ይዘው ከወዲያ ወዲህ እየተሯሯጡ ይጫወታሉ። የአዳል በግ የሚመስል አንድ ጋዜጠኛ ጥግ ላይ ቆሞ ይህን ሁሉ በአይኖቹ ፎቶግራፍ ያነሳል። ጋዜጠኛው ይህን የሚያደርገው ከእለታት አንድ ቀን ይህን እፅፈዋለሁ ብሎ አልነበረም።

በመካከሉ ያልተጠበቀ አደጋ ተከሰተ።

አጠገቤ ቆሞ የነበረው ኮሎኔል ለአሰፋ አብርሃ ድጋፉን እየሰጠ ቆየ። በመቀጠል አሰፋን ከመደገፍ አልፎ አቦይ ስብሃትን እንዲህ ሲል ተረባቸው፣

"አሰፋ በርታ! የአቦይ ስብሃት ስኮር ደክሞአል!"

አቦይ ስብሃት በድንገት ሊወረውሩ የያዙትን የከረንቦላ





ኳስ ጠረጴዛው ላይ ጣሉትና ቀና አሉ። ወደ ኮሎኔሉ አፈጠጡ። ሲንጫጫ የነበረው ሁሉ ትንፋሹን ውጦ በፀጥታ ተዋጠ። አቦይ ስብሃት የከረንቦላ ኳሱን በርጋታ አነሱ። አንድ ርምጃ ወደ ኮሎኔሉ ተጠጉ። የከረንቦላ አሎሎውን በሚንቀጠቀጥ እጃቸው ጨብጠውታል። ኮሎኔሉ ፊቱ የሸሮ ቅል መስሎ አቦይ ስብሃት ላይ በድንጋጤ አፍጥጦ ነበር።

አሰፋ አብርሃ እና ጎልያድ ድንገት ባንነው ፈጣን ርምጃ ወሰዱ። ተወርውረው መሃል በመግባት አቦይ ስብሃትን ያዙአቸው። አሎሎውንም ከእጃቸው ላይ ፈልቅቀው ነጠቋቸው። እኔና ግርማ ብሩ ኮሎኔሉን ወደ ደጅ ይዘነው ወጣን። ከአቦይ ስብሃት የቁጣ ገፅታ ገለል እንዲሆን አደረግነው። እኔና ግርማ ብሩ ኮሎኔሉን ወደ በረንዳው ይዘነው ስንወጣ የኮሎኔሉ ፊት ከሽሮ ቅል ወደ ድልህ ቅል ተለውጦ ነበር።

ግርማ ብሩ ኮሎኔሉን እንዲህ ሲል ገሰፀው፣

"እድሜያቸው ላይ እንዴት እንደዚያ ትቀልዳለህ?"

ኮሎኔሉ በተቆራረጠ ድምፅ ሊያስተባብል ሞከረ፣

"እሳቸው እየተሸነፉ ስለነበር ነው እንደዚያ ያልኩት። እድሜያቸውን አላሰብኩም።"

ግርማ ብሩ ወደ ውስጥ ሲመለስ እኔና ኮሎኔሉ ቀረን፣

"በል ወደ ቤትህ ሂድ። እግዚአብሄር አትርፎሃል" አልኩት። በዚያ አሎሎ መትተውት ቢሆን እዚያው እፊታችን አንጎሉ ይበታተን እንደነበር በማሰብ መላ ሰውነቴን እንደ ኤሌክትሪክ አጨማዶ ነዘረኝ።

ኮሎኔሉ ከመሄዱ በፊት እዚያው በረንዳው ላይ ቁጭ ብሎ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። ግራ ገብቶኝ አጠገቡ ቁጭ አልኩ። እንዲህ ያሉ የእልህና የቁጣ እንባዎችን አውቃቸዋለሁ። ስለዚህ ኮሎኔሉ ሲያለቅስ የወያኔ ሰዎች እንዳያዩት በጣም ሰግቼ ነበር። ኮሎኔሉ ጭንቅላቱን ጉልበቶቹ መሃል ቀብሮ ከሆዱ ህቅ! ብሎ ነበር የሚያለቅሰው። እስኪወጣለት ጠበቅሁትና ተቆጥቼው ወደ ቤቱ እንዲሄድ ሸኘሁት። ንጭ ኮብራውን አስነስቶ በእርጋታ ግቢውን ለቆ ወጣ። ያቺ ቀን ለኔ የመጨረሻ ቂኔ ነበረች። ወደ መኮንኖች ክበብ መሄዱን አቆምኩ። ኮሎኔል አበበንም ከዚያ ወዲያ አይቼው አላውቅም ነበር።

ከስድስት አመታት በሁዋላ ፕሪቶሪያ ሳለሁ ስለ ኮሎኔሉ ወሬ ሰማሁ። ወሬውን ያመጣልኝ፣ homofafrica.de የተባለው

ድረገፅ ነበር። ከአቦይ ስብሃት የከረንቦላ አሎሎ የተረፈው ኮሎኔል እና ጄኔራል ከማል ገልቹ ከ250 በላይ የታጠቁ ወታደሮችን ይዘው ወደ ኤርትራ የመግባታቸው ዜና የድፍን አለምን ትኩረት ለአንድ አፍታ የሳበ ነበር።

ድረገፁ ላይ የተለጠፈውን ቪዲዮ ደግሜ ደጋግሜ አየሁት። በዚያን እለት መኮንኖች ክበብ በረንዳው ላይ ተቀምጦ ስቅስቅ ብሎ ያለቀሰውን ኮሎኔል እያየሁት ነበር። በዝምተኛ ፈገግታና ርካታ እንደተዋጠ የኦሮሞ ወታደሮችን እየመራ የኤርትራን ተራሮች እያቋረጠ ነበር። መዘዙም ከዚያ የከፋ ሆነ። ከጄኔራል ከማል እና ከኮሎኔል አበበ የአመፅ ኩብለላ በሁዋላ ወያኔ 23 ሺህ ኦሮሞዎችን ከሰራዊቱ አባረረ።

* * *

አስመራ በሄድኩበት ጊዜ ታዲያ ኮሎኔሉን አፈላልጌ አገኘሁት። በተደጋጋሚ እየተገናኘንም ረጅም ቆይታ አደረግን። በተገናኘን ቁጥርም በወሬ ወሬ በርካታ ርእሰ ጉዳዮችን ማንሳታችን አልቀረም። ስለ ትውልድ መንደሩ፣ ስለ ወያኔ፣ ስላለፈውና ስለ መጪው ስለ ወቅታዊው ሁኔታ ጭምር በጥቅሉና በጨረፍታ ተጨዋውተናል...

አንድ ቀን እንዲህ ሲል አወጋኝ፣

“የመከላከያ ሰራዊት አባል ሳለሁ ድህነት ይሰማኝ ነበር። በርግጥ ከባዶ ተነስቼ ጥሩ ኑሮ ላይ ደርሼ ነበር። አግብቼ ወልጃለሁ። ቤት ሰርቻለሁ። ሞጆ ላይ በሬ የማደለብ ቢዝነስ ጭምር መስራት ጀምሬ ነበር። መርካት ግን አልቻልኩም። ወያኔዎችና ዘመዶቻቸው ያለ ድካም በሚሊዮናት ሲዘርፉ ስመለከት ድህነት ተሰማኝ። የሚዘረፈው አብዛኛው የኦሮሚያ ሃብት ነው። እና የአባቴ ቤት ሲዘረፍ እኔ ከሌሎች ዘራፊዎች በታች ነበር የማገኘው። ህሊናዬ ይህን ሊቀበለው አልቻለም።

“...ጅማ የትውልድ ሃገሬ ነው።

“...እንደምታውቀው ጅማ ጫካው ሁሉ ቡና ነው። ማልማት ለፈለገ 200 ሄክታር የቡና ጫካ ‘ምሪት’ ተብሎ ይሰጠዋል። አንድ ሚሊዮን ብር ባንክ ላይ አሳይ ትባላለህ። ከሰው ተበድረህ ያንን ገንዘብ ታሳያለህ። ከሰፊው የጅማ የቡና ጫካ ተቆንጥሮ ይሰጥህና ያንን እየተንከባከብክ ታለማለህ። ከጅማ እስከ ቦንጋ 140 ኪሎ ሜትር ግራና ቀኝ በሙሉ የቡና





ጫካ ነው። ጫካው ውስጥ ቀኑን ሙሉ ብትንዝ ሌባ የሚባል የለም። ሰው ያልደረሰበት ወፍ ዘራሽ ቡና ስላለ የሰው የሆነውን ቡና የሚነካ የለም። ይሄ ሃብት ኢትዮጵያ በእግሯ ቆማ እንድትሄድ ያደረገ ሃብት ነው። እኔ የዚህ አካባቢ ተወላጅ ነኝ። ይህ ሃብት ለጠቅላላው ለሃገሪቱ ህዝብ ጥቅም ላይ ቢውል ችግር አልነበረውም። የወያኔ ሰዎች መጥተው እንደ አንበጣ ሰፈሩበት። እነሱ ሚሊዮናት ሲዝቁ ስመለከት እኔ ድህነት ተሰማኝ።

“...ኢሊባቡር ሂድ!

“...ጫካውን መለካት አይቻልም። ጐሬ እና ሞቻ ከጫፍ እስከ ጫፍ ቡና ነው። ይህ ቡና ትግሬ ለሆኑ ሰዎች ብቻ መጠቀሚያ እየሆነ ነው። ኢትዮጵያ እንደ ሃገር ከዚህ የቡና ጫካ የምታገኘው ጥቅም ከበርሜል ላይ በስኒ እንደ መቅዳት ብቻ ይቆጠራል። ይህን በማወቄ በኔ አእምሮ ውስጥ ስቃይ ተፈጠረ። መዝረፍ ከሆነ እኩል መዝረፍ እንኳ ይሻላል። ለሚዘርፉት አጨብጫቢ መሆን ግን ቁጭት የሚፈጥር ሆነብኝ። በገዛ ሃገሬ፣ የትውልድ መንደሬ ላይ? እስከ መቼ ይህን እያየሁ እቀጥላለሁ? ይሄን ስነግርህ፣ ‘ከወያኔ የተጣላኸው ከግል ጥቅምህ ጋር በተያያዘ ነው’ ምናምን ልትለኝ ትችላለህ። አይደለም። ሰው ነኝ። እንደ ሰው በቅድሚያ ውስጤ ያደረውን ስሜት ነው የምነግርህ። እንደፈለግህ ተርጉመው እውነቱን ነው የምነግርህ...

“...ባጭሩ! ሩጫው ዝርፊያ ብቻ ነበር።

“...መቆሚያ የሌለው ዝርፊያ። ለሃገርህ መስራት ሌላ ጉዳይ ነው። ለሃገር መስራት ከሌለ ደግሞ ቢያንስ ከዝርፊያው ድርሻህን ማግኘት አለብህ። ብቻቸውን ሲዘርፉ ግን ሊሰማህ የሚችለው ድህነትና ቁጭት ነው። ቁጭት የሚለው ሊያከራክር ይችላል። በትክክል ግን ቁጭት ተሰምቶኛል። ዝርፊያው ቆሞ ገቢው ሁሉ ለሃገሪቱ እንዲሆን መመኘቴ አልቀረም። ምኞትህ እንደማይፈፀም ስታውቅ ግን አብረህ ለመዝረፍ ትሞክራለህ።

“...ከተወለድክበት መሬት ላይ እነሱ በበርሜል ወስደው፣ ላንተ በጭልፋ ሲሰጡህ ግን ልትቋቋመው ትቸገራለህ። ‘ጭልፋ’ የምልህ ትንሽ ገንዘብ ነው ብለህ እንዳትገምት። ብዙ ነው። ብዙ ስልህ በመቶ ሺህዎች ሊደርስ ይችላል። ካንተ በታች ያለው ሰው በሚሊዮናት ወስዶ ላንተ አንድ አስረኛውን ሲሰጥህ ማመፅ ተፈጥሮአዊ ነው። በልብህ የሚጠነሰሰው አመፅ ለግል ጥቅም ብቻ ላይሆን ይችላል። ለሃገር ወደ መቆርቆር ሊለወጥም

ይችላል። የኔ ቁጣ በጥቅሉ፣ 'ይህቺ ሃገር መዘረፍ የለባትም። ሃገራዊ አስተዳደርና ስርአት ሊኖረን ይገባል' ወደሚል ደረጃ አድጎአል ብዬ አስባለሁ። ሰራዊት አደራጅተን የኮበለልነው በዚህ መንፈስ ነው። እየዘረፍክና እያስዘረፍክ ከወያኔ ጋር መቆየት በጣም ቀላል ተግባር ነበር። እነ ባጫና አባዱላ ያንን እያደረጉ ነው። ያንን ባደርግ እስካሁን ባለሚሊዮን ጄኔራል መሆን እችል ነበር። ባለመሆኑ አሁን ደስተኛ ነኝ።

"...ስለ ትውልድ መንደሬ ላጫውትህ።

"...ጅማ በአንድ ብር ጠግበህ የምታድርበት ሃገር ነው። ሽልጦና ድንች በልተህ በስሙኒ ጠጅ ጠጥተህ ቤትህ ትገባለህ። ሃገራችን በወራሪዎች መዳፍ ስር የወደቀቸች ሆኖ ይሰማኛል። ወደ ቴፒ፣ ወደ ሚዛን፣ ሄደህ ታውቃለህ? ሳምንቱን ሙሉ በመኪና ስትዘዋወር ሽፍታ የሚባል አይገጥምህም። የኦሮሚያ ምድር ከደቡብ ህዝቦች ክልል ጋር ይጋጠማል። የወያኔ ሰዎችና አዲስ በቀል ነጋዴዎቻቸው ይህን ሁሉ መሬት ተቆጣጥረው እየዘረፉት ነው። ስብሃት ነጋ 'ኩባንያችን ቢሊዬኔር ሆኖአል!' ሲል ተናገረ። መላ ሃገሪቱን በብቸኛነት ተቆጣጥረው እየዘረፉ፣ ቢሊዬነር መሆን ይነሳቸው እንዴ?

"...አሳባቸው ያው ዘርፎ ለመሸሽ ነው። ማምለጥ ግን አይችሉም። ራያ ድረስ የኛ ምድር ነው። የበቀል እሳት ሊለኰስ እንደሚችል ካላሰቡ እነዚህ ሰዎች በጣም የዋሆች ናቸው። ዘርፎ ማምለጥ የሚባል ቁማር የለም። በዚህ እስካፍንጫቸው እየዘረፉ፣ መልሰው ደግሞ 'ሃገሪቱ ድሃ ናት' እያሉ ይናገራሉ። ኢትዮጵያ ድሃ ሆና አታውቅም። ድህነት ያለው የመሪዎቻችን አስተሳሰብ ውስጥ ነው።

"...አንድ ጊዜ የሆነውን ላጫውትህ?

"...የሽራሮ ልጆች ከሆኑ ሁለት የህወሃት ከፍተኛ መኮንኖች ጋር ወደ ጅማ እየተጓዝን ነበር። ትግሬዎቹ አካባቢውን ገና ማየታቸው ነበር። ኰረሪማና ዝንጅብል፣ ዘይቱንና አገዳ በየሜዳው በቅሎና ወድቆ ሲያዩ ማመን ተቸገሩና፣

'ይህ ገነት ነው። ይሄ መንግስተ ሰማያት ነው' ማለት አበዙ። ቢቸግረኝ እንዲህ አልኳቸው፣

'በስልጣን ዘመናችሁ በጐ ከሰራችሁ ስትሞቱ ነፍሳችሁ እዚህ ትመጣለች! ካልሆነ ግን ነፍሳችሁ ሽራሮ ትቀራለች።'





"...በክፉ አልያዙብኝም።

"...ደኑ መስጧቸው ስቀው ብቻ አለፉኝ። አነጋገሬን በክፉ ባይዙብኝም ለካስ ያን የመሰጣቸውን ደን በክፉ አይን አይተውት ኖሮአል። መጥረቢያ ተመኙለት። የመጥረቢያ እራት ያደርጉት ገቡ። እኔና አንተ እዚህ ስናወጋም የጅማ ጫካ እየታጨደ ነው። እንደ ጠላት ሃገር እያወደሙት ነው። የራስ መስፍን ስለሺ ንብረት የነበረው ኰምፔርሳቶ ፋብሪካ የጅማ ጫካ ጥገኛ ነበር። አሁን ወያኔዎች ተረክበውታል። እኔም ሆንኩ የጅማ ሰው የ500 አመት እድሜ ያላቸው የቀረሮ ዛፎች ሲታጨዱ ቆመን ተመልክተናል። እነዚህ የትግራይ ተወላጅ የሆኑ ነጋዴዎች ዛፎቹን እየቆረጡ፣ በቀን ከሃያ እስከ ሰላሳ ኤንትሬ እየጫኑ ወደ ሳውዲ አረቢያ ይሸጡታል። ቀረሮ ለኛ ህይወታችን ነው። ቀረሮ ተመንጥሮ ካለቀ ጅማ በረሃ ትሆናለች። ቀረሮ በጣም ግዙፍና የጥንት ዛፎች ናቸው። ቁመታቸው ሰማይ ጠቀስ ነው። አንዱን ቀረሮ ዛፍ ወያኔ እስከ 15ሺህ ብር በቁሙ እየቸበቸበው ነው። ይህን አይቼ ካልተቆጣሁና ካላመፅኩ ታዲያ መቼ ነው ልቆጣና ላምፅ የምችለው? ቡናውን እንደፈለጉ ይዝረፉ! ዛፉን ግን መንካት አልነበረባቸውም። ዛፎቹ ከሌሉ ቡናው አይኖርም። ቡና ቀጥተኛ ፀሃይ መቋቋም ስለማይችል የዛፎቹን ጥላ ይፈልጋል። የትግራይ ተወላጆቹ ስለዚህ ጉዳይ ግንዛቤ የላቸውም ብቻ ሳይሆን ደንታም የላቸውም። 'ወደፊት ትግራይ ትገነጠላለች' የሚል ነገር ጭንቅላታቸው ውስጥ ስላለ፣ ስለገንዘብ ብቻ ነው የሚያስቡት። የጅማ ደን ተመንጥሮ ካለቀ፣ ትግራይ ላይ የሚዘንበው ዝናብ ጭምር ሊቀንስ እንደሚችል ግንዛቤ የላቸውም።

"...እኔ አሁን ርቄያለሁ። የትውልድ መንደሬ ደን ሲጨፈጨፍ አለማየቱ ይሻለኛል። ቢያንስ ይህን የምነግርህን ከፃፍከው ሃላፊነቴን እንደተወጣሁ ሊቆጠር ይችላል። ከሚዘርፉት ጋር አብሬ መዝረፌን መናዘዙ ሃጢአቴን ያፀዳልኛል።

ሃገሪቱ ባለቤት እንደሌላት የሚያሳይ ገጠመኜን ልንገርህ። ሚስቴ በወለደች ጊዜ ከመከላከያ መኮንኖች ብቻ ከ20 በላይ ባለ ጆሮ ማንጠልጠያ ያለው ብላክ ሌብል እና ቺቫዝ ውስኪ መጥቶልኛል። አንዱ ደምበጃን አራት ሌትር የሚይዝ ሲሆን፣ የአንዱ ዋጋ 1800 ብር ነበር በወቅቱ። የመከላከያ

አለቆቼ ይህን ውስኪ ያመጡልኝ ገዝተው እንዳይመስልህ። መከላከያ ድንበር ላይ የሚወርሰውን ኮንትሮባንድ ውስኪና ሌላ ንብረት እያመጣ አዲሳባ መጋዘን ውስጥ ይከምራል። ከዚያ እየመረጥክ መውሰድ ነው። ጠያቂ የለም። ሚስቴ ወልዳ ሳለ ሊጠይቋት ለመጡት ገበሬዎች በጠላ ብርጭቆ ሺቫዝ ውስኪ ቀዳንላቸው። ገበሬዎቹ ቀመሱትና፣ 'ምንድነው ይሄ ትሁዋን ትሁዋን የሚል መጠጥ? አረቄ ወይም ጠላ ካለ አምጡልን' ሲሉ ጠየቁ።"

ሌላ ቀን ደግሞ እንዲህ ሲል አጫወተኝ፣

"...መለስ ዜናዊ አንድ ጊዜ አባዱላን ጠርቶ።

'ኢትዮጵያ በእግሯ የቆመችው በኦሮሚያ ሃብት ሳይሆን በእርዳታ ነው። አንተ የሚፎክርበት የኦሮሚያ ሃብት ከአዲሳባ ወሊጋ ያለውን መንገድ መስራት አይችልም። የአንግ ቫይረስ ተሸካሚ ለሆኑ አባሎችህ ይህን ቃል በቃል ንገር!' ሲል አዞታል። አባዱላም 'መለስ እንዳለው' እያለ ይህንኑ ሲያስተምር ከርሞአል። መለስ ዜናዊ ከላይ ያለውን አባባል ዲማ ነገዎ ፊት እንደማይደግመው ግልፅ ነው። የአማራ ጄኔራሎችን ደግሞ፣ 'አስር ገፅ እንኳ መፃፍ የማትችሉ ጄኔራል አድርገናችሁ በትምክህት ታስቸግሩናላችሁ!' እያለ ሲሰድባቸው ሰምቼአለሁ። ጄኔራሎቹ የመለስን የእብሪት ንግግር በፀጥታ ማዳመጣቸው የፍርሃት ነው ሊባል ግን አይቻልም። ፍርሃት ሊሆን የሚችለው እየተሰደቡ ከቀጠሉ ብቻ ነው። በተለያዩ አጋጣሚዎች የአመፅ ምልክቶች እየታዩ በመሆኑ አገሎንብሰው ተቀብለውታል ለማለት የሚቻል አይደለም። መለስ እብሪት ይዞት ያንን ተናገረ እንጂ ከትግራይ የመጡት ጄኔራሎች የተሻለ እውቀት ያላቸው ሆነው አይደለም። አካዳሚውን እንተወው። በውጊያ መስኩስ ቢሆን የትኛው ልምድ አላቸው? መንግስቱ ሃይለማርያም ራሱ እንደነገረን ደርግ ከሻእቢያ ጋር ነው ሲዋጋ የነበረው። 'ወያኔን አናውቀውም ነፋስ ነው ያመጣው' ሲል የተናገረው ግነት ቢኖርበትም እውነት ነው። ደርግ ያለቀለት 604ኛ ኰር ሽሬ ላይ ሲደመሰስ ነው። ያንን የደመሰሱት ደግሞ በሻእቢያ የሜካናይዝድ ሃይል ርዳታ ነው። ከዚያ ወዲያ ደርግ ሲሸሽ እንጂ ሲዋጋ መቼ ታየና? እንተዋወቃለን። አብረን ነበርን።

"...ወደ አካዳሚው ከመጣን ደግሞ፣ አብዛኞቹ የህወሃት ጄኔራሎች ከሶስተኛ ክፍል ያላለፉ በመሆናቸው የወታደራዊ





ሳይንሱንም ሆነ፣ የአዛዥነቱን ጥበብ ሙያው በሚፈቅደው ደረጃ አንብበው ችሎታቸውን ወደ ማእረጋቸው ደረጃ ለማድረስ ይቸገራሉ። ርግጥ ነው ይዋጋሉ! መጥፎም ይሁን ጥሩ ለአላማቸው ጠንክረው ይቆማሉ። ይህ ማለት ግን የአመራር ብቃት አላቸው ማለት አይደለም። መቶ ወታደር ብቻ የሰፈረበትን ገዢ መሬት ለመያዝ፣ አንድ ሺህ ሰው ካስፈጀህ በወንጀል ትጠየቃለህ እንጂ በድል አድራጊነት መሸለም ባልተገባህ። የኛዎቹ ጄኔራሎች በግዴለሽነት በሺህዎች አስፈጅተው ሲያበቁ፣ ውጊያው ሲያልቅ የታሰሩ ብሮችን ተሸክመው ሴትና መጠጥ ፍለጋ በየከተሞቹ ሲዘምቱ ነው የምናውቃቸው። በተለይም ቆንጆና ወጣት ሴት ማሳደዱ የአብዛኞቹ አዛዦች ልዩ መለያ እስከ መሆን ደርሶአል። ርስበራስ እየተነጣጠቁ ጭምር ይዝናናሉ። እንደ መዝናኛ ያስቡት እንደ ስልጣኔ አይገባኝም። ያንዱን ሚስት ሌላው መወሸም ጭምር በጄኔራሎቹ አካባቢ በጣም የተስፋፋ ባህል ሆኖአል። አንዱ የፈታትን ጓደኛው ያገባታል። ሚስቱን ፈቶ የአክስቷን ልጅ ያገባል። እንደገና ከሁለቱም ጋር ይቀጥላል። ይህን መሰል ቅሌቶች ጆሮአችን እስኪደነግጥ እንሰማለን።

"...ሳሞራ መፅሃፍ አንብቦ አያውቅም።

"...ብዙውን ጊዜ ቢሮው ውስጥ እንደ አንበሳ ተኝቶ ይውላል። ከእንቅልፉ እየነቃ የቀጠራቸውን ሰዎች ያነጋግራል። 'በሰላም ወቅት ትምህርትና ስልጠና' የሚለው ወታደራዊ መርህ ወያኔ ዘንድ አይታወቅም። 'በሰላም ወቅት መጠጥና ሴት' በሚለው የተተካ እስኪመስል ድረስ በአሳዛኝ ሁኔታ ልማድ የተዋጡ ናቸው።

ወያኔ ራሱ የፃፈውን ህገመንግስት በፍፁም አያውቀውም። ህገመንግስቱን ያረቀቀው መደረግ ስለነበረበት ብቻ ነው። ሳሞራ በምርጫ 97 ዋዜማ የአረቄ ብርጭቆ ጨብጦ፣

'ተቃዋሚዎች ቤተመንግስት የሚገቡ ከሆነ እሸፍታለሁ። በማን ደም ማን ይነግሳል?' እያለ ይናገር ነበር። በርግጥም ወያኔ ስልጣኑን ሊያስረክብ እቃውን ጠቅልሎ ነበር። የምርጫ 97 ውጤትን ተከትሎ የህወሃት አባላት፤

'እኛስ ሃገር አለን። ይብላኝ ለአማራው' እያሉ ይናገሩ ጀምረው ነበር። የወያኔ የፖሊት ቢሮ አባላት፣ 'የከፋ ነገር ቢመጣ ስልጣኑን ኦሮሞ ይወስዳል እንጂ አማራ ተመልሶ ወደ

ስልጣን አይመጣም!' እያሉ ኦሮሞን በአማራ ላይ ለማነሳሳትም ሞክረዋል።

እዚህ ላይ ታዲያ ህገመንግስቱ የት ገባ?

ችግሩ የአፈፃፀም ችግር አይደለም። የሃገሪቱ መሪዎች ህገመንግስቱን አያውቁትም። አብዛኞቹ ፅንሰ ሃሳቡን ጭምር አያውቁትም። አግበ እና ሽራሮ ዋሻዎች የደበቋቸው ተተኳሽ መድፎች ትግራይ በእግሯ እንድትቆም፣ በጡንቻዋ እንድትመካ ያስችላታል ብለው ይመካሉ...

* * *

በትካዜ እንዲህ ሲል አወጋኝ፣

"...የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ለጦርነቱ መሪዎች የሃብት ምንጭነት ሆኖ ማገልገሉን ማየት ችያለሁ። በጦርነቱ ሰበብ በተዘረፈ ሃብት ብዙዎቹ የህወሃት ጄኔራሎች ሚሊዬኔር ሆነዋል። ፃድቃን፣ ጆቤ፣ ብርሃነ ነጋሽ፣ ገዛኢ አበራ፣ አባዱላ ገመዳ፣ አበባው ታደሰ፣ ባጫ ደበሌ፣ ታደሰ ወረደ፣ ሰአረ መኰንን እና ሌሎችም ጄኔራሎች በአዲስ አበባ፣ በባህርዳርና በመቀሌ ያስገነቡት ቪላና ፎቅ ውበቱ አይንን ያፈዛል። የቤት እቃዎቻቸው፣ ምንጣፎቹ፣ መብራቶቻቸውና ኩርኒሶቻቸው በውድ ዋጋ ከአውሮፓ እየተጫኑ የመጡ ናቸው። የመጨረሻውን ቴክኖሎጂ እየተጠቀሙ ለቪላዎቻቸው ማሞቂያና ማቀዝቀዣ ተክለውላቸዋል። ከዚያ ሁሉ እልቂት በሁዋላ ጄኔራሎቹ በቀጥታ ወደ ሃብት ፉክክር ነው የገቡት። የሚፈሰው ገንዘብ በጦርነቱ ወቅት የተዘረፈ ነው። የዚህ ጦርነት አድርጊ ፈጣሪዎቹና ዘራፊዎቹ እነሱው የትግራይ ተወላጆች ናቸው። እንደ ባጫ ደበሌ፣ አለሙ አየለ የመሳሰሉት ጄኔራሎች በማእረጉ ይጠሩበታል። ዝርፊያም ይፈቀድላቸዋል። በስራ ግን አይሳተፉም። የሚቀመጡበት የረባ ቢሮ እንኳ በአግባቡ የላቸውም። የከተማ ቦታዎችን በመቸብቸብ ረገድ የመከላከያ ጄኔራሎችን የሚስተካከላቸው የለም። በዱከም፣ በናዝሬት፣ በደብረዘይትና በአዲሳባ አይናቸው ያማራቸውን ግንባር መሬት ሁሉ እየቦጨቁ ወስደው ሸጠውታል። ይህ ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም። ዘረፋው በጣም እየከፋ በመሄዱ መለስ ዜናዊ ሁለት ጊዜ ያህል ከኰሎኔል ማእረግ በላይ ያሉትን በፅህፈት ቤቱ አዳራሽ ሰብስቦ፣ ዘረፋው እንዲቆም ለማሳሰብ ሞክሮ ነበር።





የጦርነቱ ኪሳራም ሆነ ይህ መረን ያወጣ ዝርፊያ ሁሉ የዚችው ደሃና መከረኛ ሃገር ሃብት ነው። ሃገራችን የምንላት ኢትዮጵያ ባለቤት ያጣች የሽፍቶች መፈንጫ መሆኗን በዝርዝር ማወቅ በጣም ያስቆጫል።

አለማወቅ እንኳ ይሻል ነበር።

እያወቅህ ዝም ማለት ደግሞ ህሊናን ያደማል። እዚህ የምናየው ሁለት ችግር ነው። ወታደራዊ ችሎታቸው 'የጦር መሪ ጄኔራል' የሚያሰኛቸው አይደለም። የሃገር ፍቅር ስሜትም የላቸውም። ስለዚህ ነጋ ጠባ ኪሳቸውን ወደ መሙላት ይሮጣሉ። የሚፈፅሙትን የሚያስተውል 'በርግጥ ይህች ሃገር ሃገራቸው ናትን?' ብሎ መጠየቁ አይቀርም..."

ከኰሎኔል አበበ ገረሱ ጋር በተለያዩ ጊዜያት እየተገናኘን ብዙ ተጨዋውተናል። ሌላ ቀን ደግሞ እንዲህ ሲል አጫወተኝ፣

"...እኔ ኰሎኔል ነኝ።

"...ማእረጌ ግን የውሸት ነው። አንድ ትግሬ መቶ አለቃ እንደፈለገው ሊጫወትብኝ ይችል ነበር። አንድ ተራ ትግሬ ከጠላህ አለቀልህ። 'እዚ አነግ እዩ!' ብሎ ከተናገረ ያንተ ነገር አበቃ ማለት ነው..."

ስለ ጄኔራሎች ስናወራ ደግሞ በአጋጣሚ የአበባው ታደሰ ስም ተነሳና እንዲህ አለ፣

"አበባው ብልጥ ናት። ሳሞራን እያባባለ ክብሩን ሳያስነካ የሚኖር ጮሌ ነው። ችሎታ ያንሰዋል እንጂ በውጊያ ላይ ልብ ያለው ወታደር መሆኑን ማንም አይክድም። ከውጊያ በሁዋላ ግን ሳሙና ሆኖ ታገኘዋለህ። በአንድ ሌሊት 10ሺህ ብር ጨርሶ ያድራል"

"ከየት ይመጣል ይሄ ገንዘብ?" ስል ጠየቅሁት።

"ብዙ መንገድ አለ። መከላከያ ሚኒስቴር ለበቅሎ ቀለብ በአመት አንድ ሚሊዮን ብር መድቦ ነበር። በኛ እዝ ግን አንድም በቅሎ አልነበረም። የኛ በቅሎ ጄኔራል አበባው ነው። እነ ሳሞራ ደግሞ በእጅ አዙር ከአበባው ይቀበላሉ።"

"አንተስ? ምንም አይደርስህ?" ስል ጠየቅሁት።

አበበ ሳቀ!

"ብዙ አይደለም እንጂ ትርፍራፊውን እወስዳለሁ"

"ሂሳብ አታወራርዱም እንዴ?"

"ይወራረዳል። ለበቅሎ ቀለብ ያቀረቡ ሰዎች ስም ዝርዝር እየሞላን እጃችን እስኪደማ ድረስ ራሳችን እንፈርማለን። ምን ይሄ ብቻ? ብዙ ዘዴ አለ። 'ለምሽግ ስራ' በሚል ወጪ ይደረጋል። የተሰራ ምሽግ ግን የለም። ስኳር ለሰራዊቱ ሲታዘዝ መቀሌ ላይ ይራገፍና ይሸጣል። ሰራዊቱ ሻይ አያገኝም። መንግስቱ ሃይለማርያም፣ 'ሰራዊታችን ሙሰኛ አልነበረም' ያለው እውነቱን ነው። ከወያኔ ጋር የምታወዳድረው አይደለም። እዚህ ዘረፋው በግልፅ ነው የሚካሄደው። ነፍጠኛ ስልጣን ላይ በነበረ ጊዜ የጅማን ጫካ የኔ ነው ብሎ ስላመነ አልነካውም። እነዚህ እኮ አጭደውና ፈልጠው ለመሸሽ የመጡ ወሮበሎች ናቸው። ለሰራዊት እለታዊ ካምፕና ለሽሮ መቀቀያ 500 አመት እድሜ ያለውን የቀረሮ ዛፍ ያስቆርጣሉ። አንድ የቀረሮ ዛፍ የአራት የደለቡ በሬዎች ዋጋ ነው። እነሱ ሽሮ ያበስሉበታል። በሌሎች ሃገራት ዛፍ የቆረጠ እስር ቤት ይላካል..."

አቋረጥኩት፣

"ዛፍ እየተከሉ መሆናቸውን ግን በሬድዮ ሲናገሩ ሰምቻለሁ።" አልኩ።

"ለትግራይ ጥሩ የዛፍ ፖሊሲ አላቸው። በሌላው ክልል የይስሙላ በዘመቻ የዛፍ ተከላ ስራ ሰርተዋል። የሚመነጠረው ይበዛል። አዋሳ ከመግባትህ በፊት ከመንገዱ ግራና ቀኝ የነበረው ዛፍ ትዝ ይልሃል? ዛሬ አንድ ዛፍ ለአይንህ አታይም"

ከጥቂት ሰከንዶች ፀጥታ በሁዋላ ቀጠለ፣

"...ከምርጫ 97 በሁዋላማ ለይቶላቸዋል። ገንዘብ የሚያስገኝ ከሆነ ማንኛውንም ወንጀል ይፈፅማሉ። ዛፉንም መሬቱንም በቁሙ እየቸበቸቡት ነው። የሽሽት ጣቢያ የሚባሉት አሜሪካና ትግራይ ናቸው። ሳትቀደም ቅደም! ዘርፈህ አምልጥ! ይባባላሉ። በውጊያ ወቅት አንድ እግር በመሬት የሚባል ነገር አለ። እስከ ኮሎኔል ያሉት ትግሬዎች በአብዛኛው ቤተሰባቸውን ወደ አሜሪካ አሽሽተዋል። በስደት ያሉ የባለስልጣን ቤተሰቦች ዶላር የሚላክላቸው ከሃገር ውስጥ ነው። ተገላቢጦሽ። ሽመልባ የሚባል የስደተኞች ካምፕ አለ፣ ትግራይ ውስጥ። ትግሬዎቹ፣ 'ኤርትራውያን ነን' እያሉ በብዛት ወደ ውጭ ሃገር ይሄዱበታል። ምንም ነገር ከማድረግ ወደ ሁዋላ አይመለሱም..."

* * *





"...አንድ ጊዜ ያጋጠመኝን ላጫውትህ?" ሲል ጀመረና እንዲህ ሲል ቀጠለ፣ "...ግንቦት 20 አዳሪ ትምህርት ቤት ሳለሁ ምግብ ቤት ውስጥ እየተመገብኩ ሳለ፣ ውሃ ፈለግሁና በአጠገባችን በማለፍ ላይ የነበረችውን አስተናጋጅ፣ 'አንቺ!' ስል ጠራሁዋት።

ልኡል የሚባል ሻምበል ከጎኔ ተቀምጦ ነበር። አማራ ሳይንት የተወለደ አክራሪ አማራ ነው፣

'ባለጌ!' አለኝ፣ '...ሴት ልጅን አንቺ! ብለህ መጥራት ነውር ነው።'

'ማን ብዬ ልጥራት ታድያ?'

'እቴቴ ነው የሚባለው'

'እኔ የማውቀው ሴት ከሆነች አንቺ! ወንድ ከሆነ ደግሞ አንተ ማለትን ነው' ብዬ መለስኩ።

'ከንግዲህ ግን እቴቴ! ማለትን ተማር' ይለኛል።

'መማር አያስፈልገኝም። ያንተን እቴቴዋ ኪስህ ውስጥ ጨምረው!' አልኩት።

ልኡል በዚህ ይበሳጭና በግምገማ ላይ ክስ ያቀርባል፣

'አማርኛ ብሄራዊ ቋንቋችን ነው። ይህ ቋንቋችን ከአግባብ ውጭ ጥቅም ላይ ሲውል አዳምጬ እርማት ለመስጠት በመሞከሬ፣ 'አማርኛህን ቀቅለህ ብላው!' ተብያለሁ። ባንዴራ፣ ሃገር፣ ቋንቋ ክብር አላቸው። የማንነታችን መግለጫ ናቸው። ስለዚህ አበበ ላይ ሂስ አቅርቤያለሁ' ይላል።

ሃይሉ ሳንቲም የተባለ ካድሬ ተልኮ መጣ። ጉዳዩ ትኩረት አግኝቶ ሰፊ ክርክርና ውይይት ተደረገበት። የኔ መከራከሪያ፣ 'እኔ ኦሮሞ ነኝ። በምችለው መጠን አማርኛ የመናገር መብት አለኝ' የሚል ነበር።

ህወሃቶች የአማራንና የኦሮሞን መለያየት ስለሚፈልጉ ሚዛን ወደኔ አጋደለና ልኡል ተቀጠቀጠ። የህወሃት ካድሬዎች ከኔ ጎን ቆመው፣ ከኔ በባሰ ቁጣ ጭምር እየተናገሩ፣ ልኡልን በትምክህተኛነት ፈረጁት። አማርኛ ቋንቋንም በአማርኛ እየተናገርን አላገጥንበት። እኔ ነፃ ወጣሁ። ከስድስት አመታት በሁዋላ ግን በተቃራኒው ሌላ ችግር ገጠመኝ። ስህተቴን ለመመዘንም ቻልኩ።

በኤርትራ ጦርነት ወቅት አራት የጦር ሰራዊት መኰንኖች ከደምበ ገዳሙ ወደ ሽሬ እየተጓዝን ነበር። ርቀቱ

150 ኪ.ሜ ይሆናል። በመኪና ውስጥ የነበሩት መኰንኖች ትግሬዎች ነበሩ። ወዲ እጅጉ፣ ነጋሲና አለም ይባላሉ። ሽሬ ደርሰን መኪናዋ እስክትቆም ድረስ ትግርኛ ብቻ ነበር የሚነጋገሩት። መከላከያ ሚኒስቴር ሃገራዊ መስሪያ ቤት እንደመሆኑ የመነጋገሪያ ቋንቋው አማርኛ ነው። እኔ ትግርኛ አልችልም። ጦርነት ላይ ነን። እኔ ኮሎኔል ነኝ። መኮንኖቹ ለአፋቸው እንኳ፣ 'ተጫወት' አላሉኝም። በትግርኛ እያወሩ ሽሬ ገባን። የሽሬ ስራችንን እንዳበቃን ለመልስ ጉዞ ተዘጋጀን። በዚህ ጊዜ፣

'ከእናንተ ጋር አልመለስም' አልኳቸው።

'ምነው?' አሉ።

'እኔ ሰው እንጂ እንጨት አይደለሁም። እናንተ ስለ ሰው ክብር አታውቁም። እኔ መሃላችሁ ቁጭ ብዬ ሳለሁ ሁላችንም በምናውቀው ቋንቋ ለመነጋገር ፈቃደኛ አልሆናችሁም። ስለዚህ ከናንተ ጋር አልመለስም።'

ጥለውኝ ሄዱ።

እኔ በሌላ መኪና ወደ ደምበ ገዳም አቀናሁ። ይህ ጉዳይ ግን በቀላሉ አልታለፈም። አጀንዳ ሆኖ ግምገማ ላይ ተነሳ። ክስ ቀረበብኝ፣

'በትግርኛ ስለምታወሩ ከእናንተ ጋር አልሄድም' ብሎናል ሲሉ ከሰሱ። በሚያስገርም ደረጃ፣ 'የትግሬ ጠላት' ተብዬ ተፈረጅኩ።

'እኛ እኮ የታገልነው በቋንቋችን ለመጠቀም ነው። ላንተ ተብሎ አማርኛ እንዲናገሩልህ ትፈልጋለህ?' ተብዬ ተጠየቅሁ።

እዚህም ላይ እንደገና አማርኛ በአማርኛ ተቀጠቀጠ። እነሱ ሲቀጠቅጡኝ ልኡልን አስታወስኩት። ሌላም ጥያቄ ወደ አእምሮዬ ሳይመጣ አልቀረም። አማርኛ ባናውቅ ኖሮ ከነዚህ ሰዎች ጋር በምን እንነጋገር ነበር?..."

* * *

"...ክንፈ በተገደለበት ስብሰባ ላይ የልባችንን ለመናገር ሞክረን ነበር። ብዙዎች ብዙ ተናግረዋል። ያ ስብሰባ መቼም ከኢህአዴግ የግምገማ ባህል ባፈነገጠ ሁኔታ፣ ሁሉም የልቡን የተነፈሰበት ስብሰባ ነበር። ከዚያ በፊትም ሆነ ከዚያ በሁዋላ ያን





የመሰለ ስብሰባ አልተካሄደም። በኔ በኩልም አንዳንድ ነጥቦች አነሳሁ። ያልኩት ምንድነው?

'ኦሮሞዎች ተቸግረናል። የኦሮሞ ህዝብ ያለምክንያት እየታሰረና እየተገደለ ነው። ኦሮሞ የሆንን የኢህአዴግ አባላት ከሁለት ገደል አፋፍ ላይ ሆነን ተቸግረናል። ስለ ህዝቡ መበደል ስንናገር ኦነግ እንባላለን። ዝም ስንል ደግሞ ህዝባችን እንደ ጠላትና አሽከር ያየናል። በሁለቱም በኩል ገደል ሆኖብናል።'

ክንፈ እንዲህ ሲል መለሰ፣

"ከደቡብ ህዝቦች አንፃር ሲመዘን ኦሮሞዎችን አልበደልናችሁም። ኦነግ እንዳያጋልጠን እየሰጋን ኦሮሚያ ላይ እንጠነቀቃለን። የደቡብ ህዝቦችን ምን እንደምናደርጋቸው ብታዩ በጣም ታዝኑ ነበር። በኛ አስተዳደር የደቡብ ህዝቦች ያሳለፉት ዘመን አሰቃቂ ነው። ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ እና ዳውሮ የተባሉትን ብሄረሰቦች ባንድ ላይ ጨፍልቀን 'ወጋጎዳ' የሚል ስም ሰጥተን፣ አዲስ ቋንቋ ለመፍጠር ሞክረን ርስበራስ እንዲጫረሱ አድርገናል። የአዋሳ መሬት በሙሉ ለትግሬ ተሸጦ አልቆአል። ኦሮሚያ ላይ ግን ይህን ያህል አንደፍርም። ኦነግን እንፈራዋለን። ኢህአዴግ እንደ አሳ ከጭንቅላቱ ነው የገማው..."

አቋረጥኩት፣

"ክንፈ ይህን ተናገረ?"

"ቃል በቃል ነው የምነግርህ። የመኮንኖች ስብሰባ ላይ ክንፈ ቃል በቃል ይህን ተናግሮአል። በነጋታው ግን እዚያው እፊታችን በአራት ጥይት ጭንቅላቱ ላይ ተደብድቦ ተገደለ። 'የጋዜጠኛው ማስታወሻ' ላይ 'ከክንፈ ግድያ በስተጀርባ ማንም የለም' ብለህ ፅፈሃል። ስብሰባው ላይ የነበሩ መኮንኖች ግን ይህን አይቀበሉህም..."

እንዲህ ስል ተቃወምኩት፣

"ስለበረታችሁበት በመጠኑ ግልፅ መስሎ ሊያበርዳችሁ ያን ተናግሮ ሊሆን ይችላል እንጂ፣ ክንፈ የህወሃት ተቃራኒ ሊሆን አይችልም። የሆነው ሆኖ 'አብዮታዊ ዴሞክራሲ ላይ ውይይታችሁ ምን ይመስል ነበር?" ስል ጠየቅሁት።

"አብዮታዊ ዴሞክራሲና ሊበራል ዴሞክራሲን በማነፃፀር ጠንካራ ውይይቶች ተካሂደው ነበር። ክንፈ፣ 'ኢኮኖሚያችን ካፒታሊዝምን ቢከተልም መስመራችን ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ አይዛነፍም' ብሎ ነክሶ ያዘ። 'አብዮታዊ ዴሞክራሲ እያልን

ተቀርቅረን ቀርተናል። ሊብራል ዴሞክራሲ ሳይሻለን አይቀርም' የሚሉም ነበሩ። በመጨረሻ፣ 'አብዮታዊ ዴሞክራሲ ለኛ ለኢህአዴጎች የመኖርና ያለመኖር ጎዳይ ነው። ህዝቡ እንኳ ባይቀበለን ጫካ ተመልሰን እንገባለን እንጂ አንለቀውም። የህልውና ጉዳይ ነው' በሚል ተደመደመ። ያው እንደ ሁልጊዜው የተምታታ ነበር"

የደቡብ ህዝቦች ከወያኔ የሚደርስባቸውን የመብት ረገጣና ዝርፊያ ቢያንስ በጩኸት እንኳ የሚያግዛቸው አለመኖሩ የዘመናችን ትራጄዲ ሳይሆን አይቀርም። ብቸኛው የደቡብ አንጋፋ ፖለቲከኛ በየነ ጴጥሮስ ራሱን በታማኝ ተቃዋሚ ዘንቢል ውስጥ በማስቀመጡ ለዚያ ክልል መከታ ሊሆን የሚችል የፖለቲካ ሰው በአይን ማየት አልተቻለም። የእምነቱን በድፍረት በመናገርም ሆነ በማድረግ ደረጃ አሰፋ ጫቦ አንቱ የተባለ ነበር። በስደት ቀልጦ የቀረ ይመስላል።

ሌላ ቀን ደግሞ አበበ እንዲህ አለኝ፣

"ትግሬ ተናዳጅ ነው!' የሚባል ወሬ ሰምተህ ሊሆን ይችላል። ይሄ አባባል አሁን ተለውጦአል። ትግሬ መናደድ ትቷል። ትግሬ የሚናደደው ስለ ከፋው ነበር። ሰው በተመቸው ቁጥር ንዴቱ እየቀነሰ ይሄዳል። 'ኦሮሞ ቶሎ አይናደድም' የሚባል ወሬም ነበረ። እሱም ተለውጦአል። በዚህ ዘመን ገና ስትነካው እንደ ክብሪት የሚጨሰው ኦሮሞ ሆኖአል። ትግርኛ የሚናገሩ ወገኖቻችን የኢትዮጵያን ነባር ጫካ ሲያስፈልጡ፣ ኦሮሞ ካልተቆጣ መቼ እንዲቆጣ እንጠብቃለን? አዋሳ መግቢያ መንገድ ላይ ግራና ቀኝ ይታዩ የነበሩት ዛፎች ዛሬ አንዳቸውም አይታዩም። ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ፣ 'የጅማ በረሃ!' የሚል አዲስ ቃል ብንሰማ መደንገጥ የለብንም..."

ብሉናይል ከተባለ ሬስቶራንት ምሳ ልንበላ ሄደን ነበር። "የኦሮሞ ሽሮ አማረኝ" በማለቱ ነበር ወደዚያ የሄድነው። የሬስቶራንቱ የወጥቤት ሃላፊ ኦሮሞ ነበረች። የአስመራን የምግብ ቤት ገበያ ብቻዋን ሳትቆጣጠረው አልቀረችም። ሁሉም ወደዚያ ምግብ ቤት ያመራል። ብሉናይ ምግብ አዝዘን እየተመገብን ሳለ፣

"እነዚህ ሰዎች ጤነኛ ናቸው ትላለህ?" ስል ጠየቅሁት።

"አላውቅም" አለ ፈጥኖ፣ "...ችግራቸው ምን እንደሆነ አላውቅም። ኢትዮጵያን እንደ ሃገራቸው አያዩዋትም። ከዚያም





በላይ በሃገሪቱ ላይ ጥላቻ ሳይኖርባቸው አይቀርም። ምቀኝነትና ክፋት ይኖርባቸውም ይሆናል። የጅማን ጫካ ሲያዩ እንደራሳቸው፣ እንደ ኢትዮጵያ ሃብት ከማየት ይልቅ በቅናትና በጥላቻ ታመው ሊሆን ይችላል። በጥቅሉ ግን አመራሩ ሞራሉ የወደቀ አመራር ነው። 'በወንጀለኛነት እንጠየቃለን' የሚል ስጋት ሊኖርባቸው ይችላል። የአቅም ማነስም አለ። የጤና መታወክም ተደራርቦባቸዋል። ለዚህች ሃገር በጐ ህልም ማለም ሳይችሉ የቀሩት ይህን በመሰሉ የስነልቦና ቀውስ ምክንያት ሊሆን ይችላል። የቤተሰብ ቀውስ በራሱ አደጋ ነው። በፖሊት ቢሮ ደረጃ ያሉ አመራር አባላት ሶስት ጊዜ ሚስት እየፈቱ አዳዲስ ሚስት ያገቡ አሉ። ከስስት ሴቶች የወለዷቸውን አንድ ላይ ሰብስበው የሚያሳድጉ የአመራር አባላትም አሉ። አዲሱ ለገሰ ሊጠቀስ የሚችል ነው። ታጋይ ሚስታቸውን እስር ቤት ልከው የከተማ ቆንጆ ያገቡ አሉ። መድሃኒት ባልተገኘለት አደገኛ በሽታ የተያዙ አሉ። ለቤተሰቡ ፍቅር የሌለው ሰው በአናቱ በበሽታ የሚሰቃ ከሆነ አደገኛ ነው። በቤተሰቡ ደስተኛ ያልሆነ መሪ  ለሃገሪቱ ህዝብ እንዴት ተስፋ ሊሆን ይችላል? በአንፃሩ መላ ህብረተሰብ ላይ ጥላቻ ሊያድርበት ይችላል። እንደዚህ ያለ የአመራር ስብስብ እንዴት ያለ ራእይ ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል? 'አረጀችብኝ' እያሉ ሚስታቸውን የፈቱና ወጣት ቆንጆ እየመረጡ ያገቡ እንደ ተፈራ ዋልዋ አይነቶች አሉ። የሌሎችንም የአመራር አባላት ስም ልጠራልህ እችላለሁ። ኩማ ደመቅሳ አለልህ። ሚስቱን ከመኪናው ለይቶ ማየት ያልቻለ ሰው፣ ዜጐችን እንዴት በበጎ አይኑ እንዲያይ ይጠበቃል? እነዚህ ሰዎች ገንዘብ አላቸው። ገንዘቡን አምላክ ይባርክላቸው። የያዙትን ይዘው የለመዱትን ህይወት እንዲቀጥሉ እንመኝላቸዋለን። የሃገሪቱ ስልጣን ግን የጋራ የህዝብ ንብረት ነው። በሰከነ መንፈስ ወደ ልቦናቸው እንዲመለሱ እንጠብቅ ነበር..."

* * *

በዚያን ቀን አበበ ሲያወጋኝ፣ በመካከሉ ወደ አዲሳባው የመኮንኖች ክበብ በአሳብ ሽው አልኩ። ሃሳብ ፈረሰኛው። ማን ሊያቆመው? ቼ! ፈረሴ! ቁና ገብሴ! ሽው እልም...ሽው እልም፣ ሽው እልም ይላላ... እንደ ሃምሌ ጥላ...

በከረንቦላው ጠረጴዛ ዙሪያ...

ኳኳኳኳኳ! ጥይት አይደለም! የከረንቦላ ኳስ ሲንኳኳ!

ከእለታት አንድ ቀን ሁለት ጄኔራሎች የከረንቦላ ግጥሚያ ላይ ነበሩ። ሳሞራና ሃይሌ ይባላሉ። ሁለቱ የማይዋደዱ ጄኔራሎች በከረንቦላው ጠረጴዛ ዙሪያ ትንቅንቅ ላይ ነበሩ። አባዱላ ገመዳ ዋና አጋፋሪ እንደነበር ትዝ ይለኛል። ባጫ ደበሌም ከአባዱላ አጠገብ ቆሞ አረቄውን ያጋባል። ጎልያድ እና ሌሎች ስማቸውን የማላውቃቸው ሲቪልና ወታደራዊ ባለስልጣናትም ነበሩ። አበበ ገረሱም የጄኔራሎቹ ገንዘብ ያዥና በዝርፊያውም አስፈፃሚ ምስጢረኛቸው እንደመሆኑ ከአካባቢው አይጠፋም። እኔም አለሁ...

የጄኔራሎቹ ግጥሚያ አበቃ። ጄኔራል ሃይሌ አሸነፈ። ሃይሌ ደስ ብሎት እንደ ደወል ስቆ ሲያበቃ፣

"አሸነፍኩህ!" አለው።

ሳሞራ በጣም ሲናደድ አየሁት። ሳሞራ ምናልባት በሃይሌ የስላቅ ሳቅ ሳይበሳጭ አልቀረም። ሲቋሰሉ ባጅተዋል። በአሽሙር መጠራረቡን ተላምደዋል። ተናንቀዋል። እና ሳሞራ እንዲህ አለው፣

"አላሸነፍከኝም!"

"ምን ማለትህ ነው? ተሸንፈሃል!"

"አንተ መቼም ቢሆን እኔን አታሸንፈኝም! ትናንትም አላሸነፍከኝ! ዛሬም አላሸነፍከኝ! ነገም አታሸንፈኝም!"

ሃይሌ አሽሙሩ ገብቶት እንዲህ ሲል መለሰ፣

"ባለጌ ነህ! የምትናገረውን አታውቅም!"

በዚህ ጊዜ ሳሞራ ለጠብ ተጋበዘ።

ቦክስ ሊገጥም እጅጌውን እየሰበሰበ ሲጠጋው አባዱላ በፍጥነት መሃል ገብቶ ሳሞራን ያዘው። ሌሎች ከፍተኛ መኮንኖች ሃይሌን ያዙት። ባንድ አፍታ ግርግር ሆነ። የሽጉጥ ድምፅ እየጠበቅሁ ነበር።

አባዱላ ሳሞራን እንዲህ ሲለው ሰማሁ፣

"የተናገርከው ልክ አይደለም!"

ሳሞራ በንቀት መለሰለት፣

"አንተም ሰው ሆነህ እኔን ትናገራለህ? ፈርሳም!!"

ይህን በመስማቴና በማየቴ በጣም ደንግጬ እንደነበር





አስታውሳለሁ። ከግልግሉ በሁዋላ በጉዳዩ ላይ ግምገማ እናድርግ ተባብለው የመኮንኖችን ክበብ ለቀው ተያይዘው ወጡ። በሶስተኛው ቀን ሳሞራና ሃይሌ እንደገና ከረንቦላ ሲጫወቱ አገኘሁዋቸው። አባዱላም ቆሞ የሳሞራ ደጋፊ ሆኖ ጨዋታውን ያዳምቅ ነበር። አዬ አባዱላ!? ሳሞራ ልክ ብሎታል!

# - 14 -

# ፃድቃንና ፆረና

ምን ጠቀመው ቃየል - የመሳሪያ ቋንቋ፣
ሰጠመ ጠፋ እንጂ - ባቤል ደም አረንቋ፣
መኢኑም አባተ - ሰመረ መረሳ፣
አባንግ አብዱል ከሪም - ጋቸኖ ቶሎሳ፣
አብረኸት ምንትዋብ - ኛዳከም ጋዲሴ፣
በላህ በነብዩ - በሶስቱ ስላሴ፣
ሰይፉም ዶማ ይሁን - ሞርተሩም አንካሴ፣

(ግጥም - ሃይለመለኮት መዋእል)

"እንደምን አደርክ ኮሎኔል?"

"ሰላም ላንተ ይሁን ጋዜጠኛው?"

"ቀጠሮ በማክበርህ አመሰግናለሁ"

"ወታደር አይደለሁ መቸስ?"

"እንግዲህ ወደ ጉዳያችን እንዝለቅ። 'ጄኔራል ፃድቃንና የፆረና ውጊያን በተመለከተ አጫውትሃለሁ' ብለኸኝ ነበር። ከየት ብንጀምረው ይሻል ይሆን?"

"ከመሃሉ መጀመር ሳይሻል አይቀርም። ያየሁትንና የሰማሁትን እንደወረደ ላውጋህ። ፀሃፊው አንተ ነህና እንደሚሆን ታደርገዋለህ..."

"መልካም ወንድሜ። አንተ እንዳመጣልህ ተናገር። እኔ ያንን ወስጄ ለታሪክ ተረካቢው ትውልድ አደርስልሃለሁ።"





* * *

"...ወያኔ ወደ ኤርትራ ጦርነት የገባው 10 ክፍለጦሮች ይዞ ነበር" ሲል ጀመረ። እናም ቀጠለ፣

"...ከዚህ ውስጥ አንዱ ሜካናይዝድ ክፍለ ጦር ሲሆን፣ አንድ ተጨማሪ ኰማንዶ ብርጌድም ነበር። በ1991 ጦርነቱ ሲጀመርም ይህ የሰራዊት ሃይል በአራት ግንባሮች ነበር ለማጥቃት የተዘጋጀው። ቡሬ፣ ዛላንበሳ፣ ፆረና እና ባድመ ግንባሮች ላይ ማለት ነው።

በ1991 ላይ የተደረገው የመጀመሪያው ውጊያ የተበላሸና በጣም አሰቃቂ ነበር። የጦር መኮንን ሆነህ እንደ ባለ ሙያ ስታየው ውጊያው በጥቅሉ የሙያ ብቃት ያልታየበት አሳፋሪ ጦርነት ነበር ማለት ይቻላል።

ያ ሁሉ ዜጋ ያለቀበትና ያ ሁሉ የአገር ሃብት የወደመበት ጦርነት ከጦርነት አመራር ችግር መሆኑ በግልፅ እየታወቀ አንድም የጦርነቱ መሪ ተጠያቂ ሳይሆን እንደሁ መቅረቱ በጣም ያሳዝነኛል። ይልቁን በምርጫ 97 'ቅንጅትን አልተዋጋችሁም። የአመለካከት ችግር አለባችሁ' በሚል ከጦርነቱ በላይ ትኩረት ተሰጥቶ ነበር። ከጄኔራል መኮንን እስከ ተራ ወታደር 20,000 የሚገመት መለዮ ለባሽ ያለሃጢአቱ ታስሮ ተባሮአል። ከሃላፊነቱ እንዲወገድ ተደርጎአል።

አንተ የፃፍከው "የጋዜጠኛው ማስታወሻ" ላይ የሰፈረውን እንደ ምንጭ ብንጠቀምበት እንኳ፣ በጃንሆይና በደርግ ዘመን ኤርትራ ላይ ውጊያ ተደርጐ የተሰዋው ዜጋችን ቁጥር ከ250 ሺህ እስከ 300 ሺህ ይደርሳል። ከዚህ አንፃር ወያኔ በአንድ አመት ውስጥ ኤርትራ ላይ ያስፈጀው የወታደር ቁጥር በጣም አሳፋሪ ነው። ከመከላከያ የሰው ሃይል አስተዳደርና ልማት መምሪያ ሰነዶች ያገኘሁት መረጃ እንደሚያሳየው፣ በጠቅላላ በኢትዮ-ኤርትራ ውጊያ 98,700 ወታደር ሲሞትብን፣ 194,300 ቁስለኛ ተረክበናል። ከኦርዲናንስ እዝ ያገኘሁት መረጃ ደግሞ መጀመሪያ ለውጊያ ከተዘጋጀው ከባድ መሳሪያ $^2/_3$ኛው መውደሙን ነግረውኛል። ይህንን ትርጉም አልባ ጦርነት የመሩት መሪዎች ሰአረ መኮንን፣ ሳሞራ የኑስ፣ ዮሃንስ ገብረመስቀል፣ ታደሰ ወረደ፣ ኳርተር (አብርሃ ወልደማርያም) ብርሃነ ነጋሽ የተባሉት ጄኔራሎች ናቸው። የጦርነቱ የማእከላዊ

እዝ አባላት ደግሞ መለስ ዜናዊ፣ ስዬ አብርሃ፣ ተወልደ ወልደማርያም፣ አለምሰገድ ገብረአምላክ፣ ተፈራ ዋልዋ፣ ፃድቃን ገብረትንሳኤ እና ክንፈ ገብረመድህን ነበሩ።

የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ሰነድና መረጃ ገና ታሪክ ፀሃፊዎች እጅ አልገባም። ወደፊት ብዙ አስገራሚ ታሪኮችን ልንሰማ እንችል ይሆናል። በ1991 የተካሄደውን የመጀመሪያ ዙር ጦርነት እንኳ ብናይ በጣም መሰረታዊ የሆኑ ወታደራዊ ስህተቶችን በቀላሉ ማውጣት እንችላለን።

የቡሬ ግንባር ላይ ታደሰ ወረደ ተመደበ።

የተሰጠው ትእዛዝ አሰብን ከያዘ በሁዋላ የቀይ ባህርን ዳርቻዎች እያጠቃ፣ ምፅዋን እንዲቆጣጠርና እዚያው ሆኖ ቀጣዩን ግዳጅ እንዲጠባበቅ ነበር።

ፆረና ላይ አብርሃ ወልደገብርኤል፣ (በቅርብ ፃድቃን እየተከታተለው) ዛላንበሳ ደግሞ ብርሃነ ነጋሽ ነበሩ።

ሁለቱም በየአቅጣጫው አጥቅተው ሰገነይቲ ላይ በመገናኘት አንድ ግንባር እንዲፈጥሩና በአንድ ኮማንድ ስር በመደራጀት አስመራ እንዲገቡ ታዘዙ።

ባድመ ላይ ሰአረ መኮንንና ዮሃንስ ገብረመስቀል፣ እንዲሁም አበባው ታደሰ (በቅርብ ሳሞራ እየተከታተላቸው) ተሰየሙና ቆላማውን የኤርትራ ክፍል ሙሉ በሙሉ እንዲቆጣጠሩ ተነገራቸው።

ለዚህ እቅድ የአሸዋ ገበታ በየአካባቢው ተዘጋጅቶ ያን መሰረት ያደረገ ሰፋፊ ልምምዶች ተደርገዋል። የጦርነቱ እቅድም በየደረጃው ተነግሮአል። በእቅዱ ላይ ታዲያ ብዙ አከራካሪ ጉዳዮች ተነስተው ነበር። ለምሳሌ አዲግራት ላይ በተዘጋጀው የአሸዋ ገበታ ልምምድ ላይ የ23ኛ ክፍለ ጦር አዛዥ የነበረው ኰሎኔል በርሄ ገብረማርያም (ቅፅል ስሙ በርሄ ሻእቢያ)፣

'ኤርትራን የመውረር እቅድ ፖለቲካዊ ኪሳራ አያስከትልብንም ወይ? ሰራዊታችንስ የመዋጋት ፍላጐት እንዴት ይኖረዋል? እንዴትስ ማሳመን ይቻላል? በትክክልስ ውጊያውን በተባለው መሰረት ማካሄድ እንችላለን ወይ? እቅዱን እንደገና ብታዩት ጥሩ ነው' የሚል አስተያየትና ጥያቄ አነሳ።

ጄኔራል ፃድቃንና ወዲ መድህን የሰጡት መልስ፣

'ሻእቢያን ካላጠፋን እኛ መኖር አንችልም። የሻእቢያ





ሃይል ደካማ ነው። የኤርትራ ኢኰኖሚ ጦርነቱን መሸከም አይችልም። በተኩስ ሃይልም የበላይነት አለን። ይህ ውሳኔም የመንግስት ውሳኔ በመሆኑ ማንም ሊያደናቅፈው አይችልም' የሚል ነበር።

በአሸዋ ገበታው ዙሪያ የነበሩት የበታች አዛዦች፣ 'እቅዱ ሊሳካ አይችልም' የሚል ጥርጣሬ ነበራቸው። አሸዋ ገበታው ላይ የምናየውን፣ በተግባር መሬት ላይ በትክክል መፈፀም የመቻላችን ጉዳይ ሚዛኑን ያልጠበቀ ነበር። ይህ የጥርጣሬ ጥያቄ በባድመና በቡሬ ግንባሮችም ተነስቶ የነበረ ሲሆን፣ እንደ አዲግራቱ ውይይት፣ 'ውሳኔው የመንግስት ነው' በሚል ነበር የተዘለለው።

ጦርነቱ ተካሄደ።

በባድመ ግንባር ነበር የተጀመረው። ማጥቃቱን የጀመሩት ሶስት ክፍለ ጦሮች ከፍተኛ ጉዳት ስለደረሰባቸው፣ 20ኛው ሜካናይዝድ ክፍለ ጦርና አንድ ኰማንዶ ብርጌድ ተጨምሮ፣ ሌሎች ሁለት ክፍለ ጦሮች ታክለው በድጋሚ ተሞከረ። ከፍተኛ ሰብአዊና ማቴሪያላዊ ጉዳት ደርሶብን እቅዱ ሳይፈፀም ቀረ።

በባድመ ውጊያ በእቅዱ መሰረት መሄድ እንዳልተቻለ እየታወቀ፣ በፆረና በኩል ውጊያው እንዲቀጥል ፃድቃን አዘዘ።

የውጊያው እቅድ መግለጫ የተሰጠው እንፋራ በተባለ ቦታ ላይ ነበር። ፆረና ላይ ልዩ ዝግጅት ተደርጐ ነበር። 12,000 ያህል የትግራይ ሚሊሺያ፤ ከ5,000 በላይ አግላይ እንዲሁም ስንቅና ጥይት አቀባይ፤ በሺህዎች የሚቆጠሩ አህያና ፈረስም ለዚሁ ጦርነት ተሰልፈው ነበር። ለአንድ ሳምንት ያህል ከፍተኛ የጭንቀት ሙከራ ቢደረግም በዚያች ጠባብና ሙት መሬት የተሰለፈው ያ ሁሉ ንብረት፣ መሳሪያ፣ ሚሊሻና አግላይ፣ አህያና ፈረሶቹ ሳይቀር አንድ ላይ ረገፉ።

የ20ኛው ግዙፍ ሜካናይዝድ ሃይል እግሪ መከል ላይ አመድ ሆኖ ቀረ። ታንኰቹና ተሽከርካሪዎች በሙሉ አረሩ። ሻእቢያ በቀላሉ ከዛላንበሳ፣ ከአዲኳላና ከማይአይኒ አቅጣጫዎች በተጠመዱ መድፎች ሰራዊታችንን ተቀበለው። ይህ የጀግንነት ጉዳይ አይደለም። የኛ የጦር መሪዎች ወታደራዊ ቴክኒክ ከአለማወቅና ከብቃት ማነስ የመጣ ነበር። ሰራዊታችን እንዳለ ገብቶ ረገፈ። ከዚህ እልቂት የተረፉት ወደ ሁዋላ ሸሽተው ገርሁ

ስርናይ እና እንትጮ፣ አድዋ ገቡ። ለአንድ ሳምንት የተሞከረው ውጊያ በከፍተኛ ኪሳራ ከተደመደመ በሁዋላ የጦርነቱ አዛዥ የነበረው ጄኔራል ፃድቃን በወቅቱ ማዘዣ ጣቢያ ከነበረችው እንፋራ ላይ ስብሰባ ጠራ።

ፃድቃን ስብሰባውን ሊጀምር ሲል እንባው ቀድሞት ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። ሁሉም ተሰብሳቢ ተያይዞ መላቀስ ሆነ።

እንፋራ የለቅሶ ቦታ ሆነች።

ፃድቃን በመጨረሻ እንደ ምንም ራሱን ተቆጣጥሮ ከተረጋጋ በሁዋላ ተሰብሳቢውንም ለማረጋጋት ሞከረ። እንዲህ ሲልም ተናገረ፣

'እስካሁን ብዙ ጦርነቶችን መርቻለሁ። ብዙ ውጊያዎችንም ተዋግቼያለሁ። አይቻለሁ። ሰምቼያለሁ። እንዲህ አይነት መጥፎ ሁኔታ ግን ገጥሞኝ አያውቅም'

የስብሰባው አላማ የጦርነቱን ሁኔታ ገምግሞ መፍትሄ ለመፈለግ የታሰበ ነበር። በመሆኑም ጦርነቱ ሁለት መሰረታዊ ችግሮች እንዳለበት ተሰብሳቢው ገመገመ።

'ከቦታው አስቸጋሪነት አኳያ የውጊያ እቅዱ ስህተት ነበር። ቦታው ለመከላከል ለጠላት ምቹ ሲሆን፣ ለወገን ጦር ማጥቃት ምቹ አልነበረም። በቂ ዝግጅት አልነበረንም። በቂ የሰው ሃይልና የተኩስ አቅም አልነበረንም። በጠላት ላይ የነበረን ግምገማ የተሳሳተ ነበር። ጠላት የመሬቱን አመቺነት ተጠቅሞ ተኩስ እንደፈለገ ማዘዋወር ችሎአል። ጠላት በቂ የሰው ሃይልና የውጊያ ቁመና ይዞ ነበር' ተባለ።

ወደ ዝርዝር ጉዳይ ሳይገባ፣ ግምገማው በዚሁ ተዘጋ። ይህን መነሻ በማድረግም ሌላ ውሳኔ ተወሰነ።

*'...በዛላንበሳና በቡሬ ተይዞ የነበረው የማጥቃት እቅድ እንዲሰረዝ። የተኩስ አቅምን ለማጠናከር ከአየር ሃይልና ከምድር ሃይል ኮሚቴ ተቋቁሞ በጄኔራል አበበ ተክለሃይማኖት መሪነት መሳሪያዎች እንዲገዙ። ከፍተኛ የሰው ሃይል ምልመላ ተደርጐ በስፋት ስልጠና እንዲካሄድ። ይህን የምልመላ ስራ ደግሞ በረከት ስምኦን እንዲመራው። የስልጠና ስራውን አባዱላ እንዲከታተለው። አሁን ያሉን 12 ክፍለጦሮች በአጭር ጊዜ ወደ 30 ክፍለጦሮች እንዲያድጉ። ሰራዊቱ ማገገም እንዲችል በመከላከል ብቻ እንዲቆይ...'*





እነዚህ ውሳኔዎች ከጦርነቱ ማእከላዊ እዝ መወሰናቸውን ፃድቃን እንፋራ ላይ ከክፍለ ጦር አመራር በላይ ላለን አዛዦች ጠርቶ ውሳኔውን ነገረን።

በዚህ መመሪያ መሰረት እንድንዘጋጅም ተነገረን።

በዚህ ውሳኔ መሰረትም ለአንድ አመት ያህል ዝግጅት አደረግን። በ1992 ሚያዝያ ወር ላይም አጠቃላይ የጦርነት እቅድ ወጣ። ፃድቃን፣ ጀቤ እና አባዱላ በመቀሌ ከተማ የምክር ቤት የስብሰባ አዳራሽ ሰብስበው እቅዱን ገለፁልን።

*(የ1992 እቅድ ከ1991 እቅድ የሚለየው ነገር ነበረው። በ1991 ኤርትራን ጠቅልሎ የመያዝ ፍላጐት ነበረ። በ1992 ግን 'አቅማችን የፈቀደውን ያክል እንዋጋለን' የሚል ሆነ። በ1991 በነበረው እቅድ፣ 'ወደ ኤርትራ መሬት ስንገባ የኤርትራን ሃብትና ንብረት እናወድማለን። ህዝቡም የሻእቢያ ደጋፊ ስለሆነ ልናምነው አይገባም' የሚል ነበር። በ1992 እቅድ ይህ በግልፅ አልተቀመጠም። 'ህዝቡ የሻእቢያ ደጋፊ ስለሆነ ከፍተኛ ጥንቃቄ እናደርጋለን' የሚል አረፍተነገር ግን ነበረበት።)*

በ1992 ሚያዝያ መጨረሻ ግንቦት መጀመሪያ ላይ ጦርነቱ በባድመ ግንባር ተጀመረ። በውጊያው ከፍተኛ ጉዳት ቢደርስብንም እስከ ባረንቱ መዝለቅ ቻልን። ሻእቢያ ሰራዊቱን ይዞ ስልታዊ ማፈግፈግ እያደረገ ስለሆነ፣ የጠላት ኪሳራ አነስተኛ መሆኑን፣ ይልቁን ወደ መግደያ ወረዳ እየሳበን መሆኑን አዛዦች ሃሳባቸውንም ለፃድቃን ያቀርቡ ነበር። በአንፃሩም ወደ ኤርትራ ምድር እየዘለቅን በገባን ቁጥር ከዋና ማዘዣችን እየራቅንና የድርጅት ድጋፍ እያጣን እንሄድ ስለነበር፣ የሚያዋጣን አማራጭ ወደ ሁዋላ መመለስ ሆነ።

ከባድመ ግንባር ውጊያ በኋላ የባድመ የውጊያ ችግር ሳይገመገም በችኮላ በራማ፣ በያረና እና በዛላንበሳ ግንባሮች በተመሳሳይ ጊዜ ማጥቃቱ ተጀመረ።

የነበረው ግምገማ፣

'በባድመ ውጊያውን ቀድመን ስንጀምር ሻእቢያ ብዙ ሃይል ወደ ባድመ ሊያመጣ ስለሚችል ሌሎች ግንባሮች በሰው ሃይልና በመሳሪያ አቅም ይሳሳሉ' የሚል ነበር።

እንደታቀደው ግን አልሆነም።

በመሆኑም በእነዚህ ሶስት ግንባሮች በተመሳሳይ ሰአት የተጀመረው ውጊያ በእቅዱ መሰረት ሳይሳካ ሲቀር ባጭር ጊዜ ውስጥ ሌላ የውጊያ እቅድ ተዘጋጀ።

'በቡሬ ግንባር  አሰብ ከተማን መያዝ ከቻልን የሞራል ግንባታ እናገኝበታለን' የሚል አሳብ መጣ። አሰብን ለመያዝ ያደፋፈረው ዋናው ምክንያት፣

'ጠላት በቡሬ ግንባር እንጠቃለን ብሎ ስለማይገምት በቂ ዝግጅት አይኖረውም። ከጅቡቲ መንግስት ጋር ስለተነጋገርን ሃይላችንን በቀላሉ በጅቡቲ መሬት ማስጠጋትና ለውጊያም ምቹ ሁኔታ መፍጠር እንችላለን' የሚል ነበር።

በዚሁ መነሻና ገለፃ ላይ በርካታ ጥያቄዎች ተነስተው ነበር። ለምሳሌ የ36ኛ ክፍለጦር አዛዥ ኰሎኔል መሃመድ ኢሻ፣ የ39ኛ ክፍለጦር አዛዥ ኰሎኔል ወንደሰን ተካ፣ የ14ኛ ክፍለ ጦር አዛዥ ኰሎኔል ወዲ አባተ ያነሱት ጥያቄ፣

'እስካሁን ባደረግናቸው ውጊያዎች ሁሉ ሻእቢያን ከያዘው ምሽግ እንዲያፈገፍግ አደረግነው እንጂ፣ በእቅዳችን ያስቀመጥነውን ተግባራዊ አላደረግንም። ለዚህም ብዙ ኪሳራ ከፍለንበታል። በኪሳራው ምክንያትም የጦሩ ሞራል መጥፎ ሁኔታ ላይ ይገኛል። የቡሬ አየር ጠባይም ሆነ መሬቱ በጣም አስቸጋሪ ነው። በቂ የሎጀስቲክ ዝግጅት የለንም። ድንገተኛ ድል እናገኛለን ብለን ድንገተኛ ሽንፈትም ሊከተል ይችላልና ቢታሰብበት? ስለ ጠላት እስካሁን የተናገራችሁት ሁሉ ልክ አልሆነም። እና አሁንስ ምን ያህል ትክክል ናችሁ?' የሚል ጥያቄ አንስተው ውይይት አደረግን።

በመጨረሻ አሳማኝ ነጥቦች ባይቀርቡም፣ የማይቀየር የመንግስት ውሳኔ ነው ተብሎ 'አሰብን መያዝ' የሚለው እቅድ ፀደቀና ውጊያው ተካሄደ። ውጊያው ለአምስት ተከታታይ ቀናት የተካሄደ ቢሆንም፣ እንዲያውም ከሌሎች ውጊያዎች ሁሉ የከፋ ውጊያ ሆነ። ሰራዊታችን ከፍተኛ የሰው ሃይል የከፈለው በቡሬ ግንባር ነበር። ሻእቢያ በበርካታ ውጊያዎች የሚጠቀምበትን ወደ መግደያ ቦታ እያስገባ የመምታቱን ስልት ቡሬ ላይም ስለ ደገመው ከፍተኛ እልቂት ተቀብለን አሰብን የመያዙ እቅድ ከሸፈ...

"....የኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ሲነሳ ከሁሉም እንቆቅልሽ





የሚሆንብኝ የፆረናው ውጊያ ነው። እንደገለፅኩልህ ከፍተኛ መስዋእትነት ከፍለንበታል። የውጊያ እቅዱ ስህተት ነበር ወይስ ሆን ተብሎ የተፈፀመ? ለሚለው ጥያቄ ግን ገና ምላሽ አልተገኘም። ስህተት ከነበረ 'የማን ስህተት?' 'ማነው ተጠያቂው?' ለእነዚህ ጥያቄዎች አንድ ቀን ምላሽ መገኘቱ አይቀርም..."

*(በ1993 የህወሃት ክፍፍል ወቅት መለስ ተሸንፎ ቢሆን ኖሮ በፆረናው እልቂት ሊወነጅሉት ተዘጋጅተው እንደነበር የጨረፍታ ወሬዎች አሉ። ወዲ አሸብር ላይ የተሞከረው ጥቃት መለስን ለማዳከምና ለመምታት ያለመ ነበር ብለው የሚያምኑም አሉ። በእርግጥም የፆረናው ውጊያ ሳይገመገም ተደፋፍኖ ቀርቶአል።*

*በወቅቱ ግን የግድ አንድ አካል ተጠያቂ ማድረግ ስለነበረባቸው፣ አምስት ኦሮሞ መኮንኖች እንዲወነጀሉ ተደርጎአል።*

*"የውጊያውን እቅድ በኦነግ በኩል ለሻእቢያ አሳልፋችሁ ሰጥታችሁዋል" የሚል  ክስ ቀርቦባቸው፤ ኮሎኔል ብራ የተባለች ሴት ጢጣ ካምፕ ውስጥ ስታስገርፋቸው ሰነበተች።*

*ኦሮሞ መኮንኖቹ ድብደባው ሲበረታባቸው፣ "አድርገናል፤ ፈፅመነዋል" ብለው አመኑ። "ግንኙነታችሁ በማን በኩል ነበር?" ተብለው ሲጠየቁ፣ "አባዱላ" ሲሉ መለሱ።*

*አባዱላ ግን ወያኔን እንደማይከዳ ይታወቅ ስለነበር ምርመራዋ እዚያው ላይ ቆመ።*

*በኮሎኔል ብራ ግርፊያ ከተፈፀመባቸው ከፍተኛ መኮንኖች አንዱ በድብደባ የዘርፍሬው የተኮላሸ ሲሆን፤ ሌላው ፓራላይዝድ ሆኖአል። መኮንኖቹ በህይወት ያሉ ሲሆን፤ የወያኔ ስርአት ለሚፈፅመው አሰቃቂ የመብት ጥሰት ህያው ምስክር ሆነው የተፈፀመውን ሁሉ ህግ ፊት የሚገልፁበት እለት ይመጣ ይሆናል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። እነዚህ ኦሮሞ መኮንኖች ላይ የደረሰው አሰቃቂ ግፍ "በፆረናው እልቂት ማን ይጠየቅ?" የሚለውን ጥያቄ ከህወሃት ዝሆኖች ሰፈር ለማውጣትና አጀንዳውን ለመዝጋት እንጂ መኮንኖቹ ንፁህ መሆናቸውን ፃድቃን፣ ስዬ እና መለስ ያውቁ ነበር።)*

- 15 -

# ያልተፃፈ መፅሃፍ

የዋሁ ገበሬ............
ቤተክስያን ይሄዳል - ዘወትር እሁድ፣
ወዶ ነው በግድ?
ይሰማል ሲሰበክ - የክርስቶስ ትምህርት - በሄደ ቁጥር፣
'ድሆች ብፁእ ናቸው!' የሚባል ነገር፣
የመሬቱ መንግስት - ባይሆነውም ለሱ፣
የሰማዩን መንግስት - እንድትወርሰው ነፍሱ፣

................

ግና አንዳንዴ ደግሞ፣
ከቤተክስያን ሄዶ፣
ሲያዳምጥ አርፍዶ - ስብከተ ወንጌል፣
ሰምቶ ይመጣና - ተቃራኒ ትምህርት - የሆነ አንጎል፣
'ይጨመርለታል - ላለው' የሚል ቃል፣
ለጊዜው መንፈሱ ይበጠበጣል...

(ግጥም - ዮሃንስ አድማሱ)

*ኢትዮጵያ ማለት ወሎ ናት...*

*የወሎ ማእከል ደግሞ ደሴ።*

*ኮምቦልቻ፣ ወልዲያ፣ ባቲ፣ ጢጣ፣ አምባሰል፣ ሃይቅ ደሴን በሩቅና በቅርብ ከበዋታል። የደሴ ልጅ የሆነ ሁሉ ለቦርከና ወንዝና ለጦሳ ተራራ ልዩ ትዝታ አለው። በኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛት ውስጥ እንደ ወሎ ባህል፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖትና ወግን ያዋሃደ ከቶውንም አይገኝም።*

*ወሎ ማለት ኢትዮጵያ ማለት ናት።*

*ወሎ የጥበብ መፍለቂያ። የባህላዊ ሙዚቃችን ምንጭ።*





*የአምባሰል፣ የባቲ፣ የአንቺ ሆዬ፣ የትዝታ፣ ቅኝቶች ሃገር። ወሎ ከበላይ ዘለቀ ጀምሮ ስንቱን አፍርታዋለች? በላይ ዘለቀ ቂልጡ የኦሮሞ፣ የአማራ፣ የክርስትያንና የእስላም ቅልቅል በመሆኑ በላይ ከማንም በላይ ኢትዮጵያዊ ነው። ወሎ ስንቱን አፍርታዋለች?*

*የወይዘሮ ስህን ትምህርት ቤት ያፈራቻቸውን የፖለቲካና የሳይንስ ምሁራን ቆጥሮ መዘለቅ አይቻልም። ሙዚቃ፣ እውቀት፣ ውበት፣ ጀግንነት፣ እንደ ምንጭ የፈለቀበት ቅዱስ ምድር..."*

ከላይ ያለውን ትረካ ያገኘሁት ካልታተመ የአንድ ሽማግሌ ረቂቅ ፅሁፍ ውስጥ ነው። የሰውየውን ስም አልነግራችሁም። ያልታተመውን የአባቱን ዲያሪ አሳልፎ ለሰጠኝ ልጃቸው ቃል በገባሁት መሰረት "አባትየው" አሊያም "ሽማግሌው" እያልኩ አወጋችሁዋለሁ። በቅድሚያ ግን ይህ ያልታተመ ጥራዝ እንዴት እጄ ላይ ሊገባ እንደቻለ በጨረፍታ ልጠቁም።

* * *

አንድ ማለዳ የማላውቀው ሰው በጂሜይል አድራሻዬ በኩል ብቅ ብሎ ያዋራኝ ጀመር። እንዲህ ሲል ፃፈ፣

"መፅሃፍህን አድንቄያለሁ"

"አመሰግናለሁ" ስል ምላሽ ሰጠሁ።

"አንድ ነገር ላማክርህ ፈልጌያለሁ። በskype መነጋገር እንችላለን?"

"ይቻላል" አልኩና አድራሻዬን ሰጠሁት።

ደወለና እንዲህ አለኝ፣

"እኔ የለንደን ከተማ ነዋሪ ነኝ። አባቴ በህይወት የለም። 2001 መግቢያ ላይ ነው ያረፈው። ሃዘን ለመድረስ አዲሳባ ሄጄ ሳለ የአባቴን ዲያሪ አገኘሁና ይዤው መጣሁ። 73 ገፆች ናቸው። አንዳንድ ምስጢሮች አሉበት። ይህንን ነው ላማክርህ የፈለግሁት። ምናልባት አንተ ልትጠቀምበት ከቻልክ ብዬ ነው..."

"ላክልኝና አየዋለሁ" አልኩ።

እያቅማማ እንዲህ አለ፣

"ከመላኬ በፊት ግን እንድንነጋገር እፈልጋለሁ። የአባቴ ማስታወሻ ከታተመ ወያኔ ዝም ብሎ አይተወኝም። ለኔ አደገኛ ነው። ስለዚህ ስለ ክፍያ መነጋገር እፈልጋለሁ..."

ያልጠበቅሁት ስለሆነብኝ አሰብኩና እንዲህ መለስኩ፣

"የሞቱ ሰዎችን ማስታወሻ ደብተር ገዝቼ አላውቅም። ምናልባት ሌሎች የሚገዙህ ሰዎች ካሉ አፈላልግ።"

"ማን ሊገዛኝ ይችላል?"

"ምናልባት አዲሳባ ያሉ የግል ጋዜጦች"

"ለጋዜጦች የሚሆን ፅሁፍ አይመስለኝም።" አለ ርግጠኛ ባልሆነ ድምፀት፣ "...አንተ በሚቀጥለው መፅሃፍህ ብትጠቀምበት ይሻላል። አባቴ ወያኔን የሚመለከቱ፣ የደርግና የጃንሆይንም ምስጢሮች ፅፎአል። ላንተ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል..."

"ስለ ገንዘብ እያሰብክ ከሆነ ሌላ ሰው ፈልግ!" አልኩት።

"ለገንዘብ ብዬ አይደለም" ካለ በሁዋላ አያይዞ እንዲህ ሲል አከለበት፣ "...ችግሬን ብትረዳልኝ ደስ ይለኛል። እዚህ ለንደን በመንግስት ድጎማ ነው የምኖረው። አምስት አመት ያለ ስራ ነው ቁጭ ያልኩት። በዚያ ላይ አልተማርኩም። እንደ ዛፍ ማደግ ብቻ ሆኛለሁ። ለአንዳንድ ነገሮች ትንሽ ገንዘብ ባገኝ ብዬ ነው።"

"እዚያው አካባቢ ገዢ ለምን አታፈላልግም ታዲያ?"

"ሞክሬ ነበር። አላገኘሁም። ላንተ ብልክልህና ጠቃሚ ሆኖ ካገኘኸው ክፍያውን አስበህ ትሰጠኛለህ..."

"ወንድሜ!" አልኩት "... የገንዘቡን ነገር እርሳው"

"ዲያሪው ግን ብዙ ምስጢር ይዞ ነበር"

"ይዘቱን እስኪ ባጭሩ ንገረኝ?" አልኩት።

እንዲህ አለ፣

"አባቴ ደሴ ወይዘሮ ስህን ትምህርት ቤት ነው የተማረው። ብዙ ታዋቂ ሰዎች ጓደኞቹ ነበሩ..."

"እነማን ለምሳሌ?"

"ኢሳይያስ አፈወርቂና ነጉደ ጉበዜን ጠቅሶአቸዋል። ዋለልኝ የሚባል ጓደኛም ነበረው። በአሉ ግርማ 'ኦሮማይ' የተባለ መፅሃፉ ላይ 'ቢሮክራሲ' ሲል የጠቀሰው ሰውም ጓደኛው ነበር። ስለ ወያኔ ብዙ ፅፎአል። ሙሉውን አላነበብኩትም። አለፍ አለፍ ብዬ ሳየው ግን ጠቃሚ ይመስላል..."





"ለምን አላነበብከውም?"

"ስጀምረው አባቴ ትዝታው እየመጣብኝ በቃ ተውኩት"

"Scan አድርገውና ላክልኝ" አልኩ።

"በቅድሚያ ትከፍለኛለህ?"

ትእግስቴ አለቀ፣

"ገንዘብ ከሆነ ፍላጎትህ በዚሁ እናቁም!"

የግንኙነት መስመሩን አቋረጥኩት። በዚያው ይቀራል ብዬ ገምቼ ነበር። ምሽት ላይ ጂሜይል ስገባ ቁጭ ብሎ ሲጠብቀኝ አገኘሁት፣

"የአባቴን ዲያሪ ልልክልህ ወስኛለሁ" ሲል ፃፈ። አያያዘናም ያንኑ የገንዘብ ነገር አከለበት፣ "...ካነበብከው በሁዋላ ራስህ አስበህ፣ መረጃውን አይተህ ትከፍለኛለህ"

መልስ ሳልሰጠው ዝም አልኩ።

ቀጠለና እንዲህ ፃፈ፣

"Scan አድርጌዋለሁ። አሁኑኑ ሳጥንህ ላይ ታገኘዋለህ።"

እንዳለውም አደረገው።

TOYOTA የሚል የንግድ ምልክት ያለበት አጀንዳ ላይ በጥሩ የእጅ ፅህፈት የተፃፉ 73 ገፆችን ላከልኝ።

በአንድ ትንፋሽ ጭልጥ አድርጌ አነበብኩት።

አንብቤ ስጨርስ ደስ የሚል ረጅም ሳቅ ሳቅሁ። በአባትየው የፅሁፍ ችሎታ ተደንቄ ነበር። በርግጥም የሽግግሌው የብእር አጣጣል የሰጠ ነበር።

ዳሩ ምን ያረጋል?

የልባቸውን አደራጅተው ለመተንፈስ አልቻሉም። ውስጥ ውስጡን እንደ ንፍሮ ተርገብግበው ተቀቅለው አልቀዋል። ስንቱ ይሆን እንደዚህ ችሎታውን የፍርሃት ጉድጓድ ውስጥ ቀብሮ በዚያው ያመለጠ?

እነዚያን 73 ገፆች ካነበብኩ በሁዋላ፣ "ያልተፃፈ መፅሃፍ" በሚል ርእስ አንድ መፅሃፍ ለመፃፍ ተመኘቼ ነበር። "ያልተፃፈ መፅሃፍ" አሪፍ ርእስ ነበረች። "ያልተመለሰው ባቡር" በሚል ርእስ ያሳተምኩትን መፅሃፍ ደረጄ ደስታ በዚህ ርእስ ነበር ሪፖርተር ጋዜጣ ላይ አፈር አባቷን ያበላት። የተመኘሁት ግን በዚህ ርእስ "በየቤቱ የታሸጉ ረቂቆችን ለፀሃይ የማብቃት አብዮት!" ማካሄድ አይነት ነበር።

ተከታታይ ጥራዞች።

ያልተፃፈ መፅሃፍ…

እርግጥ ነው፣ የአባትየውን 73 ገፆች "ልጠቀምባቸው አልችልም" ብዬ አስቤ ነበር። አባትየው ብዙ መረጃ የአንጐላቸው ዋሻ ውስጥ ቀብረዋል። ሊያወጡት ግን አልቻሉም። ይጀምሩትና ይተውታል። አንዳንድ ጊዜ ስጋት እየመጣ በመዶሻው ይወቅራቸዋል። ሌላ ጊዜ የፍርሃት ብርድ እንደ ደራጎን በጭራው በጥፊ ይወለውላቸዋል። አንዱን ምእራፍ እንኳ እንደልባቸው፣ ከልባቸው ሳይተነፍሱ፣ የተነፈሱትንም አደራጅተው ለፀሃይ ሳያበቁ ሞት "ዘልአለማዊ" ወደ ተባለው ሩቅ ሃገር ይዞአቸው ነጎደ።

የመጀመሪያዎቹ አምስት ገፆች ስለ ልጅነት ህይወታቸው የሚተርክ ነበር። ደሴ ላይ በድህነት ማደጋቸውን በጥሩ ብእር ገልፀውት ነበር። አልፎ አልፎም ከባለቤታቸው ጋር ያላቸውን አለመግባባትና የግል ምስጢራቸውን አስፍረዋል። ልጅየው ይህን አንቀፅ ያነበበው አይመስለኝም። የሚወዷቸውን አንዳንድ ግጥሞችና ጥቅሶችም ለማሰባሰብ ሞክረዋል። ራሳቸው የቋጠሯቸው ስንኞችም ነበሩ። የወይዘሮ ስህን ትምህርት ቤት ገጠመኞቻቸው ላይ ግን ልጅየው እንደጠቆመኝ ፋይዳ ያለው ነገር አላገኘሁበትም። ይልቁን በፖለቲካ ጉዳይ ላይ የሚሰጡት አስተያየት እና ገጣሚው ዮሃንስ አድማሱን በተመለከተ ያሰፈሯቸው ነጥቦች ትኩረቴን መሳብ ችለው ነበር። የአባትየው ማስታወሻ ከፊሉ ተጀምረው ያልተቋጩ፣ መያዣ መጨበጫ የሌላቸው ነበሩ። ሽማግሌው ሲፅፉ ቀን አይጠቅሱም። ቅደም ተከተል አይጠብቁም። ሲሻቸው እለታዊ ገጠመኞቻቸውን ያሰፍራሉ። ወደ ሁዋላ ተመልሰው የሚተርኩበት ቦታም አለ። የእጅ ፅሁፋቸው የተለያየ መሆኑ በተለያዩ ጊዜያት እንዳሰፈሯቸው ግንዛቤ ይሰጣል። ከባለቤታቸው ጋር ግንኙነታቸው መሻከሩን የሚገልፁ አንቀፆች ኑሮአቸው ችግር ላይ መውደቁን የሚጠቁም ነበር።

ቢሆንም የአባትየው ማስታወሻ ቀልጦ አልቀረም። ቅደም ተከተሉን ለማስተካከል ሞክሬና ጠለቅ ያለ የአርትኦት ስራ ሰርቼበት አንድ ቁራጭ ምእራፍ ለመሆን በቅቶአል። እንዳጀማመሬ "አባት" እና "ልጅ" እያልኩ አወጋለሁ። እነሆ! ያልተፃፈው መፅሃፍ።





* * *

"…መንፈሳችን እስኪቃጠል ድረስ ገጣሚው ዮሃንስ አድማሱ ንቁ እንድንሆን አድርጐናል። አንድ ቀን ማለዳ በአንደኛው የትምህርት ክፍለ ጊዜ ጋሽ ዮሃንስ ክፍል ውስጥ እንደገባ እንዲህ አለን፤

'መፅሃፍ ቅዱስ ላይ 'ድሆች ብፁአን ናቸው' የሚል ቃል አንብባችሁዋል? በሌላ ቦታ ደግሞ፣ 'ላለው ይጨመርለታል' የሚል ሰፍሮአል። እስኪ እነዚህን መርምሩ?'

ዮሃንስ አድማሱ ይህን ብሎን ሲያበቃ ከኛ ምላሽም ሳይጠብቅ በቀጥታ ወደ መደበኛ የማስተማር ስራው ገባ። በኔ በኩል የተቃጠለ ኰሚኒስት መሆን የጀመርኩት በዚህ እለት ሳይሆን አይቀርም…

ሌላ ጊዜ ደግሞ ጋሽ ዮሃንስ የውይይት ክለብ ስብሰባችን ላይ እንዲህ አለን፣

'ኢትዮጵያ ከአለም ሰልፍ ጭራ ነች። ቀኝ ሁዋላ ዙር ከተባለ ግን የአለም መሪ እንሆናለን። ስለዚህ ተስፋ አለን!'

በዚህ ንግግሩ በጣም ሳቅን።

ጋሽ ዮሃንስ አንዲት ድንቅዬ ድንክ ቡናአይነት ውሻ ነበረችው። እሷን አስከትሎ ሲሄድ እስካሁን በአይኔ ላይ ይታየኛል።

የዛሬው ዶክተር ሃይሉ አርአያ ያኔ የእንግሊዝኛ መምህራችን ነበሩ። በወቅቱ ዮሃንስ አድማሱን እንደ ተራማጅ እንወደው ነበር። መምህር ሃይሉ አርአያን ግን 'አድርባይ ነው' ብለን ስለምናስብ አንቀርበውም ነበር። ሃይሉ አርአያ ታማኝ የንጉሱ ጠባቂ ሆኖ ተመልምሎ ነበር። መምህር ሃይሉ የቋንቋውን ትምህርት ትራስ በማድረግ የJohn F. kennedyን የሽከላ እትም፣ በንግስ በአላቸው ላይ በነጩ ቤተመንግስት ያደረጉትን ንግግር ያስተምር ጀመር፣ My fellow citizen's of the world: ask not what America will do for you, but what together we can do for the freedom of man. እያለ መቀስቀሱን ተያይዞት ነበር። ጋሽ ዮሃንስ ሃይሉ አርአያን 'ነጭ አምላኩ' ይላቸው ነበር። ሳይጣጣሙ ተለያዩ።

በመጨረሻ ገጣሚው አባታችን አሰበ ተፈሪ ላይ ተገደለ። መጠጥ እንደገደለው የሚናገሩ አሉ። እኔ ይህን

አላምንም። የመንግስት ነጭ ለባሾች የሚጠጣው መጠጥ ውስጥ መርዝ ጨምረው ሳይገድሉት እንዳልቀረ ወሬ አለ..."

* * *

"...ጥላሁን ግዛው ወይዘሮ ስህን ከኛ ጋር የተማረው አንድ አመት ብቻ ሲሆን፣ ዋለልኝ ግን ሙሉውን High School ከኛ ጋር ነው የጨረሰው። ኢሳይያስ አፍወርቂም አንድ አመት ወይዘሮ ስህን ተምሮአል። ከዚያም ወደ አስመራ ተመለሰ። የኢሳይያስ አጐት በወቅቱ የደሴ አስተዳዳሪ ነበሩ። ነገደ ጐበዜም እንደ ኢሳይያስ ከኛ ይቀድም ነበር እንጂ፣ እሱም የስህን ግርፍ ነው። የነገደ አባት ጎበዜ ጣፈጠ ይባላሉ። ደራሲና የፖለቲካ ሰው ነበሩ። 'እስላማዊ አፍሪቃ' የሚል መፅሃፍ ፅፈው ነበር። በዚህ መፅሃፍ ምክንያት በቅጣት አምባሳደር ሆነው ወደ ሶቪየት ህብረት ተላኩ። የነገደ እህት ሃና ጐበዜ ትባላለች። በዚህ ሰሞን (ምርጫ 97ን ማለታቸው ነው) እና ጐሚዝን 'ሃና ጐበዜ' ይሏት የነበረው ከነገደ እህት ጋር እያመሳሰሉ ለመቀለድ ነበር። የነገደ ወንድም እያሱ ጐበዜ ኢንጂነየር ሆኖአልን ሰማሁ። የጅምናስቲክ መምህራችን ጋሽ አሸንፍ አበራ ነገደንና እያሱን 'አማች' ይሏቸው ነበር። ጋሽ አሸነፍ ቆንጆ እህት ያላቸውን ተማሪዎች 'አማች' የማለት ልምድ ስለነበራቸው እኛም መልሰን 'አማች' እንላቸዋለን። ኪሮስ ወልደስላሴ መሃንዲስ ሆኖ ሳኡዲ አረቢያ ይገኛል። አባቱ (ባራምባራስ) የወሎ ፈረስ የስምሪት ሃላፊ ስለነበሩ ወደ አዲስ አበባ ስንሄድ ነፃ የአውቶብስ ትኬት ይፈቅዱልን ነበር። የደመቱ ልጅ፣ ሰለሞን እንቋይ! እሱም የወይዘሮ ስህን ተማሪ ነበር። አክሱማይት የተባለች አንዲት ምስኪን መምህር እህት ነበረችው። ሰለሞን ለንደን እያለ የሻእቢያ ተባባሪ ደጋፊ ነበር። ደርግ ሲወድቅ ሻእቢያ በስጦታ ለወያኔ ሰጡት። ወያኔ ከሾሙት በሁዋላ ጉራ ቢጤ ይሞካክረዋል። ሁለት ጊዜ ደወለልኝ። ላገኘው አልፈለግሁም።

ወይዘሮ ስህን ስንቱን አፍርታዋለች?

ጌታቸው ዘሩፋኤል የሚባል ሰነፍ ተማሪ ነበር። አሁን አሜሪካን ሃገር ሳይንቲስት ሆኖአል። ድንቅ ነው። ተኮላወርቅ ሃጎስ እና ፍስሃፅዮን ተክኤም የስህን ተማሪ ነበሩ።

"ኦሮማይ" የተባለው መፅሃፍ ላይ በአሉ ግርማ፣ 'ቢሮክራሲ!' ሲል በኰድ የጠቀሰው አፈወርቂ ተወልደመድህን፣





ኰረም ነው ተወልዶ ያደገው። ታናሻችን ነበር። ቦርከና ወንዝ ላይ ዋና ያለማመድኩት እኔ ነበርኩ። polite እና unpredictable አይነት ልጅ ነበር። ሁዋላ የሻእቢያ ምልምል ሰላይ ሆኖ የደርግን የስለላ መዋቅር ለመበዝበዝ በቃ። በአሉ ግርማ እንደፃፈው አደገኛ ሰላይ ነበር። የሁዋላ ሁዋላ አሳደው ድሬዳዋ ላይ ያዙትና ረሸኑት።

ከብርሃነ መስቀል ረዳ ጋርም አንድ ላይ ነበርን። 'ብርሃነ' ብቻ ነበር ስሙ። እንደ አፄ 'ሃይለ ስላሴ' ለስሙ አጃቢ አስፈለገውና 'መስቀል' የምትለዋን ጨመረባት። ብርሃነ ረዳ ጠንካራ የማደራጀት ችሎታ የነበረው ጎበዝ ሰው ነበር። ምን ያደርጋል? ችኩል የሆነ ፍጡር። ቸኰላው ይዞት ጠፋ...

"...ከወይዘሮ ስህን ትምህርት ቤት እንዲህ ያሉ እሳት የላሱ ሰዎች ሊገኙ የቻሉት ለምን ይሆን? ቢባል አንድ ምክንያት ብቻ ሊኖረው አይችልም። ወቅቱ ራሱ የለውጥ ወቅት ነበር። በመላ አለም ኰሚኒስቶች የአብዮት ችቦ እየለኰሱ ነበር። ንጉሱም አርጅተው መምራት አቅቶአቸዋል። የመምህራኖቻችን ተፅእኖም ነበር። የአማርኛ መምህራችን ጋሽ ዮሃንስ 'የገደል ስር አጥንት' እና 'ተወርዋሪ ኰከብ' የተሰኙ ስነ ግጥሞችን በስነ ፅሁፍ ክበብ ውስጥ ያነብልን ነበር። በጥቅሉ ግን ጊዜው ራሱ የፖለቲካ ትኩሳቱ የፈላበት ዘመን ነበር..."

* * *

"...የዋለልኝ መኰንን መሞት ይፋ እንደሆነ ሰው ሳይሆን ተስፋ ራሱ የተገደለ ሆኖ እንደተሰማኝ ትዝ ይለኛል።

'የኢትዮጵያ ተስፋ ሞተ' አልኩ።

ማርታና ዋለልኝ ጓደኞቼ ሆነው ዘልቀው ነበር። ብዙውን ጊዜ መስቀል ራንዴቡ ይመጡ ነበር። ከእኔም ጋር እዚያ ነበር የምንገናኘው። ከፍቅራቸው ባላነሰ ጓደኛነታቸው የጠነከረ ነበር። ማርታ ጀግና ነበረች።

'ማርታ ለምን ለምን ሞተች?' የሚለው ጩኸታችን አሁንም ጆሮዬ ውስጥ አለ። ኢትዮጵያዊቷ አንጄላ ዴቪስ ለዋለልኝ የተተኰሰውን ጥይት በደረቷ ተቀበለችው። ዋለልኝ የሞተው የማርታን ደረት በስቶ ባለፈው ጥይት ተመትቶ ነበር። ከማርታ ጋር በተያያዘ ልቤን ከሰበሩት የዘመናችን ክስተቶች

አንዱ የኤርትራ መገንጠል ነው።

ወፈፌው መንግስቱ ጄኔራል አማን አንዶምን የገደለ ጊዜ ነበር ሁሉም ነገር የተበላሸው። ኤርትራንና ኢትዮጵያን መለያየት ማርታና ዋለልኝን መነጣጠል መስሎ ነበር የተሰማኝ። ወሎየው ዋለልኝና ኤርትራዊቷ ማርታ የፍቅርና የአንድነት ጀግኖች ነበሩ። አንድ ልብ ነበራቸው። ያም ልብ ኢትዮጵያዊነት ነበር። ዛሬ ባለ ሃምሳ ልብ ሆነናል። ጠላቶቻችን ከምድረ ገፅ ካላጠፉን አይተኙም። እኛም እየተባበርናቸው ነው። መጥኔ ለዚች ሃገር...

የሁለቱ ጓደኞቼ የመገደል ወሬ በኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን እንደተሰማ በብሽቀት ዊስኪ ስለበልብ ነጋብኝ። በነጋታው ረፋዱ ላይ ላሊበላ ሆቴል ቁጭ ብዬ ሳለ አጥወለወለኝና መፀዳጃ ቤት ገብቼ አስመለስኩ። አሞት በቁና ነበር የወጣው። ድሮውንስ አሞታችንን በየመፀዳጃው እያፈሰስን ምን አሞት ቀርቶን ቁም ነገር ልንሰራ? ጋሽ ዮሃንስ ይህን ቢያይ ሁለት ሞት በሞተ...

ዋለልኝና ማርታን አይሮፕላን ላይ ተኩሶ የገደላቸው ማን መሆኑን ለማወቅ የደሴ ልጆች መከታተል ጀምረን ነበር። በወቅቱ ሳናውቀው ተድበስብሶ ቀረ። የጓደኞቼ ገዳይ የዛሬው ጄኔራል ተስፋዬ ሃብተማርያም መሆኑን በቅርቡ ነበር የሰማሁት። ስሰማ በጣም ደንግጬ ነበር። ጄኔራሉ ብሄራዊ ጀግና እንደመሆናቸው በጣም አከብራቸዋለሁ። የሁለቱ ጓደኞቼ ሞት ከእኚህ ከማከብራቸው ሰው ጋር ሲያያዝብኝ ምን ልሁን? እየቆየሁ ግን ስሜቴን ለማስታረቅ ሞከርኩ። ጄኔራሉ በወቅቱ ወጣት ኮማንዲስት እንደመሆናቸው የታዘዙትን ፈፅመዋል። ግዴታቸውን ተወጥተዋል። እና ይቅርታ ላደርግላቸው ሞክሬያለሁ። የተሳካልኝ ግን አይመስለኝም..."

* * *

"...ጄኔራል አማን አንዶም የተገደሉት ለመንግስቱ ሃይለማርያም ስልጣን ስጋት በመሆናቸው ብቻ ነበር። ሌላ ምክንያት የለውም። ጄኔራሉ የኤርትራን ችግር በሰላም ለመፍታት ያደረጉት ሙከራ በክህደት ሊታይባቸው ባልተገባ። ወፈፌው መንግስቱስ ምን አስገኘ? ያን ሁሉ ፎክሮ፣ ያን ሁሉ ሰው ጨርሶ ሲያበቃ ሃገሪቱን ለጅቦች ትቶ ፈረጠጠ።





'እንደ አጤ ቴዎድሮስ ለምን ሽጉጥ አልጠጣህም? ስትፎክር አልነበረም ወይ?' ተብሎ ሲጠየቅ፣

'ጊዜ አልነበረኝም' ሲል አላገጠብን። ስድ አደግ!

የጄኔራል አማን አሟሟት፣ "House of sand and Fog" የሚለውን ድንቅ ፊልም ያስታውሰኛል። ፊልሙን ከማየቴ በፊት መፅሃፉን ያነበብኩ ቢሆንም፣ ፊልሙን ሶስት ጊዜ ተመልክቼዋለሁ። የፊልሙ ዋና አክተር Ben Kingsley አሟሟት ጄኔራል አማን አንዶምን ያስታውሰኛል።

አማን ራሳቸውን ከመግደላቸው በፊት የክብር ልብሳቸውን ለብሰው ሜዳሊያዎቻቸውንም አጥልቀው እንደነበር ዳዊት ወልደጊዮርጊስ ፅፎ አንብቤያለሁ..."

* * *

"...ጃንሆይ ተገልብጠው መንግስቱ ሃይለማርያም ወደ ስልጣን ብቅ ሲል እኔ አዋሳ ነበርኩ። በዚያን እለት ምሽት በደስታ ብዛት ከጓደኞቼ ጋር እየጠጣን ስንጨፍር አደርን። ከአንድ ከተናቀ የድሃ ቤተሰብ የተወለደ የወታደር ልጅ ወደ ስልጣን መምጣቱ ብቻውን በስሜት አሳብዶን ነበር።

ብዙም ሳንቆይ ግን መሳሳታችንን አወቅን።

መንግስቱ ፈሪ እና ባለጌ መሆኑን ተረዳን። ጃንሆይ ያመፀባቸውን ሰው ፈትተው የመልቀቅ ድፍረት የነበራቸው አርቆ አስተዋይ መሪ ነበሩ። የትምህርት መስፋፋት ለስልጣናቸው ጠንቅ መሆኑን እያወቁ ለትምህርት ጥራት ይጨነቁ ነበር። 'የባሰ አለ፤ አገርህን አትልቀቅ' ነበር ተረቱ። በእኛው እድሜ ከደርግ የከፋ ስርአት ለማየት በቃን..."

* * *

"...ምቀኝነትና ቅናት የውርስ እሴቶቻችን ስለመሆናቸው ከመናገር ባሻገር እንዴት ከዚህ ስንኩል ባህል ልንወጣ ሳንችል ቀረን? የባህል መሰረቱ ሲደፈር አንገቱን እንደ በግ ለቢላ የሚሰጥ የሰው ልጅ ይኖር ይሆን? ደርግ ግንባራችንን በጥይት ይፈረክስ ገባ። ወደ ድንጋይ ዘመን ተመለስን።

እሰይ! ደግ አደረገን!

እኛ የታሪካችንና የትውልዳችን ውጤት ነን። መካድ ምን ያደርጋል? መንግስቱ ሃይለማርያምን ለዚህ ያበቃነው

እኛው ራሳችን ነን። ዳዊት ወልደጊዮርጊስ በመፅሃፉ አንድ አስቂኝ ወግ አንስቶ ነበር።

አንድ ጊዜ ዳዊት ከመንግስቱ ሃይለማርያም ጋር ቢሮው ውስጥ እየተጫወቱ ሳለ መንግስቱ ለዳዊት እንዲህ ይለዋል፣

“ዳዊት! እንደምታውቀው by Profession Economist ነኝ”

ዳዊት የዚህን ባለጌ ሰው ትምህርትና ታሪክ አሳምሮ ስለሚያውቅ ግራ ተጋብቶ ራሱን እየነቀነቀ አዳምጦ ወጣ። ከወጣ በሁዋላ ባለስልጣን የነበረ ጓደኛውን ያገኘውና ይህንኑ መንግስቱ ያለውን ያጫውተዋል።

ባለስልጣኑም እየሳቀ እንዲህ አለው፣

“ላንተ Economist ነኝ አለህ? ለኔ Lawyer ነው ያለኝ”

ይሄ ባለጌ እንዲህ እየቀለደ 15 አመት ገዛ።

የማንክደው እውነት አለ።

መንግስቱ ሃይለማርያም ኢትዮጵያን ያፈቅራት ነበር። ኢትዮጵያ የተባለችውን እናት ሃገር፣ ጉሮሮዋን አንቆ ለአመታት ከንፈሯን ሳማት። ሳማት ከማለት እየነከሰ አደማት ማለት ይቀላል። መሳምና መንከስ ለይቶ ሳያውቅ የጋራ አገራችንን ተጫወተባት። ኢትዮጵያ በመንግስቱ የፍቅር የጥርስ ንክሻ ለ15 አመታት ተሰቃየች። ጉሮሮዋ ታንቆ፣ ትንፋሽ አጥሮአት በአፍንጫዋ ብቻ እየተነፈሰች ከንፈሯን መሳም የምትሻ የለችም። ኢትዮጵያ የገጠማት ግን እንዲያ ነው። ኰሎኔል መንግስቱ አሻግሮ ማየት ቢችል ኖሮ የግል ፍላጐቱን በመተው ይህች ሃገር የተሻለ እድል ይገጥማት ዘንድ አንድ እርምጃ መራመድ በተቻለው ነበር። የዳዊት ወልደጊዮርጊስን የልብ ምክር በማዳመጥ ብቻ መባነን በቻለ ነበር። ይህንን ማድረግ ባለመቻሉ ግን ይህን መከረኛ ህዝብ እዚህ የጨለመ ገደል ውስጥ ጣለው።

መለስ ዜናዊ ከመንግስቱ በተለየ መንገድ እየነጐደ ይገኛል። ኳሷ እግሩ ላይ አለች። ፀሃይ ከመጥለቋ በፊት ኳሷን እንደሚለጋት ይታመናል። Plan A እና Plan B አስቀምጦ ማብቃቱ ምንም ጥያቄ የለውም። Plan B የተባለው ተለዋጭ ህልም ትግራይን እንደ እስራኤል ሃያል አድርጎ የመፍጠሩ ህልም ነው...”

* * *

“...የቤተሰቤ ሁኔታ ጥሩ አይደለም። ህይወት





ተሳክቶልኛል ማለት አልችልም። የመጀመሪያው ችግር የባለቤቴ ባህርይ ነው። ኑሮአችንን ሲኦል አደረገችው። ከ31 አመታት በፊት መጀመሪያ ያየሁዋት ቀን እንዴት በፍቅር እንዳበድኩላት ይታወሰኛል። ጥርሰ በረዶ ነበረች። አመሏ ወርቅ ነው ብዬ አመንኩ። ወገቧ አለንጋ ነበር። የወገቧ አለንጋ መምሰል ያያትን ሁሉ የሚያነሆልል ነበር። ዳሩ ምን ያደርጋል? ምላሷም አለንጋ ሆነ...”

* * *

“...በረጅም ጊዜ ውስጥ እንደ ውሻ ኖርኩ። በጥልቅ የፍርሃት ጉድጓድ ውስጥ ተቀብሬ የህይወት ዘመኔን ጨረስኩ። ልጆቼንም ከኔ የባሱ ፈሪ አደረግሁዋቸው። ወደ አሜሪካና አውሮፓ አሻግሬያቸው ሳበቃ ከሚስቴ ጋር ባዶ ቤት ውስጥ ቀረሁ። ልጆቼን ወደ ስደት አባርሬ ሳበቃ እድለኛ የሆንኩ መስሎኝ ነበር። ለካስ መውለድና መክበዴ በኪሳራ ኖሮአል የተደመደመው? ከስድስቱ ልጆቼ አንዱ እንኳ አጠገቤ የለም። ‘ታመምኩ’ ስላቸው ልጆቼ ገንዘብና መድሃኒት ይልኩልኛል። በሽታዬ ግን ተስፋ እና ፍቅር ማጣት ነበር ...”

* * *

“...ጨዋነት ምንድነው? ሃጢአትስ? ተፈጥሮ ራሱ ጉያችን መሃል እሳት ተክሎብን ሲያበቃ፤ በዚህ ደግሞ ግብረገብ! እዚህ ውበት የፈሰሰበት ከተማ ውስጥ ሰው እንዴት በግብረገብ መኖር ይችላል?

የምመኛት አንዲት ወይዘሮ ነበረች።

እንዴት ውብ ናት? ኤድያ! ደክሞአል፤ አይሰራም። ከዱባይ በመጣ ሃይል ሰጪ ሞክርኩት። ጥሩ ነበር። ልቤ ግን ቀጥ ልትል ደረሰች። ለጥቂት ተረፍኩ።

ይሄ ብቻውን ሙሉ መፅሃፍ ይወጣው ነበር።

መፃፍ እወዳለሁ። ሰነፍ ባልሆን የደራሲ ነፍስ ነበረኝ። ‘የጋን ውስጥ ሻማ’ ነው የሚሉት? ከዱባይ በመጣው ማነቃቂያ ታግዤ...ኤዲያ! ዋጋ የለውም። ብደግመው እሞት ነበር። ገሃነብ! ቤት ስገባ ታዲያ ለህሊና ማፅጃ ቢሆን ብዬ ጠቦት ይዤ ገባሁ።

ለነገሩ ሂያጅ አይደለሁም።

ወጣትነት ድሮ ቀርቶአል። የዳጃች አላምረው ልጅ፣ አሰገደች አላምረው የኛ ዘመን ኮከብ ነበረች። ከተማ ይፍሩ

(ኩቴ - ከትኩቴ) ዋነኛ ውሽማዋ ሲሆን፤ ለኛም ደርሳናለች። 'ውቤ በረሃ - በሶስት ቀን - አደረግሽኝ ደሃ' እያልን አዚመን ነበር። የማያልፍ የለም፤ አለፈ። ቀሪ ሃብቴ የባለቤቴ ምላስ ብቻ ሆኖአል። መፈጠሬን እስከጠላ እንደለበለበችኝ ነው። እኔ ምኔ ሞኝ? እናትና ልጅ ለብልቤ ለጥ"

* * *

"ሴቶች ሲባሉ ምላስና ፀጉር ማለት ናቸው። ሰው ደክሞት ውሎ ቤቱ ገብቶ በሰላም ማረፍ አይችልም?

'አትጠጣ! አታምሽ!'

ሴትየዋ ሌላ ቃል አታውቅም። ሰው ሁሉ እየጠጣ አይደለም እንዴ? እንዴት ነው እኔ ከሰው ተለይቼ ሳልጠጣ የምገባው? በአመት ውስጥ 365 ጊዜ 'አታምሽ!' ትለኛለች። 60 አመት ያለፈኝ አባወራ ነኝ። አመሻለሁ! እጠጣለሁ! እድሜዬን ሙሉ የፈፀምኩትን ላቆም አልችልም።

ከትናንት ወዲያ ደግሞ የሊፒስቲክ ቀለም ሸሚዜ ላይ አገኘችና እዬዬዋን አቀለጠችው። ነጠላ አዘቅዝቃ ፍራሽ ማውረድ ነው የቀራት። የሚደንቅ ነው። ወላዲትን! በዚያን ቀን ምንም የፈፀምኩት ነገር አልነበረም። ቡና ቤት የሚሰሩት አስተናጋጆች ተንኮላቸው አይቻልም። ሰላምታ የሚሰጡ እየመሰሉ የአባወራውን ሸሚዝ እየለቀለቁ የስንቱን ትዳር በጥብጠዋል። ወላዲትን! ማን እንደቀባችኝ እንኳ አላውቅም።

ይህን ለመበቀል ነው መሰለኝ፣ ትናንት ቤት ስገባ ከቀድሞ የከንፈር ወዳጇ ጋር የተነሳችውን ፎቶ ጠረጴዛው ላይ ቁጭ አድርጋ ጠበቀችኝ። ልታስቀናኝ መሆኑ ነው።

የወፍ ጭንቅላት!

ደስ እንዲላት ብዬ ቡራ ከረዩ አልኩ...

እንዳልኩት ሂያጅ አይደለሁም። በዚያ ላይ ደክሜያለሁ። የማልክደው ነገር ብዙውን ጊዜ ጎዳናዎች ላይ እየተዘዋወርኩ የሴቶችን ውበት አደንቃለሁ። አንድ Paranoid የሆነ ሽማግሌ ጓደኛ አለኝ። ማንኛውንም ነገር ሲጠራጠር ይውላል። ከእሱ ጋር ከመደንዘዝና ጭንቀቱን ከሚያራግፍብኝ የሴቶችን እግር እያየሁ መዋል ይሻለኛል። ዛሬ ያየሁዋት ሴት እግርዋ የሚጣል የለውም። እስከ እቤቷ ተከተልኳት። እህ!..."

* * *





ሽማግሌው ሰው ጓደኛዬ ነው ማለት እንኳ አልችልም። የምንገናኘው ፖፖላሬ ፊያት አጠገብ ካለችው መጠጥ መሸጫ ግሮሰሪ ወስጥ ሲሆን፤ የምንለያየውም እዚያው ነው። አንድ አመት በዚህ መንገድ አብረን ጠጣን። ብዙውን ጊዜ እነዚህን ከይሲዎች እናማለን። ከዚያ በተቀረ ለስድስት ወራት ያህል ሰውዬው ምን እንደሆነ እንኳ አላውቅም ነበር። Paranoid መሆኑን በመጀመሪያው የተገናኘን ቀን ነበር ያወቅሁት።

ጎን ለጎን ቁጭ ብለን ነበር። ጠጋ አለኝና፣

"ቢራ በባዶ ሆዴ ብጠጣ ምን ይሆናል?" ሲል ጠየቀኝ።

"ምንም አይልህ። ቢራ ራሱ ምግብ ነው" አልኩት፣

"መድሃኒት ግን ውጫለሁ"

"መቼ?"

"ከሁለት ሰአት በፊት"

"ምንም ችግር የለውም። እንዲያውም መድሃኒትን በቢራ የሚውጡ አሉ" አልኩት።

በተረጋጋ መንፈስ ፊቱ ፈክቶ ቢራ አዘዘና በአንድ ትንፋሽ ግማሽ አደረሰው፣

"መጠጥ ከጀመርክ ስንት ጊዜ ሆነህ?" ስል ጠየቅሁት።

"45 አመት"

"የረጅም ጊዜ ጠጪ ነሃ!" አልኩ፣

"አዎን!" ካለ በሁዋላ እንዲህ ሲል ያብራራልኝ ገባ፣

"ስለ ቢራ አንተን መጠየቄ ወሬ ለመጀመር ብዬ ነው።"

ከዚያም ስለ መጠጥ ያብራራ ገባ።

"...መጥፎው አረቄ ነው። አረቄ ሄዶ ጉብትህን ያነደዋል። ጉብት በአረቄ ከተነካች አለቀላት። መመለሻ የላትም። በልተህ ከጠጣህ ግን ምንም አትሆንም። ከመጠጦች ሁሉ መጥፎ ምን እንደሆነ ልንገርህ? ጠጅ! ጠጅ ብዙ ከጠጣህ ማጅራትህና ጉንጭህ እየተስማማው መወፈርና ማብረቅረቅ ይጀምራል። ይሄ ምን ማለት እንደሆነ ልንገርህ? የሚቀጥለው ቅዳሜ በጠዋት ትሞትና እሁድ ቀብርህ ይሆናል..."

ትምህርታዊ ገለፃውን ከጨረሰ በሁዋላ እንዲህ አለኝ፣

"አንተ በጣም ትመቻለህ"

"ማለት?"

"አንተን ባላገኝህ ኖሮ ዛሬ ደብሮኝ ይውል ነበር። አንተ ግን ምን እንዳልከኝ ታውቃለህ?

'ጠጣ!' አልከኝ።

ሞራልህ ብቻ ይበቃል። እኔ የመጠጥ ልምድ አለኝ። አንተን ያማከርኩህ ሞራል ፈልጌም ነው።

አንዳንዱ ምቀኛ ምን ይልሃል?

'ሄደህ ተኛ!'

ግንድ ሆዱ ላይ ይተኛበት።

'መድሃኒት ውጫለሁ' ብዬ ስናገር፣

'ሄደህ እረፍበት' የሚለኝ ጠላቴ ነው።

ምክንያቱም 'እረፍበት' የሚልህ ላንተ አስቦ አይደለም። የአበሻ ምቀኝነት ነው። አንዳንዱ ጭራሽ ሆን ብሎ መካከሉ ላይ ያስታውስሃል።

'መድሃኒት ውጠህ የለንዴ? ይብቃህ' ይልሃል። የጠጣው አይብቃው!..."

እንዲህ እየሳቅን የጀመርነው ወግ ለጓደኛነት አበቃን። ከአስተናጋጆች ጋር ሁልጊዜ እንደተጋጨ ነው።

'ሲታዘዙ የሚዘገዩት ሽማግሌዎች ስለሆንን ነው። ወጣት ብንሆን ከፈገግታ ጋር ፈጠን ብለው ያመጡልን ነበር' ብሎ ስለሚያስብ እንደሰደባቸው ነው ሁልጊዜ፣

"ማነሽ!? ቢራ አምጪ!
ጆሮሽ ላይ ተኛሽበት?
ፀጉርሽ ምን ይመስላል? ጃርት!
ሴትዮ! አንችን አይደለም እንዴ? ጉልቻ!
ፊቷ ደሞ ምን ይመስላል? ያለቀ ካርቦን!
ተመልከተው ከንፈሯን? ላፒስ!
ወገቧን አታየውም እንዴ? አክንባሎ!
ምላስ የለቀቀባት፤ መቀስ አፍ!
ይቺ በምላሷ ፀጉር ትከረክማለች!"

በስድስተኛው ወር ቤቱ ወስዶ ራት ጋበዘኝ።

ድቅቅ ያለች የስምንት አመት ልጅና በእድሜ በጣም የምታንሰው ሚስት ነበረችው። ሁለቱም በጣም ይፈሩታል። ምግብ በልተው የሚያውቁ አይመስሉም። ራት በልተን ጨርሰን ከዚያ ቤት እስከምወጣ በጣም ተቻኩዬ ነበር። አንድ ሰአት ብቻ





በፈጀው የራት ቆይታችን አስጨናቂ ቃላትን ብቻ ነበር የሰማሁት። ገና እንደገባን ልጁን በሃይለ ቃል አናገራት፣

"አጠናሽ?"

ራሷን ላይ ታች ነቀነቀች።

እግሯን ውሃ የሞላ ቁና ውስጥ ከትታ እያወዛወዘችው ነበር። ልጅቱ በስርቆሽ እኔን ደጋግማ ተመለከተችኝ። መለሰና እንዲህ ሲል ጠየቃት፣

"ራት በላሽ?"

እንደገና ራሷን ላይ ታች ነቀነቀች።

"ለምን ታስፈራታለህ?" ስል ጠየቅሁት።

"ፍቅር ከየት ይምጣ?" ሲል መልሶ እኔኑ ጠየቀኝ። "...የምትሰጠው እኮ ሲኖርህ ነው። ከየት አምጥቼ ልስጣት?"

እንደገና አምባረቀባት፣

"ጨዋታውን ተይና ታጥበሽ ግቢና ተኚ"

እሷ ግን አልሰማችውም። ቀና ብላም አላየችው።

"አትሰሚም እንዴ? ዲስኩ!?"

ቀና ብላ ስሜቱ ባልታወቀ ሁኔታ ካጤነችው በሁዋላ እግሯን መታጠብ ጀመረች፣

"ዲስኩ ስሟ ነው?" ስል ጠየቅሁት።

ራሱን ላይ ታች ነቀነቀ።

"ለምንድነው ዲስኩ ያልካት?"

"ስም ነዋ!"

"ማለቴ ልዩ ምክንያት አለህ?"

"ንግድ የጀመርኩት በዲስኩ ሰአት ነበር"

ሰውነቷ ጥውልግ ማለቱን ስላስተዋልኩ፣

"ምግብ ትወስዳለች?" ስል ጠየቅሁት።

"ምናባቷ አውቄላት። ተፈጥሮዋ ነው። ረሃብተኛ ትመስላለች። እየበላች እጀ ሰባራ ታደርጋለች። ዲቃላ!"

ባልና ሚስቱ ሁለቱም ጥቋቁሮች ሲሆኑ ዲስኩ ደግሞ በግልባጩ ፈረንጅ ትመስል ነበር፣

"ማንን ነው የምትመስለው?" ስል ጠየቅሁ።

"ምናባቷ አውቄላት?"

"መስደብ ግን ጥሩ አይደለም" ስል አስተያየት ሰጠሁ።

"ምን ትሆናለች? እኛም እየተሰደብን ነው ያደግነው"

ቆየና ግን ጠርቶ አቀፋትና ያባብላት ገባ፣

“የኔ ዲስኮ! የኔ ዲቃላ! እንደምወድሽ ታውቂያለሽ መቼም? ዲስክዬ! ዲስኮ፣ አይዞሽ! በይ ሂጂና ተኚ”

ይህ ሁሉ ሲሆን ሚስቱ አንዲትም ቃል ያልተነፈሰች ሲሆን፤ እጃችንን አስታጥባ ራት አበላችን። በችኮላ ቤቱን ለቅቄ ወጣሁ።

ዲስኮ በዚያው ሰሞን ሞተች።

ጓደኛችን ለአንድ ሳምንት ያህል ከግሮሰሪዋ ጠፍቶ ነበር። በሳምንቱ አንድ ሰንበት ተስያት ላይ ቀን ድንገት ብቅ አለ። የጠፋበትን ምክንያትም እንዲህ ሲል ነገረኝ፣

“ዲስኮ ታማ ነበር። እና ሞተችብኝ!”

ይህን ካለ በሁዋላ አይኖቹ በርበሬ የሚተፉ መስለው በእንባ ተሞሉ። ፈጥኖ መሃረብ አውጥቶ አይኖቹን አባበሰ። እናም ጂን አዘዘ። ከዚያ ቀደም ጂን ሲጠጣ አይቼው አላውቅም ነበር...”

* * *

አባትየው ማስታወሻቸውን የሚፅፉት ማታ ማታ ሳይሆን አልቀረም። ባለፈው ምሽት ያቆሙበትንም የሚያዩ አይመስሉም። ከውሎአቸው ጋር በተያያዘ አጀንዳ ላይ ብሶታቸውን የሚያራግፉት እዚያችው ጉድጓዳቸው ላይ ነው። ገፅ 69 ላይ እንዲህ አስፍረዋል፣

“...አንድ ግለሰብ በዘር ሃረጉ ብቻ የአመለካከት ቆብ ሊጫንበት አይገባም። ጉበና ዳጩ ዛሬ በኦሮሞዎች ዘንድ ስሙና ታሪኩ በጣም የተጠላ ነው። በዚህ ዘመን ማንኛውም ኦሮሞ ‘ጉበና’ ብለህ ከምትሰድበው ብትገድለው ይመርጣል። በዚህ ዘመን ልጁን ‘ጉበና’ ብሎ የሚጠራ ኦሮሞ በፍፁም አይገኝም። ‘ራስ ጉበና ከሃዲ ነበር’ ማለት ግን አንችልም። ራስ ጉበናና አጤ ምኒልክ አብረው ያደጉ ጓደኛሞች ነበሩ። ‘ኢትዮጵያ’ የተባለች የተማከለች ሃገር ለመፍጠር በዘመናቸው ብዙ ሰርተዋል። ጉበና ለምን ከሃዲ ይባላል? ጉበና በዘር ኦሮሞ ቢሆኑም፣ በወቅቱ የራሳቸው የፖለቲካ አመለካከት ነበራቸው። አበቃ!”

እንዳመጣላቸው ነው የሚፅፉት። ከራስ ጎበና በቀጥታ ወደ ታምራት ላይኔ ነበር የዘለሉት፣

“....የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ታምራት ላይኔ ከእስር





እንደተፈታ በቴሌቪዥን ቀርቦ፣ ‘አለቅሳለሁ ገና!’ ብሎ ሲናገር በውነቱ ደስ አላለኝም። ማልቀሱ አልነበረም ደስ ያላለኝ። በመንፈሳዊ ህይወታቸው የመጠቁ ምእመናን የተቀደሰ እንባቸው ገፅታቸውን ሲያጥበው ተመልክቼ አውቃለሁ። ስሜቱንም እገነዘበዋለሁ። ታምራት ላይኔ ከነበረበት ፅንፋዊ የፖለቲካ ተሳትፎ አንፃር ግን አባባሉ ከምናውቀው ሰብእናው ጋር የሚቃረን ይመስላል። ታምራት ለህዝብ የማይጠቅመውን የጥላቻና የዘር ፖለቲካ በማውገዝ የተቀደሰ መንገድ መከተሉ የሚያስወድሰው ነው። ሆኖም ወደ ሰባኪነት ከመሸጋገሩ በፊት እንደ ንጉስ ዳዊት ሃጢአቱን በወፍራም ጥራዝ ቢናዘዝ በተሻለ ነበር።

ንጉስ ዳዊት ወንጀል ነክ ምስጢሩን ለመደበቅ ሲል በስልጣኑ ስር ከነበሩ ጄኔራሎች አንዱን ሆን ብሎ አስገድሎ ሲያበቃ። መልሶ ደግሞ ቤርሳቤህ የተባለችውን የጄኔራሉን ሚስት የጠቀለለ፤ ድርብ ድርብርብ ወንጀለኛ ነበር። ያን ሃጢአቱን ግን በአደባባይ ስለተናዘዘ። ፈጣሪያችን ይቅርታ አድርጎለታል። ይሄ ታሪክ ለኛ ለብዙሃን መፅናኛችን ነው። የኛ ትውልድ እንኳን የሰው ባል አስገድሎ የሰው ሚስት ደርቦ ሊወሽም የኑሮ ውድነት እያንገላታው የራሱንም ሚስት ማስተዳደር ከብዶት ችግር ላይ ነው። በተለይ ይቺ የኔ ሚስት! ምላሷ! አይጣል! የጉማሬ አለንጋ! ከይሲ የሆነች...

በርግጥ ታምራት ላይኔ በስልጣን ዘመኑ የፈፀመውንና ያስፈፀመውን ሁሉ በመፃፍ ላይ ይሁን አይሁን አላውቅም። VOA ላይ ከጋዜጠኛ አዲሱ አበበ ጋር ሲነጋገር እንደሰማሁት ግን ያለፈውን፣ ‘ሆድ ይፍጀው!’ ብሎ ማለፍ የፈለገ ይመስላል። ጥላሁን ገሰሰ ባንድ ወቅት አንገቱን ማን እንዳረደው ሲጠየቅ። ‘ሆድ ይፍጀው!’ ማለቱ ጉዳዩ የግሉ ስለነበረ ነውና አለመናገር መብቱ ነው። ታምራት ላይኔ ‘ሆድ ይፍጀው!’ የማለት መብት ግን የለውም። ምክንያቱም እሱ ስልጣን ላይ በነበረበት ጊዜ የታረደው አንገት የሌሎች ነው። ‘አለቅሳለሁ ገና!’ የሚለው አባባል ብዙዎችን የጎረበጠው ለዚህ ሳይሆን አይቀርም..”

* * *

ባለቅኔና ፀሃፊ ተውኔት መንግስቱ ለማ ከሞቱ በሁዋላ ብሄራዊ ቴአትር አዳራሽ ለመታሰቢያቸው በተዘጋጀ አንድ

በአል ላይ መገኘታቸውንም ጠቅሰዋል። በዚያ ዝግጅት ላይ አስራት አንለይ የተባለ ሰው አንድ ግጥም ማቅረቡንም ይገልፃሉ። የግጥሙንም አዝማች ማስታወሻ ደብተራቸው ላይ አስፍረውት ነበር፣

በጠራ ጨረቃ - በእኩለ ሌሊት፣
አንደበተ ርቱእ - ፀሃፊ ተውኔት፣
የለማ ዘር ፍሬ - መንግስቱ ገነት፣
ጠርተውት አርጎአል - የቅኔ አማልክት፣

በሽማግሌው ማስታወሻ ደብተር ላይ የሰፈሩትን አብዛኞቹን ግጥሞች አውቃቸው ነበር። ስነግጥሞቹን ካሰፈሩ በሁዋላም የገጣሚውን ስም ከስር ያስቀምጡታል። የገጣሚው ስም ያልሰፈረባቸው ጥቂት ስንኞችንም አግንቼ ነበር። ቀደም ሲል ያላነበብኳቸው በመሆኑ ራሳቸው የቋጠሯቸው ሊሆኑ እንደሚችሉ ገምቻለሁ። ባለቤት ከሌላቸው ግጥሞች አንዱ እንዲህ ነበረች፣

"አማርኛ ታመመ" ሰምቼ፣
ስጨነቅ አመሸሁ ሰግቼ፣
ሳልተኛ ነጋ ፈርቼ፣
............ዳሩ ግን..............
ስጋቴ! ፍርሃቴ! - ነበረ ለካ ከንቱ፣
ጨለማው ሲገፍ ሌሊቱ፣
ፀሃይ ብቅ አለች በጧቱ፣
ከእንቅልፌ ስነቃ በርግጌ፣
ስጋቴን አጣሁት ፈልጌ፣
ቦቅቧቃው ስጋት!
ማነህ ለመሆኑ አንተ?
ሞራልህ አርጅቶ - እንደ ጨርቅ የሞተ!
ይልቁን ልንገርህ - ዜና አለኝ ጉደኛ!
ከቶ አይሞትም - አማርኛ!
እኛ እያለን እኛ!

ጥቅሶችንም አስፍረዋል። በአብዛኛው አፍሪቃ ነክ ሲሆኑ፣ ከነዚህ ጥቅሶች አንዱ አንድ ጋናዊ ምሁር የተናገራት ነበረች። እንዲህ የምትል፣ "አፍሪካ! ብልሆች በጅሎች የሚመሩበት አህጉር"

* * *





ከወያኔ ጋር የተያያዙ ገፆችም ነበሩ።

"...የወያኔ አለቆች ከዛሬ ነገ ልብ ይገዛሉ ተብሎ ይጠበቅ ነበር። አልሆነም። የቤት ቁሳቁስ ሲገዙ ነው የሚታዩት። የሃገሪቱን ኢኮኖሚ መገንባት ትተው፤ ጓዳቸውን መገንባቱን ተያይዘውታል። በረሃ በነበሩ ጊዜ 'ድንጋይ ኳሱ፣ ጠመንጃ ትራሱ፣ ሰማይ ዳሱ' ነበሩ። አዲሳባ ከገቡ በሁዋላ 'ውሸት ኳሱ፣ እብሪት ትራሱ፣ አለማወቅ ዳሱ' ተብለዋል።

...የትግራይ ምሁራን በያዙት መንገድ እስከቀጠሉ ድረስ በታሪክ ተጠያቂ መሆናቸው የማይቀር ነው። 'የመለስ በስልጣን መቆየት ለትግራይ ክልል ጠቃሚ ነው' ከሚል መነሻ ስርአቱን መደገፋቸውን ከቀጠሉ አደጋውን መልሰው ያጭዱታል። ከዚህ ከሚታጨድ አደገኛ አደጋ ለማምለጥ ይችሉ ዘንድ ኢትዮጵያ በሃገር ደረጃ እያጋጠማት ያለውን አደጋ ማጤን ይጠበቅባቸው ነበር። 'የትግራይን ሪፑብሊክ ማወጅ' እንደ ሁለተኛ አማራጭ የሚያዩት ቢሆን እንኳ ከአደጋው አያመልጡም። ከታሪክ እንደምንማረው ጭቆና የሚወልደው አመፅን ብቻ ነው። ከጭቆና ነፃነትን ያገኘ ስርአት በማንኛውም ዘመን አልታየም..."

* * *

"...ድምፅ ለመስማት ብረትና ብረት መጋጨት አለባቸው። ጨርቅና ወርቅ ተጋጭተው ድምፅ ሊያወጡ አይችሉም። በወርቆችና በጨርቆች የተሞላው ፓርላማም ድምፅ ሊሰጠን አልቻለም። ተቃዋሚዎች ብረት ሆነው ከብረት ጋር ተጋጭተው ድምፅ ሊሆኑን አልቻሉም። በእድሜው ወጣት ስለሆነ ልደቱ አያሌው ባህር ይሆናል ብለን ተስፋ አድርገን ነበር። አሳ ሆኖ ተገኘ። ፕሮፌሰር መስፍን የፊውዳል ጠባይ አለው። ያገኘውን ሁሉ እየተቃወመ እድሜውን ጨረሰ። ፓርላማ የገቡት በየነና መረራ የብረቱ ገበና ሽፋኝ አልባስ ሆነዋል። ሰውና ጀግና የጠፉበት ዘመን! ጀግና ማለት፤ ጀግና የሚሆን ነበር፤ ጀግና የጠፋ እለት። በኛ ዘመን ጀግና ጠፋ። ጊዜ ያነሳው ፍየል በነብር ጭራ ሲጫወት እያየን ነው። በአጤ ምኒልክ ዘመን አይጥ በልቶ፣ ዳዋ መደብደቡን ነበር የሰማነው። በመለስ ዘመን ይሄ ተለውጦ፣ 'ወያኔ በበላ! ደሃው ተቆላ' ሆኖአል ተረቱ። "

* * *

"...እቴጌይቱ አዜብ መስፍን አገሩን እየተዘባነነችበት ነው። ወልቃይቴ ናት አሉ። በእናቴ በኩል ሳትዛመደኝ አትቀርም። እናቴ ከወልቃይት ትወለዳለች። ይች ሴትዮ ከተማው ውስጥ ጥሩ ስም የላትም። ነገረኛ ሰናፍጭ ናት ይላሉ። ቤተመንግስቱን የሚጠብቁት ባልደረቦቿ ሳይቀሩ እብሪተኛ ናት በሚል ይጠሏታል። የእቴጌይቱ ሃብት ልክ የለውም ይባላል። የሚደንቀው ግን 'ይህን ሃብት ያገኘሁት ደክሜ ሰርቼ ነው' ብላ ትናገራለች መባሉ ነው። ርግጥ ነው፤ በቅርብ የሚያውቋት የወልቃይት ሰዎች እንዳጫወቱኝ ፍሰሃዬ ደባልቀው በሚመራት ጋንታ ውስጥ የጋንታ አስመጋቢ በነበረች ጊዜ ስራዋ ከባድ ነበር። የወጥ መቀቀያ ጎላዎች በሷ ሃላፊነት ስር ነበሩ። በዚያ ምክንያት 'አዜብ ጎላ' ነበር የበረሃ ስሟ።

ዘመዶቼ የሆኑ የወልቃይት ሰዎችን ቤተመንግስት ጋብዛቸው ነበር። ንግስታችን ከ20 በላይ የፈረንጅ ውሾች እንዳላት በአይናቸው አይተው ነገሩኝ። በርግጥ ውሾቹ ከውጭ ሃገር በስጦታ የመጡላት ይሆናሉ። ውሻ በስጦታ መስጠት በፈረንጅ የተለመደ ነው። እንደ ቅብጠት ላይቆጠርባት ይችላል። ሶስት ልጅ መቀለብ በተቸገረ ህብረተሰብ መሃል፣ ውድ ሳሙናና ሽቶ በመጠቀም እነዚህን ውሾች መንከባከብና ከውጭ ሃገር የሚመጣ የውሻ ምግብ መመገብ ግን ጥሩ ስነምግባር አይደለም። ምናልባት ጃንሆይ ለአንድ ውሻ ኬክ ስለመገቡ የደረሰባቸውን ውግዘት ንግስታችን አታውቅም ይሆናል። ባህልና ልማድም አለን መቼም። እኛ ሃበሾች ቤታችን በውሻ ይጠበቃል እንጂ ውሾቻችንን የሚጠብቅ ዘበኛ ቀጥረን አናውቅም። ይህን መሰሉን 'ከህብረተሰብ መነቀል' የተባለ የእብደት በሽታ የሚያድን መርፌም ሆነ ኪኒና ስለመኖሩ እስካሁን አልተሰማም..."

* * *

"...ህዝብ ተስፋ አይቆርጥም። የእምነቱን ባንዲራ የሚያነሳለት ካገኘ ከግቡና ከህልሙ ለመድረስ መፍጨርጨሩ አይቀርም። ለድርጊት ራሳችንን ማዘጋጀት አለብን። የት ላይ ቆመናል? 'እኔ የቤተሰቤን ህይወት ማሻሻል ብቻ ነው የምፈልገው' የሚል አቋም የያዘ ዜጋ ጥቂት አይደለም። ከእነዚህ





አንዱ እኔ ነኝ።

መፍትሄው በእጃችን ነበር...

የአምባገነኖች ግንብ በቁሙ በስብሶ ነበር። አልተጠቀምንበትም። የደከምነው እኛ ነን። የበሰበሰው ግንብ እንደበሰበሰ ቀጥ ብሎ ቆሞአል። ገጣሚው መምህራችን እንዳለው ጥቂት እውቀት ያላቸው፣ ፍርሃትን፣ ሽንገላን፣ ንዝህላልነትን በጅምላ ሸመቱ። ምንም የማያውቁት ደግሞ፣ ሳይታወቃቸው አይናቸው ተጋርዶ ገደል ገብተው ሞቱ። መንፈሳችን ከውስጡ በስብሶ፣ ቁንቁን ቆርጥሞት፣ በቆመበት ያማረ ይመስላል እንጂ መተንፈሻ የህይወት ዘር የሌለው የደረቀ ዛፍ ምሰሶ ሆኖአል።

* * *

የሽማግሌው ማስታወሻ ግልፅ ባልሆነና ባላለቀ አንቀፅ ነበር የሚያበቃው። ምናልባትም ከመሞታቸው በፊት ያስፈሩት ሊሆን ይችላል። እንዲህ የሚሉ አረፍተነገሮች ነበሩበት፣

"...የነበረኝን ጥሩ የስንዴ ዘር ሁሉንም ዘራሁት። እና እንክርዳድ በቀለ። ያንን እንክርዳድ አጨድኩት። የዘራኸውን ታጭዳለህ ይባላል። እኔ እንዴት ያልዘራሁትን አጨድኩ?"

ይህን ዘግተው ሲያበቁ ደ'ሞ እንዲህ ሲሉ አስፍረዋል፣

"...አባ ጨጓሬ! ቀድሶ አያውቅ አባ ይሉታል! 'አባ!' ከሚሉት 'እባብ ጨጓሬ!' አይሉትም? የዚህ ምስጢር ምንድነው? ትግሬ ሲባል ጠልቻለሁ..."

* * *

በነጋታው ልጅየውን መስመር ላይ አገኘሁት። በጣም ኀጉቶ ነበር። ሰላምታም አላቀረበ፣

"አነበብከው?"

"አነበብኩት"

"እንዴት ነው ታዲያ"

"አባትህ ብዙ መረጃ እንደነበራቸው አልጠራጠርም። ሳይናገሩት አልፈዋል..."

"ባለው ደረጃ ልትጠቀምበት አትችልም?"

“አልችልም። የተሟላ አይደለም…”

በዚህም በዚያም ብሎ ሊያሳምነኝ ቢሞክርም እንደማይሆን ቁርጡን ነገርኩትና ተለያየን። ይህ በሆነ በሁለተኛው ወር ግን የአባትዬውን ማስታወሻ በዚህ መንገድ ልጠቀምበት እንደምችል ተረዳሁና መልሼ ወደ ለንደን ደወልኩ።

“ስለ ክፍያ የማታነሳ ከሆነ እጠቀምበታለሁ” አልኩት።

ተስማማ።

“ቅር ይልሃል እንዴ?”

“የለም። ተጠቀምበት”

በመጨረሻም አንድ የማሳረጊያ ጥያቄ ጠየቅሁት፣

“ለመሆኑ አባትህ ምን ሆነው አረፉ?”

ዘግየት ብሎ ነበር ምላሽ የሰጠኝ፣

“ሞቶ ነው የተገኘው። ብዙም የሚታወቅ ነገር የለም። እናቴ እየተከታተለች ነው…”

“አይዞህ እንግዲህ! ጥናቱን ይስጥህ…”

“አሜን!”



# - 16 -

# የተቀበረ ህዝብ

የትም ዞሬ ስመለከት፣ ጉድ ነው! የማየው እለት በእለት፣
የትም የት ያለው ግርፊያ ነው፣ የትም የት ያለው ሰንሰለት፣
የወጣው ህግ የሞት ነው፣ አስፈሪና ክብር አዋራጅ፣
ሳይወድ በግድ በሚፈሰው፣ በድኾች እንባ ላይ ቀላጅ፣
ህገወጥ ስልጣን የትም አለ፣ ህግ አልባ አሰራርም አብሮ፣
የፍትህ ስርአቱም አለ፣ በጨለማ ውስጥ ተቀብሮ፣

(ግጥም - አሌክሳንድር ፑሽኪን)
- አያልነህ ሙላቱ እንደተረጎመው -

“ጤና ይስጥልኝ ኮሎኔል?”

“እንዴት አለህ ወንድሜ?”

“የምፅዋ ቅዝቃዜ እንዴት ይዞሃል ታዲያ?”

“ይገርምሃል! ምፅዋ ሲባል ምንጊዜም ሙቀት ነበር የሚታሰበኝ። እንዲህ ያለ ጃኬት የሚያስለብስ የቅዝቃዜ ወራት ይኖረዋል ብሎ ማን ያስባል? የምፅዋ ሰው ዝናብ ጠብቆ በቆሎ ይዘራል ብሎስ ከቶ ማን ሊገምት?”

“እኔም የመጀመሪያ ቀን እንዳንተው ነበር የተሰማኝ” ካልኩ በሁዋላ ማስታወሻ ደብተሬን ገለጥኩ።

* * *

"...ክረምት ነበር።

"...ሃምሌ 1999 አንድ ምሽት አንድ ሁኔታ ተከሰተ። ከምሽቱ በግምት ሶስት ሰአት ላይ ሲግናል ከሚገኘው የመከላከያ አፓርትመንት መኖሪያ ቤቴ ቁጭ ብዬ ከባለቤቴና ከልጆቼ ጋር እየተጫወትኩ ሳለ የቤቴ በር ተንኳኳና ስንከፍተው ስድስት ወታደሮች ተከታትለው ገቡ።

ሁሉንም አውቃቸዋለሁ።

በአግአዚ ኮማንዶ ክፍለ ጦር የልዩ ሃይል አባላት ነበሩ። ስድስቱም ትግሬዎች ነበሩ። ሻለቃ ገብረሊባኖስ 'ቦራ' በሚል ቅፅል ስም በሚጠራ ሻለቃ እየተመሩ ከገቡት አምስት ወታደሮች ሶስቱ መቶ አለቆች ነበሩ። እንደገቡ፣

'ምን ሆናችሁ ነው?' ስል ጠየቅሁ።

'ርስዎን በቁጥጥር ስር እንድናውል ታዘን ነው። ቤቱንም እንድንፈትሽ ታዘናል። መሳሪያም፣ ሞባይልም እንዲያስረክቡን ታዘናል' ሲሉ ገለፁልኝ።

ቦራ ይህን ሲናገር ገፅታው ላይ የጭንቀት ምልክት አይቼበታለሁ። አለቃቸው ነኝ። አማራ ከመሆኔ በቀር ወንጀል እንደሌለብኝ ይረዳሉ። ሰው ናቸውና ግን ታዛዦች ነበሩ። እኔም ችግሩን ተገንዝቤ ነበር። ወታደሮች ናቸው፣

'እኔን ለመያዝ የማዘዣ ደብዳቤ አላችሁ? ቤቴን ለመፈተሽስ የፍርድ ቤት ትእዛዝ ይዛችሁዋል?' ስል ጠየቅሁ።

'ምንም የያዝነው ነገር የለም። ታዝዘን ነው የመጣነው'

'እንግዲያው ያለምንም የማስረጃ ትእዛዝ እኔን ልታስሩ አትችሉም። ቤቴን ለመፈተሽም አልፈቅድላችሁም። ለላካችሁ ሰው ይህንኑ ንገሩት' አልኩ።

ሻለቃ ቦራ ወደ ደጅ ወጥቶ በስልክ ተነጋገረ።

እና ተመልሶ ወደኔ መጣ።

የሞባይል ስልኩንም ሰጠኝ። የመከላከያ ዘመቻ ሃላፊው ጄኔራል ገብረእግዚአብሄር መስመር ላይ ነበር። እንዲህ አለኝ፣

'የመጡት ሰዎች አንተን ለመውሰድ ነው። አንዳንድ የሚጣራ ነገር ስላለ አብረሃቸው ሂድና ተጣርቶ ትመለሳለህ'

'ይህን ለመፈፀም ሳሞራ ራሱ ያነጋግረኝ' አልኩ።

'ሳሞራ ውጭ ሃገር ሄዶአል'

'እንግዲያው አንተ እኔን አታስረኝም። አላውቅህም።'





'ተው ይብስብሃል' ሲል ለማስፈራራት ሞከረ።

ደግሜ ከቤቴ እንደማልወጣ አረጋገጥኩለት።

አምስት ደቂቃም ሳይሞላ ሳሞራ ለቦራ ደወለ። ቦራ ስልኩን ለኔ ሰጠኝ። ሰላምታ ካቀረበልኝ በሁዋላ፣

'የሚጣራ ነገር ስላለ ሊወስዱህ ከመጡት ጋር አብረህ ሂድ። ቤትህ ግን አይፈተሽም' አለኝ።

ከሳሞራ ጋር ትንሽ ተጨቃጨቅን።

በመጨረሻ ግን ሽጉጤንና ሞባይሌን አስረክቤ በስድስቱ ወታደሮች ተይዤ ከቤቴ ወጣሁ።

ባለቤቴ በጣም ደንግጣ ነበር።

ልጆቼም የጨው ሐውልት ሆነዋል።

አፅናንቼያቸው ወጣሁ። በሁለት ፓትሮል ሆነን በቀጥታ ወደ አዋሳ ወሰዱኝ። ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰአት ሲል አዋሳ ገባን። እዚያም በአንድ ማጐሪያ ክፍል አስረው አሳደሩኝ። ከሁለት ቀናት በሁዋላ አዋሳ የክፍለ ጦሩን ስታፍ ሰብስበው 400 በሚጠጋ ወታደር ፊት አንዳንድ ጥያቄዎች አነሱ።

ጥያቄዎቹ የተለመዱ አይነት ነበሩ።

'ከቅንጅት ጋር ትስስር ነበረህ። በምርጫ 97 ወቅት አግአዚ ግዳጁን በብቃት እንዳይወጣ ቅስቀሳ አድርገሃል። አማራን ታደራጃለህ። ኢህአዴግን ትጠላለህ። ትግሬዎችን ትሳደባለህ። በጠቅላይ ሚኒስትራችን ላይ የግድያ ወንጀል ለመፈፀም ተዘጋጅተህ ነበር' የሚሉና ሌሎችም ተራና አሳፋሪ መረጃዎች ቀረቡ።

'ትግሬን ትጠላለህ' የሚለውን ክስ ለማሳመን ያቀረቡት ማስረጃ በጣም አስቂኝ ነበር። አንድ ጊዜ አንድ ትግሬ ወታደር የቢሮዬ መስኮት ስር ቆሞ የትግርኛ ሬድዮ ያዳምጥ ነበር፣

'ሬድዮ አታጨህብኝ! ዘወር በል ከዚህ' ብዬው ነበር።

ያንን በምስክርነት አቀረቡ። ለቀረቡት ጥያቄዎች ሁሉ ምላሽ ለመስጠት ሞከርኩ። ሳጠቃልልም፣

'አካሄዳችሁ የዘረኝነት መንገድ ነው። ተመልሶ እናንተኑ ጠልፎ ይጥላችሁዋል። ይህ የስጋትና የፍርሃት እርምጃችሁ ከፍርሃትና ከስጋታችሁ የሚያድናችሁ አይደለም። ይልቁን ስጋታችሁን ያባብሰዋል' አልኳቸው።

አዋሳ አራት ቀናት ካሳደሩኝ በሁዋላ መስከረም 16፣ 1999 ከምሽቱ 2፡30 ሲሆን፣ ሁለት ኒሳን ፓትሮል መኪኖች

ከዘጠኝ አጃቢዎች ጋር መጥተው፣ ሻለቃ ሃየሎም የተባለ መኮንን የቡድኑ መሪ ሆኖ ይዘውኝ ወደ ምስራቅ ኢትዮጵያ ጉዞ ጀመሩ።

አዋሽ እረፍት አደረግን።

እዚያ እንዳረፍን፣ 'ስልክ ስጡኝ' ስል ጠየቅሁዋቸው።

አንዱ ወታደር፣

"...ብናስደውልዎት ደስ ባለን። ግን ስልክ እንዳንሰጥዎት ከባድ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል" አለኝ።

ያጀቡኝም ሆኑ ሾፌሩ ሁሉም ትግሬዎች ነበሩ። ጥሩ ሰዎች ነበሩ። በአክብሮት ይዘውኝ ነበር። ሊነጋጋ ሲልም ሃረር ገባን። ሃረር ከተማ ውስጥ ከሚገኝ ወታደራዊ እስር ቤት ከመሬት ስር ከሚገኝ ጠባብ ክፍል ውስጥ ከተቱኝ።

እስር ቤት ስገባን እነዚያ የወሰዱኝ የትግራይ ወታደሮች የገባሁበትን ክፍል አይተው ቅር እንዳላቸው አስተዋልኩ።

ሲሰናበቱኝም፣

"ኮሎኔል! አይዞህ! እግዚአብሄር ከአንተ ጋር ይሁን።" ብለው ተሰናበቱኝ።

የእስር ቤቱ ክፍል ጠባብና በጣም ቆሻሻ ነበር።

ከዚህ ቀደም የአልኢትሃድ፣ የኦብነግና የኦነግ ተጠርጣሪዎች ለረጅም ጊዜ የታሰሩበት ክፍል ነው። ይህን እስር ቤት ቀደም ሲልም በዝና አውቀዋለሁ። መረጃዎች ነበሩኝ። በርካታ ሶማሌዎችና ኦሮሞዎች በእነዚህ እስር ቤቶች ውስጥ ሞተው፣ ሬሳቸው እየተጐተተ ወጥቶ መጣሉን የእስር ቤቱ ጠባቂዎች አጫውተውኛል። የታሰርኩበት ክፍል ወለሉ የደረቀ ደም የበዛበት፤ ጣሪያውና ግድግዳው እየተፈረካከሰ አቧራና ብናኝ የሚበዛበት፤ በአንድ አቅጣጫ ጠባብ የብረት ፍርግርግ የተሰራች ለአየር ማስገቢያ ያክል መስኰት ያላት፤ በሩ ደግሞ በከባድና ወፍራም ላሜራ የተሰራ ነበር።

ወርሃ መስከረም እንደመሆኑ ቢንቢዎች በዚያች የአየር ማስገቢያ ቀዳዳ ገብተው ዙሪያዬን ሰፈሩብኝ። መከላከል አልቻልኩም። የቻልኩትን ያህል ልገድላቸው ሞከርኩ። ትርፉ ጉልበት መጨረስ ሆነ። በጆሮዬ ሙሉ ጆሮ የሚበሳ ሙዚቃቸውን ያስታቅፉኛል። በመጨረሻ እንዳሻቸው ያኙኩኝ ዘንድ እንደ አራስ ውሻ ተዘርግቼ ተኛሁላቸው። ቡችሎች በፀጥታና በርጋታ ከእናታቸው ጡት ወተት እንደሚጠቡት፣





ቢንቢዎቹ ደሜን ሲጠቡት አደሩ።

በእስር ቤቱ ግቢ ውስጥ አንድ የውሃ ኰንቴይነር አለ። በአፄ ሃይለስላሴ ጊዜ የተተከለ ነው። ቦቴዎች በየሳምንቱ ይመጡና ውሃ ይሞሉታል። የምንጠጣው ውሃ ከዚያ ከዛገና ከበሰበሰ ኰንቴይነር እየተቀዳ ነበር። ለዚያውም ያልቃል እየተባለ በቁጠባ ነው። ውሃው በጠቋቋሩ ደቃቃ ብናኞች የተሞላ ቢሆንም፣ ያንን ከመጠጣት በቀር አማራጭ አልነበረም። ምግቡ ላለመሞት ያህል የሚበላ፣ ለጠላት ታስቦ የሚዘጋጅ አይነት ነበር። ጠዋትና ማታም ከጨለማው ማጐሪያ እያወጡ ደጁን ያሳዩኛል።

እየቆየሁ አንዳንድ መረጃዎችን አገኘሁ።

እዚያ እኔ በነበርኩበት እስር ቤት አካባቢ ከቅንጅት ጋር በተያያዘ ብቻ 1700 አማራ ወታደሮችና ኦሮሞዎች ታስረው ነበር። ኰሎኔል ሃይሉ እና ሻለቃ መራ የተባሉ ኦሮሞ መኰንኖችም በኦነግነት ተጠርጥረው ታስረው ነበር። ሁለቱም እንደኔው ለየብቻ ታስረዋል። ሶስታችንም እንዳንተያይ በየተራ ነበር ወደ ሽንት ቤት የሚያወጡን። እኛ ስንወጣ በአንድ ላይ የታሰሩት 1700 ወታደሮች ወደ ማጐሪያ አዳራሻቸው እንዲገቡ ይደረጋሉ።

በእዚህ ሁኔታ ላይ ሳለሁ ታመምኩ።

በሚጠቡኝ ቢንቢዎች ሳቢያ እግሬና ፊቴ በጣም ቆሳሰለ። ውሃውና ምግቡ በፈጠረብኝ ችግር ደግሞ የተቅማጥ በሽታ ያዘኝ። የእስር ቤቱን ሃላፊ አስጠርቼ ይህንኑ ነገርኩት።

'ሪፖርት አድርገን መልሱን እንነግርሃለን' አለኝ።

በድጋሚ ጠየቅሁት።

'ወደ አዲሳባ ደውለን ነበር። ህክምናው አልተፈቀደልህም' አለኝ።

በእግዚአብሄር ተአምር ከአንድ ሳምንት በሁዋላ ተቅማጡ በራሱ ጊዜ ቆመ። ቢንቢዎቹ የሚፈጥሩት ችግር ግን ቀጠለ። ፊቴ ከማበጥ ባሻገር መድማት ጭምር አመጣ። እንደገና ከሁለት ሳምንት በሁዋላ በድጋሚ ቷቅማጥ ጀመረኝ። በድጋሚ አመለከትኩ። ተመሳሳይ መልስ አገኘሁ። ተቅማጡም እንደገና በራሱ ጊዜ ቆመ።

ብቻዬን በጨለማ ቤት ውስጥ ተቀምጬ የማሰላስለው፣ 'ከቶ ምንድነው የፈፀምኩት?' የሚለውን ነበር። ምግብ ከደጅ

አይገባልኝም። ጠያቂ የለኝም። ህክምና አልተፈቀደልኝም። እኰ ለምን?..."

ኮሎኔሉ ትረካውን አቋርጦ እንዲህ ሲል ጠየቀኝ፣

"የቡርቃ ዝምታ' በሚለው መፅሃፍህ ላይ በቅዱስነታቸው ያወደስካቸው ታጋዮች እንግዲህ እንዲህ ሆነው ተገኙ። 'ህዝብ ድንጋይ ሲወረውርባቸው ጠመንጃቸውን ቁልቁል ደፍተው አቀርቅረው ይሄዳሉ' ብለህ ያልካቸው ነፃ አውጪዎች፣ ባሪያ ፈንጋይ ኖረዋል። የታገሉት ለራሳቸው ኖሮአል? ልባቸው የማይገኝ እስስቶች! በጦርነቱ ጊዜ ያሳዩት ስነስርአት የልብ ቢሆን የት ይሄድ ነበር? ግመል መጀመሪያ ለአንገቷ ማስገቢያ ትጠይቃለች። ከዚያ ድንኳኑን ትቆጣጠረዋለች። እንደዚያ ነው የሆነው። እንዳልከው ብፁእ ይመስሉ ነበር በርግጥ። ሁላችንም ሰው መስለውን ነው ያገዝናቸው። አዲስ አበባን ከተቆጣጠሩ በሁዋላ ግን የተሸሸገ ማንነታቸው ፈጥጦ ወጣና ሌላ ፍጡር ሆነው ተገኙ። ራሳቸውን ወደ አየር ባየር ነጋዴነት ለመለወጥ ጥቂት ወራት ብቻ ነበር ያስፈለጋቸው። ሶማሊያ ስትፈርስ ሃየሎም አርአያ ከሶማሊያ የሚመጡ እቃዎችን ሃረር ላይ እየተቀበለ፣ በተፈራ ዋልዋ በኩል አዲስ አበባ ላይ ይነግድ ነበር። በመጨረሻ ይኸው ፍፁም ሰብአዊነታቸውን አጥተው፣ ለታሰረ በሽተኛ መድሃኒት እስከ መከልከል ደረሱ። ያውም አብሮአቸው ለደማና ለቆሰለ ጓደኛቸው..."

አቀርቅሬ ከመስማት በቀር አስተያየት አልሰጠሁም።

ኮሎኔል አለበል ጥቂት ፋታ ወሰደና ቀጠለ፣

"...መንበረ ሃብቱ የምትባል እህት ነበረችኝ። ኢንጂነየር ናት። እኔን ለማየት ከደብረታቦር መጥታ ሁለት ቀናት ሙሉ እያለቀሰች ለምና ሳይፈቅዱላት ቀርተዋል። ወንድሜ ከጐንደር፣ ሌሎች ዘመዶቼ ካዲሳባ፣ የባለቤቴ እህት ከሳኡዲ አረቢያ እኔን ለማየት መጥተው ሳይሳካላቸው ተመልሰዋል።

*(መስከረም 11 ቀን እኔን ከቤቴ በስድስት ወታደሮች በወሰዱኝ እለት ከሳሞራ ጋር በስልክ ስንነጋገር ቤቴ እንደማይፈተሽ ገልፆልኝ ነበር።*

*ውሸቱን ነበር።*

*ስድስት ሰዎች ከቤቴ ጀርባ ተዘጋጅተው ኖሮ፣ ልክ እኔ እንደሄድኩ ቤቴን ለመፈተሽ ገብተው ኖሮአል። ሁዋላ እንደሰማሁት ባለቤቴ፣*





*'ምን ፈለጋችሁ?' ትላቸዋለች።*

*'ቤቱን ልንፈትሽ ነው' ይሏታል።*

*ከሳሞራ ጋር ያደረግነውን የስልክ ንግግር ስለሰማች፣*

*'ቤቱ እንዳይፈተሽ ከሳሞራ ጋር ሲነጋገሩ ሰምቻለሁና ቤታችን አይፈተሽም' ትላለች።*

*ሲነታረኩ ቆይተው እኩለ ሌሊት ላይ ወታደሮቹ በሃይል ለመፈተሽ ሙከራ ሲያደርጉ ባለቤቴ ወደ ደጅ ወጥታ እሪታዋን ታቀልጠዋለች። ሲግናል በሚባለው ግቢ 800 ያህል አባወራ ይኖራል። ሁዋላ እንደሰማሁት ባለቤቴ እሪታዋን ስታቀልጥ የአካባቢው ሰው ሁሉ ተገልብጦ ወደ ቤታችን ይመጣል። በመቶዎች የሚቆጠር ሰው ተሰብስቦ ቤታችንን ሲከበው ፈታሾቹ ይደናገጣሉ፣*

*'እኛ ሀጋዊ ነን! እኛ የተበጠበጥነው በቅንጅትና በሻእቢያ ነው!' ብለው ይናገራሉ።*

*ቅንጅት እኔ መሆኔ ነው። ሻእቢያ ደግሞ ሚስቴ። የሚገርመው ግን ሚስቴ አስመራ የተወለደች ኢትዮጵያዊት ነበረች። አባቷ አማራ ነው። እናቷ ደግሞ ከትግራይ። ንግስት ፋሲል ነው የምትባል። በጣም ጥሩ ስነምግባር ያላት ጠንካራ ሴት ናት። ያ ወታደር ባለቤቴን "ሻእቢያ' ሲላት፣*

*'ሂድና ራስህን መርምር!' ስትል መለሰችለት።*

*ፈታሾቹ ወታደሮች የህዝቡን ግርግር አልፈሩም። ምንተእፍረታቸውን፣ 'ካልፈተሽን አንሄድም!' በማለታቸው፣ የአካባቢው ሰው ባለቤቴን አግባብተዋት ቤታችን ተፈተሸ። አንዳችም ያገኙት መረጃ ወይም የጦር መሳሪያ አልነበረም። የግል ማስታወሻዎቼን፣ ሰነዶች፣ የትምህርት መፃህፍት፣ የልጆች መማሪያ ኮምፒውተር፣ ሲዲዎች፣ የእኔን ልዩ ልዩ የትምህርት ማስረጃዎች ጨምሮ ወረቀት የተባለውን ሁሉ በጆንያ አስረው ወሰዱ።)*

ከታሰርኩ በሁዋላ ባለቤቴ የታሰርኩበትን አድራሻ እንደምንም ብላ አጊኝታ ከአዲሳባ ሃረር ድረስ ልትጠይቀኝ መጥታ ነበር። መጀመሪያ እዚያ አለመኖሬን የምስራቅ እዝ ምክትል አዛዡ ነገራት። ወዲ እምበይተይ የሚባል ጄኔራል ነው። እሷም፣ "የታሰረው እዚህ መሆኑን ሰምቻለሁ" ብላ ናትናኤል የተባለውን የአራት አመት ልጄን ይዛ፣ ከጠዋቱ 2 ሰአት እስከ 10 ሰአት ፀሃይ ላይ ከልጇ ጋር ስታለቅስ ውላ

በመጨረሻ ለአምስት ደቂቃ ብቻ ፈቀዱላት።

ሰቀቀን ነበር የሆነብን።

በታሰርኩ በአስረኛው ወር አንድ መርማሪ ቡድን መጣና ለጥያቄ አስጠሩኝ። አዋሳ ግምገማ ላይ ያነሱትን ጥያቄ መልሰው ጠየቁኝ። ምላሽ ሰጠሁ። ምርመራቸውን አጠናቀው ሄዱ። እኔም ወደማጉሪያዬ። እንደገና በ14ኛው ወር አራት ወታደሮች መጥተው፣

'ወደ አዲስ አበባ ልንወስድህ ነው' አሉኝ።

ጠዋት ተነስተን ማምሻው ላይ ታጠቅ ጦር ሰፈር ገባን። እዚያ ወስደው ከ800 እስረኛ ወታደሮች ጋር ቀላቀሉኝ። ከዚህ ቀደም ከማውቃቸው መኰንኖች ጋር እስርቤት ውስጥ ተገናኘን። ኰሎኔል አበበ፣ ኰሎኔል ተስፋዬ፣ ሻምበል ፍርድአወቅ፣ ሻምበል ካሳሁን እና ሌሎችም ተሰባስበው አገኘሁዋቸው።

ሲያዩኝ በጣም ደነገጡ።

እኔ ስታሰር እነሱ ገና አልታሰሩም ነበር። ብዙዎቹ የሚኖሩት ሲግናል ግቢ ነበር። እኔ የታሰርኩ ጊዜ ባለቤቴ እንዴት እሪታ አሰምታ ግቢው እንደተተራመሰ፣ የባለቤቴ ድርጊት እንዴት ህዝቡን እንዳስደሰተ አጫወቱኝ። 'ሞቶአል' ብለው ተስፋ ቆርጠው እንደነበር ጭምር ነገሩኝ።

ሙሉ ሌሊቱን ሳንተኛ ስንጨዋወት አደርን።

በ14ኛ ወር የሰው ሽታ በማግኘቴ፣ የተሻለ ምግብ በመብላቴና በመተኛቴ እንደ አዲስ የተወለድኩ መስሎ ተሰማኝ። ታጠቅ በገባሁ በአምስተኛ ቀኔ ደግሞ ኰሎኔል አስካለ የተባለች የመከላከያ ፍትህ ቢሮ ሃላፊ ወደ ቢሮዋ አስጠራችኝ። የጀኔራል አበበ (ጀቤ) ሚስት ናት። ሌሎች ኰሎኔሎችም አብረዋት ነበሩ። ልታባብለኝና ልታታልለኝ ሞከረች። አብረዋት የነበሩትም ምንም ወንጀል እንዳልተገኘብኝ ገለፁልኝ።

አዳመጥኳቸው።

አስካለ የሃረሩን የእስር ቤት ሁኔታ አንስታ፣

'እኛ ህክምና አልከለከልንም። ቤተሰብ እንዳይጠይቅም አልከለከልንም። ምግብ እንዳይገባልህ አላልንም። የእነርሱ ስህተት ነው' በማለት ሁሉን ሳሞራ ላይ ለመጫን ሞከረች።

'አንቺ የማታውቂው ድርጊት ይፈፀማል ብዬ እንኳ አላስብም' አልኳት።





ታጠቅ በገባሁ በ7ኛው ቀን ህዳር 15፣ 2000 ከእስር ቤት ተፈታሁ። ስፈታ ያልተከፈለ ደሞዜ እንደሚከፈለኝና ሳሞራም እንደሚያገኘኝ፣ ስሜትም እንዳልይዝ ገለፁልኝ።

ከእስር ከተፈታሁ ከአንድ ሳምንት በሁዋላ ሳሞራ በፀሃፊው በኩል ወደ ቢሮው አስጠራኝ። እኔም በቀጠሮው መሰረት ህዳር 30 ቀን 2000 ከሳሞራ ጋር ተገናኘሁ።

ከወንበሩ ተነስቶ በክብር ሰላምታ አቀረበልኝ።

ሳመኝ!

እኔም አፀፋዊ ሰላምታ ሰጠሁትና ቁጭ አልን።

'እስር ቤት እንዴት ነበር?' ሲል ጠየቀኝ።

የእስር ቤቱን አሰቃቂ ሁኔታ ሁሉ ዘረዘርኩለት።

አዳምጦ ሲያበቃ፣

'ሁሉም ለፈተና ነው' ሲል ፈገግ ብሎ ነገረኝ። አያይዞም፣ '...በአንተ ላይ አንዳንድ ጥርጣሬዎች ነበሩን። አሁን ግን ብዙም የተረጋገጠ ነገር አላገኘንም' አለ።

በትእዝብት ማዳመጤን ቀጠልኩ። ሳሞራ ሲያመነታ ቆየና እንዲህ አለ፣

'አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ?'

'እሺ ጠይቀኝ'

'አማሮች ተደራጅታችሁ እንደነበር ምንም ጥርጣሬ የለንም። አንተም የአማሮችንም የኦሮሞዎችንም አደረጃጀት ታውቃለህ። ይህን ምስጢር ንገረኝና ወደፊትም ከእነዚሁ በምስጢር ከተደራጁት ሰዎች ጋር አብረህ መስራትህን እንድትቀጥል እናደርጋለን። ለዚህም የፈለግኸው ቦታ እመድብሃለሁ!' አለኝ።

በአጭሩ ምላሽ ሰጠሁት።

'ምንም የማውቀው ነገር የለም። ወደፊትም በአሰብከው ነገር ከእኔ የምታገኘው ነገር የለም። ምክንያቱም ምንም ነገር የለምና' አልኩት።

እንደገና ሳሞራ ስሜታዊ ሆነ። ልንግባባም ሳንችል ቀረን። በመጨረሻ፣

'ወደ ሰሜን እዝ ትመደባለህ። እስከዚያው ጠብቅ' አለ።

ይህን ሲለኝ እኔም ቅድመ ሁኔታ አስቀመጥኩ።

'እኔ እንደታሰርኩ ለሰራዊቱ ገልፃችሁዋል። ጠላት መሆኔን አውጃችሁብኛል። ወንጀል ለመፈፀም የተዘጋጀሁ

እንደነበርኩ ተናግራችሁዋል። ስለዚህ ወደ ስራ ገበታዬ ከመመለሴ በፊት በደብዳቤ ወይም በአካል እኔ ላይ የተነገረው ወንጀል ሃሰት መሆኑ እንዲስተባበል እፈልጋለሁ'

ሳሞራ ይህንን እንደማያደርግ ቁርጡን ነገረኝ። 'መንግስት ግለሰብን ይቅርታ አይጠይቅም' አለኝ።

በዚሁ ተለያየን።

ከአንድ ወር በሁዋላ እንደገና ጠራኝ።

'የነገርኩህን ሁኔታ አሰብክበት ወይ?' ሲል ጠየቀኝ።

'የማላውቀውን አውቃለሁ አልልህም። ያልነበረውን ነበረ አልልህም። ስለዚህ ያሰብኩበት ነገር የለም። ስለምደባው ከሆነ ግን የትም ቦታ ለመስራት ዝግጁ ነኝ። የምጠይቀው የማረሚያ ደብዳቤ እንድትፅፍልኝ ነው። በስህተት እንደ ወነጀላችሁኝ ካልገለፃችሁ ግን የፈለጋችሁትን ርምጃ ውሰዱ እንጂ አልሰራም' አልኩት።

ሳሞራ በጥላቻ አይኑ እንደ ቀስት ከወጋኝ በሁዋላ፣

'ስማ! አለበል!' አለኝ ረጋ ብሎ '...የቀበርናቸውን የአያቶቻችሁን አፅም ቆፍራችሁ ለማውጣት እየሰራችሁ ነው። አይሳካላችሁም። አርቀን ቀብረናቸዋል። ቆፍራችሁ ልታወጧቸው አትችሉም። እናንተንም በተመሳሳይ ጉድጓድ እንቀብራችሁዋለን!' አለኝ።

እኔም በተመሳሳይ ርጋታ ምላሽ ሰጠሁ።

'ሳሞራ! አያቶቻችንን እኮ አብረን ነው የቀበርናቸው። ብቻችሁን አልቀበራችሁዋቸውም።'

ይህን ብዬው ከሳሞራ ቢሮ ወጥቼ ሄድኩ።

የደረስንበት መደምደሚያ ከሰራዊቱ እንዲያሰናብተኝ ነበር። ልክ በወሩ መጨረሻ ላይም የስንብት ደብዳቤ ተሰጠኝ።

ጥር 2000 ከመከላከያ ተሰናበትኩ።

ርግጥ ነው፣ ይህ የሽንፈት ምልክት አልነበረም። በአዲስ አእምሮና በአዲስ መንፈስ ለሌላ ትግል ዝግጁ ነበርኩ። የኔን ያህል የስርአቱን አስከፊ ገፅታ ማን ያየ አለ? የገዳይ ቡድን ባልደረባ መሆኔ ብቻ አልነበረም አስከፊው ገፅታ። የገዛ ወገኖቼን የሚገድለው ቡድን አመራር መሆኔ ነበር ስቃዬን ይበልጥ መራራ ያደረገው።

እና ምን ማድረግ ይጠበቅብኝ ነበር? ልጆቼን ይዤ ከሃገር መሸሽ? የለም! ያንን ላደርግ አልችልም። ይህ የሽፍታና





የቀማኛ ቡድን እንዴት በእግሩ እንደቆመ አውቃለሁ። አሰራራቸውን ብቻ ሳይሆን፣ መግቢያና መውጫቸውን፣ ማምሺያና መዋያቸውን ጭምር አውቃለሁ። አስተሳሰባቸውን አውቃለሁ። ከባድ ሃጢያት የሚሆነው የማውቀውን እንዳወቅሁ ይዤ ዝምታን ከመረጥሁ ብቻ ነበር ..."

# - 17 -

# ወንዞች እና ኅርፎች

አበባየሆሽ - የለም! አበባየሆሽ የለም፣
ባልንጀሮቼ ጠጡ በተራ፣ ፀሃይ እስክትሸሽ ጨለማን አፍራ፣
ባልንጀሮቼ ጠጡ በተራ፣ቱቦ ስር ወድቅን እስክናቅራራ፣
እንኳን ቀረርቶ የለኝም አቅም፣
እዚያው አድራለሁ - ጥርሴን ስለቅም፣
ኮማሪቶቼ ቅዱ ባካችሁ፣ ዶላር አላጣም የምከፍላችሁ፣
እንኳንስ ዶላር የለኝም ዱዲ፣ የጠጄ ጌታ ምታኝ እንግዲህ
አልመታም ካልከኝ ልሂድ ስለው፣ ቦዩን ጠራና ጎኔን አለው፣
ከጎኔም ጎኔን ኩላሊቴን፣ አረቄን ጥሯት መድሃኒቴን፣
ሰከረው ይቆዩን ሰከረው፣ ሰባት ብርሌ ሰብረው፣
ታመው ይቆዩን ታመው፣ ባመት ሺህ ኪኒን ውጠው፣
ይሸታል ጠጁን ጠጁን ሲጎትቱት እጁን፣
ይሸታል ቢራ ቢራ፣ ልጃችን ሲያቅራራ፣

(ግጥም - ታገል ሰይፉ)

**ወ**ንዝና ኅርፍ...

ወንዞች ከተራሮች ይፈልቃሉ። ኅርፍ መነሻው አይታወቅም። ኅርፎች ፈጥነው ያልፋሉ። ወንዞች ግን ለረጅም ጊዜ አሊያም ለዝንተ አለም ይኖራሉ። የወንዝ ጉዞ ለረጅም ጊዜ አያቋርጥም። ኅርፍ ተቀላቅሎ ካላደፈረሰው በቀርም ንፁህ ነው። ኅርፍ እለታዊ ነው። ቆሻሻና ግብስባሽ ያቀፈ፤ የድመትና የውሻ ሬሳ፣ የአህያ መንጋጋ፣ ቡትቶ ጨርቅ ሳይቀር ተሸክሞ የቻለውን ያህል አጓርቶ ከዚያ በራሱ ጊዜ ድራሽ አባቱ





ይጠፋል።

ወንዞችና ኅርፎች...

በውነቱ በኅርፍ ሊመሰሉ የሚችሉ ተሳዳቢ ፀሃፊዎች ሞልተውናል። እነዚህን ብእረኞች "ስድብኤል" ሲል በስማቸው የሰየማቸው ስብሃት ገብረእግዚአብሄር ነበር። እኔም ታዲያ በምፅፋቸው ፅሁፎች ምክንያት ስድብ አዘል ደብዳቤ ሲገጠመኝ በተከረከመ አረንጓዴ የሳር መስክ ላይ ጉች እንዳለ የውሻ ኩስ እየዘለልኩ የመሻገሩን ጥበብ ተላምጄዋለሁ።

"የጋዜጠኛው ማስታወሻ" ከታተመ በሁዋላ ከአስር ወራት በላይ አያሌ በጎ እና ክፉ መልእክቶችን ተቀብያለሁ። ወይም አንብቤያለሁ። እነዚህንም "ወንዞች" እና "ኅርፎች" ብዬ ሰየምኳቸው። ኅርፍና ወንዝ በማለት የለየሁዋቸው በድጋፍና በተቃውሞ ጎራ ሳይሆን በይዘታቸው ነው። አንዳንድ "የዋህ" የወያኔ ካድሬዎች ስድብ ደግሞ የሚያስቅ ሆኖ አግንቼዋለሁ።

እንዲህ የሚል ደብዳቤ ደርሶኛል፣

'ኦሮሞና አማራውን በኛ ላይ ለማነሳሳት የሞነጫጨርከው መፅሃፍ መሆኑን ደርሰንበታል። አታመልጠንም አንተ የሻእበያ ባንዳ! ለትምክህተኞች አጎብዳጅ! የጠባቦች ተላላኪ! የጥገኛ ትምክህተኞች አጨብጫቢ! የተለጣፊ ነፍጠኞች ሎሌ። ጥቅማቸው የተነካባቸው ደመኛ ጠላቶች ፍርፋሪ ለቃሚ! ለፕሮፌሰር ተብዬ አማሮች ያጎበደድክ የሻእቢያ ርዝራዥ። ጭቁን ብሄረሰቦቻችን በህወሃት አመራር በዴሞክራሲ ተንበሽብሸው፣ የልማት ጎዳናው ፖሊሲ ተቀይሶ፣ በህዳሴው ዋዜማ፣ (ሚሊኒየማችን) አንፀባራቂ ድል የጨበጠበት ጊዜ ላይ መሆናችን ሃቅ ነው።"

ከላይ ያለውን አንቀፅ 11 ጊዜ ብታነቡት እንኳ ሊገባችሁ አይችልም። አማርኛ መሆኑ ራሱ ያጠራጥራል። ይህን የፃፈው ተጋዳላይ ደግሞ ከOpen University በህግ የማስትሬት ዲግሪ በጡንቻው የጨበጠ የዘመናችን ሹም ነው። ይህ ሹም ኢትዮጵያ የተባለችው ሃገር ላይ አዛዥ ናዛዥ የነበረ ወይም የሆነ የ50 አመት አዛውንት መሆኑን ስትገነዘቡ የሚቀራችሁ ብቸኛ አማራጭ ስቅስቅ ብሎ ማልቀስ ይሆናል።

እንዲህ ያለ ደብዳቤ ከፃፉልኝ አድካሚ ሰዎች አንዱ ተክሉ ተክላይ (አታክልቲ) ይባላል። ሆላንድ ላይ በስደት ነዋሪ ሆኖአል። "አረና" የተባለውን የገብሩ አስራት ድርጅት

ከመቀላቀሉ በፊት 'ወይን' የተባለው የወያኔ ጋዜጣ ዋና ተቆጣጣሪ ነበር። ይህ አዛውንት መሳደብ እጣ ክፍሉ ናት። እድሜው ከ50 ቢያልፍም ሰከን ሊል አልቻለም። ሰዎች ሁሉ የሚንቁት ይመስለዋል። ሲፅፍም ሆነ ሲናገር ጥላቻና ስድቡን ያዘንበዋል። ስለ ህወሃት ሲገልፅ ምንጊዜም፣ 'ትምክህተኛውን በማንበርከክ' ካላለ አይሆንለትም። ይሄ የተሳዳቢነት ችግር የአታክልቲ ወይም የተክሉ ተክላይ ችግር ብቻ አይደለም። የህወሃት ካድሬዎች በጥቅሉ በዚህ ልማድ ተጠልፈዋል። የወያኔም ብቻ አይደለም። የሃገራችን ባህልና ልማድ እየሆነ በማደግ ላይ ይገኛል። የወያኔ ሰዎች እንደ ሙያ ተራቀውበታል። የስድብ ችሎታችንም እንደ ኢኮኖሚያችን 11% እድገት አሳይቶአል።

*(ኢኮኖሚያችን ለምን 10% ወይም 12% እንዳላደገ አውቃችሁዋል? ወያኔ ከ11 ቁጥር ጋር 'ፍቅር እስከ መቃብር' የተባለ ቃል ኪዳን ገብቶአል።)*

"ተለጣፊ ነፍጠኛ" የተባለችውን ቃል መጀመሪያ የሰማሁዋት ቀን በጣም ነበር የሳቅሁት። ለብርሃኑ ነጋ ተብላ የተፈጠረች ቃል ነበረች። ብርሃኑ ወደ ፖለቲካው ብቅ ሲል ለስድብ ወይም ለፍረጃ አስቸግሮ ነበር። "ጠባብ" እንዳይሉት፤ "ኢትዮጵያዊነት" ሆነ መፈክሩ። "ትምክህተኛ" እንዳይሉት "ጉራጌ" ሆነባቸው። "ነጋዴ" እንዳይሉት "ምሁር" ነው። "ተለጣፊ ነፍጠኛ" የምትለው ተገኘችለት።

በአንድ ውይይት ላይ ተፈራ ዋልዋ ብርሃኑ ነጋን በዚህችው ቃል ሲገልፀው ብርሃኑ፣

"የአቅም ግንባታ ሚኒስትራችን ዛሬ ተሳክቶላቸዋል። የጉራጌ ነፍጠኛ መስራት ችለዋል" ሲል አላግጦበታል።

* * *

እርግጥ ነው፤ እኔም ራሴ የጋዜጠኛነትን ሙያ 'አቦጊዳ - ሄውዞ' ብዬ የጀመርኩት ሙሉጌታ ሉሌን እና ፕሮፌሰር መስፍንን በመሞለጭ ነበር። በነዚያ የተምታቱ ዘመናት እነዚህን ሰዎች እያሳደድን በስድብ ጅራፍ ካልገረፍን ስራ የሰራን አይመስለንም ነበር።

አለቆቻችንም፣ "ጎበዝ! አንበሳ! በርታ! ብላ! ጠጣ!" የሚሉን እንዲህ ያሉ ተቃዋሚዎችን በስድብ አፈርድሜ





ስናስግጥላቸው ነበር። በተለይ፣ "ኢትዮጵያዊነት" የሚል ባንዴራ የሚያውለበልቡ ብቅ ካሉ አለቆቻችን በትግርኛ ይናደዳሉ።

ዛሬ እንደምገነዘበው የጋዜጠኛነት ስራውን በስድብ የጀመረ ሰው እግዚአብሄር ካላገዘው በቀር ከገባበት የስድብ አዙሪት ከሆነ የስድብ ጎርፍ መውጣት አይቻለውም።

ከተሳዳቢነት ጎርፍ ለመውጣት ትግልና ሂደት ይጠይቃል። መባነን ያሻል። ለመባነንም መነሻ ያስፈልገዋል። በኔ በኩል ስድብኤል ከተባለው ጎርፍ በጊዜ ተላቅቄያለሁ። ከተሳዳቢነት ወራጅ ጎርፍ ተንፏቅቄ እወጣ ዘንድ በርካታ ሁኔታዎች አግዘውኛል።

አንድ ጊዜ ሙሉጌታ ሉሌ፣

"ያልሰደቡኝ እለት ቅር ይለኝ ጀምሮአል" ሲል አላገጠብን። በዚያን ሰሞን ይህ አባባሉ በጣም ሲከነክነኝ ከረመ። የሙሉጌታ ሉሌን ፅሁፎችም እንደዋዛ ብድግ አድርጌ በቅጡ ማጤን ጀመርኩ።

በእንክብካቤ እንደተያዘ ፓርክ ንፁህ ነበሩ። ንዴት፣ ስድብ፣ ቁጣ፣ ፉከራ፣ ያዙኝ ተዉኝ የለባቸውም። ጋዣውን እያስተኛ እንደሚፈስ ጅረት በፀጥታ ይወርዳሉ። ሙሉጌታ ሲፅፍ የሰዎችን ሰብእና አይነካም። በዝምታ ይናገራል። የኔን ፅሁፎች ደግሞ አነሳሁዋቸው። ገና ከርእሱ ስድብ ነበሩ፣

*"መቅዘፊያው የጠፋበት ፕሮፌሰር"*
*"ከተሰነጠቀ ደወል የሚወጣ ድምፅ"*
*"ተቀብራችሁዋል! አርፋችሁ ተኙ!"*
*"ውሾቹ ይጮሃሉ! ግመሉ ጉዞውን ቀጥሎአል!"*

ርእሱን አልፌ ወደ ይዘቱ ስገባ የሚሰቀጥጡ ቃላት ግንባሬን በመዶሻ ይደውሉኝ ያዙ። ልዩነታችን ግልፅ ነበር። ሙሉጌታ አይሳደብም። እኔ እሳደባለሁ። ወንዝና ጎርፍ ነበርን። የኔ ፅሁፍ ጎርፍ ነበር። ግብስባሽ ተሸክሞአል። የበሬ ቀንድ፣ የተቀዳደደ አንድ እግር ጫማ፣ ጣሳ፣ ግንድ፣ የሰሌን ኮፍያ ቅዳጅ፣ የሞተ ዶሮ፣ የጠርሙስ አንገት፣ መሃሉ የተቀደደ ትሪ እነዚህን ሁሉ ያቀፈ ጎርፍ ከየት መጣህ ቢባል ከየት ነኝ ይላል? መነሻ የለው መድረሻውን አያውቅ። የሙሉጌታ ሉሌ መጣጥፎች ግን እንደ አባይ ወንዝ ነበሩ። እንደ ማርቆስ ዋሽንት

ቃና ነበራቸው። እንደ አክሱም ሃውልት ደግሞ መልክና ቅርፅ ነበራቸው። መነሻና መድረሻቸው ይታወቃል። ይዘምራሉ። ያወጋሉ።

እኔስ?

ከመሬት ተነስቼ እናደዳለሁ። ምን ያናድደኛል? ማለት የምፈልገውን ረጋ ብዬ አልናገርም? የምን እንደ ክላሽ መንጣጣት ነው?

በዚያው ሰሞን ይመስለኛል ጋዜጠኛና ገጣሚ አበራ ለማ ወደ ቢሮዬ ደወለና ማምሻው ላይ ቀጠረኝ። ቢራ ጋብዞኝ ሲያበቃም እንዲህ ሲል መከረኝ፣

"ስድብ አትፃፍ! ስድብ ስነፅሁፍ አይደለም። ቆሻሻ ብቻ ነው። ቃላት አትደርት። ለሰዎች ስም ተጠንቀቅ። ለጓደኛነት ክብር ስጥ። ቅፅል አታጅጎድጉድ። ቃላት መከመር ጥበብና ውበት አይደለም። ይህን ውብ ብእርህን አታበላሸው። እባክህ!?"

አበራ ለማ ከመከረኝ በሁዋላም ቢሆን ወዲያውኑ ስድብ አልተውኩም። ስድብ የሌለበት ፅሁፍ ለመፃፍ ሞከርኩና አቃተኝ። ለካስ መከራከሪያ ሃሳብ ካጠረህ ጭንቅላትህ ውስጥ የሚቀረው የመመከቻ ዱላ ስድብ ብቻ ይሆናል። እየቆየሁ ግን በጭቃ ከተሞላው የስድብ ጎርፍ እንደምንም ወጣሁ። ዳርቻው ላይ ቆሜ ስድብኤል የተባለው ጎርፍ ለጆሮ የሚቀፉ አፀያፊ ግብስባሾችን ይዞ ሲጓዝ ቆሜ አየሁት። እናም ወደ ተራራው ጫፍ ወጣሁ። ንፁህ ወንዝ እየዘመረ ሲጓዝ ሰማሁ። ካልተሳሳትኩ የወንዙ ስም ፑሽኪን ይባል ነበር…

ልብሷ የባላገር - አየሯ ገጠር፣  
ኩለንታዊ ውበት - ይዛ የምትኖር፣  
አየሁዋት በመስኩ - ወደ ገጠር ሄጄ፣  
ተፈጥሮን ስፈልግ - ተፈጥሮን ወድጄ፣



# - 18 -

# የከሸፉ ኩዴታዎች

እኔ ምናገባኝ - የምትሉት ሃረግ፣  
እሱ ነው ያረዳት - ሃገሬን እንደ በግ፣  
የተሰኘች ግጥም - ልፅፍ አሰብኩና፣  
ምናገባኝ! ብዬ - ቆጭ አልኩ እንደገና፣

(ግጥም - ኑረዲን ኢሳ)

"ክቡር ኮሎኔል! ዛሬ የመጨረሻችን መሆኑ ነው። ህወሃት 'እነ መለስ' እና 'እነ ተወልደ' የተባለ ሁለት ጎራ ለይቶ ሲተራመስ እኔም እዚያው ነበርኩ። በቀዳሚው መፅሃፌ የማውቀውን ያህል መፃፌንም አይተኸው ይሆናል። በአንተ እይታ ሌላውን ገፅታ እስኪ አውጋኝ?"

"ወንድሜ ሆይ! የህወሃት ክፍፍል ጉዳይ ላይ የተለየ የምነግርህ የሚኖር እንኳ አይመስለኝም። ይልቁን ስላከሸፍኩትና ስለከሸፈብኝ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ላውጋህ…"

* * *

እና እንዲህ ሲል ቀጠለ ኮሎኔሉ…

"…*የጋዜጠኛው ማስታወሻ'* ላይ የፃፍከውን አይቼዋለሁ። አንድ ስህተት ያገኘሁበት ይመስለኛል። የህወሃት አመራር የመጨረሻውን ስብሰባ ያካሄደው አንተ በመፅሃፍህ እንደገለፅከው ሂልተን ሆቴል አልነበረም። እዚያው ቤተመንግስት ግቢ ውስጥ ነበር የተሰበሰቡት። ሆኖም ስብሰባቸው ሂልተን ሆቴል በመካሄድ

ላይ መሆኑን ያስወሩ ነበር። የወሬው አላማ ምናልባት ያልተጠበቁ ጥቃቶችን ለመከላከል ሊሆን ይችላል..."

ኮሎኔሉ አያያዘና ቀጠለ፣

"...እርግጥ ነው፤ በወቅቱ ያስተዋልኳቸው አንዳንድ አስገራሚ ትዝብቶች ነበሩ። በጦርነቱ ወቅት የወያኔ አመራር የመከፋፈል ነገር እንደነበረበት በተለያዩ አጋጣሚዎች እንሰማ ነበር። ሰራዊቱን በበላይነት የሚመራው ያው ፃድቃን ስለነበር ሁሉም የጦር ከፍተኛ አመራር አባላት ልብና ጆሮ ሁሉ ለፃድቃንና ከፃድቃን ጋር ነበር። ሳሞራ እና ዮሃንስ የተባለው የመረጃ ክፍሉ ጄኔራል ብቻ ነበሩ በተፃራሪነት የሚታዩት።

"...አንድ ጊዜ ከክፍለ ጦር አመራር በላይ የምንገኝ አዛዦች አዲግራት ላይ የአሸዋ ገበታ (sand model) ልምምድ ላይ ሳለን ጄኔራል ሰዩም በአንድ የውጊያ እቅድ ውይይት ላይ፣

'ሳሞራን ብናማክረው' ሲል ይጠይቃል።

የመድረኩ መሪ የነበረው ጄኔራል ብርሃነ ነጋሽ የሰዩምን አሳብ በማጣጣልና እጁን በማወናጨፍ፣

'ሳሞራን ተወው! ሳሞራ አቅሙን ጨርሶአል። ምንም ጠብ የሚል ነገር ከሱ ልናገኝ አንችልም' ሲል ተናገረ።

ይህ የመከፋፈል አዝማሚያቸውን በይፋ የሚጠቁም አንድ ምልክት ነበር። በርግጥም ፃድቃን ሳሞራን አግልሎት ነበር። ሰአረን ቡሬ ግንባር፣ ብርሃነ ነጋሽን ዛላንበሳ፣ አበባውን ባድመ ግንባሮች አዛዥ አድርጎ ሲመድብ ሳሞራ የኑስን አዲሃገራይ አስቀምጦት ለአበባው ድጋፍ እንዲያደርግ ነበር የመደበው። ዮሃንስም በዚያው በባድመ አካባቢ ያለ ሥራ እንዲቀመጥ አድርጎት ነበር።

ይህ ለሳሞራ ውርደት ነበር።

በርግጥም በወቅቱ ሳሞራ ለመዝናኛ የኪስ ገንዘብ እንኳ አጥቶ የተቸገረበት ጊዜ ነው። ከግለሰቦች በግል ገንዘብ እስከመጠየቅ ደርሶ ነበር። የጄኔራል አበባው ኮር ልዩ ገቢ ቦርድ የነበረው ኰሎኔል አበበ ገረሱ ብዙ ጊዜ በአዘኔታ ለሳሞራ ገንዘብ ይሰጠው እንደነበር አጫውቶኛል።

ሌላ ጊዜ ደግሞ ባድመ ላይ አንድ ስብሰባ ተደርጎ ነበር። ስብሰባውን ፃድቃን ነበር ይመራው የነበር። በስብሰባው ላይ በረከትና አለምሰገድ ተገኝተው ነበር። የፃድቃን እይታ ለበረከትና ለአለምሰገድ እኩል አልነበረም። በረከት እንደ ልዩ





ጥበቃ አጃቢ ዳር ዳሩን ተገፍቶ ነበር። ሰራዊቱ ይህን ሁኔታ ታዝቦ በኢህአዴግ ውስጥ ውስጡን የሚብላላ መፈረካከስ ስለመኖሩ ይነጋገር ነበር። የወያኔ ሽኩቻ የተጀመረው ዞሮ ዞሮ የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ከታወጀ በሁዋላ ወዲያውኑ ነበር።

ከሃምሌ 1993 እስከ ጥቅምት 1994 ለአምስት ወራት ያህል የአጤ ምኒልክ ቤተመንግስት ተወጥሮ ነበር የሰነበተው። በዚያን ጊዜ እኔ የአግአዚ ክፍለ ጦር አመራር አባል በመሆኔ፣ ቢሮዬ እዚያው ቤተመንግስት ውስጥ ነበር። የሚካሄደውን በቅርብ ለመታዘብ እና ለመከታተል እድሉ ነበረኝ።

በቅድሚያ ክረምቱ ላይ የህወሃት ፖሊት ቢሮ አባላት ረጅም ጊዜ የፈጀ ስብሰባ አደረጉ። ከጠዋት የጀመሩ እስከ ምሽት አራት ሰአት ይዘልቃሉ። በየመካከሉ የሻይ እረፍት ነበራቸው። ገፅታቸው ላይ የጭንቀት ምልክት ይታያል። ንዴታቸውን ማቀብ የሚችሉ አለመሆናቸው መቼም ይታወቃል። ጠባያቸውና አነጋገራቸው ያው እንደ ጐረምሳ መገንፈል ነው። ሰከን ብለው እንደ ሃገር መሪ የመነጋገር ችሎታው ያጥራቸዋል። ለሻይና ለቡና ሲወጡ ሲጋራቸውን እያቦነኑ፣ እንደገና በየቡድናቸው እየሆኑ ድምፃቸውን ሳይቀንሱ ይንተከተካሉ።

መለስ ዜናዊ ግቢውን በእግሩ እየዞረ ወዲያ ወዲህ እያለ ሲንቀገቀኝ መውጫ ቀዳዳ የሚፈልግ የተዘጋበት ቀበሮ ነበር የሚመስል። አድርገውት የማያውቁትን ወደኛ ከሰብ እየመጡ ሻይ መጠጣት ጀምረዋል። የመለስን ከበብ የጠሉት ይመስላሉ። መለስ ዜናዊ ድጋፍ ማጣቱን፣ እያለቀለት መሆኑ እና የነተወልደ ቡድን እየነገሰ መሆኑን እንሰማ ነበር።

በነሃሴ ወር ላይ ስብሰባው ከፖሊት ቢሮ አባላቱ ወደ ማእከላዊ ኰሚቴው ተሻገረ። ቁጥራቸው ወደ 40 ይጠጋ ነበር።

የህወሃት ማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ እየተካሄደ ደግሞ ሌሎች የእንጀራ ልጅ ድርጅቶች ጐን ለጐን የራሳቸውን የማእከላዊ ኰሚቴ ስብሰባ እንዲያካሂዱ ታዘዋል። ብአዴን ከብሄራዊ ቤተመንግስት ጐን ካለው የእንግዶች ማረፊያ (Guest House) ከተባለው ቦታ ነበር የተሰበሰቡት። ኦህዴዶች ከዶክተር ነጋሶ ቢሮ መሽገዋል። የደቡብ ህዝቦች ደግሞ ኢህአዴግ ፅህፈት ቤት ውስጥ ነበሩ። የሁሉንም የጥበቃ ሃላፊነት አግአዚ ስለተረከበ ሂደቱን በቅርብ እየተከታተልኩት ነበር።

ብአዴን ስብሰባውን በአስር ቀናት ውስጥ አጠናቀቀ።

ደቡብና አህዴዶች ያለ ስምምነት ተነካክተው ተበተኑ። ለሶስቱም የእንጀራ ልጆች፣ 'በነበራችሁበት ቆዩና እኛ እስክንጨርስ ጠብቁ' የሚል ተነገራቸው።

የህወሃት ማእከላዊ ኰሚቴ አባላት በእረፍት ሰአት ወደ እኛ የሻይ ክበብ መምጣታቸውን ቀጠሉበት። አካባቢያቸውን ለመቆጣጠር እንኳ ሳይሞክሩ፣ የስብሰባ አጀንዳቸውን እያነሱ ይከራከራሉ። ወደለየለት ፀብ እያመሩ መሆኑን ማንም ሊገነዘበው የሚችል ነበር።

መለስ ዜናዊ ሁለት ጊዜ ያህል በእግሩ ከበር ውጭ ሊወጣ ሲል መልሰነዋል። ቀውሶ ነበር። በብስጭት እየጨሰና እያጨሰ ግቢውን በፈጣን ርምጃ ይዞረዋል። ሲጋራ ማጨስ አቁሞ ነበር። በዚያ ስብሰባ ላይ ግን እንደ አዲስ ያቦነው ጀመረ። አንድ አሳብ እያኘከ፣ አንድ ነገር እየገመደ ሳያውቀው ዝም ብሎ ወደ መውጫው በር ይገሰግሳል። ስንከለክለው እንደገና ይመለሳል።

ስብሰባው እየጠነከረ ሲሄድና ክፍፍሉም ከሚዛን በላይ እየሆነ ሲመጣ፣ የነተወልደ ቡድን ሃይል እያገኘ መሄዱ ግልፅ ሆነ ..."

ኰሎኔሉ ፋታ ወሰደና እንዲህ አለኝ።

"...ስለ ህወሃት ክፍፍል ስትፅፍ አንድ ያልገለፅከው መረጃ አለ። 'ክፍፍሉ ይፋ ከመሆኑ በፊት መለስ አንድ አደገኛ ተንኰልና ቁማር ተጫውቶአል። ክንፈ ገብረመድህንን ወደ እነተወልደ እንዲያዘነብል አደረገው። ማታ ማታ ታዲያ እነ ተወልደ አህዴዶችንና ደቡቦችን ይዘው መለስን ለመጣል የሚያደርጉትን ምክክር ሁሉ ክንፈ ፀረ-መለስ መስሎ ከነተወልደ እየቀዳ ሁሉን ለመለስ ያቀብል ነበር። እናም ላይ ላዩን ሲታይ እነተወልደ የጠነከሩ ይመስል ነበር።

እነ ተወልደ፣ 'ክንፈን ይዘናል' ብለው ስለገመቱ ተዘናጉ። ሰራዊቱም በእጃቸው ነበር። በጥቅሉ ደህንነቱና ሰራዊቱ ስለተያዘ 'መለስ አንዳችም ሃይል አልቀረውም' ብለው ገመቱ። እነተወልደን ከመለስ በላይ የጐዳቸው ክንፈ ነበር። ዶክተር ነጋሶ በስዬ ተፅፎ የተሰጠውን ለሰራዊቱና ለህዝቡ የሚተላለፍ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ደብዳቤ ይዞ ቀን እየጠበቀ ነበር። በመጨረሻ እነተወልደ በድምፅ ሲሸነፉ፤ በቀላሉ ክንፈን በማዘዝ መለስን ወደ እስር ቤት መላክ እንደሚችሉ ገምተው





ነበር። ባልጠበቁት መንገድ እንደ ተልባ እስር ሁሉም ከእጃቸው አፈተለከ። መለስ ታማኝ አማካሪዎቹን ስብሃት ነጋ፣ አዲስአለም ባሌማ፣ በረከት ስምኦንና ሙሉጌታ አለምሰገድን ይዞ የጥይት ድምፅ ሳይሰማ የተጐነጐነበትን ሴራ ማክሸፍ ቻለ። መንግስታዊ ስልጣኑ ችግሩን ለመፍታት አግዞታል። ቅዱሳን ነጋ፣ አርከበ ኡቅባይ፣ ሃለቃ ፀጋይና ስዩም መስፍን የመሳሰሉትም የትግራይን ካድሬ በማደራጀት አቢይ ሚና ተጫውተዋል።

የቤተመንግስቱ ስብሰባ ተቋርጦ ሁሉም ወደ መቀሌ ተጓዙ። እንደሰማነው ከሆነ በመቀሌው ኮንፈረንስ አንድ አከራካሪ ጉዳይ ብቻ ነበር የተነሳው።

ይህም 'ስብሰባውን በሊቀመንበርነት ማን ይምራው?' የሚል ነበር። መለስ 'እኔ ነኝ ሊቀመንበሩ። እኔ መምራት አለብኝ' አለ። እነተወልደ፣ 'ሌላ ጊዜያዊ ሊቀመንበር ያስፈልገናል' ሲሉ ልዩነት አነሱ።

በዚህ ያለመግባባት ሆነ።

እነተወልደም ስብሰባውን ረግጠው ወጡ። ይህቺ ቀን ለመለስ ዳግም የውልደቱ ቀን ሆነችለት።

የመለስ ቡድን ወዲያውኑ የ12 ሰዎችን ስም ዝርዝር ፅፎ ቤተመንግስት እንዳይገቡ አገደ። ይህን ደብዳቤ የፃፈልን ሙሉጌታ አለምሰገድ ነበር።

በሶስተኛው ቀን ነው መሰለኝ ስዬ አብርሃ ወደ ቤተመንግስት መጣ። እኛም የተባልነውን ገለፅንለት። አንዳችም ቃል ሳይተነፍስ መኪናውን አዙሮ ተመለሰ። ብዙም ሳይቆይ ቢተው በላይ መጣ። ለእሱም ተመሳሳዩን ገለፅንለት። እሱ ግን ተሳደበ፣

'እነዚያ ትምክህተኞችና የባንዳው ልጅ ነው ያዘዟችሁ?' ብሎ ተወናጭፎ ተመለሰ። 'የባንዳ ልጅ' ማለቱ መለስን ሲሆን፣ ትምክህተኞች ደግሞ ብአዴኖች መሆናቸው ነው።

ከዚያ በሁዋላ የመጣ አልነበረም።

እነ መለስ በመቀሌው ስብሰባ ድል ማድረጋቸው ሲሰማ ክንፈ ገብረመድህንና ሃሰን ሺፋ ግለሂስ በማድረግ የነመለስን ቡድን ተቀላቀሉ ተባለ። ይህ ግን የሚታመን አይደለም። ሁለቱም ገና ከመጀመሪያው ከመለስ ጐን ነበሩ።

የህወሃት አመራር በዚህ ሁኔታ ሲታመስ ሌሎች የእንጀራ ልጆችና መከላከያ ውስጥም ተመሳሳይ ውዝግብ ጦፎ

ነበር። ፃድቃን፣ አበበ ተክለሃይማኖት፣ ታደሰ ጋውና፣ ገዛኢ፣ ወዲ መድህን፣ ታደሰ ወረደ፣ ሰአረ ወዘተ እየተባሉ የሚታወቁት የህወሃት ጄኔራሎች በአንድ ቡድን ሆነው እነ ተወልደን ደገፉ። በሌላ ወገን ደግሞ ዮሃንስ፣ አባዱላ፣ አለምሸት፣ አበባው የተባሉት ጄኔራሎች በሳሞራ እየተመሩ መለስን ወገኑ። ማእከላቸውንም ጐልፍ ክለብ አድርገው ነበር የሚንቀሳቀሱት።

ጄኔራል ፃድቃን 600 የወታደር ሃይል ያላት አንድ ሻለቃ ጦር በድብቅ ሁርሶ እና ፍቼ አሰልጥኖ ብላቴ አስቀምጦአቸው ነበር። ከፃድቃን በቀር ይህን ጦር የሚያውቀው አልነበረም። ማንም አያዘውም።

የእኛ የአግአዚ አንድ ብርጌድ ጦር ታዲያ ብላቴ ለስልጠና ገብቶ በልምምድ ላይ ነበር። የብርጌዱ አዛዥ ሻለቃ ግርማይ ደቻሳ (ስብሃት) ይባላል። ምክትል አዛዡ ሻለቃ አምሳሉ መሰለ ይባላል። እኔ የአግአዚ ክፍለ ጦር አመራር በመሆኔ ቢሮዬ ቤተመንግስት ውስጥ ሆኖ አዲስ አበባ ነበር መኖሪያ ቤቴ።

አንድ ቀን ምሽት ሻለቃ አምሳሉ ስልክ ደውሎ፣

'ተዘጋጁ! ተብለናል። መኪናም መጥቶ በቅርብ ተዘጋጅቶአል። 'ሄሊኮፕተሮችም ሊመጡ ይችላሉ' ተብሎአል። 'ለአንድ ወሳኝ ጉዳይ ተዘጋጁ' ብለውናል። የምታውቀው ነገር አለ ወይ?' ሲል ይጠይቀኛል።

ከአንድ ሳምንት በፊት ታዲያ አዲሱ ለገሰ መኖሪያ ቤቱ ጠርቶን ነበር። በአዲሱ መኖሪያ ቤት የተገኘነው አራት መኮንኖች ነበርን። ጄኔራል አለሙ አየለ፣ ጄኔራል አሳምነው ፅጌ፣ ጄኔራል አከለ አሳየ እና እኔ ነበርን።

አዲሱ ለገሰ አጠቃላይ ሁኔታውን ገልፆልን ሲያበቃ፣

'እነተወልደ መፈንቅለ መንግስት ለማድረግ እየተዘጋጁ ነው። ኦሮሞና ደቡብንም ይዘዋል። ብአዴን ከመለስ ጐን ነው። ተጠናክረንም ሁሉን እየተቆጣጠርን ነው። በየአካባቢው የምታዩትን ምልክት ሁሉ ዝም ብላችሁ አትለፉት' ብሎን ነበር።

ሻለቃ አምሳሉ ደውሎ ይህን ሲነግረኝ ወዲያውኑ ለጄኔራል አበባው ደውዬ ነገርኩት። ስለ ጉዳዩ የሚያውቀው ነገር አለመኖሩን ገልፆልኝ፣ መልሶ እንደሚደውልልኝ ነገረኝ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በሁዋላ ሳሞራ ደውሎ ስለሁኔታው ጠየቀኝ። የሰማሁትን ነገርኩት።





ከግማሽ ሰአት በሁዋላ በድጋሚ ደውሎ ወደ ጐልፍ ክለብ ጠራኝ። እዚያ ስደርስ ከምሽቱ 4 ሰአት ሆኖ ነበር። አባዱላ፣ ባጫ፣ አለምሸትና አበባው ሳሞራን አጅበው ጠበቁኝ። በጉጉት ሲጠብቁኝ አገኘሁዋቸው። ሳሞራ፣

'ሁኔታው እንዴት ነው?' አለኝ።

በስልክ የተናገርኩትን ደገምኩላቸው።

ሳሞራ ሻለቃ አምሳሉን በስልክ ማግኘት ፈለገና ደውዬ አገናኘሁዋቸው። ከእኔ የሰማውን ከሻለቃውም አረጋገጠ። ከዚህ በሁዋላ ጄኔራሎቹ ለብቻቸው የተወሰነ ደቂቃ ተመካከሩ። በመቀጠል ሳሞራ ወደ ውስጥ ይዞኝ ገባና በፈፀምኩት ተግባር አመስግኖኝ ሲያበቃ፣ አጣዳፊ ግዳጅ ሰጠኝ።

ሳሞራ የራሱን ኰብራ ከነሾፌሩ ስለሰጠኝ ሌሊቱን ስገሰግስ አድሬ ከመንጋቱ በፊት ብላቴ ገባሁ።

የተሰጠኝ ትእዛዝ የአይሮፕላን ማረፊያውን በመቆፈር እንዳበላሸውና ይቺ ለልዩ ግዳጅ የተዘጋጀችው ብርጌድ እንድትታሰር ማድረግ ነበር።

እኔ ብላቴ ስደርስ ኰሎኔል ሽኩር አህመድ የተባለው የብላቴ ማሰልጠኛ ማእከል አዛዥ የተወሰኑ ወታደሮችን ይዞ አይሮፕላን ማረፊያውን እያስቆፈረና ድንጋይ እየከተረ ጠበቀኝ።

*(ይሄ መኮንንም አማራ በመሆኑ ከምርጫ 97 ጋር በተያያዘ ተባርሯል።)*

ሳሞራ ደውሎ ቁፋሮውን እንዲፈፅም እንዳዘዘው፣ ቀሪውን ተግባር ከኔ ጋር ተነጋግሮ እንዲሰራ መታዘዙን ነገረኝ። ሊነጋጋ አካባቢ ግዳጃችንን በብቃት ተወጥተን ጨረስን። አይሮፕላን ሜዳውን አበላሸነው። አይሮፕላን ማረፍም መነሳትም እንደማያስችል አድርገን አወደምነው።

ጨርሶ ሲነጋም ከሻለቃ አመራር በላይ አስቸኳይ ስብሰባ ጠራሁ። የታዘዝኩትን አብራርቼ ጠንካራ መመሪያ ሰጠሁ። ከማሰልጠኛ ጣቢያው ዝቅ ብሎ ካለው ጫካ 22 VOLVO የሰራዊት ማጓጓዣ መኪኖች ተደብቀው አገኘናቸው። ሾፌሮቹን በሙሉ አስሬ፣ መኪኖቹ ካሉበት እንዳይንቀሳቀሱ አስጠበቅሁዋቸው። ይህን ፈፅሜ ሳበቃ ወደ ሳሞራ ደውዬ ሁኔታውን አብራራሁለት። ሳሞራ ስሜታዊ ሆኖ በደስታ ሳቅ ሰከረ። ማወቅ የሌለብኝን ምስጢሮች ጨምሮ በፍንደቃ እንዲህ ሲል ተናገረ፣

'ኩዴታው ከሽፎአል! ከአየር ሃይልም ሄሊኮፕተሮች ተዘጋጅተው ነበር! ከመነሳታቸው በፊት አስቆምናቸው! ከሽፈ ኩዴታው! ኩዴታው ከሽፈ!!'

የሳሞራ ኰብራ ለአንድ ሳምንት ያህል አብራኝ ከቆየች በሁዋላ መለስኩለት..."

* * *

"በመጨረሻስ እንዴት ሆነ?" ስል ጠየቅሁት።

ኮሎኔሉ በፈገግታ እንዲህ ሲል መለሰ፣

"የወያኔ ስርአት ሳይወድቅ ምን መጨረሻ አለ?"

"እንዴት ካገር ወጣህ? ከግንቦት7 ጋር በመተባበር የሞከራችሁት ኩዴታ ለምን ከሽፈ? ወያኔ እንዴት ምስጢሩን ሊደርስበት ቻለ? ከመካከላችሁ የከዳችሁ ሰው ነበር? አሁንስ መዋቅራችሁ በሙሉ ተበጣጥሶአል? ከእናንተ ስህተት ተምሮ መንቀሳቀስ የሚችል ሃይል መከላከያ ውስጥ ያለ ይመስልሃል? በግለሰብ ደረጃ ተስፋ የሚጣልባቸው መኮንኖች ሊኖሩ ይችላሉ? ወይስ እነ ዘውዱ እሸቴ ብቻ ነው የቀሩት?"

ለሰከንዶች ያህል በፀጥታ ቆየ።

መናገር ከጀመረ በሁዋላ ግን ለአራት ሰአታት ያህል ያለማቋረጥ አጫወተኝ። አንዳችም ሳይደብቅ ሁሉን በዝርዝር ተረከልኝ። ያለውን ሁሉ ሰጠኝ። የሰጠኝን ሁሉ ተቀበልኩ። እና እንዲህ ሲል ቋጨ፣

"...ጥር 2000 ከመከላከያ ከተሰናበትኩ በሁዋላ ብዙ ጓደኞቼ፣ ትግሬዎች ጭምር፣ 'ከዚህ በሁዋላ ሁኔታው ከባድ ሊሆንብህ ስለሚችል ተጠንቀቅ' ሲሉ መክረውኝ ነበር።

በርግጥም 'ከሁሉም ነገር ነፃ ወጥቻለሁ' ብዬ ላስብ አልችልም ነበር። ህሊናዬ ግን በርግጥ ነፃ ነበር። ከዚያ የቀትር ወንበዴና የሽፍታ ቡድን ጋር የቆየሁባቸውን ጊዜያት ዘወር ብዬ ሳስታውሳቸው ቅዠት ሆነው ይታዩኝ ነበር።

ወገኔንና አገሬን ጐድቻለሁ።

ይቅርታም እጠይቃለሁ። የበደልኩትን ህዝብ የመካስ የሞራል ግዴታም ነበረብኝ...

....የሆነው ሆኖ ከመከላከያ ከተሰናበትኩ በሁዋላ የወያኔ





የደህንነት መዋቅር ክትትል ያደርግብኝ ጀመር። በጥር ወር ተሰናብቼ፣ የካቲት ክትትል ጀመሩኝ። ለአንዳንድ ጉዳዮች ጐንደርና ጐጃም እመላለስ ነበር። አጅበውኝ መጓዝ ጀመሩ። ቀደም ሲል ከማውቃቸውና ከሚያውቁኝ ከነ ጄኔራል አሳምነው ፅጌ፣ ከነ ኰሎኔል ደምሰው አንተነህ፣ ከነሻለቃ መኰንን ወርቁ፣ ከነሻለቃ አዱኛ አለማየሁ፣ ከነሻለቃ ምስጋናው ተሰማ ጋር በተለያዩ ጊዜያት እየተገናኘን መጨዋወታችንን በልዩ ሁኔታ ይከታተሉት ነበር። አዲሳባ ላይም አብረን ውለን እናድራለን። በመኪና ብንዝም ለውጥ አልነበረውም። ይከተሉኛል። ተንቀሳቃሽ ስልኬም ሆነ ቀጥታው የቤት መስመር መጠለፋቸውን መረጃ አለኝ። እኔ በአይኔ ከማየው በተጨማሪ የወያኔ የመረጃ አባሎች በየጊዜው ይነግሩኝ ነበር። አንድ ቀን ባደባባይ ምስጋናዬን የማቀርብላቸው ጊዜ ይመጣል። የሆነው ሆኖ በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለሁ ሚያዝያ 16፣ 2001 የመጨረሻ ቀኔ ልትሆን በቃች።

መኖሪያ ቤቴ ኰተቤ ነበር።

ከባለቤቴ ጋር በመኪና ከግቢ ስንወጣ ሰርካለም የምትባል አንዲት ጐረቤቴ በአጋጣሚ መኪናዋ ሰርቪስ ላይ ስለነበረች ሊፍት እንድንሰጣት ጠየቀችንና አብረን ወጣን። ወደ ጐዳናው ስንወጣ፣ ከቤቴ ሰላሳ ሜትር ርቀት ላይ ስድስት የደህንነት የክትትል ሰዎችን አየሁ። ሁለት ሁለት ሆነው ተበታትነው ቆመዋል። የሁሉም አይን እኔው ላይ አርፎ ነበር። ባለቤቴ ሁኔታቸውን ስታጤን ደስ አላላትም መሰለኝ ወይም ማን እንደሆኑ አላወቀች ይሆናል፣

'እንዴት ብለው ነው የሚያዩህ?' አለች።

'ተያቸው ምን እንዳያመጡ?' ብዬ ወደ አስፋልቱ ወረድኩ። የኔ ቤት በግምት ከአስፋልቱ የ200 ሜትር ርቀት ላይ ቢሆን ነው። አስፋልቱ ላይ ስደርስ ሁለቱ የደህንነት አባሎች እኔን ተከትለው በፍጥነት ደረሱ። አራቱ እዚያው ሰፈራችን የቀሩ ይመስለኛል። አስፋልቱ ላይ ሶስት DX መኪኖች ተራርቀው ቆመው አየሁ። ፊታቸው እኔ ወደምሄድበት ወደ መገናኛ አቅጣጫ ነበር። ሁለቱ መኪኖች ቀደም ሲልም ይከታተሉኝ ስለነበር አውቃቸዋለሁ። የመኪኖቹ ታርጋ ቁጥር አ-አ-2-74773፣ አ-አ-2-21945 እና ኢ.ት-3-17264 ነበር።

ሁኔታው ስለገባኝ ወደ መገናኛ መሄዱን ትቼ ወደ ግራ

ታጠፍኩ። ወደ ካራ አቅጣጫ መንዳት ስጀምር ሶስቱም መኪኖች በፍጥነት አቅጣጫቸውን ቀይረው ተከተሉኝ። ሁለቱ የክትትል ሰዎችም ወደ መኪኖቹ ሲገቡ በመስታወት አይቼያቸዋለሁ። ሁለት ኪሎሜትር ያህል እንደሄድኩ ወደ ቀኝ በመታጠፍ ውስጥ ለውስጥ ወደ ሲኤምሲ ወደሚያመራው መንገድ ገባሁ። እነርሱም ተከተሉኝ።

ፍጥነት ስጨምር ይጨምራሉ። ስቀንስ ይቀንሳሉ። አላማቸው ከክትትል እንደማያልፍ ብገምትም ርግጠኛ አልነበርኩም። ሁኔታቸው ከወትሮው የተለየ ነበር። በዚህ ሁኔታ እየተጓዝን ባለቤቴን ገርጂ ኢምፔርያል ሆቴል አጠገብ አወረድኳት። እዚያ አካባቢ ነበር የምትሰራው። ጐረቤቴን ወደምትሰራበት ለመሸኘት ቀለበት መንገዱን ይዤ ወደ ሳሪስ ቀጠልኩ። ቦሌ ሚካኤል አካባቢ ስደርስ እሷን አውርጄ እኔ ወደ ቀኝ ታጥፌ ወደ ውስጥ ስገባ እነርሱም ተከተሉኝ።

ወደ ቦሌ አቅጣጫ አመራሁ።

ወደ ግራ ታጥፌ እንደገና ወደ ቦሌ መድሃኔአለም ስታጠፍ እየተከተሉኝ ነበር። ፍጥነት ጨመርኩና ከቦሌ መድሃኔአለም በጀርባ ባለው አስፋልት ወደ ቀኝ ታጥፌ ስረግጠው ተተረማምሰው መቅረታቸውን አረጋገጥኩ። ወዲያው መኪናዬን ለባለቤቴ ሰጥቼ በእግሬ ጉዞ ጀመርኩ።

መንገድ እያሳበርኩ አንድ የማውቀው ሰው ቤት ገብቼ ምሳ በላሁ። ስልክ ደውዬም ለምሳ እንደማልገባ ለባለቤቴ ነገርኳት። ምሳ ሰአት ላይ ከመኖሪያ ቤቴ ደጃፍ የደህንነት የክትትል ሰዎች ተኰልኩለው እየተጠባበቁኝ መሆኑን አረጋገጥኩ። ሁኔታው ከወትሮው ለየት ስላለብኝ፣ ተጨማሪ መረጃ ባገኝ ብዬ ወደ ጓደኞቼ ስልክ መደወል ጀመርኩ። በቅድሚያ ስልክ የደወልኩት ለጄኔራል አሳምነው ፅጌና ለጄኔራል ተፈራ ማሞ ነበር።

የሁለቱም ስልክ አይመልስም።

ወደ ሌሎች ቀጠልኩ። ሻለቃ መኰንን ወርቁ፣ ኰሎኔል የሸዋስ አጥናፉ፣ ኰሎኔል አስቻለው አምባቸው፣ ሻለቃ አዱኛ አለማየሁ፣ የሁሉም ስልክ ከስራ ውጭ መሆኑን አረጋገጥኩ። ይህን ጊዜ በርግጥ ችግር እንዳለ ገባኝ። ለማጣራት መረጃ ወደሚሰጡን የደህንነት ባልደረቦች ስልክ ደወልኩ። የጠቀስኳቸው መኰንኖች ሁሉ በቁጥጥር ስር መዋላቸውና እኔም





እየተፈለግሁ መሆኑ ተነገረኝ።

ሌሊቱን ወደ ቤቴ አልገባሁም።

የደህንነት ሰዎች እንደቆሰለ አውሬ እየተወራጩ የኔንና የጐረቤቴን መኖሪያ ቤቶች እየገለባበጡ ሲፈትሹ ማደራቸውን ሰማሁ። ቅዳሜና እሁድ ሙሉ ቀን ቤታችንን ሲበረብሩ ውለው አደሩ። ብረት ነክ ነገሮችን የሚመረምር ማሽን ጭምር አምጥተው ፈተሹ ተባለ። ምንም ነገር ሲያጡና እኔንም ስላላገኙኝ እሁድ ምሽት ባለቤቴን ወስደው አሰሯት። የሶስት አመት ህፃን ልጅ ትታ ሁለት ወራት ያህል እስር ቤት እንድትቆይ አደረጉ። ሁለቱንም ወራት ከማንም ጋር አልተገናኘችም ነበር።

ከተሰወርኩ ከአምስት ቀናት በሁዋላ ወደ ምስራቅ ተጓዝኩ። በወሎ፣ ወልዲያ፣ ጋይንት አቋርጬ፣ ወደ ሱዳን ድንበር አቅጣጫ አመራሁ።

ጉዞዬ በእግር ነበር።

በረሃ በረሃውን፣ ጫካ ጫካውን፣ ውሃ መውረጃ ቦዮችን እየተከተሉ፣ ከወያኔ ጥበቃ እየተሰወሩ መጓዝ፣ ራሱን የቻለ ፈታኝና አስቸጋሪ ምእራፍ ነበር። በመጨረሻም ይኸው እዚህ አለሁ! ይህ ሽሽት አይደለም! ከሃገሬ የመሸሽ ፍላጐት የለኝም። በቅርቡ ወደ ሃገሬ እመለሳለሁ። ሁላችንም ወደ ሃገራችን እንመለሳለን። የወያኔ የሽፍታ ቡድን ገና አልገባቸውም እንጂ የጫሩት እሳት መልሶ ራሳቸውን ይፈጃቸዋል..."

ታህሳስ ወር 2002 ላይ የወያኔ ፍርድ ቤት ኰሎኔል አለበል አማረ በሌለበት የእድሜ ልክ እስራት የበየነበት ሲሆን፣ አምስት ግለሰቦች ላይ ደግሞ ሞት ፈርዶባቸዋል። እነዚህም ዶክተር ብርሃኑ ነጋ፣ አንዳርጋቸው ፅጌ፣ ሙሉነህ እዮኤል፣ መስፍን አማን እና መላኩ ተፈራ ናቸው።

የእድሜ ልክ እስራት ከተፈረደባቸውና በስደት ላይ ከሚገኙት መካከል ያረጋል ይማም የተባለውን ዱባይ ላይ አግንቼው ሁሉን አውግቶኛል። ኮሎኔሉ ያጫወቱኝን ሁሉም እዚህ አልፃፍኩላችሁም። ከግማሽ በላይ የሚሆነውን መረጃ ቦርሳዬ ውስጥ ቆልፌ ለመደበቅ ተገድጄያለሁ። በቀጣዩ መፅሃፌ *"የስደተኛው ማስታወሻ"* ላይ አጫውታችሁ ይሆናል። ጠቢቡ ሰለሞን እንዳለው፣ 'ቦ ጊዜ ለኩሉ'...

# - 19 -

# ከበረሃ ወደ በረሃ

የውበት መቅረዟ፣
የዳሌዋ ለዛ፣
የባቷ እስክስታ...
ድንገት ቢወረወር - እንዳፋር አንካሴ፣
ልቧን ሙጢኝ አልኩት - እንዳትወጣ ነፍሴ፣

(ግጥም - አበራ ለማ)

* * *

አወይ ድንቁርና - አወይ መሳሳት፣
ለካስ ትግሉ ኖሮአል - ለከተማ እሴት፣

(ቅኔ - እንዳርጋቸው ፅጌ)

- ባሏ በከተማ ኮማሪት የቀየራት አንዲት የኢህአዴግ ታጋይ ስትቆዝም የተቀኘችው በሚል ደወል ጋዜጣ፣ ግንቦት 1985 እንዳተመው -

አንድ ሰው በፃፈልኝ ደብዳቤ ላይ፣ ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ 2001 አጋማሽ ላይ ለአውራምባ ጋዜጣ የሰጡትን ቃለመጠይቅ ጠቅሶ፣

"ከፕሬስ መምሪያ ሃላፊነቱ ያነሳነው ሴት አያያዙ ልክ ስላልነበረ ነው። ወደ ዝርዝሩ መግባት ግን አልፈልግም' ብለውሃልና ምን ማለታቸው ይሆን?" ሲል ጠይቆኛል።

በውነቱ ምን ማለት እንደፈለጉ ነጋሶ ናቸው የሚያውቁት። ገምት ከተባልኩ ግን፣ "ሴት አውል" ማለታቸው ሳይሆን አይቀርም።

የኛ ሰው መቼም አንድ ቀን ከሴት ጋር ካየህ ችኮላው አይቻልም! ለነገሩ እኔ አንድ ቀን ብቻ ሳይሆን ብዙ ቀን ከሴቶች ጋር ታይቼ ሊሆን ይችላል። ብታይስ ታዲያ ምንድነው? ዶክተር ነጋሶ ለምን በግልፅ አልተናገሩም? 'ዝርዝር ውስጥ መግባት አልፈልግም' ብለዋል። ከጀመሩ ላይቀር ግን





ቢዘረዝሩት ይሻል ነበር።

"እገሊት ወይም እንቶኒት ከተባለች ሴት ጋር በዚህ ቀን እዚህ ቦታ ሲገባና ሲወጣ ታይቷል" ብለው የሰሙትን ለምን ፍርጥርጥ አላደረጉትም? የምን አጓጉቶ መተው ነው?

በኔ በኩል ትዝ የሚለኝ ልዩ ነገር የለም።

እንደ ማንኛውም ወጣት በተለያዩ ጊዜያት ጥቂት የሴት ጓደኞች ነበሩኝ። በቀዳሚው መፅሃፌም አልደበቅሁም። መቼም መተዋወቅ፣ ማብሰል፣ መለያየት ሊያጋጥም ይችላል። ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ ስለየትኛዋ ሴት እንደተናገሩ ግን ሊገባኝ አልቻለም። ስሟን ከረሱት በምልክትም ቢሆን ረጅሟ፣ አጭሯ፣ ፍንጭቷ፣ ቀይዋ፣ ጠይሟ ብለው ትንሽ ፍንጭ ቢጤ ቢሰጡኝ እኔው ራሴ አሳምሬ አብራራው ነበር።

የሆነው ሆኖ እስኪ የውጫሌው ይቆይልንና የአድዋውን እንነጋገር። እኔ ያላገባሁ ወጣት ነበርኩ። ሚስት ባፈላልግ ሃጢአት ሊሆን አይችልም። እድሜዬም ይፈቅድልኛል።

በወቅቱ አግብተው የወለዱ የኢህአዴግ ባለስልጣናት ጨለማ ለብሰው ቆንጆ እየመረጡ ያበስሉ አልነበረም እንዴ?

ምነው የሌሎቹ ሳይነሳ ቀረ?

በቀዳሚው መፅሃፌ ይህን መሰል ጉዳዮች ያላነሳሁት ባህላችን አይፈቅድም በሚል ነበር። አሁንም ቢሆን ዝርዝር ጉዳዮች ውስጥ የመግባት ፍላጎት የለኝም። ዶክተር ነጋሶ ህሊናቸውን ሚዛን ላይ ያስቀምጡ ዘንድ ግን የኢህአዴግ አመራር አባላትን ገበና በትንሹ ገለጨ ማሳየት እፈልጋለሁ።

ታጋይ ባለስልጣናቱ አዲስ አበባ እንደገቡ ምንድነው ያደረጉት? ፀጉራቸው ዞማ፣ ወገባቸው ቀጤማ፣ ተረከዛቸው ኮረሪማ፣ ከንፈራቸው ጣዝማ፣ አስተዳደጋቸው በከተማ እያሉ የከተማ ሴት ሲያማርጡ አልነበረም እንዴ? ታጋይ ሚስታቸውን እየፈቱ እየተሻሙ ይመርጡ አልነበረም?

ስዩም መስፍን ምንድነው ያደረገው?

ሚስቱ ማህታ የተባለች አንዲት አብራው የታገለች፣ የትግራይ የገጠር ሴት ነበረች። ወዲያው አባረራትና የኤርትራ ሪፈረንደም ዋዜማ ላይ ማዶናን የመሰለች ኤርትራዊት አገባ። የኢትዮ - ኤርትራ ጦርነት በሁዋላ ደግሞ ከእሷም ተፋታና ጄት የመሰለች ነጋዴ የትግራይ ሴት አገባ። ዶክተር ነጋሶ ይህን አሳምረው ያውቃሉ። ስለዚህ ጉዳይ ግን አንዲት ቃል ትንፍሽ

ብለው አያውቁም። ቢል ክሊንተን ጥቂት ስለ ቀበጠ የደረሰበትን ፈተና የምናውቀው ነው። ምክንያቱ ግልፅ ነው። አገርን መምራት ከቤተሰብ ይጀምራል። በኔ በኩል ሃገር የመምራት ፍላጎት አድሮብኝ አያውቅም። ዶክተር ነጋሶ የዋና ዋና መሪዎቹን ቅሌት በዝምታ አልፈው እንዴት የኔን ስነምግባር ነጥለው ሊያዩት ቻሉ? 'ስለ ሌሎቹ አላውቅም ነበር' ሊሉን አይችሉም። ያውቃሉ። ከረሱትም ላስታውሳቸው እችላለሁ።

ዶክተር ነጋሶ የተፈራ ዋልዋን ቅሌት አበጥረው ያውቃሉ። ዋልዋ የበረሃ ሚስቱን መፍታት ብቻ ሳይሆን፤ እንዳትረብሸው ታጠቅ ጦር ሰፈር ወስዶ አሳስሮአት ነበር። ፕሬዚዳንቱ ይሄን አልሰማሁም ሊሉ አይችሉም።

አባዱላ ገመዳ ሴት ይዞ ወደ ሼራተን ልዩ የመኝታ ክፍሎች ሲገባ የመከላከያ ፀረ መረጃ አባላት እነ ኮሎኔል ጌትነት ጉደያ ጥበቃ ያደርጉለት የለም እንዴ? ዶክተር ይህን አያውቁም? ካላወቁ ሌላ ልጨምር።

አባተ ኪሾ ሚስቱን እስር ቤት አስገብቶ በጠለፋ አይደለም እንዴ አንዲት ቆንጆ ያገባው? ገብሩ አስራት ባለቤቱ ፓራላይዝድ ስትሆንበት ፈትቶአት የለም እንዴ? መፍታት ደህና። አይኗን ማየት ባለመፈለጉ አዲሳባ፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት አጠገብ አንድ አፓርታማ ውስጥ አልቀረቀረባትም? በወቅቱ ይህን ወሬ እንደሰማሁ በአካል ሄጄ ጠይቄያት አልቅሳ ነግራኛለች። ውሃ የሚያቀብላት ሰው እንኳ አልነበረም። እየተንፏቀቀች ነበር ከአልጋ ወደ ሽንት ቤት የምትመላለሰው። ሳሞራ ስንት ጊዜ ነው አግብቶ የፈታው? የ70 አመቱ አዛውንት ስብሃት ነጋ የልጆቻቸውን እናት ፈትተው የ18 አመት ኮረዳ አግብተው የለም እንዴ? ይህ ሁሉ ሲሆን ነጋሶ ፕሬዚዳንት ነበሩ። አንድም መድረክ ላይ ግን ይህን ጉዳይ አላነሱም።

ከመቼ ወዲህ ነው ደግሞ ኢህአዴግ ውስጥ ብልግና ወንጀል የሆነው? ያስወለዱትን መካድና ውሽማ ማስቀመጥ በኢህአዴግ አመራር ዘንድ ፋሽን አይደለም እንዴ?

ዶክተር ነጋሶ እንዴት ነው እኔን በስነምግባር ጉድለት የሚተቹት? በእድሜ እና በስልጣን ከኔ በላይ የነበሩት፣ የነጋሶ ጓደኞች ቅሌት ምን ማለቂያ ነበረው?

ኩማ ደመቅሳ የልጆቹን እናት በከተማ ሴት ሲለውጣት፣ ዶክተር ነጋሶ፣ "አይገባም" ብለው አልመከሩትም። ጄኔራል ባጫ





ደበሌ አራት ጊዜ አግብቶ ሲፈታ ነጋሶ ምነው ትንፍሽ ሳይሉ ቀሩ? አንድ ኮሚቴ ውስጥ አልነበረም እንዴ የሚሰሩት? ይባስ ብለው ክራቫታቸውን ግጥም እያደረጉ የባጫ ሰርጎች ላይ ይገኙ አልነበረም እንዴ? የእነዚህን ሰዎች ቅሌት ማየት ያልቻሉት ስልጣን ላይ ስለነበሩ ይሆን? እኔ በወቅቱ የስልጣን ዝውውር ሳደርግ ጠርቶ የነገረኝ በረከት ነው። የነገረኝ፣ "የበለጠ ልትሰራ ወደ ምትችልበት ቦታ አዘዋውረንሃል" የሚል ብቻ ነው። ደሞዜም በእጥፍ ጨመረ እንጂ አልቀነሰም። ፀሃዬ ደባልቀው እኔን እንዲተካ አሳብ ያቀረብኩትም እኔው ነበርኩ። ስብሰባውን የመሩትም ነጋሶ ሲሆኑ፣ አማረ አረጋዊና ፈቃደ የምሩ ስብሰባው ላይ ነበሩ።

ለመሆኑ ከኢህአዴግ ባለስልጣናት መካከል ከስዬ እና ከበረከት ስምኦን ሌላ በቀሚስ አሳዳጅነት የማይታማ ማን አለ?

በርግጥ ዶክተር ነጋሶም አይታሙም።

ጀርመናዊት ሚስትና ሩዋንዳዊት የማደጎ ልጅ አላቸው። ዶክተር ከስራ ሲወጡ ወዲያ ወዲህ የለም። ወደ ሚስታቸው ጥልቅ ነው። በዚህ አደንቃቸዋለሁ። ለነገሩ ጀርመናዊቷ እውነተኛዋ ቀዳሚ እመቤትም ሃይለኛ ናቸው። አያፈናፍኑም። አንድ ቀን ግብዣ ላይ ጨብጫቸው ነበር። ሲጨብጡህ የጨመደዱህ ነው የሚመስለው። ደግመህ ለመጨበጥ ትፈራለህ። እኔም ለነገሩ ከብእር ሌላ ጠንከር ያለ ነገር ጨብጬ አላውቅም...

የቀሚስ ጉዳይ ኢህአዴግ ውስጥ በወንጀል ሲነሳ ገና ከነጋሶ መስማቴ ነው። መባለግ ወንጀል ከሆነ አብዛኛው ባለስልጣን ከስራው መባረር ነበረበት። እንደ አመራሩ ቅሌት ቢሆን፣ "የጋዜጠኛው" እና "የደራሲው" ሳይሆን፤ "የብልግናው ማስታወሻ" የሚል መፅሃፍ ነበር ከኔ የሚጠበቅ። ብቻውን 500 ገፅ ይወጣዋል። በተለይ ሱሪያቸውን አውልቀው ከሴት ጋር አንድ ሽርጥ ውስጥ ገብተው በለጬ የተባለውን የወንዶ ገነት ጫት የሚቅሙ ባለስልጣናት! አያስፈልግም እንጂ፣ ስም እየተጠቀሰ ዝርዝር ነገር መፃፍ በተቻለ...

"በየገደሉ እየዞሩ መቀደስ፣ የተኛውን ሰይጣን መቀስቀስ" ይባላል። ነጋሶ ቀስቅሰውኛል። በዚህ መረጃ የምትበሽቁ በኔ ሳይሆን በነጋሶ ብሽቁ። እኔማ አበሻ እንደመሆኔ በጨዋ ደምብ አርፌ ቁጭ ብዬ ነበር። ዶክተሩ መጡና ነካኩኝ።

በርግጥ በቀዳሚው መፅሃፌ ዶክተሩን፣ "የተቆለፈበት አንበሳ" ብዬአቸው ነበር። ዶክተሩ በዚህ አነጋገሬ ደስ ካላላቸው፣ እኔ ካልኳቸው ጋር የሚመጣጠን ቃል ፈልገው፣ "የኮበለለ ድመት" ሊሉኝ እየቻሉ ወደ ግል ጉዳይ ገብተው ስለ ቀሚስ አነሱ።

እንዲህ መነጋገር ከተጀመረ ደግሞ የምናውቀውን ማፍረጥ መብታችን ነው። እርግጥ ነው፣ እኔ ጨዋ እንደመሆኔ ስለ ሴት አንስቼ 'እገሌ ከእገሊት ጋር እንዲህ አደረገ፤ ጂኒ ቁልቋል፣ ቲማቲም፣ ቃሪያ' ብዬ በዚህ ርእስ ላይ የመፃፍ ፍላጎት አልነበረኝም። ሌላው ወገን ከጀመረው ግን ምንም ምርጫ የለኝም።

"የለም! እንከባበር። ፖለቲካው ላይ ብቻ እንነጋገር" ከተባለ በኔ በኩል ችግር የለብኝም። በጨዋ ደምብ፣ ጨዋ የሆኑ ጭምት፣ ጨው ያላቸው ጨዋታዎችን አወጋለሁ።

ጉራ አይደለም! ብዙ አውቃለሁ። በጣም አደገኛ መረጃዎችን ጭምር አውቃለሁ። መረጃውን ከየት እንዳገኘሁት ልጠቁምም እችላለሁ። ማታ ማታ ባለስልጣኖች ቤታቸው እስኪገቡ ድረስ እንቅልፍ አጥቶ ይጠብቅና ይሸኝ የነበረው የ4ኛ ሻለቃ አዛዥ ኮሎኔሉ ጓደኛዬ ነበር። ኮሎኔሉ ብዙ እንደሚያውቅ የቀድሞ አለቆቼ ያውቃሉ። እሱ የሚያውቀውን ሁሉ እኔ አወቅሁ ማለት ደግሞ ትርጉሙ ግልፅ ነው። ስለዚህ ዝምታ ወርቅ ነው። የዶክተር ነጋሶ አይነት የዋህነት መዘዝ ያመጣል።

በዚህ ውስጠ ወይራ አነጋገሬ አንባቢዎቼ የተደበቀውን ለማወቅ እንደሚጓጉ ግልፅ ነው። አዝናለሁ። ሁሉን ልናገር አልችልም። ይሂ ከኔ መርህ ውጭ ነው። በርግጥ በተፈጥሮዬ አጓጉቼ መተው ደስ አይለኝም። ስለዚህ ከማውቀው የቀድሞ አለቆቼ የሌሊት ህይወት በጨረፍታ ላውጋችሁ...

ለአብነት እንደ ዳዊት ዮሃንስ አይነት ቀምቃሚ በዚህች ምድር ላይ የለም። ውድቅት ላይ ጨርቅ ሆኖ በድጋፍ ነው ቤቱ የሚገባው። ከመኪና ወደ መኝታ ቤቱ እንኳ መግባት እየተቸገረ እንደ ስጋ ግራና ቀኝ ብብቱ ላይ ይዘው እየጎተቱ መኝታ ቤቱ ውስጥ ያስገቡታል። አጃቢዎቹ እንደሚያወሩት ብዙውን ጊዜ ከነጫማው እንደ ቀረሮ አጋድመውት ይወጣሉ። መለስ ዜናዊ በዳዊት ጠጪነት መማረሩን በየስብሰባው ይናገር ነበር። አንድ





የማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ላይም እንዲህ ብሎታል፣

"ዳዊት! ሰካራም ነህ! የኢህአዴግ አመራር አባል በመሆንህ ግን ተሸክመንሃል።"

ታምራት ላይኔም ያው ነበር።

እንደ ዳዊት ራሱን ባያዋርድም በጊዜ ቤቱ ገባ ከተባለ ከእኩለ ሌሊት በሁዋላ ስምንት ሰአት ላይ ነበር። ጥሎበት ደግሞ ሴቶች አይናቸውን ይጥሉበታል። እሱም አይሰንፍም። እንደ ፍቅረስላሴ ወግደረስ ሽቅርቅር ማለቱን ያውቅበታል። እንዲህ እንደ ዛሬው ፊቱን ወደ አምላክ ከመመለሱ በፊት በር እያዘጋ መጨፈር እለታዊ ፕሮግራሙ ነበር። እጁን ዘርግቶ ጣቶቹን እያንጣጣ...

*ከተራራው ወዲያ - ናፍቆቴ!*
*ከወንዙ ባሻገር - ናፍቆቴ!*
*ከደመናው ውስጥ - ናፍቆቴ!*
*ልቤ ተጨነቀ - ናፍቆቴ!*
*መልሶ አይታፈስ - ናፍቆቴ!*

እያለ ያዜመባቸው እኒያ ውብ ዘመናት አልፈው ታምራት ዛሬ እንደ እኔ የእግዚአብሄር በግ ሆኖአል። ሰው ሲለወጥ ደስ ይላል። ታምራት ክፉ ተግባራትን ትቶአልናም አንወቅሰውም።

ነፍሱን ይማረውና ክንፈም የሌሊት ወፍ ነበር።

ሊነጋጋ ሲል ነበር ቤቱ የሚገባው። ፈንክቶና ተፈንክቶ እንደ ገጠር መኪና ብቻውን ሊነጋጋ ሲል ወደ ቤቱ ይገሰግሳል።

አንድ ጊዜ ሳሙኤል የተባለው የሰንሻይን ኮንስትራክሽን ባለቤት (ሳትኮን) መጠጥ ቤት ውስጥ ከክንፈ ጋር ተጋጨ። ሳሙኤል ክንፈን በስም እንጂ በአካል አያውቀውም ነበር። እና አንድ ሁለት ሲባባሉ ቆዩ። ሳሙኤልም ያው ትግሬ በመሆኑ 'ማን ይነካኛል' አይነት እብሪት ይገፋፋውና ባለጌ ወንበር አንስቶ ክንፈን አናቱ ላይ ይፈልጠዋል። የኢትዮጵያ የደህንነት ሚኒስትር ወለሉ ላይ ወርዶ ጥቅልል! ወዲ መድህን የሚባል ጄኔራል ከክንፈ ጋር አብሮት ነበር። ሽጉጡን መዘዘና የሳሙኤልን እግር አነደደው። ሳሙኤል ወደ ፖሊስ ሆስፒታል ተወሰደ። ክንፈ ቆይቶ ነቃ። ስላልተጎዳ ራሱን አሻሽቶ ቤት ቀይሮ መጠጣቱን ቀጠለ። ሳሙኤል ፖሊስ ሆስፒታል ደርሶ ህክምና እስኪያገኝ ድረስ ማንን በወንበር እንደፈነከተ ኣላወቀም

ነበር። ታክሞ ሲያበቃ ቀስ ብለው ነገሩት፣

"የደበደብከው ክንፈ ገብረመድህንን ነው!"

ሳሙኤል ቃል አልተነፈሰም። እዚያው በዚያው ሩሁን ሳተ። አንድ ቀን ተኩል ያህልም ኮማ ውስጥ ገባ።

ሳሙኤል የትግራይ ሰው በመሆኑ፣ አንድ አዲስአበቤ በመደብደቡ ማንም እንደማይነካው ርግጠኛ ነበር። ባጋጣሚ ግን የራሱን አምላክ መደብደቡን ሲነግሩት ሩሁን ሊውጣት ለጥቂት ተረፈ። ሳሙኤል ትግሬ በመሆኑ ዳነ እንጂ፣ ትግሬ ባይሆን ኖሮ የክንፈን ጭንቅላት በወንበር ፈንክቶ በህይወት አይኖርም ነበር።

ይህንን ወሬ የሰማሁት ማለዳ ላይ ነበርና ምሳ ሰአት አካባቢ ደውዬ ክንፈን አገኘሁት።

ክንፈ አጫወቶኝ ሲያበቃ፣

"እንዳትፅፈው ደግሞ" አለኝ።

"ጅል አደረከኝ እንዴ?" ስል መለስኩ።

ለካስ ጅል ኖሬያለሁ። ይኸው ፃፍኩት።

ነፍሱን ይማረውና ብዙ ጊዜ ከክንፈ ጋር መስመር ላይ እንገናኝ ነበር። የ26 አመት ጎረምሳ ስለሚመስል የደህንነት ሹም ነው ብሎ የሚጠረጥረው የለም። ጥግ ላይ ቁጭ ብለን ስንት ጊዜ አብረን ቀምቅመናል?

ወሬን ወሬ ያመጣዋል...

አንድ ጊዜ ከኮሜድያን ደረጄና ሃብቴ ጋር እየቀመቀምን ሳለ ክንፈ ከአንዷት ቆንጆ ልጅ ጋር መጣ። (ሁዋላ ከልጅቱ ጋር ተጋቡ መሰለኝ። ርግጠኛ አይደለሁም።) የሆነው ሆኖ ቆንጆዋ ልጅ ደረጄና ሃብቴን ስታይ ክንፈን ረስታ አይኗ እኛ ላይ ሆነ። ክንፈ ቢቸግረው ይዞአት ወደኛ ጠረጴዛ መጣ። የማይተዋወቁትን አስተዋወቅሁና ተቀላቀልን። ደረጄ እና ሃብቴ ክንፈ የሃገሪቱ የደህንነት ሚኒስትር መሆኑን ሊያውቁ ቀርቶ፤ ቢነገራቸውም ባላመኑ። ቲሸርት ለብሶ፣ በዚያ ላይ ቀጭን፤ መቀለድ የሚወድ፣ ትንሽ ባር ውስጥ፤ ማንም ሊጠረጥረው አይችልም ነበር።

ደረጄና ሃብቴ ለህዝብ የማይቀርቡ የፖለቲካ ቀልዶች ነበሯቸውና እነዚያን ለክንፈ እንዲነግሩት ገፋፋሁዋቸው።

ደረጄ ክንፈን እያጤነ፣

"ይታመናል?" ሲል ጠየቀኝ።





"የኛው ነው ችግር የለውም" አልኩ።

ክንፈም እየሳቀ፣

"የናንተው ነኝ" አለ።

አንድ ቀልድ አወሩልን፣

*...አንድ ጊዜ ተፈራ ዋልዋ ፕሬዚዳንት ነጋሶን አየር ሃይልን ሊያስጎበኙው ደብረዘይት ይዞት ሄደ። (በወቅቱ ተፈራ መከላከያ ሚኒስትር ነበር።) ከዚያም ተፈ ፕሬዚዳንቱን አስጎብኝቶት ከጨረሰ በሁዋላ፣*

*"ሚግ ማብረር የሰለጠኑ አምስት ታጋዮች የምረቃ በረራ ያካሂዳሉ" ብሎ ገለፃ አደረገ። እነዚሁ ታጋይ አብራሪዎች የአየር ላይ የመገለባበጥ ትርኢት ያሳያሉ ተባለናም ለማየት ተዘጋጁ። ነጋሶና ተፈራ ዋልዋ ጎን ለጎን ተቀምጠው ሰማዩን ያዩ ጀመር። አምስት ጀቶች በተርታ ሰማዩን ሰንጥቀው አለፉ።*

*ተፈራ አብራራ፣*

*"ይሄ የሙከራ በረራ ነው። ዞረው ሲመለሱ ይገለባበጣሉ"*

*ነጋሶም ራሱን እየነቀነቀ ሚጎቹ ሲገለባበጡ ለማየት ሰማይ ሰማዩን ያይ ጀመር።*

*አምስቱ ሚጎች ተመልሰው መጡ።*

*አሁንም ግን ሳይገለባበጡ ቀጥ ብለው አለፉ።*

*ተፈራ አብራራ፣*

*"እየሩን እየፈተሹ ነው። አሁን ሲመለሱ ጠብቅ። ተገለባብጠው ድብልቅልቁን ያወጡታል።"*

*ሚጎቹ ለሶስተኛ ጊዜ ዞረው መጡ። ቢሆንም አልተገለባበጡም። ቀጥ ብለው አለፉ። በዚህ ጊዜ ነጋሶ ወደ ተፈራ ዘወር አለና እንዲህ አለው፣*

*"ተፈ! የኢትዮጵያ አየር መንገድ አየር ሃይልን ወርሶታል እንዴ?"*

በዚህ ቀልድ ክንፈ በሳቅ ወደቀ። ስቆ ሲያበቃም ወደ ሽንት ቤት ሄደ። በዚህ ጊዜ ቀስ አልኩና ለደረጄ፣

"ባለስልጣን ነው" አልኩት።

አይኑን አፈጠጠ።

"የኛው ነው አላልክም እንዴ?"

"እኮ የኛው ነው። እኔ ወያኔ አይደለሁ እንዴ?"

"እየቀለድክ ነው?"

ክንፌ ተመልሶ በመምጣቱ ንግግራችን ቆመ። ክንፌ እንደመጣ እንዲህ አለ፣

"ሌላ የፖለቲካ ቀልድ ንገሩኝ?"

ኮሜዲያኑ ተጠቃቀሱና ሌላ አስታራቂ ቀልድ ነገሩን፣

*…ኢህአዴግ አዲስ አበባ እንደገባ መለስ ዜናዊ የሽግግር መንግስቱ አባል ለሚሆኑ ተቃዋሚዎች የፓርላማ ወንበር ማደል ጀመረ። ለኦነግ፣ ለአብነግ፣ ለኢዳቅ፣ ለምናምን እደላ ሲያደርግ ኢዲዩ አንድ ወንበር ደረሰው። የኢዲዩ ሊቀመንበርም መለስ ዜናዊን በቀጠሮ ያገኘውና ቅሬታውን ገለፀ፣*

*"እኛም ደርግን ለመጣል ታግለናል። እንዴት አንድ ወንበር ብቻ ይሰጠናል? ሊጨመርልን ይገባል…"*

*መለስ ዜናዊ መልስ ሰጠ፣*

*"የሚገባችሁን ሰጥተናችሁዋል። አንጨምርላችሁም"*

*የኢዲዩ መሪ ምሬታቸውን እንዲህ ሲሉ ገለፁ፣*

*"አንድ ወንበር ብቻ!? በጣም ያሳዝናል። እንግዳ ቢመጣብን ምን ላይ ልናስቀምጠው ነው?")*

ወግን ወግ አነሳውና ወደ ቀልድ ገባን እንጂ አጀንዳችን ዶክተር ነጋሶና የወያኔ አመራር ብልግናን የሚመለከት ነበር…

ሴቶችን በተመለከተ ይዘክዘክ ከተባለ እኔ በበኩሌ እንደ ፈንጣጣ ወጥቶልኛል። ያስታወስኩትን ያህልም በቀዳሚው መፅሃፌ ፅፌዋለሁ። እንዳይሰለቻችሁ እንጂ የረሳሁት ካለ ልተርከው ዝግጁ ነኝ። ዶክተር ነጋሶ እንደ ጀመሩት "ውሃ መረጫጨት" ከቀጠለ ግን እገሌ ከእገሌ ማለት አይኖርም። ከመለስ ጀምሮ፣ ቀዳማዊ እመቤቲቱን ጨምሮ፣ የአብዛኛው ጉድ ይዘከዘካል። የአዜብና የሶሎሜ ታደሰ ፀብ መነሻው ጭምር ይፋ ይሆናል። ስለዚህ ሃበሻ እንደመሆናችን ወደ ግል ጉዳይ እየገባን ባንነካካ ይመረጣል።

'ጉረኛ! አታስፈራራ! ምንም የምታውቀው ምስጢር የለም!' የሚሉ ካሉ ደግሞ ፍንጭ ልሰጥ እችላለሁ።

ለአብነት የቆቃውን ምስጢር አውቃለሁ።

አሮጌው አይሮፕላን ማረፊያ አካባቢ በሚገኙ የደህንነቱ





መስሪያ ቤት በያዛቸው ድብቅ ቪላዎች ውስጥ እነማን፣ ከማን ጋር ምን ያደርጉ እንደነበር አውቃለሁ። ማን መሆናቸው እንዳይታወቅ አርተፊሻል አፍንጫ፣ አርተፊሻል የፀጉር ኮፍያ፣ አርተፊሻል ፂም እየተለበሰ፣ ማታ ማታ ምን እንደሚሰራ እናውቃለን። ይህን ለማውራት ግን ባህላችን አይፈቅድልንም። የእኛ ብእር እንደ ምእራባውያኑ ስድ አይደለም።

በኔ በኩል 26 አመት ሳይሞላኝ ከአስረሽ ምቺው ህይወት ወጥቼ ወደ መደበኛ ማንነቴ መመለስ ችያለሁ። 56 አመት እድሜ ላይ ደርሰው፣ "ክቡርነትዎ" ሲባሉ የምር ክቡር የሆኑ የሚመስላቸው፣ ጭፈራውን በትኩሱ የተያያዙት ስልጣኑ ላይ አሉ። ለነገሩ ነጋሶ ጊዳዳ ገፋፍተውኝ ይችን ጫጫርኩ እንጂ ህዝቡ ከዚህ በላይ ዝርዝሩን ያውቀዋል። "ከደደቢት በረሃ፤ ወደ ውቤ በረሃ" ብሎ የቀለደውስ አዲሳበቤው አይደል?

- 20 -

# ዘርና ዘርማንዘር

ከህይወትህ ወዲያ ሳያልፍ - የጥናትህ መደቡ፣
ከህዝብ ጉያ ሳይርቅ - የምርምርህ ክበቡ፣
ምን ብትረቅ፣ ምን ብትርቅ - እምትደርስበት ግቡ፣
ወይ የመነሻህ ርካቡ................

....የስንቱን አይነ ልቡና አታለልክ?
አስተዋይነቱን አጭበረበርክ?
በቋንቋ ግርዶሽ እየተጠለልክ፣
ተጠበብኩ ስትል ጠበብክ፣
አወቅሁ ስትል ደነቆርክ፣

(ግጥም - ደበበ ሰይፉ)

በቅርቡ ኤርትራ ሄጄ የሩቅ ዘመዶቼን ስተዋወቅ ትኩረት የሚስብ ሁኔታ ገጠመኝ። ይህም በእናቴ በኩል አፋርና እስላም ልሆን የመቻሌ መረጃ ነው።

ሳብራራላችሁ!

የእናቴ የትውልድ መንደር፣ "ሰም አሰም" ይባላል። ሰምአሰም ቀደም ሲል ሰራዬ ተብሎ በሚጠራው አውራጃ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፣ አሁን አካባቢው ደቡብ ዞን ተብሎ ይታወቃል።

"ሰምአሰም ምን ማለት ነው?" ብዬ ጠይቄ ነበር።

"ሰብ አሰብ' ነው የምንባለው። ከጊዜ ብዛት ግን ተለወጠና ሰምአሰም እንባላለን' አሉኝ።





መጨረሻውን ለማወቅ ጥያቄዬን አራዘምኩ፣

"ለምንድን ነው ሰብ-አሰብ የተባላችሁት?"

"ቅድመ አያቶቻችን ከአሰብ ነው ወደዚህ የመጡት'

ይህን አባባላቸውን የሚያረጋግጥ ሌላ መረጃም አገኘሁ። ዘመዶቼ ከእጃቸው ላይ ድንገት እቃ ሲወድቅባቸው፣ ወይም ስፎክሩ፣ አለያም ሲዝቱ፣ 'ደቂ ባህሪ!' ይላሉ። "የባህር ልጆች!" እንደማለት ነው። እንግዲህ በኛ ሃገር "ኢጆሌ ዋራ ቢሾፍቱ!" እንደምንለው ማለት ነው። ወይም ሌሎች፣ "ጀግናው ጎንደሬ!"፣ "ወዲ ትግራይ!" "ቆፍጣናው መንዜ!" እንደሚሉት አይነት ማለት ነው።

አዬ ጉድ!

እነሆ! እስላምና አፋር ሆኜ ተገኘሁላችሁ።

ሉሲ የስጋ ዘመዴ ናት ማለት ነው። የዘር ግንዴን ለማወቅ ማጠያየቁን ከቀጠልኩ የት ሊደርስ እንደሚችል ከወዲሁ መገመት የሚቻል አይሆንም። የዘር ፍተሻ ጉዳይ እንዲህ በሶስት አረፍተነገር የሚጠቃለል ባይሆንም ወደድንም ጠላንም የዘር ግንዳችን የአዙሪት ታሪክ ከዚህ አያልፍም።

ዞረን ዞረን እኛው ነን።

ዞረን ተዟዙረን እኛው ብንሆንም ዘር እና ዘረኛነት፣ ጐሳና ጐሰኛነት የአካባቢያችን አጀንዳ ሆነዋል። በአካባቢያችን ዘርና የዘር ጉዳይ፣ ጐሳና የጐሳ አጀንዳ ፖለቲካውን እየመሩት ይገኛሉ። በመሰረቱ ለፖለቲካ መጠቀሚያና መቀስቀሻ ስላዋልነው መዘዙ እየከፋ ሄደ እንጂ ስለ ዘር ማውጋት ዘረኝነት ባልሆነ ነበር። ከቅድመ አያታችን አለፍ እያልን ስለዘራችን ጥቂት ማውጋት ብንችል፣ ምን ያህል እንደተቀላቀልን ልንገምተው እንኳ አንችልም ይሆናል። ወደ ዘር ፍተሻ ከገባን 'ኦሮሞ ነኝ' የሚለው ሁሉ ኦሮሞ ላይሆን ይችላል። ጉራጌዎች ጉራእ ከሚባለው የኤርትራ ወረዳ ተነስተው በራስ ስብሃት እየተመሩ ዛሬ ወደ ሰፈሩበት የኢትዮጵያ መሬት ስለ መምጣታቸው ጥቂት ተፅፎአል። ኤርትራ ውስጥ ናይጄሪያውያን አሉ። ወደ መካ መዲና ለመስገድ የኤርትራን መሬት ሲያቋርጡ ወባ ይዞአቸው ይሁን፣ ወንዙ ደስ ብሏቸው ባይታወቅም ኤርትራ ላይ በቋሚነት ሰፈሩ። ኤርትራውያን ሆነዋል። የዛሬዎቹ እንግሊዞች ከጀርመን የፈለሱ እንደመሆናቸው፣ መንዜዎች ከኤርትራ ወደ ሸዋ የተሻገሩ

ሃማሴኖች ስለ መሆናቸው ጥናታቸውን የፃፉ ከጥቂት በላይ ናቸው። ከጎንደር የፈለሱ የአገው ሰዎችና የአፄ ገላውዴዎስ ወታደሮች ኤርትራውያን ሆነው ቀርተዋል። በጌምድር የሚለው ቃል "ቤጃ ምድር" ከሚለው መምጣቱ ተፅፎአል። የቤጃ ሰዎች በኤርትራና በሱዳን ይገዙ ነበር። የዘራቸው ሰንሰለት እስከ ፖርት ሱዳን ተዘርግቷል። ካርቱምን የመሰረቱት አማራ የተባሉ ወታደሮች ናቸው። የኦሮሞና የአማራ መቀላቀል መገመት ከሚቻል በላይ ሰፊ ነው። ኦሮሞዎች በጦርነት ድል ሲያደርጉ የተሸናፊውን ወገን ሚስትና ልጆች ወርሰው በጉዲፈቻ የራሳቸው የማድረግ ባህል ነበራቸው። የአጤ ምኒልክ ወታደሮች እንደ ከዋክብት ኦሮሚያን ሲያጥለቀልቁ ምን እንደተፈፀመ መገመት አይቻልም። የዘር መነሻና መድረሻው እንደ ወንዝ ነው። ከየት ተነስቶ የት እንደሚደርስ አይታወቅም። የዘር ሃረግና ዜግነት ለየቅል ናቸው...

"ዮሃንስ ወልደማርያም" የተባሉ የተጉለት ሰው በፃፉት መፅሃፍ ደግሞ፣ "ከሃረርጌ ግንብ የሚኖር ህዝብ ከሃማሴን የመጣ ነው" ብለዋል። ታሪኩንም እንዲህ ያብራሩታል፣

"በዳዊት ዘመን በሃማሴን አንድ ሃይለኛና ጀግና ሰው ነበር። በሃይለኛነቱ ሰው ስለጠላው ከሰው ተለይቶ ሚስቱንና ልጆቹን ይዞ ለብቻው በችፍግ ዱር ውስጥ ቤት ሰርቶ ተቀመጠ። ሃይለኛው አባት ሲሞትም አገሬው፣ 'እንግዲህ የዚያን የርጉም ልጆች ከምድር እናጥፋቸው' ብለው ተነሱባቸው። በተዋጉም ጊዜ እኒህ ልጆች ድል አድርገው ጠላቶቻቸውን ፈጁቸው። ጦርም ከፊታቸው የማይቆም ሆነ። አገር እያሴረ፣ እንደገና ጦር እየሆነ፣ ቢያስቸግራቸው ጓዛቸውን አንስተው ከብቶቻቸውን ነድተው እየተዋጉና እየተከላከሉ፣ እስከ ሃረርጌ ተሰደዱና በዚያ ተቀመጡ። የአካባቢው (ኦሮሞ) እየተዋጋ ሲያስቸግራቸውም የአገራቸውን ዙሪያ በብርቱ ግንብ አጠሩትና አምስት በር አደረጉለት። ቋንቋቸው ትግርኛ የነበረው ከዘመን ብዛት ተለውጦ ሌላ ሆነ። ነገር ግን ይኸውም ቢሆን ከትግርኛ በብዙ ይመሳሰላል..."

ገጠር የሚኖሩ ሃረሪዎች ሲፎክሩ፣ "ይፋት ሃገሬ! ይፋት ሃገሬ!" እንደሚሉም ተረድቼ ነበር። ሃረሪዎች፣ "ዘራፍ!" እንደሚባለው እነሱም፣ "ይፋት ሃገሬ!" እያሉ ይፎክራሉ። በርግጥ "ሃገር" የሚለውን ቃል ሳባውያንም ይጠቀሙበት ስለነበር





ቃሉ ከአማርኛ በፊት የነበረ ነው። ሃረሪዎች "ይፋት ምንድነው?" ተብለው ሲጠየቁ ግን ትርጉሙን አያውቁትም። "ሃገሬ ማለትስ ምን ማለት ነው?" ብዬ ስጠይቅ፣ እሱንም "አናውቅም!" አሉ "ከቅድመ አያቶቻችን ከጥንት ጀምሮ 'ይፋት ሃገሬ!' እየተባለ ይፎከራል" ብለው አጫወቱን።

ከሃማሴን የተሰደደው ቤተሰብ በቅድሚያ ይፋት ላይ ሰፍሮ ሊሆን ይችላል። በመቀጠል ወደ ሃረር ተሻግረው ሊሆን ይችላል። በርግጥ "ሊሆን ይችላል" እየተባለ ታሪክ እንደማይፃፍ አውቃለሁ። ይህ ግን ታሪክ አይደለም። የእሳትዳር ወግ ነው።

* * *

ፕሬስ መምሪያ ላይ አንድ ትንታግ የሆነ ጋዜጠኛ ነበር። ጋረደው ደምሴ ይባላል። እዚያ መስሪያ ቤት ሃላፊ በነበርኩበት ዘመን በየጊዜው ቢሮዬ እየመጣ፣

"ኤርትራ ከምትገነጠል ኢሳይያስ አፍወርቂ እዚህ መጥቶ ለምን አይመራንም?" እያለ በቁጭት እየተንገበገበ ይጠይቀኝ ነበር። ማህተማ ጋንዲም እንደ ጋረደው ደምሴ ያለ ተመሳሳይ ስሜት ነበራቸው፣

"ፓኪስታን ከምትገነጠል እባካችሁ ወንበሩን ውሰዱትና ምሩን" እያሉ ይለምኑ ነበር።

ይህን መሰል አነጋገር የሃገር ፍቅር የወለደው ስሜት መሆኑ አይካድም። ተጨባጩን እውነት ተቀብሎ ወደ ሚቀጥለው ምእራፍ መሸጋገር ግን ከህልመኛነት ያድናል።

ኢትዮጵያዊነትም ሆነ ኤርትራዊነት በአንድ ወቅት አልነበሩም። ሰዎቹ ግን ከዛሬው የማንነታቸው መጠሪያ በፊትም በነበሩበት ነበሩ። በአንድ አጋጣሚ አንድ ማንነት ሊፈጠር ይችላል። ሊከስምም ይችላል። ሮዶዢያዊ መሆናቸውን በኩራት ይናገሩ የነበሩት የብሪጣኒያ ዝርያ ያላቸው ነጮች ዛሬ ሮዶዢያዊነታቸውን በህግ ጭምር አጥተውታል። "ሶቪየት" የሚለው ግዙፍ የማንነት መግለጫ ቃል ወደ ልብስ አርማነት ተፈጥፍጦ ወድቋል። "ኤርትራ" ማለት ትርጉሙ "ቀይ" ማለት ነው። "ኢትዮጵያ" ማለት ደግሞ "ጠይም" ማለት ነው። እነዚህ ሁለቱም ቃላት የግሪክ ናቸው። "ሃበሻ" የሚለውም ቃል የዛሬው የማንነታችን የቅፅል ስም ለመሆን የበቃበት መነሻ ከማንነታችን

በጣም የራቀ ነው። አባ ጋስፒሪያ የፃፉትን እንደ ምንጭ ከተጠቀምን ሃበሳት የሚባል ከደቡብ የመን የመጣ አንድ ጠይም አጎት ነበረን። የዚያን ሰውዬ ስም ወርሰን ራሳችንን "ሃበሻ" እንላለን። "ሃበሻ" ማለት "ቅልቅል" ማለት ነው ሲሉ የሚከራከሩም አሉ። እርግጥ ነው፤ ስሙ ከየትም ይምጣ ከየት ከስነልቦናችን ጋር ከተዋሃደ የኛ ሆኖ መቅረቱ ግድ ነው። ዚምቧብዌ ማለት "የተደራረቡ ድንጋዮች" ማለት ነው። ትርጉሙና ስሜቱ ግን ከቀጥታ ትርጉሙ በላይ አድጐ የማንነት መግለጫ ለመሆን በቅቶአል። ዚምባብዌያውያን ራሳቸውን ሲገልፁ፣ "በዚምባብዌነታችን እንኮራለን" ይላሉ። ይሄ ሲተረጎም፣ "እኛ የተደራረብን ድንጋዮች! በመደራረባችንም ሆነ በድንጋይነታችን እንኰራለን" ማለታቸው ሊሆን አይችልም።

መራራውን እውነት መራራም ቢሆን እየጎመዘዘን ልንውጠው ይገባል። መራራውን እውነት ለኛ በሚጠቅም መንገድ ልናጣፍጠው እድልም አለን። አካባቢያችን እየተተራመሰ መሆኑ አይካድም። ጨርሶ ከቁጥጥር ውጭ ከመሄዱ በፊት ልናድነው ግን ይቻለናል። ይህ ህዝብ እስከዛሬ አብሮ መኖር የቻለው በሰንሰለት ስለተያያዘ አይደለም። በመሪዎች በጎ ፈቃድም አይደለም። መሪዎች በሚዘሩት የመለያየት መርዝ ሊበታተን እንደማይችል ግን ዋስትና የለንም።

ሱዳን ወደ አራት ያለመከፈል ዋስትና አላት ማለት አይቻልም። ኦሮሚያና ኦጋዴን በኢትዮጵያዊነት ላይ የመደራደር ዝንባሌ አላቸው። የትግራይ ኢትዮጵያዊነት ጥያቄ ውስጥ ገብቶ ባያውቅም የህወሃት ካድሬዎች ግን አጀንዳውን እንደ ማስፈራሪያ እየቆመሩበት ይገኛሉ።

"ትምክህተኛው ዳግም ወደ ስልጣን ከመጣ ትግራይ ነፃነቷን ታውጃለች" የሚለውን ህልማቸውን በተለያዩ ጊዜያት ብቅ ጥልቅ ማድረጋቸው አልቀረም። ሶማሊያ ተከፋፍላም እንኳ ሰላም የማግኘቷ ነገር አጠራጣሪ ሆኖአል። የሶማሊያ ምሁር ተሰባስቦ "አንድነት" መፍጠር ይችል የነበረበት አጋጣሚ ሁሉ አምልጦት አካባቢው ወደ ነበረበት ከማይመለስበት ደረጃ ላይ ደርሶአል። ጅቡቲ በጐረቤቶቿ በሚደርስባት ጫና እና ጉያዋ ገብተው ድንኳን በተከሉት ሃያላን አገራት ታፍና ተይዛ ትንፋሽ አጥታለች። ሻእቢያና ህወሃት ጥርስ ተናክሰው ያለሰላምና





ያለጦርነት ድንበር ላይ እንደተፋጠጡ አሉ? የኤርትራ ህዝብ ከግማሽ በላይ የወታደር ቁመና ይዞ በተጠንቀቅ ላይ ይገኛል። ከ18 አመት እድሜ በላይ ያለ ወንድና ሴት ኤርትራዊ ሁሉ ጠመንጃ ፈትቶ መግጠምና መተኰስ ይችላል። የኢትዮጵያ ሰሜንና ምእራብ ድንበሮች ላይ ታጣቂ ሃይሎች ይንቀሳቀሳሉ። የኦሮሞ፣ የትግራይና የአማራ አማፅያን ድንበርና በረሃ በረሃውን ሰፍረውበታል። "የአርበኞች ግንባር" የቴዎድሮስ መንደር እስከሆነችው እስከ ቋራ፣ እየተጠጋ ገባ ወጣ ይላል። ኦነግ በባሌ ተራሮችና በምእራብ ጫካዎች የማይነካ ይዞታ አለው። የኦጋዴን አማፅያን ክልሉን በጠመንጃቸው ቁጥጥር ስር አስገብተውታል። በመጨረሻም አፍሪቃ ቀንድ በጭጋጋማ ጉም ውስጥ ወድቆ የሚደናበር ክልል ለመሆን በቅቶአል፣

"ወዴት እያመራን ይሆን?" ለሚለው ጥያቄ መልስ ለማግኘት የፖለቲካ ጠበብት ቁምስቅላቸውን እያዩ ነው። ልዩነታችን ሰፍቶአል። የሚያጣላ በዝቶአል። የሚያስታርቅ ጠፍቶአል። የእብድ ገላጋይ በርክቶአል። የሚናገር እንጂ የሚያዳምጥ ጆሮ የለም። አእምሮው በጥያቄ የተወጠረ ዜጋችን ቁጥር የትየለሌ ነው...

ይህን ጨለማ ለመጪው ትውልድ አውርሰን እናልፍ ይሆን? እንደምንመኘው መኖር ለምን አንችልም? ለዚያ ለምንመኘው ህይወት አንመጥንም? ሃገር በጨለማ ጎጆ ውስጥ ተዘጋግታ ተቀምጣለች። የተሰደደው ወገን የስደት እድሜ ይቆጥራል። ባለንበት የሰለጠነ ዘመን እንዴት ከጃንሆይና ከደርግ የከፋና የዘቀጠ የአገዛዛ አስተዳደር ስር ልንወድቅ ቻልን? ለምንስ ሊከፋፍሉን ቻሉ? ወይስ ቀድሞውኑ አንድነታችን የቅጥፈት አንድነት ነበር? ሃገርን የሚከዱ ሰዎች እንደ ክረምት አንበጣ ሊፈሉ የቻሉበት ምክንያት ከቶ ምን ይሆን? መጠየቅ ለምን ወንጀል ሆነ? አሸናፊ አሳብን የመቀበል ወኔ ለምን ላይኖረን ቻለ? ግለሰቦች በአቅማቸው ሊያበረክቱ የሚችሉትን ልዩ አስተዋፅኦ የመናቅን ልማድ ከየት አመጣነው? ከመከባበር ይልቅ ግለሰብን የማዋረድ ባህል ለምን አዳበርን? ከሰለጠነው አለም ከመማር ይልቅ ለምን ይሆን በተቃራኒው መንገድ ለመጓዝ የተጣደፍነው? እንዴት እንዲህ ሊሆን ቻለ? ...

"አዲስ 40" በሚል የጫካ ስም ከሚታወቁት አቶ መልኬ

መንግስቱ ጋር አስመራ ላይ ተገናኝተን ስንጫወት፣

"እኔን ያሳሰበኝ 'ቀሪዋን ኢትዮጵያ ለማዳን እንችል ይሆን?' የሚለው ነው" አሉኝ።

እኔ በበኩሌ የአቶ መልኬን ስጋት አልጋራውም። ከዚያ የላቀ ራእይ ሊኖረን ይችላል ባይ ነኝ። ወያኔ ከደገሰልን ከጨፍና ከበርበሬ ፖለቲካ የላቀ ህልም ማለም እንችላለን። ለዚያም ደግሞ እንመጥናለን።

የላቀው ራእይ በአፍሪቃ ቀንድ ደረጃ ማሰብ ነው። የኤርትራ መገንጠል የችግራችን ማእከል አልነበረም። ርግጥ ነው፤ አቶ መልኬ መንግስቱ እንደሰጉት የኦጋዴንና የኦሮሚያ አጀንዳም ገና መልክ አልያዘም። ከሃያ አመታት በሁዋላ በኢትዮጵያ ምድር ላይ አማርኛ መናገር የሚችል አንድም ኦሮሞ አይኖርም። ይህን አስተውለናል? የጋራ ቋንቋ በምንናገርበት በዚህ ዘመን ቁጭ ብለን ካልተግባባን በቱርጁማን ኢትዮጵያዊነትን እንገነባለን ብሎ ማሰብ ህልም ነው። መፍትሄዎች በአፍሪቃ ቀንድ ደረጃ መታሰብና መፈለግ አለባቸው ብዬ እየጮህኩ ነው። ኢትዮጵያን ከካርታ ላይ ለመደምሰስ የሚሮጡ ሃይሎችን መቋቋም የምንችለው ከብጥስጣሽ የጎሳ ስሜቶች ባሻገር ሰፊ ራእይ ካለን ብቻ ነው። ይህን መሰሉ ራእይ ሊፈፀም እንደማይችል ቅዠት በመቁጠር፣ 'እግዚአብሄር ያውቃል' የሚሉ አጎቶች ሞልተውናል።

አጎታችን ሆይ!

ርግጥ ነው! እግዚአብሄር ያውቃል። እንጀራህን ግን ራስህ መጋገር አለብህ። እግዚአብሄር አምላክህ እንጂ አሽከርህ አይደለም።

ድብልቅ ነን።

ድብልቅ ስለሆንን ግን የብሄር ጥያቄ ተፈቶአል ማለት አይደለም። ጠርነቶች ይካሄዳሉ። ጠርነት ስደትን ይወልዳል። በጠርነት ድልና ሽንፈት ይከተላል። ዜግነትና ማንነትም እንዲሁ ከፖለቲካው ጋር ይቀያየራል። እኔና ጓደኞቼ ኦሮሞ፣ አማራ፣ ጉራጌ ወይም ትግሬ ስለመሆን አለመሆናችን ትዝ ብሎን አያውቅም ነበር። ይህን ባህል ያመጡብን ከኛ የቀደሙት ፖለቲከኞች ናቸው። ተከታይ ትውልድ እንደመሆናችንም ችግሩ ከነአተላው ተደፍቶብናል።

ወያኔ በግድ ስለ ዘራችን እንድናወራ አስገድዶናል።





ሰዎችን በዘራቸው የመፈረጅን በሽታ ወያኔ ጀመረው ማለቴ ግን አይደለም። በሚኒልክና በጃንሆይ ዘመን የነበረው የብሄር ጭቆና የዛሬውን መረን የለቀቀ መከፋፈል እንደ ወለደው ማመን ይገባል። ወያኔ በሽታውን ከማከም ይልቅ አባብሶታል። በመሆኑም እከሌ ከእከሌ ሳይባል ሁላችንም ገብተንበታል። እንደገባንበት መካድ መፍትሄ አይደለም። ከዚህ ቆሻሻ የዘረኝነት ገንዳ እንዴት እንደምንወጣ ማሰብ ግን አለብን።

በቀዳሚዎቹ ስርአት በቋንቋቸው ምክንያት በደል ያልደረሰባቸው አማሮች ሳይቀሩ በዚህ ዘመን "ኢትዮጵያዊነት" ከሚለው ዝቅ ብለው "አማራ ነኝ!" ማለቱን እየለመዱት መጥተዋል። ፕሮፌሰር አስራት "መላው አማራ" የተባለውን (መአህድ) ሲመሰርቱ በእነመለስ ዘንድ ከፍተኛ ትረባ እንደነበር አስታውሳለሁ። "ጐትተን አስገባናቸው!" የሚል የድል ምልክት ነበር። መአህድ ከተመሰረተ በሁዋላ አማራው የአማራን ጉዳይ ለይቶ መከታተል ጀመረ። "ሌላው አይመለከትህም" ተባለ። ኢትዮጵያን የመበታተኑ አጀንዳ ሙሉ በሙሉ መልክ መያዝ የጀመረው አማራው በወያኔ መንገድ ተጉዞ መአህድን ሲመሰርት ነበር። በወቅቱ ፕሮፌሰር አስራት ያን ማድረጋቸው ልክ ነበር። ታምራት ላይኔ ሃረር ወርዶ፣

"ሽርጣም! እያለ የሚሰድብህን ነፍጠኛና ትምክህተኛ በለው! ፍለጠው! ቁረጠው!" ብሎ ሲያውጅ አማራውን የሚታደግ አንድ ድርጅትም ይሁን ማህበር መመስረት የወቅቱ ወሳኝ ጥያቄ ነበር። ቢሆንም ውጤቱ ለወያኔ በእጅጉ ጠቃሚ ለመሆን በቅቶአል።

ዛሬ ይቺ ሃገር በጎሳ ፖለቲከኞች እና በኢትዮጵያዊነት አራማጆች ፅንፋዊ ትግል መካከል የስንግ ተይዛለች። ኢትዮጵያዊነት ማሸነፉ አይቀርም። ምን ያህል ዋጋ እና ጊዜ እንደምንከፍል ግን ገና አልታወቀም።

"የትብብር ጩኸት!" የሚባል ነገር አለ። ይህችን ቃል ያገኘሁዋት ሙሉጌታ ሉሌ በ1997 ከፃፈው አንድ መጣጥፍ ላይ ነበር። ባለንበት ዘመን የሚያስፈልገን ግን ከዚያም በላይ፣ "የትብብር ቁጣ!" ጭምር ነው። እንደ ኢያሪኮ በጩኸት የሚፈርስ ግንብ የለም። እስካሁን የተሳሳትናቸው፣ ምን ማድረግ እንደሌለብን ጠቁመውናል። የከሸፉ ሙከራዎቻችን ማድረግ የሌለብንን መጠቆም ከቻሉ፣ በእጃችን ላይ የቀረውን አማራጭ

ማየት አለብን።

አምላክ ነፃ አድርጎ ፈጥሮናል። ነፃ ሰው ነን። እያንዳንዳችን አንድ ሰው ነን። መሪዎችም ግለሰቦች ናቸው። እስከ መቼ በፍርሃት ባርነት ሰንሰለት ታስረን መኖር እንዳለብን የሚወስኑት መሪዎች ሳይሆኑ እኛው ነን። 'ከጭጋጋማው ጉም ወጥተን የነፃነትን ብርሃን መቼ እናያታለን?' የሚል ጥያቄ ጭንቅላታችን ውስጥ አለ። መልሱም አብሮ አለ። እኛ ጠይቀን፣ እኛ አስበን፣ እኛው መፍትሄ መስጠት እንችላለን። ምክንያቱም ማንኛውንም ነገር ለማድረግ የምንችል ሙሉ ሰው ነን። አፍሪቃ ቀንድን ወደ አንድ መንደር የመለወጥ ህልም ያላቸው ሊመሩን የሚችሉ ሰዎች እጥረት አይደለም ችግራችን። ሰዎች አሉ። ከሌሉም መፍጠር የምንችለው እኛው ነን።



# - 21 -

# ደስተኛው ጄኔራል

ነሸጠው ሸፈጠ - ሄደ ሸመጠጠ፣
በመስተፋቅር ጦር - ልቤ አመለጠ፣
ባር ባር አለ ሆዴ - ልቤ መሬት ለቆ፣
ሊያከንፈኝ እንዳይሆን - አለግብሩ መጥቆ፣
አላስተዳደጉ - አለባህሉ ወድቆ፣
ሸው እልም ሸው እልም - ልቤ ወፌ-ይላላ፣
በመስተፋቅር ቀስት - በሮሮ ምህላ፣
እንደ ደመና አክናፍ - እንደ ጮራው ጥላ፣
ሸው እልም ሸው እልም - ሸው እልም ይላላ፣

(ግጥም - ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን)

ጄኔራል ባጫ ደበሌ በ1995 መጨረሻ ላይ ፕሪቶሪያ ለህክምና መጥቶ ሳለ 'ትርሲት' ተብሎ ከሚታወቅ ሬስቶራንት ውስጥ አግንቼው ነበር።

ከኢትዮጵያ ኤምባሲ የተመደቡለት ሾፌርና አጃቢ አብረውት ነበሩ። አካባቢውን በአይን እየተቆጣጠሩ የጄኔራሉን ደህንነት ይጠብቁ ነበር። ትእዛዝ ሆኖባቸው እንጂ ፕሪቶሪያ ላይ ባጫ ደበሌን የሚተናኮለው ቀርቶ የሚያውቀው እንኳ አልነበረም።

ባጫ ቴክሱ እንደ ወትሮው ሸክ ብሎ ነበር።

ቄንጠኛ ጫማ ተጫምቶአል። የነጭ ሸሚዙን እጅጌ

ሁለት ዙር አጥፎአታል። የወርቅ ሃብሉ በሸሚዙ መሃል ያበራል። የዳንሰኛነት ቅርፁንና ተፈጥሮውን ጠብቆ መቆየቱን አልተጠራጠርኩም። በሞቀ ሁኔታ ከተቃቀፍን በሁዋላ ቁጭ ብለን ጥቂት ተጨዋወትን፣

"እዚህ ነህ እንዴ ለካ?" ሲል ጠየቀኝ።

"እዚህ ነኝ የውልህ። አንተስ እዚያው ነህ?"

"እኔም እዚያው ነኝ"

ይህን ከተባባልን በሁዋላ የምናወራው ጠፋን።

"ጓደኞቻችን እንዴት ናቸው?" ስል ጠየቅሁት።

"ደህና ናቸው"

ከጥቂት ዝምታ በሁዋላ እንዲህ አለኝ፣

"አቦይ ስብሃትን ላነጋግርልህና ወደ ሃገር ቤት ተመለስ?"

ስስቅበት ጊዜ ሊያሳምነኝ ጥረት አደረገ፣

"ምን መሰለህ? እንደቀድሞው እንዳይመስልህ። ብዙ ነገር ተሻሽሎአል። ብዙ ነገር ተለውጦአል። እንደምታውቀው የሃገሪቱ ዋና ችግር የነበረው ዘረኛው ስዬ ነበር። እሱ ደግሞ እንደምታውቀው ሸቤ ገብቶአል። አንድ ነገር ልንገርህ? እነ ስዬ ሊያርዱን ተዘጋጅተው ነበር። ግን ቀደምናቸው። አሁን ብዙ አሰራሮች ተስተካክለዋል። ደበሌ ይሙት! ኢኮኖሚያችን እየተመነጠቀ ነው። "

በጣም ሳቅሁ። ባጫ ግን ቀጠለ፣

"...ደበሌ ይሙት ስልህ! ኢኮኖሚው አድጎአል። ብትመለስ ይሻልሃል። እዚህ ደቡብ አፍሪቃ ምን ታደርጋለህ? ለአቦይ ስብሃት ልንገርልህና ተመለስ..."

"ባጫ!" አልኩት ትከሻውን ይዤ፣ "...ላንተም እያዘንኩልህ ነው። ላንተ የምመኝልህ ያን እግዚአብሄር የሰጠህን የተደበቀ ተአምራዊ ችሎታህን ብትቀጥልበት ነው። የኢትዮጵያን ህዝብ ፍቅር ልታተርፍ የምትችልበትን ያን ድንቅ ችሎታህን ተጠቀምበት። እርካታ ታገኝበታለህ..." አልኩት።

ባጫ አላዳመጠኝም። በመከፋት ተከዘ። ከዚያ በሁዋላ ልናወራ የምንችለው ርእስ አልነበረንም፣

"ጤንነትህ እንዴት ነው ታዲያ?" ስል ጠየቅሁት።

"ደህና ነኝ።"

ከመቀመጫዬ ተነስቼ ለስንብት እየጨበጥኩት፣

"አምላክ ምህረቱን ይስጥህ። ሰሞኑን እንኳ እዚህ





ፕሪቶሪያ የለሁም። ከቆየህ ግን ምናልባት በድጋሚ እንገናኝ ይሆናል" ብዬ ተለየሁት።

ከዚያ በሁዋላ ደስተኛውን ጄኔራል አላገኘሁትም።

አዲሳባ እንደተመለሰ ግን ለቀድሞ ጓደኞቹ ስለኔ አንስቶ፣ "ፕሪቶሪያ ላይ አገኘሁት" ሲል ነገራቸው። አያያዘናም፣

"እንደማንኛውም ስደተኛ ሲንከራተት አገኘሁት። ተራ ሰው፣ ተራ ስደተኛ ሆኖአል።" ሲል አብራራላቸው።

ጓደኞቹ ይህን ሲፅፉልኝ፣

"ባጫ አልዋሸም። እውነቱን ነው" ስል መልስ ሰጠሁ።

በርግጥም ባጫ አልዋሸም ነበር። ተራ ስደተኛ፣ ተራ ሰው ነበርኩ። ከባጫ ጋር የሚንግባባው 'አዲሳባ ከወያኔ ጋር ሳለሁስ ምን ነበርኩ?' የሚለው ጥያቄ ላይ ነው። ይህም የአስተሳሰብና የምርጫ ጉዳይ ነበር። በተቀረ እንደ ሚሊዮናት ሃበሾች ሁሉ እኔም ተራ ስደተኛ መሆኔ ርግጥ ነው። በገዛ ፍላጎቴ ለወያኔ አስረክቤ የነበረውን ነፃነቴን መልሼ እንዳገኘሁ ባጫ የመገንዘብ ችሎታ ይኖረዋል ተብሎ ግን አይታሰብም።

ከባጫ ደበሌ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋወቅነው አዴት ከተባለ ቦታ ላይ በ1982 መጨረሻ ነበር። ነፍሱን ይማረውና እያሱ በርሄ ነበር ያስተዋወቀን። ባጫ የሙዚቀኛነት ስራውን ትቶ ወደ ፖለቲካው የገባበት ወቅት ነበር። በወቅቱ አዴት ላይ ዮናታን ዲቢሳ በሚመራው መድረክ፣ እነ ክንፈ አህዴድ የተባለውን ድሮ ዳቦ እየጋገሩ ነበር። በዚያን እለት እያሱ በርሄ ስለ ባጫ ጥቂት አጫውቶኝ ነበር። ሁዋላ ደርግ ሲወድቅም ከሌሎች ሰዎች ስለ ባጫ ተጨማሪ ሰማሁ። አልፎ አልፎም በተለያዩ አጋጣሚዎች እንገናኝ ነበር። ጓደኛሞች ግን አልነበርንም። ጥሩ ሰላምታ ብቻ ነበረን።

የባጫ የህይወት ታሪክ በጣም አጭር ነው።

የቡራዩ ልጅ ሲሆን፣ ሲወለድ ወላጆቹ "አትንኩኝ ደበሌ" ሲሉ ሰየሙት። አትንኩኝ እድሜው ለጋብቻ ሲደርስ ወታደር ሆነ። ቀልጣፋ ስለነበርም ከጓደኞቹ ቀድሞ የአስር አለቃነት ማእረግ ማግኘት ቻለ። አስር አለቃ አትኩኝ ደበሌ ኤርትራ ላይ እንደ ማንኛውም ወታደር ለእናት ሃገሩ በጀግንነት ሲዋጋ ቆይቶ፣ ድሉ ለጠላት ሆነና ባጫ የመማረክ እጣ

ገጠመው። ባጫ ከተማረከ በሁዋላ በምርኮኛ ማእከል ቆይታው በአጭር ጊዜ ውስጥ በሙዚቃ አፍቃሪነቱ ታዋቂ ለመሆን በቃ። ምርኮኞችን በማዝናናት ሃዘናቸውን እያረሳሳ የማይረሳ አስተዋፅኦ አደረገ። ያለምንም የሙዚቃ መሳሪያ በከንፈሩ ብቻ ድምፅ እያወጣ፣ በራሱ ድምፅ መልሶ እየደነሰ ጓደኞቹን ለማስደሰት ያደርግ የነበረውን ጥረት አብረውት የነበሩት በፍቅር ያስታውሱታል። በወቅቱ በባጫ የሙዚቃ ፍቅርና ችሎታ የተመሰጠ ሃይሌ አሲንባ የተባለ የሻእቢያ የባህል ክፍል ባልደረባም ለባጫ ክራር ሸልሞታል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ያሬድ ጥበቡና በረከት ስምኦን ወደ ሻእቢያ ነፃ መሬት ሄደው ለመታገል ፈቃደኛ የሆኑትን ምርኮኞች ለይተው ወደ ኢህዴን ነፃ መሬት አመጧቸው። አትንኩኝ ክራሩን አንድ ቅያሬ ሱሪ ይዞ ወደ ኢህዴን ከመጣ በሁዋላ የኢህዴን ኪነት ውስጥ ከጃዝ መቺነት እስከ ሃላፊነት እየሰራ ታገለ። ኦህዴድ ሲመሰረትም "አትንኩኝ" የተባለውን የወተት ስሙን በመተው፣ ራሱን በራሱ "ባጫ" ሲል ሰየመ። በዚያው ሰሞንም ደርግ ወደቀ። ደርግ ሲወድቅ እነ ፃድቃን "ሜጀር ጄኔራል" የሚለውን ማእረግ ከባጫ ስም ፊት ጨመሩለት። ሜጀር ጄኔራል ባጫ ደበሌ ሆነ። ባጫ ከጄኔራልነቱ ይልቅ በአስደናቂ የዳንስ ችሎታውና በሙዚቃ ፍቅሩ በሰራዊቱ ውስጥ በሰፊው ይታወቅ ነበር።

ስለ ዘመናችን የወያኔ ባለስልጣናት ስናወጋ መቼም ስለዚሁ ደስተኛ ጄኔራል ማንሳታችን አይቀሬ ይሆናል። በሰራዊቱ ውስጥ ስለ ባጫ ብዙ ቀልዶች ይነገራሉ። እነ ጄኔራል ረጋሳ ጂማን የመሰሉ ወታደራዊ ጠበብት የጨበጡት በትረ መኮንን ባጫ እጅ ላይ በመውደቁ ከልብ የሚያዝኑ አጋጥመውኛል። ማዘን አያስፈልግም። እንዳልጨበጠ ማሰብም ይቻላል። ለስላቃዊ ፈገግታ ቢሆናችሁ ታዲያ፣ የጄኔራሉን አንዳንድ ገድሎች በጨረፍታ ላውጋችሁ...

* * *

ጄኔራል ባጫ አንዳንድ ጊዜ መድረክ ላይ ያልተጠበቁ ንግግሮችን ያደርጋል። እንዴት እነዚያን ደፋር ንግግሮች ሊናገር





እንደሚችል ግን የሚያውቅ የለም። እንዲያ እየተናገረ የህወሃት ምርጥ ሰው ሆኖ ሊቆይ በመቻሉ የሚገረሙም አሉ።

ክንፈ በተገደለበት ስብሰባ ላይ ባጫ እንዲህ ብሎ ነበር፣

"ኢትዮጵያ በመላ ሃገሪቱ በመቶ አመት ያልገነባችውን፣ ትግራይ በአስር አመት ፋብሪካ በፋብሪካ ሆናለች! ይሄ ፍትሃዊ አይደለም..."

የትግራይ መኰንኖች በዚህ የባጫ ንግግር ከመደነቅ በላይ ተገርመዋል። ያስገረማቸው ባጫ የተናገረው ሳይሆን፣ ያን የመሰለ ንግግር ከባጫ አንደበት በመስማታቸው ነበር። ኮሎኔል ተወልደ የተባለው የመከላከያ የመረጃ ሃላፊ እጁን ያወጣና እንዲህ ይላል፣

"እዚህ ስብሰባ ውስጥ ሚሊዮናትን ዘርፎ ያከማቸ ጄኔራል አለ። የዚህ መረጃ ዝርዝር በእጄ ላይ ይገኛል"

ባጫ ለተናገረው መልስ መሆኑ ነው። ባጫ የዘመኑ ባለ ሚሊዮን ቱጃር መሆኑ በድፍን መከላከያ የተከካና የተቦካ ወሬ ስለነበር ነው ተወልደ ወደ ዝርዝሩ ያልገባው።

ባጫ ይህን ያህል ገንዘብ ማከማቸቱ የታወቀው፣ አሮጌው ገንዘብ በአዲሱ በተለወጠበት እለት ነበር። ባጫ እንደ ሱፔቦሩ የቡና ነጋዴ ገንዘቡን ባንክ አያስቀምጥም። የገንዘብ ለውጡ የመጣ ጊዜ ታዲያ ችግር ውስጥ ገባ። ጠባቂዎቹን በቡድን አሰልፎ ገንዘቡን ከፋፍሎና በታትኖ ሲያስመነዝር ዋለ። የህወሃት ሰዎችም ይህን መረጃ አግኝተውታል።

ባጫን ግን አልነኩትም።

ገንዘብ ከማፍቀሩ በቀር ምንም የፖለቲካ በደል ያልፈፀመ "ንፁህ ሰው" ነው ብለው ያምናሉ። ገንዘብ ማፍቀር ደግሞ ምን ችግር አለው? ባለስልጣናቱ ሁሉ የቻሉትን ያህል እያፈቀሩ ነበር።

በዚያን እለት ባጫ ትግራይ ላይ ስለተገነባው ፋብሪካ ሲናገር ግን እንደዋዛ ዝም አልተባለም። መከላከያ ውስጥ የተቋቋመው ጊዜያዊ የሙስና ኰሚቴ ባጫ ደበሌን ጠርቶ አነጋገረው። የሙስና ኰሚቴው ዳኞች፣ ጄኔራል ክንፈ ዳኘው፣ ግርማ በዶ፣ አባተ (ጐሚቢሶ) እና ጌትነት ጉደያ ነበሩ። ባጫ ተከሰሰና እነዚህ ፊት ቀረበ፣

"ከዲንሾ ጫት ላኪ ኩባንያ አስር ሚሊዮናትን መብላትህ ተረጋግጦአል። ይህን ገንዘብም በገንዘብ ለውጡ ጊዜ ፒካፕ

መኪና መድበህ ሞላ እና ሺመክት በተባሉ አጃቢዎችህ አማካይነት በፌስታል እየሞላህ ማስመንዘርህ ታውቆአል። እምነት? ክህደት?" ሲሉ ጠየቁት።

ባጫ ካደ።

ኮሚቴው ተጨማሪ መረጃ ለማሰባሰብ በቀጠሮ ያሰናብቱታል። በዚህ መሃል ባጫ በብቸኛ ወዳጁ በአዜብ መስፍን በኩል አማላጅ ወደ መለስ ዜናዊ ይልካል።

መለስ ዜናዊ እጁን አስገባ።

ወደ ጄኔራል ሳሞራ ደውሎ እንዲህ ይለዋል፣

"49 *ያመጣና፣* 50 *ያመጣ ተማሪ* እኩል ነው። ባጫን አትንኩት!"

*(መለስ ይህን የተናገረው ሳሞራም ሆነ ባጫ ወይም ሌሎቹ ጄኔራሎች በዝርፊያው አንዱ ከሌላው እንደማይተናነስ ለማመልከት ነበር)*

ሳሞራ ይህችን የመለስን ውስጠ ወይራ ንግግር እንደ ቀልድ እያደረገ መኮንኖች ክበብ በከረንቦላ ዙሪያ ሲያወጋት ሰነባበተ። ከዚያም የባጫ ክስ ተሰረዘለት። የመለስን ንግግር መነሻ በማድረግ፣ በተጨማሪ የቅድመ ትግል ስሙን በማስታወስና በማዳቀል ቅፅል ስም ወጣለት። "ጄኔራል አትንኩት ደበሌ"

*(ባጫ ብዙ ቅፅል ስሞች አሉት። ከነዚህ አንዱ "ራስ ባጫ" የተባለችው ናት። ይህን ስም ያወጣለት አለምሸት ደግፌ የተባለው ጄኔራል ነበር። በጄኔራሎች ስብሰባ ላይ ባጫ በዝምተኛነቱ ይታወቅ ነበር። አንድ ጊዜ ታዲያ ሳሞራ፣*

*'ስብሰባ ላይ አሳብ የማትሰጡ ጄኔራሎች ብታስቡበት ይሻላል' ሲል ያስጠነቅቃል።*

*በነጋታው ባጫ እንዲህ የሚል አሳብ አቀረበ፣*

*'ማእረጋችን በባእዳን ቋንቋ በፈረንጆች ከሚጠራ እንደቀድሞአችን በሃገራችን ባህል ለምን አንጠራም?'*

*ተረኛው ተናጋሪ አለምሸት ነበረና እንዲህ ሲል ንግግሩን ጀመረ። 'ራስ ባጫ የጠየቁን ይቆይልንና...)*

በዚያን ጊዜ ባጫ በሙስና የተከሰሰው ለአፍ ወለምታው እንዲቀጣ እንጂ ባጫን ለመጉዳት ታስቦ አልነበረም። ያን ቀን ምን እንደነካው ባይታወቅም ክንፈ በተገደለበት በዚያ ስብሰባ





በርግጥም ባጫ አንበሳ ሆኖ ነበር የዋለው። ለአብነት እንዲህ ሲል ጠይቆ ነበር፣

"ለኔ የተሰጠኝ የጄኔራልነት ማእረግ የኦሮሞን ህዝብ ትኩሳት ለማቀዝቀዝ ነው። እኔ በማእረጌ አልተጠቀምኩበትም"

ጉልያድ የተባለ የህወሃት ኮሎኔል እጁን አውጥቶ እንዲህ ሲል አላገጠበት፣

"ባጫ! ጄኔራልነትህን አልተጠቀምክበት እንዴ? አንተስ እንዴት ነው የኦሮሞን ህዝብ ትኩሳት ልታቀዘቅዝ የምትችል? ለአንተ የጄኔራልነት ማእረግ መስጠት ስላለብን ነውኮ እኔ በወቅቱ ዝቅ ብዬ የሻምበልነት ማእረግ የተሰጠኝ!"

ከፍተኛ ሳቅ አዳራሹን አናጋው።

ኮሎኔሉ ጄኔራሉን ሲሞልጨው መኮንኖች ተሰብስበው በሳቅ አውካኩ። በየትም አለም ወታደራዊ መስሪያ ቤት ይህን መሰል ሁኔታ ተከስቶ እንደማያውቅ ርግጠኛ መሆን ይቻላል። አበበ ገረሱ የተባለ ኦሮሞ ኮሎኔል ከስብሰባው ተካፋዮች አንዱ ነበር። ጄኔራል ባጫ መሳቂያና መቀለጃ መሆኑ ተሰምቶት እጁን አውጥቶ እንዲህ ሲል ተናግሮአል፣

"ጎልያድ! አሁን እንኳ ኮሎኔል ሆነሃል። ሻምበል እያለህም ግን ስልጣንህ ከጄኔራል ባጫ ጄኔራልነት እንደሚበልጥ እኮ ሰራዊቱ ሁሉ ያውቃል! ለምን ትመፃደቃለህ?"

* * *

በኢትዮ - ኤርትራ ጦርነት ካልተካፈሉት ጄኔራሎች መካከል ባጫ አንዱ ነው። በወቅቱ ባጫ የምስራቅ እዝ አዛዥ ነበር። እሱ የሚመራው ጦር ለጦርነት ወደ ሰሜን ሲንቀሳቀስ ባጫ ከሰራዊቱ ተለይቶ እዚያው ሃረር ቀረ። የድሬዳዋና የሃረር ተቋማት ጥበቃ ሃላፊ የሚል ሃላፊነት ቢሰጡትም ዋና ስራው የቁጩ ቀዳሚ እመቤታችንን የጫት ንግድ ስራ ማሳካት ነበር። በዚያን ሰሞን ታዲያ ሃሜት በዛበት። ሰዎች ሁሉ ይጠይቁታል፣

"ጄኔራል! ምነው ወደ ግንባር አይሄዱም እንዴ?"

"ክቡር ጄኔራል! ሰራዊትዎ ግንባር ሄዶ የለም እንዴ?"

ባጫ እንዲህ ሲል ይመልሳል፣

"እኔ ግንባር መሄድ ፍላጎት ነበረኝ። ችግሩ ግን ፃድቃን አይወደኝም። እኔን ለማዋረድ ነው እዚህ ያስቀረኝ"

ባጫ በዚህ መንገድ መቆየት ስላልቻለ እንደተለመደው

በአዜብ በኩል ወደ መለስ ስሞታ አቀረበ። መለስ ዜናዊም የሰዎችን ችግር ፈጥኖ የሚገነዘብ አርቆ አስተዋይ እንደመሆኑ 49/50 በሚለው ቀመር መሰረት ባጫ ቡሬ ግንባር እንዲመደብ አደረገ። ጦርነቱ ሊጀመር አንድ ሳምንት ሲቀረውም ታደሰ ወረደ የተባለ አንድ የህወሃት ብርጋድየር ጄኔራል ወደ ቡሬ ግንባር መጣ። ሜጀር ጄኔራል ባጫን ጨምሮ ሁሉንም የግንባሩን አዛዦች ሰበሰባቸውና እንዲህ ሲል መመሪያ ሰጠ፣

"ከዛሬ ጀምሮ አዛዣችሁ እኔ ነኝ! ባጫ ወደ ሃረር መመለስ ትችላለህ። ጨርሰናል!"

ባጫ ቅሬታ አላደረበትም። ግዳጁን ስለተወጣ የበታቹ ያዘዘውን ተቀብሎ ወደ ሃረር ነጎደ። ጀለቢያውን ለብሶ፣ ጫቱን በነጭ ጨርቅ ሸፍኖ ለተክዚና ከተዘጋጀ በሁዋላም የጦርነቱን ወሬ ለመስማት ቴሌቪዥኑን ከፈተ።

*(ከጦርነቱ በሁዋላ በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት የተካፈሉ የሰራዊት አባላትና አዛዦች የፎቶግራፍ ኤግዚቢሽን ሲቀርብ የባጫ ደበሌ አንድም ፎቶግራፍ አልነበረም።)*

ባጫ አልፎ አልፎ በብስጭት እላፊ ቢናገርም፣ ለህወሃት በጣም አስፈላጊ ሰው ነበር። ከመለስ ሚስት ጋር በጫት ንግድ ስራ መተባበሩ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ረቂቅና ለህወሃት አስፈላጊ ተግባራትንም ይፈፅማል።

ከእነዚህ ገድሎቹ አንዱ የሚከተለው ነው…

በህወሃት ክፍፍል ሰሞን ጄኔራል ባጫ፣ "መፈንቅለ መንግስት አስቤያለሁ" ብሎ ውስጥ ውስጡን ኦሮሞ መኮንኖች ዘንድ ማስወራት ጀመረ። ባጫ ምንም እንኳ የተናቀ ሰው ቢሆንም፣ ምናልባት ቁጭት አድሮበት ኢትዮጵያ ላይ አንድ ተአምር ሊፈጥር ይችል ይሆናል ብለው ተስፋ ያደረጉ ጥቂት ኦሮሞዎች፣

"ህይወታችንን እንሰጣለን! ምራን! እንከተልሃለን'" እያሉ በቁርጠኛነት ደገፉት።

ባጫ በመፈንቅለ መንግስቱ ሊተባበሩ የሚችሉ ቆራጥ ኦሮሞ መኮንኖችን መልምሉልኝ እያለ ስም ሲመዘግብ ሰነበተ። በመጨረሻ ግን ያልተጠበቀ ነገር ተከሰተ።

ባጫ ሃረር ቤተመንግስት ግምገማ ላይ ቀረበና፣





"መፈንቅለ መንግስት ለማድረግ አስቤ ነበር። አሁን ግን ተፀፅቻለሁ። ግለሂስ አውርጃለሁ። እኔን ስትከተሉ የነበራችሁ ራሳችሁን አጋልጡ" ብሎ አወጀ!

ባጫን የተከተሉት አብዛኞቹ ስብሰባው ላይ ነበሩ። እንኳን ራሳቸውን ሊያጋልጡ በተቀመጡበት ደንዝዘው ነበር። በመሆኑም ባጫ ተባባሪዎቼ የሚላቸውን ስም እየጠቀመ አስያዛቸው። የተጠቆሙት እዚያው በቁጥጥር ስር ዋሉ። ታሰሩ፣ ተደበደቡ፣ ተባረሩ።

ባጫ ግን፣ "ግለሂስ በማውረድህ ያስመሰግንሃል። ዳግም መፈንቅለ መንግስት እንዳታስብ" የሚል የቃል ማስጠንቀቂያ ተሰጠው።

ባጫ መፈንቅለ መንግስት ስለ መሞከር ሲያስወራ የነበረው ልባቸው የሸፈተ የኦነግ ደጋፊዎችን ለመለየት እንዲያመች በነሳሞራ ታዞ ሊሆን እንደሚችል የሚያጠራጥር አልነበረም። የቻይናው ማኦ ዜዱንግ ያን የመሰለ ዘዴ ይጠቀም ነበር። አንድ አባባልም ነበረችው። "እባቡ ከጉድጓዱ እንዲወጣ አለማምደው! ከዚያም አናቱን ቀጥቅጠው!"

* * *

በ1998 በመከላከያ ውስጥ የሪፎርም ኮሚቴ ግምገማ ተካሂዶ እንደነበር ዝርዝሩን ሰምቻለሁ። የመከላከያ አባላት በረጅም ጊዜ ሂደት የስነስርአትና የስነምግባር ደረጃቸውን እንዲያሳድጉ እቅድ ተነድፎ እየተሰራ ነበር። ይህ ሪፎርም ከአለባበስ ጀምሮ የሰራዊቱ አባል ወታደራዊ አቋም እንዲላበስ የሚያደርግ ነበር።

በአመቱ ግምገማ ሲደረግ፣ ግምገማውን የመራው ጄኔራል ሳሞራ የኑስ ነበር። ባጫ ደበሌ ተራው ይደርስና እሱ በሚያዘው ክፍል የተሰራውን ስራ በፅሁፍ ማቅረብ ይጀምራል። ከጄኔራል ባጫ ስር የነበረ ኮሎኔል ሃይሉ ፍሮምሳ የተባለ መኮንን የፃፈውን ሪፖርት ነበር ባጫ የሚያነበው። ወዲ ባቤ የተባለ ሌላ የባጫ እዝ ባልደረባ ታዲያ እጁን ያወጣና እንዲህ ሲል ይጠይቃል፣

"ይህ የተነበበው ሪፖርት የኛ እዝ ነው ወይስ የሌላ?"

ሳሞራም በወዲ ባቤ ጥያቄ ተደንቆ፣

"አብራችሁ አልሰራችሁም እንዴ?" ሲል ይጠይቃል።

ወዲ ባቤ እንዲህ ሲል መለሰ፣

"እኔ ጄኔራል ባጫን ያለ ዛሬ አይቼው አላውቅም። ይሄ የተነበበው ሪፖርትም አንዱም እንኳ አልተሰራም"

ይህን ጊዜ ሳሞራ ግልፍ ብሎት፣

"ባጫ ለነገሩ ጫት ስትቅም ነው የምትውለው። መቼ ጊዜ አግኝተህ ነው ስራ የምትሰራው?" ይለዋል።

ባጫ በበኩሉ ገንፍሎ ለሳሞራ ምላሽ ሰጠው፣

"ሳሞራ! ምን እኔን ትናገራለህ? አንተስ ብትሆን ሴት ስታሳድድ አይደል እንዴ የምታመሸው?"

በሁለቱ ጄኔራሎች ፀብ አዳራሹ በመበጥበጡ ስብሰባው ተቋረጠ። በዚያው ሰሞንም፣ "ባጫ ልብ አገኘ!" ተብሎ በሰፊው ተወራለት። እንዲያውም "ባጫ እንዴት እንደዚህ ደፈረ? ምናልባት ከአነግ ጋር ተፃፅፎ እንዳይሆን?" የሚል ትንበያዎች ተከታትለው መጡ።

በሳምንቱ ግን ባጫና ሳሞራ እንደ ቀድሟቸው 'ባጫ!' 'ሳሞራ!' እየተባባሉ ሲገባበዙ ታዩና ትንበያው ሁሉ ፎረሸ። ቀጣዩ ጥያቄ፣ "እንዴት ታረቁ?" የሚል ሆነ።

ምላሹም ወዲያው ተገኘ።

ስብሰባው ከተበተነ በሁዋላ ባጫ ሳሞራ ዘንድ ሄዶ ይቅርታ ጠየቀው። "ተናድጄና ተሳስቼ ነው። አንተስ እንዴት አዛዦች ፊት፣ 'ጫት ስትቅም ትውላለህ' ትለኛለህ?" ብሎ አረጋጋውና ወዲያው ታረቁ። እና መከላከያ ላይ እንዲህ የሚል ተረት አለ፣ "አርብም ገበያ ነው! ቅንጥብጣቢም ስጋ ነው! ባጫም ጄኔራል ነው!"

* * *

ከዚህ ሁሉ ባሻገር ግን ባጫ በሰራዊቱ ውስጥ የሚታወቅበት ልዩ ችሎታው ዳንሰኛነቱ ነው። ማንኛውንም አይነት ዳንስ እንደፈለገው ያስኬደዋል። በተለይ ግን በእንግሊዝኛ ሙዚቃዎች ሲደንስ ወንዱም ሴቱም አፉን ከፍቶ በስሜት ይጮህለታል። ሲውረገረግና ሲንቀጠቀጥ ሰውነቱ ውስጥ አጥንት ያለ እንኳን አይመስልም። እንደ ዘንዶ እየተጥመለመለ፣ እንደ እሳት ነበልባል ሲኾርመለመል ሴቶች በተለይ፣ ስሙን





እየጠሩ ያብዱለታል። በአድናቆት የማይጮህለት የለም።

ይህ የዳንሰኛነቱ ጣጣ በአንድ ሚስት እንዳይረጋ እንቅፋት ሆኖበታል። በሰርግ ካገባቸው በርካታ ሚስቶቹ አንዷ ሳትነግረው ቤቱን ጥላለት የሄደችው በዚሁ የዳንስ ፍቅሩ ነው።

አንድ ጊዜ ከሃረር እንደተመለሰ ወደ ቤቱ ከመሄድ ይልቅ ደሳለኝ ሆቴል አልጋ ይይዛል። ከዚያም ወደ ጭፈራ ክለብ። ሲደንስ ያድራል። ከዚያም አንዷን ይዞ ወደ ደሳለኝ ሆቴል። አደሩ። ለሆቴሉ ሂሳብ ሲከፍል ደረሰኝ በስሙ አሰርቶ ነበር። ያን ያደረገው በደረሰኙ ከመከላከያ ሂሳብ ሊያወራርድ አስቦ ነበር። ዳሩ ምን ያደርጋል? ሚስቱ ደረሰኙንና የህይወት መጠበቂያውን ኪሱ ውስጥ አገኘችበት። ምንም አላለችው። ጥላው ሄደች። እሱም ምንም አላላትም። ሌላ ሚስት አገባ ወይም አስገባ። በተለይ 22 ማዞሪያ የፍቅረአዲስ ነቃጥበብ የዳንስ መድረክ የባጫ ማደሪያ ነበር። ኤክስትሪም ሆቴል የቀን መመሸጊያው ሲሆን፤ እርጎዬዎችና ባጫም አይለያዩም።

ሸው እልም ሸው እልም - ልቤ ወፌ-ይላላ፣
በመስተፋቅር ቀስት - በሮሮ ምህላ፣
እንደ ደመና አክናፍ - እንደ ጮራው ጥላ፣
ሸው እልም ሸው እልም - ሸው እልም ይላላ፣

እነሆ! ደስተኛው የዘመናችን ሰው እንደ ባንዲራ መውለብለቡን ቀጥሎአል። እንደ ነበልባል ይኾርመለመላል። የታጋዮች ግብዣ ሲኖር፣ አለያም የጓዶች ፓርቲ ላይ ባጫ ይደንስ ዘንድ ይለመናል። ለነገሩ እስኪለመንም አይቆይ። ራሱ ወደ መድረኩ ያመራል። ገና ሳይደንስ ታዲያ የአድናቆት ጩኸት አዳራሹን ቀውጢ ያደርገዋል። በተለይም እንደ ማይክል ጃክሰን፣ "አ!" "እ!" "ኡ!" እያለ አውራ ጣቱን ወታደራዊ ቀበቶው ላይ አሳርፎ እንደ እንዝርት ሲሾር ጭብጨባውና አድናቆቱ መጠንና ልክ ያጣል። አንድ ጊዜ አክሱም ሆቴል ግብዣ ላይ የሜጀር ጄኔራልነት ማእረጉን እንደለበሰ የማይክል ጃክሰንን Moon Walking እየደነሰ እንደ ጎማ ሲንሸራተት የመመልከት እድል ገጥሞኛል። ለምን ይዋሻል? እንደ ማንኛውም ጥበብ አፍቃሪ በስሜት ተፈንቅዬ አጨብጭቤለታለሁ። ችሎታው የሚካድ አልነበረም። እነ መለስ ልዩ ፓርቲ እያዘጋጁ ያስደንሱታል የሚል ወሬም አለ። ርግጠኛ ግን አይደለሁም...

- 22 -

# ሮሮ እና ይቅርታ

ከጐራው ዘልቄ - እስኪ ልነጋገር፣
ካለሰው ቢወዱት - ምን ያደርጋል አገር?
ህንፃ መች ሆነና - የድንጋይ ክምር፣
መንገድ መች ሆነና - የድንጋይ አጥር፣
ህንፃው ምን ቢረዝም - ምን ቢፀዳ ቤቱ፣
መንገዱ ቢሰፋ - ቢንጣለል አስፋልቱ፣
ሰው ሰው ካልሸተተ - ምንድነው ውበቱ?
የኔ ውብ ከተማ - የኔ ውብ አገር፣
የሰው ልጅ ልብ ነው፣
የሌለው ዳርቻ - የሌለው ድንበር፣

(ግጥም - በአሉ ግርማ)

አንድ ጊዜ ጅማ ሰነበትኩና ሮሮ መገርሳ የሚባል ሰው ተዋወቅሁ። የቡና እርሻ የሚያለማ ሃብታም ገበሬ ነበር። ወደ ቡና ጫካው ወሰደኝና አስጐበኘኝ። አማርኛ ማንበቡንም መፃፉንም በመጠኑ ያውቃል። ቁቤ አይችልም። በመምህርነት ሙያ የሚሰራ ወንድ ልጁ *"የቡርቃ ዝምታ"*ን አንብቦ ታሪኩን አጫውቶት ነበር። እሱም አለፍ አለፍ እያለ አንብቦታል። በመሆኑም ክቡር እንግዳው አደረገኝና የቡና ጫካውን ወስዶ አስጐበኘኝ፣

"አንተ እንዳልከው" አለኝ በጫካው ውስጥ እየተጓዝን ሳለ፣ "ጠላት የሆነብን ይህ የተፈጥሮ ሃብታችን ነው። አንዳችም





ሃብት ባይኖረን ጭቆናው እንዲህ ባልበረታብን ነበር። ትግላችንም ባልተራዘመ..."

ሮሮ መገርሳ ከአንድ እንጆሪ የመሰለ የቡና ዛፍ ስር ይዞኝ ቁጭ አለ። በትካዜም እንዲህ አለኝ፣

"ጠባቦች እያሉ ይዘልፉናል። ኦሮሞ በታሪኩ ጠባብ ሆኖ አያውቅም። እኛ ያመፅነው በደል በዝቶብን ነው። ገዢዎቹ ነፃነታችንንም ሆነ መብታችንን ሊቀበሉት አልቻሉም። የመብታችን ተጠቃሚ ሊያደርጉን አልፈቀዱም። እኛ ይህን ሃብት ብቻችንን እንብላ ያልንበት አንድም ዘመን የለም። ብቻችሁን አትብሉ በጋራ እንጠቀምበት ነው የዘመናት ፀባችን። በመሰረቱ ባህላችንን ያየህ እንደሆነም የኦሮሞ ህዝብ በቀላል ብሶት የሚያምፅ ህዝብ አይደለም።"

ምላሽ ስላልሰጠሁት እንዲህ ሲል ጠየቀኝ፣

"ሮሮ ማለት ትርጉሙን ታውቃለህ?'

"እሮሮ ማለት ብሶት መሆኑን አውቃለሁ" አልኩ።

"ልክ ነህ!' አለ። አያያዘናም እንዲህ አለኝ፣"...አባቴ ያጫወተኝን ልንገርህ። መገርሳ ሮሮ ይባላል። እኔን መልሶ 'ሮሮ' ሲል ጠራኝ። እንዳልከው ሮሮ ማለት 'በደል' ወይም 'ብሶት' ማለት ነው፡። ቃሉ ግን ተራ በደልና ተራ ብሶትን የሚወክል ቃል አይደለም። ሰፊ ትርጉም ያዘለ ነው። አማሮች፣ 'እሮሮ' ይላሉ። ከኛ ነው ቃሉን የወሰዱት። 'ሮሮ' ትንሽ ብሶት አይደለም። 'ሮሮ' የምንለው 'ብሶት' ደረጃው በጣም ከፍ ያለ ነው። የተጠራቀመና የፈነዳ ብሶት ነው። 'ሮሮ' ላይ የደረሰ ይቅርታ አያዳርግም። 'ሮሮ' ከይቅርታ በላይ ነው። የሰው ልጅ በደሉ ከይቅርታ በላይ ሲሆንበት፣ ይሞታል ወይም ይገድላል።

በምሳሌ ባስረዳህ ይሻላል!

አንድ ጐረቤትህ በገባህ በወጣህ ቁጥር በአሽሙር ይሰድብሃል። ክብርህን የሚነካ ስድብ ይሰድብሃል። እሱ 'ሮሮ' አይደለም። ስድቡ አልበቃው ብሎ ጠብቆ በዱላ ይመታሃል። ይህም 'ሮሮ' አይደለም። ልትታገሰው ወይም በሽማግሌ እርቅ ሊመጣ ይችላል። ሲመታህ ከይቅርታ በላይ አይደለምና 'ሮሮ' አይሆንም። ይቅር ካላልከውም አንተ ባለጌ ነህ። ስድቦህና መትቶህ ይቅርታ ቢጠይቅህና አንተ ይቅርታውን ባትቀበል በደል የፈፀምከው አንተ ነህ ማለት ይሆናል። በመቀጠል ያ ጐረቤትህ ወንድምህን ይገድልብሃል። ወንድምህን በመግደሉ

ሮሮ ደረጃ ላይ አትደርስም። ወደ ፍርድ ቤት መሄድ አለብህ። ፍርድ ቤት ሄደህ ታመለክትና ዳኛ ጉዳዩን ከተመለከተ በሁዋላ ባንተ ላይ ይፈርድና ገዳዩን ወንጀለኛ በነፃ ይለቀዋል።

ይሄ ሮሮ ነው!!

ከዚህ በሁዋላ ትእግስት የለም። እርቅ የለም። ከዚህ በሁዋላ ሮሮ ብቻ ነው ያለው። ሮሮ የመጨረሻ አመፅ ነው። ሮሮ የመጨረሻ ቁጣ ነው። ከዚህ በሁዋላ አንተ ወደ ይቅርታ ልትመጣ አትችልም።

ትገድላለህ ወይም ትሞታለህ።

ይህን ካላደረግህ ደግሞ አንተ የአባትህ ልጅ አይደለህም። ሰውም አይደለህም..."

"ሮሮ" እና "ይቅርታ" የሚሉት ቃላት ለስምንት አመታት ማስታወሻ ደብተሬ ላይ ተፅፈው ተቀምጠዋል። በሁለቱ ቃላት መካከል ያለውን ይዘት በእኛ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ስመዝነው ኖሬያለሁ። በኢትዮጵያ ህዝብ ውስጥ በፖለቲካ ቡድኖችና ብሄሮች መካከል ያለው ግንኙነት ሮሮ ነው ወይስ አይደለም? ሮሮ ከሆነ እንዴት ወደ ሮሮ ደረጃ ሊደርስ ቻለ?

በአፄ ዮሃንስ ዘመን የጐጃም ሰዎች ብሶት ሮሮ ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር። አፄ ዮሃንስ አክራሪ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይ ተብለው ይታወቃሉ። በ1880 ከንጉስ ተክለሃይማኖት ጋር ለመዋጋት ጐጃም በገቡ ጊዜ ግን ልክ ግራኝ አህመድ ይፈፅም እንደነበረው ጉዛምን እና ማቻከል ላይ አብያተ ክርስትያናትን አቃጥለው ታቦት ሰባብረዋል። ጳጳሱ አቡነ ሉቃስ፣ በዚህ ድርጊት ክፉኛ በማዘናቸው፣

"ደርቡሽን አጠፋለሁ ብዬ መጣሁ ያልከው፣ ለጎጃም አንተ ደርቡሽ ሆንክበት" ሲሉ ቅሬታቸውን ለንጉሱ ገልፀው ነበር።

የጎጃም ህዝብ ታቦቱ ከመቅደስ ወጥቶ እየተሰባበረ ሜዳ ላይ ሲወረወር ባይኑ በማየቱ ሮሮ ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር። አፄ ዮሃንስ በደርቡሽ ሲገደሉም የጐጃም ህዝብ እልልታ ወሰን አልነበረውም። ደርቡሽ ጎንደር ከተማን ያቃጠለ፣ ካህናትና መነኮሳትን ያረደ ሃይል ነበር። የጎጃም አዝማሪዎች ግን ደርቡሽ አፄ ዮሃንስን ስለገደለ ብቻ ተደስተው እንዲህ ሲሉ አዚመውለታል፣





በእጃችን ሳይጠጣ - በእጃችን ሳይበላ፣
ደም መላሽ ሆነን - መሃመድ አብደላ፣
ዘሩን ይባርክለት - የሚያምንበት አላ፣

በተመሳሳይ በአፄ ምኒልክ ዘመን የአርሲዎችና ሃረሪዎች ብሶት "ሮሮ" ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር። አንድ የአርሲ ሰው በማንኛውም የአስተዳደር መለኪያ ከአፄ ምኒልክ ይልቅ ይማም አህመድ ግራኝን ሊመርጥ ይችላል። ጣይቱና ምኒልክ አዲስአበባን እንደቀረቀሩት ሁሉ ጎንደርን ያቆሙትም ግራኝ አህመድ ናቸው። አህመድ ግራኝ ኢትዮጵያን ለ15 አመታት ሲገዙ ለክርስትያኖች መልካም አልነበሩም። አርሲ እና ባሌ ግን ለይማም አህመድ በጎ ትዝታ አላቸው። በመሆኑም የአፄ ምኒልክ ዘመን ለኦሮሞዎች የሮሮ ዘመን ነበር። የግራኝ አህመድ ዘመን በአንፃሩ ለመላ ክርስትያኖች ዘመነ ሮሮ ነበር።

ዛሬ፣ "ኢትዮጵያውያን በአንድነት መኖር አለብን" ስንል የሁሉም ወገን ፍላጎት ካልተጠበቀ ሮሮ አለመቀጠሉ ዋስትና አይኖረውም። በረከት ስምኦን ጎንደር ላይ የግራኝ አህመድን ሃውልት የማቆም ፍላጎት ነበረው። ግራኝ ከተቀበረበት ዛንዛራ ላይም የመሰረት ድንጋዩ ተተክሎ ነበር። የአካባቢው ህዝብ በዚህ ክፉኛ ተቆጥቶ የሃውልቱን የመሰረት ድንጋይ በፈንጂ አፈራርሶታል። በርግጥ ግራኝ አህመድ ሃውልት ያስፈልጋቸዋል ከተባለ፣ ሃረር ከተማ ላይ እንጂ ጎንደር ላይ ሊሆን ባልተገባው። ይህን መሰል ርምጃዎች የመቻቻል ልማዳችንን ያዳብሩታል። ሚዛናዊ ግንኙነታችንን ያሻሽሉታል። አብሮ የመኖር ባህላችንንም ያጠናክረዋል።

የአጤ ምኒልክ ዘመን ለትግራይ ህዝብ የሮሮ ዘመን አልነበረም። የትግራይ ባላባቶች፣ "ከአፄ ዮሃንስ ህልፈት በሁዋላ በራሳችን ድክመት ስልጣን ወደ ሸዋ መንግስት ተላለፈ" ብለው ይቆጫሉ። አጤ ምኒልክንም "ከሃዲ" ይሏቸዋል። በኢትዮጵያ የንጉሳውያን ታሪክ ዘመን ውስጥ ግን መከዳዳት ያልነበረበት አንዳችም ዘመን አልነበረም። አብዛኞቹ ንጉሶች የራሳቸውን ስልጣን ለማጠናከር ከውጭ ሃይሎች ርዳታ ይጠይቁ ነበር። ይህ መካካድ አይደለም። አጤ ዮሃንስ እንግሊዞችን መቅደላ ድረስ እየመሩ በመምጣት አጤ ቴዎድሮስ ላይ የመጨረሻውን የመቃብር ምስማር መትተዋል። በተመሳሳይ ንጉስ ምኒልክ አጤ ዮሃንስን ለማዳከም ከኢጣልያውያንና ከግብፆች ጋር አሲረዋል።

ከማሴርም ባሻገር ደርቡሾችን የሚያጠናክር ተንኮል ፈፅመዋል። ህወሃት በተመሳሳይ ደርግን ለመጣል የዚያድ ባሬን ርዳታ አግኝቶአል። "ግንቦት 7" የተባለው ድርጅትም ወያኔን ለመጣል ከኤርትራ እርዳታ ሊያገኝ ይችላል። ይህን መሰል ታሪኮችን፣ "ክህደት" ካልናቸው የክህደት ትርጉም ሚዛኑን ይስታል። ይህ ሮሮም ክህደትም አይደለም።

የትግራይና የወሎ ህዝብ በ1966 ረሃብ በንጉሱ ችላ በመባሉ ግን ሮሮ ደረጃ ላይ ለመድረስ በቅቶ ነበር። የፖለቲካ ሽኩቻዎች ሮሮ አይደሉም። ከይቅርታ በላይም አይደሉም። ህገመንግስትን መጣስ በጥቅሉ ወንጀል ነው። በዚህ በኛ ዘመን የኢትዮጵያን ህገ መንግስት መጣስ ግን ወንጀል አይደለም። ምክንያቱም ህገመንግስቱ የህዝብ ንብረት አይደለም። ወያኔ ራሱ ህገወጡን ህገመንግስት ሲጥሰው ስለሚውል ህገ መንግስቱን መጣስ የሚያስጠይቅ ከሆን በቅድሚያ ፍርድ ቤት የሚቀርቡት መለስ ዜናዊና ሳሞራ የኑስ ናቸው። ስለዚህ በመሰረቱ ህገመንግስት የሚባል ነገር የለንም።

ሃረሪዎች ለዘመናት በዘራቸው ምክንያት ግፍ ሲፈፀምባቸው ነበር። ዛሬ ደግሞ ህገመንግስቱ መብታቸውን እንዳጎናፀፋቸው ይነገረናል። ይህ የተሟላ እውነት ይሆን?

በ1992 ጁገል ውስጥ ነዋሪ ለሆኑ፣ አመቱላ ሻሽ አቦኝ ለተባሉ በእድሜ የገፉ ሴት እንዲህ የሚል ጥያቄ አቅርቤ ነበር፣

"በኢህአዴግ ዘመን የሃረሪ ህልም እውን ሆኖአል?"

ፈገግ ብለው እንዲህ ሲሉ መለሱ፣

"ነፃነታችን ተገኘ ብለን ተደስተን ነበር። ፍርሃት ግን አለብን። ጎረቤቶቻችን ኦሮሞዎች ቂም ይዘውብናል። አዳዲስ ጠላቶች እያፈራን ነው"

ወያኔ ሆን ብሎ የህዝቡን ግንኙነት ሮሮ ደረጃ ላይ ለማድረስ ጥረት እያደረገ ነው። እንግሊዞች ናይጄሪያን በሚገዙበት ዘመን የኢቦ ጐሳዎችን በተለየ ያቀርቡ እንደነበረው፣ ወያኔ ሃረሪዎችን በዚያ መልኩ ሊጠቀምባቸው እየሞከረ ነው። ሃረሪዎችን ከኦሮሞዎች ጋር ማናከስ የመጀመሪያው ርምጃ ነበር። ኦሮሞዎች ሃረሪዎች ላይ ቂም ቋጥረዋል። ኦሮሞዎች ምን እንደሚሏቸው አመቱላ ሻሽ አቦኝ አጫውተውኛል፣

"ዛሬ ወያኔን ተማምናችሁ በኛ ላይ ነግሳችሁዋል። ነገ ወያኔ ሲባረር በአንሶላ ጠቅልሎ ይዞአችሁ የሚሄድ ከሆን





እናያለን"

ይህን ዛቻ ወያኔ ይፈልገዋል።

ሃረሪዎችን ጠቅልሎ ጉያው ውስጥ በማስገባት መጠቀሚያ ሊያደርጋቸው እየሞከረ ነው። የቅንጅት መሪዎች ፍርድ ቤት ሲቀርቡ ወያኔ የሃረሪ ተወላጅ የሆኑ የህግ ሰዎችን ብቻ ማመን ቻለ። በተመሳሳይ በምርጫ 97 ህገወጥ ድርጊት ለመፈፀም ከማል በድሪን ተጠቀሙበት። ይህ የሚያስከትለው አደጋ አለው። ከሚገባው በላይ ሊያስከፍላቸው ይችላል።

ባለንበት ዘመን በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ለኢትዮጵያ አንድነት ጠንቅ ሊሆን ይችላል ተብሎ ከሚታሰበው መካከል አንዱ የኦሮምያ የፖለቲካ ጥያቄ ጉዳይ ነው። የኦሮሞ ተቃዋሚዎችን በጠባብነት የመፈረጅ ሰፊ ዝንባሌም አለ። በተቃራኒው አማራውን፣ "ከአማራነቱ ይልቅ በኢትዮጵያዊነት የሚያምን ጠባብ ያልሆነ ዜጋ" አድርጐ የማየት የተሳሳተ ዝንባሌ አለ።

ሮሮ ጉርሜሳ እንዳሉት ኦሮሞ በተፈጥሮው ጠባብ አይደለም። ኦሮሞ ወደ ጠባብነት ተገፍቶ ከሆነ ሮሮ ደረጃ ላይ ይደርስ ዘንድ አንድ በደል ደርሶበታል ማለት ነው።

የኦሮሞ ህዝብ ወደ ሮሮ ደረጃ እንዲደረስ ያደረጉት በርካታ ምክንያቶች ይኖራሉ። ከነዚህ ህልቆ መሳፍርት ምክንያቶች አንዷት አብነት ብቻ እንኳ ማየት ለጉዳዩ ሚዛናዊ እይታ ይኖረን ዘንድ ያግዘናል። የጄኔራል ታደሰ ብሩ ጉዳይ ለዚህ አባባሌ ሁነኛ አስረጅ መሆን የሚችል ይመስለኛል።

በ1956 ሰኔ ወር ላይ አክሊሉ ሃብተወልድ የተባሉት የወቅቱ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ጄኔራል ታደሰ ብሩን ከቤታቸው ራት ጋብዘዋቸው ወግ ይዘው ነበር። በጨዋታ መሃል ታዲያ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደዋዛ አንድ አሳብ ጣል ያደርጋሉ፣

"ታደሰ! አንተ የፊደል ሰራዊትን መምራት ከጀመርክ ወዲህ ተማሩ! ተማሩ! ማለትን አዘውትረሃል። ተማሩ ማለት ጥሩ ነው። ግን ማንን ማስተማር እንዳለብን ማወቅ ይኖርብሃል። እኛ (አማሮች) ኦሮሞውን ቢያንስ ቢያንስ ባንድ ሴንቸሪ ወደሁዋላ ይዘን ነው በመምራት ላይ ያለነው። ይህንን ህዝብ አስተምረዋለሁ ብትል ውቅያኖስ ነው። ያጥለቀልቅሃል" በማለት

ይናገራሉ።

ጀኔራል ታደሰ ብሩ በተቀመጡበት ደነዘዙ።

ከፊት ለፊታቸው ጠረጴዛው ላይ የተቀዳላቸውን ዊስኪ አትኩረው እየተመለከቱ ነበር። ደም መስሎ ታያቸው። ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግር በሁዋላ ጀኔራሉ እዚያ ቤት መቆየት አልቻሉም። ስሜታቸው እንዳይታወቅባቸው እየተጠነቀቁም እንዲህ አሉ፣

"ዊስኪ ተቀዳልኝ እንዴ? እኔ'ኮ መድሃኒት እየወሰድኩ ነው። አልጠጣም" በማለት ጠቅላይ ሚኒስትሩን ተሰናብተው ወጡ።

ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሃብተወልድ አንድ ያላወቁት ነገር ነበር። ጀኔራል ታደሰ መንዜ-አማራ መስለዋቸው ነበር። አማራ ናቸው ብለው ስላሰቡም የልባቸውን አሳብ አጫወቷቸው። በአጋጣሚ ግን ጀኔራሉ የሰላሌ ኦሮሞ ነበሩ። የጀኔራሉ መዝገብ ላይ 'ዘር' በሚለው ቦታ 'መንዜ' ተብሎ መሞላቱን በማየት ነበር ጠቅላይ ሚኒስትሩ አንድ ከባድ ምስጢር ያወጡት። የሆነው ሆኖ አንድን ወንዝ ሁለት ጊዜ መሻገር አይቻልም። ከዚያች ደቂቃ ጀምሮ ጀኔራል ታደሰ ብሩ ሸፍተው ነበር። ከጠቅላይ ሚኒስትሩ አንደበት የወጣችው ያቺ ዘረኛ ቃል ወደ ሚሊዮናት ኦሮሞዎች ተዘርታ ነበር።

ጀኔራል ታደሰ ብሩ ወደ ቤታቸው በመጓዝ ላይ ሳሉ ሁሉን ወደሁዋላ ተመልሰው አሰላስለውታል። እየተሰማቸው ያለውን ሁሉም መርምረውታል ...

ቀደም ሲል ሜጫና ቱለማ የተባለው ማህበር አባል ይሆኑ ዘንድ ሲጠየቁ ታደሰ ብሩ የሰጡት ምላሽ የሚከተለውን ነበር፣

"እኔ ተመልሼ የጐሳ ፖለቲካ አላካሂድም። 'አላማችን ህዝቡን ለማስተማር ነው' ላላችሁትም በፊደል ሰራዊት ኰሚቴ ሊቀመንበርነቴ አማካይነት ድንቁርና ያጠቃው ወገኔን ለማስተማር የሚቻለኝን አደርጋለሁ። ደግሞም ልጆቼ በእናታቸው አማራ መሆናቸውን አትርሱ። እነርሱን ከፊላቸው ነው የምትሉኝ?"

ጀኔራል ታደሰ ብሩ ኦሮምኛ ቋንቋ ይሰማሉ እንጂ መናገር የሚችሉ አልነበሩም። 'ኢትዮጵያዊነት' የሚል ጠንካራ ስሜት ነበራቸው። ከዚያች እለት በሁዋላ ግን ጀኔራሉ





'ኢትዮጵያዊነት' የሚለውን ጠንካራ ስሜታቸውን ልባቸው ውስጥ ፈልገው አጡት። በቀጥታ ለኦሮሞ ህዝብ አርነት ትግል ጀመሩ።

ይህ ሮሮ ነበር።

ከዚህ በሁዋላ ጀኔራሉ ይቅርታ ለማድረግ የሚቻላቸው አልነበረም። የጃንሆይ ስርአት የኦሮሞ ህዝብ እንዳይማር በመንግስት ደረጃ እየሰራ መሆኑን ከጠቅላይ ሚኒስትሩ አንደበት ማረጋገጥ ቻሉ። ይህ ከይቅርታ በላይ ነበር። በዚህ ምክንያት ጀኔራሉ እስከ እለተሞታቸው ለኦሮሞ ህዝብ ነፃ መውጣት ተዋጉ። እየተዋጉም ሞቱ። ዛሬ ያ ሮሮ በእያንዳንዱ ኦሮሞ ልብ ውስጥ አለ። ጀኔራል ታደሰ በ1967 እስከተገደሉበት እለት ድረስም፣

"እናት ለልጅዋ እንዲቃጠልባት እሳት እንደአለማቀበሏ መጠን፣ የወገኖቼን መደንቆርና መደህየት የሚፈልግ ሰው የለም" እያሉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው አስተምረዋል።

"የነፃነትን ዋጋ! የመብትን ትርጉም አውቆ ይህ ቀረብኝ ይህ ጐደለብኝ ለማለት የሚችል የተማረ ህዝብ ብቻ ነው" ሲሉ ወጣቶችና ገበሬዎችን እየሰበሰቡ ተናግረዋል።

የጐሳ ፖለቲካን ያልተጠየፉትን ያህል፣ በከፍተኛ የጥላቻና የቁጭት ስሜት የኦሮሞ ብሄር መብት ከጠመንጃ አፈሙዝ ብቻ የሚገኝ የትግል ውጤት መሆኑን አምነው ወደ ትጥቅ ትግል ገብተዋል። ሃይለስላሴን ለማስወገድም ለመግደልም ሞክረው ነበር። ስላልተሳካላቸው ራሳቸው ሞተዋል። ሮሮ ደረጃ ላይ የደረሰ ግለሰብም ሆነ ህዝብ ሁለት ምርጫዎች ብቻ ነው ያሉት። መግደል! ካልሆነ መሞት!

አክሊሉ ሃብተወልድ የዚህ አመለካከት ብቸኛ ተሸካሚ ናቸው ሊባሉ አይችሉም። ስርአቱ ራሱ ጠባብና ዘረኛ ነበር። ዘረኛነት ዘረኛነትን ብቻ ነው የሚወልደው። ዛሬ ያለው የፖለቲካ እውነታ የተዘራው ዘር ቡቃያ ነው። ቡቃያው አድጎ እሾክ አውጥቶአል። ስለዚህ ማንም እንዳሻው እየሄደ ሊሸመጥጠው አይችልም።

የኦሮሞ ህዝብ ላይ እንደቀድሞው በአሉታዊ ሁኔታ መቀለድ ጨርሶ ሞቶአል ባይባልም፣ ከምድራችን እየተወገደ መሄዱ አያጠያይቅም። እየተወገደ የሄደው የአመለካከት ለውጥ ስለመጣ ብቻ ላይሆን ይችላል። በአጠቃላይ የህብረተሰብ ንቃት

ህሊና መዳበርን የሚጠቁም ሊሆን ይችላል።

የመገንጠል ጥያቄ ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል በኤርትራ ጉዳይ ታይቶአል። የመገንጠልን አጀንዳ ማንሳት ከመቅለሉ የተነሳም ጐጃምን የመገንጠል አሳብ የነበራቸው ነበሩ። 'አማራው የራሱን አገር ይመስርት' ማለት የጀመሩ አማሮችም ተሰምተዋል። ይህ አሳብ እየዳበረ ሄዶ የአማራ ተገንጣዮች ግንባር የሚመሰረትበት ዘመን ሊመጣ እንደሚችል ማሰብ የዋህነት አይደለም። ሮሮ ደረጃ ላይ የደረሰ ህዝብ ሊወስደው የሚችለውን ርምጃ ቀደም ብሎ መተንበይ ሊቸግር ይችላል።

አንድ ህዝብ ሮሮ ደረጃ ላይ ሲደርስ መገንጠልን እንደ አማራጭ ሊያነሳ ይችላል። የኤርትራ ህዝብ ሮሮ ላይ ባይደርስ ኖሮ ዛሬ የምናየው የጂኦግራፊ ሁኔታ የመምጣት እድሉ ጠባብ እንደነበር በወቅቱ የክፍለሃገሩ ባለስልጣን የነበረው ዳዊት ወልደጊዮርጊስ ደጋግሞ ገልፆልናል።

ዳዊት እንዲህ አስፍሮአል፣

"...ኢትዮጵያዊ ነኝ፣ አንድነትን እፈልጋለሁኝ ብሎ ያመነውን (ኤርትራዊ) ህዝብ እየገፋን፣ እየዘረፍን፣ እየገደልን፣ እያሰርን ሳይወድ በግድ እንዲሸፍት አደረግነው። ኢትዮጵያዊነት ምን ትርጉም አለው? ኢትዮጵያዊነት ከመብትና ከነፃነት ጋር ካልተያያዘ ኢትዮጵያዊ ነኝ ማለቱ ምን ጥቅም አለው? በህብረት እዝ ጊዜ ከጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን ጋር ተሰልፈው የነበሩ እነ ኮሎኔል ነጋሽ ዱባለ፣ ጄኔራል ስዩም መኮንን፣ ኮሎኔል ዘነበ፣ አንድ ጊዜ የፒያኖ ዋየር ኦፕሬሽን በሚል ስያሜ ስንቱን ህዝብ በአስመራ ከተማ አንቀው ሲገድሉ፣ በተለያዩ ወቅቶች ሴቱን፣ ወንዱን፣ ልጁን፣ እናቶችና አባቶችን ሳይቀር በግፍ እያሰሩ፣ እየገደሉ፣ በየቦታው ሬሳቸው እየተጣለ፣ በተለያዩ ጊዜያትም ከተማዎች ውስጥ ያሉ የግል፣ የመንግስትና የድርጅት ንብረቶች በግል ሰዎች እየተዘረፉ ወደ አዲሳባ ሲጓዝ፣ ጉቦና ዝርፊያ የየእለቱ ስራ ሲሆን፣ እንዴት አድርጐ ህዝቡ ይህንን ይቀበል? ህዝቡ ሸፈተ! ለምን አይሸፍትም? ምን አይነት ሃይል ነው እንደዚህ ያለ በደል የደረሰበትን ህዝብ ኢትዮጵያዊ ስሜት እንዲኖረው ሊያደርግ የሚችለው?"

የኤርትራ ህዝብ ሮሮ ላይ በመድረሱ ነፃ አውጪ በረኸኞቹን ሙሉ በሙሉ ደገፈና ነፃነቱን አወጀ። 'ነፃነት





ይሻለዋል ወይስ አንድነት?' የሚለውን ጥያቄ እዚህ አናነሳም። ዳዊት የገለፀልንን ሁኔታ መሸከም ያልቻለው ግን ሮሮ ላይ ስለደረሰ ነው። ሮሮ ደረጃ ላይ የደረሰን ህዝብ ምንም አይነት ሃይል ሊያቆመው አይችልም። ግለሰብም ሆነ ቡድን፣ ትንሽም ሆነ ትልቅ ህዝብ ሮሮ ደረጃ ላይ ከደረሰ ቢያንስ መሞት አያቅተውም። ለመሞት የወሰነ ደግሞ ከመሞቱ በፊት መግደል ይችላል።

ሮሮ ደረጃ ላይ የደረሰ ቡድን ቀርቶ ግለሰብም አደገኛ ነው። ሃረሪዎች "ኢትዮጵያ" የሚባለውን ቃል ሳያውቁ 400 አመታት ያህል በራሳቸው አሚር እየተዳደሩ የኖሩ ጠንካራ ህዝብ ናቸው። 42ኛው አሚር አብዱላሂ ላይ ግን ነፃነታቸው አከተመ። ነፃነታቸው ያበቃው ፈልገው ሳይሆን ተገደው ነው። 'ነፃነታቸው ይሻላቸው ነበር ወይስ ከኢትዮጵያ መቀላቀላቸው?' የሚለው አሁን አጀንዳችን አይደለም። ጥያቄውን የማናነሳው ሃረሪዎች ብዛታቸው ትንሽ ስለሆነ 'ምን ያመጣሉ?' በሚል ንቀት አይደለም። ምን ያመጣል? ተብሎ ችላ የሚባል ህዝብ የለም። እንኳን ህዝብ ግለሰብ ብቻውን ሃገር ሊያፈራርስ ይችላል። ዚያድ ባሬ ኢትዮጵያን እንዲወር አሳብ ያቀረቡትና የሶማሊያን ሰራዊት እየመሩ ድሬዳዋ የደረሱት ሃረሪዎች ናቸው። በወቅቱ ኢልያስ የተባለው የሶማሊያ የደህንነት ሹም ጁገል ተወልዶ ያደገ አደሬ ነበር። የሶማሊያን ወታደሮች እየመሩ ጅጅጋን የተቆጣጠሩት ኮሎኔሎች ሃረር ተወልደው ያደጉ፣ ካይሮ ላይ ወታደራዊ ሳይንስን ያጠኑ ሃረሪዎች ነበሩ።

አንድ ሰው እና አንድ ጠመንጃ በፍፁም አይናቁም። ከእለታት አንድ ቀን አንድ ነገር ማድረግ ይችላሉ። ይስሃቅ ራቢን የተባሉትን የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስተር የገደለው አንድ መናኛ ወጣት፣ በአንድ መናኛ ሽጉጥ ነበር። ከዚያ በሁዋላ የእኒያን አስፈላጊ አዛውንት ህይወት መልሶ ማምጣት ሳይቻል ቀርቶአል።

በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ የተገጣጠሙ አጋጣሚዎች ምንጊዜም አሉ። 99 ቀናት መጠንቀቅ ትችል ይሆናል። ቀሪዋ አንድ ቀን ግን ትጫወትብሃለች። ሃረሪዎች፣ 'ምንም ሊያደርጉ አይችሉም' ከሚባሉት ዜጎች አንዱ ነበሩ። በርግጥም 99 ቀናት አንዳችም ማድረግ አልቻሉም ነበር። በቀሪዋ አንዲት ቀን ግን ዚያድባሬን ሊጠቀሙበት ቻሉ። ያለሙት ባይሳካም አንድ

ትምህርት ማስተላለፍ ግን ችለዋል። መብታቸው እስካልተከበረ ድረስም በ99ኛዋ ቀን አንድ ነገር ማድረግ ይችላሉ። ስለዚህ አንድ ችግር መፍጠር የማይችል ህዝብም ሆነ ግለሰብ የለም። እኔ በግሌ ግለሰብ ነኝ። በአንድ ወቅት ወያኔዎች፣ "ምን ያመጣል?" ብለው ተመፃድቀው ሊሆን ይችላል። አሁን ያቺን ቃል አይደግሟትም። በተመሳሳይ በርካታ የተናቁ ሆኖም አንድ ነገር ማድረግ የሚችሉ ግለሰቦች በእያንዳንዱ ግዙፍ ቡድን ጉያ ውስጥ ምንጊዜም አሉ። ወደፊትም ይኖራሉ። ነገም ሌላ ቀን ነው...

በአብዛኛው የመሃል አገር ሰዎችና የሰሜን ምእራብ ዜጎች፣ "ኢትዮጵያዊነት" በሚል ጃንጥላ ስር መሰባሰብ እንሻለን። በዚህ ፍላጎት የሚጎዱ ይኖሩ ይሆን? ካሉ ጉዳታቸው ምንድነው? መፍትሄውስ? ሮሮ እንዳይከተል ተገቢ ጥያቄዎች መነሳትና ምላሽ ማግኘት አለባቸው።

እኔ አማርኛ ተናጋሪና የአማርኛ ቋንቋ ደራሲ በመሆኔ አማርኛ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን፣ የአለም ቋንቋ ጭምር እንዲሆን እመኛለሁ። ከመመኘት አልፌ ለአማርኛ ቋንቋ እድገት እሰራለሁ። ይህ ሃጢአት አይደለም። ሃጢአት ወይም ሮሮ የሚሆነው ለአማርኛ እድገት ስል ሌሎች ቋንቋዎችን ማፈን ከጀመርኩ ነው። አማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ ትምህርት ቤቶች ኤርትራ ውስጥ እንዲከፈቱ እኔ ፍላጎት አለኝ። ይህ ለትግርኛና ለብሌን፣ ለትግረና ለኩናማ ቋንቋዎች የስነፅሁፍ እድገት አስተዋፅኦ እስካደረገ ድረስ አማርኛ ተቀባይነት ይኖረዋል። ሌላውን የመግደል ስውር አላማ ከያዘ ግን ጨዋታው መልኩን ይቀይራል። ኦሮምኛን የመግደል አላማ ስለነበረው በኦሮሞዎች ዘንድ አማርኛ እንደ ጠላት ቋንቋ ይታያል። በኦነግ ሰራዊት ውስጥ አንዲት የአማርኛ ቃል በንግግሩ መካከል የደባለቀ ታጋይ አስቂኝ ቅጣት ይቀጣ ነበር። ቅጣቱ Doofaa የሚል ቃል ያለበት ባጅ (ታርጋ) ደረቱ ላይ ተለጥፎበት ቀኑን ሙሉ ሰራዊቱ ውስጥ መደበኛ ስራውን ሲሰራ ይውላል። "ዶፋ" ጅላጅል ማለት ነው። ኦነግ በአማርኛ ቋንቋ ላይ ያሳደረው መረን የለቀቀና ስሜታዊ ጥላቻ የሮሮ ውጤት ነው።

በአካባቢያችን ጉዳይ ያልተመለሱ ቀጣይ ጥያቄዎች ከጥቂት በላይ ናቸው። የኦሮሞ፣ የኦጋዴን፣ የደቡብና የአማራው ህዝቦች ይቅርታ ወደ ሌላው ሮሮ ደረጃ እንዳይደርሱ ምን





መደረግ አለበት?

መለስ ዜናዊ ወደ ሮሮ በሚያደርስ መንገድ ቀጥቅጦ የመግዛትን ስልት እየተከተለ ነው። ህዝቡም ወደ ሮሮ እያመራ ነው። በዚህ መንገድ በሚደረገው ጉዞ ሮሮ ደረጃ ላይ መድረስ የማይቀር ይሆናል። እስካሁንም ሮሮ ደረጃ ላይ ካልደረስን ሃገሪቱ እድለኛ ናት። ሮሮ ላይ የደረሰ ህዝብ ብቀላ ሊፈፅም ይችላል። በምርጫ 97 ማግስት የሰማነው፣ "ትግሬ ወደ መቀሌ - ንብረት ወደ ቀበሌ!" የሚለው መፈክር ሮሮ ነው። የህዝቡን የሮሮ ደረጃ ይጠቁማል። እዚህ መፈክር ውስጥ "ትግራይ ብትገነጠልም ትገንጠል! ብቻ ከዚህ ይሂዱልን!" የሚል የመረረ ቁጣ አቅፎአል። ይሄ ከይቅርታ በላይ የሄደ ሮሮ ነው። እነ መለስ ካልባነኑ አደገኛ አደጋ ከፊታቸው እየመጣ ነው።

አንዳርጋቸው ፅጌ ሚንአሶታ ላይ ባደረገው ንግግር እንዲህ ሲል ገልፆ ነበር።

*"...በ2005 ሰኔ ወር ላይ ትግርኛ ተናጋሪዎች ብቻ ያሉበት የወያኔ አፋኝ ቡድን አጥር ዘሎ ወደ ግቢያችን ገባ። ግቢው ውስጥ በሚኖሩ ሰዎችና በአባቴ ፊትም አንዱ በዱላ ጆርባዬን መታኝ። ተደባዳቢውን ወጣት፣*

*'ለምን ትመታኛለህ? የጠየቃችሁኝን አላደርግም አላልኩም' ስል ጠየቅሁት። ወጣቱ 15 ሰዎች እየሰሙት፣*

*'ደብድቡት! የሚል ትእዛዝ ተሰጥቶናል' ሲል መለሰ።*

*ዱላው በዚህ አላበቃም። አራተኛ ፖሊስ ጣቢያ ወስደው በትግርኛ እየተነጋገሩ ቀጠቀጡኝ። የራሳቸው ዘር እየቀጠቀጠ የመግዛት መብት እንዳለው፣ ለዚያ መብት ያበቃቸው የተለየ ጀግንነት የተላበሱ መሆናቸውን በድንፋታ እየተናገሩ ነበር ዱላውን የሚያዘንቡብኝ። በደህና ቀን የተማርኳት ትግርኛ ባለጌ ስድባቸውን ለመስማት አስቻለቺኝ። የሰማሁትን ከሰማሁ በሁዋላ ትግርኛ የማልሰማ ቢሆን ደስ ባለኝ ነበር። ሁሉንም ዘር ነበር የሚሳደቡት። በአደባባይ እንዲህ ያለ ዘረኛ ንቀት ይወጣቸዋል ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር። አማራ ብለው የሚጠሩትን ዘር በተለይ፣ እጅግ አስፀያፊ፣ እዚህ ለመድገም የሚቀፍ ስድብ እየተሳደቡ ዱላና ርግጫ አወረዱብኝ። ግማሽ ፊቴን በሰደፍ አፍርሰው ኮማ ውስጥ ጨምረውኝ፣ ጭቃ መሬት ላይ ጥለውኝ ሄዱ። በዘር ጥላቻ የተመሰረተ ብልግና የሞላው ድርጊታቸውን*

*የፈፀሙት ከ700 እስከ 800 የሚሆን እስረኛ ፊት ነው። የደበደቡኝ የቅንጅት ደጋፊ በመሆኔና የኔን ቅስምም ለመስበር ነበር። በድብደባው የተነሳ ስንት ሰአት ወይም ደቂቃ ኮማ ውስጥ እንደቆየሁ አላውቅም። ከኮማ ስወጣ ያገኘሁት ማንነቴ ግን በፊት ከነበረኝ ማንነቴ የተለየ ነበር። ከደብዳቢዎቼ ዘር ጋር ለተገናኘ ማንኛውም ሰው ከፍተኛ ጥላቻና ምሬት ልቤን ሞልቶ አገኘሁት። ከሚደበድቡኝ ስድስት የመለስ ዜናዊ አሽከሮች በላይ የሚሻገር ከሰዎቹ ትግሬነት ጋር የተሳሰረ፣ ለዘራቸው በሙሉ መጥፎ ስሜት እንዲሰማኝ ያደረገ፣ ጥላቻ ሰብእናዬን እንደ አሲድ ሲበላው አገኘሁት። በጣም የሚያስደነግጥ ስሜት ነበር። በግሌ የማውቀውን የትግራይ እናቶች ሩህሩህነት፣ የትግራይ አርሶአደር ለሰው ልጅ ያለውን ፍቅር ከህሊናዬ እና ከልቤ ፍቆ፣ ማንኛውንም ከትግሬነት ጋር የተያያዘ ነገር በጠላሁበት ሁኔታ ውስጥ ሆኜ ራሴን ከሳትሁበት ነቃሁ። ይሄ ነበር ያሳዘነኝና ያበሳጨኝ። እንግዲህ አስቡት፣ እኔ በቅርቡ ስለ ትግራይ ህዝብ ምንነት ብዙ የማውቅ ሰው ነኝ። ከደርግ ጥይት ሰሸሽ ህዝቡ መጠለያ ሆኖኛል። ከወባ፣ ከተስቦ፣ ከረሃብ ተርፌ በህይወት አሰንብቶኛል። እኔ ይህን ማህበረሰብ በአንድ ጨፍልቄ ለዘርማንዘሩ ጥፋት ከተመኘሁ፣ ሌላው የኔ አይነት የሀሊና ወቃሽ የሌለው ተመሳሳይ በደል የሚደርስበት ምን ሊያስብ እንደሚችል ገምቱት። በመለስ ዜናዊ ወታደሮች ቤቱ የተቃጠለው፣ ሚስቱንና ወጣት ሴት ልጁን የተደፈረው፣ የተዘረፈው፣ የተዋረደው፣ በጥቅሉ የዘር ማጥፋት እርምጃ የተወሰደበት መላው የሃገሪቱ ህዝብ ምን ይሰማዋል?"*

አንዳርጋቸው ራሱ እንደገለፀው ትግሬን በጥቅሉ እስከመጥላት በሚያደርስ ደረጃ ላይ ከደረሰ ይሄ የከፋ ሮሮ ነው። የህወሃት ኤሊትና ዘመን አመጣሽ ቱጃሮች ከዚህ አደጋ ከመማር ይልቅ የአዲሳባ ቪላዎቻቸውን እየሸጡ፣ በምትኩ መቀሌ ላይ ቪላ መገንባቱን ተያይዘውታል። "እንደ አፄ ዮሃንስ መሸወድ የለብንም!" የሚል አስተሳሰብ በህወሃት አመራር ዘንድ ዳብሮአል። "እስከተቻለ በስልጣን ላይ መቆየት፣ ካልተቻለ ሌላውን እንደማይታረቅ ለያይቶና አውድሞ ትግራይን መገንጠል" የሚሉ እቅዶቻቸው እስከየት እንደሚያራምዱቸው ለራሳቸውም አያውቁም።





"አማራው በድጋሚ ስልጣን ከያዘ እንደቀድሞው ለረጅም ጊዜ ተቆጣጥሮን ይቆያል" የሚለውን ስጋት ለማስወገድ ከመመካከር የተሻለ መፍትሄ የለውም። የትግራይ ህዝብ "የድህነት ሮሮ" ደረጃ ላይ በመድረሱ ቆርጦ እንደታገለው ሁሉ በተመሳሳይ ሌሎችም 'ከባርነት ሮሮ" ለመውጣት ታግለው ውጤት ላይ ለመድረስ ይቻላቸዋል።

ወገኖቻችን ሆይ!

አትጠራጠሩ!

ነፃነት ፈላጊው ህዝብ ከእለታት አንድ ቀን ይሳካለታል!! በተሳካለት ጊዜ ሊመጣ የሚችለውን የማይፈለግ አደጋ ለማስቀረት የሚቻለው ግን ነገ አይደለም። ዛሬ ብቻ ነው! ዛሬ ብቻ!!

- 23 -

# ቦረና! የስልጣኔ ዋሻ

ባዘቅት ይመሰላል - የሰው ህይወት ጠባይ፣
ጨለማ የሆነ - ስሩ የማይታይ፣
በጥልቀቱ መጠን - ወደ ታች ሲሰምጡ፣
ያላሰቡት ነገር - ይታያል በውስጡ፣

(ግጥም - ከበደ ሚካኤል)

* * *

ነፋሱ ፀጥ አለ - ድምፁን አጠፋና፣
ባህር ዛፉም ቆመ - አደገደገና፣
ስትሰግድ ሳለች - ወደ ምእራብ ፊቷ፣
ተደፍቶ እንዳዘዛት - ፀሃይ ሃይማኖቷ፣
ያን የወርቁን ግምጃ - ምድር ላይ አንጥፋ፣
ሁሉም እያየላት - ማማሩን በይፋ፣

(ግጥም - መንግስቱ ለማ)

አንጋፋው አንትሮፖሎጂስት ነዋሪነታቸው አስመራ የተባለችው ከተማ ላይ መሆኑን እንደሰማሁ ጊዜ ሳላጠፋ ወዲያውኑ ነበር ፍለጋዬን የጀመርኩት። በጠቋሚ ቢሮአቸው ስደርስ ግን ፀሃፊያቸውን ብቻ አገኘሁዋት።

አዳራሽ ትባላለች።

ቡና ጋበዘችኝና ወያኔን እንደ ሽንኩርት እየገሸለጥን





በሃሜት ቡጭቅጭቁን አወጣነው።

ወያኔ ሃሜቱ በዝቶበት፣ "ኸረ ባካችሁ በቃኝ! ማሩኝ! አጥፍቼያለሁ!" እስከሚል አፈርአባቱን አስቅመነው ስናበቃ ወደ መጣሁበት ጉዳይ ዘለቅሁ።

ፕሮፌሰር አስመሮም ለገሰን ማግኘት እንደምፈልግ በመግለፅ ቀጠሮ እንዲያዝልኝ ጠየቅሁ። አዳራሽ ጠረጴዛዋ ላይ ከነበረ ቢጫ ቁራጭ ወረቀት ላይ ማስታወሻ ያዘች።

እና እንዲህ ስትል ጠየቀችኝ፣

"ስልክ አለህ?"

ያረፍኩበትን የሳቫና ሆቴል ቁጥር ሰጠሁዋት።

በአምስተኛው ቀን ደውላ እንዲህ አለችኝ፣

"ፕሮፌሰሩ ሊያገኙህ ፈቃደኛ ናቸው። እንዲያውም የምሳ ግብዣ ነው የተያዘልህ። በነገራችን ላይ ፕሮፌሰሩ 'የጋዜጠኛው ማስታወሻን' አንብበውታል። ለማንኛውም ነገ 12.00 ሰአት ሜዲያን ሆቴል!"

አስር ደቂቃ ቀደም ብዬ ሜዲያን ሆቴል ደረስኩ።

ስለኒህ አንጋፋ ምሁር አጥብቄ እያሰላሰልኩ ነበር። መኮንን ቶላ የተባለ የአዲስ ዘመን ጋዜጠኛ ነበር ስለኒሁ ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ የነገረኝ። ፕሬስ በምሰራበት በዚያን ዘመን ከመኮንን ጋር ስናወጋ፣

"አስመሮም ለገሰ የኦሮሞ ህዝብ አባት ናቸው። 'ገዳ' የሚል መፅሃፋቸውን ማንበብ አለብህ" ሲል ሃሳብ ሰጠኝ።

"ገዳ"ን አግንቼ ያነበብኩት ግን ከአስር አመታት በሁዋላ ነበር። ፕሪቶሪያ ሳለሁ መፅሃፉን ከUNISA ላይብረሪ ተውሼ ቋንቋው ቢከብደኝም አንብቤ ጨረስኩት። በመዝገበ ቃላት እርዳታ አጠናሁት ቢባል ይቀላል...

ስጨርሰው በጣም በሸቅሁ።

እንዴት ያለሁት ደፋር ኖሬያለሁ? 'ገዳ'ን ሳላነብ ነው፣ "የቡርቃ ዝምታ"ን የፃፍኩት? ካነበብኩት በሁዋላ የኦሮሞ ህዝብ ማነው? ምንነበር? ለሚሉት ዋርካ ጥያቄዎች ጥልቅና ጥናታዊ መልስ የሰጡን ቀዳሚው ሰው እኒሁ አንጋፋ አንትሮፖሎጂስት መሆናቸውን ለመገንዘብ ችያለሁ።

እና ይኸው ዛሬ ከኒህ አዛውንት ጋር ጥቂት ለመጨዋወት ቀጠሮ አለኝ። ከፕሮፌሰሩ ጋር በሚኖረኝ አጭር ቆይታ ምን አይነት የወሬ ርእሶች ሊኖሩን እንደሚገባ በወረቀት

ላይ ጫጭሬያለሁ። ከመነሻውም ጥያቄ ከመጠየቅ በቀር እኔ ምንም መናገር እንደሌለብኝ አውቄያለሁ። የመናገር እድሉን ሙሉ በሙሉ ለፕሮፌሰሩ በመስጠት ብዙ ትርፍ ዝቄ መመለስ እንዳለብኝ ወስኛለሁ። መሆን ያለበት እንዲያ ነበር...

*(በወጣትነቴ ዘመን ከበአሉ ግርማ ጋር ቁጭ ብዬ የማውጋት ከፍተኛ ፍላጎት ነበረኝ። ሳይሆን ቀረ። ነፍሰበላዎቹ ከትፈው በሉት። ሃዲስ አለማየሁና ብርሃኑ ዘርይሁንን ግን ደርሼባቸዋለሁ። ሃዲስ አለማየሁ መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ከሚገኘው ፅህፈት ቤታቸው ተቀብለው ሲያነጋግሩኝ የ18 አመት ልጅ ነበርኩ። ከባለቅኔ ፀጋዬ ገብረመድህን ጋር ጥሩ ትዝታ አለኝ። ከእሳቸውም ድምቡሎ ሳልከፍል እስከጠግብ ድረስ እውቀት ዘርፌያለሁ። መንግስቱ ለማ ለጥቂት አመለጡኝ። ያናድዳል! እኔ ጦርነት ውስጥ ሳለሁ እሳቸው አረፉ። ከበደ ሚካኤል ቁጡ እና ገለልተኛ ነበሩ። የሚቻል አልነበረም። ሁሌ የሚፀፀተኝ የዳኛቸው ወርቁ ነው። ዛሬ ነገ አገኘዋለሁ እያልኩ ሳይታሰብ የእረፍት ዜናውን ሰማሁ። 'አደፍርስ'ን በመፃፉና የአማርኛ ቋንቋን አንድ ደረጃ ከፍ በማድረጉ ላመሰግነው ምኞት ነበረኝ። ከዳኛቸው እረፍት በሁዋላ ግን ጥሩ ትምህርት በማግኘቴ በህይወት ያሉትን አንጋፋ የጥበብ ሰዎች እያሳደድኩ ልምድና ችሎታቸውን መዝረፉን በሰፊው ተያይዤው ነበር። ወያኔ የተባሉት ወያኔዎች ከሃገሬ አፈናቅለው፣ ለስደት እስኪዳርጉኝ ድረስም ኢትዮጵያ ካፈራቻቸው የጥበብ ሰዎች ጋር ጥብቅ ግንኙነት ነበረኝ። እርግጥ ነው ቴክኖሎጂው በፈቀደው መጠን አሁንም በርቀት እያገኘሁዋቸው ነው። ወያኔ እንዳይጎዳቸው በማሰብ እዚህ ስማቸውን ከመጥቀስ ተቆጥቤያለሁ። ምንም ቢሆን ግን በአንድ ጠረጴዛና በአንድ ገበታ ዙሪያ ተቀምጦ እንደማውጋት ሊሆን አይችልም። የደነቆረው ደንቆሮ ፖለቲካችን ስንቱን አራርቆታል? ስንቱ ይሆን በፖለቲካው ምክንያት ወላጆቹን እንኳ መቅበር ያልቻለው?)*

እነሆ! በክብር መዝገቤ ላይ ካሰፈርኳቸው ሰዎች አንዱ ዛሬ ምሳ ጋብዘውኛል። ጎርኪይ እንደሚለውም ይህን መሰል ቀጠሮዎች ለኔ ከዩኒቨርሲቲዎቼ ዋነኞቹ ናቸው። በትምህርት





ቤት ከሚገኘው እውቀት ይልቅ፣ ይህኛው ለኔ ከፍተኛ ዋጋ አለው...

* * *

ፕሮፌሰር አስመሮም ከሁለት ሰዎች ጋር መጡ። ጥቁር የእጅ ቦርሳ ይዘው ነበር። ኪሶች የበዙበት እጅጌ አልባ ቤዥ ጃኬት ለብሰዋል። ከስር ቀላል ግራጫ ቲሸርት። ሃጫ በረዶ የመሰለ ፀጉራቸው ብን ብሎ ሳስቶአል።

የገዳ አባት፣ የቦረናው ሃዩ...

እኔ ከመወለዴ በፊት ያንን ድንቅ ጥራዝ የፃፉት ሰው እኒህ ኖረዋል? ከተቀመጥኩበት ተነስቼ በአክብሮት ተቀበልኳቸው። የማይከብድ ገፅታ ነበራቸው። ከሞቀ ሰላምታ በሁዋላ ወደ ሞቀ ወግ ዘለቅን። ነገሮችን በቀላል መንገድ የማስረዳት ብቃታቸውንም ወዲያውኑ ተገነዘብኩ። ማንኛውም ሰው እንደ ጓደኛው ቀርቦ ሊያዋራቸው የሚችል ቀለል ያለ ጠባይ ያላቸው፣ የማይኮፈሱ፣ ለሰዎች ሁሉ በሰውነታቸው እኩል ሚዛን የመስጠት ችሎታ ያዳበሩ ሰው ሆነው አገኘሁዋቸው።

"እድሜዎ ስንት ሆነ?" ስል ጠየቅሁ በወግ መሃል።

"78"

እሳቸውም በበኩላቸው እንዲህ ሲሉ ጠየቁኝ፣

"እነዚያን ቁርጥራጭ ወረቀቶች እንዴት እንዲህ አገጣጥመህ መፅሃፍ ልታደርጋቸው ቻልክ?"

ስለኔ መፅሃፍ ካወጋን ለኔ ኪሳራ መሆኑ ግልፅ ነበር። እና ርእሰ ወጋችን በአንትሮፖሎጂስቱ ህይወት ዙሪያ ይሆን ዘንድ ጥረት ማድረጌ አልቀረም። ያም ሆኖ ቆይታችን በጠረጴዛው ዙሪያ የነበርነውን ሁሉ ያሳተፈ ነበር። በጠረጴዛው ዙሪያ ከነበሩት አንዱ ተክኤ በየነ የተባለ ደራሲ ነበር።

*(ተክኤ 2002 አጋማሽ ላይ፣ "ካብ ሪቅ ህፍንቲ" የሚል ርእሰ የያዘ "ማስታወሻ" አሳትሞአል። የርእሱ ትርጉም ይዘት "ከባህር በጭልፋ" አይነት ሲሆን፤ በዚህ መፅሃፍ ላይ የፖለቲካ ገጠመኞቹን በጨረፍታ አስፍሮአል። በተለይ ግን "ሶፊያ" በተባለው ፍልስፍና ነክ የትርጉም ስራው ይበልጥ ይታወቃል።)*

* * *

ፕሮፌሰር አስመሮም የወጣትነት ጊዜያቸውን አንስተው ጥቂት አጫወቱን። ወሎ፤ ውጫሌ ከተማ ላይ ነበር ተወልደው ያደጉት። ወላጆቻቸው አምባሰል ጋራ ስር በሚሌ ወንዝ ዳርቻ ትልቅ የፍራፍሬ እርሻ ነበራቸው። ለዚያ የፍራፍሬ እርሻ ከፍተኛ ፍቅር እንደነበራቸው አጫወቱን።

ስለ ትምህርት ቤት ጓደኞቻቸውም አነሳን። ከፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ጋር የረጅም ጊዜ ጓደኛነት እንደነበራቸው አወጉን። የጃንሆይ ስርአት በተገለበጠበት ዘመን አዲሳባ እንደነበሩም አጫወቱን። አንዳንድ አይረሴ ትዝታዎችም ነበራቸው። በተለይ አብራቸው ለዶክትሬት ማእረግ ምርምር ታካሂድ ስለ ነበረች አንዲት ሴት አንስተው ነበር። ላቀች ድረሴ ትባላለች። በጃንሆይ ዘመን ጄኔራል ከነበሩት የአንዱ ልጅ ነበረች - የድረሴ ዱባለ። የደርግ ባለስልጣናት ይህች ልጅ ከሃገር እንዳትወጣ አግደዋት ነበር። አስመሮም ለገሰ ጥረት አድርገው ልጅቱ እንድትወጣ ተፈቀደላት። ላቀች ከወጣች ከጥቂት ወራት በሁዋላ አባቷ ከስድሳዎቹ ባለስልጣናት ጋር ተረሸኑ። ዶክተር ላቀች ዛሬ ዩኒፌም (UNIFEM) በሚባል የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ውስጥ ከፍ ያለ ቦታ ይዛለች።

አስመሮም ረጅሙን የህይወታቸውን ክፍል ኢትዮጵያ ማሳለፋቸውንም አወጉን። በተለይ ግን "GADA" የተባለውን መፅሃፍ ለመፃፍ ወደ ቦረና እንዴት እንደተጓዙ ያጫወቱን ይበልጥ ትኩረቴን ሊስብ የቻለ ነበር፣

"ጥናቱን በ1961 ነበር ቦረና ውስጥ የጀመርኩት" ካሉ በሁዋላ ባጭሩ እንዲህ ሲሉ አጫወቱን፣

"...በዚያን ጊዜ የቦረናው አባገዳ ጀልዴሳ ሊበን ይባል ነበር። የሱ ኬሱማ (እንግዳ) ሆኜ ነው ጥናቴን የጀመርኩት። ኬሱማ መሆን ብቻ ሳይሆን Protection (ጥበቃ) ነበረኝ። ከኔ የማይለይ አንድ የታጠቀ ፈረሰኛ ነበረ።

በየደረስኩበት ሁሉ፣

'ይሄን ሰው እንዳትነኩት!' እያለ አዋጅ ይነግራል።

የኔን ከመካከላቸው የመገኘት ፋይዳ በትክክል ተገንዝበውት ነበር። አለም ያላወቀውና ሊያውቀው የሚገባ





ታሪክና ባህል፣ የኑሮ ስልትና ዘይቤ እንዳላቸው በሚገባ ያውቁ ነበር። በመጀመሪያ መጥቶ የተቀበለኝ ጀልዴሳ ሊበን ራሱ ነበር። በላቀ ስሜትና መንገድ ነበር የተቀበለኝ፣

'ከሲዳማ እንዳንተ ስለ ባህላችን የሚጨነቅ አይተን አናውቅም' አለኝ።

*(ሲዳማ ወይም ሲዳሃማ ማለት በኦሮምኛ አደገኛ ጥቁር ድንጋይ ማለት ነው። ከሲዳሞ ጋር የሚያያዝ አይደለም። ኦሮሞዎች አማራውን በዚህ ቅፅል ስም ይጠሩታል። ሲዳሃማ ያሉትም አማራው አስቀድሞ ጠመንጃ ታጥቆ ኦሮሞዎችን በአደገኛ ሁኔታ ይዋጋቸው ስለነበረ ነው።)*

እና ጀልዴሳ ሊበን እንዲህ አለኝ፣

'...ሲዳማ ገዳ ምን እንደሆነ አያውቁም። እንዳንተ ደግሞ ስለኛ ማወቅ የፈለገ አላየንም። ስለዚህ ወደ መንደራችን አብረኸን ትሄዳለህ' አሉኝ።

ላንድሮቨር ነበረኝ።

አባገዳውና ሃዩዎቹ ወደ ገበያ የመጡት በፈረስ ነበር። አንድ ችግር ግን ነበር። መንገድ አልነበረም። ላንድሮቨሬ እመንደራቸው መግባት አትችልም። ለዚህ መፍትሄ ተበጀ። አባገዳው ሁለት ሰዎች ሰጡኝ። ጫካው ጋር ስንደርስ ሁለቱ ሰዎች በመጥረቢያና በቆንጨራ እየመነጠሩ ለመኪናዋ መግቢያ መንገድ ያበጁ ገቡ። እንግዲህ ቀን ተነስተን ማታ ነው የምንገባው። የተሰጡኝ ሰዎች ባትሪ ነበራቸው። በባትሪ እያበሩ፣ የሁለቱን የመኪና ጎማ እየመሩ፣ እንደዚህ አድርገው እመንደራቸው አስገቡኝ። እዚያ ስደርስ ጀልዴሶ ሊበን እኔን እየጠበቀ ነበር። በክብር ተቀብሎ እንዲህ አለኝ፣

'ድንኳንህን እዚህ ትከል። ሚስቶቼ እነዚህ ናቸው። ታላቋ ማሱሌ ትባላለች። ታናሿ ተሪ ትባላለች። እነዚህ የሚያስፈልግህን ሁሉ ያዙልሃል። ለመነሻ ደግሞ አንድ ጭሬ እርጎ ይኸውልህ'

ዳቦ ከመሰለው እርጎ አንድ ጉንጭ በመጎንጨት ስራዬን ጀመርኩ። እንግዲህ ከዚያች ቀን ጀምሮ ለሁለት አመታት ከዚያች መንደር አልወጣሁም። መነሻዬ ሁልጊዜ የአባገዳው መንደር ነበር። ከዚያ እየተነሳሁ ቦረናን በሙሉ እየዞርኩ፣

ጥናቱን አካሄድኩ።

የአባገዳው ታላቅየዋ ሚስት ልጅ አልነበራትም። ታሳዝናለች። ታናሽየዋ ግን እኔ ከመልቀቄ በፊት አርግዛ ነበር። ያኔ የተረገዘው ልጅ አርባ አመት አልፎት፣ 5ኛው የገዳ ስልጣን ላይ ወጥቶ፣ አምና በ2000 ስልጣኑን አስረከበ..."

እንዲህ ስል ፕሮፌሰሩን ጠየቅሁዋቸው፣

"የገዳን ሲስተም ለማጥናት እንዴት ተነሱ?"

በአጭሩ አጫወቱን፣

"...አንድ ጊዜ የሃርቫርድ ላይብረሪያን፣ 'አንተ ከኢትዮጵያ አይደለም ወይ የመጣኸው?' ስትል ትጠይቀኛለች።

'ልክ ነው' ስል መለስኩ።

'ሃርቫርድ ስለ ኢትዮጵያ ያሳተመው መፅሃፍ መኖሩን ታውቃለህ ወይ?'

'አላውቅም'

አንድ ኮፒ አንስታ ሰጠችኝ።

The folk literature of the Galla ይላል። ቼሩሊ የተባለ ኢጣሊያዊ ነበር የፃፈው።

ቤቴ ወሰድኩና አነበብኩት።

ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ወርራ ባስተዳደረችበት ዘመን ቼሩሊ የኢትዮጵያ ገዢ ሆኖ መጥቶ ነበር። በዚያን ጊዜ ሸዋ ያለውን ቱለማ ኦሮሞ እየተዟዟረ ተመልክቶ ስለ እነሱ ብዙ ነገር ፅፎአል። ቼሩሊ ስለ ኦሮሞ ስርአት፣ በተለይም ስለ ገዳ ብዙ ተጨንቆበት ነበር።

"...ኦሮሞዎች ባህል የላቸውም። መንግስትም የላቸውም' የሚባል ነገር ነበረ። ይሄ ማለት ምንድነው? ንጉስና የንግስና ስርአት የላቸውም። ንጉስ ከሌላቸው ደግሞ መንግስትም ዴሞክራሲም ሊኖራቸው አይችልም' የሚል ነበር።

ቼሩሊ ይህን ይዞ ነው ጥናቱን የጀመረው።

'...ኦሮሞዎች የራሳቸው የተለየ ስርአት አላቸው። የንግስናው ስርአት የክርስትያን አማራው ሲሆን፣ ገዳ የሚባለው የዴሞክራሲው ስርአት ደግሞ የኦሮሞዎች ነው...' ሲል ነበር ያቺን መፅሃፍ የፃፋት።

በጥልቀት ተመራምሮ ሊፅፋት ግን አልቻለም። ምክንያቱም ኢትዮጵያን እያስተዳደረ ነበር። ያቺንም የሰራት





በትርፍ ሰአቱ ነበር። ቼሩሊን ካነበብኩ በሁዋላ እኔ በጥልቀት ላጠናው ወሰንኩና ገባሁበት...

በ1963 ከቦረና በቀጥታ ወደ ማንቸስተር ሄድኩ።

ስለ ራሴ ጥናት ወረቀት ለማቅረብ ነበር የሄድኩት። እዚያ ወረቀቴን ሳቀርብ አንድ በጣም የሸመገለ ሰው እፊት ቁጭ ብሎ ነበር። በመልክ ስለማላውቀው ቼሩሊ ይሆናል ብዬ አልገመትኩም። የገዳ ሲስተም ሳይክሏን፣ ጥቁር ሰሌዳ ላይ ሳልኩና ሳበቃ፣

'መነሻዬ ፕሮፌሰር ቼሩሊ የፃፈው መፅሃፍ ነው። ቼሩሊ አንድ ቦታ አድርሶ ሳይጨርሰው የተወው ነገር ስለሆነ ስራውን እኔ ቀጥዬዋለሁ። የምቀጥለው ደግሞ እንደዚህ ነው' ብዬ ማስረጃ ስሰጥ ቼሩሊ እዚያው ቁጭ ብሎ ይከታተለኛል። እኔ አላወቅሁትም።

እኔ ስጨርስ ቼሩሊ ተነስቶ መናገር ጀመረ። በዚያን ጊዜ የጣሊያን ሃገር የአካዳሚ ኦፍ ሳይንስ ፕሬዚደንት ነበር። ተነስቶ እንዲህ አለ፣

'እኔ አንጠልጥዬ የተውኩትን እሱ ጨርሶታል። ደግ አድርጎአል።'

በዚያን እለት ለሁለት ሰአታት ያህል የምሳ ላይ ወግ አድርገን ተለያየን። የሞባይል ቁጥራቸውንም ሰጡኝ። በሰፊው ልናወጋ እንደምንችልም ገለፁልኝ። ዳሩ እኔ ወደ አስመሮም ከመደወሌ በፊት በሌላ አጋጣሚ ለመገናኘት በቃን።

* * *

ፕሮፌሰሩን በድጋሚ ያገኘሁዋቸው የኢድአልፈጥር በአል በተከበረበት ምሽት ነበር። አስመራ የሚገኘው የኦነግ ዋና ፅህፈት ቤት ለፕሮፌሰሩ እና ለኔ የእራት የግብዣ ጥሪ ላከ።

በጥሪው ሰአት ከቦታው ተገኘሁ።

ፕሮፌሰር አስመሮም ዘግየት ብለው ከሁለት ሴት ልጆቻቸው ጋር መጡ። በግብዣው ላይ አባጫላ ለታ እና የኦነግ ምክትል ሊቀመንበር ቡልቱም ቢዮ ተገኝተዋል። የኦነግ ሊቀመንበር ዳውድ ኢብሳ በግብዣው ላይ አልተገኘም።

ዋሽንግተን ዲሲ ላይ ከAFD ባልደረቦች ጋር ስብሰባ መቀመጡን ግን ወሬ ሰምቼ ነበር። ሌሎቹን የግብዣው ተካፋዮች አላውቃቸውም። በተለያየ የሃላፊነት ስልጣን ላይ የሚገኙ የኦነግ ሰራዊት አባላት ሳይሆኑ አይቀሩም። ጥቂት ሴቶችም ነበሩ።

ራት ቀረበ።

ራቱ ከመቅረቡ በፊት ግን በኦሮሞ ባህል መሰረት የሃገር ሽማግሌዎች ምርቃት ተደረገ። እኔና ቡልቱም ቢዮ ላለንበት ስምንት ሰው የያዘ ቡድን በአንድ አረንጓዴ ትሪ እንጀራ በወጥ ቀረበልን። አባጫላና ፕሮፌሰሩም በሌላ ተመሳሳይ ገበታ ላይ ተሰየሙ። ቀላልና ባህላዊ የራት ስነስርአት ነበር። ገበታው ከፍ እንዳለም የቡና እቃዎች ቀራረቡ። የፈንዲሻ ድምፅም ተሰማ።

ግብዣው የተዘጋጀው ለፕሮፌሰር አስመሮም ክብር ሲባል መሆኑ ተገለፀልን። የ"ኦዳ" ምስል ያለበት ስጦታ ከከፍተኛ ጭብጨባ ጋር ለ"ገዳ" ደራሲ ተበረከተላቸው። የሽልማት ስነስርአቱ ካበቃ በሁዋላም አስመሮም ንግግር ያደርጉ ዘንድ ተጋበዙ። አንጋፋው አንትሮፖሎጂስት ማይክራፎን ሲጨብጡ እኔም የተፈጥሮ ግዴታዬን መፈፀም ቀጠልኩ....

"ገዳ የተባለው መፅሃፌ ከታተመ በሁዋላ፣ አንድ ሽማግሌ ቦረና ውስጥ አጋጥመውኝ ነበር። መፅሃፍ ማንበብ የማይችሉ ገበሬ ነበሩ" ሲሉ ነበር ንግግራቸውን የጀመሩት።

እና ቀጠሉ ፕሮፌሰሩ፣

"...በዚያን ጊዜ የኔ መፅሃፍ ዋጋው 33 ዶላር ነበር። እኚህ የቦረና ሽማግሌ መፅሃፌን ገዝተው እቤታቸው ሳጥን ውስጥ ቁጭ አድርገውታል። እኔን እንዳገኙኝ ሚስትየዋን ጠርተው፣

'አምጪው ሳጥኑን' አሏት።

ሳጥኑ ቀረበ። በቁልፍ ከፍተው የሚያንፀባርቅ አንድ የመፅሃፌን ኰፒ አውጥተው አሳዩኝ። ስለተገረምኩ፣

'ለምን ገዙ ይህን መፅሃፍ?' ብዬ ጠየቅሁኝ። '...እርሶ አያነቡም፤ ልጆችዎ አያነቡም፤ ለምን ገዙት?' ብላቸው፣

'ዛሬ ባይነበብ፣ ነገ ባይነበብ፣ የልጅ ልጆቼ ያነቡታል። ለዚህ ብዬ ነው እዚህ ቁጭ ያደረኩት' አሉኝ።

"...ቁምነገሩ ምንድነው?

"...እንደኔ ያለ ይህን ውጤት ሲያይ ልዩ ትርጉም





ይሰጠዋል። የስራ ጓደኞቼ የሚሰጡኝ አክብሮት አለ። እሱ አይደለም፤ ህዝብ ስለ ራሱ የቀረበውን ፅሁፍ በአክብሮት ሲቀበል፣ አንብቦ ደግሞ አስተሳሰቡን ለመቀየር ሲችል ይህ ከሁሉ የላቀ ውጤት ነው።

"...አንድ አብነት ልሰጣችሁ...

"...ካሊፎርኒያ አንድ ትልቅ ስብሰባ ተደርጎ ነበር። ስብሰባውን የጠራችው ሌንሳ ጉዲና ነበረች። የቄስ ጉዲና ልጅ። በጣም ሃይለኛ ሰው ነበረች። ስብሰባው ላይ ስለገዳ ንግግር አድርጌ ነበር። ኤርትራውያንም መጥተው ነበር። 'ይሄ የኛ ወጣት ስለ ኦሮሞ ምን ሊል ነው?' እያሉ፣ ጉድ ሊሰሙ! ከተሰበሰቡት አንዱ ደግሞ ነጋዴ ነበር። ካሊፎርኒያ ብዙ ተቀምጦአል። ቤተሰብ አለው። ሚስቱ ልጆቹ አብረው ነው የመጡት። ልጆቹ የኔን መፅሃፍ ይዘው መጡ። በእጃቸው ይዘዋታል።

'ይችን መፅሃፍ አንድ ቀን አገኘናት' አሉኝ። '...አጊኝተን ቤተሰብ በሙሉ ተሰብስቦ ከዳር እስከ ዳር አነበብናት። አንበን ስንጨርስ ያደረግነው ምንድነው? ስማችን የክርስትያን ስም ነበር። ማለትም እንደ ጴጥሮስ፣ ዮሃንስ የመሰለ ስማችንን ቀይረን የኦሮሞ ስም አደረግነው' አሉኝ።

"...እድሜዬን በሙሉ የሚያሳስበኝ ምን ነበር? ፈረንጆችም፣ ኢትዮጵያውያን ደራስያንም ስለ ኦሮሞ የሚፅፉትን ሳነብ የንቀትና የሃሰት ይዘታ ያለው መሆኑ አጥብቆ ያሳስበኛል። አንድ የተማረ ሰው ይህን ሲያይ መቼም ቅር ይለዋል። ለምንድነው ይሄ ሃሰት የሚሰራጨው? ለምንድነው አሁንስ እንደነበረ የሚቀጥለው? የሚል አስተሳሰብ ወደ አእምሮዬ ይመጣል..."

ፕሮፌሰር አስመሮም ለአፍታ ንግግራቸውን ገታ አደረጉ። ተጋባዡ ሁሉ ትንፋሹን ውጦ በተመስጦ እያዳመጣቸው ነበር። እኚህ አንጋፋ ምሁር ህይወታቸውን ሙሉ ያጠኑትን እውቀት እዚህ በጥቂት አረፍተነገሮች እየገለፁልን ነበር። እና ወደ ንግግራቸው ማጠቃለያ ግድም እንዲህ ሲሉ አወጉን፣

"...በቦረና የቀን አቆጣጠር ላይ አንድ ጠለቅ ያለ ምርምር አቅርቤ ነበር። በጣም አስቸጋሪ ነው። እኔን ራሴን በጣም አስጨንቆኝ ነበር። ስለዚሁ የቀን አቆጣጠር ያስተማረኝ

ሰው አሬሮ ረመታ የሚባል ሽማግሌ ነው። Ani hurjjii nan beeka namni hurjjii beeku waa hundumaa ni beeka. ነው የሚሉት። 'ከዋክብትን የሚያውቅ ሰው ብዙ ነገር ያውቃል' ማለት ነው። እና አሬሮ ምን አለኝ? '...አንተም ከዋክብትን ማወቅና መማር አለብህ' አለኝ።

እንዴት አድርጌ ነው ስለ ከዋክብት የማውቀው? እኔ ስለ አስትሮኖሚ ምንም የማውቀው ነገር አልነበረም።

"...እነሱ ምን ይላሉ?

'...ጨረቃ ስትወጣ በቀን በቀን ቦታዋን ትቀያይራለች። በመጀመሪያ ቀን ከአንደኛው ኰከብ ጋር ከወጣች በነጋታው ከሁለተኛው፣ በመቀጠል ከሶስተኛው... ሁለተኛው ወር ሲጀምር ከሁለተኛው ኰከብ ጋር ነው የምትጀምረው። ከአንደኛው ጋር አይደለም። ቀጥሎ ከሶስተኛው ኰከብ ጋር ትወጣለች። ይሄን ሁሉ በአንገላቸው አስፍረውታል። ይሄንን ሊያስረዳኝ ይሞክራል ይሄ ሽማግሌ። አቃተኝ። ፈፅሞ ሊገባኝ አልቻለም። ቦረና ሆኜ ሊገባኝ አልቻለም። በመጨረሻ አሬሮ ረመታ ምን ይለኛል?

'እዚህ ስራ ይበዛብኛል። ሰው ሁሉ ነው የሚፈልገኝ። ስለዚህ እዚህ ምንም ላስተምርህ አልችልም። ተያይዘን አዲሳባ እንሂድ'

እውነቱን ነበር።

አባገዳ ምክር ሲፈልግ አሬሮ ረመታን ነበር የሚጠራው። አሬሮ ሲጠራ ነጭ ፈረስና ነጭ ልብስ ተሰጥቶት ነው የሚመጣው። ሰው ይፈልገዋል።

ስለዚህ እውነቱን ነበር።

ሄድን ተያይዘን ወደ አዲሳባ።

ማታ ማታ እንጠጠ ተራራ ላይ እንወጣለን። ረጅም ዘንግ ይዘን ነው የምንወጣው። ከዋክብቱን ሁሉ አንድ ባንድ እየጠቆመ ይነግረኝ ጀመር። ይሄ ላሚ ይባላል። ይሄ በከልቻ ይባላል። የሁሉንም አስረዳኝ። ጨረቃዋ ስትወጣ ከየትኛው ኰከብ ጋር እንደ ወጣች አስረዳኝ። አንድ ወር ነው የቆየነው እዚያ። በወሩ ጨረቃዋ ስትወጣ ከሁለተኛው ኰከብ ጋር እንደወጣች አስረዳኝ። በወቅቱ ታዲያ አንጐሌ ላይ የተቀረፀው ምንድነው Permutation በሚባል የማተማቲክስ ቴክኒክ የተመሰረተ የቀን አቆጣጠር ዘዴ ነው። ይሄ አመት ሙሉ ዞራ





ስትመጣ ቢቶቴሳ በምትባል ወር፣ ቢታቃራ በምትባል ቀን የመጀመሪያው አዲሷ ጨረቃ ከአንደኛው ኰከብ ጋር ትወጣለች። ይሄ የአመቱ መጀመሪያ ይባላል።

በዚህ ጊዜ ሁሉም ተገለፀልኝ።

ፃፍኩት።

ፅፌ ሳበቃ የሆነው ምንድነው? ከኔ በሁዋላ የተደረገውን ጥናት አላውቀውም እንግዲህ። የተደረገው ግን ምንድነው? ናሳ (NASA) የሚሰራ ፈረንጅ አስትሮኖመር መፅሃፌን ያነባል። መፅሃፌን አንብቦ፣

'ይሄ ነገር ባስትሮኖሚ ይሰራል አይሰራም?' ሲል መረመረ። መርምሮ በደንብ ሊሰራ ይችላል አለ።

"...ዋናው ያስጨነቀው እሱ አይደለም። ያስጨነቀው ምንድነው? ኬንያ ውስጥ ጥንት የተተከሉ ሃውልቶች አሉ። ኦሮሞዎች ለምንድነው ሃውልት የሚተክሉት? አባት ከሞተ ልጆቹ ሃውልት ይተክሉለታል። የምናውቀው ይሄንን ነው። የሚበዙት በኢትዮጵያ ያሉ የኩሽ ዘሮች እንደዚያ ያደርጋሉ። ኬንያ ላይ የተገኙት ሃውልቶች ግን እንደዚያ አይደለም አቀማመጣቸው። ቀጥ ያሉ ሃውልቶች ሆነው አቅጣጫቸው ግን ለየብቻ ነው። ወደ ላይ ቀጥ ያሉ አይደሉም። አንዱ ወዲህ ነው፤ ሌላው ወዲያ፤ ምስቅልቅል ያለ ነው አተካከላቸው። አርኪዮሎጂስቶቹ ትርጉሙ አልገባቸውም።

"ይሄ አሜሪካዊው አስትሮኖመር ምን ይላል?

'ይሄ ነገር እኮ Premitive Observatory ሊሆን ይችላል።'

Observatory ማለት የከዋክብት መመልከቻ ህንፃ ወይም መነፅር ማለት ነው። 'ይህ ከሆነ' ይልና የኔን መፅሃፍ ይዞ ወደ ኬንያ ይሄዳል። ያያል። ቢያይ አንደኛው ሃውልት ወደ በከልቻ ያመለክታል። በከልቻና ጨረቃዋ አብረው የሚወጡበት በየት እንደሆነ ሃውልቱ ያመለክታል። "ጠሃ" ይባላል። ለእያንዳንዱ ጠሃ አንድ ሃውልት ተተክሎአል። ኰከብ ጨረቃዋን "የሚመታበት" ጊዜ ማለት ነው። ይሄን የሚያመለክት ነው ይሄ ሃውልት።

"ይህንን ሁሉ አጥንቶ ሲጨርስ ምን ያገኛል?

ሃውልቱ ሁሉም በሁለት ዲግሪ አቅጣጫውን ስቷል። ለምን እንዲህ ሊሆን ቻለ? ይሄ ነገር በደንብ በጥናት በምርምር በobservation የተሰራ ነገር ነው። ስህተቱ የመጣበት ምክንያት

ይኖረዋል።

አስትሮኖሚስቶች ተሰብስበው፣

'እንዴት ሊሆን ይችላል? ስህተት አለ ወይ? ይህንን ሊያመጣ የሚችል ስህተት አለ ወይ? ይህን ሊያመጣ የሚችል ምን ስህተት አለ?' ሲሉ ይጠያየቃሉ።

አንዱ ከአስትሮኖመሮቹ ምን ይላል?

Precession የሚባል ነገር አለ። Precession ምንድነው? አለም አቀማመጧ ከፀሃይ ጋር ስትተያይ እንዲህ ተንጋዳ ነው የምትዞረው። ስለዚህ ሰሜኑና የደቡቡ የአለም ክፍል ለየብቻው ነው በየወቅቱ ተከታትሎ የሚመጣው። ነገር ግን ይሄ እንዲህ የተንጋደደው ቀጥ ያለ አይደለም። wobble ያደርጋል። wobble ሲያደርግ ደርሶ እስኪመለስ 26 ሺህ አመት ይፈጅበታል። ስለዚህ እኛ ከዋክብቱን ስናያቸው የሚታየው ሁልጊዜ አንድ አይደለም። በየአንድ ሺህ አመቱ አቀማመጡ ይቀየራል። ይሄ የሁለቱ ዲግሪ ልዩነት ሊመጣ የቻለው በዚህ ምክንያት ነው' ይላሉ አስትሮኖሚስቶቹ። እንዲያ ከሆነ ወደ ሁዋላ ተመልሰን እናስላው ይላሉ። የአለም እንቅስቃሴ ተጠንቶ፣

'ይሄ ሃውልት ትክክል የነበረበት ዘመን መቼ ነው?' ተብሎ ሲሰላ 300 አመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ሆኖ ተገኘ። ይሄ እንግዲህ በስሌት የተደረሰበት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ሃውልቱ የተገኘበትን ቦታ በሬድዮ ካርቦን (Radio carbon dating) መረመሩት። እሱም 300 አመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ሆኖ ተገኘ።

"...ስለዚህ ይሄ ምን ማለት ነው?

"...የኦሮሞ አያቶች ከ2000 አመት በፊት Astronomical Observatory ነበራቸው ማለት ነው።"

ፕሮፌሰር አስመሮም ለገሰ ረጅም ሳቅ በማሰማት ንግግራቸውን ሲገቱ፣ የአንጋፋውን አንትሮፖሎጂስት ሳቅ ውጦ ያስቀረ፣ እንደ ቢሾፍቱ ነጎድጓድ የከበደ ጭብጭባ በሶሎኑ ውስጥ አስገመገመ።

ጭብጨባው በረድ ሲል ጠበቁና እንዲህ ሲሉ አሳረጉ፣

"...እንደዚህ ያለ እውቀት በአክብሮት ያጠኑት እንደሆነ ሊገኝ ይችላል። በንቀት ከተነሱ ግን ሊገኝ አይችልም። ማለቴ ምንድነው? ከኔ በፊት ሁለት ትልልቅ አንትሮፖሎጂስቶች፣ ስለኦሮሞና ስለገዳ ሲስተም አጥንተዋል። አንዱ ፖል ባክስተር፣





እንግሊዛዊ ሲሆን፤ ሌላው አይከ ሃበርላንድ የተባለ ፍራንክፈርት ዩኒቬርሲቲ ያለ ጀርመናዊ ፕሮፌሰር ነው። ሁለቱም ምንድነው የሚሉት?

'ኦሮሞ ስለ ከዋክብት ብዙ ይጨነቃል። ግን ጥንቆላ ነው። አያና ይሉታል። ቀኑ ሁሉ ትርጉም አለው ይላሉ። በዚህ ቀን ልጅህን እንድታገባ የፈቀድክ እንደሆን አያናህን ይዛብህ ትሄዳለችና አንድ ነገር ማድረግ አለብህ። ቀን ቆጥረህ ነው ልጅህ እንድታገባ መፍቀድ ያለብህ' ይላሉ። ስለዚህ ይህ ጥንቆላ ነው እንጂ ሌላ አይደለም' ብለው ነገሩን ይዘጉታል። ሆኖም ለኔ ተሰጥቶኝ የነበረው መረጃ ሁሉ ለነዚህ ለሁለቱም አንትሮፖሎጂስቶች ተሰጥቶአቸው ነበር። ትርጉም ሊኖረው አይችልም' ብለው ግን አስቀድመው ወሰኑ።

አንዱ ይህን ሲያብራራ፣

'ኦሮሞ simple ህዝብ ነው። simple ህዝብ ከሆንክ ደግሞ እንዲህ ያለ የተወሳሰበ ነገር ልትፈጥር አትችልም። ስለዚህ ገዳ ራሱ በጣም የተወሳሰበ ሲስተም ስለሆነ ኦሮሞ ሊፈጥረው አይችልም። ከሌላ ቦታ ነው የመጣው' አለ።

'ከየት መጣ?' ተብሎ ሲጠየቅ፣

'አላውቅም' ሲል መለሰ። '...ግን ከህንድ ሊሆን ይችላል' አለ። ህንድ በዚያን ጊዜ ኢትዮጵያ አልመጣም። ኦሮሞም ወደ ህንድ አልሄደም። ኦሮሞ አይዋኝም። ታንኳም የለውም። ጀልባ አልነበረውም። ከኢትዮጵያም ወጥቶ አያውቅም። ስለዚህ ኦሮሞዎች ባህላቸውን ራሳቸው ፈጠሩት እንጂ ከህንድ መጣ የሚባለው ስህተት ነው።

"...ዋናው ነገር ምንድነው?

"...አዋቂዎች ሲመራመሩ በንቀት ስለሚነሱ ትርጉሙም መሰረታዊ መዋቅሩ (Basic structure) ሊገባቸው አይችልም። አዲሱ የኦሮሞ ትውልድም ራሱ ባህሉን በንቀት ገምግሞ ከተነሳ በእጁ የለም። ሊገባውም ሊደርስበትም አይችልም። ጥልቅና ውስብስብ መሆኑን አውቆ፣ ተጨንቆ ሊረዳው የሚፈልግ ግን ይደርስበታል። ኸረ ስንት የቀረ ነገር አለ? የገዳ ጥናት ገና አላለቀም። ገና ገና አልተነካም። እኔ ላይ ላዩን ብቻ ነው የነካሁት። ሌሎች ይቀጥሉት ይሆናል..."

* * *

ለመጨረሻ ጊዜ አስመሮም ለገሰን ያገኘሁዋቸው በጣም ለአጭር ደቂቃዎች ነበር። ቲራቮሎ ከተባለው ሰፈር ቆሜ ታክሲ እየጠበቅሁ ሳለ፣ ፕሮፌሰሩ በዚያ ሲያልፉ መንገድ ዳር ቆሜ አይተውኝ ኖሮአል...

መኪናቸውን አቆሙልኝና ተሳፈርኩ።

ወደምሄድበት እየሾፉኝ ሳለም እንዲህ ስል ጠየቅሁዋቸው፣

"ገዳ በድጋሚ ለምን አይታተምም? ለምንስ ወደ አማርኛና ኦሮምኛ አይተረጎምም?"

እንዲህ አሉኝ፣

"ገዳ በቅርቡ በድጋሚ ታትሞ እንዲወጣ አደርጋለሁ። ሪቪዥን ሳደርግ ቆይቻለሁ። መጀመሪያ ሲታተም ዋጋው ውድ ነበር። ሰው የሚነካው አልነበረም። አሁን ግን ህዝብ በሚችለው ዋጋ እንዲታተም አደርገዋለሁ። የመጀመሪያው መፅሃፍ እንዳለ ሳይሆን፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስካሁን የተደረገው ጥናትና ምርምር ውስጡ ገብቷል። ከዚህ ከተደረጉት ምርምሮች አንዱና ዋነኛው ባለፈው ያጫወትኳችሁ የቦረና የቀን አቆጣጠርና የናሳ (NASA) ተመራማሪ ማረጋገጫ ጥናት ይገኝበታል..."

መኪናዋን ዳር አስይዘው እያቆሙ እንዲህ ሲሉ አከሉ፣

"መፅሃፉን ወደ አማርኛና ኦሮምኛ መመለስ አስፈላጊ መሆኑ አያጠያይቅም። ይህን መስራት የሚችሉ ግን መኖር አለባቸው..."

ተሰናብቼያቸው ከመሄዴ በፊትም እንዲህ ስል ጠየቅሁዋቸው፣

"ከእርሶ ጋር ያደረግሁዋቸውን ቆይታዎች በቀጣዩ መፅሃፌ ላይ ባካትተው ይፈቅዱልኛል?"

ረጅም ሳቅ ስቀው እንዲህ ሲሉ መለሱልኝ፣

"የመጀመሪያውን ስትፅፍ እያስፈቀድክ ነበር እንዴ?"

የመሳቁ ተራ የኔ ሆነ።



# - 24 -

# ደጋግ ሰዎች

ለሽማግሌዎች - ለወላጆቻቸው -
ደጋፊ ለመሆን - ለመከፈል ብድር፣
ወጣት ጎረምሳዎች - የስራ ቀኝ ክንዶች -
የሚንከራተቱት - ለመሆን ቅጡር፣
ነውኮ ለማብዛት -
የገባሩንና ያሽከሩን ቁጥር፣

* * *

አይ ይሆን! ወይ ጓዶች!
ነፃ የሆነ ህዝብ - የማይኖር ተጨምቆ፣
የባርነት ቀንበር - ከሰው ጫንቃ ወርዶ - ተሰባብሮ ወድቆ፣
አይ ይሆን! ነፃነት - ደምቃ ስታብራ - በአገሬ መሬት፣
ያማረም ጎህ ቀዶ - ሲወጣ በጠዋት፣
አይ ይሆን! ወይ በእውነት....?

(ግጥም - አሌክሳንደር ፑሽኪን)
- እያልነህ ሙላቱ እንደተረጎመው

ጆሃንስበርግ OR Thambo አየር ማረፊያ ስደርስ፣ ገና በጠዋቱ ምድሩ ጨላልሞ ነበር። የክረምቱ ጭጋግ ከነጓዙ ኢጎሊ ምድር ላይ ወርዶአል። መላ ሰውነትን እንደ መርፌ የሚጠቀጥቅ ብርድ ደቡብ አፍሪቃን አደንዝዞአታል። ሻንጣዬን በጋሪ እየገፋሁ ወደ ደጅ ብቅ ስል ቆፈኑ የአፍንጫዬን ጫፍ እንደ በረዶ አደረቀው። አርተፊሻል አፍንጫ የሰካሁ ያህል

ሆነብኝ...

የፕሪቶሪያ ሃበሾች ግን አስፈሪው ክረምት ሲመጣ በደስታ ጮቤ ይረግጣሉ። ደቡብ አፍሪቃ ላይ ሃበሾች በብዛት የጨርቃ ጨርቅ ነጋዴዎች እንደመሆናቸው፣ በክረምቱ ወራት የአልባሳትና የብርድ ልብስ ገበያው ይደራላቸዋል። "ገንዘብ ካለ፣ በቆፈን ውስጥ ወበቅ አለ!" ያለው ማን ነበር?

ወደ Sunnyside ብቅ ያልሁት በቂ እረፍት ከወሰድኩ በሁዋላ በሶስተኛው እለት ነበር። በዘመነ አፓርታይድ ሰኒሳይድ የአውሮፓውያን የመዝናኛና የመኖሪያ ቀበሌ ነበረች። የአፓርታይድ ስርአት ሲወድቅ አውሮፓውያኑ ቀስ በቀስ ወደ ምስራቅ ፕሪቶሪያ አፈገፈጉ። ሰኒሳይድ ዛሬ የአፍሪቃ ስደተኞች መከማቻ ሆናለች። በአፓርታይድ ስርአተ - ዘመን የሰኒሳይድ መንገዶች ማታ ማታ በውሃ ይታጠቡ ነበር። ዛሬ መንገዱ አይታጠብም። ማታ ማታ ማጅራት መቺዎች የነዋሪውን ኪስ ሲያጥቡ ያመሻሉ...

ሰኒሳይድ ላይ የሌለ አፍሪቃዊ ዜጋ የለም። ከሴኔጋል፣ ከኢትዮጵያ፣ ከታንዛኒያ፣ ከኤርትራ፣ ከሶማሊያ፣ ከዚምባቤ፣ ከናይጄሪያ፣ ከአልጄሪያ፣ ከአንጐላ...

ተከባብረን እንኖራለን። ባንከባበርም ፖሊስና ህግ ፈርተን በአንድነት እንኖርባታለን። ሃበሾች በተለይ በዚህች መንደር ሳንበዛ አንቀርም። ወደ ሰኒሳይድ ብቅ የሚል እንግዳ የሃበሻ ምግብ ቤቶችን አድራሻ መጠየቅ አያስፈልገውም። የበርበሬ ቁሌት ሽታና የትኩስ እንጀራ ወላፈን ገና ከሩቅ ይጠራዋል።

የሃበሾች መከማቻ ወደ ሆነው River of Africa ባርና ሬስቶራንት ነበር በቀጥታ ያመራሁት። ወደ ባሩ ዘልቄ ስገባ ማንንም አልነበረም። ሰአቱ ገና ስለሆነ ነው መሰለኝ ጭር ብሎ ጠበቀኝ። ተካ ጨቤ ብቻውን ከባንኮኒው ጀርባ አቀርቅሮ ወረቀት ላይ ሂሳብ እያሰላ ነበር። ሲያየኝ በጣም ደነገጠ፣

ተካ ጨቤ!

በደግነታቸው ከመዘገብኳቸው ሃበሾች አንዱ ነው። እንዴት ጥሩ ልጅ መሰላችሁ? ሲያዩት ግን ክፉ ይመስላል። አፍንጫው ሹል ነው። ሹል ያልሆነ ነገር የለውም። ጫማው ሳይቀር እንደመርፌ ሹል! ጠልቀው የሚያዩ ደቃቃ አይኖች! መብረቅ የምትመስል ቀጭን ፈገግታ! ጠጉሩን በራ ጀምሮታል።





ቀጭን የባህር ወሽመጥ የመሰለች በራ መሃል አናቱን ሰንጥቃ እያለቀሰች ቁልቁል ትወርዳለች።

ድንገት ወደ ባሩ ገብቼ ሰላምታ ሳቀርብለት በደመነፍስ ነበር ዞሮ መጥቶ በሞቀ ስሜት የተቀበለኝ።

በርግጥም ከፕሪቶሪያ ከወጣሁ ቆየሁ። ስራዬን ጨራርሼ ወደ ፕሪቶሪያ ለመመለስ ጥቂት ወራት ፈጅቶብኝ ነበር። ከጨቤ ጋር የሞቀ ሰላምታ ከተለዋወጥን በሁዋላ ፕሪቶሪያ እንዴት እንደሰነበተች በስሜት ያወጋኝ ያዘ፣

"መፅሃፍህ መወያያ ሆኖአል!"

"እውነት? እንዴት ነበር?"

"የሁሉም ሰው ወሬ ለሳንቲ መፅሃፍ ሆኖ ሰነበተ..."

ስለመፅሃፌ መተረክ የጀመረው በሞቀ ሁኔታ ስለነበር ጆሮዬን በረጋግጄ ልሰማው ተዘጋጀሁ። ይሁን እንጂ አልቀጠለም። "ጠፋሁ!" አለኝና ከንፈሮቹን አገጣጠማቸው።

"ወዲያ ወዲህ እያልኩ ነበር" ስል መለስኩ።

ከተካ ጨቤ ጋር ወሬያችን እንዳለቀብን በመገመቴ ምናልባት አንዳንድ ነገር ቢናገር በሚል ራሴው ቀሰቀስኩት፣

"አንተስ አነበብከው?"

"አላነበብኩትም። ፋንታሁን ግን አንብቦታል። 'ወያኔን ጨፍጭፎታል! አላስተረፋቸውም! ካገኙት አይለቁትም' ብሎ ነገረኝ። ዋናው ግን 'በረከት ስምኦን የሚባለውን አላስተረፈውም' ብሎ ነገረኝ። ምን አድርጉህ ነው? ፀበኞች ነበራችሁ እንዴ?"

መልስ ስላልሰጠሁት ራሱ ቀጠለ፣

"...ባለፈው ወር በረከት እዚህ መጥቶ ነበር። እነ ወንደሰን ምግብ ቤት ምሳ ጋበዙት። ገና ወደ ምግብ ቤቱ ሲገባ ትግሬዎቹ ፈንዲሻ በተኑለት። እሱም ሳቅ በሳቅ ሆነ። እነ ወንደሰን ክትፎንሽ፣ ዱለትንሽ፣ ቀይወጥንሽ፣ በዚህ አልጫ፣ በዚያ ኮርኒስ፣ በወዲያ ካፕሬቶ፣ በወዲህ መረቅ...ቡፌ አዘጋጅተው ጠብ! እርግፍ! ሲሉለት እሱ ምኑ ሞኝ? እየሳቀ የራሱን አገልግል ከፈተ። ቆቅ ነው አሉ! ሰው አያምንም! መጠጡን ጭምር ካዲሳባ አስጭኖ ነው የመጣው።" አያያዘናም፣ "...የሚጠጣ ምን ላምጣልህ ታዲያ?" አለ።

ቮድካ አዘዝኩ።

የተቀዳልኝን ቮድካ በዝምታ እያጣጣምኩ ሳለ፣

"ደ'ሞ ልንገርህ? መጠንቀቅ አለብህ።" ሲል ድምፁን

ዝቅ አድርጎ መከረኝ፣ "...በረከት ካገኘህ በጥርሱም ቢሆን አይለቅህም። እዚህ ከተማ ጓደኞች አሉት። ሊታከም በመጣ ቁጥር ከነቶኒ ጋር ነው የሚጠጡት ..."

"ማነው ቶኒ?"

"ባለ ሱቁ፣ የአድዋ ልጅ..."

ብዙም ሳይቆይ River of Africa በሃበሾች ተሞላ። ነጋዴዎች ሱቆቻቸውን እየዘጉ ወደ መከማቻችን ጐረፉ። መደበሪያችን ባንድ አፍታ ደመቀች። ተካ ጩቤ ደጁ ላይ እሳት አነደደ። በእሳት ተከብበን ባሊ ሙሉ ሄይኒከን ቢራና ቮድካ በጠርሙስ አወረድን። የቢራ ጠርሙሶችን በረዶ በሞላ ባሊ ውስጥ ጠቅጥቆ ማቅረብ በደቡብ አፍሪቃ የተለመደ ነበር።

ዳዊት ራስታና ጴጥሮስ ተከታትለው ገቡ። ፈቃዱ በረዳ የትረባ ቀንዱን አስቀድሞ ተቀላቀለን። ሰለሞን ባደንጋ ሹሩባውን እየነሰነሰ፣ ፈገግታውን እንደ ፈንዲሻ እየበተነ ገባ። ፋሲልም መጣ። የቦክስ ስፖርተኛው ሳሚ ተከተለ። ስሙ ሳሙኤል ይሁን ሳምሶን አይታወቅም። ለባድሚንተን ውድድር ኢስት ለንደን ከመጡ በሁዋላ ፕሪቶሪያ ላይ የቀሩት አብይና በሃይሉ፣ መንግስቱና ቴዲ አራቱም አንድ ላይ ገቡ። ደምሴ ፖለቲከኛውና መስፍን መላጣውም እንዲሁ እሳት ወደ ከበበው ጠረጴዛ ተጠጉ። በመጨረሻ በሃበሾች ዘንድ ተወዳጅ የሆነው መሃመድ ሶማሌው መጣ። ይኸው ነው! አንዱ ይሄዳል፣ ሌላው ይመጣል። ህይወት እንዲሁ ትቀጥላለች፤ ፕሪቶሪያ ላይ...

* * *

በጋ አለመሆኑ ደስታችንን ቢቀንሰውም ግር! ብሎ በሚነደው የግንዲላ እሳት ብርዱን ተቋቁመነዋል። ፕሪቶሪያ ባልነበርኩባቸው ስምንት ወራት ስለመፅሃፌ የተወራውን እያጫወቱኝና እየተረቡኝ፣ ከጣራ በላይ መሳቅ ይዘናል።

"ልጠይቅህ" ሲል አቋረጠ አብይ፣"... የናይሮቢው ትረካ ላይ ዱባለ ብለህ የገለፅከው ማንን ነው?"

"ዱባለን ነዋ!"

"እዚህ ግን ዳዊት ራስታ ነው ተብሎ ተወርቶአል"

ፋሲል አቋረጠ፣

"የራስታውን ተወው! ብቻዬን ያሳቀኝን ለምን





አልነግርህም? ነልስፕሪት ላይ የታሰራችሁ ጊዜ...እብድ ነኝ ብሎ መርፌ ሲወጋ የሰነበተው ከበደ...ፊነዳሁ ነው የሚባለው..."

በሃይሉ ጣልቃ ገባ፣

"በረከትን ግን ጨከንክበት! ገብርኤልን! በሽታውን ትናገርበታለህ እንዴ? በንዴት ቢብሰበትስ? ሰው ልታስፈጅ ነው እንዴ? ነርሷ ደሞ ወሬውን ሰምታ በጣም ደነገጠች። የምር ዘመድህ መስሎአት ነውኮ የነገረችህ..."

መስፍን መላጣው እንዲህ አለኝ፣

"እኔን ያሳቀኝን ለምን አልነግርህም? ሲያትል ላይ ቺክህን ሊነጥቅህ የመጣው ክልሱ ሰውዬ...አንተ ግን ትእግስተኛ ነህ... እኔ ብሆን የወተት ቱቦውን ነበር የምዘጋለት... በገዛ ቺክህ ቆመህ ትከራከራለህ እንዴ?"

ዳዊት ራስታ ዝምታ በማብዛቱ በወሬ ቆሰቆስኩት። አስመጪና ላኪ ነጋዴ ነው። ፕሪቶሪያ ላይ ራሱን እንደ ቀዳሚ ፖለቲከኛ ቢቆጥርም፣ ይበልጥ የሚታወቀው የተቸገሩ ሃበሾችን በመርዳት ሲሆን፣ በተጨማሪ በበአላት ቀናት የቅርጫ ስጋ በማዘጋጀት፣ አበሻነታችንን ያስታውሰናል። ካዲሳባ ያስመጣቸው ጥቋቁር ቢላዎች አሉት። ለቢላዎቹ የቆዳ መያዥያ አስፍቶላቸዋል። በሬው በሚታረድበት እለትም እንደ ሽጉጥ ሲታጠቃቸው ፊታውራሪ ቁሲ ዲነግዴን ይመስላል።

ዳዊት ራስታ አስመጪና ላኪ ነው።

ከአዲሳባ የማያስመጣው ነገር የለውም። ቦሶ፣ ቅቤ፣ ቆሎ፣ ጭኮ፣ አዋዜ፣ ሽሮ፣ በርበሬ፣ ሚጥሚጣ፣ ምጣድ፣ ረከቦት፣ ላቀች ምድጃ፣ እጣን ማጤሻ፣ ጀበና፣ የጀበና ማስቀመጫ፣ ምን ይህ ብቻ? ጥበብ ልብስ፣ ተነፋነፍ፣ የቆዳ ጃኬት፣ የቆዳ ቀበቶ፣ የቅዱሳን ስእል እና የኩሶ መድሃኒት ሳይቀር ያስመጣል። ማስመጣት ብቻ ሳይሆን ገንዘብ እየተቀበለ አበሾችን ወደ አውሮፓና አሜሪካ ይልካል። አስመጪና ላኪ ነው።

ቤቱ ከጋበዘህ እንዲህ ይልሃል፣

"በሃገር ቤት ቅቤ የተሰራ ክትፎ ነው - ብላ! በሃገር ቤት ቅመም የተፈላ ሻይ ነው - ጠጣ! የትራስ ልብሱ ከሃገር ቤት የመጣ ነው - ተንተራስ! የባህል ዘፈን አለኝ - አዳምጥ! ካዲሳባ ዛሬ የገባ ጫት ነው - ቃም! ዛሬ ካገር ቤት የመጣች ዘመዴ ናት - ተዋወቃት!"

ዛሬ ዝምታው ሲበዛብኝ በወሬ ቆሰቆስኩት፣

"ሃገር ቤት ደርሰህ መመለስህን ሰማሁ..."

"ሄጄ ነበር" አለ ባለመደሰት ስሜት፣ "ቤት መስሪያ መሬት ይሰጣል' ብለውኝ እዚህ ኤምባሲ ተመዝግቤ ነበር። 'አባል ሆነሃል' አሉኝ። ፎርም አስሞልተው አስፈረሙኝ። 'መዋጮ ክፈል' አሉኝ። ከፈልኩ። 'አንዳንድ መረጃዎችንም አምጣ' አሉኝ። 'እኔ አቃጣሪ አይደለሁም' አልኳቸው። ሆኖም 'መሬቱን ታገኛለህ' አሉኝና አዲሳባ ሄድኩ። እንኳን ለቤት መስሪያ ለመቃብር የሚሆንም አላየን። ቀዳዳዎች! ትግሬ ካልሆንክ መሬት ማግኘት አይቻልም..."

"የምን አባል ነው ያደረጉህ?" ስል ጠየቅሁት።

"ምናቃለሁ! ሙላ ሲሉኝ ፎርሙን ሞላሁ! መሬት የሚሰጡኝ መስሎኝ ነበር..."

ይህን ጊዜ ደምሴ ፖለቲከኛው፣

"የወያኔ አባል መሆንህን ራስህ አረጋገጥክ" አለው።

"የወያኔ አባል አይደለሁም"

"ፎርም ሞላሁ አላልክም? ፎርሙ የአባልነት ነው"

"ቤት መስሪያ መሬት ለማግኘት ነዋ! አንተ ሰውዬ! እኔን መከታተል ብታቋርጥ ይሻልሃል። ገገማ ጎንደሬ!"

"ገገማ መሆኔን ለኔ ተወው። ስለ ጎንደሬነቴም እኮራበታለሁ። የአፄ ቴዎድሮስ ዘመድ ነኝ። ይሄን እንተወውና ወያኔ መሆንህን ግን እዚሁ ላስረዳህ። ባለፈው የግንቦት 20 በአላቸውን ኤምባሲ ውስጥ ሲያከብሩ በአሉ ላይ ተገኝተህ አልነበረም?"

እንደገና በገነፈለ ድምፅ ምላሽ ሰጠ፣

"ብገኝስ ታዲያ? ተጠርቼ ነው የሄድኩት። ሳልጠራ ልቀላወጥ አልሄድኩም። አንተስ ብትሆን ብትጠራ አትሄድም?"

"እኔማ ተቃዋሚ ነኝ! የኢትዮጵያ ጠላቶች ድግስ ላይ አልገኝም። የግንቦት 20 በአል ላይ የሚገኝ ወያኔ ብቻ ነው..."

"የብዙ አገር አምባሳደሮች ግብዣው ላይ ተገኝተዋል። እነሱ ሁሉ ወያኔዎች ናቸው?" እያያዘና እንዲህ ሲል አስጠነቀቀው፣ "... እኔን ወያኔ እያልክ መናገርህን ብታቆም ይሻልሃል። አንተ ፖለቲካ ሳትጀምር እኔ ተቃዋሚ የነበርኩ ሰው ነኝ። ገባህ? አንተ ዛሬ መጥተህ እኔን ወያኔ ትላለህ? ተወኝ ብዬሃለሁ ተወኝ። ከንግዲህ ስለኔ ስታወራ ብሰማህ ገብርኤልን





ቢላ ነው የምሰካብህ..."

"ቢላውን ተወው። በአፍህ ቢላ ያልሰካህበት ሰው የለም"

"ገብርኤልን ብያለሁ። ወደ ሰይጣን ስራ አታስገባኝ። እልህ አታስይዘኝ" አለ ራስታውን እየናጠ "... አንተን ወግቼ እስር ቤት ብገባ ጉቦ ከፍዬ እወጣለሁ። እልህ አታስይዘኝ..."

* * *

ፕሪቶሪያ በደጋግ ሰዎች የተሞላች ናት።

"ፈቃዱ በረዳ" እና "ደምሴ ፖለቲከኛው" ቀዳሚዎቹ ደግ ልብ ያላቸው ሃበሾች ናቸው። ፈቃዱ በረዳ ራሱን የሁሉም ጓደኛ አድርጎ ይቀርባል። ስለዚህ እኔም ጓደኛው ነኝ። ደምሴ ብዙም አይቀርበኝም ነበር። "የጋዜጠኛው ማስታወሻ" ግን አቀራረበን። በዚያን ቀንም እንዲህ አለኝ፣

"'...መፅሃፍህን ከማንበቤ በፊት በጣም ነበር የምጠላህ። 'ትግሬ ነገር ነህ!' ብዬ አስብ ነበር። 'ትግሬ ነገር' ስል ትምክህት እንዳይመስልህ። እኔ የጎንደር ልጅ እንደመሆኔ በአጤ ቴዎድሮስ አስተሳሰብ ተኮትኩቼ ያደግሁ ነኝ። የኢሜይል አድራሻዬም ethiod3000@yahoo.com ነው። ትርጉሙ ምን መሰለህ? 'ethio' ማለት 'ኢትዮጵያ' ማለት ነው። 'd' ደግሞ 'ደምሴ' የኔ ስም ነው። 3000 የሚለው ደግሞ ኢትዮጵያ የ3000 አመት የነፃነት ታሪክ እንዳላት ያመለክታል። ለማንኛውም ብቻችን ከተገናኘን ብዙ የማጫውትህ የአገር ጉዳይ ቁም ነገሮች አሉ..." እናም በሰፊው ልንጨዋወት ቀጠሮ ያዝን።

ደምሴ ባለ ትዳርና የሁለት ልጆች አባት ሲሆን፣ ከUN በሚያገኘው ድጎማ ኑሮውን ይመራል። በፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ንቁ ተሳታፊ በመሆኑ "ፖለቲከኛው" የሚል ቅፅል ተጨምሮለታል። በግልባጩ ፈቃዱ በረዳ ፖለቲካ ውስጥ የለበትም። ስራም ሆነ የገቢ ምንጭ የለውም። የፍቂ ችግር ስራ አይወድም። የሰነፍ የበኩር ልጅ ነው። ከዚህም ከዚያም እየቃረመ ይውላል። የሚሰሩትን እያሳሳቀ፣ እየተረበ፣ እያጀበ ሳንቲም እየፈለጠ የስደቱን አለም ይገፋዋል። ቱጃር ከተባሉ ስደተኞች እኩል እየበላ፣ እየጠጣ፣ እየቃመ፣ እየለበሰ፣ እየጠበሰ እድሜውን አገባዶአል። አንዱ ሲሰለቸው ሌላው ዘንድ ሄዶ

ይጠጋል። በዚህም በዚያም ብሎ አለታዊ ጉርስ፣ ሳምንታዊ ጥብስ(ቺክ)፣ አመታዊ ልብስ አያጣም። አንዱን ሲያማ፣ ሌላውን ሲቦጨቅ፣ አንዳንዴ ቡጢ ያቀምሱታል። እንዲያም ሆኖ አያርፍም። ሲበዛ ግን፣

"ፍቄ አልበዛም እንዴ?" ማለት ያለ ነው።

በዚያው ሰሞን በቁም ነገር መጥቶ እንዲህ አለኝ፣

"አንድ ነገር ላማክርህ ነበር"

"ምንድነው?"

"በርግጥ ለሰው የሚነገር አይደለም። አንተ ግን የበሰልክ ሰው ስለሆንክ፣ ብነግርህ ችግር የለውም.."

ድፍን ፕሪቶሪያ ላይ፣ "አንተ የበሰልክ ሰው ነህ!" ያልተባለ አንድም ተፈልጎ አይገኝም። በመሆኑም ለምደነዋል። እንደተለመደው ራሴን ላይ ታች በመነቅነቅ የበሰልኩ መሆኔን ተቀበልኩ።

"እኔ አንድ ችግር አለብኝ" ሲል ተንደረደረ፣ "...ችግሬ የፍቅር ጉዳይ ነው። ምን መሰለህ? ቆንጆ ሴት ባየሁ ቁጥር ወዲያው ፍቅር ይይዘኛል። እዚህ ፕሪቶሪያ ላይ ብቻ፣ 'አግቢኝ' ወይም 'እወድሻለሁ' ያልኳቸው ሴቶች ቁጥር ተወው። 'ፍቅር አንድ ጊዜ ነው' የሚባለው ለምን እኔ ላይ ሳይሰራ ቀረ? ከእህትማማቾች ጋር ጭምር እኩል ከሁለቱም ጋር ፍቅር ይዞኝ ያውቃል። እጄ ላይ ያለውን ትቼ ሁልጊዜ ሌላ ያምረኛል። ይሄ ጤንነት ነው ወይ? ምን ሆኛለሁ? ለምን እንደዚያ ሆንኩ? እስኪ ችግሬን ከነመፍትሄው ንገረኝ?"

"አትስጋ! የብዙ ሰው ችግር ነው" አልኩት።

"እንዴት?"

"በእጁ ያለውን ትቶ፣ ሌላ የሚያምረው ይበዛል..."

"የኔ አይነት ሰው ሊኖር አይችልም" ሲል ተሟገተ።

"በምን አወቅህ ሊኖር እንደማይችል?"

"ጓደኞቼ አብዛኞቹ ጨዋ ባለትዳሮች ናቸው። አንድ አግብተው የወለዱ፣ ትዳራቸውን የሚያከብሩ ናቸው"

"አሁን ምኑ ነው ያስጨነቀህ?"

"በአንድ መርጋት ያልቻልሁት ምን ሆኜ ነው?"

"እድሜህ ስንት ሆነ?" ስል ጠየቅሁት፣

"47"

"ለመሞት ምን ያህል ጊዜ ቀረህ?"





"እንዴት አውቃለሁ? ምን አይነት ጥያቄ ነው?"

"በግምት ሃያ አመት ቀርቶሃል እንበል። ከሃያው ደግሞ ግማሹን ተኝተህ ስለምታሳልፈው የቀረህ አስር አመት ብቻ ነው። አትጨነቅ! እንደ ተፈጥሮህ ኑርና ከዚያ ትሞታለህ..."

በመከፋት ተከዞ ጥቂት ቆየ። እናም እንዲህ አለኝ፣

"ይሄ ምክር አይደለም። ስድብ ነው። እዚህ ውስጥ ስለ ሞት ምናመጣው? እኔ ስለምሞትበት ቀን... እሱን ማን ጠየቀህ? 'በአስር አመት ውስጥ ትሞታለህ?' ... ምን ለማለት ነው?"

ፊቃዱ በረዳ ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደ ሽንት ቤት ሄደ። ሲመለስ የኔን ጠረጴዛ ተወና አለፍ ብሎ ብቻውን ተቀመጠ። ዝም አልኩት። የ🙤 ዝምታ ይበልጥ አበሳጨው መሰለኝ እንደገና ማልጎምጎም ጀመረ፣

"ራስህን ግደል የማለት ያህል ነው ንግግርህ!" አለኝ።

"እኔ ራስህን ግደል አላልኩህም"

"ለመሞት አስር አመት ነው የቀረህ ብለሃል። አንተ ምን ታውቃለህ? ጠንቋይ ነህ? HIV Positive ለሆነ ሰው እንኳ እንዲህ አይባልም። ይሄ ጭካኔ ነው። ድሮውንስ ከወያኔ ምን ይጠበቃል? ወያኔ ስትባሉ መግደል! ነው የምታቁት። በገደላችሁ መጠን ማእረግ ሲሰጣችሁ መግደል!"

"ራስህን ግደል አላልኩህም። ከፈለክ ግን መብትህ ነው"

"ለምንድነው ራሴን የምገድለው?" ሲል በቁጣ መለሰ። "...ጤነኛ ወጣት ነኝ። ሰርቼ ህይወቴን ለውጬ፣ ትዳር መስርቼ፣ ልጆች ለማፍራት ጊዜው አላለፈብኝም። ለምንድነው ተስፋ የሚያስቆርጥ ንግግር የምትናገረው?"

"ስደቱ ከሞት አይሻልም ብዬ ነው"

"ላንተ ከሞት ካልተሻለ የራስህ ጉዳይ! እኔን አንተ ውስጥ አትጨምረኝ! እንዴት ያለ ነገር ነው?"

ስለ ሰለቸኝ እንዲህ አልኩት፣

"አሁን አትጨቅጭቀኝ! ሂድና ሌላ ሰው ምክር ጠይቅ"

ሊለቀኝ ግን አልቻለም።

"ምክር የጠየቅሁህ አክብሬህ ነበር። አንተ ግን ክብር አታውቅም። ሰው አዋቂ ነው ብሎ ምክር ሲጠይቅህ እንደዚህ ነው የምታነጋግረው? አበሻ ነን። ባህል አለን። በእድሜም ታላቅህ ነኝ።"

ከተቀመጥኩበት ተነሳሁና ደጃፉ ላይ ወዳሉት ወንበሮች

ላይ ሄጄ ተቀመጥኩ። ያልጨረስኩት አንድ መፅሄት እጄ ላይ ነበርና እሱን ማንበብ ቀጠልኩ። ፈቃዱ በረዳ ወደኔ መጣና ተንጎራደደብኝ። እየተንጎራደደም እንዲህ ይለኝ ያዘ፣

"የኛ ደራሲ!? ወያኔዎች ስትባሉ ፍቅር መቼ ታውቁና? ሁላችንም ሞተን ብናልቅላችሁ ምኞታችሁ ነበር። የኛ ነፃ አውጪዎች! የነፃነትን ትርጉም የት ታውቁትና!? ፋሺስት ባንዳ ሁላ! ደራሲ ነህ ብዬ ባማክርህ...ትንሽ እንኳ ትህትና አይሰማህም? ለነገሩ ትግሬ ብሎ ደራሲ!"

ማንበቡን አቆምኩና ቁራጭ ወረቀት አውጥቼ መጫጫር ጀመርኩ። ፈቃዱ እየተንጎራደደ የቻለውን ያህል ካሽከመኝ በሁዋላ ደከመውና ወንበር ስቦ አረፍ አለ። ገባ ወጣ የሚሉትን አበሾች እያስቆመም 'ራስህን ግደል' ስል የሰጠሁትን ምክር እየገለፀላቸው አረመኔነቴን ሊያስረዳቸው ሙከራ አድርጎ ነበር። ብዙዎቹ አልሰሙትም። እየሳቁ እጃቸውን በግድ እያስለቀቁት ጥለውት ወጡ። ደጋፊ ሲያጣ እንደገና ወደኔ ዞረ፣

"ትንሽ አታፍሩም ደግሞ ስማችሁን ታጋይ ትላላችሁ። እረኛ ሁላ! እናውቃችሁዋለን!! ለሴትና ለገንዘብ ሩጫ! ገና ከመግባታችሁ ቤት! መኪና! ገንዘብ! መጥኔ ለዚች አገር! ዘረኞች! አንተ ራስህ ዘር ከልጓም ስቦህ የተንቀጠቀጠ ተራራ እያልክ ስትክባቸው አልነበረም? ከስልጣን ሲያባርሩህ ደግሞ እነሱን የሚያወግዝ መፅሃፍ ፃፍክ! አንተ እንደ ሱፍ አበባ ፀሃይ እያየህ በተገለበጥክ ቁጥር እኛም አብረን እየተገለበጥን ያንተን መፅሃፍ ማንበብ አለብን?"

"ከዚህ በላይ ከተሳደብክ ለፖሊስ እደውላለሁ" አልኩት።

"ፖሊስ!?" የሹፈት ሳቅ ሳቀ። "ተመስገን! እናንተም ፖሊስ አውቃችሁ! እዚህ ህግ ያለበት ሃገር ነዋ! እንደለመዳችሁት ስልክ ደውሎ ማሳሰር እዚህ አይሰራም..."

ቢቸግረኝ መጫጫሬን አቋርጬ ለመንኩት።

"ስራ እየሰራሁ ስለሆነ እባክህ አትረብሸኝ?"

"ምን ስራ አለህ አንተ? እኛ የምንናገረውን እየለቀምክ መፃፍ ነው ስራህ። ስራ ሰጠሁህ እንጂ መቼ ረበሽኩህ? እንደ ደንቡማ ልትጋብዘኝ በተገባ። አንተ ግን ለራስህ ቢራ እየቀዳህ፣ የኔን ወሬ ደግሞ በነፃ ትቀዳለህ..."

መልስ ሳልሰጠው መፃፌን በመቀጠሌ፣

"እኔ የተናገርኩትን እየፃፍክ ነው? ቾክቾክ! ለማኝ ሳያራ





ተነስተህ ለኤምባሲ ሄደህ ስጥ! ጆሮ ጠቢ ሁላ! የፈለከውን ፃፍ! የምፈራ መሰለህ? ልጨምርልህ ከፈለክህ? መለስ ዜናዊን 'ተዘቅዘቅ!' በለው። ፃፍ ይሄን! ፅፈህ ስትጨርስ ከስሩ እፈርምልሃለሁ። የት ሄደን እንኑርላችሁ? ተሰደንም መኖር አንችልም? ለመሆኑ እግዚአብሄር በህይወት አለ?"

"ለምን የሆነ ነገር አትጠጣም?" አልኩት።

"ብጠጣ ባልጠጣ ምናገባህ?"

"አትግደርደር! ያዝ የሆነ ነገር..."

"ያንተ ግብዣ ባፍንጫዬ ይውጣ"

አስተናጋጇን ጠራሁዋትና ሄይኒከን ቢራ እንድታመጣለት አዘዝኳት። ተነሰሁናም የፍቄን ጠረጴዛ ተጋራሁት። ምንም አላለ። ቢራው እንደመጣ ቃል ሳይተነፍስ ተቀብሎ በአንድ ትንፋሽ ግማሽ አደረሰው።

"ዛሬ ተሳዳቢ ወጥቶሃል" አልኩት።

መልስ ሳይሰጠኝ ደጅ ደጁን ማየት ያዘ፣

"ምን ሆነህ ነው?" ስል ጠየቅሁት።

"አይመለከትህም" አለ በደከመ ድምፅ።

"ንገረኝ? ምን ሆነሃል?"

ዘግየት ብሎ እንዲህ አለ፣

"ብሶት ነው" አያያዘና ጨመረበት "...አንዳንድ ጊዜ በህይወት መኖር የሚያስጠላኝ ቀን አለ..."

"ምሳ በልተሃል?"

"አርፍጄ ነው ቁርስ የበላሁት። አልራበኝም።"

* * *

በቀጠሮአችን መሰረት ከደምሴ ፖለቲከኛው ጋር ተገናኘን። በርግጥ ቀጠሮውን የተቀበልኩት ተገድጄ ነው ማለት ይቻላል። ደምሴ አስቸጋሪ ሰው መሆኑን አውቃለሁ። የፖለቲካ ወሬ ማውራት ከጀመረ ማቆሚያ ስለማይኖረው ብዙዎች በቆመበት ጥለውት ይሄዳሉ። 'ይናገራል እንጂ አያዳምጥም' እያሉ ያሙታል። እሱ ግን ይህን አይቀበልም። 'በድፍን ደቡብ አፍሪቃ ከኔ የተሻለ የፖለቲካ ሰው የለም' ብሎ ደምድሞአል። የኢትዮጵያ የችግር ቋጥኞች ሁሉ ጫንቃው ላይ የወደቀበት ይመስል ጎብጦ ነው የሚራመድ። በኢትዮጵያ ባንዴራ የተንቆጠቆጠች የአንገት ልብስ ከአንገቱ አይለይም። ፖለቲከኛ

የመሆኑ መገለጫ ነው፣

"ቢሮ ክፈትና ባንዴራውን በሩ ላይ ስቀል። በየቀኑ ባንዲራ ለብሰህ መዞር ግን ጅላጅል ያስመስልሃል" ተብሎ ቢመከርም አልሰማ አለ። አንገት ልብሱን እንደ ጋብቻ ቀለበት ከአንገቱ አይለያትም። በዚህ ምክንያት፣ "እብዱ ፖለቲከኛ" የሚሉትም አሉ። እብድ ግን አይደለም። ደምሴ እንደሚተርቡት አይነት ሰው አልነበረም። ለራሱ ክብር ያለው ሙሉ ሰው ነው። ስለዚህ በቁምነገር ሲቀጥረኝ ቀጠሮውን መቀበሉን መረጥኩ።

እኩል ቀን ላይ Spur ከተባለ ምግብ ቤት ተገናኘተን ምግብና ቢራ አዘዝን። እንደጠበቅሁትም ደምሴ ለመናገር ብቻ ነበር ተዘጋጅቶ የመጣው። እኔም የማዳመጥ ትእግስትና ችሎታ ስላለኝ፣ ግጭት እንደማንፈጥር ርግጠኛ ነበርኩ። እናም ያችን እለት ለደምሴ ሰዋሁዋት፣

"...በጣም እጠላህ ነበር።" ሲል ጀመረ፣ "...እዚህ አራት አመት አብረን ስንኖር፣ ካንተ ጋር ባንድ ጠረጴዛ ቁጭ ልል ቀርቶ ሳይህ ራሱ ታስጠላኝ ነበር። መፅሃፍህን ካነበብኩ በሁዋላ ግን መሳሳቴን አወቅሁ። ድረገፆቻችንን ሁሉ ተከታትዬአለሁ። አብርሃ በላይ ብቻ ነው በተቃራኒ የቆመው። መቼም ያው እሱ ትግሬ ነው። ማለቴ የነስዬ ደጋፊ ነኝ ይላል። አቋሙ ግን አይታወቅም። አንተ ላይ ጠላት የሆነብህ ግን ስለነካኸው ይመስለኛል..."

"ልጆችህ እየተማሩ ነው?" ስል ጠየቅሁት።

በኩራት ነበር ምላሽ የሰጠኝ፣

"ኮትኩቼ እያሳደግሁዋቸው ነው። ጎበዝ ተማሪዎች ሆነዋል። ኢትዮጵያዊነታቸውን እንዲያውቁ አድርጌያቸዋለሁ። እንግሊዝኛቸውን ተወው። አማርኛ አይችሉም። ቤት ውስጥ ከኔ ጋር በእንግሊዝኛ ስለምናወራ እናታቸው ጠጣ ሆናለች። እንግሊዛውያን ቤት የገባች እስኪመስላት..."

የስላቅ ፈገግታ ስላሳየሁት ሊያስተባብል ሞከረ፣

"...እንግሊዝኛ ብቻ ማወቃቸው የኔ ጥፋት አይደለም። ከአቅም በላይ ሆኖብን ነው። እዚህ ጠንካራ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ የለንም። ቤት ውስጥ ባማርኛ እንዲናገሩ ሞክረናቸው አልሆነም። ቢሆንም የኢትዮጵያን የፖለቲካ ሁኔታ እንዲያውቁ አድርጌያለሁ። ሁለቱም ልጆቼ መለስ ዜናዊን ሲጠሉት አይተህ





አታውቅም። ወንዱ ልጄ በተለይ እንዴት አንበሳ መሰለህ? ስእል መሳል ይችላል። መለስ ዜናዊን ቂንድ ሰርቶለት እራሱን ቁጭ ነው ያረገው፤ ቅንድቡን በተለይ። ፒዛ ገዛሁለት ያን ቀን። የአንበሳ ልጅ አንበሳ መሆን ይገባዋል..."

እየተመገብን ሳለ እንዲህ ሲል አጫወተኝ፣

"...ያንተን መፅሃፍ ሳነብ ነው ስለ በረከት ስምኦን ማወቅ የቻልኩት። እንደዚህ አይነት ተኩላ ኖሮአል? ኢንተርኔት ገባሁና google, Image ላይ ገብቼ ፎቶግራፉን አገኘሁ። ማታ ወስጄ ለልጄ ሰጠሁት። 'ማነው ይሄ?' አለኝ፣ 'ሌላ ጭራቅ' አልኩት። አታምነኝም። ለበረከት ደግሞ ጭራ ሰርቶለት የሚያስቅ አድርጐ ሳለው። አንበሳ! የአንበሳ ልጅ!"

ኮረሪማ የመሰለች ቦርጩን እያንቀጠቀጠ ብቻውን ስቆ ሲያበቃ እንዲህ ሲል አከለበት፣

"ያን ቀንም ለልጄ ፒዛ ገዛሁለት። ከእህቱ ጋር ተካፍለው በሉት"

ልተኛ ምንም አልቀረኝም።

አይኖቼ እንባ አቀረሩ። አዛጋሁ። በሁለት እጆቼ አፌን ሸፍኜ እንደ ጉማሬ አዛጋሁ። እንደገና ደግሞ እንደ ውሻ አፌን ከፍቼ ደምሴን ልጎርሰው ጥቂት ቀረኝ። ደምሴ ንግግሩን አቋረጠና፣

"አሰለቸሁህ እንዴ?" ሲል ጠየቀኝ።

"የለም! ትናንት በበቂ ስላልተኛሁ ነው። ቮድካ ከጠጣሁ ይለቀኛል" አልኩና አስተናጋጁን ጠራሁ።

በዚያን እለት ከደምሴ ጋር ብዙ ርእሰ ጉዳዮችን እያነሳን አወጋን። ከአንዱ ርእስ ወደ ሌላው እንዴት እንደምንዘል ግልፅ አልነበረም። የጀመርነውን ሳንቋጭ ወደ ሌላው እየነጠርን፣ መያዥያ መጨበጫ በሌላቸው ርእሰ ጉዳዮች ላይ ወጋችን ቀጠለ። እንዲህ ሲል ጠየቀኝ፣

"በየነ ጴጥሮስ ጆሃንስበርግ የመጣ ጊዜ ትዝ ይልሃል?"

"ትዝ ይለኛል"

"አንድ ታሪክ ላጫውትህ። ዶክተር በየነ የተቃዋሚ አባላትን ሰብስቦን ንግግር ሲያደርግ ተሰብሳቢው ሁሉ ተሰላችቶ ነበር። የዶክተር በየነ ንግግር አብቅቶ ወደ ውይይት ስንገባ፣ በቅድሚያ እጄን አወጣሁና ንግግር ሳደርግ ልነግርህ አልችልም፣ ጭብጨባው ቀለጠ! የህዝቡን ስሜት ማመን

አትችልም። በተፈነቀለ ስሜት፣ አነጐደው ጭብጨባውን! እኔ ጥሩ የንግግር ችሎታ አለኝ..."

"ምን ብለህ ተናግረህ ነው ያጨበጨቡልህ?"

ደምሴ ጥቂት እንደ ማሰብ ብሎ ማብራሪያውን ቀጠለ፣

"ምናልኩ መሰለህ? 'ለኢትዮጵያ ህዝብ ለመታገል ፕሮፌሰር መሆን አለብን? ባለ መኪና መሆን አለብን? ሃብት ማለትስ ምንድነው? ሃብት በሶስት ይከፈላል። መንፈሳዊ ሃብት አለ፣ የገንዘብ ሃብት አለ፣ የአእምሮ ሃብት አለ። ስለዚህ እኛ የአእምሮ ሃብት ያለን፣ ባለ ማእረግ፣ ባለ መኪናና ባለ ሱቅ ባለመሆናችን ከትግሉ ልንገለል አይገባም' ብዬ ስናገር ተወኝ ወንድሜ! ጭብጨባው!"

ወጋችን እንዲሁ ቀጠለ፣

"ቅንጅቶች ከእስር የተፈቱ ጊዜ ወደዚህ የመጣው ቡድን በሻለቃ መንግስቴ ይመራ እንደነበር ትዝ ይልሃል?"

"ትዝ ይለኛል"

"ምን ብዬ ተናገርኩ መሰለህ? 'ቅንጅቶች!' አልኩ፣'አሁን ከእስር ተፈታችሁዋል። እቅዳችሁ ምንድነው?' ሻለቃ መንግስቴ ምላሽ ሰጡኝ፣ 'ቀዳሚ ተግባራችን ገና ያልተፈቱ የቅንጅት አባላትን ከእስር ማስፈታት ነው' አሉ። እኔም ፈጣን ተቃውሞ አቀረብኩ። 'ለምን ስለቅንጅት አባላት ብቻ ታስባላችሁ? የኢትዮጵያዊነት መንፈስ ሊኖራችሁ ይገባል። ፍትህ በጐደለው ሁኔታ ስለታሰሩ ኢትዮጵያውያን ሁሉ መታገል አለባችሁ' ብዬ ስናገር ጭብጨባውን ተወው! ሻለቃ መንግስቴ ብልህ ናቸው። 'ደምሴ' አሉኝ '...አንተ ያለጊዜህ ቀድመህ የተወለድክ ነህ። የረሳነውን ነው ያስታወስከን' ብለው መዘገቡት። ሻለቃውን አከበርኳቸው። 'ያለጊዜህ ቀድመህ የተወለድክ ነህ' ያሉኝ ልክ ነበር። በጣም ልክ ናቸው..."

እንደገና ፈገግ በማለቱ ደምሴ እንዲህ ሲል አከለበት፣

"አንተም እኮ ያለጊዜህ ቀድመህ ነው የተወለድከው። እኔም ሆንኩ አንተ ከህብረተሰቡ ቀድመን የበሰልን ሰዎች ነን። አፄ ቴዎድሮስም በዘመናቸው ተመሳሳይ ችግር ገጥሞአቸው ነበር። ልክ እንደዚያ ማለት ነው..."

* * *





ፈቃዱ በረዳ የህፃናት አምባ ልጅ በመሆኑ የልጅነት ትዝታዎቹ ሁሉ ከመንግስቱ ሃይለማርያም ጋር የተቆራኙ ነው። ከዚያ ሊያመልጥ አይችልም። ጓድ ሊቀመንበር፣ ጓድ ለገሰ የሚሉ ስሞችን በቀን አንድ ጊዜ ሳያነሳ አያልፍም።

ዘወትር እንዲህ ሲል ይፎክራል፣

"የአብዮታዊት ህፃናት አምባ ልጅ መሆኔን አትርሱ። የጓድ መንግስቱ ልጆች በመሆናችን ዝንባችንን የሚነካ አልነበረም..."

"ዝንባም ነበራችሁ ማለት ነው?" ሲል ቀለደበት አንዱ።

"አባባል አይገባህም? ዝንብ ስል ዝንብ ማለት መስሎህ ነው? አይደለም። አማርኛ አታውቅም?"

ስለመፅሃፌ አስተያየት ሲሰጠኝም ስለ "ጓድ ለገሰ አስፋው" ማንሳቱ አልቀረም፣

"...አለፍ አለፍ እያልኩ አንብቤው ነበር። ጓድ ለገሰ አስፋውን ድንጋይ ብለሃቸዋል። ተሳስተሃል። በአብዮታዊት ኢትዮጵያ ህፃናት አምባ ካደጉ ልጆች አንዱ እንደመሆኔ ጓድ ለገሰና ጓድ መንግስቱ ለኛ አባታችን ማለት ናቸው። አንተ ድንጋይ አልካቸው። ድንጋይ ማን እንደሆነ ልንገርህ? ታምራት ላይኔ ነው።"

"ታምራት ምናደረገ?" ስል ጠየቅሁት።

"እሱ አይደል እንዴ ህፃናት አምባ ድረስ መጥቶ የበተነን። ወያኔዎች አዲሳባ ከገቡ በሁዋላ መጀመሪያ መጥቶ ሰብስቦ ያነጋገረን ታምራት ነው..."

ትረካውን አቋርጦ እንዲህ ሲል ጠየቀኝ።

"ቢራ ልድገም?"

"ድገም"

ወዲያው ከተቀመጠበት ተነሳና አንድ ሄይኒከን ይዞ ተመለሰና ትረካውን ቀጠለ።

"ታምራት ላይኔ መጣና፣ 'ህፃናት አምባን ለሌላ ጉዳይ ስለምንፈልገው እናት ያላችሁ ወደ እናታችሁ ሂዱ። እናት የሌላችሁ ደግሞ ወደተወለዳችሁበት ቀበሌ ሂዱና በቀበሌ በኩል ርዳታ ይደረግላችሁዋል' አለን። በዚህ ጊዜ አንድ ደፋር የአምቦ ልጅ ተነስቶ ታምራት ላይኔን ምን አለው መሰለህ?

"ነፍሱ!" አለው ታምራትን፣ "...ነፍሱ! እኛ የጓድ መንግስቱ ልጆች ነን። ማንም ደፍሮ ቀና ብሎ አያየንም።

ስንመገብ እንኳ ምግብ ቤት ውስጥ የጓድ መንግስቱ ፎቶግራፍ ስለተሰቀለ፣ እንደፈለግን ወጥና እንጀራ እያስጨመርን ነው የምንበላው። እናንተም ብትሆኑ ቀና ብላችሁ ልታዩን አትችሉም' የአምቦው ልጅ እንዲህ ሲናገር ጭብጨባውን አቀለጥነው..."

ጠጉሬን ቆፍሬ ስስቅበት በፍቃዱ በስሜት ቀጠለ፣

"...ምን ያስቅሃል? የዋሸሁ መስሎህ ነው? ታምራት ምን አለን መሰለህ? 'ጓድ መንግስቱ ጥለዋችሁ ሸሽተዋል። እሳቸው መሸሻቸውም ለናንተ ጥሩ ነው። ምክንያቱም ባይሸሹ ኖሮ ወታደር አድርገው ያስፈጁችሁ ነበር' ብሎ ሊያታልለን ሞከረ። እኛ በተቃውሞ ጮህን። እሱን ሄዶ ላክስቱ አይነግራትም? ወያኔ ባይመጣ ኖሮ ኩባ ሄደን ዩኒቨርሲቲ እንማር ነበር..."

* * *

ህይወት እንዲሁ ቀጠለ።

ከስራ መልስ በሚነድ እሳት ዙሪያ እንኮለኮላለን። ክረምት አይመስልም። የእሳቱ ነበልባል ጉማጅ ግንዲላዎችን እየቀረጣጠፈ ይበላቸዋል።

በፕሪቶሪያ ሃበሾች ዘንድ በጥሩ ጠባዩ የሚታወቀው ሳሚ መጠጥ ቤት ውስጥ ሃበሾች ከሌላ ዜጋ ጋር ፀብ ካነሱ ምንጊዜም ወደ ፀቡ ተሽቀዳድሞ ይገባል። ለድብድብ የሚመች ግዙፍ ሰውነት አለው። ሃበሻ ለሃበሻ ሲጣላ ካየ ደግሞ ቀዳሚው ተወርዋሪ ገላጋይ እሱ ነው። ለተደባደቡ በማገዝና በመገላገል ሂደት በደረሰበት አደጋ ምክንያት የጠባሳ አይነቶች ገፅታውን አሳምረውታል። ከሁለት አመታት በፊት ሳሚ በቁም ነገር ጠርቶኝ እንዲህ ሲል መክሮኝ ነበር፣

"ሃበሾች ድብድብ ሲያነሱ ብዙ ጊዜ ስትሸሽ ነው የማይህ? ይሄ ልክ አይደለም። ሃበሾች ከታንዛንያውያን ጋር ሲጋጩ ማገዝ ግዴታህ ነው። ትናንት ግን ገና ፀብ ሲጀመር በጓሮ በኩል ወጥተህ ሄድክ..."

"እኔ ድብድብ አልወድም" አልኩ።

በዚህ ንግግሬ ሳሚ ክፉኛ ተበሳጨ፣

"ምን ማለትህ ነው? ድብድብ የሚወድ ሰው ማን አለ?"

"ማለቴ ድብድብ ውስጥ መሳተፍ አልፈልግም። እናንተ መደባደብ ስትጀምሩ ግን ለፖሊስ ደውዬ ልነግርላችሁ





እችላለሁ።"

በዚህ አነጋገሬ ቅሬታ አደረበት። ምክሩንም ቀጠለ። ምክሩን ተግባራዊ እንደማላደርገው ባውቅም ደስ እንዲለው ብዬ በጥሞና አዳመጥኩት፣

"ታንዛኒያውያንን ከቁም ነገር መቁጠር አይገባም። ከሃበሻ ጋር የሚጣሉት ተሰብስበው ብቻ ነው። ብቻ ለብቻ እንደማይቋቋሙን ያውቃሉ። ስለዚህ ተሰብስበው ሲመጡ እኛም መተጋገዝ አለብን። የቢራ ጠርሙስ ይወረውራሉ እንጂ ቡጢ አያውቁም። ጠርሙሶቹን በእጅህ እየመከትክ ከተጠጋኻቸው አበቃላቸው። እያነቅህ ከግድግዳ ማጋጨት ነው። ታንዛኒያውያን ድብድብ ጀመሩ ብለህ መሸሽ ግን አበሻን ማስደፈር ነው..."

እኔም በቁም ነገር እንዲህ ስል ጠየቅሁት፣

"የታንዛንያውያኑ ገብቶኛል። ወደፊት ለማሻሻል እሞክራለሁ። ፀቡ ከደቡብ አፍሪቃውያን ጋር ከሆነስ? ምን ማድረግ አለብኝ?"

ሳሚ እያመነታ እንዲህ አለ፣

"በርግጥ ከደቡብ አፍሪቃውያን ጋር መጋጨት አያስፈልግም። እነሱ ኪሳቸው ውስጥ ሽጉጥ አያጡም። ከነሱ ጋር ተከባብረን መኖር ይሻላል..."

መልሼ እንዲህ ስል ተቃወምኩ፣

"ጠርሙስ ውርወራስ ቢሆን እንዴት ይናቃል? የተሰበረ ጠርሙስ አደገኛ ነው። ይኸው የአንተ ግንባር የተበላሸው በጠርሙስ ነው"

ሳሚ በስሜት ተቃወመኝ፣

"በርግጥ በጠርሙስ ግንባሬን ተርትረውኛል። ግን ደግሞ ግንባሬን የተረተረኝን ታንዛኒያዊ ወጥ በወጥ ነው ያደረግሁት። 'ማረኝ' ብሎ እግሬ ስር ወድቆ እስኪያለቅስ በደም ነው ያጠብኩት..."

"የሱ ፊቱ ላይ ግን ጠባሳ የለም" ስል እየሳቅሁ መለስኩ፣ "...እሱ ግን ለዘልአለሙ የማይጠፋ ማህተም ነው ያተመልህ..."

ሳሚ አስተያየት ሳይሰጥ ጥቂት ቆየ።

ወዲያው ገፅታው በቁጣ ሲለዋወጥ አየሁት። ፊቱ በንዴት ጋለ። ጆሮዎቹ ቀሉ። እናም ሙግቱን አቁሞ እየተንተከተከ እንዲህ አለ፣

"የኔ ግንባር ላይ የጠባሳ ምልክት አለ። እሱ ግን ምንም

የተጐዳው ነገር የለም”

አያያዘና ቀጠለ፣

“አልለቀውም! ፊቱን ወንፊት አደርገዋለሁ! ይህን ካላደረግሁ ደግሞ እንደ ሴት ቁጭ ብዬ እሸናለሁ”

ጠረጴዛውን እየደበደበ ሲጮህ በጣም ደንግጬ ላረጋጋው ሞክሬ ነበር። መተንፈስ እስኪያቅተው ድረስ ደረቱን እንደ ከበሮ ወጥሮ በእልህ ይቃትት ጀመር። በወቅቱ የማደርገው ጨንቆኝ እንደነበር አስታውሳለሁ። እንዲህ ለሌላ ጠብ በትኩስ ስሜት ይነሳሳል ብዬ ከቶውንም አልጠበቅሁም ነበር። እንደዋዛ በተጀመረ ጨዋታ ወዳልተፈለገ እልህ ስለገፋሁት ወዲያውኑ ተፀፅቼ መፍትሄ ወደ መፈለግ አመራሁ። ‘ያለፈው አልፎአል’ እያልኩ ላበርደው ያደረግሁት ሙከራ ግን ውጤት ሳያመጣ ተለያየን።

ይህ በሆነ በሳምንቱ አካባቢ ይመስለኛል። ሳሚ እና ታንዛኒያዊው የአንድ ሩስያዊ ባርና ሬስቶራንት ውስጥ አንድ ጠረጴዛ ላይ ተቀምጠው ቢራ ሲጠጡ አገኘሁዋቸው። የተጠበሰ የበግ ስጋ ቀርቦላቸውም እየበሉ ነበር። ማመን እያቃተኝ የተቀመጡበትን ወንበር ተጋራሁዋቸው። የተፈጠረውን ለማወቅ ጓጉቼ ነበር። ሳሚ ስሜቴን ተረድቶ በአማርኛ እንዲህ አለኝ፣

“ዛሬ ምሳ ሰአት ላይ አገኘሁትና ጉሮሮውን አነቅሁት። ልፈረካክሰው ነበር። እውነቱን ሲነግረኝ ተውኩት”

“ምን ነገረህ?”

“ያን ቀን ጠርሙሱን የወረወረው እኔን ሊመታ አስቦ አልነበረም። ጠርሙሱ እኔ ላይ ያረፈው በስህተት ነው።”

አስተያየት አልሰጠሁም። ዝም በማለቴም አከለበት፣

“የሆነው ሆኖ ይህን ግብዣ እሱ ነው የሚከፍለው...”

* * *

እንደተለመደው በጠረጴዛ ዙሪያ እያወጋን፣ ሳምንቱን ሙሉ እንዲሁ ቀጠልን። እሳቱን አንድደን ምሽቱ ላይ እዚያችው ጠረጴዛ ላይ መሰየሙ ተስማማን። ደጁ ላይ በተዘረጉት ቀያይ ጃንጥላዎች ስር በአልኮል መቃጠሉን ቀጠልንበት።

ፕሪቶሪያ እንደገባሁ በቅድሚያ የፈፀምኩት ተግባር





ስልክ መግዛት ነበር። ያንን የስልክ ቁጥር የVOA ጋዜጠኛ ለሆነው ለአዲሱ አበበ ልኬለት ነበር። አዲሱ ደግሞ የስልክ ቁጥሬን ለትዝታ በላቸው አስተላልፎላት ኖሮአል፣

በዚያው ሰሞን በጠረጴዛው ዙሪያ ሳለን ስልኬ ጮኸ!

“ሃለው” አልኩ።

“ትዝታ ነኝ”

ወደ ደጅ ወጣ ብዬ የስልክ ንግግሬን አብቅቼ ስመለስ ጓደኞቼ ማን እንደደወለልኝ ጠየቁኝ። ትዝታ በላቸው መሆኗን ገለፅኩ። አብይ ስሜታዊ ሆነ፣

“ምናለበት ብታገናኘኝ? እንደምወዳት እነግራት ነበር”

ለጥቂት ደቂቃዎች የጠረጴዛችን ወግ ስለ ትዝታ ብቻ ሆነ። ድምፅዋ በጣም እንደሚጥም ባንድ ድምፅ አፀደቅን። እድሜዋና መልኳን የሚያውቅ ከመካከላችን ባለመኖሩ ማድነቅ የቻልነው ድምፅዋንና የጋዜጠኛነት ብቃቷን ብቻ ሆነ።

ጫት ነጋዴው ጴጥሮስ ግን ትዝታ በላቸው ማን እንደሆነች ሊያውቅ አልቻለም። እንደ ጊታር ሽቦ በከረሩ ጣቶቹ ትከሻዬን ይዞ ይንጠኝ ያዘ።

“ትዝታ ማናት? ሚሚ ስብሃቱ ማለታችሁ ነው?”

ደምሴ ጣልቃ ገብቶ፣

“‘ትዝታ በላቸው’ እየተባለ እንዴት ሚሚ ስብሃቱ ብለህ ትጠይቃለህ? ሁለቱን ምን አገናኛቸው?” ሲል ጠየቀው።

“መብቴ ነው መጠየቅ! አፍህን አትክፈት!”

“አይገባህም!” አለው።

“ቢገባኝ ባይገባኝ ምናገባህ!? ዝም ብለህ አወቅሁ አወቅሁ ትላለህ!” ብስጭቱን በመቀጠልም እንዲህ አለው፣ “....ትናንት የወሰድከውን የጫት ሂሳብ ደግሞ ክፈል! ‘መጣሁ’ ብለህ በዚያው ሹልክ ብለህ ትሄዳለህ?”

“ሹልክ ብለህ? ዝርዝር የለኝም ስላልክ አይደል እንዴ ሳልከፍል የሄድኩት። እኔ ካንተ ዱቤ ወስጄ አውቃለሁ?”

“ክፈል አሁን። ወሬ አታብዛ”

ደምሴ ዋሌቱን አወጣ፣

“ስንት ነው?”

“30”

“አታጭበርብር። 25 ነው ስትሸጥ የዋልከው...”

“ካወቅህ ታዲያ ምን አስጠየቀህ?”

ጴጥሮስ ገንዘቡን ተቀብሎ ኪሱ ከተተ።
በዚህ ጊዜ ማሙሽ ጣልቃ ገብቶ ወሬውን ቀየረው፣
"የእንቁላል ጦርነቱን ተፅፈዋለህ ብዬ ጠብቄ ነበር"
"ረስቼው ነበር" አልኩ፣ "በሚቀጥለው መፅሃፍ ጠብቅ..."

* * *

የእንቁላል ጦርነቱ ከተፈፀመ አመታት አልፎአል።
እንዲህ ነበር የሆነው...

አንድ ጊዜ መለስ ዜናዊ ደቡብ አፍሪቃ እንደሚመጣ ወሬ ተሰማ። ወሬው እንደ ተሰማ የጆሃንስበርግና የፕሪቶሪያ ሃበሾች በጥፍራቸው ቆሙ። ጫጫታ ሆነ። ጆሮአችንም ልባችንም እንደ ባንዴራ ተውለበለበ።

መለስ ፕሪቶሪያ UNISA (University of South Africa) ተገኝቶ ከታሪክና ከፖለቲካ ሳይንስ ምሁራንና ከተጋበዙ እንግዶች ጋር በአፍሪቃ ቀንድ ጉዳይ ላይ ውይይት እንደሚያደርግ የተረጋገጠ መረጃ ተገኝቶ ነበር። አመጣጡ እንኳ ከቶኒ ብሌየር ጋር ስብሰባ ለመቀመጥ ነበር።

ሃበሾች ለአመፅ ወገባቸውን ታጠቁ!

ለአመፁ አመቺ ቦታ ሆኖ የተገኘውም ይህ የእግረመንገድ ፕሮግራሙ ሆነ።

ዝግጅቱ ግልፅና ያልተንዛዛ ነበር።

የተቃውሞ ሰልፍ ለማካሄድ የፈቃድ ወረቀት ተያዘ። በአበሻ ምግብ ቤቶችና መገናኛ ቦታዎች ሁሉ የጥሪ ወረቀት ተለጠፈ። ፕሮግራሙን የሚያስረዳ የSMS መልእክቶች ተሰራጩ። ምን ቀረ? ምንም? ጦርነት ብቻ!!

"ጊዜው አሁን ነው!" እየተባለ ነበር።

እቅዱም እንዲህ ተብራራ፣

"...ከቀኑ ዘጠኝ ሰአት ሲል፣ እያንዳንዱ ሃበሻ በግል መኪናውም ሆነ በተዘጋጁት አውቶብሶች UNISA ግቢ ይገኛል። እያንዳንዱ ሃበሻ ቢያንስ ሁለት እንቁላል በኪሱ ይይዛል። 9.30 ላይ መለስ ዜናዊ ውይይቱን ጨርሶ ሲወጣና ልክ የግቢው ደጃፍ ላይ ሲደርስ፣ እያንዳንዱ ሃበሻ የእንቁላል ፈንጂውን የመለስ መኪና ላይ እያነጣጠረ ያፈነዳል። ቪዲዮ ቀራጮችም መለስ ላይ





በማተኮር ቀረፃቸውን ያካሂዳሉ። የእለቱ እለት ደግሞ ምስሉ ለቴሌቪዥን ጣቢያዎችና ለድረገፆች ይላካል!"

ይኸው ነበር እቅዱ!

የሚደነቅ ዝግጅት ነበር። የሚጨመርም የሚቀነስም አልነበረውም። እኔ በግሌም ታዲያ ማድረግ የምችለው እስተዋፅኦ ካለ አስቤበት ነበር። ይህን የአመፅ ሰልፍ በቦታው ተገኝቼ ማየትና ስለ አመፁም ለድረገፆች ለመፃፍ ወሰንኩ።

የአመፁ እለትም ደረሰ!

ግማሽ ሰአት ቀደም ብዬ UNISA ተገኘሁ። 8.30 ከግቢው ስደርስ በቅፅል ስሙ ማሙሽ ብለን የምንጠራው የካዛንቺስ ልጅ ብቻ ነበር የቀደመኝ። ሰላምታ ተለዋውጠን ወግ እንደጀመርን ሶስት ጥቋቁር መኪኖች ተከታትለው መጡ። መኪኖቹ አጠገባችን ሲደርሱ መውጫው ደጃፍ ላይ ነበርንና ቀዝቀዝ አሉ። ሁሉም ነገር በፍጥነት የተፈፀመ ነበር። ከመካከል ያለችው መኪና የፊትና የሁዋላ መስኮቶች ክፍት ነበሩ። ከሁዋላ መለስ ዜናዊ ተቀምጦአል። ከፊት መቀመጫ ላይ ኤልያስ አሸብርን አየሁት።

*(ኤልያስ በወቅቱ የመለስ የፕሮቶኮል ክፍል ባልደረባ የነበረ ሲሆን፣ ይህን ስፅፍ ካውንስለር ሆኖ ሞስኮ ተመድቦአል። ኤልያስን በደንብ አውቀዋለሁ። አባቱ የደርግ ኮሎኔል ሲሆኑ፣ እስር ቤት ናቸው። እሱ የመለስ እልፍኝ አስከልካይ። ኤልያስ እጣ ክፍሉ ንግድ ነበረች። እድል ዲፕሎማት አደረገችው። በዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ወደ ፕሪቶሪያ ሲመላለስ ብዙውን ጊዜ ጫት ይዞ እየመጣ ጥሩ ትርፍ ያገኝበታል።)*

እና አብሮኝ የነበረው ማሙሽ፣ "መለስ ያውና!" ብሎ ከመጮኽ በቀር ያደረገው ነገር አልነበረም። ይህ ሁሉ በአንድ ደቂቃ ውስጥ የተከናወነ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደቂቃ ላይ መኪኖቹ ከአይኖቻችን ተሰውረው ነበር። ግራ ተጋብተን ከማሙሽ ጋር ተፋጠን ቀረን፣

"እንዴት እንዲህ ሊሆን ቻለ?" ሲል ጠየቀኝ።

"ሰአቱን ሆን ብለው አሳስተው ሰጥተውናል" አልኩት።

ዘጠኝ ሰአት ሲል አበሾች በግል መኪኖችና በአውቶብስ የዩንቨርሲቲውን ግቢ አጥለቀለቁት። የአምባሻ ምስል የሌለበትን

ባንዴራችንን ያልያዘ የለም።

መፈክሮች! ጃሎታው! ሆታው!

የጆሃንስበርግ ሃበሾች የንግድ ሱቆቻቸውን ዘጋግተው በአውቶብስና በግል መኪኖቻቸው ንቅል! ብለው መጥተው ነበር። ወያኔን የሚያወግዙ ዜማዎች ቀልጠዋል። ብዙዎቹ እንቁላል ጨብጠው ነበር። አንዳንድ ሴቶች ወፈር ያለ ሽንኩርትና የጎረምሳ ቡጢ የመሰለ ድንች ይዘው አየሁ። በደንብ ያልበሰለ ቲማቲም የያዙም ይታያሉ...

"አትነሳም ወይ! አትነሳም ወይ!
ይሄ ባንዴራ! ያንተ አይደለም ወይ!?
ይለያል ዘንድሮ፣ ይለያል ዘንድሮ፣
የወያኔ ኑሮ!"

ማሙሽ ድምፁን ከፍ አድርጎ እየሳቀ ነበር።

እኔም እያጀብኩት፣

"እንቁላልህ የታለ?" ስል ጠየቅሁት።

"አልያዝኩም"

"ለምን?"

"እዋሳለሁ ብዬ ነበር ያሰብኩት"

ከግማሽ ሰአት በሁዋላ የአመፁ አስተባባሪዎች እጃቸውን በማጨብጨብ ሆታውን አስቁመው ለሰልፈኛው የሚከተለውን መርዶ ነገሩ፣

"ለተፈጠረው ስህተት እናዝናለን! የተነገረን ሰአት ስህተት ነበር። ዘረኛውና ባንዳው መለስ ዜናዊ ውይይቱን ጨርሶ ከአንድ ሰአት በፊት ግቢውን ለቆ ሂዶአል።"

የተፈጠረው ቁጣና ብስጭት መጠን አልነበረውም።

"ማነው ይህን ስህተት የሰራው!? ወያኔዎች በመካከላችን ካሉ ንገሩን!? የበግ ለምድ የለበሰውን ወያኔ አሳዩን!"

ቁጣዎች ሲበረክቱ ማሙሽን ጠቀስኩትና ወደ መኪናዬ አመራሁ። መኪና ውስጥ ሆነን የሚሆነውን እንከታተል ቀጠልን። ብዙም አልቆዩ። አውቶብሶቹና ከሃያ በላይ የግል መኪኖች የዩኒቬርሲቲውን ግቢ ለቀው ወጡ። እኛም ተከተልን።

ማምሻውን River of Africa በጠጪዎች ተጨናንቆ አመሸ። የቁጣና የብስጭት ድምፆችም ተሰሙ። በተለይም፣ "የተቃዋሚዎች አመራር ላይ ወያኔዎች አሉ" የሚሉ ቃላቶች





በብዛት ይደመጡ ነበር። ቀስ በቀስ ግን ቁጣው እየረገበ ሄደ። ወሬውም ተለወጠ። እንደተለመደው በመዋጮ ስጋ ተገዛ። የብረት ምጣድ ጥብስ ተጠበሰ። ጥብሱ ላይ የኬፕታውን ወይን ተቸለሰበት። የጥብሱ ሽታ አካባቢውን አወደው። ሰልፈኞቹ እየተቀላለዱ እንቁላሎቻቸውን ከየኪሶቻቸው እያወጡ ስጋው ላይ አከሉበት። ሴቶች መለስ ላይ ሊወረውሩ ያዘጋጁትን ሽንኩርትና ቲማቲም ከቦርሳቸው ውስጥ አወጡ። ተከተፈና ስጋው ላይ ተነሰነሰበት። እጅ የሚያስቀረጥም እንቁላል በስጋ በላን። ቢራ ሰረገብን። ቮድካ በአናቱ ተጨመረበት። አብዱ ኪያር "መርካቶ ሰፈሬ" እያለ አንጎራጎረ። ምሽቱም መልካም ሆነ...

ይህ አመፅ በከሸፈ በሰባተኛው አመት ገደማ ይመስለኛል፣ መለስ ዜናዊ ቴሌቪዥን ላይ ቀርቦ እንዲህ ሲል ሰማሁት፣

"ግንቦት7 የተባለው ድርጅት አያሰጋንም። እኛን የሚያሰጋን አልሸባብ ነው።"

በነጋታው እዚያው ባር ተሰብስበን ሳለ፣ ደምሴ ፖለቲከኛው በባንኮኒው ዙሪያ ለነበርነው ይህንኑ መለስ የተናገረውን አነሳ። አያያዘናም፣

"ምን እያለን እንደሆነ ይገባችሁዋል?" ሲል ጠየቀ። ትኩረት የሚሰጠው ባያገኝም፣ የሞት ሞቱን የጀመረውን አረፍተ ነገር መጨረሱ አልቀረም፣"...ከእንቁላልና ከቲማቲም አታልፉም እያለን ነውኮ?"

ለጥቂት ሰከንዶች ፀጥታ ሆነ!

እና ማሙሽ እንዲህ ሲል ፀጥታውን ሰበረው፣

"ዛሬ ሊቨርፑል ከማን ጋር ነው የሚጫወተው?"

በዚያን እለት እስከ እኩለ ሌሊት ስለ እንግሊዝ ክለቦች ስናወጋ አመሸን። አርሰናል፣ አርሰን ቬንገር፣ ፋብሪጋዝ፣ ሊቨርፑል፣ ጎልአግቢው ጄራልድ፣ ስፔናዊው ቶረስ፣ መሃል ተጫዋች...

ወሬዎች እንዲሁ ቀጠሉ። በርግጥ ይህን መሰል ወግና እነዚህ ስሞች ለኔ ባእድና ሩቅ ነበሩ። በጣም እሩቅ...

* * *

ፕሪቶሪያን እየጠላሁትና እየሰለቸኝ ሄዶአል።

ብርዱ ራሱ መቼ ይቻልና? ሙቀቱስ ቢሆን? 13 ወራት

ለስላሳ ፀሃይ በሚያበራበት ምድር የተወለድኩ እንደመሆኔ ከአመት አመት መጠን አልባ ብርድና ሙቀቱን የመቋቋም አቅም እያጣሁ መጥቻለሁ። ብርድ ሲሆን ብዙውን ጊዜ 30th ተብሎ ከሚጠራው ባር እና ሬስቶራንት ገብተን እንታሸጋለን።

ስለዚሁ ባር አያሌ መልካም ትዝታዎች ነበሩኝ። በተለይም ባርማን ሆነው የሚሰሩት ህንዳዊው ኤልቨን እና አልጀሪያዊው አብዱልመጂድ ከቶውንም አይረሱኝም...

"የጋዜጠኛው ማስታወሻ"ን እሩቡን ያህል የፃፍኩት 30th ባለጌ ወንበር ላይ ተቀምጬ ነበር። ኤልቨን የህንድ ዘር ያለው ቢሆንም፣ ትውልዱ ደርባን ላይ ነው። ህንዶችን አጥብቆ ይጠላል። ለምን እንደሚጠላቸው ግን በቂ ምክንያት አያቀርብም። ዌይተር ከመሆኑ በፊት የአደንዛዥ እፅ ነጋዴ ነበር። በዚሁ ጦስ ታስሮ ከተፈታ በሁዋላ እፅ መነገዱን ርግፍ አድርጐ ተወውና ባር ማን ሆነ። አያቶቹ በጥንት ዘመን ደርባን አካባቢ ለሚገኘው የስኳር ፋብሪካ በአገዳ ቆራጭነት ተቀጥረው ከኬርላ እንደመጡና በዚያው ደቡብ አፍሪቃዊ ሆነው እንደቀሩ አጫውቶኛል። በአለባበሱ ምንጊዜም ሙሽራ የሚመስል ንፁህ፣ ሳቂታና ሙዚቃ የሚወድ የደስታ ሰው ነው። ነገረኛ እንግሊዛዊት ሴት አግብቶ ህይወቱ ሁሉ ስቃይ ሆኖበት ነበር። ማታ ማታ ከክፍል ወደ ክፍል እያሳደደች በቢላ ጭምር ትወጋዋለች። በየጊዜው ሸሚዙን እየገለጠ አዳዲስ የተወጉ ቁስሎችን ያሳየን ነበር። በመጨረሻ ግን መከርነውና ፈታት። የፈታት ቀን የ30th ደንበኛ የሆንነውን ሃበሾች ሁሉ ጋበዘን። ግብዣውን ሲያሳርግም እንዲህ ሲል አጭር ንግግር አደረገ፣

"ከእስር ቤት ስፈታ እንኳ እንደ ዛሬ ደስታ አላገኘሁም"

ብዙ ጊዜ ስጫጭር ይመለከተኝ ነበርና አንድ ቀን እንዲህ ሲል ጠየቀኝ፣

"ምንድነው የምትፅፈው?"

"ጥቅሶች" አልኩት።

"አንድ ጥቅስ ልንገርህ?"

"ንገረኝ?"

"ጥቅስ ሳይሆን ምክር ልንገርህ?"

"ምከረኝ"

"ከሴቶች ጋር አብረህ አትዋል። አብረህ ከዋልክ በመጨረሻ ራስህን ትገድላለህ።"





ስስቅ ተመለከተና ሊያሳምነኝ ጥረት አደረገ፣

"እመነኝ!! ከልምድ ነው የምነግርህ። የፈለገውን ያህል የተማረች ብትሆን ሴት ምንጊዜም ሴት ናት። ሚስቴን አይተሃታል? ስንት ጊዜ ነው በቢላ የወጋችኝ? ሴት ሰይጣን ናት። እግዚአብሄር እኔን ይወደኛል። እሁድ ቤተክርስትያን ቀርቼ አላውቅም። ሰክሬ ባድር እንኳ ከቤተክርስትያን አልቀርም። በእግዚአብሄር እርዳታ ነው ህይወቴ የተረፈችው..."

መሳቄን በመቀጠሌ ኤልቨን ስሜታዊ ሆነ፣

"አላመንከኝም? ለማንም እንዳትነግር አንድ ምስጢር ልንገርህ? ጠጥቼ ከመጣሁ ፊኛዬ ላይ በቡጢ ትመታኝ ነበር። ሳልፈታት ትንሽ ብቆይ የዘር ፍሬዬን ታፈነዳው ነበር። አንተ ባለውለታዬ ነህ። መጀመሪያ እንድፈታት የመከርከኝ አንተ ነህ። ከንግዲህ ካገባሁ ህንዳዊት ነው የማገባው..."

30th ከተባለው ባር ያጋጠሙኝ ደጋግ ሰዎች ቁጥር ስፍር አልነበራቸውም። ጃኔት ሌላዋ ናት። እድሜዋ ከ60 ይበልጣል። ጭምድድ ያለች ነጭ ስትሆን በየእለቱ ከእኛው እኩል ባንኮኒው ላይ ተሰይማ፣ ከኛው ጋር እኩለ ሌሊት ላይ ወንበር ትለቃለች። እንደ እድሜዋ አይደለችም። ጠንካራ ናት። ከብዙ ጊዜ መተያየት በሁዋላ አንድ ቀን እንዲህ ስትል አጫወተችኝ፣

"አፍሪካንስ ቡር ነኝ። ሁለት ልጆች ከወለድኩ በሁዋላ ከባሌ ጋር ተፋታን። ቀዥቃዣ ጣሊያናዊ ነበር። በራሱ ቋንቋ ቴስታ ዲጋሊና ብዬ ካልቾ አቅምሼ አባረርኩት..."

"የት ነበር የምትኖሩት?"

"እዚሁ ፐሬቶሪያ! እዚሁ ነው ተጋብተን የወለድነው። ወንድ ልጄ አሁን ኬፐታውን አለ። መሃንዲስ ነው። ሴቷ ቨርጂኒያ ናት"

ሲጋራዋን ለኮሰችና ቀጠለች፣

"በቅርቡ ደግሞ አንድ አልጄርያዊ አግብቼ ነበር። በገዛ መኝታ ቤቴ ውስጥ ከጥቁር ሴት ጋር ተኝቶ ያዝኩት። ጉሮሮውን አንቄ በቴስታ አፍንጫውን! እንደገና በጥፊ ጆሮ ግንዱን! በቡጢ ሆዱን! ጩኸቱን ለቀቀው! እሱ ሲጮህ እኔ ደነገጥሁ። ወንድ እንዴት ይጮሃል? ነጭ መስሎኝ ነበር ያገባሁት። ለካስ አልጄርያዊ ነው። አልቃይዲ ሳይሆን አይቀርም። በዚያኑ ቀን ሻንጣውን አስይዤ የመሰናበቻ አንድ

ካልቾ አቅምሼ ስኩሮኞ! ማኔሎ! አልኩና አባረርኩት። ሊፍቱን እንኳ ሳይጠብቅ በደረጃው እየበረረ ወረደ…"

ጃኔት ከሄደች በሁዋላ፣ አብዱልመጂድ ወደኔ ቀርቦ፣

"ምንድነው የምትልህ?" ሲል ጠየቀኝ።

"አልጄሪያዊ አግብታ እንደነበርና በጥፊና በካልቾ ደብድባ፣ እድለ ቢስ ዱርዬ ብላ ሰድባ እንዳባረረችው ነገረችኝ። ነጭ መስሎኝ ነበር ያገባሁት አለችኝ…" አልኩት።

አብደልመጂድ በንዴት እሳት ጨበጠ። የርግማን በረዶ ያወርድባት ገባ። ውሸታም መሆንዋን የቻለውን ያህል ነግሮኝ ሲያበቃ፣ የተናገረው አልበቃ ስላለው፣ እንዲህ ሲል አሳረገ፣

"ኪስ አውላቂ ናት! ተጠንቀቅ!"

* * *

ፕሪቶሪያን ጠቅልሎ የመልቀቅ አሳብ በአእምሮዬ ተፀንሶ ነበር። በዚያው ሰሞንም ፈቃዱ በረዳ የፖለቲካ እንቅስቃሴ መጀመሩን ሰማሁና ፈልጌ አገኘሁት። ምን እንደሚል ልሰማውና ላየው ጓጉቼ ነበር።

አለባበሱና አነጋገሩ በጣም ተለውጦ አገኘሁት። ሰከን ብሎአል። ኮት ለብሶአል። ክራቫት ቢጤም ሸብ አድርጎአል። ጥራዝ ነገር በእጁ ይዞአል። ፍላሽ ሚሞሪ እንደ ሃብል አንገቱ ላይ አንጠልጥሏል። ቃላቶቹ ጭምር መለወጣቸውን ታዘብኩ። ገና ሲያገኘኝ እንዲህ አለኝ፣

"የታሪክ ጎማ መሽከርከር ጀምሮአል"

"ትግል ጀመርክ ማለት ነው?"

"ጀመርኩ ሳይሆን ቀጠልኩ" አለ ኮራ ብሎ።

"እስከዛሬ ግን ሰምቼህ አላውቅም ነበር"

"የፖለቲካ ስራ በአዋጅ አይሰራም"

"ጥሩ ነው" አልኩት።

እያያዘና አብራራ፣

"….እንደ ደምሴ የኢትዮጵያን ባንዴራ ለብሶ መዞር ለኢትዮጵያችን መፍትሄ አይደለም። የደቡብ አፍሪቃን ሃበሾች ትግል የገደለው ደምሴ ነው። 'ሶስተኛ አማራጭ' የተባለውን የፖለቲካ መስመር በመያዝ የደቡብ አፍሪቃን ሃበሾች ለትግል ማስተባበር ጀምሬያለሁ። አበረታች ውጤት እያገኘሁ ነው…"





"ከልደቱ ጋር ነህ ማለት ነው?"

"እንተጋገዝ ብዬ ፅፌለታለሁ። መልስ ገና አላገኘሁም"

"ጥሩ ነው! ማነው ሊቀመንበሩ?"

"እኔ ነኛ! ሌላ ማን ሊሆን ይችላል?"

"ስንት አባላት አሉህ?"

"ለጊዜው ምስጢር ነው። በጠቅላላ ጉባኤው ሲፀድቅ ይፋ ይሆናል። መግለጫ እሰጥበታለሁ…"

"ምንድነው የያዝከው ጥራዝ?" ስል ጠየቅሁት።

"አንዳንድ ነጥቦችን እየያዝኩ ነው። የትግሉን አጀማመር…" ካለ በሁዋላ፣ "ወይ ጋብዘኝ ወይ ልጋብዝህ በቁሜ አታድርቀኝ" አለኝና ተያይዘን ገባን።

የተለመደውን ካዘዝን በሁዋላ ፍቄ ወጉን ቀጠለ፣

"ያው መቼም ገንዘብ ያስፈልጋል። መዋጮ! እያንዳንዱ ሃበሻ ሊደግፈኝ ይገባል። የግድ ነው። በየቀኑ ጥሬ ስጋ እየተበላ መዋጮ ላይ ግን ወገብ መያዝ! ከራስታ ጋር ትናንት ተገናኘንና አላማዬን አስረዳሁት።

'ደሞ በዚህ በኩል መጣሽ?' አይለኝ መሰለህ?

በንዴት እሳት ነው የሆንኩት። እኔ የፖለቲካ ሰው ነኝ። መሳደብ የለብኝም። ራስታ እንዲያ ሲናገረኝ ግን አልቻልኩም። በጣም አናደደኝ። ምን እንዳልኩት ታውቃለህ?

'አፍህን አትክፈት! 30 አመት የደከምክበትን ፀጉር ላጭቼ ሃብሃብ አስመስልሃለሁ' አልኩት።

በዚህ ምክንያት አሁን አንነጋገርም። ገና በገና 'መወጮ እጠየቃለሁ' ብሎ የኔን ጥረት ያንኳስሳል? ስንት ለካፌ ሰው አለ? መዋጮስ ቢሆን ምን ይጎዳል? እሱ በየቀኑ ለቢራ ያወጣ የለ እንዴ? ደሞ ቁጥር ያለው ደረሰኝ አዘጋጅቼያለሁ። ማህተም አለኝ። ከዚህ በላይ ምንድነው የሚፈልገው?…"

"መበርታት ነው እንግዲህ" ካልኩ በሁዋላ 20 ራንድ አዋጣሁ። ፍቄ የኑሮ ስልቱን መቀየሩን አልጠላሁትም። የሰው ፊት ከሚገርፈው በዚህ ዘዴ የተለመደውን መጠየቁ መጥፎ አልነበረም…

* * *

በውነቱ ፕሪቶሪያ ሰለቸኝ!

የፕሪቶሪያ ህይወት ከምንጊዜውም በላይ አሰልቺ

እንደሆነብኝ መገንዘብ ችዬ ነበር። የስደትን ህይወት ዝቅተኛነት የሚገልፁ በርካታ ገፀባህርያት ፕሪቶሪያ ላይ አሉ። በርግጥም የስደትን ዝባዝንኬነት ፍንትው አድርገው ማሳየት ይቻላቸዋል።

ወጐች አድካሚ ናቸው፣

ፀብና መሰዳደብ የለም ከተባለ ረጃጅም ወሬዎች አሉ። እነዚያ ወጐች ደግሞ ከጨርቃ ጨርቅ ንግድ ያለፉ አይሆኑም። ስለ ብርድ ልብስ ዋጋና አይነት ከሰአታት በላይ ማዳመጥ የተለመደ ነው። የብርድ ልብሱ ካለቀ ጨዋታው ወደ አልጋ ልብስ ይዞራል። ከአልጋ ልብስ ቀጥሎ የወሬ ርእሱ በጣም ተቀየረ ከተባለ ወደ ጫማ ዋጋ ነው የሚዞር። በርግጥ በዚህ ወግ መሳተፍ ግዴታ አይደለም። የመስማት ወይም የመሸሽ አማራጮች አሉ። እኔ ግን መሸሺያ ሊኖረኝ አልቻለም።

አንድ ሰሞን ከሃበሾች ሳልገናኝ ትርፍ ጊዜዬን በማንበብና በመፃፍ ብቻ ለማሳለፍ ወስኜ ሞክሬው ነበር። ከአምስት ቀናት በላይ አልዘለቅሁም። አይኔን ሰው እራበው። አማርኛ መናገር ጠማኝ። በአማርኛ መሳቅ አማረኝ። አበሻ የሆነ አበሻ በማየት ምኞት መንፈሴ ተሰቃየ። ከአምስት ቀናት በሁዋላ እየተንደረደርኩ River of Africa ተገኘሁ...

በዚህ መንገድ መዝለቅ እንደማይቻል ግን ግልፅ ነበር። እና ወሰንኩ። ደቡብ አፍሪቃን ጠቅልዬ ለመልቀቅ ወሰንኩ...

የአለን ፓተን ሃገር - የዊልበር ስሚዝ - የዋልተር ሲሱሉ - የስኩማን - የኦሊቨር ታምቦ - የፕሪቶሪየስ - የጆሃንስ - የሃኒ ክሪስ ሃገር - የኢሊዛቤት - የፒተር አብርሃመስ - የማሪያ ማኬባ - የብሬንዳ ፋሲ ሃገር - የስቴቭ ቢኮ - የፖል ሳይመን - የሊዮን ሼስተር - የሻባላላ እምሲማንግ ሃገር - የቻርሌዚ ቴሮን ሃገር - የዊኒ ማንዴላ ሃገር...

'ከኢኮፓ ወደ ጆሃንስበርግ የሚያደርሰው መንገድ ውብ ነው' የሚለውን ትረካ ያነበብኩት ገና የ12 አመት ልጅ ሳለሁ ነበር። በዚያ ውብ መንገድ ላይም ተጉዤያለሁ። በፍፁም የማልረሳቸው ውብ አረፍተ ነገሮች ሞልተዋል። ባቡሩ የኡምዙምኩሉን ጫካ እየሰነጠቀ ሲጓዝ ... በትክክልም በኡምዙምኩሉ ጫካ ውስጥ በባቡር ተጉዣለሁ... ወደ ጥቁርት





የሚያደላ አረንጓዴ ቀለም ያለውን የድራክንስበርግ ተራራ ግማሹ ድረስ በእግር ጉዞ ወጥቼዋለሁ። Cape town ላይ Cape point የሚባል ቦታ አለ። እዚያ ሆኜ በአቅርቦ የሚያሳይ መነፅር ወደ አንታርክቲክ አቅጣጫ ተመልክቼያለሁ።

ደርባን ራሱ እንዴት ከአእምሮ ይጠፋል?

ማንዴላ ለመጨረሻ ጊዜ በፖሊሶች የተያዘው፣ ከደርባን ወደ ጆሃንስበርግ ሲጓዝ ነበር። በዚያ መንገድ ላይ እንደ ወፍ እየበረርኩ ነድቼበታለሁ። የደቡብ አፍሪቃ መልካም ትዝታዎች ከቶ እንዴት ይጠገባሉ? OH, But Our Land is Beautiful የተባለውን የአለን ፓተን ድርሰት ያነበብኩት ደግሞ በፈጣኑ ሰማያዊ ባቡር ወደ ኬፕታውን ስጓዝ ነበር። ሁለት ቀናት የሚፈጅ የባቡር ላይ ጉዞ። በመኝታ ክፍሌ ውስጥ ብቻዬን ነበርኩ። ባቡሩ ውብ የመመገቢያ አዳራሽ ነበረው። በኤሌክትሪክ ሃይል የሚጓዘው ፈጣን ባቡር መንደሮችን እየሰነጠቀ፣ የማእድን መቆፈሪያ ጉድጓዶችን እያለፈ ሲጓዝ ያለማቋረጥ ትዝ የሚለኝ አለን ፓተን ነበር። የሱ ቃላቶች....ቲቲሆያ የተባለችው ብቸኛ ወፍ! የማእድን ጉድጓዶች! ባቡሩ! ሁሉም አእምሮዬን እያቋረጠ ያልፋል ...

ይኸው ነው!

በሚቀጥለው ቀን ምንም አዲስ ነገር የለም። እለታዊ ህይወትን ብቻ እያጣፈጡ መጓዝ ይቻላል። ይህ ጣፍጭ ስለመሆኑም ርግጠኛ መሆን አይቻልም። በሚቀጥለው ቀን ሁሉም ነገር አሰልቺና አሮጌ ይሆናል።

ነጮችንም ሆነ ጥቁሮችን ማየት ሰለችቶኛል። በርግጥ ጥቁሮቹም ሆኑ ነጮቹ ጥሩ ሰዎች ነበሩ። ቢሆንም ግን፣ ቢሆንም ግን፣ ማናቸውም ቢሆኑ ከኔ ባህርይና ባህል ጋር ከቶውንም የሚስማሙ አለመሆናቸውን ከተረዳሁ ቆይቻለሁ።

እኔ ሃበሻ ነኝ!

ወደድኩም ጠላሁም ሃበሻ ነኝ! የግድ በሃበሻ ምድር ላይ መኖር አለብኝ። እስከ መቼ ከባህር የወጣ አሳ ሆኖ መኖር ይቻላል? የለም! ሁኔታዎች እንዲህ ሊቀጥሉ አይችሉም። በዚህም አለ በዚያ መጓዝ ግዴታዬ ሆኖአል። ከንግዲህ ከደቡብ አፍሪቃ ሩጫ ጋር አብሮ መሮጥ አይቻልም...

በርግጥም ደቡብ አፍሪቃ የሩጫ ምድር ናት።

እስትንፋስ ያለው ሁሉ ይሮጣል። ከማለዳ አንስቶ እስከ

ምሽት ህይወቱ ሩጫ ናት። ከድራክንስበርግ ተራራ አንስቶ፣ ሰፊውንና ለምለሙን የዙሉ ምድር አቋርጦ፣ እስከ ህንድ ውቅያኖስ ዳርቻ… ጫካ ጫካውን የዚያች ምድር አራዊት ሁሉ ህይወታቸው ሩጫ በሩጫ ናት። አንበሶች በጠዋት ተነስተው ደካማ ሚዳቋ ያገኙ ዘንድ እየተመኙ ሩጫ ይጀምራሉ። ሚዳቆች በበኩላቸው ስልቹና ያረጀ አንበሳ ይገጥማቸው ዘንድ እየፀለዩ ሩጫውን ይያያዙታል።

ማን የማይሮጥ አለ?

ነጭ ደቡብ አፍሪቃውያንም ጠዋትና ማታ ሲሮጡ ይታያሉ። እነሱ በርግጥ ስፖርት እየሰሩ ሊሆን ይችላል። ማምሻው ላይ ጥቁሮች ሲሮጡ ካያችሁ ግን ምናልባት ከሁዋላ የሚያሳድዳቸው ፖሊስ ሊኖር ይችላል። ህንዶችና ፓኪስታኖችም ከማለዳ እስከ ምሽት ሲሮጡ ይታያሉ። ሌላ አይደለም። ቢዝነስ ነው። እኛ አበሾችም ታዲያ እዚህ አባባል ላይ የራሳችንን ቀልድ ማከላችን አልቀረም። ምሽት ላይ አበሾችም ሲሮጡ ይታያሉ። የሚሮጡት የመጠጥ መሸጫው መደብር ከመዘጋቱ በፊት ለመድረስ ነው።

…ከሶስት ቀናት በሁዋላ የአይሮፕላን ትኬት ቆረጥሁ። ሃምሌ ማብቂያ ግድም 2001 የግብፅ አየር መንገድ አይሮፕላን የጆሃንስበርግን ምድር በመተው ወደ ሰማይ አሻቀበ። እናም የሰሜንን አቅጣጫ ያዘ። በመስኮት ቁልቁል ወደ ታች አየሁ። ጆሃንስበርግ ማመን በማይቻል ግዝፈት ጧ ብላ ተዘርግታለች። ወርቅ የተቆፈረባቸው ቢጫ ጉድጓዶች የፍልፈል ጉሬ አክለው ታዩኝ።

ቁልቁል አየሁዋት!

ደቡብ አፍሪቃ ሆይ ደህና ሁኚ!

ፀጋው ይብዛልሽ! ላደረግሽልኝ ሁሉ አመሰግንሻለሁ። በነዚያ አሰቃቂ ጊዜያት፣ መጠጊያ ባጣሁባቸው ዘመናት፣ ሁለት እጆችሽን በርህራሄ ዘርግተሽ ተቀብለሽኛልና አመሰግንሻለሁ።

ደቡብ አፍሪቃ ሆይ!

ባዶ እጄን ብመጣብሽም፣ ቸር ነሽና ባዶ እጄን አላሰናበትሽኝም። የቻልሽውን ያህል፣ እንደ ብርታቴ መጠን ወተትና ወርቅሽን አካፍለሽኛል። የክፉ ቀን እናትነትሽ ግን ከወርቅ የላቀ ክቡር ትዝታ ሆኖ በልቤ ውስጥ ይኖራል…





ደቡብ አፍሪቃ ሆይ!

ከብዙ ዘመናት በፊት ኢትዮጵያ የተባለችው ሃገር ኔልሰን ማንዴላን በክብር ተቀብላ እንዳስተናገደችው ሁሉ፣ አንቺም እኛ ሃበሾችን በደግነትና በቸርነት በማስተናገድሽ ምንጊዜም እናከብርሻለን። እነዚያ ደጋግ ወገኖቼም ለሃገራቸው እስኪበቁ በርህራሄ ጠብቂያቸው። እኔ ግን ሄጃለሁ! ለዘልአለሙ ሄጃለሁና ደህና ሁኚ…

- 25 -

# ሰቆቃወ መህቡባ

የኛ ፅጌረዳ ያች! ያማረች፣
ጓደኞቼ! አሁን የት አለች?
ወጥታ ከፀሃይ ጋራ፣
ጠውልጋ ጠፋች እንዴ! አብራ?

* * *

ፍንድቅ! ፍክክ ያሉ! አዳዲስ አበቦች፣
ማበብ ያብባሉ፣
ግን ለቀበጥባጦች፣ የስሜት ማብረጃ፣
ሆነው ይቀራሉ፣

(ግጥም - አሌክሳንድር ፑሽኪን)
- አያልነህ ሙላቱ እንደተረጎመው -

እነሆ! ዱባይ ሰነበትኩ።

ዱባይ ላይ ሶስት አይነት ሃበሾችን ማስተዋል ችዬ ነበር። በሚሊዮናት ዶላር የሚያንቀሳቀሱ፣ አለያም በአነስተኛ ንግድ ተሰማርተው ጥሩ የሚሰሩ ሃበሾች ዱባይ ላይ አሉ። እነዚህ አብዛኞቹ ወንዶች ናቸው። ጥቂት በእድሜ ገፋ ያሉ ሴቶችም አሉ። ሁለተኞቹ ተመላላሽ ነጋዴዎች ናቸው። ዱባይን በሁለተኛ ደረጃ መቀመጫነት ይዘው ወደ ኢትዮጵያና ወደ ሌሎች የአፍሪቃ ሃገራት ይነግዳሉ። ገባ ወጣ፣ ብቅ ጥልቅ ባይ ናቸው። ሶስተኞቹ ወጣት ሴቶች ናቸው።

እነሆ! ወደ እነዚህ የተሸጡ ወጣት አበቦች ጤጋ ብዬ ከረምኩ። ፈራ ተባ እያሉም ቢሆን እነርሱም ቀርበውኛል። ወጣቶቹ ቆነጃጅት፣ ወደ ሃበሻ ዘንድ መቅረብ የማይሹ ቢሆንም





ከመላመድ ብዛት ብዙዎቹ እያቀረቡኝ ሄዱ። የመጠሪያ ስማቸውን ለመያዝ በጣም አስቸጋሪ ቢሆንም፣ አብዛኞቹ ሄለን፣ ፌቨን፣ ራሄል፣ ሃና መሆናቸውን መታዘብ ችያለሁ። በተለይም ኤርትራውያን ሴቶች ከ"ሄለን" ወይ ከ"ፌቨን" ፍንክች አይሉም። እውነታቸውን ነው።

እዚያ ቦታ ላይ በእውነተኛ ስም መተዋወቅ አስፈላጊ አልነበረም። አብዛኞቹ የገላ ሽቀላ ስራ የሚሰሩት ችግሮአቸው እንጂ መች ወደው ሆኖ? የኛዎቹ አበቦች በውበታቸው ተመርጠው ዱባይ ላይ ፈሰውታል። ልቅም ያሉ አበባዎች፣ ፍንድቅ! ፍክክ! ያሉ እምቡጦች፣ ይኸው እዚህ ሃገሩን እንደ ሳር አልብሰውታል። ወደ ሃበሻ ብዙም አይቀርቡም። እምቡጦቹ ከዚህም ከዚያም ሸቃቅለው የሚያመጡትን ሊካፈል ደጅ የሚጠና፣ "ወንድም ጋሻ" ሳይሆን፣ "ወንድም ውሻ" በነዚያ መቆመሪያ ጎሬዎች አካባቢ መታየቱም አልቀረ።

እርግጥ ነው ከገላ ሽቀላው ባሻገር በየሰዉ ቤት ግርድና ተቀጥረው የሚሰሩ እህቶቻችንም አሉ። እነዚህ ግን ስሞቻቸውን ለመደበቅ ብዙ አይቸገሩም።

መህቡባ ኡመር ከእነዚህ አንዷ ናት። ይህን ማስታወሻ ስጫጭር ታዲያ የመህቡባ ገፅታ ብልጭ እያለ መከራዬን ያበላኛል። በልቤ፣ "መህቡባ የት ነሽ? እንወድሻለን" እያልኩ ማንጐራጎሬም አልቀረ። ይህን በምፅፍበት ደቂቃ መህቡባ የት እንዳለች ግን አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው። ምን መህቡባ ብቻ? ያቺ ግንባሯ ላይ የመስቀል ንቅሳት የወቀሩባት የትግራይ ልጅ፤ ማን ነበር ስሟ?

በመቶዎች የሚገመቱ ሃበሻ ቆነጃጅት ሺሻ የሚጨስባቸውን ሻይ ቤቶች ከፍተው ደጅ ደጁን እያስተዋሉ ገበያ ይጠብቃሉ። በአብዛኛው ሱዳናውያንን በደምበኛነት ይዘዋል። ሱዳናውያን ነጋዴዎችና የኛ እህቶች ዱባይ ላይ አንድ የሚያገናኛቸው ክር ተዘርግቷል። ረጅም ዘመን ያደረገ መግባባት ፈጥረው አብረው ይጓዙት ይዘዋል።

ቀን ቀን፣ "የጋዜጠኛው ማስታወሻ"ን በጅምላ ለመሸጥ ወዲያ ወዲህ ስል እውልና ተስያቱ ላይ ሺሻ ቤቶች ገብቼ እሰየማለሁ። ፀሃይ ጨርሳ ስትጠልቅ ደግሞ፣ "DULF" ከተባለ ሆቴል ገብቼ ጃምቦ የድራፍት ብርጭቆ ጨብጬ፣ ጀለቢያ ከለበሱ የአገሬው አባወራዎች ጋር ፑል እጫወታለሁ። ዱባይ

ላይ ከዚህ የተሻለ ላደርገው የምችለው አንዳችም ነገር ላገኝ አልቻልኩም።

* * *

ሺሻ ማጨስ ጀምሬ ነበር።

አልከበደኝም።

ሰዎች ሁሉ እንዲያ ያደርጉ ነበር። የሺሻ ገመዱን አፋቸው ላይ ሰክተው ሲያምበለብሉት ያውላሉ። በሳምንት ጊዜ ውስጥ ሺሻው ሱስ የማስያዝ ባህርይ እንዳለው ለመረዳት ቻልኩ። ካላጨስኩት ትከሻዬ አካባቢ ከመጨምደዱም በላይ ራስ ምታት ይወቅረኝ ጀመረ። ሳጨሰው ደግሞ ልክ እንደ ቤንዚን ሽታ ራሴን ይበጠብጠኝና መልሶ ያረጋጋኛል። ቆነጃጅቱም ቀስ በቀስ ለመዱኝ። አንድ ቀን ከዘለልኩ፣ "ምነው ጠፋህ ታዲያ?" ማለትም ጀመሩ። የልብ የልብ ወደ መጨዋወቱም ገባን። "ወንድም ጋሻ" መሆኔ ባይረጋገጥም፣ "ወንድም ውሻ" አለመሆኔን አስተውለዋል። ገና ብቅ ስል እንዲህ ይሉኛል፣

"Mixed ይሻልሃል ወይስ Nana?"

ይህ እንግዲህ የሺሻው አይነት ነው። ምሳ መብላት አለመብላቴንም ይጠይቁኛል። በመቀጠል፣ "ሺሻ ጋብዘን" የሚል ይከተላል። ስጋብዛቸው ግን አይጠጡትም። ቀመስ፣ ቀመስ ያደርጉና ይተዉታል። የሚቀጥለው ደምበኛም ሲመጣ እንደዚያው ያደርጋሉ። "ጋብዘኝ" የሚለውን ቃል የግብዣውን ገንዘብ ለማግኘት ይጠቀሙበታል። ቀኑን ሙሉ ከደምበኞቻቸው የአንድ ሺሻ ግብዣ ገንዘብ ሲሰበስቡ ይውሉና ማምሻው ላይ ደግሞ ሱዳናውያን ደምበኞቻቸውን በተስፋ ይጠብቃሉ። በአብዛኛው የሚከፍቱት ዘፈን የንዋይ ደበበን፣ "ማእበል" የተሰኘውን ነው። ንዋይ ደበበ፣

*"ወዶ የገባ ሰው ከባህር ከውሃው፣*

*ዋኝቶ ይውጣት እንጂ ሌላ ማን ሊረዳው?"* እያለ ሲዝትና ሲያስፈራራ ይውላል። ከዚህ የዘፈን ምርጫቸው ቆነጃጅቱ የደቡብና የምእራብ ኢትዮጵያ ልጆች ሊሆኑ እንደሚችሉ መገመት ችዬ ነበር።

ዱባይ ላይ የሺሻ ንግዱ ሽፋን ነበር።

ቆነጃጅቱ ተመላላሽ ነጋዴዎችን፣ የአረብ ወጣቶችንና የስራ ጫና ያጐበጣቸውን ፓኪስታኖች በማማለል በሚሰሩት ገላ ሽቀላ ለወላጆቻቸው ደጋፊ ለመሆን የሚያደርጉት ድካም ውስጡ





በስቃይ የተሞላ ነበር። አረቦቹ ልብስ ገዝተው ስጦታ ሰጥተዋቸው ሲያበቁ፣ ሲጣሉ የሰጧቸውን ስጦታ ሁሉ አንድ ባንድ ቆጥረው ይነጥቋቸዋል። በተሻለ ደረጃ ማታለል የቻለች ብቻ ይሳካላታል። በተቀረ የእያንዳንዱ እለት ህይወት የአራት ኪሎውን የኤልሳ ሰፈር የሚያስታውስ ነበር።

ቀይ መብራት አብርታ፣ አምበረጭቃ ተለቅልቃ፣ እጣን አጢሳ፣ ቀጤማ ጐዝጉዛ፣ የቡና ስኒ አቀራርባ፣ አንድ ሁለት ከገጠር የመጡ ወጣቶችን ደጁ ላይ እያንጐራደደች ገበያ የምትጠብቅ ሴት ህይወት!

ትክ ብላ ጐዳናውን እያየች፣ እዚያችው ዛኒጋባ ውስጥ ድንግልናዋን አስረክባ፣ እዚያችው ቱጆ ውስጥ ለዘመናት ገላዋን ያከራየች ሴት ህይወት! የዱባይ ቆነጃጅት ህይወት ቅርፁን ቢለወጥም ይዘቱ ያን ይመስል ነበር።

የኛዎቹ ቆነጃጅት በዚህ አይነቱ ስራ መሰማራታቸውን ማመን አይፈልጉም። በተቻለ መጠን ሃበሾች ፊት ሺሻ በመሸጥ ብቻ የሚተዳደሩ ለመምሰል ጥረት ያደርጋሉ። የስጋታቸው መነሻ ግልፅ ነው። ወሬው ከቤተሰቦቻቸው ዘንድ ደርሶ፣ የቤተሰባቸው ክብር እንዳይነካ ይጠነቀቃሉ። አንዳንዶቹ ስራውን ተላምደውት ለይቶላቸው አደባባይ ወጥተዋል። በባህርያቸው ላይ ለውጥ እየታየ መሆኑን ግን ያስተዋሉት አይመስሉም። አስፀያፊ የብልግና ስድቦች እየቦጠለቁ ካንደበታቸው ሲያመልጣቸው ጆሮዬ ሰምቶአል። በትናንትናው እለት አብረዋቸው ያደሩ አረቦችን ስም እያነሱ እንደ ክትፎ አድቅቀው ይከትፉታል። እንዴትና ምን እንዳደረጓቸው ሳይቀር ድምፃቸውን ዝቅ አድርገው ይጨዋወታሉ። ቀኑን ሙሉ ለሺሻው የሚሆን የምድጃ ከሰል እያያዙ ይህንኑ ያወጋሉ። በጉልበት ስራ የተሰማራ፣ እንደ መቃ የቀጠነ ፓኪስታናዊ ተሳስቶ ድንገት ጥልቅ ብሎ መልሶ ሊወጣ ሲል ማጅራቱን እያነቁ ይጎልቱትና ኪሱን በርብረው ገንዘብ በመውሰድ አንድ ኰካ አጠጥተው ያሰናብቱታል።

እንደ ዱባይ አስቀያሚ ከተማ አይቼ አላውቅም። የህይወት ዘር ያለባት አትመስልም። በገንዘብ ሃይል የተገነቡት ህንፃዎችና በውብ ጐዳናዎቿ ላይ የሚርመሰመሱት እንቁላል የመሰሉ መኪኖች ህይወት ሊዘሩባት አልቻሉም።

*(አፄ ሃይለስላሴ፣ "ዱባይን ጎብኙ" ተብለው ሲጠየቁ፣*

*“ምንድነው የምነበኘው? አሸዋ?” ብለው መጠየቃቸው ተደጋግሞ ይወሳላቸዋል። የዱባይ ንጉሳውያን ቅሬታቸውን አሁን ድረስ አልፋቁትም። ቆነጃጅቶቻችን ግን ለዚያ “አሸዋ” እየሰገዱ ነው። አንድ ውብ የመጣጥፍ ርእስ ታወሰችኝ። “አረብ ወደ እኛ ለግብርና - እኛ ወደ አረብ ለግርድና” ማን ነበር ፀሃፊው?)*

ከአውሮፓና ከአሜሪካ ታላላቅ ከተሞች ጋር የሚስተካከለው የትራንስፖርትና የገንዘብ እንቅስቃሴ ሲስተሙ ነፍስ ሊዘራባት አልቻለም። ዛሬም የሲራራ ነጋዴዎች ሃገር ከመሆን ማምለጥ አልቻለችም። ዱባይ ላይ ሰውም ፖለቲካም ያለ አይመስልም። ከተማዋ ባንክ ቤት ወይም መጋዘን ትመስላለች። በየትም ቦታ ሸቀጣ ሸቀጡን በማዳበሪያ የሚቋጥር ነጋዴ ነው የሚታየው። ከጥቂት ቀናት በሁዋላ ሰው ሁሉ ከተማዋን ለቆ የሚጠፋ ቢመስልም ቋጠሮው ምንጊዜም አለ።

ታላላቆቹን የሌሊት ክበቦች አደርኩባቸው። ሆቴሎቻቸውን አየሁላቸው። ከውቅያኖሱ ዳርቻ አሸዋው ላይ፣ ከዘንባባ ጥላ ስር ተኝቼ ከአመት አመት ደመና አልባ የሆነ ሰማያቸውን እያየሁ ዋልኩ። ዱባይ በርግጥም አንድ የጐደላት ነገር አለ። ያ ነገር ህይወት ነበር። ህፃናት የታሉ? ሽማግሌዎች የታሉ? ተማሪዎችስ? ኳስ የሚጫወቱ ህፃናት እዚህ ለምን የሉም? መፅሃፍና ጋዜጣ የሚያነቡ ሰዎች ለምን አይታዩም? ለመሆኑ እዚህ አገር ለቅሶ አለ? ቀብር አለ? ሰርግ ያደርጉ ይሆን?

“አላህ አ'ክበር!” የሚለውን ድምፅና ዜማ ከልጅነቴ ጀምሬ በፍቅር እወደዋለሁ። ይህ የፀሎት ድምፅ በምናብ ሩቅ ይዞኝ ይሄዳል። ይህ ድምፅ በትክክል እግዚአብሄር ጋር የሚደርስ ድምፅ መስሎ ይሰማኛል። “አላህ አ'ክበር!” የሚለው ድምፅ ከተሰማ በሁዋላ በመካከሉ የሚኖረው የፀጥታ ክፍተት ድምፁ ፈጣሪ ካለበት ሰማይ ጋር እስኪደርስ በሚል የሚተው ክፍተት መስሎ ጭምር ይሰማኛል። እዚህ ዱባይ ግን ይህም አላማረባት! ዱባይ የሙስሊም ከተማ መሆን እንኳ አልቻለችም። ዱባይ እንደ ካይሮ፣ አለያም እንደ ጂጃ እስላማዊ ይዘትና ታሪካዊ እሴት የላትም። እንደ ኬንያ የቀጭኔና የዝሆን ምድር መሆን አልቻለችም። የራሷ መለያ ነገር ላይባት አልቻልኩም። ከየት እንደመጡ የማይታወቁ ሰዎች እቃ ሲጭኑና ሲያርግፉባት





ውላ የምታድር፣ አንግታ የምትውል፣ እቃ በእቃ የሆነች የሲራራ ነጋዴዎች ከተማ!

አንድ ቀን እንደተለመደው ሺሻ እያጨስኩ ደጅ ደጁን እያስተዋልኩ ነበር። በየወንበሮቹ ላይ ተቀምጠው ደምበኛ የሚጠብቁት ቆነጃጅት ድንገት መጨቃጨቅ በመጀመራቸው እንደዋዛ ጆሮዬን ጣል ማድረጌ አልቀረም። ሶስት ነበሩ። ሁለቱ ጥርሶቻቸው ቢጫ በመሆናቸው የናዝሬት ወዲያ ማዶ ልጆች መሆናቸውን ገመትኩ። ቀሪዋ ሴት ግንባርዋ ላይ የመስቀል ንቅሳት አለባት። የአክሱም ልጅ ስትሆን፣ አማርኛዋ ትግሬ መሆኗን ያሳብቃል። በጣም ቆንጆ ነበረች። ምን ዋጋ አለው? ግንባርዋ ላይ ጉብ! ያለው መስቀል ውበቷን ድራሹን አጥፍቶታል። እሷም ያንን መስቀል እንደጠላችው ተረድቻለሁ። የመስቀሉ አንድ እጅ ተፈቅፍቆ ደብዝዞ ነበር። ልታጠፋው ሞክራ አልተሳካላት ይሆናል። ገጠር እንኳ ደህና። ያን መስቀል ግንባር ላይ ይዞ ከተማ መግባት ግን አስቸጋሪ ነው። ከተሜው መቼ ጤና ይሰጥና? ያን መስቀል ይዞ ዱባይ መምጣት ደግሞ ትራጀዲውን ኮሜዲ ያደርገዋል።

ልጅቱ መስቀሏን ግንባሯ ላይ እያውለበለበች ደጅ ደጁን ስትመለከት አያሌ አሳቦች ወደ አእምሮዬ መጥተዋል። በኦርቶዶክስ እምነት ስር በጥብቅ ስነስርአት ያደገች ሴት...ሙስሊም ሃገር መጥታ ስጋዋንና መስቀሏን ለፓኪስታንና ለሱዳን መንገደኞች ስትሰጥ...መስቀሏን ፈቅፍቃ ለማጥፋት ያደረገችው ሙከራ...ይህ ግጭት ሊያሳድርባት የቻለው የስነልቦና ቀውስ...

*(....ይህን ምእራፍ በምፅፍበት ወቅት መለስ ዜናዊ የህወሃትን 20ኛ አመት በአል ለማክበር መቀሌ ሄዶ ነበር። ድምፁን ከፍ አድርጎ፣ “የትግራይን ህዝብ አንገቱን ቀና አድርጎ በኩራት የሚራመድበት ደረጃ ላይ አድርሰነዋል” ብሎ ሲናገር በሬድዮ ሰማሁት። መለስ ማንኛውንም ነገር በሁለት ከፍሎ ማየት ይወዳል። የትግራይ ህዝብም በሁለት ሳይከፈል አይቀርም። አንገታቸውን ቀና ያደረጉና አንገታቸውን የደፉ።*

*ከቆነጃጅቶቻችን የወሲብ ሸቀላ ባሻገር በጉዲፈቻ ስም የሚሸጡ ህፃናት አይንና ሳንባ እንደ መለዋወጫ እቃ እየተቸበቸበ ስለ መሆኑም ዜናዎች አሉ። በተለይም ግብፅ አካባቢ ኩላሊታቸውን በግድ የሚነጠቁ ሃበሾችና ሶማሊያውያን*

*ቁጥር እያሻቀበ ሄዶአል።)*

ሶስቱ ሴቶች መጨቃጨቅ ሲጀምሩ እንደዋዛ ጆሮዬን ጣል አደረግሁ። የሚጨቃጨቁበት አጀንዳ ትኩረቴን ስለሳበው በጥሞና እያዳመጥሁ ደጅ ደጁን መመልከቴን ቀጠልኩ። የድምፃዊ ቴዲ አፍሮ የመታሰር ጉዳይ ነበር ያጣላቸው። ባለመስቀሏ ኰረዳ ሽንጧን ገትራ ትሟገት ይዛለች፣

"ያለጥፋቱማ አልታሰረም! በመኪናው ሰው ገጭቶ ገድሏል። ሰው ገድሎ በነፃ እንዲለቀቅ ትፈልጊያለሽ?"

"ሲገድል የት አየሽው? አውቀው ራሳቸው ገድለው ነው በሱ ያሳበቡት። ዜና ብትሰሚ ይህን ባወቅሽ! ሞተ የተባለው ልጅ የሞተ ቀን ቴዲ ኢትዮጵያ ውስጥ አልነበረም። አንቺ ግን እነ መለስ ዘሮችሽ ስለሆኑ ነው የምትከራከሪላቸው!"

"ዘሮቼ ስለሆኑ አይደለም። ለኔ ምንም አላደረጉልኝም"

"ታዲያ ምን ያከራክርሻል?"

"በመኪና ሰው ገጭቶ ገድሎ ስለሸሸ ታስሮአል!" ብላ በቁጣ ስትጮህ፣ ባለ ቢጫ ጥርሶቹ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በሹፈት መልክ ሳቁባት። "ተባለ እንዴ? ተባለ እንዴ?" እያሉ በዜማ ሲስቁባት ይበልጥ እየጋለችና እየተናደደች ሄደች። ከአማርኛው እጥረት ጋር ተዳምሮ አሳቧን በትክክል ማስረዳት ተስኖአት ነበር። የባለመስቀሏ ሴት ንዴት በጋለ ቁጥር ባለቢጫ ጥርሶቹ የከርከር ርእሳቸውን አሰፉት፣

"መለስ ዜናዊ የሚሰራውን ግፍ ልትደብቂለት ትፈልጊያለሽ? የቴዲን ተይው! አገር ያወቀው፣ ፀሃይ የሞቀው ወሬ ነው። ከፈለግሽ ግን ሌላም ልጨምርልሽ! ሌላው ቀርቶ እኛ እዚህ ሽሌ የሆንነው መለስና የዱባይ ሼክ ተነጋግረው ሸጠውን ነው..."

ባለመስቀሏ እጇ ብቻ ሳይሆን ከንፈሮቿና ጉንጮቿ ተንቀጠቀጡ። በቁጣና በእልህ ስሜትም እንዲህ አለች፣

"እዚህ የመጣሽው ወደሽ ፈልገሽ ነው። ገንዘብሽን ከስክሰሽ፣ ለቪዛ ከፍለሽ፣ የምን መለስ ላይ ማሳበብ ነው?"

ባለቢጫ ጥርሶቹ አልተበገሩም፣ ሞገቷት፣

"ገንዘቤን ከፍዬ ብመጣም የዚህ አገር ሼክና መለስ ግን ተፈራርመዋል። እኛ እዚህ እንድንመጣ ሲፈራረሙ በቲቪ ታይቶአል። መለስ ዜናዊ እዚህ መጥተን ሽሌ እንደምንሆን





እያወቀ አሳልፎ ሰጠን። ደሞ ሃገር ቤት ስራ የለም። ስለዚህ ነው ወደዚህ የመጣነው። መለስ ቢፈልግ ስራ እንድናገኝ ማድረግ አይችልም? ከፈለገ ይችላል። ግን አልፈለገም። እናውቃለን! የማናውቅ አይምሰልሽ። ፋራ ዘረኛ አትሁኝ። መለስ ወርቅ ቢልሽ፣ እውነት አይምሰልሽ። እኛም ሽሌ! አንቺም ሽሌ!"

ባለመስቀሏ ተቆጥታ በስሜት እግሯን ስትዘረጋ የሺሻ ማጨሻያውን በእግሯ ስለመታችው እሳቱ ተከነበለ። ውሃው ተደፋ። ቆነጃጅቱ ንትርካቸውን በመተው እሳቱ የፕላስቲክ ወለሉን እንዳያቃጥለው ተረባረቡ። እየተንጫጩ እሳቱ ላይ ውሃ ደፉበት። የተደፋው ውሃ የኔን ጫማ ጭምር በማጠቡ ሂሳቤን ከፍዬ ወጣሁ።

በነጋታው በተመሳሳዩ ሰአት ወደዚያ ቤት ብቅ ስል ባለመስቀሏ ብቻዋን ነበረች። ሺሻ አዘዝኩና ቁጭ አልኩ። እንደዋዛም ወግ ጀመርኩ፣

"ጓደኞችሽ የት ሄዱ?"

"ይመጣሉ"

"ትናንት ትጨቃጨቁ ነበር። ምን ሆናችሁ ነው?" ስል በትግርኛ ጠየቅሁዋት።

የትግርኛ ቃላት ከአንደበቴ ሲወጡ በመስማቷ ወዲያውኑ ጨፍግጎ የነበረ ገፅታዋ ሁሉ ፈካ። ፈገግ አለች። እንደ ጨረቃ ደማመቀች። ጥርሶቿ ነጭና ችምችም ያሉ ውብ ነበሩ። እዚህ ግንባሯ ላይ ከተደነቀረው መስቀል በቀር ልቅም ያለ ውበት ነበራት። በተለይ ፈገግ ስትል ውስጧ ሃይል ያላት ንቁ ልጅ መሆኗን ማስተዋል ይቻል ነበር። ለጠየቅሁዋት ጥያቄ በስሜት ምላሽ ሰጠችኝ፣

"ሆን ብለው ነገር ይፈልጉኛል። እኔ ላይ እየተጣቀቀሱ መለስን ሲሰድቡት ይውላሉ። መጀመሪያ መለስን ሲሰድቡት አይሰማኝም ነበር። ቢሰድቡት ባይሰድቡት እኔ ምን ያገባኛል? በሁዋላ ግን እኔ ትግሬ ስለሆንኩ ሆን ብለው እኔን ለማናደድ መለስን እንደሚሰድቡት ሳውቅ እልህ ያዘኝ! ትግሬ ስለሆንኩ ብቻ አውቀው አሽሙር ይናገራሉ! እኔ እዚህ የመጣሁት እንደነርሱ እንጀራ ፍለጋ ነው። መለስ ለኔ ምን አደረገልኝ? በየቀኑ ስለቴዲ አፍሮ ያነሳሉ። እኔ ነኝ እንዴ ቴዲን ያሰርኩት? በአሽሙር ይሰድቡኛል! እልህ ይዞኝ 'ሰው ገድሎ ነው የታሰረው!' ስል ይስቁብኛል። እኔ ተናድጄ ነው እንጂ ቴዲ

ይግደል አይግደል አላውቅም። ግን ለምን ፖለቲካ ያወራሉ? መለስ ትግሬ ናት ብሎ ቢጠቅመኝ ኖሮ እኔ እዚህ ምን ላደርግ እመጣለሁ? እንደዚህ ብዬ ስነግራቸው ደግሞ፣ 'ስለላ ይሆናል፣ ማን ያውቃል?' እያሉ አፋቸውን እያጣመሙ አሰቃዩኝ? እኔ እነሱን ልሰልል ብዬ እዚህ ራሴን ሳዋርድ እውላለሁ?"

ይህን ብላ ስታበቃ እንባዋ ግንፍልፍል ብሎ ባንድ አፍታ ሙሉ ጉንጯን አጠበው። ትከሻዋ እየተናጠ ከውስጥ ከልቧ ውስጥ የተፈነቀለ የእልህ እንባ ስታነባ እዚያው ቁጭ ብዬ አየሁዋት። ይህን መሰል የእልህ እንባ ጥርግርግ ብሎ ካልወጣ እውስጥ ቀርቶ ህመም ስለሚሆን ለጥቂት ደቂቃዎች ዝም አልኳት። ሲበቃት ወደ መፀዳጃ ቤት ገብታ ተጣጥባ ተመለሰች፣

አፅናናሁዋት!

ባለቢሜ ጥርሶቹ ያን ያደረጉት ባለማወቅ መሆኑን አጫወትኳት። እነርሱ ባለማወቅ በሚናገሩት ተገፋፍታ ደግሞ የመለስ ጠበቃ ሆና እንዲህ እስክትጐዳ መሆን እንደሌለባት መከርኳት። ባለቢሜ ጥርሶቹ ዘረኛ የሆነ ንግግር መናገራቸውን በግልፅ ነገርኳት። እነርሱ ዘረኛ ዝንባሌ የያዙት ግን እነመለስ በሚፈፅሙት ዘረኛ ድርጊቶች ምክንያት ሳያውቁት ገብተውት መሆኑንም በርጋታ አስረዳሁዋት።

ይህን ተናግሬ ሳበቃ ለመሄድ ተዘጋጀሁ።

ከመሄዴ በፊት ግን እንዲህ አለችኝ፣

"እኔ ፖለቲካ አላውቅም። ትግሬ ስለሆንኩ ነው የጠሉኝ"

"ልክ ነሽ!" አልኳት "...ትግሬ ስለሆንሽ ብቻ ሊጠሉሽ እንደቻሉ አውቃለሁ። የውልሽ የኔ ቆንጆ፣ ከልቤ አንድ ነገር ልንገርሽ? ኢትዮጵያ ውስጥ የትም ቦታ ብትሄጂ ትግሬና ወያኔን ለያይቶ የሚያይ የለም። እነ መለስ ትግሬ እንዲጠላ የሚያደርግ ተግባር ስለፈፀሙ የተከሰተ ጊዜያዊ ቁጣ ነው። አማርኛ የሚናገሩ መሪዎች በፈፀሙት ግፍ ምክንያትም ከብዙ አመታት በፊት ትግሬዎች በተመሳሳይ እንዲሁ አማራን ሁሉ በጅምላ ይጠሉ ነበር። አሁን ተገላቢጦሽ ሆነ። ይህ ግን አይቀጥልም። ጊዜያዊ እንደሆነ አረጋግጥልሻለሁ። ከነመለስ መወገድ ጋር አብሮ ሊወገድ ይችላል። በቅርቡ ስለ ዘር ማውራት የጥንት ታሪክ ይሆናል!!"

ተሰናብቼያት ስወጣ መጨረሻ ላይ የተናገርኩት አረፍተ ነገር ጆሮዬ ላይ ተመልሶ ጮኸብኝ። አረፍተነገሩ ራሴንም





አላሳመነኝም። ስለ ዘር ማውራት የጥንት ታሪክ የሚሆንበት ጊዜ ቅርብ ስለመሆኑ ለመናገር አንዳችም መነሻ አልነበረኝም። ፕሮፓጋንዳ ብቻ ነበር። በርግጥም ከባለ መስቀሏ ስቃይና ሮሮ ማምለጥ ስለፈለግሁ እነዚያን ቃላት ተናግሬያለሁ። ምኞት አይከለከልም። መልካም ቃላትን መግለፅም አያስወቅስም። እነዚያ በጐ ቃላት የህልም ወተት ብቻ ከሆኑ ግን ከቶ ምን ፋይዳ ይኖራቸዋል? የዚያች ልጅ የምሬት እንባ አሁን ድረስ ይታየኛል። እርር ምርር ብላ ነበር ያነባችው። በትግርኛ ስላዋራሁዋት ሆድ ብሷት እንባዋን ዘረገፈችው። 'ከወገኖቼ አንዱ ነው' ብላ ላመነችው ሰው የልቧን ተነፈሰች። ርግጥ ነው አልተሳሳተችም። እኔ ለዚህች ሴት ታማኝ ነኝ። የትግራይን የገበሬ ልጆች "እርሶ አደሩ" በተባለ የጅምላ ቃል ስር ብቻ አይደለም የማያቸው። የትግራይ የገበሬው ልጆች ከጐጃም የገበሬ ልጆች የሚለዩበት አንዳችም ልዩ ነገር የለም። ከዚያም ባሻገር የአፍሪቃ ቀንድ ገበሬዎች ከአንድ ምንጭ የተቀዱ ናቸው። ባለመስቀሏና ባለቢሜ ጥርሶቹ ለምን እንደተጋጩ አያውቁም። ክብርን በሚያዋርድ የስራ መስክ ላይ በአንድ ጣራ ስር ተቀምጠው ይናጫሉ። ግን ለምን? ምላሹ አጭር ነው። የሚያስታርቅ ጠፍቶ፣ የእብድ ገላጋይ በዝቶ!

የሚያስታርቅ የሚነግስበትና የእብድ ገላጋይ ሰሚ የሚያጣበት እለት መቼ ይመጣ ይሆን? ለዚያች ለተገፋች የትግራይ ሴት፣ "ያለ ሃጢአትሽ በእሳት የምትለበለቢበት ዘመን በቅርቡ ያበቃል" ብዬ መከታ እንደሚሆን ወንድም ጋሻ ተስፋ ሰጥቼያታለሁ። የሰጠሁዋት የምኞት ተስፋ ብቻ ስላለመሆኑ ግን አላውቅም። ለመሆኑ ይህን ተስፋ እውን ሊያደርጉልን የሚችሉ ወንድም ጋሻዎች የት ገቡ? እህት ጋሻዎች የት ተሰወሩ? እንደ ማለዳ ጉም ብን! ብለው ጠፍተዋል? ይችን በምጫጭርባት ደቂቃ ያች ባለመስቀል ቆንጆ ዱባይ ላይ እየተዋረደች ነው። አልፍርጅ ምራር ወደተባለው ሰፈር ብቅ ካላችሁ ታገኟታላችሁ። ያች ልጅ ትግሬ ናት። ወያኔ ግን አይደለችም። ዱባይ ላይ እንደፈሰሱት እህቶቻችን ወዲያ ወዲህ ብላ ቤተሰቧን ለመርዳት እየጣረች ነው።

የተጀመረው የዘረኛነት ነበልባል እሳት መቼ እንደሚያቆም ለመተንበይ እንደ ኤልያስ ነቢይ መሆን አስፈልጎናል። ነቢይ መውለድ እንችላለን። ከመካከላችን

ሊመሩን የተነሱትን መዝነን መዝመት ካልቻልን ነቢይ ከሰማይ አይወርድልንም። ካስተዋልናቸው መሪዎቻችን አጠገባችን አሉ። ካላስተዋልናቸው መህቡባ ኡመር ያለወንድም ጋሻ መቅረቷ ነው። ለመሆኑ ማናት መህቡባ?

* * *

አንድ ቀን፣ "የጋዜጠኛው ማስታወሻ" የተባለውን መፅሃፍ በካርጐ ወደ ዋሽንግተን ዲሲ ልኬ ካበቃሁ በሁዋላ፣ እንደተለመደው ቀዝቃዛ ድራፍት ፍለጋ ወደ DULF HOTEL በረርኩ።

በግምት ከአንድ ሰአት በሁዋላ ሶስት ወንድ ሃበሾች ወደነበርኩበት ባንኮኒ አካባቢ መጡ። አንድ ወር ሙሉ እዚህ ሆቴል በየቀኑ ስመጣ የሃበሻ ፊት አላየሁም ነበርና የነዚህ ሃበሾች ድንገት በኔ ዙሪያ መገኘት ሳያጠራጥረኝ አልቀረም። ሁኔታቸውና አስተያየታቸው ደስ የማይል አይነት ሆነብኝ። አንደኛው በተለይ ነፍሰ ገዳይ ይመስላል። ጃፖኒ ለብሶ ነበር። የዘንዶ ምስል ክንዱ ላይ አስቀርፆአል። ቁምጣ ለብሶአል። "ግብዳ" የሚባለው አይነት ግዙፍ ሰው ነው።

ግብዳው ቮድካ መጠጣት ሲጀምር ሌሎቹ ዊስኪ አዘዙ። ባለጌ ወንበሩ ላይ የተቀመጡ ሲሆን በመካከላችን ያለው ርቀት የሁለት ወንበሮች ብቻ ነበር።

ወጠምሻው ጐረምሳ፣

"አበሻ ነህ አይደለም?" ሲል ጠየቀኝ።

"ነኝ አዎ!" አልኩ።

"የማውቅህ ይመስለኛል"

"የት ነው የምታውቀኝ?"

"እንጃ! የሆነ ቦታ ያየሁህ ይመስለኛል"

"ሊሆን ይችላል። እኔኳ አላውቅህም"

"ዱባይ የነጋዴ አገር ነው። አንዱ ይገባል። ሌላው ይወጣል። የሰው ፊትም የዚያኑ ያህል ይምታታል። ለማንኛውም መልካም ትውውቅ። ብቻህን ከሆንክ ከኛ ጋር መቀላቀል ትችላለህ"

"አመሰግናለሁ!" አልኩ።

ሶስቱ ሃበሾች በራሳቸው የሞቀ ወሬ ተጠመዱ። ጆሮዬን ጥዬ አዳመጥኳቸው። ከድለላ ስራ ጋር የተያያዙ ወጐች





ነበራቸው። በተለይም ወደ አንጐላ ስለተላኩ የውሃ መሳቢያ ጄኔሬተሮች ጉዳይ ነበር የሚጨዋወቱት።

እንደተለመደው ብጫቂ ወረቀቶቼን አውጥቼ የእለት ገጠመኞቼን ስመዘጋግብ ጥቂት እንደቆየሁ ሁለቱ ሃበሾች ወጠምሻውን ተሰናብተውት ሄዱ። ይህን ጊዜ እንደገና ሊያናግረኝ ሞከረ። እያመነታሁ አጭር ምላሽ ሰጠሁት። ፊት ብነሳውም ማዋራቱን ገፋበት። እኔም እያጠናሁት አጫጭር ምላሽ ስሰጠው ቆየሁ።

ቀስ በቀስ ግን መግባባት ጀመርን። በቅጡ ወግ ስንጀምር አሪፍ ልጅ መሆኑን በመሃላ ማረጋገጥ ከምችልበት ደረጃ ላይ ደረስኩ። እንዲያውም ባለጌ ወንበሮቻችንን አጠጋጋናቸው። መገባበዙንም ተያያዝነው፣

"አንድ ወር ሙሉ እዚህ ዱባይ ስቀመጥ አንተን ባለማወቄ እንዴት ያሳዝናል?" እስከ ማለት ደረስኩ።

እሱም፣ "የሚደንቅ ነው። ሲያዩህ ሰው የምትንቅ ትመስላለህ። ሲቀርቡህ ግን የእግዚአብሄር በግ ነህ!" አለኝ።

"ልክ ነህ!" አልኩት "እንዳልከው በግ ነኝ። ከበግም በግ። የበጎች ሁሉ በግ። አንተም ብትሆን የእግዚአብሄር ፈረስ ነህ። ለመሆኑ ማነው ስምህ?"

እየተደናነቅንና እየሳቅን መገባበዙን ተያያዝነው።

ሞቅ ሊለኝ ጀምሮ ሊሆን ይችላል።

ቢሆንም ከሙሉጌታ ጋር ጥቂት መቆየት ፈለግሁ። ዘወትር ከትከሻዬ የማትለየውን የእጅ ቦርሳዬን በመክፈትም "የጋዜጠኛው ማስታወሻ"ን ኰፒ በማውጣት አሳየሁት። እያገላበጠ ሲመለከተው፣

"አንብበሽዋል?" ስል ጠየቅሁት።

"መፅሃፍ አንብቤ አላውቅም"

"እኔ ነኝ የፃፍኩት! በስጦታ ሰጥቼሃለሁ!" አልኩት።

ማመን እያቃተውም ርእሱን አነበበውና፣

"ስለዚህ መፅሃፍ ሰዎች ሲያወሩ ሰምቻለሁ። አንተ የዚህ መፅሃፍ ደራሲ ነህ?" ሲል በአድናቆት ጠየቀኝ።

"ልክ ነህ!"

"ከዚህ መፅሃፍ ደራሲ ጋር ነው እያወራሁ ያለሁት?"

"አልተሳሳትክም!"

በረጅሙ ስቆ በግብዳ እጁ ጨበጠኝ። መፅሃፉ ላይ

እንድፈርም ካደረገኝ በሁዋላም፣

“ምን መስለኸኝ እንደነበር ልንገርህ?” አለ።

“ንገረኝ?”

“የመኪና ጐማ ነጋዴ!”

“ኸረ በጊዮርጊስ! ምኔ ነው የጐማ ነጋዴ የሚመስለው?”

“እንጃ! ብቻ እንደዚያ መስለኸኝ ነበር”

ሁለታችንም ስለራበን DULF ሆቴልን በመተው ወደ ሃበሻ ምግብ ቤቶች ተያይዘን መንገድ ጀመርን።

ጨልሞ ነበር።

መኪናው እንደተበላሸችበት ነገረኝና በእግር ጉዞ ጀመርን። ዋናውን አስፋልት በመከራ ተሻገርን። ‘አቋራጭ መንገድ አሳይሃለሁ’ አለኝና ወደ ሹሉክሉክ ቀጫጭን መንገዶች ውስጥ ገባን። ጨልሞ ነበር። የአበሻ ሺሻ ቤቶችን እያቋረጥናቸው በደጃፎቻቸው ስናልፍ ሴቶቹ ብቅ እያሉ፣

“ሙሉጌታ! ሙሌ! ና ግባ!” እያሉ አስቸገሩት።

“እመለሳለሁ! አሁን ከእንግዳ ጋር ነኝ! ራት በልቼ እመለሳለሁ...” እያላቸው አልፈናቸው ጉዞ ቀጠልን።

“ምን ትሰራለህ ዱባይ ላይ?” ስል ጠየቅሁት።

“ደላላ ነኝ!”

“ምን መስለኸኝ እንደነበር ልንገርህ?” ስል ጠየቅሁት።

“ምን መሰልኩህ?”

“የወያኔ ጆሮ ጠቢ”

“በስመአብ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ!” ብሎ አማተበ።

እኔ ስስቅ እሱ ቀጠለ፣

“እስኪ አሁን ምኔ ነው ጆሮ ጠቢ የሚመስለው? እየቀለድክ መሆን አለበት።”

በመገረም አየኝናም፣

“ለዚህ ነው ግንባርህን ጨምድደህ የነበረው? እኔ ደሞ የመኪና ጐማ ትርፍ ያሳበጠህ መስሎኝ? የመኪና ጐማ የሚነግዱ እዚህ ብዙ ዝቀዋል። ሰሞኑን ሌላ ንግድ የለም። እንዴት እንደራበኝ ልነግርህ አልችልም። እዚህ ዱባይ አልሃበሻ ሬስቶራንት ነው አሪፍ። ጥሩ ዱለት ይሰራሉ...”

በልተን ስናበቃ ወደ መጠጡ ተመለስንበት።

እኩለ ሌሊት ድረስም አብረን ቆየን። ስንለያይ ታዲያ እንዲህ አለኝ፣





“ነገ ቅዳሜ ነው። እቤቴ ምሳ ልጋብዝህ? ሚስትም አለችኝ። አንዳንድ ጓደኞቻችንም ስለሚመጡ ጥሩ ጊዜ እናሳልፋለን። መኪና ይዤ ካረፍክበት ሆቴል መጥቼ ልወስድህ እችላለሁ። ምን ይመስልሃል? ከደራሲ ጋር ስተዋወቅ ይሄ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነው። ፎቶም እንድንነሳ እፈልጋለሁ። ይችን የሰጠኸኝን ደግሞ ሌሊቱን ማንበብ እጀምራለሁ። መፅሃፍ አንባቢ እንኳ አይደለሁም። ግን እንደምንም አነባታለሁ። ምን ይመስልሃል ታዲያ ነገ?”

ተስማማሁ።

ያንን ግብዣ በመቀበሌም መህቡባ ኡመር ከተባለች ልጅ ጋር ለመተዋወቅ በቃሁ። በኋላታው “የእግዚአብሄር ፈረስ” ካረፍኩበት ሆቴል ድረስ መጥቶ፣ “የእግዚአብሄርን በግ” በመኪናው ጭኖ ወደ ቤቱ ይዞት ሄደ...

* * *

ጠንካራ ግብዣ ጠበቀኝ።

የምግብና የመጠጥ አይነቶች ጠረጴዛውን ሞልቶት ነበር። በርግጥ ግብዣው ለኔ ተብሎ የተዘጋጀ አልነበረም። ሙሌ ደላላ እንደመሆኑ በርካታ ገቢ የሚያስገኙ ተግባራትንም ጐን ለጐን ይሰራል። በዱባይ ከሃብታም አረቦች መኖሪያ ቤት በግርድና ስራ ተቀጥረው የሚሰሩ ቆነጃጅት፣ በወር አንድ ቀን እረፍት ያገኛሉ። ቅዳሜ ማለዳ ይወጡና እሁድ ማለዳ ተመልሰው ከስራ ገበታቸው ላይ ይገኛሉ። ይህች እረፍት የ24 ሰአት ወርሃዊ እረፍት ተብላ ትታወቃለች። አበሾቹ ቆነጃጅት ታዲያ ይህችን የ24 ሰአት እረፍት በአግባቡ ሊጠቀሙባት ይሻሉ። እንጀራ ይናፍቃቸዋል። የሃበሻ ፊት ይናፍቃቸዋል። በሃገር ቋንቋ ሳቅና ጨዋታ ያምራቸዋል። አዳዲስ የመጡ ዘፈኖችና ድራማዎችንም ማየት ይፈልጋሉ። ቅዳሜ ሌሊቱን የሚተኙበት አልጋ ማግኘትም ሌላው ጉዳይ ነው። በየወሩ ይህን ሁሉ አሟልቶ የሚያዝናናቸው ወዳጅና ወገን ዱባይ ላይ ማግኘት ደግሞ የሚቻል አይደለም። ሙሌ ታዲያ አንዳንድ የሚያውቃቸውን ቆነጃጅት እሱ ዘንድ እንዲያርፉ ያደርጋቸዋል። ሁሉንም አዘጋጅቶ ይቀበላቸዋል። ይህን በማድረጉ መጠነኛ ክፍያ ያስከፍላቸው እንደሁ ግን አላውቅም። ሊሆን ቢችል ለሁለቱም ጠቃሚ ነው።

የሆነው ሆኖ በዚያን እለት ተስያት ከሙሌ መኖሪያ ቤት ስደርስ ጠንካራ ግብግ ጠበቀኝ። ቢራው፣ ዊስኪው፣ ቮድካው፣ ቪኖው ምን የቀረ አለ? ምግቡስ ቢሆን? ዱለቱ፣ ቀይ ወጡ፣ ጥሬ ስጋ እንኳ አልቀረም። በዚያች አንድ ክፍል ቤት ውስጥ ሁሉም ነገር ተሟልቶ ነበር። የቡና እቃውም ቀራርቦአል። እጣኑ እየጨሰ ነው። ፈንዲሻው ገና ድሮ ፈነዳድቶ በእንቅብ ሞልቶ፣ ከበረዶ የተሰራ ተራራ መስሎአል። አምስት ቆነጃጅት በዚያች ክፍል ውስጥ ይርመሰመሳሉ። በርግጥ የሙሌ መኖሪያ አንድ ክፍል ትሁን እንጂ ሰፊ ናት።

እኔና ሙሌ ብቻ ነበርን ወንዶች።

የምንጠበቀውም እኛው ነበርንና እንደገባን ምግቡ ቀረበ። መጠጡ ወረደ። ቡናው መቆላት ጀመረ። እጣኑ እንደ ጠባዩ ወደ ሰማይ አቀና። ቴሌቪዥኑ ተከፈተ። ሲዲ አጐረሱት። ከበበው ገዳ፣ "ጋሽ ፎሊሱ!" እያለ መዝፈን ጀመረ። አየሩ ቃጠሎ ባይሆን ኖሮ ደብረዘይት ስላለመሆኔ አንዳችም ማረጋገጫ አልነበረም።

ከሁሉም አይነት ምግብ በላሁ። ጣፋጭ ነበር በጣም። ጥሬ ስጋውንም በሰናፍጭ እያጣቀስኩ አፈር ድሜ አበላሁት። ሁላችንም ከመጥገብ በላይ ጠገብን። በመቀጠል የመጠጥ ጉዳይ ተነሳ። እኔና ሙሌ የቮድካውን ጠርሙስ ለሁለት ያዝነው። ሴቶቹ ሄይኒከን የተባለውን ቢራ እና ለስላሳ እንደየፍላጎታቸው ያዙ። ቀለል ይለን ዘንድ ቁምጣና ቲሸርት ለበስን።

የቀረ ነገር አለ እንዴ?

አይመስለኝም።

ከበበው ገዳ እየቀለደ እኛ መጠጣቱን ተያያዝነው። ትናንት ለሙሌ ፈርሜ የሰጠሁት መፅሃፍ ከቴሌቪዥኑ አጠገብ ጠረጴዛው ላይ ቁጭ ብሎ ይታያል...

ሰከርን።

እኔ እንኳ መስከር ትቻለሁ።

ሞቅ ይለኛል፤ አለያ ባለሁበት ድንዝዝ እላለሁ እንጂ የመስከርና ያለመስከር ልዩነቱ ራሱ ጠፍቶብኛል። በሞቅ መንፈስ በሞባይል ካሜራዎች ፎቶግራፍ ተነሳን። እዚያ ያለነው ሁሉ የአንድ ሃገር ልጆች ነን። የአንድ ባህል ግርፎች ነን። ከምንለያይበት ይልቅ የሚያግባቡን እሴቶች በርክተው ነበርና ከመደሰት በቀር የሚረብሸን አንዳችም እንቅፋት አልነበረብንም።





መህቡባ አጠገቤ ተቀምጣለች።

ቀስ በቀስ በግል መጨዋወታችን አልቀረም። አፍንጫ የሚባል ነገር አልነበራትም። በጣም ታምራለች! ስትስቅ ሁለቱ ጉንጮቿ ከአፍንጫዋ ጋር እኩል ይሆናሉ። እና ሶስት አፍንጫ ያላት ትመስላለች። ውበቷ ደሞ እዚያ ላይ ነበር። ጥርሶቿ የጅማ ወተት ይመስላሉ። እሷም የጅማ ልጅ ናት።

መህቡባ!

ስሟ ደሞ ደስ ሲል?

አጠር ያለች ጠይም የደም ገንቦ! እድሜዋ 23 ደርሶአል። ከአንድ ሃብታም አረብ ቤት በግርድና ተቀጥራ እየሰራች መሆኑን እያጫወተችኝ ነበር። ሁሉንም ስራ ያሰሯታል። ቤት ትወለውላለች። ልብሶች ታጥባለች። ልብስ መተኮሱ ነበር ከባዱ ጣጣ። እና እንዲህ አለችኝ፣

"እባያ አቃጠልኩና የወር ደሞዜ ተቆረጠ"

"እባያ ምንድነው?"

"እስላም ሴቶች የሚለብሱት ጥቁሩ ልብስ"

በዚህ መልኩ ወጋችን ቀጠለ።

ውሾቹን እንደምታጥባቸው አጫወተችኝ። የውሾቹ የጠጉር ብናኝ ወደ አፍንጫ ከገባ ካንሰር የተባለ በሽታ ያመጣል ብለው ስለነገሯት አፍንጫዋ ውስጥ ጥጥ እንደምትወትፍ አጫወተችኝ። በአፏ ብቻ መተንፈስ ሲያደክማት ግን፣ "የሆነውን ይሁን" እያለች ጥጡን ወዲያ ትወረውረዋለች።

በመቀጠል ደግሞ ያለፈ ታሪኳን አንስታ አጫወተችኝ።

ጅማ ነው ተወልዳ ያደገችው። እናቷ አማራ ናት። አባቷ ደግሞ ኦሮሞ። አባቷ "የኦነግ ሽብርተኛ ነህ" ተብሎ ሲገደል በአይኗ በብረቱ አይታለች። አባቷ ሲገደል እናቷ ልጆቿን ይዛ ወደ አዲሳባ ሸሸች። እናቷ አማራ ስለሆነች "ነፍጠኛ" ብለው እንዳይገድሏት እሷም ፈርታ ነበር። ደሞ በሽተኛ ናት እናቷ። ሶስት ታናናሽ ወንድሞች አሏት። ምንም ገቢ የላቸውም። አባቷ ግን ቡና ይሸጥ ስለነበር እሱ በተወላቸው ገንዘብ እናቷ ወደ ዱባይ ላከቻት። ዱባይ ስትልካት ታዲያ እንዲህ አለቻት፣

"መህቡቤ! ተስፋችን ሁሉ አንቺ ነሽ! አንቺ ከበረታሽ ያልፍልናል። ካልበረታሽ ደግሞ ትቀብሪናለሽ!"

በተመስጦ ሳዳምጣት ቆየሁ።

እሷ ስትናገር አንዳችም ቃል እንኳ አልተነፈስኩም። በዝምታ ብቻ አዳመጥኳት። በርግጥም በጥልቀት አዳመጥኳት። እሷ የምታወጋኝ ሁሉ ስእሉ ይታየኝ ነበር። ምስሉ ህይወት ዘርቶ ይታየኝ ነበር። መህቡባ ተርካ አብቅታ እኔም አገጬን መዳፌ ላይ እንዳስደገፍኩ የሽኮኮ ፀሎት የማካሂድ መስዬ ነበር።

መህቡባ ፈገግ ስትል ነበር የባነንኩት።

ንፁህ ፈገግታ ነበር። እስካፍንጫው ፍቅር የሞላው ፈገግታ። የሰው ልጆችን ሁሉ የማመንና የማፍቀር ልብ ያላት አንዷት ኮረዳ ይኸው አጠገቤ ቁጭ ብላ ሁሉን ታወጋኛለች። እና ዝምታዬን ልሰብር ስላልቻልኩ እንዲህ ስትል ጠየቀችኝ፣

"እስኪ ስላንተ ደሞ አጫውተኝ?"

"ምን ላጫውትሽ መህቡባ?"

"ያንን መፅሃፍ የፃፍከው አንተ ነህ?"

"አዎ እኔ ነኝ መህቡባ"

"ያንተ የህይወት ታሪክ ነው?"

"አይደለም። በርግጥ ስለ ራሴም ጥቂት ፅፌያለሁ"

"ጀመርኩትና ደስ ይላል። ወጥ መስራቱን ላግዛቸው ብዬ አቋረጥኩት። ለስራ ፍለጋ ከደብረዘይት ወደ አዲስ አበባ ሄደህ ነበር አይደል?"

"አዎ ሄጄ ነበር"

"ከዚያም አንቀጥርም አሉህ አይደል? ከዚያም ተበሳጭተህ ወደ ደብረዘይት ተመለስክ። አምስት ብር ብቻ ነው የነበረህ አይደል? እሱ ላይ ነው ያቆምኩት። ከዚያ ምን ሆነ? እስኪ ንገረኝ?"

ቁልቁል የረዘመ ጢሜን ማሻሻት ብቻ ሆኜ ቀረሁ። ከ400 ገፅ መፅሃፍ መህቡባ ያነበበችው 3 ገፅ ብቻ ነው። ከዚያ በሁዋላ ያለውን ታሪክ ምን ብዬ ነው የምነግራት?

"ረጅም ነው ታሪኩ መህቡባ። እንደምታይው ትልቅ መፅሃፍ ነው። ሁሉን እንዴት ልንገርሽ? ጊዜ ስታገኚ ቀስ ብለሽ ታነቢዋለሽ"

ቆየችና ደግሞ እንዲህ ስትል ጠየቀችኝ፣

"እዚህ ዱባይ ታዲያ አሁን ምን እያደረግህ ነው?"

"ይህን መፅሃፍ እየሸጥኩ ነው"

"ተሸጠልህ ታዲያ?"

"ደህና ነው፣ መህቡባ"





ቮድካ ቀዳሁና ደረቁን ባንድ ትንፋሽ ገለበጥኩት።

ሊያረካኝ ስላልቻለ ሌላ ደብል ያህል ቀዳሁና እንደ ጦር ውርወራ ወይም በቲኪላ የአጠጣጥ ልማድ ደህና አድርጌ ወደ ጉሮሮዬ ለቀቅሁት። እያቃጠለኝ ወረደ።

እኩለ ሌሊት ሆነ።

እዚያው እንዳድር በጠየቁኝ መሰረት ተስማማሁ። ያች አንድ ክፍል ቤት ሰባት ሃበሾችን አቅፋ ለማሳደር ተዘጋጀች። ክፍሉ ውስጥ አንድ አልጋና ጥቂት ሶፋዎች ነበሩ። አልጋው ላይ ሙሉጌታ ከነሚስቱ፣ በተጨማሪ አንዷት ሴት አዳብለው ጋደም አሉ። ሌላዋ ሴት ሶፋውን ያዘች። የቀረነው ደግሞ ወለሉ ላይ በተነጠፉት ፍራሾች ላይ ጋደም አልን።

በጣም ቀላል ነበር።

ከተቀመጥንበት ሸርተት በማለት ተኛን።

መህቡባም እንዲሁ አደረገች።

የፍሪጁ ድምፅ እንደ ከርካሳ ጋሪ ጩኸቱን ያሰማል። ግድግዳው ላይ ከተሰካው AC የሚወጣው ድምፅ "ጭቋላ' የተባለውን የደብረዘይት የእህል ወፍጮ ቤት አስታወሰኝ። ቴሌቪዥኑም አልተዘጋም። በሩ በተከፈተና በተዘጋ ቁጥር እንደ ጐርፍ የሚገባው ወበቅ ከድምፆቹ ጋር ተዋህዶ ያችን ክፍል ሲኦል አስመስሏታል። የመህቡባ ትረካዎች በአናቱ ሲኦሉን ህያው አድርገውታል።

የጠጣሁት ሁሉ ብን! ብሎ ከደሜ ውስጥ ድራሽ አባቱ ሳይጠፋ አልቀረም። ቢሆንም ግን እዚያው ለማደር ወሰንኩ። በጀርባዬ እንደተኛሁ ሲሆን አይኖቼ ግን በደመነፍስ ቴሌቪዥኑ ላይ ነበሩ። መህቡባ ፊቷን ወደኔ አዙራ በጐኗ ጋደም ብላለች። በዚያ ሁሉ ድምፅ ውስጥም ታዲያ ጥቂት መንሾካሾካችን አልቀረም፣

"ቤተሰብሽን እየረዳሽ ነው?" ስል ጠየቅሁዋት።

"ያገኘሁትን ሁሉ ወደነሱ ነው የምልከው"

"መቼ ነው ወደ ስራሽ የምትመለሺው?"

"ነገ በጠዋት"

"ነገ መዋል አትችይም?"

"አልችልም። መሄድ አለብኝ። እንደውም ዛሬ በጣም ጥሩ ጊዜ ስላሳለፍኩ ደስ ብሎኛል። አንተ ከልብህ ስታዳምጠኝ

ጊዜ በጣም ደስ አለኝና በቃ የልቤን ሁሉ ነገርኩህ።"

"ነገ አብረን ብንውል ደስ ይለኝ ነበር" አልኳት።

"ውይ! አልችልም! ልክ የዛሬ ወር ቅዳሜ ግን ልንገናኝ እንችላለን። እዚህ ትኖራለህ?"

"ርግጠኛ አይደለሁም፤ መህቡባ!"

አያያዝኩና እንዲህ ስል ጠየቅሁዋት፣

"አሳዳሪዎችሽስ እንዴት ናቸው?"

"ጥሩ ናቸው"

"ሰውየው አያስቸግርሽም?"

"ብዙም አይደለም"

"ያስቸግርሻል?"

"ቤት ውስጥ ሰው ካለ ምንም አይልም። ሰው ከሌለ ግን... አንድ ጊዜ ልብሴን እየቀየርኩ እያለ ወደ ክፍሌ ገባና ሽቶ ነፋብኝ። ደንግጬ በርሬ ወጣሁ። ሌላ ጊዜ ደግሞ ማንም አልነበረም። ወጥ ቤት ውስጥ ነበርኩ። በፓንት ብቻ መጣና ፍሪጅ ውስጥ እቃ የሚፈልግ መስሎ እዚያው ያዘኝ... ሁለቱ መንታ ህፃናት ልጆቹ ደግሞ ባለጌዎች ናቸው። እጐንብሼ እያፀዳሁ እያለ ከሁዋላ ቀስ ብለው እየተጠጉ ይሸኑብኛል። በርግጥ ልጆች ናቸው። እነሱ መጫወታቸው ነው። ግን ያበሳጫል። የሰው አገር ሰው ነኝ። ምን አደርጋለሁ?"

"እናታቸው ዝም ትላቸዋለች?"

"እሱማ ትቆጣቸዋለች። ግን አይሰሟትም። ከጀርባ እየመጡ አንገቴ ላይ እየሸኑ እኔን ማስደንገጥ ያስደስታቸዋል። ሽንታቸው አይጐዳኝም። ሻወር እወስዳለሁ። ግን እጐንብሼ ተመስጬ፣ ስለ እናቴና ስለ ወንድሞቼ እያሰብኩ እየወለወልኩ እያለ ከሁዋላ መጥተው ሲሸኑብኝ በጣም ያስደነግጣል። ደሞም ያናድዳል። ግን ምን ማድረግ ይቻላል? ቤተሰቤን እረዳለሁ ብዬ ነው። እናቴ በኔ ትኩራለች። ኩራቷን እንዴት አድርጌ ላበላሽባት?"

ከጥቂት ዝምታ በሁዋላ እንዲህ አለች፣

"በሚቀጥለው ወር ቅዳሜ ባገኝህ ደስ ይለኝ ነበር"

"መህቡባ አልዋሽሽም። የምንገናኝ አይመስለኝም"

ገፅታዋ ሲከፋ አስተዋልኩ።

ለደቂቃ ያህል ፀጥ አለች።

"ካልቻልክ ደህና!"





መልሳ እንዲህ ስትል ጠየቀችኝ፣

"ነገ በጠዋት ነው የምሄደው። አትሸኘኝም?"

"እሸኝሻለሁ። እኔም በጠዋት ነው የምነሳው"

ከፊሎቹ እንቅልፍ ይዞአቸው ጥርግ ብሎአል። ማንኩራፋት የጀመሩም አሉ። መህቡባም ብዙ አልቆየች፣

"ደህና እደር" አለች።

"ደህና እደሪ መህቡባ"

አይኖቿን ከደነቻቸው።

እኔ ግን አልቻልኩም።

ብዙ አሳቦች ወደ አእምሮዬ እየመጡ ነቅቼ እንድቆይ አስገደዱኝ። በጥቅሉ አንዳንድ የተደበላለቁ ስሜቶች አጥንቴን ሳይቀር እየፈጩት ነበር።

ተስፋ የሚባል ነገር ጥርግርግ ብሎ ከውስጤ የሚጠፋበት ጊዜ አለ። እንዲያ በተሰማኝ ጊዜ ራሴን ለመግደል ምንም አይቀረኝ። መህቡባ መህቡባን የሆነችው መርጣ አይደለም። እኔም ይህን በመሰለ ግለታሪክ መሃል መገኘቴ መርጬው አይደለም። ቀደምት ሰዎች ጠይቀው መልስ ያጡለት ጥያቄ እኔ አእምሮ ውስጥም አለ። ከየት እንደመጣሁ አላውቅም። ወዴት እንደምሄድም አላውቅም።

"እንደ ብረት የጠነከረ" እያልኩ የምመካበት መንፈሴን ይህች የ23 አመት ልጅ ይኸው ድራሹን አጠፋችው። "አባቴን 'አነግ' ብለው ገደሉት" አለችኝ። "እናቴ ደግሞ 'ነፍጠኛ' ተብላ እንዳትገደል ፈርታ ወደ አዲሳባ ሸሸች" እያለች ለኔ ታጫውተኛለች። ከትናንት ወዲያ ደግሞ ግንባሯ ላይ የመስቀል ንቅሳት ያለባት አንዲት ቆንጆ፣ "ትግሬ ስለሆንኩ ጠሉኝ" ብላ እኔ ፊት ተንሰቅስቃ አለቀሰች። እኔ ደግሞ ይህንን ሁሉ ሮሮ እና ሰቆቃ የሚፈፅመው ቡድን ካድሬ ነበርኩ። እነዚህ ሴቶች ግን ይህንን ሁሉ ስለማያውቁ እኔን እንደ ወንድም ጋሻ በመቁጠር ብሶታቸውን ሁሉ ዘክዝከው ያጫውቱኛል። ልቤ አካባቢ እንደ ጩቤ የሚወጋኝ ነገር አለ። አይኖቼ ዙሪያ ደግሞ መርፌ ነገሮች ይጠቀጥቁኛል።

ባለፉት ሃያ አመታት ውስጥ ያጋጠመኝ የህይወት መንገድ ላይ ልምድና እውነታ በአእምሮዬ የተጠራቀመውም ገጠመኝ አንድ ግለሰብ ሊሸከመው ከሚችለው በላይ ሆኖብኛል።

መህቡባ እነዚያን ለሰው የማይነገሩ ተብለው በልቤ የተቆለፉትን ታሪኮች ብታውቅ ምን በተሰማት? ህዝቡን ይከፋፍላሉ በሚል በየልባችን የቀበርናቸው የዘመናችን ቅሌቶችስ? በመሰረቱ ግን እኔ በግሌ ምናገባኝና ነው ይህን ሁሉ ሮሮ እንዳውቅ የሆነው? ለምን እንደ አሳማ፣ "ተወለደ፣ ከዚያም ወለደ፣ በመቀጠል ሞተ" የተባለ ታሪክ ብቻ ሳይኖረኝ ቀረ? የብእር ሰው ከመሆን ይልቅ ምነው ፖስተኛ ብቻ ሳልሆን ቀረሁ? እንዲያ ሆኖ ቢሆን የመህቡባን ታሪክ በዚህ መንገድ መች እመለከተው ነበር? እንዲህ እያሰብኩ ስንቱን ሳነሳና ስጥል በመካከሉ እንቅልፍ ይዞኝ ጥርግ ሳይል አልቀረም...

ገና ሳይነጋ ቀሰቀሰችኝ።

ጫማዬን አጥልቄ፣ ልብሴን ለባብሼና ፊቴን በውሃ አባብሼ መህቡባን ለመሸኘት፣ በዚያውም ወደ ሆቴሌ ለመሄድ ዝግጁ ሆንኩ፣

ገና አልነጋም።

ቢሆንም ነግቷል ማለት ይቻላል። ፓኪስታኖች በብዛት መንገዱ ላይ ውርውር ይላሉ። መኪኖች ገና ድሮ መወነጫጨፉን ተያይዘውታል። ገና ባልነጋው ንጋት በዝግታ ርምጃ ወደ አውቶቡስ ማቆሚያው ማዝገም ያዝን። መህቡባ ነቅታ ነበር። እንደ ወፍ ነቅታ እኔንም አነቃችኝ፣

"አውቶቡስ የት ነው የምታገኚው?" ስል ጠየቅሁዋት።

"ከዚህ የአስር ደቂቃ መንገድ ይቀረናል"

በዝምታ ጥቂት እንደ ቆየን፣ እንዲህ ስትል ጠየቀችኝ፣

"የፃፍከው መፅሃፍ ስለምንድነው?"

"ፖለቲካ ነው፣ መህቡባ"

"ፖለቲካ ምን ያደርግልሃል?"

መልስ ስላልሰጠሁዋት እሷ ቀጠለች፣

"ፖለቲካ ውስጥ አትግባ!" ብላ በቁርጠኛነት መከረችኝ። አያያዘችናም ቀጠለች፣ "...ፖለቲካ ውስጥ ከገባህ ወያኔዎቹ ይገድሉሃል። እነሱ ማንን ፈርተው ልጄ? ከፈለጉ ይገድሉሃል፣ ካልፈለጉ ያስሩሃል። አንተ ከነሱ ጋር መጋጨት ምን ያደርግልሃል? ኀመን በጤና አይሻልም እንዴ?"

መልስ ሳልሰጣት ዝም አልኩ።

ምንስ ልላት እችላለሁ?





በቁርጠኛነት ምክሯን ቀጠለች፣

"እነሱ ልጄ ተንኰለኞች ናቸው። እነሱን ማሸነፍ አይቻልም። ከነሱ ጋር ባትጣላ ይሻላል። ብዙ ሰው ገድለዋል። ማንን ፈርተው? ሰው እንደሚገድሉ አታውቅም እንዴ?"

"አውቃለሁ፣ መህቡባ?"

"ባለፈው ምርጫ የተደረገ ጊዜ ቅንጅቶችን መንገድ ላይ ሳይቀር እንደገደሏቸው አልሰማህም?"

"ሰምቻለሁ መህቡባ"

"በምርጫው ሲሸነፉ ተናደው ነውኮ የገደሏቸው"

"አውቃለሁ መህቡባ"

"ከሚገድሏቸው ግን መጀመሪያውኑ ምርጫ ባያደርጉ አይሻልም?"

"ይሻል ነበረ። ምን ታደርጊዋለሽ?"

"ህፃናትም እኮ ሞተዋል"

"ሰምቻለሁ መህቡባ"

"አንዷን ደግሞ አይኗ እያየ እዚያው በራፋቸው ላይ እናቷን ገደሉባት። አባቷን ደግሞ አሰሩት። አባቷ ቅንጅት ነበር አሉ። የልጅቷን ስም ረሳሁት እንጂ እናቴ ነግራኝ ነበር። እኛ ሰፈር ውስጥ ልጅቷን የሚያውቋት አሉ..."

ዝም በማለቴ እንዲህ ስትል ጠየቀችኝ፣

"አይገርምም?"

"ይገርማል፣ መህቡባ!"

"በጣም ነው የሚገርመው እንጂ! እንዴት እንደዚህ ይጨክናሉ? እነሱ እናት የላቸውም እንዴ? ወልዳ ከምታጠባው እናት አይደለም እንዴ የተፈጠሩት? የእናት ጡት ጠብተው አይደለም እንዴ ያደጉት?"

ሰውነትን የሚያልፈሰፍስና ተስፋ የሚነፍግ፣ ነፍስን የሚያደቅቅ ገዳይ መርዝ በሰራ አካላቴ ሳይሰራጭ አልቀረም። ፊፅሞ ተዳከምኩ። ከመህቡባ ድምፅ ውስጥ የማዳምጠው ፍፁም የሆነ ደግነትና ቅንነትን ነበር። እንዴት እንዲህ ያለ ህዝብ ላይ መጨከን ተቻለ? ከወያኔ ጋር በሰራሁባቸው ዘመናት ህዝብ የሚባሉት እነ መህቡባ መሆናቸውን እንዴት ሳላስተውል ቀረሁ? ለምን ነበር ወደ ህዝቡ ጠጋ ብዬ እንዲህ እንደዛሬው በጥሞና ማዳመጥ ሳልችል የቀረሁት?

መህቡባ ያለማቋረጥ ስትናገር እኔ ከእሷ ተለይቼ

ብቻዬን የምሆንባትን ደቂቃ ነበር የማስበው። እሷ ግን ቀጠለች፣

“ስለ ወያኔዎቹ ምን ፃፍክ?”

“ብዙ ነው፣ መህቡባ”

“የጅማውን ፃፍከው?”

“ምንድነው የጅማው?”

“ራሳቸው ፖሊሶቹ እስላም መስለው ክርስትያኖቹን በቆንጨራ አርደዋቸው የለምንዴ?”

“ሰምቻለሁ። ግን አልፃፍኩትም”

“ታዲያ ምንድነው የፃፍከው?”

“ሌላ ሌላውን ነው። አንቺ ስለጅማው በምን አወቅሽ?”

“የተገደሉት ሰውዬ የሳቸው ልጅ ጎረቤታችን ነበረች።”

ከአውቶቡስ ማቆሚያው ቦታ ደረስንና መጠበቅ ጀመርን። የደቡብ ኤዢያ ጥርቃሞ ኩሊዎች ቋጠሮአቸውን እንዳንጠለጠሉ አውቶቡስ ይጠብቃሉ። አውቶቡሱ እስኪመጣና እስክትሳፈር አብሬያት እንድቆይ ጠየቀችኝ። ተስማምቼ አጣብቃት ያዝኩ፣

“የምንገናኝ ይመስልሃል?” ስትል በድጋሚ ጠየቀችኝ።

“አይመስለኝም፣ መህቡባ!”

“ብንገናኝ ጥሩ ነበር።”

ዘግየት ብላ ደግሞ እንዲህ አለች፣

“ጊዜ ቢኖረኝ መፅሃፍህን አነበው ነበር። ግን ፖለቲካ አልወድም። ከዚህ በፊት ያነበብኩት መፅሃፍ ‘ሰመመን’ እና ‘ሳቤላ’ የተባለውን ነው። ሁለቱም ደስ ይላሉ። በጣም ደስ ይላሉ። ፖለቲካውን ትተህ እንደ ሳቤላ እና ሰመመን ለምን አትፅፍም?”

“እሞክራለሁ መህቡባ!”

“ስለ ፍቅር መፃፍ አትችልም?”

“እሞክራለሁ እስኪ?”

“እንደሱ ይሻልሃል። ፖለቲካ ይቅርብህ። ጣጣ ውስጥ ለምን ትገባለህ? ጎመን በጤና...”

ጨለማው አሁን ጨርሶ እየገፈፈ ነው።

ገና ወገግ ከማለቱ ሙቀቱ እሳት የሚተፋ ምላሱን እንደ ደራጎን ያወናጭፈው ጀምሮአል።

“ከዚህ ወዴት ነው የምትሄደው?” ስትል ጠየቀችኝ።

“ገና አልወሰንኩም መህቡባ”





አውቶቡሱ እንደ ጭልፊት እየተወነጨፈና፣ እንደ ዘንዶ እየተምዘገዘገ መጥቶ እግራችን ስር እንደ ውሃ ፈሰሰ፣

ተሰናብታኝ ወደ አውቶቡሱ ጥልቅ አለች።

ቆሜ አየሁዋት!

አውቶቡሱ ይዞአት ነጐደ።

እኔም ፊቴን አዙሬ ብቻዬን ወደ ሆቴሌ አቅጣጫ አዘገምኩ። የለም! የለም! ብቻዬን አልነበርኩም። ቁጭት አብሮኝ ነበር። እንደ እሳት የሚፋጅ የቁጭት ፍም ልቤ ውስጥ ተጎልቶ ነበር። ነበልባል በሆኑ ጥያቄዎችም ተወጥሬያለሁ።

“ይህን ደግ ህዝብ በቀናው ጐዳና ላይ መርቶ ከምኞቱ የሚያደርሰው መሪ እንዴት አጣ!?” ብል ጮሁኩ። “....ከቶ ለምን መሪ አጣ!?”

* * *

በተፈጥሮዬ ቁጡ አይደለሁም። በዚያን እለት ግን ተሳዳቢና ቁጡ ሆኜ ዋልኩ። እኔ ብቻ ሳልሆን ብእሬም በቁጣ ስትንተከተክ ዋለች። የብእሬን ቁጣ እኔው ለራሴው እፈራዋለሁ። ከጫፉ እሳት የሚተፋ ያህል ይፈላል። ይህን መሰል ማስታወሻዎቹ ለህትመት እንዳይበቁ በጣም እጠነቀቃለሁ። ብዙውን ጊዜ ቀዳድጄ እጥላቸዋለሁ።

በዚያን እለት ግጥም አይሉት ስድ ንባብ ድብልቅልቁ የወጣ ፅሁፍ ነበር የፃፍኩት። ርግጥ የሚንተከተክ ቁጣዬን ለማብረድ ረድቶኛል። በዚያን ቀን ስፅፍ የፀጋዬ ገብረመድህንን፣ የደበበ ሰይፉን፣ የዮሃንስ አድማሱን ስንኞች ከራሴው ቃላትና ስንኞች ጋር እየደበላለቅሁ ቁጣዬን ለማብረድ ሞክሬ ነበር...

*ማነህ አንተ የቅርባችን እሩቅ?*

*እኛማ እኛ ነን፣ ሰለስቱ ደቂቅ! እድል ጠፍቶ ያልተማርን። ደም አፍሰስን ያስተማርን! ወንድም ጋሻን እምንጠብቅ! እኛ ነን እኛ! ያንተስ ከየት ይሆን? የፍልስፍናህ ጥበቡ? የአስተሳሰብህ መደቡ? ማነህ አንተ? ሳጥናኤል ነህ ከንቱኤል? ዳንኤል ነህ ዋሾኤል?*

*“ጋሼ!” በሉኝ የምትል፤ የአዛውንት ቅምጥል፤ ያለባበስና የንግግር ሊቅ! የት ነህ አንተ የቅርባችን ሩቅ? ሆደባሻ ነህ*

ወንድም ውሻ? ወንድም ጋሻ ነህ የተስፋ እርሻ? ፕሮፓጋንዳህ የሆነብን ግርሻ? ባለ ራእይ ነህ ወይስ ተልካሻ?

እባክዎ "እርሶ" ማኖት አንቱ? እውነቱ ወይስ ክህደቱ? ቃሎት የሆነብን ከንቱ? ማኖት እርሶ? የፖለቲካ ካሊፕሶ?

እኛማ እኛው ነን - ዝንተ አለም የተስፋ መዝሙር፤ መዘመር ሆነን ቀረን እንጂ - እኛስ ዘምረን ነበር፤ ስለ እናት መሬት - ስለ አባት አገር፤ ሞትንም ሞተናታል - ለተስፋና ለፍቅር፤ ፍፃሜው ሆነብን እንጂ - ቃል ብቻ የቃል ክምር፤ እጣችን ሆነብን - እንደ ፍልፈል መኖር፤ ፀጋ ሳናጣ ከሰማይ - ወርቁ ተርፎ በከርሰ ምድር፤ ቅፅል ስማችን ልመና - መታወቂያችን አራጣ ብድር፤ በርግጥ አንክድም! ቀምሰናት ነበር - የነፃነትን ግማሽ ቀን፤ መቅመሱንስ ቀምሰናት ነበር፤

ዳሩ ምን ያደርጋል?

እንዳይቀርብን አፍሪቃዊነቱ፤ እንደ አግማል ቅፍለት በአንድ ውርጋጥ እንደሚጎተቱ፤ ነፃነት ተረት ሆነችብን - ሃሳዊ መሲህ ከንቱ፤ እና የነፃነትን ግማሽ ቀን - እንደ ግማሽ ጨረቃ፤ የባርነት ጉድጓድ ውስጥ - እንደ አይጠመጎጥ ተደብቃ፤ የነፃነትን ግማሽ ናፈቅናት - በመናፈቅ ብቻ ቢበቃ፤

ሌላ ታዲያ ምን ይባላል?

ሲቃ ብቻ ካልሆነ - በቁም ሲሰቀሉ፤ መቼም ሃበሻ ተረት ሆኖአል እጣ ክፍሉ፤ ስምን መልአክ ያወጣዋል እንዲሉ፤ ስማችን ቀንድ - ግብራችን ቀንድ - ሆነ እንደ ቃሉ፤ አለም ባንድ ጀምበር ሽቅብ ሲመነጠቅ፤ እኛ ገና አኩዋኩሉ፤ መልሰን ደግሞ 'እንዴት ዋሉ?' 'ኑጋ?' ተብሎ ሲጠየቅ፣ ዝንተአለም ምላሻችን - 'አልነጋም!' መቼ ይሆን የሚነጋልሽ እናት አለም!? እና ያቺ ልጅ ገደለችኝ በቁም፤ 'ስለ ፍቅር ፃፍ' አለችኝ መህቡባ፤ ስለ ፍቅር እና ስለ ውበት አበባ፤ ' እዮሃ!' በል አለችኝ፣ መስከረም ሳይጠባ፤ ዶሮ በሌለበት እንቁላል ለቀማ፤ ምን ፍቅር አለ እህት አለም? ተስፋ ባጣ ምድረበዳ፣ ድቅድቅ ባለ የቀትር ጨለማ?

አንተኛውስ ማነህ?
ጆሮጠቢ ነህ የገንዘብ ወፍጮ?
መቀጮ ነህ ወይስ መዋጮ?
ማነህ አንተ? ማነሽ አንቺ? የት ነሽ አንቺ?





ሃሌ ነሽ ሃሌ ሉያ? ቃሌ ነሽ ቃሌ ሉያ? ፀጋዬ እንዳለው በስንቁ፣ የሃሌ እናት አለም ብቁ፣ እስከዚህ ነው የኑሮ ጭንቁ? ይሄ ኖሮአል የእድሜ ብርቁ? ወንድም ውሻ በበዛበት ሃገር፣ የአንድ እህት ዱካ! ብራቅ ዳእሩን ተርከኮት፣ እንደማይነድ ያድባር ዋርካ፣ በቁም ሞተን ስናወካ፣ የብርቱካን ኪሩቤል እሳት፣ በኛ በቁም ሙታን ህዋሳት፣ አይን እያየ ልቧን አጧት፣ ብሎ ሲያበቃ ሎሬት ሊቁ፣ ጓደኞቹ እንኳ ሳያውቁ፣ እልም ከነ ትጥቁ!

ብርቱካን! ብርቱካን! ይላል ሰው ሁሉ፣

አንድ እግር ብርቱካን ራሷ በቅላ፣ ጀግና ቆሞ እያየ - ስትደቆስ ከእጁ ተገንጥላ፣ 'እና ምን ላድርግ!?' ይላል አሉ፤ እንዲህ ኖሮአል የመስዋእትነት ውሉ? የሰፌድ ጋሻ እንኳ መሆን ያልቻለ፣ እንዲህም አድርጎ አትንኩኝ ባይነት የለ! በቁሙ ተረት የሆነ አርበኛ፣ አባ ዘራፍ ብቻ ብቻ ጉረኛ! እንዲህ ነበር እንዴ የአመራር ጥበቡ ፍልስፍና? የተራራ ክምሩን አፈር ሲያበላው አንድ ቁና፤ ከየትኛው ጎሬ ተሸሽጎ የአንተ የምሁሩ ሚና? "ምሩኝና እኔ ልሙት ከፊት ሆኜ!" እያለ ሲማፀን ህዝበ ደቂቅ፤ ተመሪው ከመሪው አስተሳሰቡ ሲልቅ፤ በመካከሉ የእድል ጀምበር ጥልቅ!

ሄለን መሃመድ እንዳለችው፣

አብዮት አሽቶ፣ የሚበላው ጠፍቶ፣ ጅቡ በላው አሉ ሌት ከማሳው ገብቶ! እናም ጀግና ያልነው በፍርሃት ወደቀ፤ ለጅብ አሳልፎ እየሰጠ፣ ለጅብ ቦታውን ለቀቀ! እና "አበባየሁ ወይ" ሲባል እባካችሁ አትበሉ "ለምለም፣ ለምለም"፣ የደረቀ መሶብ እንጂ - የለመለመ መስክ የለም።

ያኛው ደግሞ የሰይፉ ልጅ ደበበ።

ታዝቦ ታዝቦ በቁጣ፣ ሰው ፈልጎ ሰው ቢያጣ፣ እንዲህ አለ በለበጣ፣ አሁን እንዳንተ ማን ሊመጣ? አባቱን መስሎ የወጣ? እንዳንተም ያባቱ ልጅ የለ! ተስፋን አቅፎ የገደለ፣ በዚህስ መቼ አበቃ? "አባትህ" አለ ለጥቆ፣ እንደ ውሻ ሳቅ ስቆ፣ "አባትህ!" አለ። ራሱ በማይፈታው እንቆቅልሽ፣ ተረብ የድግምት ወጀቦ፣ ፈውስ እያለ ሲያደባይ፣ የስንቱን ሰው ቀልብ ሰልቦ፣ አንተም የመዝለፊያ ልጅ ዛቢያ፣ ዘመናይ ደብተራ አባያ፣ ተጠበብኩ ስትል ጠበብክ፣ አወቅሁ ስትል ደነቆርክ፣ መቅረዝ ሲሉህ እንቅቡም አንተው ሆንክ።

*እና እኔ ደግሞ ለማን እንደሆነ ባላውቅም!*

*"እባክህ ማነህ አንተ?" ብዬ ጠየቅሁ። እንደሆዱ ነህ እንዳንጎሉ? የት ነው ያስተሳሰብህ ክልሉ? የራእይህ ኮከብ ቃሉ? የት ነው? ማነህ አንተ? የት ነህ አንተ? ምነው የተሰፋህ ጫፉ ራቀ? ምነው የህሊና ባንዴራህ ተደበቀ? ምነው ክብርና ኩራትህ ተሳቀቀ? የነፃነት ህልምህ ተፍቆ፣ የታሪክ መሰረትህ ወደቀ! ሌላው ሁሉ ቢቀር እንዴት የቁጣ ውርስህ ጠወለገ? ያገሬ ሰው ሆይ! የታለ የሃበሻነትህ ቀለሙ? የእምነትህ ስጋወደሙ? ግዴለም ደህና! ሁሉም ይቅር። እንዴት ህሊናህ ዝም አለ? ወንድም ውሻዎች እንደ ዝንብ ሲያምሙ? እንደ ተርብ በአናትህ ላይ ሲተሙ። ለመምራት ያልሞከርክ፣ መመራትን የተጠየፍክ፣ ማነህ አንተ? ጀብደኛ ነህ ቀልደኛ? ታጋይ ነህ መልከኛ? ወይስ ተመፃዳቂ ህልመኛ? እና የት ነህ አንተ? ማነህ አንተ? ወንድም ውሻ? ወይስ ወንድም ጋሻ?....*

በመጨረሻም እንዲህ ማለት ችዬ ነበር፣

መህቡባ ሆይ! አይዞሽ!

የወንጀለኞች ጉልበትና ሃይል እንደ ጅብራልታር ቋጥኝ ለዘልአለሙ ቆሞ ይቆይ ዘንድ አይቻለውም። ፍቅርና እውነት አሸንፌው ይነግሳሉ። እንጀራ ፍለጋ ርቆ የተጓዘው ዜጋ ሁሉ፣ በወገንና በሃገር ፍቅር ናፍቆት የደቀቀው ሁሉ ወደ ህልሙ መድረሱ አይቀርም። ህይወት በዚህ መንገድ አትቀጥልም። ነገ ማለዳ ከምትወጣው ጀምበር ጋር የነፃነት ቀን አብራ ብቅ ትላለች።

መህቡባ ሆይ! አይዞሽ!
አይዞሽ የኛ ቆንጆ!!ቆንጆ!!
የኛ ውብ ፅጌረዳ!!

ወንድም ውሾች ብቻ አይደሉም። ወንድም ቆሻሾች ብቻ አይደሉም። ወንድም ጋሻዎችም አሉሽ። እህት ጋሻዎችም አሉሽ። የሰቆቃ ድምፁን ተከትለው፣ ይመጣሉ ወዳንቺ ፈልገውሽ። በአንድ ነገር ርግጠኛ ሁኚ! ከተጣልሽበት የውርደት ጉሮኖ፣ የተሰፋ ማጣት ጨለማ ጎትተው ወደ ብርሃን የሚያወጡሽ፣ ወንድሞች አሉሽ። አይዞሽ መህቡባ! አይዞሽ...



## ውድ አንባብያን

ስለዚህ መፅሃፍ ያላችሁን አስተያየት
ብትልኩ ደራሲው በደስታ ይቀበላል፣
አድራሻ፣

ttgebreab@gmail.com

Www.tgindex.blogspot.com